**ማውጫ** **ገፅ**


1. የኢትዮጵያ የይርጋ ሕጎች መሰረታዊ ሃሳቦች ----------1
   ወርቅነህ አለምነው

2. ተደራራቢ ወንጀሎች ፅንሰ-ሀሳብ ሕጉና አፈፃጸሙ በአማራ ክልል ---------- 38
   ሰለሞን ተገኘወርቅ

3. በኢፌዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ-ቁጥሮች መካከል ያለው የልዩነት ወሰንና
   በሥራ ላይ የሚታዩ ችግሮች ---------- 77
   ታፈሰች ወልዴ

4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ካለመቁረጥ ጋር ተያይዞ ስለሚኖር የወንጀል
   ተጠያቂነት አድማስ ---------- 103
   ሳባ አበረ

5. በመንግስት የግንባታ ውል አፈፃፀም አተረጓጎም ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች
   ለመፍታት አማራች የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ያላቸው ሚናና ተፈፃሚነት በአማሪ
   ክልል ---------- 134
   በላይነህ አድማሱ

6. መልካም አስተዳደርን በፍትሕ አስተዳደር ዘርፍ ውስጥ በማስፈን ረገድ የጠበቆች ሚና -
   ---------- 167
   በወርቁ ያዜ ወዳጅ

7. አንድ የክስ ምክንያትን መነጣጠል ፅንሰ ሃሳብ አተገባበሩ፡በአብክመ ጠቅላይ ፍርድቤት
   ሰበር ሰሚ ችሎት ---------- 217
   ሳባ ደመቀ

8. የመዳረግ መብት በኢትዮጵያ በኢንሹራንስ ህግ አጭር ዳሰሳ ---------- 253
   በላይ ወርቁ አለም

# የዋና ዳይሬክተር መልዕክት

የአብክመ የፍትሕ ባለሙያዎች ማሠልጠኛና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት በደንብ ቁጥር 74/2003 ዓ.ም መሠረት ሲቋቋም የፍትሕ ባለሙያዎች በእውቀት፣ በክህሎት፣ በሥነ-ምግባርና አመለካከት ብቁና የሕዝብ አገልጋይነት ስሜት የተላበሱ እንዲሆኑ ለማስቻል ተከታታይነት ያለውና አዳጊ ሥልጠና መስጠት እና የክልላችን የፍትሕ ሥርዓት ከተደራሽነት፣ ከቅልጥፍና፣ ጥራት፣ ውጤታማነትና ተገማችነት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ሳይንሳዊ በሆነ የሕግ ጥናትና ምርምር በመለየት የመፍትሔ ኃሣቦችን ማመንጨትና ለፍትሕ ሥርዓቱ መሻሻል አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መሠረት አሁን በመሰልጠን ላይ ያሉ 250 ቅድመ-ሥራ ሠልጣኞችን ሳይጨምር ከ3,370 በላይ የሚሆኑ ባለሙያዎችን በቅድመ-ሥራና ሥራ ላይ በማሠልጠን እና በማስመረቅ ለፍትሕ ሥርዓቱ ላይ የሰው ኃብት ልማት አቅም ግንባታ ላይ አተኩሮ በመሥራት ለፍትሕ ሥርዓቱ ውጤታማነት ጉልህ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡ ከአጫጭር ጊዜ ሥልጠና አኳያ የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት እና ጥያቄ መሠረት ያደረገ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ተሰርቶ በዚህም ላይ የተመሠረተ ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾ ለዚህ የሚመጥን የሥልጠና ማንዋል ተቀርጾ በተቀናጀና በተደራጀ አካኋን በተለያዩ ጭብጦች ላይ አትኩሮ ከ5000 በላይ የሚሆኑ ባለሙያዎችን በማሰልጠን ውጤታማነቱን አሳድጓል፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት የባለድርሻ ፍላጐት እና ጥያቄ እንዲሁም በኢንስቲትዩቱ መነሻነት በ19 ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የጥናትና የምርምር ሥራ በማከናወን የሕግ መጽሔት ቁጥር 1 እና 2 ጥቅም ላይ እንዲውል ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህም ለክልሉ የፍትሕ ሥርዓት መሻሻል ጉልህ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

በዚህ በጀት ዓመትም የጥናትና የምርምር ሥራዎች የተሰሩ ሲሆን በኢዲቶሪያል ቦርድ ከሚታወቁና ከሚያግባቡ የጥናትና የምርምር ሥራዎች መስፈርትና መለኪያ አንፃር ታይተውና ተመርምረው ተቀባይነትና ይሁንታ አግኝተው ለህትመት ብቁ ናቸው የተባሉ የምርምራ ሥራዎችን በዚህ መጽሔት በማሳተም የኢንስቲትዩቱ ለ3ኛ ጊዜ የሆነውን ቁጥር 3 የሕግ መጽሔት በአክብሮት ስናቀርብ በታላቅ ደስታ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ሥራ የሰሩትን የውስጥና የውጭ ተጋባዥ ተመራማሪዎች በአርትኦት የተሳተፉትን ሙህራንና የኢዲቶሪያል ቦርድ አባላት በራሴና በኢንስቲትዩቱ ሥም ከፍ ያለ ምሥጋናየን እያቀረብኩ ለአንባቢያን መልካም ንባብ እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞቴን ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!

# የኢትዮጵያ የይርጋ ሕጎች መሰረታዊ ሀሳቦች

በወርቅነህ አለምነው*

## 1. መግቢያ

የይርጋ ጽንሰ ሀሳብ የሚመነጨው "ረጋ" ከሚለው የአማርኛ ቃል ሲሆን "ረጋ" የሚለውን ቃል ደራሲ ተሠማ ኃብተ ሚካኤል "የሰው ሀሳቡ ከመውጣት ከመውረድ በሀሳብ ከመዞር ከመባከን ከመናወጥ ፀጥ አለ" በሚል ገልጸውታል።[1] ከዚህ በመነሳትም ይርጋ የሚለው ቃል የአንድ ሰው የመብት ጥያቄ በጊዜ ማለፍ ምክንያት ቀሪ የሚሆንበትና ባለ እዳውም ከሚቀርብበት ክስ ስጋት እፎይ የሚያስብል የህግ መርህ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።[2] የህግ ምሁራን አንደሚገልጹት ሁለት አይነት የይርጋ ደንቦች አሉ። የመጀመሪያው አይነት የይርጋ ደንብ ያልነበረ መብት የሚያስገኝ (acquisitive prescription) በመባል የሚታወቅ ሲሆን አንድን ጠያቂ የሌለው ንብረት ለረጅም ጊዜ በይዞታው ይዞ ሌሎች የህግ መከላከያወችን በማሟላት የተጠቀመ ሰው ህግ ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ ሲያልቅ የንብረቱ ባለቤት የሚሆንበትን አግባብ የሚፈጥር የይርጋ ደንብ ነው።[3] ሁለተኛው አይነት የይርጋ ደንብ ደግሞ ግዴታ አስቀሪ የይርጋ ደንብ (liberative prescription) የሚባል ሲሆን ባለመብቱ መብቱን ሳይጠይቅ በህግ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ካለፈ ጥያቄ የማቅረብ መብቱን የሚያሳጣ የይርጋ ደንብ ነው።[4] ይህ ጽሁፍ በማህበረሰባችን ውስጥ ሁለቱም የይርጋ ደንብ አይነቶች በተደጋጋሚ ለክርክር ምክንያት እየሆኑ በመሆኑ የሁለቱም የይርጋ ደንብ አይነቶች መሰረታዊ ባህሪወችን አግባብነት ካላቸው የኢትዮጵያ የህግ ድንጋጌወች እና የኢትዮጵያ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት(ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጠ/ፍ/ቤት) ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጣቸው የይርጋ ህግ ትርጉሞች ጋር በማገናዘብ ይመረምራል።

ይርጋን በተመለከተ ሁሉም አይነት የኢትዮጵያ ህጎች ተመሳሳይ የይርጋ ጊዜ የሌላቸው በመሆኑ ለእያንዳንዱ ጉዳይ ክስ ለማቅረብ ወይም ያልነበረ መብት ለማግኘት የተቀመጠው የጊዜ ገደብ፣ የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምርበት ጊዜ፡ በሕግ የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ

---

* LL.B, በንግድ ህግ LL.M፣ ቀደም ሲል የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ በአሁኑ ጊዜ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የህግ መምህር፣ ማንኛውንም አይነት አስተያት በ ኢ-ሜ-ል አድራሻ worknehalemnew@gmail.com መላክ ይችላሉ። ለዚህ ጽሁፍ መሳካት ገንቢ አስተያየቱን ለሰጠኝ አሰልጣኝና ተመራማሪ አቶ ጋሻየ ቢያድጌ ምስጋናየን አቀርባለሁ።

[1] ተሰማ ሀብተ ሚካኤል "ከሠቴ ብርሀን ተሰማ" የአማርኛ መዝገበ ቃላት ፣ ኩራዝ አሳታሚ፣1972 ዓ.ም፣ ገጽ 280

[2] Garner Black, Blacks law Dictionary, 9th Edition, 2004, West Publishing Company, p. 723.

[3] ዝኒ ከማሁ፣ እንዲሁም George Krzeczunowicz, Formation and Effect of Contracts in Ethiopian Law, Faculty of law, Addis Ababa University, 1983, page 181.

[4] ጥላሁን ተሾመ፣ የውል ህግ መሰረታዊ ሀሳቦች፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህግ ፋኩልቲ፣ 1999 ዓ.ም ገጽ 181

ሊቋርጥ የሚችልባቸው ምክንያቶች እና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦች በዚህ ጽሁፍ ተካተዋል። በመሆኑም ይህ ጽሁፍ የይርጋ ደንቦች መሰረታዊ ሀሳቦች፣ አላማወች፣ ስለሚያስጠብቋቸውና ስለሚፈጥሯቸው መብቶች እንዲሁም የይርጋ ደንብን የተመለከቱ የተለያዩ የኢትዮጵያ የህግ ድንጋጌወች ይመለከታል። በዋናነት ግን የኢ.ፌ.ደ.ሪ. ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የይርጋ ድንጋጌወችን አስመልክቶ በፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህግ፤ በውል ህግ፣ በውርስ ህግ፣ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህግ፣ ከውል ውጭ ሀላፊነት፣ በንግድ ህግ፣ በቤተሰብ ህግ፣ በንብረት ህግ እና በወንጀል ህግ ላይ የሰጣቸውን 70 (ሰባ) የህግ ትርጉሞች በመዳሰስ የኢትዮጵያ ይርጋ ህጎች መሰረታዊ መርሆዎች ላይ የአንባብያንን ግንዛቤ ለማሳደግ የተዘጋጀ ጽሁፍ ነው።

## 2. የይርጋ ሕግ ዓላማ

### 2.1. ያልነበረ መብት የሚያስገኝ የይርጋ ደንብ (Acquisitive Prescription) አላማ

የይርጋ ደንብ የራሱ የፖሊሲ መሰረት ያለው ነው። የንብረት ባለቤትነት አጀማመር ከይዞታ መብት ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዳለው በመስኩ ምርምር ያደረጉ የህግ ምሁራን ይገልጻሉ።[5] የሰው ልጅ ለህልውናው አስፈላጊ የሆኑ ጠቃሚ ንብረቶችን በይዞታው ስር ማዋል ሲጀምር የግል ንብረት (private property) ጽንሰ ሀሳብ ተከሰተ። ባለቤቱ የለቀቀውን ወይም ባለቤት ያልነበረውን ንብረት አስቀድሞ የያዘ ሰው በንብረቱ ላይ ከሌሎች ሰወች የተሻለ መብት እንዳለው ህብረተሰቡ እውቅና ሲሠጠው የይዞታ ጽንሰ ሀሳብ ወደ ባለቤትነት (ባለሀብትነት) ጽንሰ ሀሳብ ተለወጠ።[6] ከቀደምት ብሂሎች መካከል "አስቀድሞ በእጅ ማድረግ የማይገሰስ መብት ነው" (the devine right of grab) የሚለው ብሂል የረጅም ዘመን ይዞታን ወደ ባለቤትነት የሚለውጠውን ያልነበረ መብት ለሚያስገኘው የይርጋ ደንብ መነሻ እንደሆነ የህግ ምሁራን ያስረዳሉ።[7]

ስለሆነም ያልነበረ መብት የሚያስገኘው የይርጋ ደንብ አንድን ጠያቂ የሌለው ንብረት ለረጅም ጊዜ በይዞታው ይዞ ሌሎች የህግ መከላከያወችን በማሟላት የተጠቀመ ሰው ህግ ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ ሲያልቅ የንብረቱ ባለቤት የሚሆንበትን እድል ይፈጥራል።[8] የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ ቀድሞ ከእርሱ የተሻለ መብት የነበረው ሰው ቢመጣም የቀድሞ ባለሀብቱ ነበርኩ ብሎ መብቱን ሊጠይቀው አይችልም። በንብረቱ ለረጅም ጊዜ ሲጠቀምበት ለቆየው ሰው ያለፈው ጊዜ ከንብረቱ

[5] G. Paton, Philisophy of law, West Publishing Company, 1945, page 485-489
[6] ጥላሁን ተሸመ፣ የግርጌ ማስታወሻ 4፣ ገጽ 182
[7] ዝኒ ከማሁ
[8] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 181

ካገኘው ቁሳዊ የሆነ ጥቅም ባሻገር የባለቤትነት ስሜትንም ለመፍጠር በቂ እንደሆነ ህጉ ይገምታል። የዚህ ይርጋ ደንብ ዋና አላማም በንብረት ባለቤትነት ላይ ሰላምንና መረጋጋትን ማረጋገጥ ነው።[9] የህግ ፍልስፍና ሊቅ የሆኑት ጆርጅ ፓተን እንደገለጹት አንድ የመብት ጥያቄ በህግ ፊት ተቀባይነት ቢኖረውም እንኳን ሊቀርብ በሚችልበት ጊዜ ላይ ገደብ ማበጀት አስፈላጊ ነው።[10]ህጉ ዳተኛውን ባለገንዘብም ቢሆን ማስጠንቀቅ ያስፈልገዋል። ስለሆነም የይርጋ ደንብ የሚፈጥረው አጠቃላይ ዋስትና ከጉዳቱ አንጻር ሲታይ ሚዛን ይደፋል።

## 2.2. የግዴታ አስቀሪ ይርጋ ደንብ (Liberative Prescription) አላማ

ግዴታ አስቀሪ የይርጋ ደንብ (liberative prescription) ባለመብቱ መብቱን ሳይጠይቅ በህግ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ካለፈ ጥያቄ የማቅረብ መብቱን የሚያሳጣ የይርጋ ደንብ ነው። ስለሆነም ባለገንዘቡ በባለእዳው ላይ ክስ የማቅረብ መብቱን ሳይጠቀምበት በህግ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ካለፈ ክስ የማቅረብ መብቱን ያጣል። የዚህ ይርጋ ደንብ አላማም በዋናነት ተከሣሽን ብዙ ጊዜ ካለፈው ክስ ለመጠበቅ ሲሆን ለዚህም ሦስት ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል።[11] የመጀመሪያው ህጉ የሚያግዘው ቀልጣፋን ባለመብት እንጅ ዳተኛውን ባለመብት ባለመሆኑ ከሣሽ በቅን ልቦና መብቱን ለማስከበር ከፈለገ ጉዳዩን በተቻለው ፍጥነት ማቅረብ ይኖርበታል ከሚል ሀሣብ የተነሳ ነው።[12] ሁለተኛው ምክንያት ጉዳዩ ከመዘግየቱ የተነሣ ተከሣሽ ክሱን ለማስተባበልና ለመከላከል ማስረጃዎችን ሊያጣ ይችላል የሚል ነው። ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ እጅግ ዘግይተው የሚቀርቡ ክሶችና አቤቱታዎች ፍትህ ከማስገኘት ይልቅ በክፉ ልቦና ተከሳሹን ለማጥቂያ መሳሪያነት ስለሚውሉ ይህንኑ ለመከላከል ስለመሆኑ ይርጋን አስመልክቶ በተፃፉ በርካታ ፅሁፎች ላይ ተመልክቷል።[13] ስለዚህ የእውነት መብቱን ማስከበር የፈለገ ሰው ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ክሱን መመስረት ይኖርበታል። በጣም ዘግይቶ ከመጣ ግን በመዘግየቱ የተነሣ የራሱን መብት ከማስከበር ይልቅ በተከሳሹ ላይ አላስፈላጊ ጫና ስለሚያሳድር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም።[14]

---

[9] Daniel W.Ambaye, Applicability of period of limitation in rural land dispute: case comment, Bahirdar University Journal of Law, volume 5, Number 1, 2014፣ page 225.

[10] G. Paton, Philisophy of law, West Publishing Company , 1945, page 485-489

[11] Halsbury's Law of England, 4th edition, as cited in Daniel W.Ambaye, Applicability of period of limitation in rural land dispute: case comment, Bahirdar University Journal of Law, volume 5, Number 1, 2014፣ page 225.

[12] Halsbury's Laws of England, 4th edition, በዶ/ር ዳንኤል፣ የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 225 እንደተጠቀሰው

[13] ዝኒ ከማሁ

[14] Rene David, Commentary on Contracts in Ethiopia, translated by Michael Kindred, 1973, Haile Sellassie I university, Faculty of Law, page 90

በሌላ በኩል የይርጋ ፅንሰ ሃሳብ በሕግ ስርዓት ውስጥ መካተቱ ተከሳሹን የሚጠቅመውን ያህል የፅንሰ ሃሳቡ መኖር መብት ጠያቂውን በእጅጉ የሚጎዳ ነው። በይርጋ ጊዜያት መለያየት፣ ትክክለኛ የይርጋ ጊዜን ባለማወቅ፣ ወይም በቸልተኝነት ምክንያቶች የሕግ ድጋፍና በቂ ማስረጃ እያላቸው በርካቶች መብታቸውን አጥተዋል። በቁጥር ቀላል የማይባሉ ክሶችም በይርጋ ምክንያት ውድቅ ተደርገው በርካታ መዛግብት ተዘግተዋል። ክስ አቅርቦ መብትን ለመጠየቅ የሚያስችል በቂ ማስረጃ እና የሕግ ድጋፍ እያለ ተከሳሽን ለመጥቀም ሲባል የይርጋ ፅንሰ ሀሳብ በሕግ ድጋፍ ተሠጥቶት በመካተቱ በርካታ መብት ጠያቂዎችን መብት አሳጥቶ ሕግ ተላላፊዎችን ከኃላፊነት ተጠያቂነት ነፃ ማውጣቱ የማይዋጥላቸው አንዳንድ ሰወች ሊኖሩ ቢችሉም የይርጋ ጽንሰ ሃሳብ ግን በመላው ዓለም በስፋት ተቀባይነት ያገኘ የሕግ ፅንሰ ሀሳብ ለመሆን በቅቷል።

## 3. የይርጋ ህግ መሠረታዊ መርሆዎች

ምንም እንኳን ሁለቱም አይነት የይርጋ ደንቦች ውጤታቸው የተለያየ ቢሆንም ለሁለቱም የሚያገለግሉ የህግ ድንጋጌወችን በኢትዮጵያ የፍታብሄር ህግ[15] ውስጥ እንመለከታለን። በፍታብሔር ህጉ 1169(1) መሰረት ስለውሎች በጠቅላላው በሚለው ክፍል ውስጥ ስለ ግዴታ አስቀሪ የይርጋ ደንብ መቋረጥ የተቀመጡት ድንጋጌወች በሙሉ ስለ ይዞታ (ያልነበረ መብት ለሚያስገኝ) የይርጋ ደንብ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚነት አላቸው። ነገር ግን ሁለቱም አይነቶች የይርጋ ደንቦች በመሰረታዊ መርሆቻቸው እና በሚያስከትሉት ውጤት የተለያዩ በመሆናቸው እያንዳንዳቸው ያላቸውን ልዩ ባህሪ ቀጥለን እንመለከታለን።

### 3.1. ያልነበረ መብት የሚያስገኝ ይርጋ ደንብ (Acquisitive Prescription) መሰረታዊ መርሆች

ከላይ እንደተገለጸው ያልነበረ መብት የሚያስገኝ የይርጋ ደንብ አላማ አንድን ጠያቂ የሌለው ንብረት ለረጅም ጊዜ በይዞታው ይዞ ሌሎች የህግ መከላከያወችን በማሟላት የተጠቀመ ሰው ህግ ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ ሲያልቅ የንብረቱ ባለቤት የሚሆንበትን እድል በመፍጠር በንብረት ባለቤትነት ላይ ሰላምንና መረጋጋትን ማረጋገጥ ነው። ይህንን የይርጋ ደንብ በፍታብር ህጉ 1168(1) ላይ ተመልክቶ እናገኘዋለን። በዚህ የህግ ድንጋጌ መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለ ይዞታ የሆነ ሰው የዚህን ንብረት ግብር ባለማቋረጥ ለ 15 (አስራ አምስት) አመታት በስሙ

[15] የኢትዮጵያ የፍታብሄር ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 165/1952፣ አንቀጽ 1169

ከከፈለ የዚሁ ንብረት ባለቤት ይሆናል። ነገር ግን ንብረቱ የርስት መሬት ከሆነ ጉዳዩ በይርጋ አይታገድም። በተጨማሪም የህብረት ስለሆኑ የእርሻ መሬቶች የሚደነግገው የፍታብሄር ህጉ አንቀጽ 1493 የህብረት የእርሻ መሬቶች (land owned by agricultural community) ለሌላ ሰው መተላለፍ እንደማይችሉ ስለሚደነግግ የህብረት መሬቶችን በተመለከተ በሚቀርቡ ክሶች ላይ የይርጋ ደንብ አይፈጸምም ማለት ነው። በተመሳሳይ በፍታብሄር ህጉ አንቀጽ 1454 መሰረት ለህዝብ አገልግሎት የተመደቡ ሀብቶች (properties fall under public domain) ለሌላ ሰው አይሸጡም፣ አይተላለፉም። በፍታብሄር ህጉ አንቀጽ 1150 መሰረትም የይዞታ መብት ያለው ሰው ከራሱ የይዞታ ጊዜ ላይ ንብረቱን ያስተላለፈለትን ሰው የይዞታ ጊዜ ለመደረብ የሚችለው የንብረቱን ይዞታ ያስተላለፈለት ሰው በይርጋ የራሱ ይዞታ ለማድረግ የሚፈቅድ መብት ሲኖረው ብቻ ነው።

ያልነበረ መብት የሚያስገኙ የይርጋ ደንቦች አብዛኛውን ጊዜ ለክርክር ምክንያት የሚሆኑት የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ ነው። በመሬት ክርክሮች ዙሪያ የተከናወኑ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአማራ ክልል ውስጥ ብቻ በወረዳ ፍርድ ቤቶች ከሚቀርቡት ከሁሉም የክርክር አይነቶች ውስጥ 70 % (ሰባ በመቶ) የሚሆኑት የመሬት ክርክሮች ናቸው።[16] ስለሆነም መሬት የአርሶ አደሮች ህይወት ህልውና መሰረት ስለሆነ በገጠር የእርሻ መሬቶች ላይ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ክርክሮችን በተመለከተ የይርጋ ደንቦቹ ያላቸውን ተፈጻሚነት እንዲሁም በይርጋ ደንቦቹ ዙሪያ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የያዛቸውን አቋሞች እና በህግ ምሁራን የሚቀርቡ ትንታኔወችን መመልከቱ ተገቢ ነው።

በሰበር መዝገብ ቁጥር (69291)[17] የሰበር ተጠሪ የሆነችው ወ/ሮ ተዋበች ፈረደ በኦሮሚያ ክልል በጉፋ ወረዳ ፍ/ቤት ከሳሽ የነበረች ሲሆን ያቀረበችው ክስ ተከሳሽ የሆነው አቶ ጀማል አማን በወለድ አገድ ውል (contract of Antichresis) በ 1020 ብር በወለድ አገድ ውል የያዘውን የእኔን መሬት በፍርድ ሀይል ተገዶ እንዲመልስልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው። ተከሳሹ በበኩሉ መሬቱን በተከታታይ ለ 11 (አስራ አንድ) አመታት ያረስኩትና የተጠቀምኩበት ስለሆነ ክሱ በፍታብሄር ህጉ አንቀጽ 1845 መሰረት በይርጋ ታግዷል በማለት ተከራክሯል። የስር ፍርድ

[16] ILA, 2015, Assessment of the implementation of rural land laws in Amhara National Regional State, Institute of Land Administration, A study sponsored by the land administration to nurture development (LAND) of USAID, Unpublished as cited in Dr. Daniel. W. Ambaye, የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 223.

[17] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 13፣ መዝገብ ቁጥር- 69291፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2005፣ ገጽ 423- 425

ቤቶች የተለያዩ ውሳኔወችን ከሰጡ በኋላ ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጠው የህግ ትርጉም በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40 (3)(4) እና አዋጅ ቁጥር 456/97 መሰረት በወለድ አገድ ውል (contract of Antichresis) አንድ ባለእዳ ግዴታውን ለመፈጸም ማረጋገጫ በማድረግ ለገንዘብ ጠያቂው የእርሻ መሬቱን ለማስረከብ የሚዋዋለው ውል ህገ ወጥ ውል በመሆኑ በፍታብሄር ህጉ አንቀጽ 1845 ላይ የተደነገገው የይርጋ ደንብ ተፈጻሚ አይሆንም በማለት ወስኗል፡፡ የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅም የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው ትርጉም ትክክለኛ እንደሆነ ያምናል፡፡ ምክንያቱም የወለድ አገድ ዉሉ የተፈጸመው በ 1990 ዓ.ም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት ከወጣ በኋላ ስለሆነና ዉሉ ከህገመንግስቱ ጋር ስለሚጋጭ ነው፡፡

በሌላ በኩል በሰበር መዝገብ ቁጥር (69302)[18] የሰበር ተጠሪ የሆነው አቶ ፈይሳ መንግስቱ በኦሮሚያ ክልል ባንጃ ወረዳ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበረ ሲሆን ያቀረበው ክስ የስር ተከሳሽ (የሰበር አመልካች) የሆነው አቶ ሽልማ ነገሰ በህገወጥ መንገድ የያዘብኝን መሬት እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ተከሳሽ በበኩሉ መሬቱን መያዙን አምኖ ነገር ግን ከከሳሽ አባት መሬቱ ላይ ያሉትን ዛፎች የገዛኋቸው በመሆኑ እንዲሁም የከሳሽ አባት ከሸጠልኝ በኋላ ወደ ሌላ ቀበሌ ለመኖር ስለተዛወረ መሬቱን በተከታታይ ለ 12 (አስራ ሁለት) አመታት የተጠቀምኩበት ስለሆነ የቀረበው ክስ በይረጋ ስለሚታገድ ልጠየቅ አይገባም በማለት ምላሽ ሰጥቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች የተለያዩ ውሳኔወችን ከሰጡ በኋላ ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጠው የህግ ትርጉም በፍታብሄር ህግ ቁጥሮች 1677 እና 1845 መሰረት ክሱ 10 (አስር) አመት ካለፈ በኋላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል በማለት ከዚህ ቀደም በመዝገብ ቁጥር 69291 ላይ ከያዘው አቋም የተለየ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በመሰረቱ በፍታብሄር ህጉ አንቀጽ 1133 ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ዛፎች እና ሰብሎች ከመሬት ሳይለያዩ በሚቆዩበት ጊዜ ከመሬቱ ጋራ እንደ አንድ አካል ሆነው ይቆጠራሉ፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ ጽሁፍ የጻፉት ዶክተር ዳንኤል አስተያየታቸውን ሲሰጡ የስር ከሳሽ አባት ዛፎቹን ለስር ተከሳሹ በቁም ከሸጡ በኋላ ወደ ሌላ ቀበሌ ለመኖር መዛወራቸውና የስር ተከሳሹ መሬቱን በተከታታይ ለ 12 (አስራ ሁለት) አመታት ሲጠቀምበት መቆየቱ የሽያጭ ዉሉ ዛፎቹን ብቻ ሳይሆን መሬቱንም ለማስተላለፍ እንደተደረገ ይጠቁማል በማለት ይከራከራሉ፡፡[19]

[18] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 13፣ መዝገብ ቁጥር- 69302፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2005፣ ገጽ 426- 429

[19] Dr. DanielW. Ambaye, የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 241

ይህ ደግሞ ከኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40 (3)(4) ጋር ስለሚጋጭና ውሉን ህገወጥ ስለሚያደርገው ሰበር ሰሚ ችሎቱ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ አይደለም በማለት ዶክተር ዳንኤል አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።[20] የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅም የዶክተር ዳንኤል ሀሳብ ሚዛን እንደሚደፋ ያምናል።

በሌላ ጉዳይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 71204 (ያልታተመ)[21] የሰበር አመልካቹ የኩታበር ወረዳ ቀበሌ 13 አስተዳደር የስር ከሳሽ የነበረ ሲሆን በአማራ ክልል በኩታበር ወረዳ ፍርድ ቤት የስር ተከሳሽ በሆነው አቶ ሀብቱ ሞላ ላይ ያቀረበው ክስ ተከሳሹ የመንግስትን ቤት በህገ ወጥ መንገድ ለ 29 (ሀያ ዘጠኝ) አመታት የያዘ ስለሆነና ቦታው ለልማት ስለሚፈለግ ቦታውን እንዲለቅ ይወሰንልን የሚል ነው። አቶ ሀብቱ ሞላ በበኩሉ ቤቱ የተሰጠኝ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የጥበቃ ሰራተኛ ሆኜ ላገለገልኩበት ምትክ (ካሳ) ስለሆነ እና ለ 29 አመታት ያለማቋረጥ የኖርኩበት ቤት በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ተከራክሯል። የስር ፍርድ ቤቶች የተለያዩ ውሳኔወችን ከሰጡ በኋላ ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጠው የህግ ትርጉም በፌዴራልና በክልሎች የመሬት አዋጆች መሰረት መሬት ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችለው መንግስት ሲደለድል፣ ወይም ከቤተሰብ ሲገኝ ፣ ወይም በሊዝ ውል አማካኝነት ነው። ስለሆነም አቶ ሀብቱ ሞላ ለሰጠሁት የጥበቃ አገልግሎት በምትኩ ቦታ ተሰጥቶኛል በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ቦታው የተገኘበት አግባብ ህገ ወጥ ስለሆነ ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት ወስኗል።

ነገር ግን ምሁራን በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ትርጉም ላይ የልዩነት ሀሳባቸውን ያቀርባሉ። በዚሁ ጉዳይ ላይ ዶክተር ዳንኤል አስተያየታቸውን ሲሰጡ ለአቶ ሀብቱ ቦታው የተሰጠው በደርግ ዘመነ መንግስት ጊዜ ሲሆን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የወጣን ህግ ወደ ኋላ መልሶ ተፈጻሚ ማድረጉ ተገቢነት ስለሌለው ጉዳዩ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል።[22] በተጨማሪም ያለ ህግ አግባብ የተያዘን የመንግስት (የህዝብ) መሬት ለማስመለስ የሚቀርብ ክስ በፍታብሄር ህግ ቁጥሮች 1168 (2) እና 1845 መሰረት በይርጋ ሊታገድ ይገባል የሚል አቋም አላቸው።[23]

[20] Dr. DanielW. Ambaye, የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 240
[21] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ፣ መዝገብ ቁጥር- 71204፣ መጋቢት 10፣ 2004 E.C፣ (ያልታተመ) በዶ/ር ዳንኤል፣ የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 235 ላይ የተጠቀሰ
[22] Dr. DanielW. Ambaye, የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 241
[23] ዝኒ ከማሁ

የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅም በዘመናዊ የህግ ፍልስፍና መሰረት ህጎችን ከወጡበት ጊዜ ወደ ኋላ መልሶ ተፈጻሚ ማድረግ ተገቢ አለመሆኑን ያምናል።[24]

በሌላ የሰበር መዝገብ ቁጥር 96203(ያልታተመ)[25] የሰበር ተጠሪ የሆነው የሰሜን አቸፈር መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የስር ከሳሽ የነበረ ሲሆን በወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ የስር ተከሳሽ የሆነው አቶ ቸኮል ቁሜ ለ 16 (አስራ ስድስት) አመታት በህገ ወጥ መንገድ ክርክር የተነሳበትን መሬት እየተጠቀመበት ስለሆነ መሬቱን እንዲለቅ ይወሰንልን የሚል ነው። የስር ተከሳሽ በበኩሉ መሬቱን ያገኘሁት በመሬት ድልድል ወቅት በህጋዊ መንገድ የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቶኝ ስለሆነና ለ 16 (አስራ ስድስት) አመታት የተጠቀምኩበት ስለሆነ ክሱ በይርጋ ሊታገድልኝ ይገባል በማለት ተከራክሯል። የስር ፍርድ ቤቶች የተለያዩ ውሳኔወችን ከሰጡ በኋላ ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጠው የህግ ትርጉም የመሬት አስተዳደር ተቋማት ያለአግባብ በግለሰቦች የተያዘ መሬትን ለማስመለስ ሲሉ የሚያቀርቡት ክስ በይርጋ እንዲታገድ የሚደነግግ የመሬት አዋጅ ባለመኖሩ የመሬት አስተዳደር ተቋማት ያለምንም የጊዜ ገደብ ክስ ማቅረብ እንደሚችሉና ጉዳዩ በይርጋ እንደማይታገድ ወስኗል።

ነገር ግን በመስኩ ምርምር ያደረጉ አንዳንድ ምሁራን እንደሚገልጹት አንድ ሰው ከ 15 (አስራ አምስት) አመት በላይ ግብር እየከፈለና የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይዞ እየተጠቀመበትን ያለ መሬት መሬቱን የተረከብከው ከህግ አግባብ ውጭ ነው በሚል ምክንያት የሚነጠቅ ከሆነ በህብረተሰቡ ዘንድ መሬቴን በማንኛውም ጊዜ ልነጠቅ እችላለሁ የሚል ስጋትና አለመረጋጋት (tenure insecurity) ይፈጥራል።[26] ስለዚህ የመሬት አስተዳደር ተቋማት ማቅረብ የሚገባቸውን ክስ በንቃትና በፍጥነት እንዲያቀርቡ ለማስቻልና የህብረተሰቡን ስጋት ለማስወገድ ይረዳ ዘንድ በፍታብሄር ህግ ቁጥር 1168 የተመለከተው የይርጋ ደንብ ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል በማለት ይከራከራሉ።

የገጠር የእርሻ መሬትን በተመለከተ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ 4ኛ (አራተኛ) የፓርላማ ዘመኑ 5ኛ (አምስተኛ) አመት፣2ኛ (ሁለተኛ) መደበኛ ስብሰባ ሠኔ 18 ቀን 2007

[24] Deborah k. Mc Knight, Retroactivity of Statutes; What Constitutional limits are there on the retroactive application of laws? , 2005, accessed at www.house.leg.state.com last visited on 12/12/2015, page 8

[25] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ፣ መዝገብ ቁጥር- 96203፣ሚያዚያ 9፣ 2006 E.C፣ (ያልታተመ) በዶ/ር ዳንኤል፣ የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 239 ላይ የተጠቀሰ

[26] ዶ/ር ዳንኤል፣ የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 239

ዓ.ም በሰጠው የህገመንግስታዊ ትርጉም መሰረት የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል ህገ መንግስታዊ መብት አላቸው። ለዚህ ትርጉም መነሻ የሆነው ከኦሮሚያ ክልል የተነሳ የባልና ሚስት የገጠር መሬት ክርክር ነው። አመልካች ከስር ፍርድ ቤቶች ጀምራ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበችው ማመልከቻ ተጠሪው የቀድሞ ባለቤቷ መሆኑን በመግለጽ ባጋጠማት የጤና ችግር ምክንያት ክስ ማቅረብ ከሚገባት 12 (አስራ ሁለት) አመታት ዘግይታ ድርሻዋን መሬት እንዲያካፍላት ክስ መሰረተች። ተጠሪው በበኩሉ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት የተከራከረ ሲሆን ይህንኑ መከራከሪያ ነጥብ በመመልከት የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎቱ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። ነገር ግን ህገ መንግስታዊ ትርጉም ያስፈልገዋል በሚል ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ 4ኛ የፓርላማ ዘመኑ 5ኛ አመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ ሠኔ 18 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው የህገመንግስታዊ ትርጉም አመልካች በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (4) መሰረት ከመሬቷ ያለመነቀል ህገ መንግስታዊ መብት ያላት በመሆኑ ያቀረበችው ክስ በይርጋ ሊታገድባት አይገባም።[27]

### 3.2. የግዴታ አስቀሪ ይርጋ ደንብ (Liberative Prescription) መሰረታዊ መርሆች

ከዚህ ጽሁፍ መግቢያ ላይ እንደተገለጸው ግዴታ አስቀሪ የይርጋ ደንብ ባለመብቱ መብቱን ሳይጠይቅ በህግ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ካለፈ ጥያቄ የማቅረብ መብቱን የሚያሳጣ የይርጋ ደንብ ነው። ከስሙ እንደምንረዳው ይህ የይርጋ ደንብ የሚያገለግለው በግዴታ ህግ ውስጥ ነው። የይርጋ ደንቡን አስመልክቶ በተለያዩ ሕጎች ውስጥ የተካተቱት ድንጋጌዎች በዋናነት የሚያመላክቱት ክስ ለማቅረብ የሚቻልበትን የጊዜ ገደብ ነው። ክስ ለማቅረብ ወይም መብት ለመጠየቅ እንዲቻል በሕግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብም እንደጉዳዩ ክብደት፣ ባሕሪና ሁኔታ የተለያየ ሲሆን ለሁሉም ጉዳዮች የተቀመጠ ተመሣሣይ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ የለም። በመሆኑም ሕግ አውጪው እንደ ጉዳዩ ዓይነት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ክስ ለማቅረብ ወይም መብት ለመጠየቅ እንደሚቻል ለማመላከት የተለያዩ የክስ ማቅረቢያ ጊዜወችን በሕጎች ውስጥ እንዲካተት አድርጓል። ክስ የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ በሕግ ውስጥ ከተካተተ በኋላ ሌላው ሊነሳ የሚገባው ሀሳብ የተቀመጠው የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ከመቼ ወይም ከምን ሁኔታ ጀምሮ መቆጠር እንደሚጀምር ማመልከት ነው። ለአብነት ያህል በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት በኢንሹራንስ

[27] በዚህ ጭብጥ ዙሪያ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በቁጥር በርከት ያሉ ህገ መንግስታዊ ትርጉሞችን የሰጠ በመሆኑ ትርጉሞቹን መመልከት ይቻላል።

ውል ምክንያት የሚቀርብ ክስ መቅረብ ያለበት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆኑ የተመለከተ ሲሆን የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ወይም በጉዳዩ ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ መገለፁ እንደጥሩ ምሳሌ ሊወሰድ ይችላል።[28]

በተጨማሪም በሕግ ላይ የተገለጸው ክስ የማቅረቢያ ወይም መብት የመጠየቂያ ጊዜ እንደ ጉዳዩ እና ሕጉ ልዩ ባህሪ በሚመለከታቸው አካላት በውል ሊያጥር ወይም ሊረዝም ስለሚችልበት ሁኔታ በህጉ ውስጥ ሊካተት ይችላል። በህጉ የተቀመጠ የይርጋ ጊዜን ማሻሻል እንደሚቻል ወይም እንደማይቻል በህጉ ማመላከት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ይርጋን አስመልክቶ ተጨማሪ መብት እንዳላቸው ወይም እንደሌላቸው ከማስገንዘብ ባለፈ መብቱ በሕግ ከተሰጠ የይርጋ ጊዜን የማሻሻል ዕድል የሚፈጥር ይሆናል። ለምሳሌ በንግድ ሕጋችን መሰረት በኢንሹራንስ ውል ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም ክስ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት እና የይርጋ ጊዜውን ተዋዋይ ወገኖች በውል ለማሣጠር እንደማይችሉ ይደነግጋል። ይህም የሚያመላክተው የኢንሹራንስ ጉዳዮችን አስመልክቶ በሕጉ የተመለከተው የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት መሰረት በውል ሊራዘም የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ነው።[29]

በሕግ የተቀመጠ ክስ የማቅረቢያ ጊዜ ሊቋረጥና የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር እንደ አዲስ ሊጀመር የሚችልባቸው ሁኔታዎች ከይርጋ ደንብ ጋር ተያይዞ ዕንሰ ሃሳቦች ናቸው።[30] ለምሳሌ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ላይ ውል እንዲፈጸም ወይም ካለመፈፀሙ የተነሳ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊጠየቅ እንደሚገባ የተመለከተ ሲሆን በቁጥር 1851 እና 1852 መሰረት በአስር ዓመት ጊዜው ውስጥ ለምሳሌ በዘጠነኛው አመት ላይ ባለዕዳው ዕዳውን ካመነ፣ በከፊል ከከፈለ፣ መያዣ ወይም ዋስ ከሠጠ ወይም ባለገንዘቡ መብቱ እንዲታወቅለት ለፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ለባለዕዳው አስታውቆ እንደሆነ ይርጋው ሊቋርጥ እንደሚችልና ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ እንደገና እንደ አዲስ የይርጋ ዘመን መቆጠር እንደሚጀመር በግልፅ የተመለከተ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል።

[28] የኢትዮጵያ የንግድ ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 166/1952፣ አንቀጽ 674(1)
[29] ዝኒ ከማሁ፣ የንግድ ህግ አንቀጽ 674(3)
[30] ጥላሁን ተሸመ የግርጌ ማስታወሻ 4

### 3.3. የይርጋ መከራከሪያን ሊያነሳ የሚችለው ማን ነው?

በወንጀል ጉዳይ ላይ ይርጋን በመቃወሚያነት አንስተው ለመከራከር የሚችሉት ተከሳሽ፣ ዐቃቤ ሕግና ፍርድ ቤቶች ስለመሆናቸው በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ[31] አንቀጽ 130 ስር ተመልክቷል። በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ[32] አንቀጽ 216 (2) መሰረት የወንጀል ክሱ በይርጋ ስለመታገዱና ክሱን ለመቀበል የማይገባ ስለመሆኑ ተከሳሹ ባያመለክትም አቃቤ ህግ ወይም ፍርድ ቤት በማናቸውም ጊዜ የይርጋ መቃወሚያውን የማንሳት ሀላፊነት አለባቸው። ስለሆነም ዐቃቤ ሕግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ እና በወንጀል ህጉ መሠረት በመዝገቡ ላይ ሕጋዊ አስተያየት በሚሠጥበት ወቅት ጉዳዩ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆን አለመሆኑ የመረዳትና ጉዳዩ በይርጋ የሚታገድ ከሆነም በይርጋ ምክንያት ክስ አያስቀርብም በሚል መዝገቡን የመዝጋት ኃላፊነት እንዳለበት መገንዘብ ይቻላል። በአንጻሩ ግን ፍርድ ቤቶችን በተመለከተ በተከራካሪ ወገኖች በኩል ይርጋ በመከራከሪያነት ባልቀረበበት ሁኔታ ፍርድ ቤቶች በራሳቸው አነሳሽነት ይርጋን እንደ አንድ የመከራከሪያ ነጥብ አንስተው ሊመረምሩ ይችላሉ ወይ? የሚለው ነጥብ ተያይዞ ሊነሳ ይገባል።

የፍትሐብሔር ስረ ነገር (ፍሬ ጉዳይ) የይርጋ ደንቦችን (substantive period of limitation) በተመለከተ በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1856(2) ሥር እንደተመለከተው ዳኞች በተከራካሪወች ካልተነሳ በቀር በገዛ ሥልጣናቸው የይርጋውን ደንብ በመቃወሚያነት ለመጥቀስ አይችሉም በሚል የተመለከተ በመሆኑ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን የሚመለከቱ ፍርድ ቤቶች የይርጋ መከራከሪያ በተከራካሪ ወገኖች ካልተነሳ ፍርድ ቤቶች በራሳቸው ጊዜ ይርጋን በመከላከያነት ሊያነሱና ሊወስኑ አይችሉም።

ነገር ግን በሥነ ሥርዓት ሕጎች የተደነገጉ የይርዳ ደንቦችን (procedural period of limitation) በተመለከተ በኢትዮጵያ የፍታብህር ሥነ ሥርአት ህግ[33] ቁጥር 49 ስር እንደተደነገገው በስነ ስርዓት ህጎች በግልጽ የሰፈረ የይርጋ ጊዜን በማሳለፍ የሚቀርብ ጥያቄን ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ ይችላል። በዚሁ ጉዳይ ላይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅጽ አንድ ላይ በሚገኘውና በመዝገብ ቁጥር 17361[34]

[31] የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 1/1954፣ አንቀጽ 130(2)(ሐ).
[32] የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 414/1996፣ አንቀጽ 216(2)
[33] የኢትዮጵያ የፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 52/1958፣ አንቀጽ 49
[34] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 1፣ መዝገብ ቁጥር- 17361፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 1997፣ ገጽ 12

በሰጠው ውሳኔ ላይ በሥረ- ነገር /Substantive/ ህጎች የተደነገጉ የይርጋ ደንቦች በሥነ ሥርዓት ሕጎች ከተደነገጉት የጊዜ ገደቦች የተለዩ መሆናቸውን እና በስነ ስርዓት ህጎች በግልጽ የሰፈረን ጊዜ ሳይጠብቅ የሚቀርብን ጥያቄ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ እንዳለበት ወስኗል፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 244(2) ላይ ይርጋን ጨምሮ የሚቀርቡ ሌሎች የክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ምክንያቶችን ተከራካሪ ወገኖች ሊያቀርቡ ይችላሉ በሚል የሚያስቀምጥ ቢሆንም ከተለመደው አሰራርና ሁኔታ ለመረዳት እንደሚቻለው ይርጋን በመቃወሚያት የሚያቀርበው ክስ የቀረበበት ወገን (ተከሳሽ) ነው፡፡ ምክንያቱም ከሳሽ የሆነ ወገን የሚያቀርበው ክስ በይርጋ እንደሚታገድ ቢያውቅም እንኳን የራሱን ክስ ውድቅ ለማስደረግ ፍላጎት አይኖረውም፡፡ ነግር ግን በፍትሐብሔር ጉዳይ ከሳሽ የሆነ ወገን ይርጋን በመከራከሪያነት ሊያነሳ የሚችለው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 236 በተቀመጠው መሰረት ከተከሳሽ ወገን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሲቀርብበት ነው፡፡

ጠበቃወች የደንበኞቻቸውን ጉዳዮች በሚመለከቱበት፣ የክስ መልስ በሚሠጡበት እንዲሁም ክርክር በሚያደርጉበት ወቅት ይርጋን አስመልክቶ የተጣለባቸው ሕጋዊ ኃላፊነት አለ፡፡ በጠበቆች ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 25 መሠረት ጠበቆች በሕግ የተቀመጡትን የይርጋ መቃወሚያወች በመከራከሪያነት ማንሳት እንዳለባቸው በአስገዳጅነት ተመልክቷል፡፡ ጠበቆች የደንበኞቻቸውን ጉዳይ ይዘው በሚከራከሩበት ወቅት ለደንበኞቻቸው በሕግ የተፈቀደላቸውን የይርጋ መቃወሚያወችን ሳያቀርቡ ሊቀሩ የሚችሉት ሁኔታውን ለደንበኞቻቸው በግልጽ ካስረዱ በኋላ ደንበኞቻቸው ይርጋን በመከራከሪያነት እንዳያቀርቡ በጽሑፍ ፈቃዳቸውን ሲሰጧቸው ብቻ እንደሆነ በስነ ምግባር ደንቡ ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን ጠበቆች በሕጉ ከተመለከተው ሁኔታ ውጭ የደንበኞቻቸውን ልዩ ፍቃድ በጽሑፍ ሳያገኙ ቀርተው ይርጋን በመከራከሪያነት ሊያቀርቡ እየተገባቸው በመከራከሪያነት ሳያቀርቡ ቢቀሩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፍቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 24(3) ሥር የተመለከቱትን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ከማግኘት እስከ ጥብቅና ፍቃድ መሰረዝ የሚደርሱ የተለያዩ ቅጣቶችን ሊቀጡ ይችላሉ፡፡

### 3.4. ይርጋ በመከራከሪያነት የሚነሳው መቼ ነው?

በፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ተከራካሪው (ተከሳሽ) ይርጋን በመቃወሚያነት አንስቶ ለመከራከር የሚችለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 234 መሰረት ለቀረበው ክስ (አቤቱታ) የመከላከያ መልስ በጽሑፍ ሲሰጥ መሆን እንዳለበት በስነ ስርአት ህጉ አንቀጽ 244(2)(ሠ) ላይ ተመልክቷል፡፡

እንዲሁም በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ ለፍርድ ቤቱ ማንነቱን ካስመዘገበና ክስ ከተነበበለት በኋላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ክስና መከራከሪያ ከመቅረቡና ማስረጃም ከመሠማቱ በፊት ይርጋን በመቃወሚያነት አንስቶ ለመከራከር እንደሚችል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 130(2)(ሐ) እና (3) ላይ ተመልክቷል። በመሆኑም ይርጋን በመቃወሚያነት ማቅረብ የሚቻለው ክስ ከመሰማቱ እና ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር በተከሳሽ በኩል ተፈፅሟል አልተፈፀመም የሚለው ነጥብ ላይ ክርክር ከመደረጉ በፊት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ነው።

### 3.5. በይርጋ ደንብ የማይታገዱ ጉዳዮች

ለአብዛኛዎቹ የህግ ጉዳዮች ክስ የማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ተቀምጦላቸዋል። ሆኖም ጥቂት በሆኑ ጉዳዮች ላይ ክስ የማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ሳይኖር ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆነው ድርጊት ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ያለምንም የጊዜ ገደብ በማንኛውም ጊዜ ክስ ለማቅረብ የሚቻልባቸው ጉዳዮች እንዳሉ በተለያዩ ሕጎች ውስጥ ተመልክቷል። የሽብርተኝነት ወንጀል በፈፀመ ሰው ላይ የሚቀርብ የወንጀል ክስ በይርጋ አይታገድም።[35] በዓለም አቀፍ ሕጎችና ስምምነቶች ውስጥ በጦር ወንጀሎች እና በሰብዓዊነት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ የይርጋ ደንብ እንዳይፈፀም በተደረገው ስምምነት መሰረት የዘር ማጥፋት፣ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እንዲሁም የጦር ወንጀሎችን የሚፈፅሙ ሰዎች ላይ የሚቀርቡ ክሶች በይርጋ አይታገዱም።[36] በተጨማሪም ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ መሰረት በአዋጁ የተመለከቱ ከሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ጋር የተገናኙ ወንጀሎችን በፈፀመ ሰው ላይ የሚቀርብ የወንጀል ክስ በይርጋ አይታገድም።[37] ከላይ የተጠቀሱት ወንጀሎች በይርጋ የማይታገዱበት ምክንያት በጣም አደገኛና የሰው ልጆችን ሰብአዊ መብትና ክብር የሚነኩ በመሆናቸው ነው።

በተጨማሪም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 10 የሰበር መዝገብ ቁጥር 43600 ላይ በሰጠው ውሳኔ[38] መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ ባለመብት የሆነው ሰው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1206 መሰረት መብት ሳይኖረው በእጁ ካደረገው ሌላ ሰው

[35] የኢፌዴሪ የጸረ- ሽብርተኝነት አዋጅ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 24

[36] William .P. Anson, Principles of English Law, 19th ed. 1945, Oxford University Press, p. 67.

[37] ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ የኢፌዴሪ አዋጅ ቁጥር 909/2007፣ አንቀጽ 25

[38] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች፣ ቅጽ 10፣ መዝገብ ቁጥር- 43600፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2003፣ ገጽ 224

ወይም ከያዘው ሰው ላይ ሃብቱ ይገባኛል ሲል የሚያቀርበው የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይችልም፡: በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1678፣ 1716 እና 1718 እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 14 የሰበር መዝገብ ቁጥር 79394[39] እና በቅፅ 12 የሰበር መዝገብ ቁጥር 43226 ላይ በሰጣቸው የህግ ትርጉሞች መሰረት የውል መሠረታዊ ዓላማ በሕግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቶች/ዳኞች ሕገ ወጥ የሆነው ውል በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ሕጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የለውም በማለት ለመወሰን የሚችሉና ሕገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በሕጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡

## 4. የይርጋ ደንብ በኢትዬጵያ አበይት ህግጋት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት (የፌ/ጠ/ፍ/ቤት) ሰበር ሰሚ ችሎት የይርጋ ደንብ ትርጎሞች

### 4.1. የውል ህግ የይርጋ ደንቦች

በፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 1845 መሠረት ውል አልተፈፀመልኝም በሚል ምክንያት እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ ሰው ወይም ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት ጉዳት ደርሶብኛል የሚል ሰው ክሱን ማቅረብ ያለበት ውሉን አልፈፀምም ከተባለበት ወይም ጉዳቱ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን በአንቀጹ ላይ "ህግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር..." የሚለው ሀረግ ልዩ ውሎችን የሚመለከቱ የተለዩ የይርጋ ጊዜ ገደቦች ካሉ አጠቃላይ የይርጋ ደንቡ ተፈጻሚ እንደማይሆን ይጠቁማል፡፡ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1852 መሰረት የይርጋ ማቋረጥ ውጤት ይርጋውን እንደገና እንደ አደስ መቆጠር እንዲጀምር ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዚሁ ህግ አንቀጽ 2024(መ) መሰረት ለቤቶች ኪራይና ለ እርሻ ሀብት ለሆነ የሚከፈል እዳን በተመለከተ እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ 2 (ሁለት) አመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ ይቆጠራል፡፡

የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ባደረገው ጥናት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከ ቅጽ አንድ ጀምሮ እስከ ቅጽ አስራ ሰባት ድረስ ይርጋን በተመለከተ የወሰናቸው ውሳኔወች በቁጥር 70 (ሰባ) ያህል ሲሆኑ ከነዚህ ውሳኔወች ውስጥ በቁጥር 21 (ሀያ አንድ) ወይም ሰላሳ ከመቶ (30%) የሚሆኑት የውል ህግን የተመለከቱ የይርጋ ደንብ ትርጎሞች ናቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሰበር

[39] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 14፣ መዝገብ ቁጥር- 79394፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2006፣ ገጽ 199

ሰሚ ችሎቱ በውል ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች (ትርጉሞች) በሰንጠረዥ መልክ እናያለን፡፡

## <u>ሰንጠረዥ 1</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውል ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ (volume) ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ዓሊ ቃሌብ አህመድ እና እነ አቶ ሚሊዮን ተፈራ | 19081 | ቅጽ 4 | በውል ባለእዳ የሆኑ ባለ እዳወች ሁሉ እዳው በይርጋ ታግዷል በማለት ባለገንዘቡን መከራከር ይችላሉ፡፡. ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሳሾች በአንድ ላይ በተከሰሱ ጊዜ አንዱ ተከሳሽ የሚያነሳው የይርጋ መቃወሚያ በሌሎች ላይ ውጤት ይኖረዋል፡፡ ፍታብሄር ህግ አንቀጽ 1901 |
| 2. | ወ/ሮ ወርቅነሽ አርምዴ እና አቶ ጥላሁን አርምዴ | 29363 | ቅጽ 8 | መሀይምነትን ወይም አይነስውርነትን መሠረት በማድረግ ውል እንዲፈርስ የሚቀርብ አቤቱታ በአሥር አመት ይርጋ ይታገዳል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719፣ 1845 |
| 3. | ወ/ሮ ሀጅራ አብሮ እና አቶ ሐሺም ሐጂ አልዬ | 34940 | ቅጽ 8 | ክርክር የሚካሄድበት የውል ጉዳይን አስመልክቶ በህግ ተለይቶ የተቀመጠ የይርጋ ጊዜ የሌለ እንደሆነ ስለ ውሎች በጠቅላላ በሚለው ክፍል የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት አለው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677፣ 1845 |
| 4 | እነ አቶ ወልደፃድቅ ብርሃኑ እና አቶ ስንታየሁ አያሌው | 38935 | ቅጽ 8 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ለገዥ ያላሳወቀ እንደሆነ ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት የመጠየቅ መብቱ በ 10 (አስር) አመት ይርጋ ይታገድበታል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731(1)፣ 1732፣ 1789 እና 1845 |
| 5. | አቶ ፀጋዬ ምትኩ እና እነ ወ/ሮ አበበች ምትኩ | 36756 | ቅጽ 8 | በፍታብሔር የውል ጉዳዮች የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ከሳሽ ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ጊዜ ጀምሮ መሆን አለበት፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1846 |
| 6. | እነ ወ/ሮ | 39725 | ቅጽ 8 | የማይንቀሣቀስ ንብረት ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት ሻጭን |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | አለምሸት ካሣሁን እና አቶ ሽመልስ እንዳለ | | | የመጠየቅ መብቱ በፍርድ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በአስር አመት ጊዜ ውስጥ ነው። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 384(ሀ)፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2892(3) |
| 7. | አቶ አብዱራዛቅ ሀሚድና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | 44800 | ቅጽ 10 | በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ እስከ አሥር ዓመት ድረስ ነው። የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058 |
| 8. | ወ/ሮ አልማዝ ተሰማ እና እነ አቶ በየነ ወ/ሚካኤል | 43636 | ቅጽ 10 | ከሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ የሚያቀርበው የውል ይፍረስልኝ ክስ ገዥ ውሉ እንዲፈፀምልኝ በሚል ሊያቀርብ የሚችለው አቤቱታ ላይ የሚቆጠረውን የይርጋ ጊዜ ያቋርጣል። የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845፣ 1851 |
| 9. | እነ ሙና እንድሪስና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | 48094 | ቅጽ 10 | አንድ ውል ህግን የሚፃረር /የሚቃረን/ ነው በሚል እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል።<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 |
| 10 | እነ ሙስጌታ ደሣለው እና አየለ ደበላ | 46019 | ቅጽ 10 | የእቁብ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024 ሥር በተመለከተው የህሊና ግምት አይሸፈንም። የፍ/ብ/ሔ/ቁ. 2024 |
| 11 | እነ ፍስሀ መንግስቱ ወ/ሮ አለምነሽ ፍስሀ | 42346 | ቅጽ 10 | በፍ/ብ/ህ/ቁ. 244(1) ላይ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ በስጦታ ውል ውስጥ የተመለከተ ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ውሉ እንዲፈርስ ሲጠየቅ ተፈፃሚነት የለውም። የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2452(1)፣ 2464(1)፣ 2441(1) |
| 12 | አደፍርስ በቀለ እና አቶ ይቁም በቀለ | 42691 | ቅጽ 10 | የስጦታ ውል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ 10 (አስር) ዓመታት ውስጥ ለአፈፃፀም ያልቀረበ እንደሆነ በይርጋ ይታገዳል።<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1676(1)፣ 1845 |
| 13 | መሐዳ ይመር እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | 55229 | ቅጽ 12 | አንድን እቃ በውል የተረከበ ሰው የተረከበው እቃ ጉድለት አለበት በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ በአንድ አመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል። የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2291፣ 2292፣ 2298(1) |
| 14 | ኡመር ከድር እና በዳዳ ሰቦቃ | 48012 | ቅጽ 12 | በፍ/ብ/ህ/ቁ 1810 (2) ላይ የተመለከተው የይርጋ ገደብ ተፈጻሚ የሚሆነው ዉሉ በፈቃድ ጉድለት ወይም በችሎታ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | ማጣት የተነሳ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1810 (2) |
| 15 | እነ ንግስት ኪዳኔ እና በለጠ ወልደሰማያት | 67376 | ቅጽ 13 | ውክይ የሆነ ወገን በተወካይ አማካኝነት የተደረገን ህገ ወጥ ውል እንዲፈርስ በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ በ አስር አመት ይርጋ ይታገዳል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2187፣ 2198፣ 1810፣ 1808 (1)፣ 1845 |
| 16 | ጀማል አማን እና ተዋበች ፈረደ | 62291 | ቅጽ 13 | በወለድ አገድ ውል (contract of Antichresis) አንድ ባለእዳ ግዴታውን ለመፈጸም ማረጋገጫ በማድረግ ለገንዘብ ጠያቂው የእርሻ መሬቱን ለማስረከብ የሚዋዋለው ውል ህገ ወጥ ስለሆነ የይርጋ ደንብ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40 (3)(4)፣ አወጅ ቁጥር 456/97 |
| 17 | አቶ ሽለማ ነገሰ እና ፈይሳ መንግስቱ | 69302 | ቅጽ 13 | መሬት ላይ ያሉትን ዛፎች በውል የሸጠ ሰው መሬቱ እንዲለቀቅለት በ ፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 መሰረት በ 10 አመት ጊዜ ውስጥ ክስ ካላቀረበ መብቱ በይርጋ ይታገዳል፡፡ |
| 18 | የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ድርጅት እና ባርጉባ ትሬዲንግ | 80642 | ቅጽ 14 | በባህር ላይ የሚደረግ የማጓጓዣ ውልን አስመልክቶ አጓዡ ለውሉ ምክንያት የሆነው ንብረት ጋር በተያያዘ የሚያቀርበው አቤቱታ እቃውን ከተረከበበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በስተቀር በይርጋ ይታገዳል፡፡ የባህር ህግ ቁ. 146፣ 203. የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1826፣1828፣1829 (ሀ). |
| 19 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ጥጋቡ ተፈራ | 78444 | ቅጽ 14 | የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሰጠው ብድር በመያዣ የያዘ ባንክ በማያዣው ላይ ያለው መብት በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት የመያዣ ውሉ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ አስር አመት ከማለፉ በፊት የመያዣ መብቱን መገልገል ያልጀመረ እንደሆነ ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058 (1) (3) |
| 20 | አብደላ ኢብራሂም እና ኡሶ አብዲ | 79394 | ቅጽ 14 | የውሉ መሰረታዊ አላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነው ውል በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈጻሚነት የለውም በማለት ለመወሰን የሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡ አዋጅ ቁጥር 130/99፣ አዋጅ ቁጥር 89/89- አንቀጽ 2 (3)፣ አዋጅ ቁጥር 456/97- አንቀጽ 8 (2). |
| 21 | አንበሳ ኢንሹራንስ | 98358 | ቅጽ 17 | የባህር ላይ የእቃ ማጓጓዝ ውልን በተመለከተ የዕቃው ርክክብ ከተፈፀመበት ወይም የማስረከቡ ጉዳይ ሳይፈፀም ቀርቶ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ኩባንያ እና የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጂስቲክ አገልግሎት | | | እንደሆነ እቃውን ማስረከብ ከሚገባበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ውስጥ ክስ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል። የባህር ህግ ቁጥር 203፤180፤162 |

## 4.2. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ የይርጋ ደንቦች

የኢፌዴሪ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/88 አንቀጽ 162 ስንመለከት አንድ በህገ ወጥ መንገድ ከስራ የተሰናበተ ሰው በዚህ መሠረት ወደ ስራው እንዲመለስ ለመጠየቅ የሚችለው ስራው ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልጠየቀ በይርጋ መብቱን ያጣል። ከህገ ወጥ ስንብቱ ጋር ተያይዞ ለሚነሱ የካሣ ክፍያዎች እና ሌሎች ተያያዥ የክፍያ ጥያቄዎችን ለማግኘት በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄዎቹ ለፍርድ ቤት መቅረብ አለባቸው። ከነዚህ ከላይ ከተገለጹት ውጪ የሆኑ ከስራ ውል ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ለማቅረብ ደግሞ የሥራ ውል ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት። የደሞዝ፣የትርፍ ሰአትና የሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ ክፍያው በተቋረጠ በስድስት ወር ውስጥ መቅረብ አለበት። የሥራ ውል በመቋረጡ የተነሳ በሠራተኛውም ሆነ በአሠሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ የሥራ ውሉ በተቋረጠ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት። ከላይ ከተገለፁት ምክንያቶች ውጪ ሌሎች ከቅጥር ውል ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ማቅረብ የሚቻለው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው። ከዚህ በተረፈም በዚህ ጠቅላላ ደንብ ያልተሸፈነ ጉዳይ ሲያጋጥም አግባብ ያለው ህግ በማሟያነት እንደሚያገለግል ተደንግጓል። ስለሆነም በፍትሐብሄር ጉዳይ የፍትሐብሄር ህግ ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነው።

በአሠሪና ሠራተኛ ህግ የተቀመጡት የይርጋ ደንቦች ከሌሎች ህጎች አንጻር ሲታዩ የጊዜ ገደባቸው አጭር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ይህ የሆነበት ምክንያት የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት በባህሪው ጥንቃቄን የሚሻ፣ የኢንዱስትሪውን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ አለመግባባቶች ተንጠልጥለው ሳይቆዩ በአፋጣኝ መፍትሔ እንዲያገኙ ለማድረግ ነው። በአዋጅ ቁጥር 377/88 መግቢያ ላይ የተቀመጡት "…. የኢንዱስትሪ ሰላምን በመፍጠር… በመተባበር በጋራ እንዲሠሩ ማድረግ ጠቃሚ በመሆኑ… የሥራ ክርክር በተቀላጠፈ መንገድ መፍትሔ

እንዲያገኝ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ...” የሚሉት ሐረጐች የሚጠቁሙትም ይህንኑ ነው። ስለሆነም የይርጋ ጊዜን የተመለከቱት ድንጋጌዎች ከዚህ አጠቃላይ መንፈስ አንፃር መታየት ይገባቸዋል።

በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 163 ላይ እንደተገለፀው በአዋጁ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በቀር የአንድ መብት የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ ለመጠቀም ከሚቻልበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ መሆኑ ተደንግጓል። በምሳሌ ለመግለጽ ያህል አንድ ሠራተኛ ከሥራ የተሰናበተበት ዕለት ጥር 16 ቀን 2000 ዓ.ም ቢሆን ያላግባብ ከስራ ተሰናብቻለሁና ወደ ሥራ ልመለስ ቢል በዚህ መብቱ መጠቀም የሚችለው ከሥራ ስለመሰናበቱ በደብዳቤ ከተገለጸለት ዕለት ጀምሮ ነው። የይርጋ ጊዜው መታሰብ የሚጀምረው ግን በመብቱ ለመጠቀም ከሚችልበት ደብዳቤ ከደረሰው ዕለት ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ይሆናል ማለት ነው። ይህ ቀን ጥር 17 ቀን 2000 ዓ.ም ነው። ጥር 17 ቀን 2000 ዓ.ም የዋለው ሥራ በማይሠራበት የበዓል ዕለት ቢሆን እንኳ አቆጣጠሩን ከመጀመር አንፃር የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም። ነገር ግን የይርጋውን መቆጠር ማብቂያ ጊዜ ከማስላት አኳያ የመጨረሻው ዕለት ሥራ በማይሠራበት ዕለት ከዋለ ሥራ የሚሠራበት ተከታዩ ቀን የመጨረሻ ማብቂያው ጊዜ እንደሆነ ይታሰባል። የወንጀል ጉዳይ ግን የይርጋው ጊዜ መታሰብ የሚጀምረው ጥፋተኛው የወንጀል ድርጊቱን ከፈፀመበት ቀን ጀምሮ ነው። ይህም ሲሆን ጥፋቱ እየተደጋገመ የተፈፀመ እንደሆነ የወንጀሉ ድርጊት መፈፀም ካቆመበት ጊዜ ጀምሮ የይርጋው ጊዜ መታሰብ ይጀምራል።

ከዚህ በመቀጠል በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ የይርጋ ገደቦችን ሊያቋርጡ የሚችሉ ምክንያቶች እንመለከታለን። በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 164(1) መሰረት ጉዳዩ የሥራ ክርክርን ለሚወስን ባለስልጣን ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥበት ቀን ድረስ ያለው ጊዜ የይርጋ ማቋረጫ ምክንያት ይሆናል። የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅን በስራ ላይ ለማዋልና ለማስፈፀም ኃላፊነት ለተሰጠው ባለስልጣን አቤቱታ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ በጽሁፍ እስኪሰጥበት ቀን ድረስ ያለው ጊዜም ይርጋን የሚያቋርጥ ምክንያት ነው። (አንቀጽ 164(2))። የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅን በስራ ላይ ለማዋልና ለማስፈፀም ኃላፊነት የተሰጠው ባለስልጣን ማነው ብለን ስንጠይቅ በአዋጁ አንቀጽ 12(6)፣ 20፣ 21፣ 89፣ 138(መ)፣ 178፣ 179 መሰረት ከዳኝነት ሰጭነት ሀላፊነት በተጨማሪ አስተዳደራዊ በሆነው ነገር ላይም አዋጁን የሚያስፈጽሙት አካላት ባለስልጣን ሊባሉ ይችላሉ። የይርጋ ጊዜ መቋረጥ የሚያስከትለው ውጤት በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ ላይ አልተገለፀም። ነገር ግን በአዋጁ ድንጋጌዎች ላይ ባልተሸፈነ የይርጋ ጉዳይ

አግባብ ያለው ህግ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው በአንቀጽ 162(5) ላይ የተገለፀ በመሆኑ ለዚሁ ጉዳይ አግባብነት ያለውን የፍትሐብሔር ህግ በማሟያነት ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ በመቀጠል ሰበር ሰሚ ችሎት በአሰሪና ሰራተኛ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች በሰንጠረዥ መልክ እንመለከታለን፡፡

## ሰንጠረዥ 2. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአሰሪና ሰራተኛ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አንለይ ያየህ /27 ሰዎች/ | 16648 | ቅጽ 3 | • የሰራተኛው ወይም የአሰሪው ጥያቄ በተተኪዎቻቸው ወይም በወራሾቻቸው በሚቀርብበት ጊዜ በአዋጅ 377/96/ አንቀጽ 162/3/ እና 162/3/ ስር በተቀመጡት የይርጋ ድንጋጌዎች ይመራል፡፡<br>• የሰራተኛው ወይም የአሰሪው ተተኪዎች ወይም ወራሾች የሰራተኛውን ወይም የአሰሪውን ሳይሆን የራሳቸውን መብት መሰረት በማድረግ የሚያቀርቡት ጥያቄ በአዋጅ ቁ./377/96/ አንቀጽ 162/3/ እና 162/4/ በተደነገጉት ሳይሆን በአንቀጽ 162/1/ በተደነገገው የይርጋ ድንጋጌ ይመራል፡፡<br>• በአዋጅ ቁ./377/96/ አንቀጽ 164/1/ መሰረት የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚቆመው ክሱ በአዋጅ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን በተሰጠው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ወይም በፍርድ ቤቶች በተቋቋሙ የስራ ክርክር ችሎቶች የቀረበ እንደሆነ ነው፡፡<br>• ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ባልተሰጠው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ወይም በስራ ክርክር ችሎት የቀረበ ክስ በአዋጅ ቁ. /377/96/ አንቀጽ 164/1/ መሰረት የይርጋ ጊዜን መቆጠር አያቋርጥም፡፡ በአዋጅ ቁ. 377/96/ አንቀጽ 164/2/ መሰረት የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚቋረጠው አቤቱታው የቀረበው ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ለአሰሪ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | የቀረበ አቤቱታ በአዋጅ ቁ. 377/96) አንቀጽ 164(2) መሰረት የይርጋ ጊዜ መቆጠርን አያቋርጥም፡፡ |
| 2. | የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እና አቶ መሀመድ አደን | 37573 | ቅጽ 8 | ከሥራ ጋር በተገናኘ በሚፈፀም ድርጊት መነሻነት በሠራተኛው ላይ በፖሊስ የሚደረግ ምርመራ የይርጋ ጊዜን አያቋርጥም፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/2/ |
| 3. | ጉደር አግሮ ኢንደስትሪ እና አቶ በለጠ ጫላ | 45746 | ቅጽ 9 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪ ሠራተኛው የፈፀመውን ድርጊት መሠረት አድርጎ ለማሰናበት የሚችለው የሥራ ውለን ለማቋረጥ ምክንያት የሆነው ነገር መከሰቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ ሰላሳ ቀናት ውስጥ ነው፡፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3) |
| 4. | ኤርፖርቶች ድርጅትና ሶፋኒት | 51912 | ቅጽ 9 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚነሣው የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚሰላው የሥራ ቀናትን ብቻ በማስላት አይደለም፡፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 163(2) |
| 5. | ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አማረ ገላው | 36730 | ቅጽ 9 | ስልጣን ለሌለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብና ክርክር ማካሄድ የይርጋ ጊዜን ያቋርጣል፡፡( ከዚህ ቀደም የሰበር ችሎቱ በተቃራኒው የሰጠው የህግ ትርጉም ተለውጧል)፡፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 138፣ 147፣ 164(1) |
| 6. | ጉልላት ወልዴ እና ጅምላ ሸቀጦች ድርጅት | 63635 | ቅጽ 11 | በአሰሪና ሰራተኛ ክርክር አሰሪው ሰራተኛው የሚጠይቀውን የገንዘብ ክፍያ በማመን የጻፈው ደብዳቤ ሰራተኛው መብቱን ለማስከበር በሚያቀርበው የክፍያ ጥያቄ ላይ የሚቆጠረውን ይርጋ ያቋርጣል፡፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 164(3)፣ ፍ/ብ/ህግ ቁ. 1852(1). |
| 7. | ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና በዳሶ መልካቶ | 53527 | ቅጽ 11 | በአሰሪና ሰራተኛ ክርክር በፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድ እንዲፈጸም የሚቀርብ አቤቱታ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በ አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡ |
| 8 | ኢትዮጵያ የርቀት ትምህርት ኮሌጅና ዶ/ር ደግለኝ ተመስገን | 96458 | ቅጽ 16 | የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሰራተኛውም ሆነ በአሰሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ ሥራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ይታገዳል፡፡ የጳጉሜ ቀናት በይርጋ ቀናት ሊካተቱ አይገባም፡፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162(4)፣የፍ/ሕ/ቁ. 1860(3) |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 9 | አቶ ዳዊት ገ/ማርያም ና ሣህለማርያም ደግፌ | 101020 | ቅጽ 17 | በሠራተኛው የሚጠየቅ የውዝፍ ደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በአሠሪው የይርጋ መቃወሚያ ካልቀረበበት በስተቀር ለሰራኛው ሊከፈል ይገባል፡፡ |

### 4.3. የውርስ ህግ የይርጋ ደንቦች

ውርስን በተመለከተ የተለያዩ የጊዜ ገደቦች ተደንግገዋል፡፡ የኑዛዜን መፍረስ የሚፈልጉ ወገኖች ይህን መብት የሚጠቀሙት ኑዛዜው ከተነበበ ወይም መነበቡን ካወቁና ተቃውሚቸውን በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለውርስ አጣሪው ከገለፁ በኋላ ባሉት ቀጣይ ሶስት ወራት ውስጥ እንደሆነና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ግን ከአምስት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን ማቅረብ እንዳለባቸው የፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥሮች 973 እና 974 ያስገነዝባሉ፡፡ ያለአግባብ የውርስ ንብረት ከያዘ ሰው ላይ ንብረት ለማስመለስ የፈለገ ከሳሽ የውርሱ ንብረቶች በተከሳሹ መያዛቸውን ባወቀ በ ሶስት አመት ጊዜ ውስጥ ክሱን ማቅረብ እንደሚገባው በፍትሐብሔር ህጉ ቁጥር 1000 (1)ላይ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል ከሳሹ ይህን ጉዳይ አወቀም አላወቀ ከሳሹ መብቱን መጠቀም ከቻለበት ወይም ሚቹ ከሞተበት ጊዜ አንስቶ አስራ አምስት አመት ካለፈ የውርስ ንብረት ለማስመለስ ክስ ማቅረብ እንደማይቻል የዚሁ ህግ ቁጥር ቁጥር 1000 (2) ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሰበር ሰሚ ችሎት በውርስ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች (ትርጉሞች) በሰንጠረዥ መልክ እንመለከታለን፡፡

**<u>ሰንጠረዥ 3</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውርስ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች**

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | እነ የሻረግ መንግስት እና የሻረግ ፈረደ | 15631 | ቅጽ 3 | ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ባለይዞታ በመሆን የ ቤቱን ግብር ባለማቋረጥ ከ15 ዓመት በላይ በሥሙ ሲከፍል የቆየ ሰው በሕጉ የዚሁ ሀብት ባለቤት ይሆናል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ ቁ. 1001/2/፣ 1168፣1845፣ 1853 |
| 2. | የገነት ዳምጤ | 38152 | ቅጽ 8 | በኑዛዜ የተገኘ ንብረት በ10 (አሥር) አመት ጊዜ ውስጥ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ወራሾች እና እነ አቶ ይልማ አስፋው | | | ካልተጠየቀ በስተቀር በይርጋ ይታገዳል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ- 1677(1)፣ 1000፣ 1845 |
| 3. | ተስፊዬ ሞላ እና እነ እሸቱ ምነ | 40418 | ቅጽ 10 | የውርስ ሀብትድርሻ ክፍፍል ጥያቄ መብት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በ አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልታወቀ ሚች ከሞተበት ቀን ጀምሮ በ አስር አመት ይርጋ ይታገዳል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080(3) |
| 4. | እነ ወ/ሮ ጽጌ ወልደ መስቀል እና አቶ ስዩም ክፍሌ | 38533 | ቅጽ 10 | የወራሽነት መብትን በህግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ ይችላሉ፡፡<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996፣ 1000(1)፣ 1000(2)፣1060፣1062 |
| 5. | እነ ፀሀይ ሀይሌ (አራት ሰዎች) እና ወ/ሮ ፈለቃ ቤኛ | 44025 | ቅጽ 10 | ከውርስ ሃብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የውርስ ሃብቱን በእጁ አድርጎ በመገልገል ላይ ያለ ተከራካሪ የሆነ ወራሽ የክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት በጋራ ይዞ የቆየ ሰው ላይ የሚያነሳው የውርስ ጥያቄ በይርጋ አይታገድም፡፡ |
| 6. | እነ በላቸው አስፋው እና መኪያ አወል | 47201 | ቅጽ 11 | ወራሽ የሆነ ሰው ወራሽ ባልሆነ ሰው ላይ ንብረቱ ይለቀቅልኝ በሚል በሚያቀርበው ክስ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ይርጋ የሚቆጠረው ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን ንብረቱ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ |
| 7. | ቀለሚ ወርቅነህ እና ሻምበል ጌታሁን | 49359 | ቅጽ 11 | የውርስ ሀብትን አስመልክቶ በሚቀርብ ክስ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1851(ለ) መሰረት ሊቋረጥ ይችላል፡፡ |
| 8 | እነ ሀዲስ አ/ስላሴ እና ብሌን አ/ስላሴ | 53223 | ቅጽ 11 | በኑዛዜ ላይ የሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ ኑዛዜው መከፈቱን ያወቁ በ አስራ አምስት ቀን ውስጥ ያላወቁ ደግሞ ኑዛዜው ከተከፈተበት ወይም ሚች ከሞተበት ቀን ጀምሮ በ አምስት አመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡<br>በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 973፣ 974 |
| 9 | ሀና ጸጋየ እና ጣእሙ ደስታ | 57114 | ቅጽ 11 | የውርስ ሀብት ወራሽ የሆነና አካለ መጠን ያላደረሰ ሰው ላይ የይርጋ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው አካለ መጠን ከደረሰበት ወይም በመብቱ መጠቀም ከቻለበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1845 |
| 10 | ውለታ ደስታና እቴቴ ደስታ | 52407 | ቅጽ 11 | የውርስ ሀብት ይጣራልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በ ሶስት አመት ይርጋ ይታገዳል፡፡የውርስ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ንብረቱ በእጅ ከተያዘበት ጊዜ እንጂ ስመ ንብረቱ ከተዛወረበት ጊዜ ጀምሮ አይደለም፡፡ |

## 4.4የፍታብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ የይርጋ ደንቦች

በፍትሐብሔር ስነ -ስርዓት ህግ ውስጥ መብት ሊያሳጡ የሚችሉ የይርጋ ደንቦች ተካተዋል። በፍትሀብሄር ጉዳይ ላይ ፍርድ ወይም ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የሚቀርብ ይግባኝ በ60 ቀናት ውስጥ መቅረብ እንዳለበት የፍትሐ ብሔር ስነስርዓት ህግ አንቀጽ 323(2) ይገልፃል። ነግር ግን ሌሎች ህጎች የደነገጉት የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ካለ የፍታብሄር ስነ ስርአት ህጉ የደነገገው የ 60 ቀን የጊዜ ገደብ ተፈጻሚ አይሆንም። ለምሳሌ ስለ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በወጣው አዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት በማንኛውም የስራ ክርክር የቋሚ ወይም የጊዜአዊ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ የሚችለው የቦርዱ ውሳኔ በይፋ ከተነበበ ወይም ለተከራካሪ ወገኖች ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ብቻ መሆን አለበት። በሌላ በኩል መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሰበር እንዲታረም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚገባው የሰበር ጥያቄ በሚቀርብበት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ በዘጠና ቀናት ውስጥ ነው።[40] ለቃል ክርክር ፍርድ ቤቱ ይዞት በነበረ ቀጠሮ በመቅረቱ የተነሳ መዝገቡ የተዘጋበት ከሳሽ አሳማኝ ምክንያት አቅርቦ መዝገቡን ማስከፈት የሚችለው መዝገቡ ከተዘጋበት ጊዜ ጀምሮ በ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ በፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 74(2) ላይ ተደንግጓል።

ይርጋ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ስለመሆኑ የፍታብሄር ስነ ስርአት ህግ አንቀጽ 244(ረ) ይደነግጋል። በኢትዮጵያ የፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 49 መሰረት በፍታብሄር ክርክር ከሳሽ ክርክሩ ሳይጠናቀቅ ከሞተ የክሱ መብት በህጉ አግባብ ለሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችለው ክሱን ለመቀጠል መብት አለኝ የሚል ወገን ከሳሹ በሞተ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ክሱን ለመቀጠል እንዲፈቀድለት ለፍርድ ቤት ካመለከተ ብቻ ነው።[41] የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 49(1) ከሣሽ ሲሞት የክሱ መብት ለሌላ የሚተላለፍ የሆነ እንደሆነ የሟቹ ንብረት አስተዳዳሪ ተተክቶ ክሱን ሊቀጥል እንደሚችል የሚፈቅድ ሲሆን የዚሁ ቁጥር ንኡስ ቁጥር ሁለት ክሱን ለመቀጠል መብት አለን የሚሉት ወገኖች ዋናው ከሣሽ ወይም ከሣሾች በሞቱ በአንድ ዓመት ውስጥ ክሱን ለመቀጠል እንዲፈቀድላቸው ሳያመለክቱ የቀሩ እንደሆነ የተጀመረው ክርክር ውድቅ ይሆናል በማለት ይደነግጋል። በሌላ በኩል በፍትሀብሔር ሥነ-

[40] የኢ.ፌ. ዲ. ሪ. ፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 25/88፣ ሁለተኛ አመት፣ ቁጥር 13፣ አንቀጽ 22(4)

[41] በኢትዮጵያ የፍታብሄር ስነ-ስርአት ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 52/58፣ አንቀጽ 49(1) እና (2)

ሥርዓት ሕግ ቁጥር 232(1) መሰረት ለፍርድ ቤቱ ያቀረበው ክስ ፎርማሊቲ አላሟላም በሚል ምክንያት በፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ውድቅ የተደረገበት ከሳሽ ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ክሱ ተቀባይነት ካጣበት ቀን ጀምሮ ለፍርድ ቤቱ በ 5 (አምስት) ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይጠበቅበታል።

የፍትሀብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ የሙግትን ሂደት ለመከታተል የሚያስችሉ የተለያዩ የጊዜ ገደቦችን አስቀምጧል። ይኸው ሕግ ያስቀመጣቸውን የጊዜ ገደቦች አፈጻጸም በሚመለከትም በሥነሥርዓት ሕጉ ምእራፍ ሰባት በርካታ ድንጋጌዎችን አሉ። የሕጉ ቁጥር 192 በአንድ ክርክር ላይ መፈፀም ወይም መደረግ የሚገባው ነገር ሲኖርና ይህም የሚፈፀምበት ጊዜ በሕግ ያልተወሰነ ሲሆን የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚመለከት ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የሚታየውን ጊዜ ይወስናል በማለት ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌ በሙግት ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት በሕግ በተቀመጠው ወይም ፍርድ ቤቱ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወን የሚጠበቅባቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው። የዚሁ ሕግ ቁጥር 195 አንድ ነገር እንዲፈፀም ከተወሰነው ጊዜ በኋላ ቢፈፀምም እንዳልተፈፀመ ሆኖ ይቆጠራል በማለት በተወሰነ የጊዜ ገደብ መፈፀም ያለባቸው ተግባራት ሕጉ ወይም ፍ/ቤቱ ባስቀመጠው ጊዜ ውስጥ ከተከናወኑ ብቻ ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ይደነግጋል። የሥነ ሥርዓት ሕጎች ዋነኛ ዓላማ ለፍ/ቤት የሚቀርቡ ክርክሮች ባነሰ ወጪ በተቀላጠፈና ፍትሃዊ በሆነ ሥርዓት እልባት እንዲያገኙ ማድረግ ነው።[42] በመሆኑም በሥነ-ሥርዓት ህጎች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች አፈጻጸም በአንድ ጉዳይ ካሉት ተከራካሪዎች ባሻገር የሌሎች ተከራካሪዎችን ጥቅም፣ በፍርድ ቤት መኖር ያለበትን የሙግት አመራርና አጠቃላይ የሀብትና የጊዜ አጠቃቀምን የሚመለከቱ ናቸው።

የጊዜ ገደቦች አለመከበር ለመዘግየት፣ ለጉዳዮች መከማቸትና መጨናነቅ ምክንያትም ስለሚሆን የሚጎዳው በአንድ ሙግት የሚሳተፉትን ብቻ ሳይሆን የሌሎች የፍርድ ቤት ተጠቃሚዎች መብትና ጥቅምም ይነካል። ይህ ሁኔታ እንዳይፈጠር የሙግት ሂደት ሥርዓት እንዲይዝ ማድረግ ደግሞ ከተከራካሪዎችም የሚጠበቅ ቢሆንም በዋናነት ግን የፍርድ ቤቱ ሃላፊነት ነው። ይህን ሃላፊነት እንዲወጣ ከሚያደርጉት መንገዶች አንዱ ደግሞ በስነ ሥርዓት ሕጉ የሰፈሩት የጊዜ ገደቦች በአግባቡ መፈፀማቸውን መከታተልና ያልተፈፀሙ ሆነው ሲገኙ ደግሞ ህጉ እንደሚያዘው ተመጣጣኝ የሆነ ርምጃ መውሰድ ነው።

[42] ዝኒ ከማሁ መግቢያውን ይመልከቱ

በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የሰፈሩ ጊዜን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ ይርጋን አስመልክቶ በፍትሀብሄር ሕግ ቁጥር 1856/2/ ከሰፈረውና የይርጋ ጉዳይ በተከራካሪዎች ካልተነሣ በፍርድ ቤት አይነሳም ከሚለው ሕግ የተለየ ነው። በፍትሐብሔር ሕግ የሰፈረው የይርጋ ሕግ ዋነኛ ዓላማ የተዋዋዮችን ጥቅም መጠበቅ ነው። የዚህ መብት ተጠቃሚ የሆነ ተከሣሽ ይርጋውን ካላነሣም የሚጎዳው እሱ ብቻ ነው። ስለሆነም ተከራካሪ ወገን የተወውን መብት ፍርድ ቤት በራሱ አነሣሽነት እንዲያነሣው አይፈቀድም። በሥነሥርዓት ሕጉ የተቀመጡ የጊዜ ገደቦች መከበር አለመከበራቸውን ግን ፍርድ ቤቱ የመከታተል ሃላፊነት አለበት። በተከራካሪ ወገን ባይነሣ ቢቀር እንኳን በሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 195 እንደተደነገገው ጊዜው ካለፈ በኋላ የተከናወነው ነገር ሁሉ እንዳልተፈፀመ ሆኖ ስለሚቆጠር የሥነ-ሥርዓት የጊዜ ገደቦች ተሟጋቾችን ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱንም ጭምር የሚመለከቱ ናቸው። በመሆኑም በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በግልጽ የሰፈረው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የሚቀርብን ማንኛውንም ጉዳይ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረጉ ትክክለኛው አካሄድ መሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጠቁሟል።[43] በመቀጠል ሰበር ሰሚ ችሎቱ ፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች (ትርጉሞች) ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ እንመለከታለን።

## ሰንጠረዥ 4. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፍታብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ጋዲሴ አርጌ እና ወ/ሮ ወርቅአንጥፉ በቀለ | 17361 | ቅጽ 1 | በሥረ ነገር /Substantive/ ህጎች የተደነገጉ የይርጋ ደንቦች በሥነ ሥርዓት ሕጎች ከተደነገጉት የጊዜ ገደቦች የተለዩ ናቸው። በስነ ስርዓት ህጎች በግልጽ የሰፈረን ጊዜ ሳይጠብቅ የሚቀርብን ጥያቄ ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ አለበት። ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 49፣ ፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1856 |
| 2. | በዛብህ አበበ እና የመንግስት | 35018 | ቅጽ 8 | የፍርድ ባለመብት ባለመቅረቡ ምክንያት የተዘጋ የአፈፃፀም መዝገብ ፍርዱ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በ 10 (አሥር) አመት |

[43] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 1፣ መዝገብ ቁጥር- 17361፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 1997፣ ገጽ 12

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ቤቶች ኤጀንሲ | | | ይርጋ ካልታገደ በስተቀር ባለ መብቱ አፈጻጸሙን ማንቀሳቀስ ይችላል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 384 |
| 3. | ሽመልስ አማረ እና አማረ መኮንን | 76601 | ቅጽ 13 | በ ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሰረት በሌለሁበት የተሰጠ ፍርድ ይነሳልኝ በሚል ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በህጉ የተመለከተው የ አንድ ወር የጊዜ ገደብ በፍታብሄር ህጉ የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ስሌት መሰረት መሰላት ይኖርበታል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 78፣ 195 የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1848፣ 1856(2) |
| 4 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ ፈቃዱ ተስፋየ | 74898 | ቅጽ 13 | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 384 ስር የተመለከተው የ 10 አመት ይርጋ ገደብ የፍርድ ባለመብት ምንም እንቅስቃሴ ሳያደርግ ቆይቶ ፍርዱን ለማስፈጸም ሲንቀሳቀስ ተፈጻሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡ |
| 5. | ቄስ ዳንኤል አርኬ እና የኮልፌ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ | 87190 | ቅጽ 15 | በፍ/ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የተመለከተው 60 ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ታሳቢ የሚያደርገው እና ተፈፃሚ የሚሆነው ተከራካሪ ወገኖች ባሉበት ውሣኔ መሰጠቱን ወይም ለውሣኔ የሚያበቃ ክርክር የተደረገ መሆኑን ተረድተው ቀርበው ለመከታተልና የዳኝነቱን ውጤት ለመስማትና ለማወቅ ያልፈለጉትን ወይም ደግሞ የተከራካሪዎችን የመደመጥ መብት ማክበር ይቻል ዘንድ በህጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በአግባቡ ጥሪ ተደርጉላቸው በጥሪው መሠረት ክርክራቸውን በአግባቡ ለመምራት ባልቻሉ ወገኖች ላይ ብቻ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 323(2) |
| 6 | እነ ወ/ሮ አለዊያ ዑመር እና አቶ ሐሺም ሁሴን | 90361 | ቅጽ 16 | በሕግ ተለይቶ የተወሰነ የይርጋ ጊዜ የመቋረጥ እና ያለመቋረጥ ጉዳይ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ ሊነሳ የሚችለው የይርጋውን መቆጠር ያቋርጠዋል የተባለው ምክንያት የተከሰተው የይርጋው ጊዜ ከመሙላቱ በፊት በሆነ ጊዜ እንጂ የይርጋው ጊዜ የሞላ ወይም ያለፈ በሆነ ጊዜ ጭምር አይደለም ። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 1851 |

## 4.5የንብረት ህግ የይርጋ ደንቦች

በንብረት ህግ ውስጥ የተለያዩ አይነት የይርጋ ደንቦች አሉ፡፡ ይዞታው የተወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የተፈጠረበት ሰው ንብረቱ ይመለስልኝ ወይም ሁከቱ ይወገድልኝ ብሎ የሚያቀርበው ክስ ወይም አቤቱታ በሁለት ዓመት ይርጋ የተገደበ መሆኑ በፍትሐብሔር ህግ 1149(2) ተገልጿል፡፡ ሌላው ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለ እጅ ሆኖ ከንብረቱ የሚፈለገውን

ግብር ለ 15 (አስራ አምስት) ተከታታይ አመታት የገበረ ሰው የንብረቱ ባለቤት የሚሆንበትን አጋጣሚ የሚገልጸው ፍታብሀር ህግ ቁጥር 1168 ነው። በተጨማሪም በዚሁ ህግ ቁጥር 1192 መሰረት ግዙፍነት ያለው የሚንቀሳቀስ ንብረት ባለ ሀብት የሆነ ሰው ሀብቱ የሚገኝበትን ቦታ ወይም ሀብቱ መሆኑን ባለማወቅ አስር አመት ያልተገለገለበት እንደሆነ መብቱን በይርጋ ምክንያት ያጣል።

በሌላ በኩል የንብረት ህግ ውስጥ ይርጋን በተመለከተ የሚነሳው አከራካሪ ነጥብ በፍራብሄር ህግ ቁጥር 1206 ድንጋጌ ስር አንድ ከሳሽ የቤቱ ባለሀብት በመሆኑ በህገ ወጥ መንገድ ቤቱን ይዞበት የሚገኘውን ተከሳሽ በፍርድ ኃይል እንዲለቅ እንዲደረግለት የሚያቀርበው የመፋለም ክስ (petitory action) ይመለከታል። በዚሁ ጉዳይ ላይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 10፣ መዝገብ ቁጥር 43600[44] ላይ በሰጠው ውሳኔ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ነው (ቀሪ ሆኗል) ሊባል አይችልም የሚል የህግ ትርጉም ሰጥቷል። ነግር ግን የተለያዩ የህግ ምሁራን በዚሁ ጉዳይ ላይ የልዩነት ሀሳባቸውን አቅርበዋል። ለአብነት ያህል ዶክተር ብሩክ ሀይሌ[45] በዚሁ ጉዳይ ላይ በጻፉት ጽሁፍ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1845 ድንጋጌ ስር የተመለከተው የ 10 አመት የይርጋ ድንጋጌ የማይንቀሳቀስ ንብረት በፍርድ ኃይል እንዲለቅ እንዲደረግለት ከሳሽ ለሚያቀርበው የመፋለም ክስ ተፈጻሚ መሆን ይገባዋል በማለት ይከራከራሉ። እንደ ምክንያት የሚጠቅሱትም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1) መሰረት ግዴታዎች ከውል ባይመነጩም እንኳን የውል ደንቦች ተፈጻሚ ሊደረጉ ስለሚችሉ አንቀጽ 1845 የንብረት ክርክሮችንም በተመለከተ ተፈጻሚ መሆን ይችላል የሚል ነው። በመቀጠል ደግሞ ሰበር ሰሚ ችሎት በንብረት ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች (ትርጉሞች) ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ እንመለከታለን።

## <u>ሰንጠረዥ 5</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በንብረት ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች

[44] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 10፣ መዝገብ ቁጥር- 43600፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2003፣ ገጽ 225-229

[45] Biruk Haile, Period of Limitation Applicable to Claims over Immovable Property under the Ethiopian Law: Gateway to Hindsight Scrutiny of Legality of Nationalization of Immovables? Case Analysis Jimma University Journal of Law, Vol. 4 No. 1 (2012), page 183

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ዲዊት መስፍን ና የመንግስት ቤቶች | 43600 | ቅጽ 10 | የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ነው (ቀሪ ሆኗል) ሊባል አይችልም፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1677፣ 1845፣ 1206፣ 1188-1192 |
| 2. | ወ/ሮ ገብርኤሊ ኒካለ ቶማስ ናክሶ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | 48048 | ቅጽ 10 | አንድን ንብረት በአደራ ለማስተዳደር (ለመጠበቅ) የተረከበ ወገን አደራ ሰጪው ንብረቱ እንዲመለስ በጠየቀው ጊዜ ወዲያውኑ መመለስ አለበት፡፡<br>ንብረትን በአደራ የሰጠ ወገን ንብረቱ እንዲመለስለት ከመጠየቅ ጋር በተያያዘ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ (ይርጋ)የለም፡፡<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2781 (1)(2)፣ 2779፣ 2989(1) |
| 3. | ሳሚኤል ታደሰ እና እጥፍ ወርቅ ሀ/ማርያም | 56011 | ቅጽ 11 | የኮንዶሚኒየም ቤት ባለሀብት የሆነ ሰው በራሱ ፈቃድ ቤቱን ለመሸጥ ለመለወጥ ወይም ለ 3ኛ ወገን ለማስተላለፍ የሚችለው ያለበትን የቤቱን ዋጋ አጠናቆ ከከፈለበት ጊዜ ጀምሮ አምስት አመት ካለፈ በኋላ ነው፡፡<br>አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀጽ 21፣ 14(2) |
| 4 | አዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክና አዱኛ አበሉ | 53749 | ቅጽ 11 | በስህተት ለጉምሩክ የተከፈለ ቀረጥ ተመላሽ የሚደረገው ስህተቱ መኖሩን ባለስልጣን መስሪያቤቱ ካወቀና እቃው የጉምሩክ ስነ ስርአት አጠናቆ ወደ አገር ከገባበት ወይም ካገር ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው ስድስት ውር ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 368/95- አንቀጽ 15 |
| 5. | ኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን እና ከበደ ወዳጆ | 59979 | ቅጽ 11 | በኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(8) መሰረት ለተወሰደ ንብረት የሚጠየቅ ካሳ በሁለት አመት ይርጋ አይታገድም፡፡ ፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1143 እና 2143 |
| 6. | አብዱ መሀመድ እና ዘበናይ ሀይሌ | 53328 | ቅጽ 11 | የይርጋ መርህ ክስን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ቀሪ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ የይርጋ መርህ ንብረትን በመያዝ ወይም ባለ ይዞታ በመሆን የባለ ሀብትነት መብት ከሚገኝበት መርህ ይለያል፡፡ ፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1168 |
| 7. | አቶ ክፍሉ ገ/ማርያም ና ወ/ሮ አስመረት መኮንን | 89148 | ቅጽ 16 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሠው ባለማቋረጥ ለ 15 ዓመታት ግብር በስሙ መክፈሉ ከተረጋገጠ የዚሁ ንብረት ባለቤት መሆን ይችላል፡፡ የፍ/ህ/ቁ 1168(1) |

## 4.6ከውል ውጭ ባለ ሀላፊነት ህግ የይርጋ ደንቦች

በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2143 መሰረት ከውል ውጭ ባለ ኃላፊነት ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ቢሆንም ጉዳዩ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ የወንጀሉ ይርጋ ዘመን ርዝመት ከሁለት ዓመት የበለጠ ከሆነ የካሳ ማቅረቢያው ጊዜ የወንጀሉን ይርጋ ጊዜ የሚተካ ይሆናል፡፡ ከላይ በተመለከተው ቁጥር መሰረት ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት ተፈጻሚ ከሚሆነው የይርጋ ጊዜ ጋር በተገናኘ ለደረሰው ጉዳት ምክንያት የሆነው ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣና ጥፋት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ አጥፊው በወንጀል ጉዳይ ክስ ያቀረበበትና ያልተቀጣ እንኳን ቢሆን በወንጀል ህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ከውል ውጭ ሀላፊነትን በተመለከተ ክሱ በጉዳት ካሣ ጥያቄ ላይ ያልተመሠረተ ከሆነ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2143/1/ በመጥቀስ የሚያቀርበው የይርጋ ክርክር ሊኖር አይችልም፡፡ ነገር ግን የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የቀረበው የይርጋ ድንጋጌ የሞት ጉዳትን ያካትታል፡፡ በመቀጠል ደግሞ ሰበር ሰሚ ችሎት ከውል ውጭ ባለ ሀላፊነት ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች (ትርጉሞች) ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ እናያለን፡፡

**<u>ሰንጠረዥ 6</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከውል ውጭ ባለ ሀላፊነት ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች**

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አረጋሽ ከበደ | 16062 | ቅጽ 3 | ከውል ውጭ ሀላፊነትን በተመለከተ ክሱ በጉዳት ካሣ ጥያቄ ላይ ያልተመሠረተ ከሆነ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2143/1/ በመጥቀስ የሚያቀርበው የይርጋ ክርክር ሊኖር አይችልም፡፡ |
| 2. | ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ፊጤ ዓለ. | 34544 | ቅጽ 9 | በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 ስር የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የቀረበው የይርጋ ድንጋጌ የሞት ጉዳትን ያካትታል፡፡ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3. | አለምነው አበበ እና ህብረት ኢንሹራንስ | 58920 | ቅጽ 11 | ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት ተፈጻሚ ከሚሆነው የይርጋ ጊዜ ጋር በተገናኘ ለደረሰው ጉዳት ምክንያት የሆነው ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣና ጥፋት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ አጥፊው በወንጀል ጉዳይ ክስ ያቀረበበትና ያልተቀጣ እንኳን ቢሆን በወንጀል ህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል። ፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 (1) (2) |

## 4.7የንግድ ህግ የይርጋ ደንቦች

በንግድ ህጎቻችን ውስጥ የተለያዩ አይነት የይርጋ ደንቦች አሉ። በንግድ ህጉ[46] አንቀጽ 807(2) መሰረት ተላላፊ ሰነዶችን በተመለከተ የሀዋላ ወረቀትን ለክፍያ እሽ ብሎ በተቀበለ ባለ እዳ ላይ የሚቀርቡ ክሶች የመክፈያ ቀን አልፎ በሶስት አመት ውስጥ ካልቀረቡ በይርጋ ይታገዳሉ። ሌላው ቸክን የተመለከተ የይርጋ ደንብ በዚሁ ህግ ቁጥር 881(1) የተገለጸ ሲሆን አምጭው የቸኩ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ክስ ካልመሰረተ በይርጋ ይታገዳል። በዚሁ ህግ ቁጥር 855 መሰረት ቸክ ለክፍያ የሚቀርበው ከተጻፈበት ቀን አንስቶ በሚከተሉት ስድስት ወራት ውስጥ ነው። ቸክ አምጭው በከፋዩ ላይ የሚያቀርበው ክስ የይርጋ ዘመን ሶስት አመት አንደሆነ በንግድ ህጉ ቁጥር 881(3) ተመልክቷል። የሀዋላ ወረቀት አምጭ በጀርባ ፈራሚወችና በአውጭው ላይ የሚያቀርበው ክስ በአንድ አመት ይርጋ እንዲሁም ፈራሚወች እርስ በርሳቸውና በአውጭው ላይ የሚያቀርቡት ክስ በ ስድስት ወር ይርጋ እንደሚታገድ በቁጥር 817(2) እና (3) ተመልክቷል። ሌላው በየብስና በአየር ማመላለስ አገልግሎት ውሎች ውስጥ በመንገደኛው ላይ ለሚደርሰው የአካል ጉዳት እንደዚሁም ለእቃ ብልሽትና ለጓዝ መጥፋት በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ክስ ካልቀረበ አጓዡ ጉዳቱን ለመካስ እንደማይገደድ በንግድ ህጉ ቁጥር 603 እና 642 ተደንግጓል። በዚሁ ህግ ቁጥር 674 ላይ ደግሞ በመድን ውል ምክንያት የሚቀርብ ክስ ጉዳቱ ከተደረገበት ወይም በጉዳቱ ጥቅም ያላቸው ሰወች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ መሆን እንዳለበት ተመልክቷል። ከዚህ በመቀጠል ሰበር ሰሚ ችሎት በንግድ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ አንመለከታለን።

[46] የኢትዮጵያ ንግድ ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 52/1952፣ አንቀጽ 807

## <u>ሰንጠረዥ 7</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በንግድ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | 42309 | ቅጽ 9 | ኢንሹራንስ ሰጪ በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት ከፈፀመ በኋላ በተሸሸገ ወይም በሀሰት ቃል የቀረበ ጉዳይ አጋጥሟል በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የተሸሸገውን ወይም በሀሰት የቀረበውን ቃል ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባለው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡<br>የንግድ ህግ አንቀጽ 674(1)(2) |
| 2. | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ | 46778 | ቅጽ 10 | የኢንሹራንስ ውልን መሠረት በማድረግ የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ ይታገዳል፡፡ የንግድ ህግ ቁ. 674(1)፣ 754(1) |
| 3. | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ቃድሮ ኑሬ | 56010 | ቅጽ 12 | ገንዘብ አበዳሪ የሆነ ባንክ ግዴታውን ለመፈጸም ያልቻለን አበዳሪ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት በንብረቱ ግምት ከተረከበ በኋላ ቀሪውን እዳ በተመለከተ የሚያቀርበው ጥያቄ በይርጋ ሊታገድ ይችላል፡፡ፍ/ብ/ህ/ ቁ. 1846 |
| 4. | ሀጅ መሀመድ እና ፍጹም ግርማ | 24435 | ቅጽ 12 | ቸክ በመፈረማቸው ምክንያት በሚገደዱ ሰወች ላይ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው ቸኩ ከተጻፈበት ቀን አንስቶ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ የንግድ ህግ አንቀጽ 855 |
| 5 | አቶ ሐሠን መሀመድ እና ማጅ አግሮ ፎረስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | 94278 | ቅጽ 17 | ክሱ የቀረበው በአንድ ተለይቶ በታወቀ ጊዜ ወይም ቀን የተፈጠረ ክስተትን መሠረት በማድረግ ሳይሆን በተለያየ ጊዜ ተከስተዋል የተባሉ የተለያዩ ችግሮችን መሠረት አድርጐ ሲሆን የማህበር ይፍረስልኝ ጥያቄ ወይም ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚባልበት ምክንያት አይኖርም፡፡<br>የንግድ ሕግ ቁ. 218(1)፣ 541(1) የፍ/ሕ/ቁ/ 1835፣1845 |

### 4.8የቤተሰብ ህግ የይርጋ ደንቦች

በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ[47] ውስጥ የተደነገጉ የይርጋ ደንቦች አሉ፡፡ በዚሁ ህጉ አንቀጽ 69 መሰረት በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ ባል ወይም ሚስት ፈቃድ ሳይሰጥ/ሳትሰጥ ያለ አንዱ ወገን ስምምነት የተደረገ የሽያጭ ውል ስምምነቱን ባልሰጠው ወገን ውሉ እንዲፈርስ የሚያቀርበው ጥያቄ ውሉን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በሌላ ሁኔታ ደግሞ ውሉ ከተፈጸመ በ ሁለት  አመት ውስጥ ካለቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍታብሄር ህግ ቁጥር 826(1) እና 1846 በሰጠው ትርጉም መሰረት ጋብቻ በባል ወይም በሚስት (በአንዱ ወገን) ሞት ምክንያት ከፈረሰ በኋላ የሚቀርብ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው ጋብቻው ከፈረሰበት እለት አንስቶ እንጂ ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ አይደለም፡፡[48] ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት መጠየቅ ያለበት በፍታብሄር ህግ ቁጥር 1845 ላይ በተቀመጠው ይርጋ ደንብ መሰረት በ አስር አመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡[49]

ሰበር ሰሚ ችሎት ቤተሰብ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች የሰጣቸውን ውሳኔወች ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ ተመላክተዋል፡፡

**<u>ሰንጠረዥ 8</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቤተሰብ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች**

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ድንቁ ተድላ እና እነ አቶ አባተ ጫኔ | 17937 | ቅጽ 4 | ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 ላይ የተቀመጠው ይርጋ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ |

[47] የኢፌዴሪ የተሸሻለው የቤተሰብ ህግ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 213/92፣ አንቀጽ 69
[48] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች፣ ቅጽ 11፣ መዝገብ ቁጥር- 59539፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2004፣ ገጽ 199፡፡
[49] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 4፣ መዝገብ ቁጥር-17937፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2001፣ ገጽ 82፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2. | አቶ ዮሀንስ ጡእማይ እና ወ/ሮ ምህረት ገብሩ | 51295 | ቅጽ 10 | በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ ያለስምምነት የተደረገ የሽያጭ ውል ስምምነቱን ባልሰጠው ወገን ውሉ እንዲፈርስ የሚያቀርበው ጥያቄ ውሉን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በሌላ ሁኔታ ደግሞ ውሉ ከተፈጸመ በ ሁለት አመት ውስጥ ካለቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 69 |
| 3. | አቶ ስዩም እና ወ/ሮ አምሳለ | 59539 | ቅጽ 11 | ጋብቻ በአንዱ ወገን ሞት ምክንያት ከፈረሰ በኋላ የሚቀርብ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው ጋብቻው ከፈረሰበት እለት አንስቶ እንጂ ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ አይደለም፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 826(1)፣ 1846 |

## 4.9የወንጀል ህግ የይርጋ ደንቦች

በወንጀል ህግ ይርጋ የክስ ይርጋ እና የቅጣት ይርጋ በሚል በሁለት ይከፈላል፡፡[50] የክስ ይርጋን በተመለከተ እንደ ወንጀሉ ክብደት የይርጋው ጊዜ ይለያያል፡፡ ዐቃቤ-ሕግም ሆነ የግል ተበዳይ ወንጀል ፈጽሟል በተባለው ሰው ላይ ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉበትን የጊዜ ገደብ የተቀመጠ ሲሆን ዝርዝር አሰራሩ በኢፌዴሪ ወንጀለኛ ህግ[51] አንቀጾች 216-222 ተገልጿል፡፡ በዚህ ህግ 217 እንደተገለፀው ከፍተኛውን ቅጣት ማለትም የሞት ፍርድ ወይም የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራትን ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎች ተፈጽመዋል ከተባሉ ከ25 ዓመት በኋላ ክስ አይቀርብባቸውም፡፡ እንደ ወንጀሎቹ ክብደት፣ ከአምስት እስከ 20 ዓመት የይርጋ ዘመን የሚታገዱ የተለያዩ ወንጀሎች በዚህ አንቀጽ ውስጥ ተካተዋል፡፡ በሌላ በኩል ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በእስራት ሊያስቀጡ ወይም በገንዘብ መቀጫ ብቻ ለሚያስቀጡ ወንጀሎች የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን ሶስት ዓመት ነው፡፡ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 218 እንደተገለጸው ልዩ የይርጋ ዘመን አለ፡፡ ይኸውም በግል ተበዳዮች አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎችን በተመለከተ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ወንጀል የይርጋ ጊዜ ሁለት ዓመት ነው፡፡

ሁለተኛው አይነት የወንጀል ህግ ይርጋ ደንብ የቅጣት ይርጋ ሲሆን ከቅጣት አፈጻፀም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አንድ ሰው ጥፋተኛ ነው ተብሎ ቅጣት ከተወሰነበት በኋላ ቅጣቱ ሳይፈፀም ቢቀር በሕግ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ ቅጣቱን የማስፈፀም መብት እንደሚቀር የወንጀለኛ

[50] ጥላሁን ተሾመ፣ የግርጌ ማስታወሻ 2፣ ገጽ 184
[51] የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 414/96፣ 1997

መቅጫ ህግ ቁጥር 223 ይናገራል፡፡እንደ ወንጀሉ ክብደትና ቀላልነት የቅጣት ይርጋ በሰላሳ ፣ በሃያ፣ በአስርና በአምስት ዓመት ሊወሰን እንደሚችል የዚህ ህግ ቁጥር 224(1) ዘርዝሮ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሰበር ሰሚ ችሎት በወንጀል ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ አንመለከታለን፡፡

## <u>ሰንጠረዥ 9</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በወንጀል ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ዘነበች ሽብሩ እና ፌደራል አቃቤ ህግ | 45572 | ቅጽ 11 | በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ክስ በአቃቤ ህግ ምስክሮች ተሟልቶ አለመቅረብ የከሳሽ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆ መዘጋት በቀረበው ወንጀል ሊይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ጊዜ ተግባራዊ ከመሆን አያግደውም፡፡ |
| 2. | ሀይላይ ተክሉና የመቀሌ ከተማ አቃቤ ህግ | 77097 | ቅጽ 14 | በወንጀል ጉዳይ የወንጀል ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር ጋር በተገናኘ ፖሊስ የወንጀል ድርጊቱን ፈጽሟል በሚል የተጠረጠረ ሰው ላይ የሚያደርገው ምርመራ የይርጋ ጊዜውን ያቋርጣል፡፡<br>የኢፌደሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 221፣ 106(1)፣ 420 (2)፣ 271(1)፣ 219(2) |
| 3 | እነ አቶ አዳሙ ዘለቀ(3 ሰዎች) እና የአማራ ክልል አቃቤ ሕግ | 95875 | ቅጽ 16 | አንድ ሰው በወንጀል ተከሶ በሌለበት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ጥፋተኛ የተባለው ሰው ቀርቦ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ለማስነሳት ሳይሆን በዋናው ጉዳይ ላይ በቀጥታ ይግባኝ ከጠየቀ በኃላ በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልኝ ብሎ ቢያመለክት በፊት የጠየቀው ይግባኝ በህጉ ላይ የተቀመጠውን የ30 ቀን የጊዜ ገደብ ያቋርጠዋል፡፡ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.198 |

# 5 ማጠቃለያ

የይርጋ ደንብ ሁለት አይነት መልክ ሲኖረው የመጀመሪያው ግዴታ አስቀሪ የይርጋ ደንብ ሲሆን ሁለተኛው አይነት የይርጋ ደንብ ደግሞ ያልነበረ መብት የሚያስገኝ የይርጋ ደንብ ነው። የይርጋ ደንብ በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሕግ ተቀባይነት ያለው ፅንሰ ሀሳብ ሲሆን ተከራካሪዎች፣ ዐቃቤ-ሕግ፣ ፍርድ ቤቶች፣ ጠበቆች እና የህግ ባለሞያዎች በጥንቃቄ ሊያጤኑት የሚገባ ለክርክር የቀረበን ጉዳይ እጣ ፈንታ ሊወስን የሚችል ፅንሰ ሀሳብ ነው። የይርጋ ደንብ የራሱ የፖሊሲ መሰረት ያለው ነው። አንድ የመብት ጥያቄ በህግ ፊት ተቀባይነት ቢኖረውም እንኳን ሊቀርብ በሚችልበት ጊዜ ላይ ገደብ ማበጀት አስፈላጊ ነው። ህጉ ዳተኛውን ባለገንዘብም ቢሆን ማስጠንቀቅ ያስፈልገዋል። የይርጋ ደንብ የሚፈጥረው አጠቃላይ ዋስትና ከጉዳቱ አንጻር ሲታይ ሚዛን ይደፋል።

የይርጋ ደንብን አስመልክቶ በተለያዩ የኢትዮጵያ ሕጎች ውስጥ የተካተቱት ድንጋጌዎች በዋናነት የሚያመላክቱት ክስ ለማቅረብ የሚቻልበትን የጊዜ ገደብ ነው። ክስ ለማቅረብ ወይም መብት ለመጠየቅ እንዲቻል በሕግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብም እንደጉዳዩ ክብደት፣ ባሕሪና ሁኔታ የተለያየ ሲሆን ለሁሉም ጉዳዮች የተቀመጠ ተመሣሣይ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ የለም። በመሆኑም ሕግ አውጪው እንደ ጉዳዩ ዓይነት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ክስን ለማቅረብ ወይም ያልነበረን መብት ለማግኘት የሚያስችሉ የጊዜ ገደቦችን በሕጎች ውስጥ እንዲካተት አድርጓል።

በወንጀል ጉዳይ ላይ ይርጋን በመቃወሚያነት አንስቶ ለመከራከር የሚችሉት ተከሳሽ፣ ዐቃቤ-ሕግና ፍርድ ቤቶች ናቸው። የፍትሐብሔር ፍሬ ጉዳይ የይርጋ ደንቦችን በተመለከተ ዳኞች በተከራካሪወች ካልተነሳ በቀር በገዛ ሥልጣናቸው የይርጋውን ደንብ በመቃወሚያነት ለመጥቀስ አይችሉም። ነገር ግን በስነ-ስርዓት ህጎች በግልጽ የሰፈረ የይርጋ ጊዜን በማሳለፍ የሚቀርብ ጥያቄን ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ ይችላል። በፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ተከራካሪ (ተከሳሽ) ይርጋን በመቃወሚያነት አንስቶ ለመከራከር የሚችለው ለቀረበው ክስ የመከላከያ መልስ በጽሑፍ ሲሰጥ ነው። እንዲሁም በወንጀል ጉዳይ ላይ ተከሳሽ ለፍርድ ቤቱ ማንነቱን ካስመዘገበና ክስ ከተነበበለት በኋላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ክስና መከራከሪያ ከመቅረቡና ማስረጃም ከመሠማቱ በፊት ይርጋን በመቃወሚያነት አንስቶ ለመከራከር ይችላል።

ጥቂት በሆኑ ጉዳዮች ላይ ክስ የማቅረቢያ ወይም መብት የመጠየቂያ ጊዜ ገደብ እንደሌለና ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆነው ድርጊት ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ያለምንም የጊዜ ገደብ

በማንኛውም ጊዜ ክስ ለማቅረብ የሚቻልባቸው ጉዳዮች እንዳሉ በዚህ ጽሁፍ ተመልክቷል። የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ባካሄደው ጥናት የኢትዮጵያ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የይርጋ ድንጋጌወችን በተመለከተ በፍታብሄር ስነ-ስርአት ህግ፤ በውል ህግ፣ በውርስ ህግ፣ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ፣ ከውል ውጭ ሀላፊነት፣ በንግድ ህግ፣ በቤተሰብ ህግ፣ በንብረት ህግ እና በወንጀል ህግ  ዙሪያ ከቅጽ 1 (አንድ) እስከ ቅጽ 17 (አስራ ሰባት) ድረስ 70 (ሰባ) ያህል የህግ ትርጉሞችን ሰጥቷል። ይህ ጽሁፍም ውሳኔዎቹን በመለየትና አንዳንድ የህግ ምሁራን በውሳኔወቹ ላይ ያነሷቸውን አስተያየቶች በመተንተን ለአንባቢያን ምቹ በሆነ መልኩ አቅርቧል።

# ተደራራቢ ወንጀሎች ጽንሰ ሀሳብ፣ ሕጉና አፈጻጸሙ በአማራ ክልል

ሰለሞን ተገኘወርቅ*

## አጽርኦተ-ይዘት

*የአንድ ሀገር የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ ውጤታማነት ከሚለካባቸው መመዘኛዎች አንዱ ወንጀል አድራጊዎች 'በአንድ ነጠላ ድርጊት ወይም በተደራራቢ ድርጊቶች' በፈጸሙት የወንጀል ተግባር ልክ ክስ ቀርቦባቸው ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ሲቀጡ ነው። በወንጀል ፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ወንጀል አድራጊዎች አዘውትረው አንድ ነጠላ የወንጀል ድርጊት የሚፈጽሙ ቢሆንም አልፎ አልፎ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ደርጊቶችን "በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ" ወይም "አከታትለው" በተደራራቢነት የሚፈጽሙበት አጋጣሚ እንዳለ ከየእለት ስራችን የምናየው ነው።ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የወንጀል ተግባራት በአንድ ጊዜ ወይም በተከታታይ ተፈጽመው ሲገኙ በመርህ ደረጃ በሁሉም የወንጀል ድርጊቶች ክስ ይቀርብና ወንጀል አድራጊው ጥፋተኛ ሲባል ስለተደራራቢ ወንጀሎች በተቀመጡት "የመደመር" ወይም "የማጠቃለል" የቅጣት አጣጣል መርሆዎች መሰረት ቅጣት ይወሰናል።በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዲ.ሪ) የወንጀል ህግ ተደራራቢ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የተካተቱ ሲሆን በባለሙያዎች ዘንድ ጽንሰ ሀሳቡን በአግባቡ ያለመረዳት ችግር ይስተዋላል። በተለይም አንድ ድርጊት ተደራራቢ ለመባል ሊያሟላቸው የሚገቡ መስፈርቶች ምንድን ናቸው? ተደራራቢ ወንጀሎች ተደራራቢ ካልሆኑት ወንጀሎች የምንለይበት ስልት ምንድን ነው? እንዲሁም በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ የተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ በመደመር ወይም በማጠቃለል መርህ ቅጣት እንዴት ይጣላል? በሚሉት ነጥቦች ዙሪያ በተግባር ችግሮች ይስተዋላሉ። ጥናቱ በወንጀል ህጉ ስለተደራራቢ ወንጀሎች የተቀመጡትን መርሆዎች ይተነትናል፤ በተግባርም በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ክስ እንዴት እየቀረበ እንደሆነና ቅጣት እንዴት እንደሚወሰን ማሳያ የሚሆኑ መዝገቦችንና ሌሎች መረጃዎችን መሰረት በማድረግ በተግባር ያለውን የአሰራር ጉድለት ያመለክታል።*

*(LLB, LMM in Business and Corporate law) በአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና ህግ ምርምር ኢንስቲትዩት ተመራማሪ አገልግለዋል። አሁን በአብክመ ፍትህ ቢሮ የክልል ዐቃቤ ህግ ሆነዉ እየሰሩ ይገኛሉ።

# 1. የተደራራቢ ወንጀሎች ጽንሰ-ሀሳብ

የተደራራቢ ወንጀሎችን ጽንሰ ሀሳብ በሚመለከት የወንጀል ሳይንስ /criminal science/ አስተምህሮቶችና ፖሊሲዎች በግልጽ በማስቀመጥ ስለተደራራቢ ወንጀሎች ያለው ግንዛቤ በበቂ ሁኔታ አድጓ ባለሙያዎች በቀን ተቀን ስራቸው ጋር በተገናኘ ጽንሰ ሀሳቡን በቀላሉ እንዲረዱት በማድረግ ረገድ ብዙ ርቀት ተሄዷል ለማለት አያስደፍርም[1]። ይህ ችግር የሚስተዋለው የወንጀል ህጎቻቸውና የወንጀል ፖሊሲዎቻቸው ባላደገበት ሀገሮች ብቻ ሳይሆን የወንጀል ህጎቻቸው ረጅም እድሜ ባስቆጠረውና በወንጀል ሳይንስ ዘርፍም ብዙ ርቀት ሄደዋል በሚባሉ ሀገሮች ጭምር ነው[2]። እንዲያውም አንዳንድ ጸሀፊዎች እንደሚሉት ከሆነ ቀደም ባሉት ጊዜያት የተደራራቢ ወንጀሎች ጽንሰ ሀሳብ በብዙ ሀገራት የወንጀል ህጎች ውስጥ የተካተተ እንዳነልበር ይጠቁማሉ[3]። ተደራራቢ ወንጀሎችን በሚመለከት በወንጀል ሀግጋት ውስጥ ከተቀመጠው በላይ በህግ መጽሀፎች እንደተጻፈና በተግባርም በፍትህ አካላት ዘንድ በመዛግብቶች ላይ በስፋት እንደሚያጋጥም ይገለጻል[4]። ለዚህ የሚቀርበው ምክንያት የተደራራቢ ወንጀሎች ጽንሰ ሀሳብ ውስብስብ እና አስቸጋሪ በመሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎች ባህሪያቸው ምን ይመስላል? ተደራራቢ ወንጀሎች እንዴት ይፈጸማሉ? ተደራራቢ ወንጀሎች ከነጠላ ወንጀሎች እንዴት ይለያሉ? የሚሉትን ጉዳዮች ህግ አውጭው ቀድሞ ለመረዳት ስለማይቻለው በህግ ማእቀፎች ውስጥ በቀላሉ ለማስቀመጥ ስለሚያስቸግር ነው። ወደፊትም ቢሆን በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ያለው ግንዛቤ ይበልጥ እያደገ ሊመጣ የሚችለው በህግ መጻህፍቶች በስፋት እየተጻፈ ሲመጣና በተግባርም የፍትህ አካላት በየእለት ስራቸው ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች በመነሳት በአዲስ የሚገኙትን ግኝቶች ወደ ወንጀል ህግ ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ ነው።

የተደራራቢ ወንጀሎች ጽንሰ ሀሳብ በህግ ባለሙያዎች ዘንድ በበቂ ሁኔታ አይደግ እንጂ ወንጀል አድራጊዎች ተደራራቢ የሆኑ የወንጀል ተግባራትን የሚፈጽሙበት አጋጣሚ እንዳለ የሚታወቅ ነው። ተደራራቢ ወንጀሎች የሚመጡት አንድ ወንጀል አድራጊ አከታትሎ ወይም በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ /simentannusly/ በሚፈጽማቸው ድርጊቶች በተለያዩ ድንጋጌዎች ስር የተሸፈኑ የአንድ ወይም የሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን መብት በመጣስ ግዙፋዊ

[1]Marianne Wells, Sentencing for Multiple Offences in western Australia, the Universtiy of western Australia, crime research center,research report no. 6, 1992, ገጽ 13-15፣ የተወሰደው የካቲት 23/2008 ዓ.ም

[2]ዝኒ ከማሁ

[3]Philippe Graven, An Introduction to Ethiopian Penal code, Haileslasie I Universty, Adiss Ababa,1965, ገጽ 164-166

[4]ዝኒ ከማሁ

ተደራራቢ ወይም ጣምራ ወንጀሎችን ሲፈጽም ነው[5]። ይህ ማለት ተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶች ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ ወይም ተመሳሳይ ያልሆኑ የወንጀል ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ግዙፋዊ መደራረብ የሚያስከትሉ ሲሆን በሌላ በኩል አንድ ህገ ወጥ ድርጊት በተለያዩ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ስር ጥበቃ ያገኙ መብቶችን በመጣስ ጣምራ ወንጀሎች ሲፈጸሙ ነው[6]። እነዚህ ወንጀሎች የተፈጸሙት በአንድ ድርጊት /in single transaction/ ከሆነ ድርጊቱ ፍጹም ተደራራቢ በሚል የሚታወቅ ሲሆን ወንጀሉ የመጣው በተከታታይ በተፈጸመ ድርጊት /in successive transaction/ ከሆነ አንጻራዊ ተደራራቢ በሚል በጸሀፊዎች ይገለጻል[7]። ተደራራቢ ወንጀሎች የሚፈጸሙት በአንድ ዓይነት መብት/ same right/ ወይም በሚዛመዱ /related right/ ወይም በተለያዩ መብቶች /different right/ ላይ ሊሆን ይችላል።

### 1.1 ተደራራቢ ወንጀሎች በፈጸመ ወንጀል አድራጊ ላይ ቅጣት ከብዶ የሚወሰንበት አግባብ

የወንጀል ህግ ዓላማ በቀዳሚነት ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል እንደሆነና ይህንን ግብ የሚያሳካው በአንድ በኩል ስለወንጀሎችና ስለሚያስከትሉት ቅጣት ከወዲሁ በማሳወቅ ማስጠንቀቅ ሲሆን ማስጠንቀቂያው በቂ ባልሆነ ጊዜ[8] ወንጀል አድራጊዎች ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ እንደሆነ ተመልክተናል። ቅጣት ሲጣልም ትክክለኛ፣ ፍትሀዊና ተመጣጣኝ መሆን ይገባዋል[9]። የወንጀል ህግ ዋነኛ መርህ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ለአንድ ድርጊትና ለአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ /mental state/ አንድ ቅጣት የሚለው የሚጠቀስ ነው። ታዲያ በተደራራቢ ወንጀሎች በአንድ ድርጊት በአንድ ወንጀል የማደረግ ሀሳብ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ወንጀሎችን የፈጸመ ወንጀል አድራጊ ስለምን በሁሉም ድርጊቶች ክስ ይቀርብበታል? ስለምንስ ቅጣቱ ይከብድበታል? የሚል ጥያቄ ብንጠይቅ አንድም ወንጀል አድራጊው ጉዳቱን ያደረሰው ዜጎች በህገ መንግስትና በዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶችና ስምምነቶች ላይ ጥበቃ በተደረገላቸው በዜጎች በህይወት የመኖር መብት፣ በአካል ደህንነት መብት፣ በንብረት ጥበቃ መብት እና በሌሎች ዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይ ስለሆነ ወንጀል

---

[5]የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ፣ 1996፣ አንቀጽ 60(ሀ፣ ለናሐ)

[6] ዝኒ ከማሁ

[7] Marianne Wells, Sentencing for multiple offences in western australia, the Universty of western Australia crime research center, research no. 6 ገጽ 5 የተገኘው የካቲት 23፣ የተወሰደው www.unswlawjournal.unsw.edu.au/

[8] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5፣ አንቀጽ 1፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣው የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006

[9]ዝኒ ከማሁ

አድራጊዎች እነዚህን መብቶች በጣሱ ጊዜ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው[10]። ወንጀል አድራጊዎች ከፈጸሙት ወንጀል ጋር የሚመጣጠን ቅጣት የማይጣል ከሆነ ዜጎች ለመብቶቻቸው ጥበቃ የህግ ዋስትና ስለሚያጡ በግል ፍትህ የመፈለግ /self justice/ አማራጭ ውስጥ እንዲገቡ ይገደዳሉ፤ በወንጀል ፍትህ ስርዓቱ ላይም እምነት ያጣሉ። ከዚህ በተጨማሪ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ወንጀሎችን በተደራራቢነት የፈጸመ ወንጀል አድራጊ አንድ ነጠላ ወንጀል ከፈጸመ ወንጀል አድራጊ ጋር ሲነጻጸር አደገኛ ስለሆነና ጥፋቱም በተለያዩ ሰዎች መብት ላይ ጉዳት ስለሚያስከትል ቅጣቱ ከፍ ሊል ይገባል ከሚል አመክንዮት በመነሳት ነው። ምክንያቱም ቅጣት ሲጣል ምንጊዜም ቢሆን የደረሰውን ጉዳት፣ የተገኘውን ጥቅም፣ የድርጊቱ ተደጋግሞ መፈጸም ግምት ውስጥ የሚገባ ስለሆነ ነው።

በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ የሚጣሉ ቅጣቶች የተመጣጣኝነትን መርህ የሚከተሉ መሆን ይኖርባቸዋል። ቅጣት በአንድ በኩል የወንጀል አድራጊዎችን የመንቀሳቀስ መብት ስለሚገድብ፣ በህይወት የመኖር መብትን ስለሚያሳጣ ወይም በንብረት የመጠቀም መብትን ስለሚነፍግ በቀጥታ ከሰብአዊ መብት ጋር የሚገናኝ ነው። ለዚህም ነው ቅጣት ሲጣል በአንድ በኩል የወንጀል አድራጊውን አደገኛነትና የደረሰውን ጉዳት በሌላ በኩል የወንጀል አድራጊው ሰብአዊ መብት በቅጣት ምክንያት አላግባብ እንዳይገደብ ግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣት ሚዛናዊ እንዲሆን በማሰብ በተደራራቢ ወንጀሎች ጊዜ የመደመርና የማጠቃለል የቅጣት አጣጣል መርሆዎች ተግባራዊ ሆነው ይገኛሉ። የመደመርና የማጠቃለል የቅጣት ዘዴዎች ተግባራዊ የሚሆኑት ምክንያታዊ ያልሆነና ዝቅተኛ ቅጣት እንዳይጣል ለማድረግና ወንጀል አድራጊው በፈጸመው ወንጀል ልክ እንዲቀጣ በማድረግ የቅጣት ቀዳሚ ዓላማ ማስተማር ነው የሚለውን አስተምህሮት ተግባራዊ ለማድረግ ነው። በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ሲጣል ቅጣቱ የወንጀል አድራጊውን የወንጀለኛነትና የአደገኛነት ባህሪ ማሳየት ይኖርበታል። ገዢው መርህ የሚጣለው ቅጣት ትክክለኛና ተመጣጣኝ መሆን ይገባዋል የሚለው ነው።

[10]የወንጀል ህግ አላማ ዜጎች በህግ መንግስትና በሌሎች ሰነዶች ላይ የተሰጣቸውን መብት ለመጠበቅ ሲሆን ወንጀል የሚፈጸመውም በህይወት ላይ፣ በአካል ላይ፣ በንብረት ላይ እንዲሁም በተለያዩ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይ እንደሆነ የሚታወቅ ነው።

# 1. ተደራራቢ ወንጀሎች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግና ተግባራዊ አፈጻጸሙ በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች

## 2.1 ተደራራቢ ወንጀሎች በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት

በሀገራችን የወንጀል ህግ ስርዓት ውስጥ ስለተደራራቢ ወንጀሎች ተደንግጎ የሚገኘው በ 1949 ዓ.ም ወጥቶ ከግማሽ ምእተ ዓመት በላይ ስራ ላይ በነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ ሲሆን በዚሁ ህግ ተደራራቢ ወንጀሎች ምን ባህሪያት እንዳሏቸውና በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ሲጣል ፍርድ ቤቶች ሊመሩባቸው ስለሚገቡ መርሆዎች የሚደነግጉ አንቀጾች ተካተውበት ይገኛል[11]። በዚሁ ህግ ከቁጥር 60-63 በተመለከቱት ድንጋጌዎች ስር ተደንግጎ ይገኛል። ተደራራቢ ወንጀሎች እንደ ልዩ የቅጣት ማክበጃ የሚወሰዱ መሆናቸውም በዚሁ ህግ በቁጥር 82 ስር የተገለጸ ሲሆን የቅጣት አጣጣሉን በሚመለከት ከቁጥር 189-193 ባሉት ድንጋጌዎች ስር ተካቶ ይገኛል። እነዚህ ድንጋጌዎች ስለተደራራቢ ወንጀሎች የሚያወሱ ድንጋጌዎችን ይያዙ እንጂ ድንገጌዎቹ ግልጽነት የጎደላቸውና ተደራራቢ ወንጀሎችን ሰፋ ባለ ሁኔታ አካተው የሚገኙ ባለመሆናቸው በአሰራር ችግር የሚፈጥሩ ነበሩ[12]። ተደራራቢ ወንጀሎች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ከአንቀጽ 60-66 በተመለከቱት ድንጋጌዎች ስር ተካተው የሚገኙ ሲሆን ቀድሞ ስራ ላይ በነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ የነበሩ ክፍተቶችን የሚሸፍንና በአዲስ መልኩ በተደራራቢ ወንጀልነት ሊፈረጁ የሚገባቸውን ተጨማሪ ድርጊቶችን አካቶ ይዟል[13]።ተደራራቢ ወንጀሎች ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መሆናቸውም በዚሁ ህግ በአንቀጽ 85 ስር የተገለጸ ሲሆን የቅጣት አጣጣል ስልቱን በሚመለከት ከአንቀጽ 183-187 ስር ባሉ ድንጋጌዎች ስር በዝርዝር ተመልክቶ ይገኛል።

በተሻረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥም ይሁን አሁን ስራ ላይ ባለው የወንጀል ህግ ውስጥ ተደራራቢ ወንጀሎች ምንድን ናቸው የሚለው በትርጉም ደረጃ የተቀመጠ ባይሆንም ተደራራቢ ወንጀሎች የሚባሉት ምን ባህሪያት አሏቸው፣ አንድ ድርጊት ተደራራቢ ወንጀል አስከትሏል ለማለት ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፣ ተደራራቢ ወንጀሎች ተደራራቢ ከማይባሉት ወንጀሎች

[11]የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ፣ 1949፣ አንቀጽ 60-63፣ ቁጥር 82፣ ቁጥር 189-193

[12]ለምሳሌ ያክል ብንመለከት በ1949 በወጣው ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ የተጎጂዎች መደራረብ የተካተተ ስላልነበር በአንድ ድርጊት ብዙ ሰዎች ተመሳሳይ ጉዳት ሲደርስባቸው አንድ ክስ ብቻ ይቀርብ ነበር። በዚህም ህጉ ኢፍትሀዊ ነው የሚል ትችት ያስተናግድ ነበር።

[13]በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ፣ 1996፣ አንቀጽ 60(ሐ) ስር የተመለከተው በአዲስ የተካተተ ነው።

እንዴት እንደሚለዩና በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ሲወሰን ፍርድ ቤቶች ሊከተሏቸው ስለሚገቡ መርሆዎች የሚደነግጉ አንቀጾችን እናገኛለን፡፡

## 2.2 የተደራራቢ ወንጀሎች ዓይነት

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ተደራራቢ ወንጀሎች የሚፈጸሙበትንና ባህሪያቸውን መሰረት በማድረግ በዋናነት በሶስት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

### ሀ. ግዙፋዊ መደራረብ (Material concurrence)

ግዙፋዊ ተደራራቢ ወንጀል የሚባለው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ሀ) ስር የተመለከተው ሲሆን የዚህ ዓይነት ተደራራቢ ወንጀል በ1949 ዓ.ም ወጥቶ ስራ ላይ በነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥም ተካቶ እንደነበር ድንጋጌዎችን በማየት መረዳት እንችለላን፡፡ አንድ ወንጀል አድራጊ ተደራራቢነት ያላቸውን ግዙፍ ወንጀሎች ፈጽሟል የሚባለው በአንድ ድንጋጌ ወይም በተለያዩ የወንጀል ሕጉ አንቀጾች ስር የሚያስቀጡ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶችን አከታትሎ የፈጸመ እንደሆነ ወይም የፈጸማቸው ተመሳሳይ ድርጊቶች በአንድ የወንጀል ድንጋጌ ስር ተጠቃለው የማይሸፈኑ ሲሆን ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 60(ሀ) ስር እንደተመለከተው ግዙፋዊ የወንጀል መደራረብ ተፈጽሟል ሊባል የሚችለው የሚከተሉት መመዘኛዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ ይሄውም አንድ ወንጀል አድራጊ “ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ፤ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ግዙፍ ወንጀሎችን አከታትሎ የፈጸመ ከሆነ ነው”፡፡ ከእነዚህ መመዘኛዎች የምንረዳው ወንጀል አድራጊው ግዙፋዊ የወንጀል መደራረብ የሚያስከትል ተግባር ፈጸመ የምንለው አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ድርጊቶችን አከታትሎ ግዙፋዊ ውጤት የሚያስከትሉ የወንጀል ተግባሮችን የፈጸመ እንደሆነ ነው፡፡ የተፈጸሙት ወንጀሎች በአንድ አንቀጽ ስር የሚሸፈኑ ወይም የማይሸፈኑ እንዲሁም ወንጀሎቹ የተፈጸሙት በአንድ ሰው ወይም በተለያዩ ሰዎች መብት ላይ ሊሆን ይችላል፤ የሚገኘው ውጤትም ተመሳሳይ ወይም የተለያየ ሲሆን ወንጀል አድራጊው ድርጊቱን የፈጸመው አስቦ ወይም በቸልተኝነት ሊሆን ይችላል[14]፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር “ግዙፋዊ” ውጤት በሚል የተገለጸውና ግዙፋዊ የወንጀል መደራረብ አለ የሚባለው ወንጀል አድራጊው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑት የወንጀል ድርጊቱ ውጤቶች በእጅ የሚዳሰሱና በዓይን የሚታዩ ውጤቶች ስለሚያስከትል ግዙፋዊ ድርጊቶችን በጣምራ የወንጀል ድርጊት አማካኝነት ከሚመጡ በዓይን

[14]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5፣ አንቀጽ 60(ሀ)

ከማይታዩና በእጅ ከማይዳሰሱ የወንጀል ውጤቶችን ለመለየት እንዲረዳ ነው። ግዙፋዊ ተደራራቢ ወንጀሎች ባህሪያቸው ምን እንደሚመስል በምሳሌ ለመመልከት ያክል አንድ ወንጀል አድራጊ የሌላን ሰው ቤት ሰብሮ በመግባት የስርቆት ወንጀል ቢፈጽም፣ ቀጥሎም በቤት ውስጥ በነበረች የ 12 ዓመት ህጻን ላይ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ቢፈጽም ይህ ወንጀል አድራጊ በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 665(1) እና በአንቀጽ 627(1) ድንጋጌዎች ስር ጥበቃ የተደረገላቸውን ሁለት የተለያዩና በሁለት የተለያዩ ሰዎች መብት ላይ ግዙፋዊ ውጤት ያስከተለ ወንጀል እንደፈጸመ መገንዘብ ይቻላል። በሌላ ምሳሌ አንድ ወንጀል አድራጊ በሀይል የ 'ሀ' ን ሱቅ ቢዘርፍና ወዲያውኑ ከጎረቤቱ የሚኖረውን የ 'ለ' ን መኖሪያ ቤት ቢያቃጥል ግዙፋዊ የወንጀል መደራረብ ስለፈጸመ የወንጀል ህግ አንቀጽ 670/671 እና 494(1) ተጠቅሰው ሁለት ተደራራቢ ክስ ይቀርብበታል። እንዲሁም አንድ ወንጀል አድራጊ በአንድ ቀን በአንድ በተወሰነ ሰፈር ውስጥ አንድ ሰው ቢገድል፣ አንድ ሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ቢያደርስ፣ በሌላ ሰው ንብረት ላይ የውንብድና ወንጀል ቢፈጽም፣ በሌላ ሰው ላይ የመግደል ሙከራ ወንጀል ቢፈጽም ይህ ወንጀል አድራጊ የሚከሰሰው በ 4 ልዩ ልዩ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ነው። በዚህም መሠረት ለግድያ ወንጀሉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 540/539(1-ሀ)፣ ለውንብድና ወንጀሉ አንቀጽ 670/671፣ ለከባድ አካል ጉዳት ማድረስ ወንጀሉ አንቀጽ 555 እንዲሁም ለመግደል ሙከራው አንቀጽ 27(1) እና 540/539(1-ሀ) ተጠቅሰው ክስ የሚቀርብበትና ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ቅጣቱን ሲጥል የማጠቃለል መርህን በመከተል ቅጣት ሊወስን ይችላል። ተደራራቢ ወንጀል በፈጸሙ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ክስ እንዴት ሊቀርብ እንደሚገባ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ በአንቀጽ 116 ስር አቅጣጫ አስቀምጧል።

ከላይ በአንቀጽ 60(ሀ) ስር ህግ አውጭው ካስቀመጣቸው መመዘኛዎች ውስጥ ግልጽ ያልሆነው ነጥብ ህግ አውጭው **"አከታትሎ"** የሚለውን ቃል ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ማናቸውንም ዓይነት ግዙፍ ወንጀሎችን አከታትሎ ያደረገ እንደሆነ የሚለው የድንጋጌው ማቋቋሚያ ባይኖር ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ድርጊቶችን ተደራራቢ ናቸው አይደሉም የሚለውን መለየት ይቻል ነበርን የሚለው ነጥብ አከራካሪ ነው። "አከታትሎ" (successively) የሚለውን ቃል በሚመለከት በወንጀል ህጉ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ድርጊቶች በተደራራቢነት ተፈጽመዋል ለማለት በመጀመሪያው እና በሚቀጥለው ድርጊት መካከል ያለው የጊዜ መለኪያ አልተቀመጠም። መለኪያውስ ሰዓታት? ቀናት? ሳምንታት? ወራት? ወይስ ዓመታት? የሚለውም የሚያከራክር ነው። ይህን ሀሳብ በሚመለከት

ባለሙያዎች ሁለት አይነት ሀሳቦችን ያስቀምጣሉ፡፡ አንዳንድ ባለሙዎች እንደሚሉት ከሆነ አከታትሎ የሚለውን ቃል መረዳት ያለብን ቃሉን በቀን ተቀን ህይወታችን እንደምንረዳው ወንጀል አድራጊው የመጀመሪያውን ወንጀል እንደፈጸመ ወዲያው ሌላ ወንጀል የፈጸመ እንደሆነ ድርጊቶቹን አከታትሎ ፈጽሟል ሊባል ይችላል በሚል ያስቀምጣሉ[15]፡፡ አከታትሎ የሚለው ቃል አንድ ወንጀል አድራጊ የጀመረውን ወንጀል የማድረግ ተግባር ሳያቋርጥ አንድ አይነት ወይም የተለያዩ ወንጀሎችን ፈጽሞ ሲገኝ ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ ይህም ሲባል ወንጀል አድራጊው ወንጀል የማድረግ ሀሳቡን ሳይገታ ወንጀሎቹን የፈፀመ እንደሆነ እንጂ ከዚህ ሀሳቡ ከወጣ በኋላ በሌላ ጊዜ እንደገና በአዲስ ሀሳብ ወንጀል ቢፈፅም ቀድሞ ከፈፀመው ወንጀል ጋር አደራርቦ ፈፅሟል ልንል አንችልም፤ ምክንያቱም ወንጀሉን ተደራራቢ እንዲሆን የሚያደርገው በዋናነት የወንጀለኛው ወንጀሎቹን አደራርቦ የመፈፅም እቅድ ነው ሲሉም ሀሳባቸውን ያጠናክራሉ[16]፡፡ ለምሳሌ አንድን ሰው በጥይት ተኩሶ ከገደለ በኋላ ወዲያው ሌላ ሰው ላይ የአካል ጉዳት ቢያደርስ በሁለቱ ወንጀሎች መካከል የድርጊት ጣልቃ ገብነት ሳይኖር ወንጀሎቹ ተከታትለው ተፈጽመዋል ሊባል እንደሚችል ይጠቁማሉ[17]፡፡ ይሄውም ከመጀመሪያው ድርጊት ቀጥሎ የሚፈጸመው ሌላው ድርጊት ከወንጀል አድራጊውና ከማህበረሰቡ አእምሮ ሳይጠፋ በትኩሱ ሲፈጸም አከታትሎ ፈጽሞታል ለማለት ይቻላል የሚል ነው፡፡ ይህን ከላይ ያለውን ሀሳብ በሚደግፍ መልኩ አንድ ጸሃፊ አከታትሎ የሚለውን ቃል በምሳሌ ሲገልጽ “ጠላቶቹን ለመጨረስ አቅዶ በ 7 ሰዓት ላይ አቶ ‹ሀ› ን በ 8 ሰዓት ላይ አቶ ‹ለ›ን በ 9 ሰዓት ላይ አቶ ‹መ›ን ቢገድል ይህ ሰው አንድ ዓይነት የሆኑ ሶስት ወንጀሎችን ፈጽሟል”[18] በሚል አስቀምጦታል፡፡ በሌላ በኩል ከላይ ከተመለከትነው በተለየ ሁኔታ ሀሳባቸውን የሚሰጡ ባለሙያዎች እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ ወንጀል አድራጊው የመጀመሪያውን ወንጀል ከፈጸመ በኋላ ይሄው ወንጀል አድራጊ ቀድሞ በፈጸመው ጥፋት ከመቀጣቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ሌላ ወንጀል ቢፈጽም የመጀመሪያው ወንጀል በይርጋ እስካልታገደ ድረስ ወንጀሎቹ ተከታትለው እንደተፈጸሙ ተቆጥሮ ተደራራቢ ወንጀሎች ሊባሉ ይችላሉ የሚል ነው[19]፡፡ ለክርክራቸው ማጣቀሻ የሚያደርጉት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 106 እና 108 ስር የተገለጹትን

[15]በሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ የወንጀል የስራ ሂደት ዓቃቢያነ ህጎች ጋር የተደረገ ውይይት፣ ሚያዚያ 2/2008 ዓ.ም
[16]ዝኒ ከማሁ
[17]ዝኒ ከማሁ
[18]ጸሀይ ወዳ፣ የወንጀል ህግ መሰረታዊ ሀሳቦች፣ 1994 ዓ.ም
[19]በአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና ህግ ምርምር ኢንስቲትዩት የ4ኛ ዙር ቅድመ-ስራ ሰልጣኞች ጋር የተደረገ ውይይት፣ ህዳር 2004 ዓ.ም

ሀሳቦች ነው፡፡ ይሄውም በአንቀጽ 106 ስር የቀላል እስራት ጣሪያ 3 ዓመት ስለሆነና በአንቀጽ 108 መሰረት በሀገራችን የጽኑ እስራት ቅጣት ጣሪያ ከ 25 ዓመት እንደማይበልጥ መደንገጉን ነው፡፡ ለምን ቢባል ወንጀሎቹ ተደራራቢ በሚል ካልተፈረጁ አንድ ግለሰብ በተለያዩ ጊዜያት የፈጸማቸው ወንጀሎች ቢደመሩ ቅጣታቸው በቀላል እስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች ከ 3 ዓመት ቀላል እስራት እንዲሁም በጽኑ እስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች ከ 25 ዓመት ሊበልጥ የሚችልበት እድል ስላለ አከታትሎ የሚለውን ቃል ከላይ በተገለጸው መንገድ ካልተረዳነው የወንጀል ህጉ በአንቀጽ 106 እና 108 ስር ያስቀመጠውን አላማ ማሳካት አይቻልም በሚል ነው[20]፡፡ በአማራ ክልል ባሉ ፍርድ ቤቶችና የዐቃቢያነ መስሪያ ቤቶች በተግባር ያለው አሰራርም የሚያመለክተው ከላይ በሁለተኛ ደረጃ ሀሳባቸውን የሚገልጹ ባለሙዎችን ሀሳብ በሚደግፍ መልኩ ሲሆን ተደራራቢ ወንጀሎችን ለመለየት አከታትሎ የሚለው መመዘኛ ግምት ውስጥ እንደማይገባና የመጀመሪያው ድርጊት በይርጋ ቀሪ እስካልሆነ ድረስ ከሚቀጥለው ድርጊት ጋር ተደራራቢ ይሆናል በሚል ክስ እየቀረበ ውሳኔ እንደሚሰጥ ባለሙዎች ይገልጻሉ[21]፡፡ ባለሙያዎች በየእለት ስራቸው አከታትሎ የሚለውን ቃል ተደራራቢ ወንጀሎችን ለመለየት መመዘኛ በማድረግ ሲከራከሩበት አይታይም፤ ጠበቆችም መቃወሚያ አያቀርቡም፤ ፍርድ ቤቶችም ክርክሮችን ተደራራቢ ናቸው አይደሉም ለማለት አከታትሎ የሚለውን ቃል እንደ መመዘኛ ወስደው ውሳኔ ሲሰጡ አይታይም[22]፡፡

በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 60/ሀ/ መሠረት በተደራራቢነት ግዙፋዊ ውጤት የሚያስከትል ወንጀል የፈጸሙ ወንጀል አድራጊዎች የሚጣልባቸው ቅጣት ከፈጸሙት ወንጀል ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን በማሰብ ህግ አውጭው ያስቀመጠው እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በአማራ ክልል ባሉ የዐቃቢያነ ህግ መስሪያ ቤቶች በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከት ዐቃብያነ ህጎች የአንቀጽ 60(ሀ)ን ዓላማ በአግባቡ ባለመረዳት አልፎ አልፎ የምርመራ መዛግብቶቹ ወንጀል አድራጊው ተደራራቢ ድርጊት መፈጸሙን እያሳዩ ተደራራቢ ክስ ሳይቀርብ በመቅረቱ ወንጀል አድራጊዎች ባጠፉት የወንጀል ተግባር ልክ ሳይቀጡ እንደሚቀሩ መዝገቦች ያሳያሉ፡፡ ለአብነት ያክል አንድ ወንጀል አድራጊ ግልጽ የሆነ የትራፊክ ደንብ በመተላለፍ በሚያሽከረክረው ባጃጅ ውስጥ ተሳፍረው በነበሩ 2 ሰዎች ላይ ከባድ ጉዳት አድርሶ ለማምለጥ ሲሞክር በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት እንዳደረሰ የምርመራ መዝገቡ እያመለከተ የግል ተበዳዮች የህክምና እርዳታ እንዲያገኙ

[20] ዝኒ ከማሁ
[21]በሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ በወንጀል የስራ ሂደት ውስጥ ከሚሰሩ ዐቃቢያነ ህጎች ጋር የተደረገ የጋራ ውይይት መጋቢት 12/2008 ዓ.ም
[22]ዝኒ ከማሁ

ባለማድረጉና በንብረት ላይ ላደረሰው ጉዳት በተደራራቢነት በወንጀል ህግ አንቀጽ 575(2-ለ)ና በአንቀጽ 572(2) መሠረት ክስ ሊቀርብበት ሲገባ ይህ ሳይሆን ቀርቶ የወንጀል ህግ አንቀጽ 559(2) ተጠቅሶ 2 ክስ ብቻ እንደቀረበበት የክስ መዝገቡ ያሳያል[23]። በተመሳሳይ 8 ሰዎች በተከሰሱበት የግድያ ወንጀል የሚች ወንድም ወንድሜን ማን መታው እያለ ሚች ወደ ወደቀበት ቦታ ሲሄድ 1ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች የሚችን ወንድም በዱላ በመደብደብ ጉዳት ያደረሱበት መሆኑን የምርመራ መዝገቡ የሚያሳይ ሲሆን 1ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች በሚች ወንድም ላይ ለፈጸሙት ቀላል የድብደባ ወንጀል የወንጀል ህግ አንቀጽ 556(2-ሀ) ተጠቅሶ በወንጀል አድራጊዎቹ ላይ ሁለት ተደራራቢ ክስ መቅረብ ሲገባው 1 ክስ ብቻ እንደቀረበባቸው መዝገቡ ያመለክታል[24]።

**ለ. ጣምራዊ (ሀሳባዊ/ መደራረብ) (የድንጋጌዎች መደራረብ) (notional concurrence)**

በወንጀል ህግጋት ውስጥ ተደራራቢ ወንጀል ተብለው ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ የሀሳብ መደራረብ (notional concurrence) የሚባለው ነው። ጣምራዊ መደራረብ በተሻረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በቁጥር 61 ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ደግሞ በአንቀጽ 60(ለ) ስር ተደንግጎ ይገኛል። በዚህ ድንጋጌ ስር አንድ ድርጊት ጣምራ ወንጀሎች አስከትሏል ለማለት በህጉ የተቀመጡት መስፈርቶች "በአንድ ድርጊት፤ በአንድ ጊዜ፣ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን መጣስ ወይም፤ በአንድ ጊዜ ልዩ ልዩ ግዙፋዊ ውጤቶችን የሚያስከትሉ ተግባሮች ተፈጽመው ሲገኙ ነው" በሚል ተቀምጧል። የዚህ ዓይነት ተደራራቢ ጣምራ ወንጀሎች የሚመጡት በአንድ ነጠላ የወንጀል ድርጊትና በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ /ቸልተኛነት/ በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ድንጋጌዎች ስር ጥበቃ የተደረገላቸው መብቶች ሲጣሱ ነው። ጣምራ ወንጀሎች ተፈጽመዋል ለማለት በአንድ ድርጊት የተፈጸሙት ወንጀሎች የተለያየ ይዘት እና ባህሪይ ያላቸው በመሆናቸው በተለያዩ ድንጋጌዎች ስር የሚሸፈኑ ናቸው። ጣምራ ወንጀሎች የፈጸመ ወንጀል አድራጊ ጥፋተኛ የሚደረግበት ዋነኛ ምክንያት ወንጀል አድራጊው የፈጸመው ድርጊት አንድ ቢሆንም የተለያየ ይዘት እና ባህሪይ ያላቸው ከአንድ በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሰ በመሆኑ ከአንድ በላይ የሆነ የወንጀል

[23]የሰሜን ጎንደር ዞን ፍትህ መምሪያ የወ/መ/ቁ 10030/2006 በዓቃቤ ህግ እና በሞገስ ቦጋለ መካከል የተደረገ ክርክር

[24]የሰሜን ጎንደር ዞን ፍትህ መምሪያ የወ/መ/ቁ. 08519/2006 በ ዐቃቤ ህግና በእነ ዲያቆን መኳንት በላይነህ /8 ሰዎች/ መካከል የተደረገ ክርክር

ማድረግ ሀሳብ አለው ተብሎ ስለሚገመት ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ወንጀል አድራጊ ድርጊቶችን መደጋገም ሳያስፈልገው በአንድ ድርጊት ብቻ ከአንድ በላይ ጥፋቶችን ለማጥፋት ሀሳብ ያለው በመሆኑ ቅጣቱም በጥፋቱ ልክ መሆን ይኖርበታል በሚል ነው፡፡ በጣምራ የወንጀል መደራረብ ወቅት ወንጀል አድራጊው ወንጀሉን የሚፈጽመው አስቦ ወይም በቸልተኛነት ሲሆን ለሁሉም ወንጀሎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡ በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ /Simultaneously/ ልዩ ልዩ የሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈጸም ጣምራ ወንጀል የሚያስከትለው ውጤት አንድም አንድ ግዙፋዊ ውጤትና ሌሎች ግዙፋዊ ያልሆኑ ውጤቶች ሊያስከትል የሚችል ሲሆን በሌላ በኩል በጣምራ ወንጀሉ የሚመጡት ሁሉም ውጤቶች ግዙፋዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ባልተመዘገበ የጦር መሳሪያ ተኩሶ ሌላ ሰው ቢገድል በአንቀጽ 60/ለ/ መሰረት የሰው መግደል እንዲሁም ህገ ወጥ መሳሪያ በመያዝ ተደራራቢ ወንጀሎች ፈጽሟል በሚል ክስ ይቀርብበታል፡፡ በዚህ ድርጊት የሰው ግድያ ወንጀሉ ያልተመዘገበ የጦር መሳሪያ ወንጀሉን ስለማይሸፍነው በሁለቱም ድንጋጌዎች ተደራራቢ ክስ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ በሌላ ምሳሌ አንድ በህጋዊ ጋብቻ ወስጥ ያለ ሰው ከ 18 ዓመት እድሜ በላይ የሆነች የስጋ ዘመዱን በህዝብ ፊት አስገድዶ ቢደፍር በአንድ ድርጊት 4 ወንጀሎችን እንደፈጸመ እንረዳለን፡፡ በመሆኑም የወንጀል ህግ አንቀጽ 620(1) ለአስገድዶ መድፈር ወንጀሉ፣ አንቀጽ 652(1) ለአመንዝራነት ተግባሩ፣ አንቀጽ 654 በዘመዳሞች መካከል ለሚፈጸም ግብረ ስጋ ግንኙነት እና አንቀጽ 639(1) ለመልካም ስነ-ምግባር ተቃራኒ የሆነ ተግባርን በአደባባይ መፈጸም ወንጀል በሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ከላይ በምሳሌው የተጠቀሱትን ወንጀሎች ባህሪ ስንመለከት ሁሉም ውጤቶች ከአንድ የወንጀል ድርጊትና ከአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የመጡ ናቸው፡፡ አስገድዶ መድፈር ወንጀሉ ግዙፋዊ ውጤት ያስከተለ ሲሆን ሌሎቹ የወንጀል ውጤቶች ግን ግዙፋዊ ያልሆኑ ናቸው፡፡ ወንጀሎቹ የመጡት በአንድ ድርጊትና በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ሲሆን የወንጀል ህጉ አንቀፅ 620(1) የአስገድዶ መድፈር ጥቃቱን የሚሸፍን ቢሆንም ዝምድናውን፣ የወንጀል አድራጊውን የጋብቻ ሁኔታ፣ እንዲሁም የግብረ ስጋ ግንኙነት በህዝብ ፊት መፈጸምን አይሸፍንም፡፡ በሌላ በኩል በጣምራ ወንጀሎች የሚገኙት ሁሉም ውጤቶች ግዙፋዊ ውጤት የሚሆኑበት አጋጣሚም አለ፡፡ ለምሳሌ አቶ ተጫኔ በቂም በቀል ተነሳስቶ፣ ጨለማን ተገን በማድረግ የ አቶ አጎናፍርን ቤት ለማቃጠል በማሰብ በእሳት ቢያቃጥልና በቃጠሎውም የ አቶ አጎናፍር ትልቅ ልጅ ቢሞትና ትንሹ ልጁ ቀላል የአካል ጉዳት ቢደርስበት እንዲሁም የአቶ አጎናፍር ሚስት ከባድ የአካል ጉዳት ቢደርስባት የተፈጸመው ተግባር አንድ ብቻ /ቤት ማቃጠል/ ቢሆንም ሁሉም የወንጀል ውጤቶች ለዓይን የሚታዩና የሚዳሰሱ ልዩ ልዩ

ግዙፍ ውጤቶች እንደሆኑ እንመለከታለን፡፡ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 58(1-ለ) መሰረት የአቶ አጎናፍርን ቤት በማቃጠሉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 494(1)፣ የአቶ አጎናፍርን ትልቅ ልጅ ለሞት በማብቃቱ በወንጀል ህግ አንቀጽ 540/539/1-ሀ/፣ በአቶ አጎናፍር ትንሽ ልጅ ላይ ቀላል የአካል ጉዳት በማድረሱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2-ሀ) እንዲሁም በአቶ አጎናፍር የትዳር አጋር ላይ ባደረሰው ከባድ የአካል ጉዳት በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 555/ለ/ መሰረት 4 ተደራራቢ ክስ ሊቀርብበትና ሊቀጣ ይችላል፡፡ ነገር ግን አቶ ተጫኔ ቤቱን ሲያቃጥል በቤት ውስጥ ሰዎች የሉም በሚል እምነት ከሆነና ሰው ሊኖር እንደሚችል መጠራጠር የሚገባው ከነበረ አስቦ ቤት በማቃጠልና በወንጀል ህግ አንቀጽ 59(1-ለ) መሰረት በቀሪዎቹ ወንጀሎች በቸልተኝነት ሰው መግደልና በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል 3 ክስ ቀርቦበት የሚቀጣ ይሆናል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ተደራራቢ ጣምራ ወንጀሎች የሚመጡት በሶስት መንገድ ሲሆን አንድም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 66/1-ሀ/ መሰረት ሁሉም ጣምራ ወንጀሎች ታስቦ በሚፈጸም የወንጀል ድርጊት ወይም በዚሁ ህግ በአንቀጽ 66/1-ለ/ መሰረት የተወሰኑት ወይም ቢያንስ አንዱ ታስቦ በሚፈጸምና ቀሪዎቹ ወንጀሎች በቸልተኝነት ሲፈጸሙ ሲሆን ሌላው በአንቀጽ 66/1-ሐ/ መሰረት ሁሉም ጣምራ ወንጀሎች በቸልተኝነት ሲፈጸሙ ነው፡፡ ወንጀል አድራጊው ጣምራ ወንጀሎቹን  የፈጸመው ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በማቀድ ወይም ቀድሞውኑ አውቆ በመቀበል ወይም በቸልተኝነት በሆነ ጊዜ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 187 መሰረት ቅጣት አጣጣሉ መሰረታዊ ልዩነት ስለሚያስከትል ጣምራ ወንጀሎቹ የተፈጸሙት ታስቦ ወይም በቸልተኝነት ነውን የሚለውን ነጥብ በጥንቃቄ ማየት ይገባል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ድርጊቶች በአንድ የወንጀል ተግባር ተፈጽመው ጣምራ ወንጀሎች ሊፈጸሙ የሚችሉት በወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ለ) ላይ የተቀመጡት መስፈርቶች ሲሟሉ ሲሆን በተጨማሪም ህግ አውጭው በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ድንጋጌዎችን በማስቀመጥ ድርጊቶቹ በአንድ የወንጀል ተግባር የመጡና በተደራራቢነት ሊያስጠይቁ የሚችሉ ድንጋጌዎችን አመልክቷል፡፡ ባለሙያዎች በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ውስጥ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች በመመልከት ድርጊቱ ተደራራቢ ወንጀል የሚያስከትል መሆኑ በልዩ ክፍሉ ተደንግጎ በተገኘ ጊዜ ተደራራቢ ክስ የማቅረብ ሀላፊነት አለባቸው ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ በወንጀል ህግ አንቀጽ 547(1) መሰረት እርጉዝ ሴትን በህገ ወጥ መንገድ እንድታስወርድ በማሰብ ህገ ወጥ ተግባር የፈጸመ ወንጀል አድራጊ ድርጊቱ የአካል ጉዳት ካስከተለ እንደ ጉዳቱ ከባድነት በአካል ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል በአንቀጽ 555/556 በተደራቢነት የሚጠየቅ

ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 349(2) ስር እንደተገለጸው ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የመንግስትን ግብር ወይም ቀረጥ ለመክፈል እምቢተኛነት ወንጀል ሲሆን እምቢተኛነቱ ዛቻን፣ የሀይል ስራን፣ የእጅ እልፊትን ወይም በጦር መሳሪያ መገልገልና መሳሪያ አንስቶ የመቃጣትን ወይም ሁከትን መፍጠርን አስከትሎ እንደሆነ ጉዳዩን በሚመለከተው ድንጋጌ መሰረት በተደራራቢነት እንደሚያስቀጣ ተመልክቷል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 441 መሰረት አንድ የመንግስት ሰራተኛ የስራ ግዴታው የሆነውን ተግባሩን እንዳያከናውን በዛቻ በማስገደድ ወይም በሀይል ደርጊት ያሰናከለ ወይም ይህን ግዴታውን እንዲያከናውን ወይም ማድረግ የሌለበትን እንዲያደርግ ያስገደደ እንደሆነ የእጅ እልፊቱ ወይም የሀይል ተግባሩ በተባዳዩ ላይ የአካል ጉዳት ወይም የጤንነት ጉድለት ያስከተለ እንደሆነ ድርጊቱ በተደራራቢነት ተፈርጆ አግባብ ባለው ድንጋጌ መሰረት ተጠያቂ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም በአንቀጽ 444 ስር እንደተመለከተው ጠቋሚዎችና ምስክሮችን በሚመለከት የሚፈጸም ተግባር ወንጀል ሲሆን መረጃ በሰጠው ሰው ላይ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ ወንጀሉ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም የጤና ጉዳትን ወይም ሞትን አስከትሎ እንደሆነ አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሰረት በተደራራቢ ወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ በአንቀጽ 587 መሰረት ሴትን መጥለፍ ወንጀል መሆኑ የተደነገገ ሲሆን የጠለፋ ድርጊቱን ወንጀል ተከትሎ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ ድርጊቱ በተደራራቢነት ክስ ሊቀርብ እንደሚገባ በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ 2 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ባለሙያዎች ጣምራ የወንጀል ድርጊት መፈጸም አለመፈጸሙን በወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ለ) ከተመለከቱት መለኪያዎች በተጨማሪ በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል በተደራራቢ ወንጀል ሊያስጠይቁ እንደሚችሉ ህግ አውጭው ያስቀመጣቸውን ድንጋጌዎች በጥንቃቄ በማየት ወንጀል አድራጊዎች በፈጸሙት የወንጀል ተግባር ልክ እንዲቀጡ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በወንጀል ህጉ አንቀጽ 60/ለ/ መሰረት አንድ ሰው በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ ተደራራቢ ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ በአንቀጽ 65 እና 187/1-2/ ቅጣቱ ከብዶ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡ በአማራ ክልል ባሉ የዐቃብያነ ህግ መስሪያ ቤቶችና ፍርድ ቤቶች ያለውን አሰራር ለማሳየት የተወሰኑ መዛግብትን ወስደን ስንመለከት በአንቀጽ 60(ለ) ስር ያለውን መርህ በአግባቡ ባለመረዳት በተግባር ጉድለቶች ይስተዋላሉ፡፡ በአንድ የምርመራ መዝገብ ወንጀል አድራጊዎቹ ሰው ለመግደል በማሰብ የወረወሩት ቦንብ በግል ተበዳይ ላይ ከባድ ጉዳት ያደረሰና በንብረት ላይ ጉዳት የደረሰ

መሆኑን የምርመራ መዝገቡ እያመለከተ ክስ የቀረበው በከባድ ሰው መግደል ወንጀል ብቻ ነው[25]። ከዚህ በተጨማሪ በአንድ የምርመራ መዝገብ ላይ ወንጀል አድራጊው የውንብድና ወንጀል እና ተራ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል የፈጸመ መሆኑን የምርመራ መዝገቡ እያመለከተ በወንጀል አድራጊው ላይ የቀረበው ክስ የመግደል ሙከራ ወንጀል ብቻ ሲሆን በውንብድና ወንጀሉ ክስ እንዳልቀረበበት መዝገቡ ያመለክታል[26]። በተጨማሪ ዐቃቤ ህግ በወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ለ) መሰረት በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት የተለያዩ ዓላማ ያላቸው አዋጆችና ድንጋጌዎች ተጥሰዋል በሚል እምነት ወንጀል አድራጊዎችን በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 31(1)ና አንቀጽ 60(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ህጋዊ /የጸና/ የንግድ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ስራ በሚያከነውኑ ወንጀል አድራጊዎች ላይ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 43 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ መሰረታዊ ምርቶችን በማከማቸት፣ ይዞ በመገኘት፣ በማጓጓዝ፣ በመደበቅ የመሳሰሉ ተግባሮችን በፈጸሙ ወንጀል አድራጊዎች በሁለቱም አዋጆች ስር የተቀመጡትን ድንጋጌዎች በመጥቀስ ዓቃቤ ህግ 2 ተደራራቢ ክስ ሲያቀርብ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ከሚያየው ፍርድ ቤት እስከ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ድረስ ድርጊቱ የተፈጸመው በመነገድ አላማ መሆኑን ዐቃቤ ህግ አላስረዳም በሚልና ድርጊቱ አንድ እስከሆነ ድረስ ድርጊት ፈጻሚው የንግድ ፈቃድ ቢኖረውም ባይኖረውም ድርጊቱ በአንድ አንቀጽ ሊጠቃለል የሚችል በመሆኑ በአንቀጽ 61(1) መሰረት ሊጠቃለል ይገባል በሚል በአንድ ክስ በማጠቃለል አልፎ አልፎ ውሳኔ ሲሰጡ ይስተዋላል[27]። እንደ ጸሀፊው እምነት ፍርድ ቤቶቹ የሚሰጡት ውሳኔ ተገቢ አይደለም። ምክንያቱም በህግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተፈጸሙት በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ ሲሆን ወንጀል አድራጊው ተመሳሳይ ባህሪ ባላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች የማይቀጣ መሆኑን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 61/1/ ስር ተመልክቷል። ይህ ማለት የተፈጸመው ድርጊት በተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች ስር የተጠቀሰ ቢሆንም እንኳ አንድ ባህሪ እና ይዘት ኖሮት በአንድ የህግ ድንጋጌ ስር የሚሸፈን ከሆነ ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ ከአንድ በላይ በሆኑ የህግ

[25]የሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ፣ የወ/መ/ቁ 59/07፣ ዐቃቤ ህግ እና እነ ጠቅል አየለ /2 ሰዎች/
[26]የሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ፣ የወ/መ/ቁ 206/07 ዐቃቤ ህግ እና ንጉሴ ገነነ
[27]በሰሜን ሸዋ ዞን ንግድ መምሪያ፣ የንግድና ሸማቾች ጥበቃ ዐቃቢያነ ህጎች ጋር የተደረገ ውይይት ሚያዚያ 3/2008 ዓ.ም

ድንጋጌዎች ክስ ሊቀርብበትም ሆነ ቅጣት ሊጣልበት አይችልም።[28] ነገር ግን አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ (31-1) የሚያስቀምጠው አንድ ነጋዴ ህጋዊ /የጸና/ የንግድ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ስራ ማከናወንን ወንጀል በማድረግ ነጋዲዎች ወደ ንግድ ስራ ከማግባታቸው ፊት ለንግድ ስራ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው እንዲገቡ በማሰብ የተደነገገ ነው። በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 43 ስር የተገለጸው መንግስት መሰረታዊ ምርቶች በማለት የሚያስቀምጣቸውን ምርቶች ከመደበኛ የገበያ ስርአት ውጭ ገበያ ለማረጋገት ሲባል መንግስት በሚወስነው የስርጭት ስርአት እንዲሰራጩ ከተፈቀደው ውጭ ሌላ ሰው ሲነግድ፣ ሲያከማች፣ ሲያጓጉዝ ከተገኘ ወንጀል መሆኑ የተደነገገ ሲሆን የክልከላው ዋና ዓላማም እነዚህ ምርቶች በመደበኛው የግብይት ስርዓት እንዲያልፉ ቢደረግ በገበያ ውስጥ እጥረት ሊፈጠር ይችላል ከሚል እምነት ስላለ ይህን ለመከላከል ሲባል ነው። በመሆኑም የሁለቱ አዋጆችና በስራቸው የተቀመጡት ድንጋጌዎች አላማ የተለያዩ ስለሆነና የአንዱ አዋጅና ድንጋጌ ይዘት በሌላው አዋጅና ድንጋጌ ስር ስለማይጠቃለል ፍርድ ቤቶች በአንድ ድንጋጌ ስር ይጠቃለላል በሚል የሚሰጡት ውሳኔ ተገቢ ያልሆነና ሁለቱ አዋጆች የወጡበትን አላማ ያላገናዘበ ነው። ሌላው በፍርድ ቤቶችና በባለሙያዎች ዘንድ ሰፊ ልዩነት ሲፈጥርና የተለያዩ ውሳኔ ሲሰጥ የሚስተዋለው በወንጀል ህግ አንቀጽ 572 ስር በተቀመጠው ድንጋጌ ላይ ነው። የወንጀል ህግ አንቀጽ 572(1) ማንም አሽከርካሪ ወይም እግረኛ በቸልተኝነት የትራፊክ ደንብን በመጣስ የሌላን ሰው ህይወት፣ አካል፣ ጤና ወይም ንብረት ለአደጋ ያጋለጠ እንደሆነ አደጋው ባይደርስም እንደሚቀጣ ይደነግጋል። የዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር 2 ድርጊቱ በሰው ህይወት፣ አካል፣ ጤና ወይም ንብረት ላይ ጉዳት አድርሶ ከሆነ አግባብነት ያለው ድንጋጌና የተጣሰው የትራፊክ ደንብ ድንጋጌ በተደራራቢነት ተፈጸሚ እንደሚሆኑ ተቀምጧል። ይህ ድንጋጌ በተሻረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ ያልነበረና አሁን ስራ ላይ ባለው የወንጀል ህግ ውስጥ እንዲካተት የተደረገ ሲሆን የመካተቱ ዋነኛ አላማም አሽከርካሪዎች የትራፊክ ደንብን በመጣስ በሰው ህይወት፣ ጤና ወይም ንብረት ላይ ቅርብ የሆነ አደጋ በመፍጠራቸው /potential danger/ ብቻ እንዲቀጡና ከተግባራቸው እንዲታቀቡ ለማድረግ በማሰብ የተደነገገ ነው። ነገር ግን ቅርብ የሆነ አደጋ ከመፍጠር አልፎ አደጋው እውን ሆኖ በሰው ህይወት፣ ጤና፣ አካል ወይም ንብረት ላይ አደጋ ከደረሰ ክስ እንዴት ይቅረብ በሚለው ዙሪያ በባለሙያዎች ዘንድ ሰፊ ልዩነቶች አሉ። አንዳንድ ባለሙያዎች አንደሚሉት ወንጀል አድራጊው ግልጽ የሆነ የትራፊክ

[28]Philippe Graven, An Introduction to Ethiopian Penal Law( Article 1- 81), Faculty of Law, Haile Silase I University, Adiss Ababa, Ethiopia 1965, p.165

ደንብ በመተላለፍ የሰዎች ህይወት፣ ጤና ወይም ንብረትን ለአደጋ ካጋለጠ ወንጀል መሆኑ ተደንግጓል፤ ድርጊቱም ጉዳት አስከትሎ ከሆነ የተጣሰው ድንጋጌ መሰረት ተደርጎ ለአደጋ በማጋለጡ የተጣሰው የትራፊክ ደንብና የወንጀል ህግ አንቀጽ 572(1) ተጠቅሶ እንዲሁም ለደረሰው ጉዳት አግባብ የሆነው ድንጋጌ ተጠቅሶ 2 ተደራራቢ ክስ ሊቀርብ ይገባል በሚል ይከራከራሉ[29]። በሌላ በኩል በዚህ ሀሳብ የማይስማሙ ባለሙያዎች እንደሚሉት ለአደጋ ማጋለጥ ወንጀል ተደርጎ የተቀመጠው የወንጀል ድርጊቱ በሰው ህይወት፣ ጤና ወይም ነብረት ላይ ጉዳት ባይደርስም የወንጀል አድራጊው እንቅስቃሴ አደጋ የሚፈጥር በመሆኑ ብቻ ይህንን ድርጊት ለመግታት ድርጊቱ ባይደርስም ወንጀል ተደርጎ ተፈርጇል እንጂ ድርጊቱ አደጋ ከመፍጠር አልፎ ድርጊቱ እውን ከሆነ ሊከሰስ የሚገባው የተጣሰው የትራፊክ ደንብና የደረሰውን ጉዳት የሚሸፍነው ድንጋጌ ተጠቅሶ በአንድ ክስ መሆን ይገባዋል እንጂ አድራጎቱ አደጋ ከመፍጠር አልፎ በሰው ህይወት፣ ጤንነት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ከደረሰ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 572(1) ተጠቅሶ ለአደጋ ማጋለጥ በሚል በተደራራቢነት ክስ ይቅረብበት ማለት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 572(1) እና በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር 2 ስር ህግ አውጭው ያስቀመጠውን አላማ አለመገንዘብ ነው በማለት ይከራከራሉ። በተግባርም በአንዳንድ ፍርድ ቤቶች እንደሚስተዋለው ዐቃቤ ህግ 2 ተደራራቢ ክስ ሲያቀርብ ፍርድ ቤቶች ጉዳቱ ከደረሰ ክስ ሊቀርብ የሚገባው ጉዳቱን በሚመለከተው ድንጋጌ ብቻ እንጂ በደረሰ ጉዳት ላይ ለአደጋ ማጋለጥ በሚል በተደራራቢነት ክስ ማቅረብ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ በ 1 ክስ ብቻ ውሳኔ ሲሰጡ ይስተዋለለል[30]። ይህን ነጥብ በሚመለከት የጸሀፊው እምነት ግልጽ የሆነ የትራፊክ ደንብ ተጥሶ የሰውን ህወት፣ ጤንነት ወይም ንብረት ላይ አደጋ ደርሶ ከሆነ ወንጀል አድራጊው ሊጠየቅ የሚገባው የተጣሰው የትራፊክ ደንብና አግባብነት ባለው የወንጀል ህጉ ድንጋጌ ተጠቅሶ በ 1 ክስ ብቻ ነው የሚል ነው። ምክንያቱም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 572(1) ስር ያስቀመጠው ክልከላ አሽከርካሪዎች አደጋ ባያደርሱም ለአደጋ ማጋለጣቸው ብቻ ወንጀል እንዲሆን በማሰብ የተደነገገ ነው። ነገር ግን ለአደጋ ከማጋለጥ አልፎ አደጋው ከደረሰ የደረሰውን አደጋ የሚመለከተው ድንጋጌ ብቻ ተጠቅሶ ክስ መቅረብ አለበት የሚል ነው። በሌላ በኩል የአሽከርካሪው አድራጎት በተወሰኑ ሰዎች ላይ ጉዳት አድርሶ በሌሎች ላይ ለአደጋ አጋልጦ ካለፈ ግን በወንጀል አድራጊው ላይ ለአደጋ በማጋለጥና አደጋ በማድረስ በ 2 ተደራራቢ ክስ

[29]በባህር ዳር ከተማ ከግንቦት 29-30/2008 ዓ.ም በአማራ ክልል ከሁሉም ዞኖች ከመጡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞችና የዞን ዐቃብያነ-ህጎች ጋር የተደረገ የጋራ ውይይት

[30]በደብረ ብርሀን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀል የስራ ሂደት ውስጥ ከሚሰሩ ዳኞች ጋር የተደረገ ውይይት፣ መጋቢት 4/2008 ዓ.ም

ሊቀርብበት እንደሚገባ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ለምሳሌ አንድ አሽከርካሪ በፍጥነት ሲያሽከረክር መኪናው በመገልበጡ በ 3 ሰዎች የአካል ጉዳት ቢደርስና በመኪናው ላይም ጉዳት ደርሶ በሌሎች ተሳፍረው በነበሩ 7 ሰዎች ላይ ጉዳት ሳይደርስ ቢቀር ተደራራቢ ወንጀሉ በወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ለ) መሰረት በአንድ ድርጊት የተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች የተጣሱ ስለሆነ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የወንጀል ህጉ አንቀጽ 559(2) ተጠቅሶ 3 ክስ፣ ለንብረት ጉዳቱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 856 ተጠቅሶ 1 ክስ እንደሁም 7 ሰዎች ለአደጋ የተጋለጡ ስለሆነ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 572(1) ተጠቅሶ 7 ክስ በድምሩ 11 ክስ ይቀርብበታል ማለት ነው፡፡

**ሐ. የተጎጂዎች መደራረብ (Victims concurrence)**

ይህ ዓይነቱ ተደራራቢ ወንጀል በወንጀል ህጋችን በአዲስ መልኩ የተካተተ የወንጀል ተደራራቢ ዓይነት ሲሆን በ 1949 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ አልነበረም፡፡ ይህ አይነት ተደራራቢ ወንጀል የተጎጂዎች መደራረብ በሚል ይጠራል። ምክንያቱ ደግሞ ድንጋጌው የሚያተኩረው አንድ ድርጊት በብዙ ሰዎች መብት ላይ ተመሳሳይ ጉዳት ስለሚያስከትል ነው፡፡ በአንቀጽ 60(ሐ) ስር የተቀመጠው መመዘኛ “በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ወይም ችልተኛነት፤ አንድን የህግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ፤ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ላይ፤ ተመሳሳይ ዓይነት ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ነው” በማለት ያስቀምጣል፡፡ በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ወይም ችልተኛነት በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ፣ የተጣሰው አንድ የህግ ድንጋጌ ሲሆን፣ የደረሰው ጉዳት ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት /ጥቅም/ ላይ ሲሆን፣ ጉዳቱም አንድ አይነት መሆን ይኖርበታል፡፡ ነገሩን በምሳሌ ለመግለጽ ያክል አንድ አሽከርካሪ ከላይ የጫነው ጎማ በአግባቡ ባለመታሰሩ ወድቆ ሁለት ሰዎች ላይ ጉዳት ቢያደርስ ድርጊቱ አንድ ነጠላ ድርጊት ቢሆንም በአንድ ድርጊት በሁለት ሰዎች መብት ላይ ጉዳት ስላደረሰ የወንጀል ህግ አንቀጽ 559(2) ተጠቅሶ 2 ተደራራቢ ክስ ይቀርብበታል ማለት ነው፡፡ በሌላ ምሳሌ አንድ ወንጀል አድራጊ ሰው ለመግደል አስቦ በቆሙ ሰዎች ላይ ቦንብ ወርውሮ ሁሉንም ቢገድል ድርጊቱ በአንቀጽ 60(ሐ) ስር የሚያርፍ ሲሆን የተፈጸመው ወንጀል በብዙ ሰዎች ላይ የሰው መግደል ወንጀል ስለሆነና ተመሳሳይ ጉዳት በመሆኑ በወንጀል አድራጊው ላይ 1ኛ፣ 2ተኛና 3ተኛ ክስ በሚል በሞቱት ሰዎች ቁጥር ልክ የሰው መግደል ወንጀል ክስ ይቀርባል ማለት ነው፡፡ ይህ ዓይነት ተደራራቢ ወንጀል በ 1949 በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ ስላልነበረ የተጎጂዎች መደራረብ ሲያጋጥም ለሁሉም ወንጀሎች አንድ ክስ ብቻ ይቀርብ ነበር፡፡ አሁን ስራ ላይ ያለው የወንጀል ህግ በቀድሞ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ ይስተዋል

የነበረውን ችግር ስለፈታ በተጎጂዎቹ ቁጥር ልክ ክስ እንዲቀርብ ተደርጓል። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ውስጥ ይህ አይነት ተደራራቢ ወንጀል እንዲካተት የተደረገበት ምክንያት አንድ ወንጀል አድራጊ በብዙ ሰዎች መብት ላይ በአንድ ጊዜ ላደረሰው ጉዳት በተደራራቢ ወንጀል ሳይጠየቅ እንደ ነጠላ ድርጊት ተቆጥሮ ለአንዱ ድርጊት ብቻ የሚቀጣ ከሆነ ዜጎች በህገ መንግስት የተደረገላቸውን በህይወት የመኖር መብት፣ የአካል ደህንነት መብት፣ የንብረት መብት ጥበቃ ዋስትና አለመስጠት ነው እንዲሁም ቅጣት ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት የሚለውን መርህም የሚጻረር ነው። በማህበረሰቡ ውስጥም ብዙ ወንጀሎች የፈጸመ ወንጀል አድራጊ ላይ የሚሰጠው የህሊና ፍርድ ቅጣቱ በቂ ስለማይሆን ማህበረሰቡ በፍትህ ስርዓቱ ላይ እምነት እንዳይኖረው ያደርጋል። በሌላ በኩል በጣምራ የወንጀል ተግባር አንድ ወንጀል አድራጊ የተወሰኑትን ወንጀሎች አስቦና ሌሎቹን በቸልተኛነት ሲፈጽም ቅጣቱ እንዲከብድ ተደርጎ በአንድ ድርጊት ብዙ ሰዎች ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ወንጀል የፈጸመ ወንጀል አድራጊ አንድ ክስ ብቻ ቀርቦበት ቅጣቱ እንዲቀል የሚደረግ ከሆነ ቅጣት ***የአድል ጉዳይና አመክንዮት የሌለው*** ይሆናል ከሚል እምነት ነው። ለምሳሌ 'ሀ' ሚስቱን የወሸመበትን 'ለ' ን ለመግደል በማሰብ በቤት ውስጥ ተኝተው እንዳለ ጥይት በመተኮስ 'ለ' ን ቢገድልና በራሱ ሚስት ላይ የአካል ጉዳት ቢያደርስ በአንቀጽ 60(ለ) መሰረት ጣምራ ወንጀል ስለፈጸመ በሰው መግደልና በአካል ጉዳት ማድረስ 2 ክስ ቀርቦበት ከፍተኛ ቅጣት መቀጣት አለበት እንደ ማለት ሲሆን ነገር ግን ሁለቱም ሰዎች ሞተው ቢሆን ኖሮ አንድ ክስ ይቀርብበትና በአንድ ሰው መግደል ወንጀል ብቻ ዝቅተኛ ቅጣት ይቀጣል ማለት ነው። በሌላ ምሳሌ ቦንብ ጥሎ አራቱንም ሰዎች መግደልና ቦንብ ጥሎ 2ቱን መግደልና 2ቱ ላይ የአካል ጉዳት ማድረስን በሚመለከት ቅጣቱ የሚቀለው 4ቱንም በገደለው ላይ ሲሆን 2ቱን ገድሎ በ2ቱ ላይ የአካል ጉዳት ያደረሰው ወንጀል አድራጊ ቅጣት ይከብድበታል እንደ ማለት ሲሆን ቅጣት ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት ከሚለው መርህ ጋርም አብሮ አይሄድም።

በወንጀል ህጉ አንቀጽ 60(ሐ) ስር እንደተመለከትነው በአንድ ድርጊት በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ወይም ቸልተኛነት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ላይ ተመሳሳይ የሆነ ጉዳት በደረሰ ጊዜ በተጎጂዎቹ ሰዎች ቁጥር ልክ ክስ መቅረብ እንዳለበት ተመልክተናል። ይህ መርህ ሲሆን የዚህ መርህ ልዩ ሁኔታ ህግ አውጭው በወንጀል ህግ አንቀጽ 543/3/ ስር ያመለከተው ነው። በዚህ ድንጋጌ መሰረት የአሸከርካሪነት ተግባሩን በአግባቡ ባለመወጣት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ሲሞቱ ድርጊቱን በራሱ የቅጣት ማክበጃ አድርጎ በመውሰድ

አንድ ክስ እንዲቀርብና ቅጣት እንዲጣል ህግ አውጭው በልዩ ሁኔታ እንዳስቀመጠ ማየት ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ በአዋጅ ቁጥር 909/2007 ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን እና ስደተኞችን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ በአንቀጽ 6 ስር እንዳመለከተው የወንጀል ድርጊቱ ተጎጂ የሆኑት ሰዎች ቁጥር በስፋትና በብዛት በሆነ ጊዜ ቅጣቱ ከብዶ እንደሚወሰን ያሳያል፡፡ ይህ አዋጅ ወጥቶ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የወንጀል ህግ አንቀጽ 98 ተጠቅሶ ክስ ይቀርብ በነበረበት ጊዜ ክሱ ይቀርብ የነበረው ጉዳት በደረሰባቸው ሰዎች ቁጥር ልክ እንደነበር የውሳኔ መዛግብቶች ያሳያሉ፡፡ አሁን በተግባር እየተሰራ ያለው የድርጊቱ ሰለባ /ተጎጂዎች/ ቁጥር ሁለትና ከዚያ በላይ በሆነ ጊዜ አንድ ክስ ብቻ በማቅረብ ሲሆን ድንጋጌው በራሱ ቅጣት ማክበጃ ሆኖ ተደንግጓል ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ አዋጅ ጋር በተገናኘ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የሚያመለክተው በህገ ወጥ መንገድ ሰዎችን የሚያዘዋውሩ አዘዋዋሪዎችን ሲሆን በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 4 ስር እንደተገለጸው ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን በሚመለከት ሌሎች የተለያዩ አካላት ሊሳተፉ እንደሚችሉ በማመን ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን በገንዘብ፣ በሀሳብ፣ በተሸከርካሪ፣ የመኖሪ ቤት በማቅረብና በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ድጋፍ የሚያደርጉ አካላትና በወንጀሉ የተሳተፉ አካላት በህገ ወጥ የሰዎች ማዘዋወር ወንጀል ሊጠየቁ እንደሚገባ አዋጁ ያመለክታል፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ ቅጣቱ ከብዶ የሚወሰነው በአዘዋዋሪዎቹ ላይ ብቻ ሲሆን የተሸከርካሪና ሌሎች ድጋፍ ባደረጉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ክስ የሚቀርበው የወንጀል ህጉ አንቀጽ 60(ሐ) በሚያስቀምጠው መሰረት በተጎጂዎቹ ቁጥር ልክ ነው ወይስ በአዋጁ አንቀጽ 6 መሰረት ነው የሚለው ግልጽ አይደለም፡፡ ይህን ነጥብ በሚመለከት ባለሙዎች ሁለት አይነት ሀሳቦችን ያስቀምጣሉ፡፡ አንዳንዶቹ እንደሚሉት በአዋጁ አንቀጽ 6 ስር በከባድ ሁኔታ ክስ ሊቀርብባቸው የሚችለው በአዋጁ አንቀጽ 3 እና 5 ላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኝ በአዘዋዋሪዎቹ ላይ ብቻ እንደሆኑ በህጉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በአዋጁ የትርጉም ክፍል ላይ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ተግባርን የሚረዱ ሰዎች በህገ ወጥ አዘዋዋሪ ሊጠየቁ እንደሚችሉ በግልጽ የተመለከተ ሲሆን እነዚህ በህገ ወጥ ማዘዋወር ተግባሩ የተሳተፉ ወንጀል አድራጊዎች ክስ እንዴት ሊቀርብ ይችላል የሚለውን ህግ አውጭው በዝምታ ማለፉ ክፍተት የፈጠረ ቢሆንም በዚሁ አዋጅ በአንቀጽ 6 ስር በተጠቀሰው መሰረት ክስ ይቅረብባቸው ማለት ግን ከህግ አውጭው ሀሳብ መራቅ ነው በማለት ይከራከራሉ[31]፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች እንደሚሉት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 60(ሐ) ስር የተቀመጠው ጠቅላላ መርህ ስለሆነ ሌሎች

[31]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 29 የተጠቀሰው

አዋጆች በግልጽ የተለየ የክስ አቀራረብ እንዲኖር እስካላስቀመጡ ድረስ በህገ ወጥ ሰዎች ዝውውር ላይ ተሳታፊ በሆኑ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ክስ ሊቀርብ የሚገባው በተጎጂዎቹ ቁጥር ልክ ሊሆን እንደሚገባ ያስቀምጣሉ[32]። በሌላ በኩል ይህን ሀሳብ የሚቃወሙ ባለሙያዎች እንደሚሉት ህገ ወጥ ሰዎች ዝውውርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ልዩ አዋጅ ስለሆነ እና የዚሁ ህግ አንቀጽ 6 ላይ አዘዋዋሪዎችን በሚመለከት የተጎጂዎቹ ቁጥር ብዙ በሆነ ጊዜ የቅጣት ማክበጃ የቀረበው በማዘዋወሩ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ለተሳተፉ ወንጀል አድራጊዎች ተፈጻሚ መሆን ይገባዋል። ምክንያቱም ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን በሚመለከት አዋጁ ልዩ ህግ ስለሆነ ወደ ወንጀል ህ ጠቅላላ መርህ መሄድ አይገባም ሲሉ ክርክራቸውን ያቀርባሉ[33]። እንደ ጸሀፊው እምነት በአዋጁ አንቀጽ 6 ላይ ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን የተፈለገው አዘዋዋሪዎችን የሚመለከት መሆኑ በግልጽ የተቀመጠ ስለሆነ ሌሎች በህገ ወጥ ዝውውር ተግባሩ ውስጥ ተሳታፊ ሆነው የሚገኙ ወንጀል አድራጊዎች በወንጀል ህጉ አንቀጽ 60(ሐ) መሰረት በተጎጂዎች ቁጥር ልክ ክስ ቀርቦ ሊቀጡ ይገባል የሚል ነው። ምክንያቱም የወንጀል ህጉ ላይ የተመለከቱ መርሆዎች በግልጽ በልዩ ህግ በተለየ መንገድ እንዲፈጸም ካልተመለከተ በስተቀር በወንጀል ህጉ ውስጥ የተቀመጡት መርሆዎች ጠቅላላ መርሆዎች ስለሆኑና ወንጀል ነክ ላላቸው አዋጆች ሁሉ ተፈጻሚ ስለሆኑ ልዩ አዋጆች ክፍተት በሚኖራቸው ጊዜ ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል ከሚል መነሻ ነው።

የወንጀል ህግ አንቀፅ 60/ሐ/ን በሚመለከት በተግባር በዐቃብያነ ህግ መስሪያ ቤትና በፍርድ ቤቶች በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከት በድንጋጌው ስር በተመለከተው መርህ መሠረት በተበዳዮቹ ቁጥር ልክ በተደራራቢነት ክስ መቅረብ እየተገባው ባለሙያዎች ይህን ድንጋጌ በአግባቡ ባለመረዳት አልፎ አልፎ በተጎጂዎች ቁጥር ልክ ክስ አለማቅረብ፤ ክስ ቢቀርብም ፍርድ ቤቶች በአንድ ክስ የሚጠቃለል ነው በማለት ውሳኔ እንደሚሰጡ መዝገቦች ያመለክታሉ። ለምሳሌ በአንድ የተሸከርካሪ አደጋ ወንጀል ዐቃቤ ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ሐ) ን መሰረት በማድረግ በ 6 ሰዎች ላይ በደረሰው የአካል ጉዳት ዐቃቤ ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 559(2) ስር የተመለከተውን በመጥቀስ 6 ክስ ያቀረበ ሲሆን ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ሁሉም ድርጊት በአንድ ክስ ሊጠቃለል ይገባል በሚል በአንድ ክስ አጠቃሎ ውሳኔ

[32] ዝኒ ከማሁ
[33] ዝኒ ከማሁ

ሰጥቷል[34]። በተመሳሳይ በአንድ የማታለል ወንጀል የማታለል ወንጀሉ የተፈጸመው በሁለት የግል ተበዳይዎች ላይ መሆኑን የምርመራ መዝገቡ እያመለከተ የቀረበው ክስ አንድ ብቻ እንደሆነ መዝገቡ ያሳያል[35]። በሌላ መዝገብ ወንጀል አድራጊዎች በአንድ ድርጊት በተለያዩ ሰዎች መብት ላይ ተመሳሳይ ጉዳት ያደረሱ መሆኑን የምርመራ መዝገቡ የሚያመለክት ቢሆንም አንድ ክስ ብቻ ቀርቦ ውሳኔ እንደተሰጠ መዝገቡ ያሳያል።[36]

### 2.3 ፍጹም ተደራራቢ ያልሆኑ ወንጀሎች (imperfect concurrence)

ከወንጀል ህግ መርሆዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው አንድ ወንጀል አድራጊ ሊቀጣ የሚገባው ወንጀል ለመፈጸም ባለው ሀሳብ ልክ ነው የሚለው ነው። የወንጀል አድራጊው ወንጀል የመፈጸም የሀሳብ ሁኔታ የሚረጋገጠው ደግሞ በወንጀል አድራጊው የወንጀል ድርጊት የተጣሱ መብቶች ወይም ህገ ወጥ ድርጊቶችና ወንጀል አድራጊው ድርጊቱን በሚፈጽምበት ጊዜ ያደረገውን እንቅስቃሴ ከአካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣመር በሚገኝ የፍሬ ነገር ትንታኔና ነው።

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 60 ስር የተመለከተው መርህ አንድ ወንጀል አድራጊ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ግዙፋዊ ወይም ጣምራ ወንጀሎችን ሲፈጽም በተደራራቢ ወንጀሎች ተጠያቂ የሚሆንበትን አግባብ ሲሆን በዚሁ ህግ በአንቀጽ 61 ስር የተደነገገው ደግሞ የተወሰኑ ድርጊቶች /ወንጀሎች/ በባህሪያቸው ተደራራቢ ቢመስሉም ተዳራራቢ ሊባሉ የማይችሉ የተደራራቢ ወንጀሎች ልዩ ሁኔታ /exception/ በመሆን የተቀመጡ ናቸው። አንዳንድ የወንጀል ድርጊቶች ከላይ ሲታዩ በተለያዩ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ስር ጥበቃ የተደረገላቸው መብቶችን የሚጥሱና የተደራራቢ ወንጀሎች ባህሪ ያላቸው ይመስላሉ። ይሁን እንጂ ሁሉንም ድርጊቶች አጠቃሎ የሚይዝ አንድ ድንጋጌ ሲኖር ወይም ድርጊቶቹ ቢደጋገሙም በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የተፈጸሙ ናቸው የሚያስብል ምክንያት በተገኘ ጊዜ ወንጀል አድራጊው

[34]በሰሜን ሽዋ ዞን ፍትህ መምሪያ የሀገረ ማሪያም ወረዳ የወ/መ/ቁ. 241/2008፣ በተከሳሽ ሰይፈ ገብረየስና በዐቃቤ-ህግ መካከል በተደረገ ክርክር ዐቃቤ-ህግ 7 ክስ ያቀረበ ሲሆን ወንጀሉ ከ1-6 ያሉት ክሶች በቸልተኛነት በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል አንቀጽ 559(2) ሲሆን የሰጠው ውሳኔ ከ1-6 ያሉት ክሶች በአንድ ክስ የሚጠቃለሉ ናቸው በማለት አንድ ክስ እንዲሆን ብይን በመስጠት ውሳኔ ሰጥቷል።

[35]የደቡብ ወሎ ዞን ፍትህ መመሪያ፣ የወ/መ/ቁ 270/2007 ዓቃቤ ህግና እነ ፈንታ በላይ

[36]የምዕራብ ጎጃም ዞን ፍትህ መምሪያ የወንጀል የወ/መዝ/ቁ/ 033240 ዐቃቤ-ህግና እስከዚያ ጥላሁን፣ የሰሜን ጎንደር ዞን ፍትህ መምሪያ የወ/መዝ/ቁ/መ/ቁ/ 09324 ዐቃቤ-ህግ እና ሞላ ታጀበ፣ የወ/መ/ቁ/ 09647 ዐቃቤ-ህግ እና አስማማው ሞገስ፣ የሰሜን ሽዋ ዞን ፍትህ መምሪያ የወ/መ/ቁ/ 209/07 ዐቃቤ-ህግና መሀመድ ይርጋ፣ የአዊ ብሄረሰብ ዞን ፍትህ መምሪያ የወ/መዝ/ቁ.134/07 ዐቃቤ-ህግና አስፋው አፈረ

ጥፋተኛ የሚባለው ሁሉንም ድርጊቶች አጠቃሎ በሚይዝ በአንድ ድንጋጌ ብቻ ሊሆን እንደሚገባ የሚጠቁሙ የወንጀል ህግ መርሆዎች አሉ፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ውስጥ ተደራራቢ ሊባሉ የማይገባቸው ድርጊቶች የተመለከቱት በአንቀጽ 61ና 63 ስር ነው፡፡ በአንቀጽ 61 ስር ተደራራቢ ያልሆኑ ድርጊቶች በሶስት ምክንያቶች ሊመጡ እንደሚችሉ ተመልክቷል፡፡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሊባሉ ከማይገባቸው ተግባሮች ውስጥ አንዱ በአንቀጽ 61(1) ስር የተጠቀሰው ሲሆን በዚህ ንኡስ አንቀጽ መሰረት አንድን ድርጊት ተደራራቢ ያልሆነ በሚል ለመፈረጅ የተቀመጡ መመዘኛዎች *"በህግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ፤ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች፤ የተደረጉት በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ወይም ቸልተኛነት ሲሆን፤ ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ" ከሆነ ነው በሚል የተቀመጠ ነው*፡፡ ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው መሰረታዊ ነጥብ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ ድርጊቶች በሚፈጸሙ ጊዜ ተደራራቢ ይባላል አይባልም ለሚለው መልስ የሚያግዘን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑና የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተፈጸሙት በአንድ መብት ላይ ነውን? ወንጀል አድራጊው ወንጀሉን የፈጸመው በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ /ቸልተኛነት/ ነውን? ሁሉም የተፈጸሙት ድርጊቶች በተለያዩ ድንጋጌዎች ስር ጥበቃ የተደረገላቸው ቢሆኑም ሁሉንም መብቶች አጠቃሎ ሊሸፍን የሚችል አንድ ድንጋጌ አለን? የሚሉትን ጥያቄዎች በጥምረት (comulatively) መመለስ ከተቻለ ወንጀል አድራጊው ስለሌሎቹ ድርጊቶች ጭምር በተደነገገው በአንድ ድንጋጌ የሚቀጣ ይሆናል፡፡ በወንጀል ህግጋት ውስጥ የተለያዩ ድንጋጌዎች አንድን መብት ወይም የተዛመዱ መብቶችን ወይም ተመሳሳይነት ባህሪ ያላቸውን ህገ ወጥ ድርጊቶች ለመጠበቅ /ለመከላከል/ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በየራሳቸው የቆሙት አንድን መብት ለመጠበቅ ቢሆንም አንዳንድ ድንጋጌዎች የሌላው ድንጋጌ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር (ingredient element) ሆነው የሚገኙበት ጊዜም አለ፡፡ እንደዚህ ዓይነት የተዛመዱ ተደራራቢ ወንጀሎች በተፈጸሙ ጊዜ ህግ አውጭው የወሰደው አማራጭ ወንጀል አድራጊውን በሁሉም ድንጋጌዎች ተጠያቂ ከማድረግ ይልቅ በአንዱ ድንጋጌ ስር ያሉት ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ለሌላው ድንጋጌ እንደ ማክበጃ ተቆጥረው በወንጀል ህግ አንቀጽ 185/2/ መሰረት ቅጣቱ መክበድ እንደሚገባው ነው፡፡ በእርግጥ በገሀዱ ዓለም ተደራራቢ ወንጀሎች የሆኑትን ተደራራቢ ከማይሆኑት መለየት ሁልጊዜም ቀላል ስራ ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተደራራቢ የሆኑትን ተደራራቢ ከማይሆኑት ተግባራት ለመለየት የሚያስችል ሳይንሳዊ ወይም ሂሳባዊ ስሌት ማስቀመጥ ስለማይቻልና ጥቂት ምሳሌዎችን በማሳየትም ተደራራቢ የሆኑትንና ተደራራቢ

ያልሆኑትን መለየት ስለሚያስቸግር ነው። በመሆኑም ተደራራቢ የሆኑትን ወንጀሎች ተደራራቢ ካልሆኑት ለመለየት ዓቃብያነ ህጎች፣ ዳኞች፣ ጠበቆችና ሌሎች ባለሙያዎች የተፈጸሙት ብዙ ድርጊቶች በአንድ ድንጋጌ ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉ መሆን አለመሆናቸውን ወይም ድርጊቶቹ ቢደጋገሙም በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የተፈጸሙ መሆናቸውን በድርጊቱ ውስጥ ካሉ ፍሬ ነገሮች በመረዳትና በመተንተን እንደ ጉዳዮቹ ሁኔታ መወሰን ይኖርባቸዋል።

በወንጀል ህግ አንቀጽ 61(1) ስር የተቀመጠውን መርህ በምሳሌ ስንመለከት በወንጀል ህግ አንቀጽ 665 እና 670/671 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በንብረት መብት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመጠበቅ የተደነገጉ ናቸው። ታዲያ አንድ ወንጀል አድራጊ የሌላን ሰው ንብረት ያለባለቤቱ ፈቃድ በመውሰድ ተግባር ቢጠረጠር ወንጀል አድራጊው የሚከሰሰው በስርቆት ወይም በውንብድና ወንጀል ነው። በተመሳሳይ ጊዜ በስርቆትና በውንብድና ወንጀሎች ሊጠየቅ አይችልም። ምክንያቱም ድርጊቱ የተፈጸመው በአንድ በህግ ጥበቃ በተደረገለት መብትና በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ በመሆኑ ነው። መብቱ በሁለቱም ድንጋጌዎች ስር ጥበቃ ተደርጎለት ይገኛል። ተጠርጣሪው ንብረቱን የወሰደው ሐይል ተጠቅሞ ከሆነ እንደ ነገሩ ሁኔታ በአንቀጽ 670/671 የሚጠየቅ ሲሆን ድርጊቱን የፈጸመው ሀይል ሳይጠቀም ከሆነ በአንቀጽ 665(1) በስርቆት ወንጀል ተጠያቂ ይሆናል። በስርቆት ወንጀል ጊዜ የመብት ጥሰት የሚደርሰው በንብረት መብቱ ላይ ብቻ ነው። በአንጻሩ በውንብድና ወንጀል ጊዜ ወንጀሉ የሚፈጸመው በአካል ደህንነት (በህይወት የመኖር መብትና) በንብረት መብት ላይ ነው። በመሆኑም በውንብድና ወንጀል ውስጥ የአካል ደህንነት መብት (የህይወት) መብትና የንብረት መብት ተቀላቅለው የሚገኙ ሲሆን ድርጊት ፈጻሚው የሚጠየቀው የሁለቱንም የመብት ጥሰጦች አጠቃሎ በሚይዘው በአንቀጽ 670/671(1-ለ) በውንብድና ወንጀል ብቻ እንጂ በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 556 /555/ እና 540/539(1-ሀ)/ እና በአንቀጽ 665(1) በተደራራቢነት የሚከሰስበት አግባብ አይኖርም። በሌላ ምሳሌ በአስገድዶ መድፈር የወንጀል ተግባር ውስጥ የመንቀሳቀስ መብትን መገደብና አስገድዶ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ድርጊቶች ተቀላቅለው ይገኛሉ። እነዚህ ሁለት ድርጊቶች ለየብቻቸው ሲታዩ ሁለት ድርጊቶች ቢሆኑም የመንቀሳቀስ መብት መገደብ ለአስገድዶ መድፈር ወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ስለሆነና የመንቀሳቀስ መብት ሳይገደብ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ስለማይፈጸም ወንጀል አድራጊው የሚጠየቀው በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 620-627 ስር ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት በአስገድዶ መድፈር ወንጀል ብቻ

ይሆናል፡፡ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ሌላ ምሳሌ ብንወስድ አንድ ወንጀል አድራጊ አንድን ግለሰብ እየደበደበ፣ እየዛተ፣ እየቆራረጠ ቢገድለው ወንጀል ፈጻሚው በድርጊቱ ውስጥ በተለያየ ድንጋጌ ሊያስጠይቁ የሚችሉ ወንጀሎችን ፈጽሟል፡፡ ሆኖም በአካል ጉዳት ማድረስ (አንቀጽ 556 /555)፣ በዛቻ (አንቀጽ 580፣ በመግደል ሙከራ (አንቀጽ 27(1)ና 540/539(1-ሀ)፣ በእጅ እልፊት ወንጀሎች ሊጠየቅ አይገባም፡፡ ምክንያቱም በሰው መግደል ወንጀል ውስጥ አካል ጉዳት ማድረስ፣ እጅ እልፊት፣ ዛቻ፣ ስድብ፣ መግደል ሙከራ ወንጀሎች ሊኖሩ የሚችሉና እነዚህ በጠቅላላው በሰው መግደል ወንጀል ውስጥ ሊጠቃለሉ የሚችሉና ብዙውን ጊዜ ሰው ለመግደል አስቦ ለተዘጋጀ ወንጀል አድራጊ የእጅ እልፊት፣ የአካል ጉዳት ማድረስ ስድብ ወይም የዛቻ ተግባሮችን መፈጸም የማይቀር የሚሆንበት አጋጣሚ አለ፡፡ የስርቆት ወይም የውንብድና ወንጀል የሚፈጽም ወንጀል አድራጊም በአንቀጽ 604 መሰረት የግል ቤቶችን ወይም የተከለከሉ ቦታዎችን በመድፈር ወንጀል በአንቀጽ 665 ወይም በአንቀጽ 670/671 በተደራራቢ ወንጀል ሊጠየቅ አይችልም፡፡ ምክንያቱም የስርቆት ወይም የውንብድና ወንጀል የሚፈጽም ወንጀል አድራጊ የግል ቤቶችን መድፈር የግድ ሊሆንበት ይችላል፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ ድርጊቶች የወንጀሉ ውጤት ከወንጀል አድራጊው ሀሳብ በላይ በሆነ ጊዜ ወንጀል አድራጊው ከአሳቡ በላይ ለሆነው ወንጀል ተጠያቂ የሚሆንበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ለምሳሌ ‘ሀ’ በ ‘ለ’ ላይ የአካል ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በጩቤ ቢወጋውና ‘ለ’ ቢሞት ‘ሀ’ ተጠያቂ የሚሆነው አስቦ ከባድ አካል ጉዳት ማድረስ ሳይሆን ድርጊቱ ሞት ሊያመጣ እንደሚችል መገመት እየተገባው ባለማድረጉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 59 እና 543(1) መሰረት በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ሊጠየቅ ይችላል፡፡ በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶችና ዐቃብያነ ህግ መስሪያ ቤቶች በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከት በወንጀል ህግ አንቀጽ 61/1/ መሰረት በህግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች የተደረጉት በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ በሆነ ጊዜ ለአንድ ድርጊት አንድ ቅጣት በሚለው መርህ መሰረት ሁሉንም ድርጊቶች የሚያጠቃልል አንድ ከባድ ድንጋጌ ካለ በሁሉም ድርጊቶች እንደማይቀጣ ይልቁንም በከባዱ ወንጀል ተጠቃለው እንደሚቀጣ ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን በአንድ የምርመራ መዝገብ ወንጀል አድራጊዎች በተከሰሱበት ከባድ ውንብድና ወንጀል ተከሳሾች በአንድ የግል ተበዳይ ላይ የውንብድና እና የአካል ጉዳት በማድረሳቸው ክሱ በከባድ ውንብድና ብቻ ተጠቃሎ መቅረብ ሲገባው በከባድ ውንብድና እና በከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ክስ የቀረበ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል[37]፡፡ በሌላ መዝገብ አንድ ወንጀል አድራጊ በግል ተበዳይ ላይ ቀላል የአካል ጉዳት በማድረስ የግል ተበዳይን ንብረት

[37]የምዕራብ ጎጃም ዞን ፍትህ መምሪያ፣ የወ/መ/ቁ/ 04650 ዐቃቤ-ህግና ክንዲሁን አዳነ

የወሰደ መሆኑን የምርመራ መዝገቡ እያመለከተ በወንጀል አድራጊው ላይ የውንብድና እና የአካል ጉዳት በማድረስ 2 ተደራራቢ ክስ የቀረበ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል።[38] በሌላ መዝገብ ወንጀል አድራጊው ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ በመገልገል በፈጸመው የውንብድና ወንጀል ዐቃቤ ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 671ንና አንቀጽ 808 ን በመጥቀስ በከባድ ውንብድና እና በህገ ወጥ ጦር መሳሪያ መገልገል ወንጀል 2 ተደራራቢ ክስ ቢያቀርብም ጉዳዩን ሲመለከት የነበረው ፍርድ ቤት ውንብድና በጦር መሳሪያ ሊፈጸም እንደሚችል በድንጋጌው ተመልክቷል በሚል በውንብድና ወንጀሉ ሊጠቃለል ይችላል በሚል ውሳኔ ሰጥቷል[39]። ይህ ውሳኔ የወንጀል ህግ አንቀጽ 61(1) ዓላማን ያላገናዘበ ውሳኔ ነው። ምክንያቱም ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ለውንብድና ወንጀል መፈጸሚያ የሚያገለግል ቢሆንም ስለውንብድና ወንጀል የተደነገጉት አንቀጾች ህገ ወጥ ጦር መሳሪያ መያዝን ወይም መገልገልን አጠቃሎ የያዘ አይደለም።

ሌላው ህግ አውጭው ፍጹም ተዳራራቢ ያልሆኑ ተግባሮች በሚል ካስቀመጣቸው ውስጥ አንዱ በአንቀጽ 61(2) ስር የተመለከተው ነው። መመዘኛዎቹም፡-

> *"በህግ በተጠበቀ በዚያው በአንድ መብት ላይ፣ ተደጋግመው ወይም ተከታትለው የተደረጉ ወንጀል ተግባሮች፣ በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኛነት ሲሆን፣ እንደ አንድ ወንጀል ይቆጠራሉ፣ ወንጀል አድራጊው የሚቀጣው ለአንዱ ወንጀል ነው፣ እንዲሁም ወንጀል አድራጊው ደጋግሞ ወይም አከታትሎ ማድረጉ፣ ወይም ወንጀልን እንደ ልማድ ወይም ሙያው አድርጎ መያዙ ለአንድ ወንጀል ማቋቋሚያ ወይም ቅጣት ማክበጃ ካልሆነ በቀር ተደራራቢ ወንጀል አይባልም" የሚል ነው።*

ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው በህግ ጥበቃ በተደረገለት በአንድ መብት ላይ ድርጊቶች ተደጋግመው ወይም ተከታትለው ቢፈጸሙ ወንጀል አድራጊው በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ እስከ ፈጸማቸው ድረስ ተደራራቢ ወንጀሎች እንደማይባሉ ነው። በድንጋጌው ውስጥ ከተካተቱት ቃሎች ውስጥ በህግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚለው የአንድን ሰው መብት የሚያመለክት ነውን? ወይስ መብቱ የተለያዩ ሰዎች ቢሆንም በአንድ ድንጋጌ ስር ጥበቃ የተደረገለትን መብት ነው? የሚለው የሚያከራክር ነው። በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የሚለውም አገላለጽ ወንጀል አድራጊዎች

[38]የዋግ ኽምራ ብሄረ ሰብ ዞን የወ/መ/ቁ 92/06፣ ዐቃቤ-ህግና ጎሸየ አማረ

ወንጀል ለመፈጸም የተነሳሱበትን የመጀመሪያ እቅድ ወይም አላማ የሚጠቁም ነውን? ድርጊቱን እየፈጸመ እያለ በዚያው ሰው መብት ላይ ወይም በሌላ ሰው ላይ ተመሳሳይ ወንጀል ለመፈጸም ቢያስብስ? በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ አይባልምን? የሚሉትን ሀሳቦች ከድንጋጌው መረዳት አይቻልም።

የወንጀል ህግ በዋናነት የወንጀል አድራጊውን የሀሳብ ክፍል የመቅጣት ቀዳሚ አላማ እንዳለው ቀደም ሲል ተመልክተናል። በአንቀጽ 61(2) ስር የተቀመጠውን ስንመለከትም አንድ ድርጊት የተፈጸመው በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ከሆነ ድርጊቶቹ ቢደጋገሙም ተግባሮቹ በተደራራቢነት እንደማያስቀጡና ወንጀል አድራጊው ደጋግሞ ለፈጸማቸው ተግባሮች እንደማይቀጣ የሚገልጽ መርህ ነው። በእርግጥ አንድ ድርጊት በተፈጸመ ጊዜ ድርጊቱ የተፈጸመው በአዲስ ሀሳብ የተፈጸመው ነው አይደለም የሚለው በእጅጉ አስቸጋሪና አከራካሪ ነው። ምክንያቱም ወንጀል አድራጊዎች አንድ ወንጀል ከፈጸሙ በኋላ ያንኑ ወንጀል በዚያው ሰው መብት ላይ ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ በድጋሚ ቢፈጽሙ በአዲስ ሀሳብ ነው አይደለም የሚለው በድርጊቱ ውስጥ ያሉትን ፍሬ ነገሮችና አካባቢያዊ ሁኔታዎችን በማየት እንደ የጉዳዮቹ አግባብ የሚወሰን ነው። በተለይም ድርጊት ፈጻሚው ድርጊቱን ለተወሰነ ጊዜ አቋርጦ እንደገና ቢፈጽምና ያቋረጠው ለቀናት? ለሳምንታት ቢሆን? ወንጀሉን የፈጸመው በሌላ ሰው መብት ወይም በሌላ አይነት መብት ላይ ቢሆን? ለተወሰነ ጊዜ የተቋረጠው ውጫዊ ባልሆነ ምክንያት ቢሆንስ? የሚሉትን ነጥቦች እያነሳን ስንጠይቅ ድንጋጌው አመላካች ነገር የለውም፡ የወንጀል አድራጊዎች የሀሳብ ሁኔታ /state of mind/ የሚታወቀው አንድን ወንጀል ደጋግመው ወይም አከታትለው ሲፈጽሙ አዲስ ሀሳብ ይዘው መሆን አለመሆኑን ለመረዳት ወንጀል አድራጊዎቹ ከሚናገሩት፣ ይዘው ከተነሱት እቅድ፣ ከሚጠቀሙት ዘዴ፣ በተደጋጋሚ በተፈጸሙት ድርጊቶች መካከል ያለውን የጊዜ ርዝመትና ሌሎች ፍሬ ነገሮችን በመያዝ የሚደረስበት ነው። አንድ ወንጀል የፈጸመ ሰው ድርጊቱን በተደጋጋሚ የፈጸመው በአዲስ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ነው አይደለም የሚለውን ለመረዳት ጉዳዮቹን በምሳሌ ለመመልከት ያክል አንድ ወንጀል አድራጊ የቤት ውስጥ ጥቃት በተደጋጋሚ በአንዲት ሴት ላይ ቢፈጽም ወንጀል አድራጊው በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ድርጊቱን ፈጽሞታል ለማለት ይቻላል። በተመሳሳይ አንድ ገንዘብ ያዥ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥራ ስትሰራ በቀን 5 ብር ለአንድ ዓመት ያክል ብትወስድ

የፈጸመችው ወንጀል ተከታታይ የእምነት ማጉደል ወንጀል ሲሆን በአንድ የንብረት መብት ላይ ገንዘብ ለማግኘት ካላት ፍላጎት በመነጨ ሀሳብ እና አከታትላ ያደረገችው ወንጀል ስለሆነ የወንጀል ህግ አንቀጽ 676(2-ሀ) ስር የተመለከተው ተጠቅሶ እንደ አንድ ድርጊት ተቆጥሮ በአንድ ክስ ብቻ ተጠያቂ ትሆናለች፡፡ በሌላ ምሳሌ አንድ ሰው ለመግደል ያሰበ ሰው 5 ጊዜ ተኩሶ ቢስተው እና በ 6ኛው ቢገድለው በተደራራቢ ወንጀል አይጠየቅም፡፡ ነገር ግን ወንጀል አድራጊው ተኩሶ ስቶት ከሄደ ከሳምንት በኋላ ተመልሶ በመምጣት ቢገድለው በመግደል ሙከራና በሰው መግደል ወንጀል በተደራራቢ የሚጠየቅ ይሆናል፡፡ በሌላ ምሳሌ አንድ መኪና የሚያሽከረክር ግለሰብ ከሚነዳው መኪና ላይ የጫናቸው ጎማዎች በአግባቡ ባለመታሰራቸው አንደኛው ወድቆ አንድ ሰው ከመታ በኋላ ቀሪው ጎማም ሊወድቅ እንደሚችል የሚገመት ሆኖ እያለ አሽከርካሪው ቀሪውን ጎማ በአግባቡ ማሰር ሲገባው ይህን ባለማድረጉ ከተወሰነ ጉዞ በኋላ እንደገና ሁለተኛው ወድቆ ሌላ ሰው ላይ ጉዳት ቢያደርስ ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀሎች ይጠየቃል፡፡ ምክንያቱም ሁለተኛው ወንጀል የተፈጸመው በአዲስ ቸልተኝነት ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በሌላ ምሳሌ ‘ሀ’ ከአባቱ ኪስ በተከታታይ ቢሰርቅና አንድ ቀን አውቆበት ቢቆጣው ለተወሰነ ጊዜ አቋርጦ እንደገና ቢጀምር አዲስ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ አለው ለማለት ይቻላል፡፡ በሌላ ምሳሌ አንድ ወንጀል አድራጊ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ በርከት ያለ ህገ ወጥ ብር ገበያ ይዞ በመውጣት ከተለያዩ ሰዎች እህል በመግዛት ሀሰተኛ ገንዘቡ እንዲዘዋወር ቢያደርግ ድርጊቱ በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የተፈጸመ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በሌላ ምሳሌ በአንድ የገጠር ቀበሌ ውስጥ አንድ የቀበሌ አመራር ለስራ አጥ ወጣቶች የገጠር መሬት ለመስጠት በማሰብ በአንድ ቀን ውስጥ  ከተለያዩ ወጣቶች 900 ብር አምጡና መሬት ልስጣችሁ በማለት ገንዘብ ቢቀበል ወንጀሉን የፈጸመው በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

የወንጀል አድራጊዎችን የሀሳብ ሁኔታ ፈልጎ በማግኘት አንድ ድርጊት በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የተፈጸመ ነው አይደለም የሚለው እጅግ አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ጉዳዩን ተደራራረቢ ይሆናል አይሆንም በሚለው ዙሪያ በባለሙያዎች ዘንድ ሰፊ ልዩነትና ክርክር ሲደረግ ይታያል፡፡ በአንድ ወቅት በአማራ ክልል በተለያዩ ከተማ አስተዳደሮች በመሬት ማስተላለፍ የስራ ሂደት ውስጥ

ይሰሩ የነበሩ የስራ ሀላፊዎችና ባለሙያዎች ስልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም ለተለያዩ ግለሰቦች በተለያየ ጊዜ መሬት አላግባብ አስተላልፈዋል በሚል ምርመራ ተጣርቶባቸው ክስ ለማቅረብ ድርጊቱ የተፈጸመው በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ነው አይደለም በሚል በጸረ ሙስና ዐቃብያነ ህጎች መካከል ሰፊ ክርክርና ልዩነት ስለነበር በተወሰኑ መዝገቦች ላይ ድርጊቱ በአዲስ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የተፈጸመ ነው በሚል ተደራራቢ ክሶች የቀረቡ ሲሆን ተመሳሳይ ባህሪ ባላቸው በሌሎች መዝገቦች ድርጊቱ የተፈጸመው በአንድ ወንጀል በማድረግ ሀሳብ ነው በሚል ወንጀሉ ተደራራቢ አይሆንም በሚል እንደ አንድ ድርጊት ተቆጥሮ አንድ ክስ እንደቀረበ ባለሙያዎች ይገልጻሉ[40]።

ሌላው በአንቀጽ 61(2) ሁለተኛ ፓራግራፍ ስር የተገለጸው የድርጊቶች መደጋገም ተደራራቢ ወንጀሎች መሆናቸው ይቀርና የድርጊቱ መደጋገም በራሱ አንድን ወንጀል የሚያቋቁም ወይም የቅጣት ማክበጃ የሚሆንበት አጋጣሚ እንዳለ በድንጋጌው ተመልክቷል። እነዚህ ድርጊቶች ከአንድ ወንጀል ከመፈጸም ሀሳብ ወይም ቸልተኛነት የሚመነጩ ሲሆን በመጀመሪያው ፓራግራፍ ከተመለከተው የተለየ የሚያደርጋቸው ወንጀል አድራጊው ድርጊቶቹን መደጋገሙ በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ለተደነገጉ የተለያዩ አንቀጾች ማቋቋሚያ ምክንያት መሆናቸው ነው። የድርጊቶች መደጋገም የድንጋጌዎቹ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር የሆነባቸው ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በወንጀል ህጉ ውስጥ ተካተው የሚገኙ ሲሆን ለምሳሌ በአንቀጽ 471 አደገኛ የሆነ ስራ ፈትነት፣ አንቀጽ 634 የሌላውን ሰው የገዘሙት ድርጊት የዘወትር መጠቀሚያ ማድረግ፣ አንቀጽ 635 ሴቶችንና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ለዝሙት አዳሪነት በማቃጠር መነገድ፣ በአንቀጽ 477 አደገኛ ቦዘኔነት፣ አንቀጽ 478 የክፉ አድራጊዎች ማህበር፣ አንቀጽ 535 በህክምና ጤና አጠባበቅ ሙያ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ መስራት፤ አንቀጽ 354 ያልተገባ ትርፍ ለማግኘት የተደረገ ህገ ወጥ ንግድ ወይም ኮንትሮባንድ መስራትን የዘወትር የሞያ ስራው ያደረገ ሰው የመሳሰሉት ድንጋጌዎች የሚጠቀሱ ናቸው።

በመርህ ደረጃ በአንቀጽ 61(2) ላይ የተመለከትናቸው ድርጊቶች በተደራራቢነት እንደማያስቀጡ የተደነገገ ቢሆንም ድርጊቱ በአዲስ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ከሆነ በወንጀል ህግ አንቀጽ 62 ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው በተገኙ ጊዜ ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀል

[40]በአብክመ የጸረ ሙስና ኮሚሽን፣ ከደብረ ብርሀን ቋሚ ምድብ ችሎት ዓቃቢያነ ህግ ጋር የተደረገ የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 4/2008

ተጠያቂ ይሆናል[41]። በአንቀጽ 62 ስር የተቀመጠው መስፈርት *"ቀድሞ አድርጎት ከነበረው ወንጀል ጋር ተመሳሳይ የሆነ፣ በአዲስ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ በሌላ ሰው ወይም ቀድሞ ፈጽሞት በነበረው ሰው ላይ ቢሆንም፣ ወይም በህግ በተጠበቀ በዚያው መብት ላይ ቢሆንም እንኳ አዲስ ወንጀል ስለሆነ በ 184 መሰረት ተደራራቢ ይሆንበታል"*።

በወንጀል ህጉ ተደራራቢ ያልሆኑ ወንጀሎች ከሚመጡበት ሌላው ምክንያት በአንቀጽ 61(3) ስር የተመለከተው ነው። በዚህ ድንጋጌ ስር ድርጊቶቹ ለዋናው ወንጀል ቅጥያ /Ancillary (subordinate) በሆኑ ጊዜ ወንጀል አድራጊው ለሁሉም ድርጊቶች ተጠያቂ አይሆንም። ይልቁንም ወንጀል አድራጊው ተጠያቂ የሚሆነው መጀመሪያ ለመፈጸም አቅዶ ለተነሳው ወንጀልና ለዋናው ወንጀል ብቻ ይሆናል። በዚህ ድንጋጌ ስር የተቀመጠው መመዘኛ፡-

> *"አድራጊው የተወሰነ ወንጀል ለማድረግ ሀሳብ አለው ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ፣በተለይም የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ በንብረት ላይ ወንጀል አድርጎ እንደሆነ፤ ወይም የሀሰት ገንዘብ ሰርቶአ ንደሆነ፤ ወይም ይህንኑ ገንዘብ እንዲዘዋወር አድርጎ እንደሆነ፤ ወይም ሀሰተኛ ገንዘብ ሰርቶ እንደሆነ፤ ወይም ይህንኑ ገንዘብ እንዲዘዋወር አድርጎ እንደሆነ፤ ወይም ሀሰተኛ ሰነድ ሰርቶ እንደሆነ ወይም ተጠቅሞበት እንደሆነ፤ የመጀመሪያውን የጥፋት ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሲል፤ መሰረታዊ ከሆነው ወንጀል በኋላ አከታትሎ የፈጸመው ከቀድሞው አሳቡና ሊደርስበት ካሰበው ግቡ ጋር የተያዘ ሆኖ በዋናው ወንጀል ይጠቃለል" የሚል ነው።*

ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው አንድ ወንጀል አድራጊ አንድ ነጠላ የሆነ ውጤት ለማምጣት በማሰብ ብዙ ህገ ወጥ ድርጊቶችን የፈጸመ እንደሆነ ወንጀሎቹ በጣም የሚቀራረቡ ከሆነ የጥፋተኝነት ሀሳብ ያለው በዋናው ወንጀል ላይ እንደሆነ ስለሚወሰድ ሌሎቹ ድርጊቶቹ የዋናው ወንጀል ቅጥያ በመሆን ስለሚወሰዱ ስለእነዚህ ድርጊቶች በተደራራቢነት ተጠያቂ አይሆንም ማለት ነው። ይህ ማለት መጀመሪያ የተፈጸመው ወንጀል ፍሬ ያፈራ ዘንድ የግድ የሚቀጥለው ወንጀል መፈጸም የሚኖርበት ይሆናል። ለምሳሌ አንድ ወንጀል አድራጊ የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ሀሰተኛ ገንዘብ አዘጋጅቶ ወይም ሀሰተኛ ሰነድ አዘጋጅቶ ይህንኑ ገንዘብ ገበያ

[41]ይህን ነጥብ በሚመለከት በአንድ ወቅት በአማራ ክልል ጸረ ሙስና ኮሚሽን ውስጥ በሚሰሩ ዐቃቢያነ ህጎች መካከል ቃሉን በመረዳት ረገድ ልዩነት ስለነበር በተወሰኑ መዝገቦች ላይ ሁለት ዓይነት ክሶች የቀረቡ ሲሆን በአንደኛው መዝገብ ላይ በወንጀሎቹ መካከል ያለው ጊዜ የተራራቀ ስለሆነ ተደራራቢ ሊሆን አይገባም በሚል በተለያዩ መዝገቦች ክስ የቀረበ ሲሆን በሌላ በኩል በድርጊቶቹ መካከል ያለው ጊዜ ሩቅ ቢሆንም በሁለቱ ድርጊቶች መካከል ይርጋ እስካላገደው ድረስ ተደራራቢነቱን አያሳጣውም በሚል በተደራራቢነት ክስ እንደቀረበ ባለሙያዎች ይገልጻሉ።

ውስጥ እንዲዘዋወር ቢያደርግ ወይም ሀሰተኛ ሰነዱን ቢገለገልበት ወንጀል አድራጊው የሚጠየቀው ለዋናው ወንጀል ለህገ ወጥ ብር ማዘጋጀቱ ወይም ለሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀቱ እንጂ ህገ ወጥ ገንዘብ ለማዘዋወሩ ወይም በሀሰተኛ ሰነዱ በመገልገሉ ተጠያቂ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ማዘዋወሩ የማዘጋጀት ወንጀሉ ቅጥያ ወንጀል ስለሆነ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን በሀሰተኛ ሰነዱ በመገልገል የማታለል ወንጀል ተፈጽሞ ከሆነ ለሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀቱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 378 ወይም በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 መሰረትና በወንጀል ህግ አንቀጽ 699 መሰረት በማዘጋጀትና በማታለል ወንጀል 2 ተደራራቢ ክስ ይቀርብበታል፡፡ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 369 መሰረት እንደተመለከተው ሀሰተኛ ሰነድ የተገለገለ ሰው የሚጠየቀው በመገልገሉ ብቻ ነው፡፡ ሀሰተኛ ሰነዱን እስካላዘጋጀው ወይም በማዘጋጀቱ ውስጥ እስካልተሳተፈ ድረስ፡፡ ለምሳሌ አቶ ደፋሩ በሐሰተኛ የምስክር ወረቀት በመገልገል አንድን የመንግሥት መሥሪያ ቤት አታሎ ከተቀጠረ በኋላ የሶስት ወር ደመወዝ እንደተቀበለ ቢደርስበት የሚከሰሰውና የሚቀጣው በሐሰተኛ የትምህርት ምስክር ወረቀት በመገልገሉ በወንጀል ሕግ ቁጥር 369 አታሎ የሶስት ወር ደመወዝ እንዲከፈለው በማድረጉ በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 696 መሠረት ነው፡፡ በተጨማሪም በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 388 ስር እንደተገለጸው ማንም ሰው ሀሰተኛ የምስክር ወረቀት፤ ሀሰተኛ የምስክርነት ማስረጃ ወይም እርሱን የማይመለከተውን ወይም እንዲገለገልበት ያልታሰበውን ትክክለኛ የምስክር ወረቀት አግኝቶ በዚሁ አስቦ በመጠቀም ተጨማሪ ወንጀል ለመፈጸም የተገለገለበት እንደሆነ በተለይም እምነት ማጉደል ወንጀል ወይም ማታለል ወንጀል ሆኖ ወንጀሉ ቢያንስ ተሞክሮ ከሆነ በአንቀጽ 66 መሰረት በተደራራቢነት እንደሚጠየቅ የሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገልን በሚመለከት በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከት ሀሰተኛ ሰነድ መገልገልና ማዘጋጀት ወንጀል በአንድ ድንጋጌ ይጠቃለል የሚለው ነጥብ በባለሙያዎች ዘንድ በስፋት ሲያከራክር ይታያል፡፡ አንዳንድ ባለሙያዎች ጽንሰ ሀሳቡን በአግባቡ ባለመረዳት በሀሰተኛ ሰነድ ሲገለገል የተገኘን ወንጀል አድራጊ በሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና በመገልገል በ 2 ተደራራቢ ክስ የሚያቀርቡ እንደነበሩ ባለሙያዎች ይገልጻሉ[42]፡፡ አንዳንድ ባለሙያዎች ከላይ ከተገለጸው በተለየ ሁኔታ ሀሰተኛ ሰነዱን ያዘጋጀውና የተገለገለው አንድ ወንጀል አድራጊ በሆነ ጊዜ መገልገሉ የማዘጋጀቱ ቅጥያ ነው በሚል በማዘጋጀት ብቻ ክስ እንደሚያቀርቡ ይገለጻል[43]፡፡

[42]በአብክመ የጸረ ሙስና ኮሚሽን፣ የደብረብርሀን ቋሚ ችሎት ከሚሰሩ ዐቃቢያነ ህጎች ጋር የተደረገ ውይይት፣ ሚያዚያ 21/2008 ዓ.ም
[43] ገዙኒ ከማሁ

## 3. በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ የቅጣት አጣጣል መርሆዎችና ተግባራዊ አፈጻጸሙ በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች

ከተደራራቢ ወንጀሎች ጋር በተገናኘ አቢይ ትኩረት ከሚስቡ ጉዳዮች አንዱና በፍርድ ቤቶችም ችግር ሲፈጥር የሚታየው በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ የቅጣት አጣጣል ስልት ነው። በብዙ ሀገራት የወንጀል ህግ ውስጥ የእኛንም ጨምሮ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተብለው ከሚመደቡት ውስጥ ተደራራቢ ወንጀሎች የሚጠቀሱ ናቸው[44]። ተደራራቢ ወንጀሎች ልዩ የቅጣት ማክበጃ ሆነው ቢደነገጉም ምንጊዜም ቢሆን ቅጣት ሲጣል የተመጣጣኝነት መርህንና የሚጣለው ቅጣት የሚፈጸም መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት እንዴት እንደሚጣል የሚጠቁሙ መርሆዎች ከአንቀጽ 183-188 ባሉት ድንጋጌዎች ስር ተመልክቶ ይገኛል። እነዚህን ድንጋጌዎች ስንመለከት ቅጣት ተመጣጣኝ መሆኑን ለማመልከት የተቀመጡ ድንጋጌዎች መሆናቸውን እንገነዘባለን።

በብዙ ሀገራት የወንጀል ህግ ውስጥ የእኛንም ጨምሮ በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ለመጣል ስራ ላይ ከዋሉ ዘዴዎች ውስጥ የመደመር /totality/ comulation rule/ እና የማጠቃለል /absorbtion rule/ የሚባሉት የሚጠቀሱ ናቸው።

### ሀ. የመደመር /totality/ የቅጣት አጣጣል ዘዴ

የመደመር ቅጣት አጣጣል ዘዴ በብዙ ሀገሮች የወንጀል ህግ ውስጥ የሚገኝና በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ለመጣል ዋነኛው ዘዴ ነው[45]። በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ለመጣል የመደመር መርህ አማራጭ የሆነበት ምክንያት በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ትክክለኛና ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ለመጣል ያስችላል ከሚል እምነት ነው። ምክንያቱም ወንጀል አድራጊዎች ለፈጸሟቸው ሁሉም ወንጀሎች ቅጣት ተጥሎ ሁሉም ቅጣቶች ስለሚደመሩ የወንጀል አድራጊውን የአደገኛነት መጠን በሚያሳይ መልኩ ስለሚወሰን የተመጣጣኝነት መርህን ስለሚያስጠብቅ ነው። በእርግጥ በተደራራቢ ወንጀሎች ጉዳይ ለነጠላ ወንጀሎቹ የተቀመጠውን ቅጣት በመደመር ብቻ ሁል ጊዜ ተመጣጣኝና ትክክለኛ ቅጣት ለመጣል አይቻልም።

[44]በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 85 ስር እንደተመለከተው ተደራራቢ ወንጀል ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተብለው ከተቀመጡት ውስጥ አንዱ እንደሆነ ተመልክቷል።
[45]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 7

የመደመር /totality/ የቅጣት አጣጣል ዘዴ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 184(1-ለ) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን መርሁ በብዙ ሀገሮች የወንጀል ህግ ውስጥ ተካቶ የሚገኝና በስፋት የሚሰራበት ነው። የመደመር ዘዴ ስራ ላይ እንዲውል የተደረገበት ምክንያት በተደራራቢ ወንጀሎች ከደረሰው ጉዳት እና ከወንጀል አድራጊው የአደገኛነት ባህሪ በመነሳት በወንጀል አድራጊዎች ላይ ትክክለኛና ተመጣጣኝ ቅጣት ለመጣል ነው። ስለሆነም የመደመር ዘዴ በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት አጣጣልን በሚመለከት ዋነኛው መርህ ነው ለማለት ይቻላል። በመደመር ዘዴ መሰረት ለተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት የሚሰላው ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ከተያዘ በኋላ እነዚህን መነሻዎች በመደመር ድምሩ የሚያርፍበትን ውጤት በመያዝ ማክበጃና ማቅለያ በቅደም ተከተል በመያዝ የሚወሰን ነው። በመደመር የቅጣት አጣጣል ዘዴ ቅጣት የሚጣለው ለእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል መነሻ ቅጣት ከተያዘ በኋላ ሁሉንም በመደመር የሚሰላ ነው። በአንዳንድ ሀገሮች ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች ተደምረው የሚገኘው አጠቃላይ ውጤት ወንጀል አድራጊው ላይ የሚወሰን ሲሆን በአንዳንድ ሀገሮች ደግሞ ወንጀል አድራጊው ላይ የሚጣለው ቅጣት ተደራራቢ ወንጀሎቹ ተደምረው የሚገኘው የመጨረሻ ውጤት ሳይሆን በወንጀል ህጉ ጠቅላላ ክፍል የተቀመጠው የጠቅላላ የጽኑ ወይም የቀላል እስራት ጣሪያ ሳያልፍ መሆኑ ተደንግጎ ይገኛል[46]። ይህ ማለት ተደራራቢ ወንጀሎቹ ተደምረው የሚገኘው ውጤት በጠቅላላ የወንጀል ህጉ ክፍል ውስጥ ከተቀመጠው ጣሪያ በላይ ካለፈ ትርፉን ቁጥር ውድቅ በማድረግ እንዳይፈጸም ይደረጋል። በአንዳንድ ሀገሮች ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች ተደምረው የሚገኘው ውጤት በወንጀል አድራጊው ላይ የሚጣል ሲሆን በመደመር ቅጣት የሚጣለው ቅጣት ከወንጀል አድራጊው እድሜ በላይ ሊሆን የሚችልና የማይፈጸም ቅጣት እንደሚሆን የሚታወቅ ቢሆንም ቅጣት በአንድ ሀገር ውስጥ የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥና ቅጣት ለሌሎች አስተምህሮ መሆኑን ለማሳየት የሚጣል ነው። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ወንጀል ህግ በአንቀጽ 184 /1-ለ/ ስር በተገለጸው መሰረት ከሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡና ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣቶችን የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ባጋጠሙ ጊዜ ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈጸመው ወንጀል ተገቢ የሆነው ቅጣት ተወስኖ ሁሉም እንደሚደመር ይደነግጋል። ሆኖም የሚገኘው ውጤት በወንጀል ህጉ ጠቅላላ ክፍል ከተቀመጠው ጣሪያ ሊበልጥ እንደማይችል ተደንግጓል። እንዲሁም በጽኑ እስራትና በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ ለመደመር እንዲያመች የሁለት ዓመት

[46]ለምሳሌ የደቡብ አፍሪካን የወንጀል ህግ ስንመለከት በወንጀል ህጉ የተቀመጠ ጣሪያ የለም። ተዳራራቢ ወንጀሎቹ ተደምረው የሚገኘው ውጤት በወንጀል አድራጊው ላይ ይወሰናል። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 106ና 108 ላይ እንደተቀመጠው የቀላል እስራት ጣሪያ 3 ዓመት ሲሆን የጽኑ እስራት ደግሞ 25 ዓመት ነው።

ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንደሚቆጠር ተቀምጧል። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት አወሳሰን ቁጥር 2 መመሪያ መሰረትም ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ ከተባለ ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ከተያዘ በኋላ እነዚህን በመደመር የድምሩ ውጤት የሚያመለክተውን ቁጥር በመያዝ ዝቅተኛ እርከኑ እንደሚመረጥ ይጠቁማል። በመቀጠልም የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ እርከኑን ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ በወንጀል ህጉ ጠቅላላ ክፍል ከተመለከተው ጣሪያ ሳይበልጥ ቅጣት እንዲሚወሰን ተመልክቷል[47]። በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ መሰረት ጽኑ እስራት ከ 25 ዓመት እንደማይበልጥ የተደነገገ ሲሆን ቀላል እስራት ደግሞ በመርህ ደረጃ ከ 3 ዓመት በልዩ የወንጀል ህጉ ክፍል ላይ በተመለከተ ጊዜ ከ 5 ዓመት እንደማይበልጥ ተደንግጓል[48]። በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ በሁሉም የተደራራቢ ወንጀሎች ላይ የቅጣት መደመር አይፈቀድም። ምክንያቱም ተደምሮ የሚጣለው ቅጣት ምናልባትም አንድ ሰው ወይም የሚጣልበት ሰው በህይወት ከሚኖረው እድሜ በላይ ሊሆን ይችላል። ይህ ከሆነ ደግሞ ከሞተ በኋላ ያለው ቅጣት የማይፈጸም ቅጣት ስለሚሆን በወንጀል ህጉ ከተቀመጠው ጣሪያ ውጭ ይሆናል እንደ ማለት ነው። በጽኑ እስራት ጊዜም ሁሉም ይደመሩ ከተባለ የሚጣለው ቅጣት ከ 25 ዓመት በላይ ይሆናል። ከቅጣት መደመር ጋር በተያያዘ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ የደንብ መተላለፍ ወንጀሎች በጽኑ እስራት ወይም በቀላል እስራት ከሚያስቀጡ ወንጀሎች ጋር በተደራራቢነት የሚመጡ ከሆነ ቅጣት እንዴት ሊወሰን ይችላል የሚለው ነው። በወንጀል ህግ ከአንቀጽ 776-865 ያሉት ድንጋጌዎች የደንብ መተላለፍ ወንጀሎች ሲሆኑ በእነዚህ ተግባራት ጥፋተኛ የተባሉ ወንጀል አድራጊዎች የሚጣልባቸው ቅጣት በገንዘብ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት በመሆኑ የደንብ መተላለፍ ወንጀሎች በጽኑ እስራት ወይም በቀላል እስራት ከሚያስቀጡ ወንጀሎች ጋር ተደራርበው በተገኙ ጊዜ ለመደመር ያመች ዘንድ በማረፊያ ቤት የሚያስቀጣ የደንብ መተላለፍ ወንጀል እንዴት ወደ ጽኑ እስራት ወይም ቀላል እስራት እንደሚቀየር በህጉ አልተቀመጠም። ቅጣቱ በእስራት ሆኖ በማረፊያ ቤት እንዲፈጸም ፍርድ ቤቱ ቢወሰን በሀገራችን ማረፊያ ቤት ባለመኖሩ ለማስፈጸም ችግር መፍጠሩ አይቀርም። በተግባር ያለውን

[47]የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅታት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 22(1-ሀ)
[48]የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 108ና 106

አሰራር ስንመለከትም ፍርድ ቤቶቻችን ይህን ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ይመስላል በአማራጭ የተቀመጠውን የገንዘብ መቀጮ ሲቀጡ ማየት የተለመደ ነው[49]።

### ለ. የማጠቃለል (absorbtion) የቅጣት አጣጣል ዘዴ

በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ለመጣል በብዙ ሀገራት የወንጀል ህጎች ውስጥ ተካቶ ከሚገኙ መርሆዎች ውስጥ አንዱ የማጠቃለል ዘዴ ነው። ይህ መርህ ተግባራዊ የሚሆነው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ወንጀሎች በተደራራቢነት ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ከተደራራቢ ወንጀሎቹ ውስጥ ከባድ ቅጣት የሚያስቀጣው ወንጀል ይወሰድና ሌሎቹ በከባዱ ወንጀል እንዲጠቃለሉ በማድረግ ቅጣት የሚጣልበት ዘዴ ነው። ለምሳሌ ከተደራራቢ ወንጀሎቹ ውስጥ አንዱ ወይም የተወሰኑት እንደ ሞት ወይም እድሜ ልክ የሚያስቀጡ ቢሆን ሌሎች በጽኑ እስራት ወይም በቀላል እስራት የሚያስቀጡት ወንጀሎች በሞት ወይም በእድሜ ልክ በሚያስቀጣው ወንጀል እንዲጠቃለሉ ይደረጋል። በተመሳሳይ ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች በጽኑ እስራት ወይም በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ሆነው በተገኙ ጊዜ በንጽጽር ዝቅተኛ ቅጣት የሚያስቀጡት ወንጀሎች በከባድ ጽኑ እስራት ወይም ከፍ ባለ ቀላል እስራት በሚስያቀጡ ወንጀሎች እንዲጠቃለሉ ይደረጋል። ተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት በሚጣልበት ጊዜ በከባዱ ወንጀል እንዲጠቃለል የሚደረግበት ዓላማ  በሞት ወይም በእድሜ ልክ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ከሌሎች በሞት ወይም በእድሜ ልክ ወይም በእስራት ከሚያስቀጡ ወንጀሎች ጋር በተደራራቢነት ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ በተጨማሪ በሞት፣ በእድሜ ልክ ወይም በእስራት የሚያስቀጣ ቅጣት ቢጣል ቅጣቱ የማይፈጸም ስለሚሆን ቅጣት መጣሉ ትርጉም አልባ ስለሚሆን ነው። በሌላ በኩል የማጠቃለል የቅጣት አጣጣል ዘዴን ተግባራዊ የምናደርግበት አጋጣሚ ተደራራቢ ወንጀሎቹ የተፈጸሙት በጣምራ የወንጀል ድርጊት ወይም ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች የተፈጸሙት በቸልተኝነት ሲሆን ነው። በጣምራ ወንጀል ተግባር ወይም በቸልተኝነት ተደራራቢ ወንጀሎችን የፈጸመ ወንጀል አድራጊ ባህሪውን ስንመለከት ግዙፋዊ ወንጀል ወይም ወንጀሎችን አስቦ ከፈጸመ ወንጀል አድራጊ ጋር ሲነጻጸር አደገኛ የሚባል አይነት ስላልሆነ የቅጣት ዓላማ ብቀላ ሳይሆን ማስተማር መሆኑን በተግባር ለማሳየት በጣምራ ወንጀል ወይም ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች የተፈጸሙት በቸልተኝነት በሆነ ጊዜ ቅጣት የሚጣለው ከተደራራቢ ወንጀሎቹ ውስጥ ከባድ ቅጣት የሚያስቀጣው ወንጀል ይወሰድና ሌሎቹ

[49]በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መመሪያ በወንጀል የስራ ሂደት ከሚሰሩ ባለሙያዎች ጋር የተደረገ የጋራ ውይይት፣ ሚያዚያ 2/2008 ዓ.ም

ተደራራቢ ወንጀሎች እንደ ቅጣት ማክበጃ ተደርገው ይወሰዳሉ[50]። የማጠቃለል መርህ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 184(1-ሀ) ስር የተደነገገ ሲሆን ወንጀል አድራጊው *"ነጻነትን ወይም ህይወትን በማሳጣት ከሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በአንደኛው ምክንያት የሞት ወይም እድሜ ልክ እስራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሳሳይ ዓይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በህጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት /አንቀጽ 108 ና 106/ ሲወሰን ---ይህ ውሳኔ ስለሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰነውን ሁሉ አጠቃሎ /ደርቦ/ ይይዛል"* በማለት ያስቀምጣል። የወንጀል ህጉ አንቀጽ 184/1-ሀ/ ስር እንደተመለከተው ነፃነትን ወይም ህይወትን በሚያሳጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በአንደኛው ምክንያት የሞት ወይም የእድሜ ልክ እስራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሳሳይ ዓይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በህጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት /አንቀጽ 106 እና 108/ ሲወሰን ይህ ውሣኔ ስለሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰነውን ቅጣት ሁሉ አጠቃሎ /ደርቦ/ እንደሚይዝ ይደነግጋል። በዚህ ድንጋጌ መሰረት ከተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ በሞት ወይም በእድሜ ልክ ወይም ቅጣቱ ጽኑ እስራት ከሆነ የመጨረሻውን ጣሪያ 25 ዓመት የሚያስቀጣ ሲሆን ሌሎቹ ቅጣቶች በሞት ወይም በእድሜ ልክ ወይም በ 25 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲጠቃለሉ ይደረጋል። ሆኖም ፍርድ ቤቱ በማጠቃለል መርህ ውስጥ አልፎ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን ከያዘ በኋላ በስተመጨረሻ ከባዱን ቅጣት ያልወሰነ እንደሆነ ስለሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣቱን በአንቀጽ 184(1-ለ) መሰረት እንደሚያሳድግ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 184(1-ሀ) ሁለተኛ ፓራግራፍ ስር ተደንግጓል። ይህም የሚያሳየው ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሲጥል የእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል ቅጣት ለየብቻው ሲሰላ ከላይ በንዑስ ቁጥር 1/ሀ/ ፖራግራፍ 1 ስር እንደተቀመጠው የሞት ፍርድ፣ የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሳሳይ ዓይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በህጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛውን ቅጣት አለመቅጣቱን ካረጋገጠ ስለሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣቱን ማሳደግ እንዳለበት የሚያመለክት ነው። እዚህ ላይ መታየት ያለበት መነሻ ቅጣት መያዝ እና የመጨረሻ ውሣኔ መስጠት የተለያዩ እንደሆነ ነው። ምክንያቱም በድንጋጌው ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው ከቅጣት ዓይነቶቹ አንዱን የወሰነ እንደሆነ የሚለው የሚያመለክተው መነሻውን የወሰነ እንደሆነ ነው። ለዚህም ምክንያቱ አንድ ወንጀል አድራጊ ሁለትና ከዚያ በላይ

[50]የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 187(1) እና (2-ለ) ስር የተደነገጉት ድንጋጌዎች የሚያሳዩት የማጠቃለል መርህን ነው።

ወንጀል ሲፈፅም የአደገኛነት መጠኑ ስለሚለያይ እና መቀጣትም ያለበት በዚሁ የአደገኛነቱ ልክ በመሆኑ ነው።

ከማጠቀለል መርህን ጋር በተያያዘ በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ያለውን አሰራር ስንመለከት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 184(1-ሀ) በሚያዘው መሰረት ዝቅተኛ ቅጣት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ከባድ ቅጣት በሚያስቀጡት ወንጀሎች አልፎ አልፎ በማጠቃለል መርህ ቅጣት እንደማይወሰን ባለሙያዎች ይገልጻሉ[51]። እንደ ምክንያት የሚቀርበው በወንጀል ህጉ ላይ የተመለከቱትን መርሆዎች ባለሙያዎች በአግባቡ ባለመረዳት እንደሆነ ነው የሚል ነው[52]። ለምሳሌ ያክል በአንድ መዝገብ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ወስደን ብንመለከት ወንጀል አድራጊው በ 2 ከባድ ሰው መግደልና በ 3 ተራ ሰው መግደል ሙከራ ወንጀል በድምሩ በ 5 ተደራራቢ ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ የተባለ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል። ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት የወንጀል አድራጊውን ባህሪ በመመልከት መነሻ ቅጣት የእድሜ ልክ መነሻ ቅጣት ከያዘ በኋላ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 184(1-ሀ) በሚያዘው መሰረት ሌሎቹ ወንጀሎች በእድሜ ልክ እስራት በሚያስቀጣው ወንጀል ይጠቃለሉ በማለት ካጠቃለለ በኋላ 3 የቅጣት ማቅለያ በመቀበል በቀድሞው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ለ 1 ቅጣት ማቅለያ 3 እርከን በመውረድ በድምሩ 9 እርከን በመውረድ ወንጀል አድራጊው በ 12 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የወሰነ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል[53]።ይህን ውሳኔ ስንመለከት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 184(1-ሀ) 2ተኛ ፓራግራፍ ስር የተመለከተውን መርህ ያላገናዘበ ነው። ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ በስተመጨረሻ የጣለው ቅጣት ቀድሞ መነሻ የያዘውን የእድሜ ልክ ቅጣት ባለመሆኑ ስለሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣቱን ማክበድ እንደሚገባ ህጉ በግልጽ ያመለክታል። ፍርድ ቤቱ ቅጣት ማቅለያ በመጠቀም ቅጣቱ ወርዶ 12 ዓመት ላይ ሲደርስ በተመሳሳይ የቅጣት ማቅለያዎች ለሌሎቹም በእድሜ ልክ ያስቀጡ ለነበሩት ተደራራቢ ወንጀሎች በትይዩ ቅጣት ማቅለያው ስለሚሰራ በውስጠ ታዋቂነት ለሁሉም ወንጀሎች ቅጣቱ ቀሎ 12 ዓመት እንደደረሰ መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም ፍርድ ቤቱ የመጨረሻውን ቅጣት ሲወስን እስከ 25 ዓመት ጽኑ እስራት ድረስ ለመቅጣት እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል።

[51]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 29 የተገለጸው
[52] ዝኒ ከማሁ
[53]የሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት የወ/መ/ቁ/ 0236951 በዐቃቤ ህግና በጌትነት ሰረቀ መካከል የተደረገ ክርክር

ሌላው የማጠቃለል መርህ የተመለከተው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 187(2-ለ) ሁለቱም በቸልተኛነት የተፈጸሙ ጣምራ ወንጀሎች ሆነው ግዙፋዊ ውጤት ያስከተሉ እንደሆነ ነው። የቅጣት አወሳሰን መመሪያው በአንቀጽ 22(1-ለ) ለአፈጻጸም ይረዳ ዘንድ በአንቀጽ 187/2-ለ/ መሰረት የሚኖር የወንጀል መደራረብ ባጋጠመ ጊዜ ለእያንዳንዱ ወንጀል ከመነሻው በ ሁለት እርከን እንዲያድግ ይደረጋል በሚል አስቀምጧል። ይህ ማለት በጣምራ ወንጀሎች ከተፈጸሙት ወይም ተደራርበው ከተጣሱት የህግ ድንጋጌዎች ውስጥ ለከፍተኛው መነሻ ቅጣት በማስቀመጥ ሌሎቹን እያንዳንዳቸውን እንደ ቅጣት ማክበጃ በመጠቀም ለእያንዳንዳቸው ከመነሻ ቅጣቱ በሁለት እርከን ማሳደግ ይገባል የሚል ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው በሚያሽከረክረው መኪና አንድ ሰው ቢገድል እና ሁለት ሰው ላይ የአካል ጉዳት ቢያደርስ በአንድ ድርጊት 3 ጣምራ ወንጀሎችን ፈጽሟል። ይሄውም በቸልተኝነት ሰው መግደል እና በቸልተኛነት በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል (አንቀጽ 60/ለ/ ሁለተኛ ፓራግራፍ) ቅጣቱ ሲሰላም በቸልተኛነት ለተፈጸመው ለሰው መግደሉ መነሻ ቅጣት በመስጠት ሁለቱን የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀሎች ለእያንዳንዳቸው በ 2 እርከን በማሳደግ ከመነሻ ቅጣቱ በ 4 እርከን በማሳደግ ቅጣት ይጣላል ማለት ነው። በአማራ ክልል በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከት ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች በቸልተኛነት የተፈጸሙ መሆናቸው ቢታወቅም ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 187(2-ለ) መሰረት ከባድ ቅጣት የሚያስቀጣውን በመውሰድ ሌሎቹን እንደ ቅጣት ማክበጃ በማድረግ እንደማይሰራና ቅጣት የሚጣለው በመደመር እንደሆነ ባለሙያዎች ይገልጻሉ[54]። በአንድ መዝገብ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ስንመለከት ዐቃቤ ህግ ባቀረበው በቸልተኛነት ሰው መግደልና በ 2 ሰዎች አካል ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል እንዲሁም በንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ 3 ተደራራቢ ክስ ቀርቦ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሲሰጥ በሁሉም ክሶች ጥፋተኛ ካለ በኋላ ለእያንዳንዱ ወንጀል ደረጃና እርከን በማውጣት መነሻ ከያዘ በኋላ ሁሉንም ወንጀሎች በመደመር ቅጣት ወስኗል[55]። ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የወንጀሉን ደረጃና እርከን በማሻሻል በተመሳሳይ የመደመር ስሌትን በመከተል ሁሉንም ተደራራቢ ወንጀሎች ደምሮ ቅጣት እንደወሰነ መዝገቡ ያመለክታል[56]።

[54]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 29

[55]የሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት/የወ/መ/ቁ. 0237320 የጠ/ፍ/ቤቱ 02-17007 ክሱ 2 በቸልተኛነት ሰው መግደልና አንቀጽ 543(3) በቸልተኛት በአካል ላይ ጉዳት አንቀጽ 559(2) ማድረስ ጥፋተኛ ተብለው ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሲጥል ለሁለቱም መነሻ ቅታት በመያዝ በመደመር እንዲቀጡ ሲል ወስኗል።

[56]የአብክመ ጠ/ፍ/ቤት የደብረ ብርሀን ቋሚ ችሎት የወ/መ/ዝ.ቁ. 16648 በዓቃቤ ህግና በጌትነት አምታቱ መካከል የተደረገ ክርክር

# 4. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

ተደራራቢ ወንጀሎች በባህሪያቸው ውስብስብ ስለሆኑና በፍሬ ነገር ላይ የተመሰረቱ ስለሆነ አንድን ድርጊት ተደራራቢ ነው አይደለም የሚለውን እንዲሁም ተደራራቢ የሆኑትን ተደራራቢ ካልሆኑት ወንጀሎች ለመለየትና ክስ አቅርቦ በፍርድ ቤት ውሳኔ ለመስጠት ቀላል ስራ አይደለም፡፡ በተለይም አንዳንድ ድርጊቶች ከላይ ሲታዩ ተደራራቢ የሚመስሉ ነገር ግን በጥልቀት ሲመረመሩ በአንድ ድንጋጌ ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉ ወይም ተደጋግመው ስለተፈጸሙ ብቻ ተደራራቢ ሊባሉ እንደማይገባ ህግ አውጭው ያስቀመጣቸው አሉ፡ ተደራራቢ ያልሆኑ የወንጀል ተግባሮችን በህግ አውጭው ከተቀመጠው ውጭ አላግባብ ተደራራቢ አድርጎ በመፈረጅ ወንጀል አድራጊው አላግባብ ከፍተኛ ቅጣት እንዳይጣልበት ባለሙያዎች ጽንሰ ሀሳቡን በአግባቡ በመረዳትና ፍሬ ነገሮችን ከወንጀል ህጉ ጋር በማገናዘብ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ሲወሰን የሚጣለው ቅጣት ከደረሰው ጉዳት አንጻር ተመጣጣኝ እንዲሆን በማሰብ የመደመርና የማጠቃለል የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች ተግባራዊ ሆነው ይገኛሉ፡፡ በተለይም እንደ ሞት፣ እድሜ ልክ ወይም በመጨረሻው ጽኑ እስራት ወይም ቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ከሌሎች ጋር ተደራርበው በመጡ ጊዜ ዝቅተኛ የሚያስቀጡት ወንጀሎች ከባድ ቅጣት በሚያስቀጡት ወንጀሎች እንዲጠቃለሉ የሚደረግበት ዘዴ ተቀምጧል፡፡ እንዲሁም ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች የተፈጸሙት በቸልተኛነት ወይም በጣምራ በሆነ ጊዜ ወንጀል አድራጊው አደገኛ የሚባል ባለመሆኑና ድርጊቱም አንድ ነጠላ ድርጊት በመሆኑ ቅጣቱ ሲጣል ከባዱ ወንጀል ከተመረጠ በኋላ ሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች እንደ ቅጣት ማክበጃ ሊወሰዱ እንደሚገባም በወንጀል ህጉ ላይ ተመልክቷል፡፡ የተደራራቢ ወንጀሎች ጽንሰ ሀሳብ በባለሙያዎች ዘንድ በአግባቡ ያላደገ በመሆኑ በፍርድ ቤቶችና በዐቃቢያነ ህግ መስሪያ ቤቶች በተግባር ጉድለቶች ይስተዋላሉ፡፡ ይሄውም በአንዳንድ ውስብስብ ጉዳዮች ተደራራቢ መሆን የሚገባቸውን ወንጀሎች በአንድ ድንጋጌ ይሸፈናሉ በሚል ክስ እንደሚቀርብና ቅጣት እንደሚወሰን መዛግብቶች ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል ህግ አውጭው አንዳንድ ጉዳዮች ከላይ ሲታዩ ተደራራቢ የሚመስሉ ነገር ግን በጥልቀት ሲመረመሩ በአንድ ድንጋጌ ስር ሊሸፈኑ እንደሚገባ የተመለከቱትን ጽንሰ ሀሳቡን ባለመረዳት ተደራራቢ አድርጎ በመውሰድ ህግ አውጭው ካስቀመጠው ውጭ ክስ ሲቀርብና ውሳኔ ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡ በቅጣት አጣጣል

ጊዜም የወንጀል ህጉ በአንቀጽ 184(1-ሀ) በሚደነግገው መሰረት በሞት፣ በእድሜ ልክ ወይም በጽኑ እስራት ወይም በቀላል እስራት የመጨረሻውን ጣሪያ የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው ሲመጡ ፍርድ ቤቱ መጀመሪያ ሊቀጣ ያሰበውን ያልቀጣው እንደሆነ ስለሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣቱን ማክበድ እንደሚገባ የዚሁ ድንጋጌ ሁለተኛ ፓራግራፍ በግልጽ አመልክቶ እያለ ፍርድ ቤቶች በህጉ አግባብ ቅጣት የማይወስኑበት ጊዜ እንዳለ መዘገቦች ይተቁማሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች የተፈጸሙት በቸልተኛነት በሆነ ጊዜ ቅጣት ሲጣል ከተደራራቢ ወንጀሎቹ ውስጥ ከባድ ቅጣት የሚያስቀጣው ተወስዶ ሌሎቹ እንደ ቅጣት ማክበጃ እንደሚወሰዱ የወንጀል ህጉ በአንቀጽ 187(2-ለ) ስር የተመለከተ ቢሆንም ይህን ባለመገንዘብ ቅጣት በመደመር ስሌት ሲወሰን ይስተዋላል፡፡ በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ጽንሰ ሀሳብ፣ ክስ አመሰራረትና ቅጣት አጣጣል ዙሪያ በባለሙያዎች ዘንድ የሚታዩ የግንዛቤ እጥረቶችን ለመፍታት ባለሙያዎች ተከታታይ የሆነ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል፡፡

# በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንዑስ-ቁጥሮች መካከል ያለው የልዩነት ወሰን እና በሥራ ላይ የሚታዩ ተግባራዊ ችግሮች

**ታፈሰች ወልዴ***

***አህፅሮተ ይዘት***

*የወንጀል ሃላፊነት ከሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች አንዱ የሞራል ክፍል ሲሆን በውስጡም የሃሳብ እና የቸልተኝነት ክፍል አካቶ ይዟል። በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀልን በተመለከተ በተሻሻለው የወንጀል ህግ የተጨመረው የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) ግልጽ ያለመሆን ለተለያየ የህግ ትርጉሞች የተጋለጠ እንዲሆን አድርጎታል። አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በተመረጡ ዞኖች ውስጥ ከተመለከትኳቸው የወንጀል መዛግብት የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) ዙሪያ የሚነሱ ሁለት የተለያዩ የህግ ትርጉሞች እንዳሉ ያሳያል። የመጀመሪያው ትርጓሜ የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ስር ከተዘረዘሩት አማራጮች ስር አንዱን ሁኔታ ሲያሟላ ሙያተኛ መሆን ሳይጠበቅበት በዚሁ አንቀፅ ስር ማንኛውም ሰው ጥፋተኛ መባልን ያስከትላል የሚል ሲሆን ሁለተኛውና ከዚሁ ተቃራኒ የሆነ የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(2) ተቀጣይ (Extension) በመሆኑ ይህ አንቀፅ ባለሙያ ለሆኑ ጥፋተኞች ብቻ የወንጀል ሃላፊነትን የሚያስከትል ነው የሚሉ ናቸው። የቸልተኝነት ጥፋትን ስንመዝን ልንከተላቸው ከሚገቡ የመመዘኛ መለኪያዎች ውስጥ ሰዎች ለነገሮች ያላቸውን ግንዛቤ አንዱ ሲሆን ሙያ ባለው ሰው እና ሙያ በሌለው ሰው መካከል ያለው የእውቀት መለያየት በተመሳሳይ ድርጊት የተለያየ የጥንቃቄ መለኪያ እንድንጠቀም የሚጠይቅ ሲሆን በስራ ላይ ግን ሙያ ያላቸውም ሆኑ ሙያ የሌላቸው በአንድ አንቀፅ ጥፋተኛ እሆኑ ይገኛሉ። ይህ ፅሁፍ የቸልተኝነት የመመዘኛ መለኪያዎችን በመከተል ሙያ ያላቸውን ሙያ የሌላቸው ሰዎች የጥንቃቄ ደረጃ ስለሚለያይ በተመሳሳይ አንቀፅ ጥፋተኛ ሊባሉ አይገባም የሚለውን ሃሳብ የሚያንጸባርቅ ነው።*

***<u>ቁልፍ ቃላት፡-</u> ቸልተኝነት፣ የጥንቃቄ መመዘኛዎች፣ ሙያ፣ ሌላ ግዴታ***

* LLM, LLB, በአብክመ የፍትሕ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት አሰልጣኝና ተመራማሪ

# 1. መግቢያ

ሰዎች በሚወስዱት እርምጃ የሌላ ሰውን ሞት ካስከተሉ አስበውም ሆነ በቸልተኝነት የሃሳብ ክፍላቸው (mental element) ልዩነት ሳይፈጥር ላደረጉት ወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ ይደረግ የነበረ ሲሆን ከአስራ ሁለተኛውም ክፍለ ዘመን ጀምሮ የወንጀል ጥፋተኝነት ሙሉ በሙሉ የተመረኮዘው በጥፋተኛው ድርጊት (actus reus) ላይ ብቻ ነበር[1]።ከአስራ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን በሃላ ግን የእንግሊዝ ህግ በተወሰነ መልኩ ሃሳባዊ ክፍል ሰዎችን ጥፋተኛ ለማለት አስፈላጊ መሆኑን በማመን የሃሳብ ክፍል በኮመን ሎው የህግ ስርአት ውስጥ እንዲዳብር አድርጓል።[2] በሃገራችን ኢትዮጵያም በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ 23 ስር የወንጀል ጥፋተኝነትን ለማቋቋም የሞራል ክፍል አንዱና ዋነኛው ፍሬ ነገር መሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እናገኘዋለን።ማንም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ለመሆንየድርጊት፣የሞራል እና የህግ መተላለፍ በአንድ ላይ ተሟልተው መገኘት ይኖርባቸዋል። የሞራል ክፍል በሁለት የሚከፈል ሲሆን የመጀመሪያውና ለማህበረሰቡ አስጊ ተብሎ የሚወሰደው ወንጀል የማድረግሃሳብ (intention) ሲሆን ሌላው የሞራል ክፍል ቸልተኝነት (negligence) በመባልይታወቃል።
ይህም በወንጀል ህግ አንቀጽ 59 ላይ በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል። በአሁኑ ጊዜ እየተበራከተ የመጣውን በቸልተኝነት የሚደርሱ ህልፈተ ህይወቶችን ለመቀነስ ሲባል የተለያዩ ሃላፊነትን የሚያስከትሉ ህጎች በሀገራችን ተደንግገው የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ከውል ውጭ ሃላፊነት እና የወንጀል ተጠያቂነት ዋነኞቹ ናቸው። በተለይ በተሸከርካሪ አደጋና በህክምና ሙያ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመቀነስ ሲባል በ1996 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የወንጀል ህግ ከዚህ ቀደም ከነበረው ንኡስ አንቀፅ በተጨማሪ ሌላ ሶስተኛ ንዑስ አንቀጽ ጨምሮ ተደንግጓል።[3]

ሆኖም በተሻሻለው የወንጀል ህግ የተጨመረውን አዲስ አንቀፅ መሰረት በማድረግ የሚነሱ ሁለት አከራካሪ ነጥቦች ሲነሱ ይስተዋላል። የመጀመሪያው የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3)[4] ሙያ ለሌላቸው ሰዎች ጥፋተኛ ለማድረግ ይችላልን? የህጉ መልዕክት የተቀመጡ አማራጮች ተሟልተው መገኘታቸው ነው የሚል ሲሆን ሁለተኛው የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ሊውል

[1]JOSHUADRESSLER,UNDERSTANDING CRIMINAL LAW, (5thedi.,2006) ገፅ 5።
[2] FrancisB.sayre, means rea, Harvard law review 45(1932) p.974
[3]የኢትዮጵያ ፌድራላዊ ዲሞክራያሳዊ ሪፐብሊክ የተሻሻለው የወንጀል ህግ ሀተታ ዘ ምክንያት፣ 1996 ገፅ 258 እንዲሁም አዋጅ 414/1996 የተሻሻለው የወንጀል ህግ፣ 1996 ዓ.ም
[4]አዋጅ 414/1996 የተሻሻለው የወንጀል ህግ፣ 1996 ዓ.ም

የሚገባው የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ላለባቸው ሰዎች ብቻ ነው እንጂ በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(1) ላይ ለተቀመጡት ሙያ የሌላቸው ሰዎች አንቀፅ 543(3) ላይ የተቀመጡትን አማራጮች አሟልተው ስለተገኙ ብቻ በዚሁ አንቀፅ ጥፋተኛ ሊባሉ አይገባም የሚል ነዉ፡፡ እነዚህ የተለያዩ የትርጉም ፅንፎችን በመያዝ በተለያየ መንገድ ድንጋጌው ስራ ላይ ሲውል ይስተዋላል[5]፡፡ስለሆነም የዚህ ንዑስ አንቀፅ መጨመር ያስከተለው የትርጉም ልዩነትን ለመረዳት ያስችል ዘንድ በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(2) እና 543(3) ያለውን ልዩነት በማሳየት እና በስራ ላይ የሚታዩትን እነዚህን የትርጉም ልዩነቶች ከቸልተኝነት መመዘኛ መለኪያዎች ጋር በማስተሳሰር ሰፋ ባለ መልኩ ተዳሰዋል፡፡

### 1.1 የወንጀል ቸልተኝነት ትርጉም

ከህግ መዝገበ ቃላት ታዋቂ ከሆነው አንዱ ብላክስ ሎው የቸልተኝነትን ጽንሰ ሃሳብ በሚመለከተው መልኩ ያስቀምጠዋል:: “ቸልተኝነት ማለት ጥፋተኛው አንድ አስተዋይ ሰው በተመሳሳይ ጉዳይ የሚያደርገውን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በህግ ማህበረሰቡን ከማይገባ ጉዳት ለመጠበቅ ከተደነገገው የጥንቃቄ ልክ በታች ያሉ ተግባራት ሲፈፅም ነው”[6]፡፡ የሃገራችንን የወንጀል ቸልተኝነት ትርጉም ከማየታችን በፊት ቸልተኝነት ይበልጥ የዳበረበትን ኮመን ሎው የህግ ስርዐት ውስጥ ያሉ ሃገራት ቸልተኝነትን በምን መልኩ እንደሚተረጉሙት ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በአሜሪካ ያሉ ግዛቶች በአጠቃላይ እንደ መነሻ የሚጠቀሙበት /ሞዴል የወንጀል ኮድ (model penal code) ሲኖር ይህ ሞዴል የቸልተኝነትን ትርጉም ሲያስቀምጥ:- አንድ ሰው ቸልተኝነት ፈጽሟል የሚባለው ከድርጊቱ የተነሳ ከፍተኛ እና ምክንያታዊ ሊባል የሚችል ጉዳት

[5]የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ስልጠና መመሪያ ቁ. 2/2005 በዚህ መመሪያ የተሳተፉ ኮሚቴ አባላት (ዳኛ አልማው ወሌ፣ ዳና ተክሊትይመሰል፣ዳኛ አንዳርጋቸው ወዳጄ፣ አቶ ከድር መሃመድ የፌደራል ከፍተኛፍርድ ቤት ዳኛ፤ አቶ ሰዓረ መንግስቱ) ሀምሌ/2006 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ፤ በተሻሻለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን ማንዋል ላይ ጥናቱን ባካሄዱ ቡድኖች ከተሰጠ የስልጠና ማንዋል ላይ የተወሰደ፡፡ በዚህ ማንዋል ላይ የወንጀልህግ 543(3) ሙያተኛ ላልሆኑ ጥፋተኞች የሚያገለግል ነው የሚለውን ክርክር እንዲሁም የወንጀል ህግ 543(3) የወንጀል ህግ 543(2) ተቀጣይ በመሆኑ ሙያተኛ ለሆኑ ሰዎች ብቻ ነው የሚያገለግሉት የሚሉት የክርክር ሃሳቦች የወንጀል ህግ የቅጣት ማዕዋል ላይ ለዐ/ህግ እና ዳኞች በተሰጡ ስልጠና ላይ እነዚህ ሁለት የህግ ትርጉሞች መኖራቸውን ተመልክቷል፡፡

[6]Bryan.A.Garner, Blacks law dictionary,2004,8th edition, west a Thomson business, p.1074, “negligence is the failure to exercise the standard of care that a reasonably prudent person would have exercised in a similar situation, any conduct that falls below the legal standard established to protect other against unreasonable harm”

ሲያስከትል እና ይህም ድርጊት አንድ አስተዋይ ሰው ከሚያደርገው የጥንቃቄ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ያፈነገጠ እንደሆነ ነው[7]።

ከላይ እንደተመለከትነው በኮመን ሎው ሃገራት የቸልተኝነት ትርጉም መሰረት ያደረገው ከቸልተኝነቱ ግዘፈት አንፃር የተቃኘ ነው። የጥፋተኝነቱን ክብደት ለማሳየትም የአስተዋይ ሰው መመዘኛ አንደ መለኪያ የተወሰደ መሆኑን እና አንድ ሰውም ቸልተኝነት አለበት ለማለት አስተዋይ ሰው ይወስደዋል ተብሎ የሚገመተው የጥንቃቄ መጠን በከፍተኛ ደረጃ ተላልፎ ሲገኝ ብቻ ጥፋተኛ ሆኖ የሚገኝ መሆኑን ያሳየናል። ከዚህም የተነሳ የኮመን ሎውየህግ ስርዓትን የሚከተሉ ሃገሮች በአብዛኛውተራ ቸልተኝነትን (ordinary negligence) እንደ ቸልተኝነት የማያካትቱ ሲሆን ሰዎች ሊቀጡ የሚገባቸው የቸልተኝነት ድርጊታቸው ከመደበኛው የጥንቃቄ ደረጃ የወጣ (deviate) በሚያደርግበት ሁኔታዎች ብቻ ነው። ወደ ሀገራችን ስንመጣ ከኮመን ሎው ሃገራት በተለየ ተራ ቸልተኝነቶች ጭምር የወንጀል ሃላፊነትን እንዲያስከትሉ ተደርጎ ተደንግጓል። በ1996 ዓ.ም በተሻሻለው የወንጀል ህግ አንቀፅ 59 እንደተመለከተው ቸልተኝነት ሃላፊነትን *የሚስከትለው*

*"ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስምበሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን"* እንዲሁም *"ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ"* በቸልተኝነት ወንጀል የፈጸመ እንደሆነ በማለት ተቀምጧል።

በዚህ ትርጉም ውስጥ ሁለት አይነት የቸልተኝነት አይነቶችን የምናገኝ ሲሆን አንደኛው አይደርስም በሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን *"lack of foresight or imprudence*" ሊፈጸም የሚችል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ድርጊቱ በወንጀል እንደሚያስቀጣ "ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ" ነገር ግን ባለመገመት ወይም ባለማሰብ የሚፈጸም ቸልተኝነት ናቸው። ለምሳሌ አንድ ሰው ዛፍ ሲቆርጥ ከታች የሚያልፍ ሰው የቅርንጫፉ ግንድ ወድቆበት ቢሞት ድርጊቱ የተፈፀመው አይደርስም በሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን በመሆኑ በህግ የሚፈለገው የቸልተኝነት ፍሬ ነገር በሚሟላቱ ቸልተኛ ነው ይባላል። አንድን የቸልተኝነት ወንጀል ተራ

[7]Model penal code of the united states, official draft,(Philadelphia: American law institute,1962) ,general section/d/, p.21.Negligence:-"A person acts negligently with respect to a material element of an offence when he should be aware of a substantial and justifiable risk that the material element exisits or will result from his conduct. the risk must be of such a nature and purpose of his conduct and their circumistances known to him, involves a gross deviation from the standard of care that a reasonable person would observe in the actors situation''

ወይም ከባድ ሊያስኛቸው የሚያስችሉ መመዘኛዎች ያሉ ሲሆን በሚቀጥለው ክፍል በዝርዝር እንመለከተዋለን፡፡

### 1.2 የወንጀል ቸልተኝነት መመዘኛዎች

የወንጀል ሃላፊነት መመዘኛን ለማስቀመጥ ዋነኛው ችግር መደበኛ ባህሪያት ከሰው ሰው መለያየታቸው ሲሆን አንድ የጋራ የሆነ መለኪያ ለማስቀመጥ ሰዎች ያላቸውን አቅም እንዴት ይጠቀምበታል የሚለውን በእርግጠንነት ምላሽ መስጠት ያስቸግራል፡፡ ለምሳሌ ሰዎች ከሰዎች በእውቀት፣ በእድሜ እንዲሁም በጊዜው በነበራቸው የአይምሮ ሁኔታ ማለትም መደሰት፣ መበሳጨት፣ መድከም፣ ከግምት አስገብቶ የጋራ የሆነ ወጥ መለኪያ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህም ቢሆን የማህበረሰቡን የጥንቃቄ መጠን ለመለካት በጠቅላላው የተቀመጡ መለኪያዎች ዘዴዎች ሲኖሩ እነዚህም ወጥ መለኪያ እና ወጥ ያልሆኑ መለኪያዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡

#### 1.2.1 ወጥ መለኪያ (objective standard)

ወጥ ስለሆነ መለኪያ ጽንሰ ሀሳብ ሲነሳ በብዙዎች አይምሮ የሚመላለሰው የአስተዋይ ሰው መለኪያ የሚለው ፅንሰ ሃሳብ ሲሆን ይህም የመመዘኛ አይነት በተለያዩ የህግ ስርዐቶች ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ “አስተዋይ ሰው መለኪያ” (reasonable person standard) ስንልም አንድ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ ሃሳባዊ አስተዋይ ሰው የሚያደርገው መካከለኛ ጥንቃቄ እንዲሁም ይህ ሃሳባዊ አስተዋይ ሰው ያለው ክህሎት ነገሮችን አገናዝቦ የመወሰን ብቃቱ እንደ ወጥ መለኪያ (objective standard) የሚያገልግል ሲሆን የአጥፊውን ተጠያቂነትን ለመወሰን እንደ ተነጻጻሪ መለኪያ ያገለግላል[8]፡፡ ወጥ መለኪያ ስንጠቀም እጅግ ጠንቃቃ የሆነውን እና ምንም ጥንቃቄ የማያደርገውን በመውሰድ ከሁለቱ የተራራቀ የጥንቃቄ መጠን አማካይ የሆነ መነሻ በመውሰድ ምክንያታዊ ሊያስብል የሚችል መመዘኛ ለመፍጠር ነው፡፡[9] *በአጠቃላይ አስተዋይ ሰው* “reasonable person” የሚወክለው በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሰዎች በአብዛኛው በሚከሰቱ

[8]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6፣ ገፅ 1294፡፡ reasonable person standard:- A hypothetical person used as a legal standard to determine whether someone acted with negligence specifically a person who exercises the degree of attention, knowledge intelligence and judgment that society requires of its members for the protection of their own and others’ interests. The reasonable person acts sensibly does things without serious delay, and takes proper but not excessive precaution also termed a reasonable man.

[9]The free legal dictionary available at:-http://legaldictionary.thefreedictionary.com/Reasonable+person+standard accessed at may, 25, 2016 at 9:07.

ድርጊቶች ላይ የሚያሳዩት የጥንቃቄ መጠን ነው።[10] ለምሳሌ በተጠረጠረበት ድርጊት አንድ አስተዋይ ሰው ሊያደርገው የሚገባውን መካከለኛ ጥንቃቄ (average care) ተከሳሽ አድርጉዋል ወይ? የሚል ሲሆን በኮመን ሎው ሃገራትም "አስተዋይ ሰው መለኪያን" (reasonable person standard) ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ነው።

### 1.2.2 ወጥ ያልሆነ መለኪያ (subjective standard)

ወጥ ያልሆነ መለኪያ ስንል እንደ አጥፊው የግል ሁኔታ የምናይበት የመመዘኛ ስልት ነው።[11] ለምሳሌ፦ የአጥፊውን ዕድሜውን ሁኔታ ከግምት በማስገባት በዚያ እድሜ ላይ ያለ ሰው ድርጊቱ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት በማወቅ /በመገመት ጥንቃቄ መውሰድ ነበረበት በሚል የአጥፊውን የቸልተኝነት መጠን ሊወስድ ከሚገባው የጥንቃቄውን እርምጃ አንጻር በመለካት ነው። ጠቀሜታው በተለይ እንደ ሃገራችን ባሉ የተማረ ማህበረሰብ ባልተበራከቱበት የሰዎችን የአስተሳሰብ እና የአኗኗር ዘዬን የአገናዘበ (flexible) መለኪያ ከመሆኑ አንጻር ፍትሃዊ ሊባል የሚችል ነው። የወንጀል ህግ አንቀፅ 59(1)(ለ) ላይ እንደተመለከተው ቸልተኝነት አለ ለማለት የአድራጊው የግልሁኔታማለትም እድሜ፣ የኑሮ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ስራው በተጨማሪም የማህበራዊ ኑሮው ተመዝኖ ቸልተኛ ሊባል እንደሚገባው ከድንጋጌው መረዳት ይቻላል።

ሆኖም ሁሉም የጥንቃቄ ደረጃዎችን በህግ መሸፈን አስቸጋሪ ቢሆንም ጠቅላላ የጥንቃቄን መለኪያ ተብለው የተቀመጡት የአስተዋይ ሰው መመዘኛ እና የወንጀል አድራጊው የግል ሁኔታ መመዘኛዎች ናቸው[12]። ፀሃይ ወዳ የተሰኘው ፀሃፊ የወንጀል ህግ መሰረታዊ መርሆች በሚለው መጽሃፉ ላይ እንደገለፀው "በቸልተኝነት ለተፈፀመው ወንጀል ጥፋተኝነትን ለመወሰን በቅድሚያ **ትክክለኛ አይምሮ ካለው** ሰው የሚጠበቀውን ጥንቃቄ ማድረጉን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሲሆን በመቀጠልም ከግል ሁኔታ የተነሳ ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ማድረጉም መረጋገጥ አለበት"[13]። ይህም ማለትአንድን ሰው ቸልተኝነት ስንለካ በድርጊቱ አንድ አስተዋይ ሰው ሊወስድ የሚገባውን ጥንቃቄ ወስዷል ወይ እንዲሁም የጥፋተኛውን የግል ሁኔታ ለምሳሌ እንደ እድሜ፣የኑሮልምድ...የመሳሰሉት መመዘኛዎች ተጠቅመን የጥንቃቄውን ልክ መመዘን እንዳለብንና ቸልተኝነትን ስንለካ ሁለቱንም መስፈርቶች መጠቀም እናዳለብን ያሣየናል።

---

[10]ፀሃይ ወዳ፣ <u>የወንጀል ህግ መሰረታዊ መርሆች፣</u> ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ ጥር 19/1994 ዓ.ም ገፅ 59።

[11]ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 58

[12]Graven Philippe, **An Introduction to Ethiopian Penal Law, Haile Selassie university, 1965.p.160**

[13]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር10፣ ገፅ 59። ማሳሰቢያ፦ የዚህ መጻሃፍ ፀሃፊ ትክክለኛ አይምሮ ያለው ሰው በሚል የገለጸው /reasonable person/ ለማለት መሆኑን ከግንዛቤ እንዲገባ።

ይህንንም ሃሳብ በሚያጠናክር ሁኔታ ፊሊጵ ግራቨን[14] አንድ ሰው በወንጀል ቸልተኛ ነው የሚባለው አንድ አስተዋይ ሰው የሚፈፅመውን ጥንቃቄ ባለመፈጸሙ ብቻ ሳይሆን ከእሱ የሚጠበቀውን ምክንያታዊ የሆነ በድርጊቱ ሊወስድ የሚገባውን የጥንቃቄ መጠን ሳያደርግ ሲቀር ነው በማለት ያስቀምጠዋል። ስለዚህ በሃገራችን የወንጀል ቸልተኝነትን ለመመዘን ሁለቱንም የመመዘኛ መለኪያዎች ከግምት በማስገባት መጠቀም እንዳለብን ያሳየናል። ይህ ማለት በሃገራችን ወጥ የሆነና ወጥ ያልሆነ መለኪያን በመጠቀም ቸልተኝነት ሊለካ እንደሚገባው ነው።

### 1.3 የወንጀል ቸልተኝነት አይነቶች

በ1949[15] ተደንግጎ በስራ ላይ የነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስለቸልተኝነት አይነቶችን በዝርዝር ሳያስቀምጥ በደፈናው ስለ ቸልተኝነት አይነቶች የሚደነግግ የነበረ ቢሆንም የተሻሻለው የወንጀል ህግ እነዚህን የቸልተንነት በግልፅ አካቶ ይዟል[16]። የወንጀለኛ ህግ አንቀፅ 59 በጥሞና ስንመለከተው ሁለት አይነት የወንጀል ቸልተኝነት የሚሰጠን ሲሆን ይህውም፡-

**ሀ.አስቀድሞ የታወቀ ቸልተኝነት** (Advertent negligence)

አስቀድሞ የታወቀ ቸልተንነት ማለት አንድ ሰው የሚያደርገው ድርጊት ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት አውቆ ነገር ግን ጉዳቱ አይደርስም በማለት ድርጊቱን መፈጸም ነው።[17]ይህ የቸልተኝነት አይነት በአብዛኛው የሚዛመደው ዶሎስ ኢቬንቹዋሊስ (Dolus eventualis) በመባል ከሚታወቀውና በሃገራችንም ቀጥተኛ ያልሆነ ሃሳብ (indirect intention) በመባል ከሚታወቀው ጽንሰ ሃሳብ ጋር በአያሌው የሚመሳሰል ነው[18]። ዶሎስ ኢቬንቹዋሊስ የሚለው ቃል የላቲን ቃል ሲሆን ከጀርመን የህግ ስርዐት ውስጥ የተወሰደ ፅንሰ ሃሳብ ነው[19]። የዚህ ቃል ቀጥተኛ ትርጉሙም ሊደርስ ወደሚችል ነገር የተጠጋ ፍላጎት ነው[20]። ይህ ቀጥተኛ ያልሆነ ሃሳብ ድርጊቱ ሊያስከትል ስለሚችለው ጉዳት እውቀት (knowledge) እና ድርጊትን (condact)

---

[14]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 12፣ ገፅ 160። "a person is criminally negligent, not whenever, he fails to exercise the care which a reasonable man would exercise, but when he fails to exercise the care that can reasonably be required "of him" in the circumstances".

[15]በ1949 ተደንግጎ የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 59 ገፅ 25

[16]የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የተሻሻለው የወንጀል ህግ ሀተታ ዘምክንያት (ያልታተመ) ገፅ 34

[17]ሮናልድ ስክላር፣ የኢትዮጵያ የህግ መፅሄት "ፍላጎት": "አንድ ነገር በእርግጥ እንዲሆን ማወቅና": ዶሎስ ኢቬንቹዋሊስ: አንድን ነግር ሆነ ብሎ አውቆ ማድረግ በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ፣ ቅፅ፣ 8 ቁጥር 2፣ ገፅ 329፣ ታህሳስ፣ 1965 ዓ.ም

[18]ከላይ የግርጌ ማስታወሻ 10፣ ገፅ 56።

[19] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ 16፣ ገፅ 386።

[20]ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 388።

በውስጡ ያካተተ ነው።ቀጥተኛ ባልሆነ ሃሳብ እና አስቀድሞ በታወቀ ቸልተኝነት በመካከላቸው ያለው ተመሳሳይነት ሁለቱም ሊከሰት ስለሚችለው ጉዳት እውቀት (knowledge) ያላቸው ሲሆን ከቀጥተኛ ያልሆነ ሃሳብ (indirect intention) የሚለየው ውጤቱን በመቀበል ደረጃ ያላቸው ልዩነት ነው። የታወቀ ቸልተኝነት ውጤቱን ቢገምትም አይደርስም ብሎ ባለመቀበል ድርጊቱን የሚፈፅም ሲሆን ቀጥተኛ ያልሆነ ሃሳብ (indirect intention) ግን ድርጊቱን በሚያከናውንበት ግዜ ውጤቱ ቢድርስም ይደርስ ብሎ በመቀበል ድርጊቱን መፈጸሙ ነው[21]።

አንድ ጥፋተኛ አስቀድሞ የታወቀ ቸልተኝነት ነበረው ለማለት ከድርጊቱ አፈፃፀም ቸልተኝነቱን በመገንዘብ መሆን አለበት። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ ለመጥቀስ የባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር04-01174[22] ተከሳሽ መኪና ለማሽከርከር መንጃ ፍቃድ ሳይኖረው ሲያሽከረክር... ከመስመሩ ወጥቶ ከድንጋይ ጋር በመጋጨቱ እና አደጋ ማድረሱ ሲታይ መጀመሪያውኑ የማሽከርከር ብቃት ሳይኖረው ማሽከርከሩ አድራጎቱ በታወቀ ቸልተኝነት የተፈፀመ መሆኑን የሚያሳይ ነው በማለት አጥፊው ማሽከርከር ሳይችል መንዳቱ አስቀድሞ የታወቀ ቸልተኝነት አድርጎ መውሰድ የተከሻሹን ድርጊት መነሻ አድርጎ መውሰዱን ፍርድ ቤቱ ከሰጠው ውሳኔ መረዳት ይቻላል።

**ለ.አስቀድሞ ያልታወቀ ቸልተኝነት** (inadvertent negeligence)

ይህ የቸልተኝነት አይነት ማወቅ ሲገባው ወይም እየቻለ ነገር ግን ይህን በመተው የተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ሲሆን ሳያመዛዝኑ የሚደረግ ድርጊት (Acting without consideration) በመባል ይታወቃል።[23] በታወቀና ባልታወቀ ቸልተኝነት መካከል ያለው ልዩነት የመጀመሪያው ወንጀለኛው ድርጊቱን ሲፈጽም ውጤቱን ሊድረስ እንደሚችል ቢገምትም አይደርስም ብሎ ውጤቱን ካለመቀበል ጋር የተያያዘ ሲሆን ሁለተኛው ሊደርስ የሚችለውን ውጤት ወንጀለኛው ማገናዘብ ወይም መገመት ሲገባው ሳይገምት የሚያደርገው ድርጊት ያስከተለው ውጤት ነው።[24] የድርጊቶች በታወቀ ቸልተኝነት መፈጸም የጥፋተኝነት ሃላፊነትን የሚያከብድ ምክንያት መሆኑን እና ባልታወቀ ቸልተኝነት የሚደረጉ ጥፋተኞች ደግሞ ከዚህ በተለየ ተመጣጣኝ የጥፋተኝነትሃላፊነት እንደሚተላለፍባቸው የተሸሻለው የፌደራል ቅጣት ማንዋሉ ያስገነዝበናል።

[21]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 10፣ ገፅ 56
[22]በከሳሽ ዐ/ህግ እና ግርማው በቀለ በባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀን ታህሳስ 14/2008ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ።
[23]ከላይ በግርጌ ማስተወሻ 4፣ ገጽ 40።
[24]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ፣12ገፅ160።

ይህንንም ሃሳብ ለማጠናከር የቸልተኝነት አይነቶቹ በተከለሰው ቅጣት ማንዋል[25] ሰንጠረዥላይ የቸልተኝነት አይነቶቹ የቅጣት ደረጃን ከፍ እና ዝቅ ለማድረግ እንደ ግብዐት ተወስደዋል።

### 1.4 የቸልተኝነት እና የድንገተኛ ነገር ወይም አደጋ የልዩነት ወሰን

አደጋ የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ብላክስ ሎው የህግ መዝገበ ቃላት ሲያስቀምጠው አደጋ ያልታሰበ ወይም ይደርሳል ተብሎ ሊገመት የማይችል አጋጣሚ ሲሆን በተለምዶ ሁኔታዎች ከሚከናወኑበት ወጣ ባሉ ሁኔታዎች የሚከሰት ወይም ሰዎች በችሎታቸው ወይም በምክንያታዊ እይታቸው ሊከላከላቸው/ ሊያስቀሯቸው የማይችሉዋቸው አጋጣሚዎች ናቸው በማለት ይህ መዝገበ ቃላት ያስቀምጠዋል።[26] የወንጀል ህግ በአንቀፅ 57(2)[27] አንድ ሰው ያደረገው ድርጊት በወንጀል ህግ የሚያስጠይቅ ቢሆንም ምንም ጥፋት ሳያደርግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሃይል ምክንያት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሃይል ምክንያት ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ነገር የተፈፀመ ወይም የደረሰ እንደሆነ በወንጀል እንደማያስጠይቅ ይደነግጋል። አደጋከቸልተኝነትጋር ያለውን ዋነኛ ልዩነት ለመወሰን ሁለቱ ሃሳቦች የሚያቋቁሟቸውን ፍሬ ነገሮች ማየት ተገቢ ነው። የወንጀል ህግ አንቀፅ 59 በጥሞና ስንመለከት የሚከተሉት ፍሬ ነገሮች በውስጡ ይገኛሉ።በመጀመሪያ ማንኛውም በቸልተኝነት ጥፋተኛ የሚባል ሰው የሚፈፅመው ድርጊቱ ጉዳት ሊያስከትል እንሚችል ማወቅ ሲገባው (imprudence) ባለማወቅ ያደረገው ከሆነ በህጉ ቸልተኛ ተብሎ እንደሚወሰድ ህጉ ያስቀምጣል። ሁለተኛው አጥፊው ወንጀል ለመስራት ሃሳብ ባይኖረውም (Acting by a criminal lack of foresight) በድርጊቱ የወንጀል ሃላፊነትን ካስከተለ እንዲሁም በሶስተኛ ደረጃ ድርጊቱ በወንጀል ሃላፊነትን ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ ሲገባው ነገር ግን ይህን ባለማወቅ ወንጀል የሰራ አንደሁ በማለት በአንቀጽ 59 ላይ ዘርዝሮ አስቀምጦዋቸዋል። ስለዚህ ቸልተኝነት በአድራጊው በሚፈጸመው ጥፋት ላይ የሚመሰት መሆኑን ያሳየናል። ነገር ግን ድንገተኛ አጋጣሚ/አደጋ ከአቅም በላይ በሆኑ ሁኔታዎችን እና የድርጊቱ ፈጸሚ ጥፋት በየትኛውም ቦታ ላይ ያለመኖሩ በሁለቱ ፅንሰ ሃሳቦች መካከል ያለ መሰረታዊ የሆነ ልዩነት ነው። ከወንጀል ህግ መርሆች አንዱ ሰዎች

[25]በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሻሻለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ለምሳሌ፦ አንቀፅ 543(1) ደረጃ ሲወጣ ለደረጃው ድርጊቱ በ6 ደረጃዎች ተከፋፍሎ የተቀመጠ ሲሆን ከነዚህ ደረጃዎች ውስጥ ደረጃ 4 ላይየወንጀሉ ድርጊት የተፈጸመው አደገኛ ባልሆነ መሳሪያ እና ባልታወቀ ቸልተኝነት በሚል አስቀምጦታል።

[26]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 6፣ ገፅ15-16። Accident is unintended and unforeseen Injurious occurrences; something that does not occur in the usual course of events or that could be reasonably anticipated or not having occurred because of anyone's purposeful act; esp. resulting from an event that could have been prevented by human skill or reasonable foresight.

[27]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 4፣ ገፅ 40

ያለጥፋታቸው ሊቀጡ አይገባም የሚል ሲሆን በወንጀል ጥፋተኛ ለመባልም የሞራል ክፍል (moral element) መሟላት በቸልተኝነት እና በአደጋ መሃል ያለው ዋነኛ ልዩነት ነው።

### 1.4 የወንጀል ቸልተኝነት ንድፈ ሃሳብ (A THEORY OF *CRIMINAL* NEGLIGENCE)

የወንጀል ቸልተኝነት ንድፈ ሃሳብ በተመለከተ የተለያዩ ጎኖችን ይዘው ምሁራን ይከራከራሉ። ይኸውም በአንድ በኩል የቸልተኝነት ፅንሰ ሃሳብ ታስቦ (with intention) የሚፈፀም ካለመሆኑና የአደገኝነቱም መጠን እንደታስቦ የሚፈጸም ወንጀል በፍላጎት የሚደረግ ወንጀል ካለመሆኑ አንፃር ቸልተኝነት የፍታብሄር ሃላፊነት እንጂ የወንጀል ሃላፊነትን ሊያስከትል አይገባውም[28] ሲሉ ሌላኛዎቹ በተቃራኒው የአደገኝነቱ መጠን የከፋ ባይሆንም በመርህ ደረጃ ቸልተኝነት በወንጀል ሊያስጠይቅ ይገባልየሚሉ ክርክሮች ያነሳሉ። እነዚህን ክርክሮች ፊሊፕ ግራቨን[29] በፃፈው መፀሃፍ ላይ ቸልተኝነት ሊያስቀጣ ይገባል አይገባም በሚል ዙሪያ የሚነሱትን ክርክሮች በጽሁፉ ላይ በጥቂቱ አንስቷቸዋል[30]። በእነዚህ ክርክሮች ዙሪያ በሁለት ታላቅ ምድቦች ተከፍለው የተቀመጡ እይታዎች አሉ። ይኸውም ወጥ ያልሆነአተያይ (subjectivist approach) እና ወጥ የሆነ አተያይ (objectivist approach) በመባል ይታወቃሉ።[31]

#### 1.4.1 ወጥ ያልሆነ አተያይ (subjectivist approach)

ወጥ ያልሆነ አተያይ (subjectivist approach) አንድ ሰው የወንጀል ሃላፊነት አለበት ለማለት ያልተገባ የሞራል ጥፋትየማድረግ ሃሳብ (culpability) ማሳየቱ እንደ አስፈላጊ ሁኔታ የሚወሰድ ነው።[32] ይህም አተያይ በመሰረታዊነት ጥፋት ላይ ያተኮረ ነው። ወጥ ያልሆነ አተያይ አላማው የወንጀል ሃላፊነትን መገደብ ሲሆን አጥፊዎች ድርጊቱን ሲፈጽሙ አስበው ያደረጉት ወይም ጉዳት እንዳይደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አስቀድመው ይመጣል/ይደርሳል (foresight) ብለው መገመት እየተገባቸው ለተደረጉ ሁኔታዎች ብቻ የወንጀል ሃላፊነት እንዲኖር ለመወሰን ነው። በዚህ አተያይ መሰረት ታስበው የሚደረጉ ድርጊቶች ብቻ ተጠያቂነት እንዲያስከትሉ በር የሚከፍት ሲሆን የመጣው ይምጣ በሚል የሚደረጉ (recklessness) በመባልየሚታወቀው ቸልተኝነት የጥፋት ደረጃቸው ከፍ ያለ በመሆኑ ብቻ እንዲያስቀጣ

[28]Jerome H.,*Negligent Behavior Should Be Excluded From Penal Liability*, 63 colombia law review, 632, 641 (1963)
[29]ይህ ፀሃፊ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሲረቀቅ የነበረና የወንጀለኛ መቅጫ ህጉን በግዜው ከተወሰደባቸው ፈረንሳይ እና ሰዊዝ ሃገር የወንጀል ህግ ጋር በማዛመድ ማባራሪያ የፃፈ ነው።
[30]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 12፣ በገፅ 161
[31]Victor Vridar Ramraj, A theory of criminal negligence, University of Toronto, p.5 (1998).
[32]ዝኒ ከማሁ

ከመፍቀድ ውጭ[33] ሌሎች ቸልተኝነቶች የወንጀል ሃላፊነት ማስከተል የለበትም በማለት አቋማቸውን ያስቀምጣሉ፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የአሜሪካውን ሞዴል ፔናል ኮድ ሲሆን ይህ ሞዴል አሜሪካ ላሉዋት የተለያዩ ግዛቶች የተለያዩ የወንጀል መርሆችን በማስቀመጥ እንደ መነሻ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን ከፍ /gross/ የሆነ ቸልተኝነቶች ብቻ እንዲያስቀጡ ይደነግጋል[34]፡፡ በዚህ አተያይ እምነት ሰዎች በአጋጣሚ ለተፈጠሩ ነገሮችሃላፊ ተደርገው በወንጀል ሊጠየቁ አይገባቸውም የሚለው መርህ ይህን አተያይ የሚያራምዱ ሰዎች የሚጋሩት ነው፡፡

### 1.4.2 ወጥ የሆነ አተያይ (objectivist approach)

ወጥ የሆነው አተያይ ቸልተኝነት እንዲያስቀጣ ቢፈቅድም እንደ ወጥ ያልሆነ እይታ ያልተገባ ጥፋትየማድረግ ሃሳብ (culpability) በወንጀል ሃላፊነትን ለማስከተል እንደ ዋና መመዘኛነት አይወስድም[35]፡፡ በዚህ አተያይ ቸልተኝነት ማስቀጣት አለበት፡፡ይህም አተያይ መደበኛ (ordinary) የቸልተኝነት አይነቶች ማህበረሰቡ ላይ ከሚያደርሱት ጉዳት አንፃር የአደገኝነታቸው መጠን ከፍያለ ነው ባይባልም ጥፋት ለሆነ ቸልተኝነታቸው ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲያስከትል ማድረግ አለባቸው የሚል እምነትን የያዘ ነው፡፡ይህን እይታ የሚያደግፉ ሰዎች ምንም እንኩን ታስበው ባይገረጉም አስቀድሞ የታወቀ ቸልተኝነቶች ለማህበረሰቡ ከሚያደርሱት ጠንቅ አኳያ ሊያስቀጡ ይገባቸዋል የሚል አቋም አላቸው፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚያስቀምጠው በውስጣቸው የያዙት የጥፋተኝነት እና የጣሱት የጥንቃቄ ደረጃ ከፍ ያለ በመሆኑ በወንጀል ሃላፊ ተደርገው ሊወሰዱ ይገባል የሚል ነው፡፡[36] ከላይ ካየነው እይታ ቸልተኝነት ከፍተኛ (gross) ካልሆነ ጭራሹንም ሊያስቀጣ አይገባውም ከሚለው ሃሳብ ለየት ባለ ቸልተኝነት በተወሰነም መልኩ ቢሆን በዚህ አተያይ መሰረት የወንጀል ሃላፊነትን እንዲያስከትል ያፈቅዳሉ፡፡ ይህም ሰዎች ለሚያደርጉት ማንኛውም ተግባር አስቀድሞ ማሳብ እና መጠንቀቅ ያስችላቸው ዘንድ ቸልተኝነት የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ፅንሰ-ሃሳብ ሆኖ መደንገጉ የማህበረሰቡን ደህንነት ከማስጠበቁም በላይ የሰዎችን የጥንቃቄ መጠን ከፍ እንዲል ያደርጋል የሚል ሃሳብ አላቸው፡፡[37] በሀገራችንም በቸልተኝነት ጥፋተኛ ለመባል ሊታዩ የሚገቡ ሁኔታዎች መኖራቸው

[33]FLETCHER,George,P.,Atheory of criminal negligence: Acomparative analysis,1973, Vol.119: No. 3, University of Pennsylvania Law Review p. 430
[34]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 7፤ በገፅ 21 ::
[35]ዝኒ ከማሁ፤ በገፅ 14፡፡
[36]ዝኒ ከማሁ
[37]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 30፤ ገፅ 16፡፡

እንደተጠበቁ ሆኖ ቸልተኝነት የወንጀል ሃላፊነትን የሚያስከትል ዕንሰ ሃሳብ ነው። የወንጀል ህግ አንቀጽ 59/2/ የመጀመሪያፓራግራፍ ስንመለከት ቸልተኝነት የሚያስቀጣው በተደረገው የጥፋት ዓይነት ወይም ከባድነት፣ በማህበረሰቡ ላይ ሊያደርስ በሚችለውአደጋ ምክንያት ነው በማለት ያስቀምጣል። በወንጀል ህጉም ሊያስቀጡ ይገባቸዋል ተብለው የተደነገጉ የቸልተኝነት አይነትቶች ከላይ ከተጠቀሰው ዕንሰ ሃሳብ ጋር የሚሄድ ሲሆን ቸልተኝነት ያስቀጣልተብሎም በህጉ ውስጥ በግልፅ ካልተደነገገ በስተቀር የማያስቀጣ ድርጊት መሆኑን የወንጀል ህግ አንቀፅ 59/2/ ይገልጻል። በዚሁ አንቀፅ ስር የተጠቀሰውና አጽኖት ልንሰጠው የሚገባው ነገር ቸልተኝነት አለ ለማለት የሰዎችን ጥፋት ስንመዝን ሰዎች አስፈላጊ ጥንቃቄ አድርገው እንዲንቀሳቀሱ በማለት ህጉ ካስቀመጣቸው ግዴታዎች ባሻገር የሰዎችንም በነገሮች ያላቸውን የግንዛቤ ልዩነት በእያንዳንዱ የጥንቃቄ እርምጃ አወሳሰዳቸው ከተለያዩ ሁኔታዎች አንፅር በማገናዘብ ውሳኔ እንዲተላለፍ ይጠይቃል።

## 2. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 543 እና አንቀጽ 543(3) ትርጉም ዙሪያ የሚታዩ ተግባራዊ ችግሮች

### 2.1 የወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ጠቅላላ ይዘት

በ1996 ዓ.ም ተደንግጎ የወጣው ኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 543 በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል የሚቀርብበትን ሁኔታዎች በሶስት ንኡስ አንቀጾች ዘርዝሮ የያዘ ሲሆን በመጀመሪያው ንኡስ አንቀፅ የቸልተኝነቱ አይነት ከንኡስ ሁለትና ከንኡስ ሶስት ከተጠቀሱት ውጭ ሆኖ ሲገኝ በማለት በዚህ አንቀፅ የሚስተናገዱት ተራ የሆኑ ቸልተኝነቶች ሲሆኑ የአንቀፁ ንአስ ቁጥር ሁለት ደግሞ ሙያ ያላቸው ሰዎች ቸልተኝነት ሲፈፅሙ የሚጠየቁበት ድንጋጌ መሆኑን ያሳየናል። በዚህ ድንጋጌ የመጨረሻ ንዑስ አንቀጽ ሶስት ጥፋተኛው በሚል ሃረግ የሚጀምርና ሁለትና ከዚያ በላይ ሰዎች የገደለ እንደሆን፣ ወንጀሉን የፈፀመው ግልፅ ደንብ ወይም መመሪያ ተላልፎ እንደሆነ፣ የሚያሰክሩና፣ የሚያደንዝዙ ነገሮች ተጠቅሞ እንደሆነ በማለት ሲዘረዝር "ጥፋተኛው" የሚለው ሀረግ ለየትኛው ንኡስ አንቀፅ ላይ የተገለፀውን ጥፋተኛ የሚመለከት ስለመሆኑ ለተለያየ ትርጉሙም የተጋለጠ እንዲሆን አድርጎታል። እዚህ ጋር በአብዛኛው የሚነሱት ጥያቄዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 543(1) ላይ የተጠቀሱት ተራ ቸልተኝነቶች በሚከብድበት ግዜ በወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) ስር የሚያርፉበት አግባብ አለ ወይ? ወይስ በወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) ላይ የተጠቀሰው ጥፋተኛው የምትለው ሃረግ ከአንቀጽ 543(2) የቀጠለና ቸልተኞች ለሆኑ ባለሙያ ብቻ

የሚያገለግል ነው በሚል የሚንጸባረቁ ሲሆን እነዚህ ጥያቄዎች የዚህ ጽሁፍ ዋና ትኩረት በመሆናቸው በዝርዝር አንድ በአንድ እንመለከታቸዋለን፡፡

## 2.2 አንቀፅ 543/2/ በቸልተኝነት ሰው መግደል

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(2)[38] ስር የተጠቀሰው የቸልተኝነት አይነት ባለሙያ የሆኑ ሰዎች የሚፈፅሙት የቸልተኝነት አይነት ሲሆን ባለሙያ እነማን ናቸው የሚለውን አንቀፁ እንደ ማሳያ ያመላከተ ቢሆንም ሙያ ምንድን ነውየሚለውንና አንድን ሰው ባለሙያ ለማለትስ ምን ምን መሟላት አለበት የሚለው ጥያቄ በወንጀል ህጉ ላይ ምላሽ ያልተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ስለሙያ ምንነት እና በዚሁ አንቀፅ የሰውን ህይወት፣ጤንነት እንዲሁም ደህንነት የመጠበቅ ሌላ ግዴታ ያለባቸው በሚል የሚያስቀምጣቸው ሰዎች እነማን ናቸው የሚለውን ህጉ በግልፅ ሳይመለከታቸው ያለፋቸው ጉዳዮች ሲሆኑ እነዚህን ጥያቄዎች ከዚህ በታች እንደሚመለከተው እንመለከታቸዋለን፡፡

## 2.3 ሙያ እና ሌላ ግዴታ

### 2.3.1 ሙያ (Profession)

ስለ ሙያ ሲነሳ በቀዳሚነት በታሪክ ውስጥ በትምህርት የሚለመዱ ሙያዎች በመባል የሚታወቁት ቅስና፣ህክምና እንዲሁም ህግ ናቸው[39]፡፡ ሙያ ምንድን ነው የሚለውን ለመመለስ የሚያስችል የተሟላ እና ሁሉንም የሚያስማማ ትርጉም የሚሰጥ መልስ ባይኖርም ሙያ በሚመለከተው መልኩ በብላክስ ሎው መዝገበ ቃላትተቀምጧል፡፡ሙያ ጠለቅ ባለ ትምህርት እና ስልጠና የታገዘ አንድ የስራ መስክ ነው በማለት ያስቀምጠዋል፡፡[40]ሙያተኛን በተመለከተ ደግሞ፡- ባለሙያ ማለት ማንኛውም ሰው ጥልቅ በሆነ ስልጠና እውቀት ያካበተ ሆኖ ይህን ሙያውን በሚተዳደርበት ስራ ላይ የሚተገብር ማለት ነው፡፡[41] በመሆኑም ሙያ ጠለቅ ባለ ስልጠና የተደገፈ መሆኑን ከትርጉሙ መረዳት የምንችል ሲሆን ይህንን ትርጓሜ እንዲያጠንክርልን አርነስት ግሪንውድ[42] የተሰኘው ፀሃፊ ስለ ሙያ ባህሪያት ትንታኔ ሲሰጥ

[38] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 4፣ ገፅ 40
[39]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 6፣ ገጽ1246፡፡
[40]ዝኒ ከማሁ Profession is a vocation requring advanced education and training.
[41]ዝኒ ከማሁ A "professional" is simply anyone with *extensive* training of an *intellectual* Character who makes his or her living in the said occupation.
[42]ፕሮፌሰርአርነስት ግሪን ዉድ የተባለው ፀሃፊ በካሊፎርኒያ ዩንቨርስቲ የማህበራዊ ዋስትና አስተማሪ ሲሆን በምርምር የስራ ሂደትም ላይ የሰራ ጸሃፊ ከመሆኑ ባሻገር የሙያ ባህሪያትን በ1950ዎቹ ያስቀመጠ እና ለሌሎች ፅሁፎች እንደ መነሻ ሃሳብ የሚወሰድ ስራን ያከናወነ ፀሃፊ ነው፡፡

ሙያ በባህሪው ጠለቅ ያለ እንዲሁም በእውቀት (intellectual) ላይ የተመሰረተ መሆኑ አንዱና ዋነኛው ባህሪው ነው በማለት ያስቀምጠዋል።[43] ከላይ እንደተጠቀሰው ሙያ ሁሉንም የሚያስማማ ትርጓሜ ባይኖረውም የሙያን ምንነት የበለጠ ለመረዳት ያስችለን ዘንድ ልዩ የሚያረገውን ባህሪያት ማየት ስለ ትርጓሜው የቀረበ ጭብጥ እንድንይዝ ያደርገናል። የሙያ ባህሪያት (characteristics of profession) መገንዘባችን የትኖቹ ሙያዎች ሙያ ተብለው ሊወሰዱ እንደሚገባቸው ለይተን ለመረዳት ይጠቅመናል። ማንኛውም ሰው በመጀመሪያ በሙያው ዙሪያ ጠለቅ ያለ ስልጠና ማገኘት እንዲሁም በተሰጠው ስልጠና እውቀት ማዳበር እና ይህን እውቀት ተመርኩዞ ወደ ስራ መሰማራት አንዱ የሙያ መገለጫ ባህሪይ መሆኑን የሙያን ትርጓሜ ባላክስሎው መዝገበቃላት ሲያስቀምጥ የሚያነሳው ዋነኛ ነጥብ ነው[44]። ይህም እንደ አንድ የሙያ ባህሪይ ተደርጎ ይወሰዳል።

በሁለተኛ ደረጃ ሙያ ለማህበረሰቡ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑ (contribution to public good)[45] አንዱ የሙያ ባህሪ ተደርጎ ይወሰዳል። ባለሙያዎች ሲባሉ ለምሳሌ እንደህክምና ባለሙያ፣ ዳኛ እና ጠበቃ በሙያቸው ለማህበረሰቡ የሚያበረክቱት አስተዎፅዖ ከፍተኛ መሆኑ እንደ አንድ የሙያ መገለጫ ባህሪያት ተብሎ የሚወሰድ ነው። በሶስተኛነት የሚነሳው የሙያባህሪ የሙያው ባለቤቶቹ የመወሰን ነፃነታቸው (autonomy of decisionmaking)[46] ሲሆን በሙያ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሙያን በሚተገብሩበት ወቅትያለማንም ጣልቃ ገብነት ሙያቸውን መሰረት አድርገው ያላቸው የመወሰን ነፃነታቸው ሌላው የሙያ መገለጫ ባህሪይ ነው። በተጨማሪም የብቃት ማረጋገጫ (certification) እና ፍቃድ (license) አሁን አሁን እዳበሩ የመጡ የሙያ ባህሪያት ሲሆኑ ሙያን ለመተግበር ከሚከተለው አካል ፍቃድ ማግኘት እንደ ቅድመ-ሁኔታ ለአንዳንድ ሙያዎች የሚቀመጥበት አግባብ ያለ ሲሆን ይህ ግን በሁሉም ሙያዎች ሳይሆን ለማህበረሰቡ አስፈላጊ ናቸው ተብለው በተመረጡ ሙያዎች ላይ ተግባራዊ የሚደረግ ነው። አስፈላጊነቱ ጉልህ ከመሆኑ አኳያ እንደ አንድ የሙያ ባህሪያት መገለጫ ተደርጎ እየተወሰደ ይገኛል።[47] ከዚህም ባሻገር ባለሙያ ለመባል የተለያዩ የብቃት ማረጋገጫዎችን አልፎ የተመሰከረለት (certificatied) መሆንን መጠየቁ የሙያ ልዩ ባህሪይ

[43]Greenwood E. *attribute of a profession*, social work, vol. 2, issue 3, july1957 P.45-55
[44]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 6፣ 1246
[45]Callahan, Joan C., ed. Ethical Issues in a Professional Life, (New York, Oxford: Oxford University Press, 1988.) P.28 እንዲሁም Hoyle, E. and Megarry J. (eds) *Professional Development of Teachers*፡Year bookof Education. (New York: Kogan Page Publishers,1980)
[46]Merriam W, *Webster's Third New International Dictionary of the English Language.* Springfield, MA: 1981.
[47]Witz, A.*Professions and patriarchy.* London: Routledge.1992.

ነው::[48] ሌላው በብዙዎች ዘንድ የሚታወቀው የሙያ ባህሪ ስነ-ምግባር ሲሆን ሙያ በባህሪው በስነምግባር መርሆች (code of ethics) የተገነባ በመሆኑ ከሙያ ባህሪያት መካከል እንደ ዋነኛ መገለጫ ይወሰዳል::[49]

በሃገራችን በተለያዩ የህግ ክፍሎች ውስጥ ስለ ሙያ የተጠቀሱ ድንጋጌዎች ሲኖሩ ለምሳሌ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ 41(2) እንደተመለከተው ማንኛውም ሰው በመረጠው ሙያ መተዳደር የሚችል መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በ1960ዓ.ም ተደንግጎ የወጣው ንግድ ህግም በሙያ ሊመሩ ስለሚገባቸው የንግድ እንቅስቃሴዎች በአንቀጽ 5(1-21) ላይ ዘርዝሮ ያስቀምጣቸዋል:: የፍታብሄር ህግ በአንቀጽ 2031 ስለ ሙያ ጥፋት ይደነግጋል:: በእነዚህ ህጎች ስለ ሙያ ምንነት ትርጓሜ ያልተቀመጠ ሲሆን ስለሙያ ነጻነት፣ በሙያ ሊሰሩ ስለሚገቡ ስራዎች ግን ተመላክተዋል:: በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(2) የሰውን ህይወት፣ ጤንነት እና ደህንነት የመጠበቅ የሙያ ሃላፊነት አለባቸው በማለት ለማሳያነት ከዘረዘራቸው ጥቂት ሙያዎች ውጭ ሙያተኛ ለመባል ምን ምን መሟላት አለበትእንዲሁም ሙያተኛስ ማነው የሚለውን ጥያቄ ህጉ እንድንመለስ አያስችለንም:: ስለዚህም ባለሙያ ማን ነው የሚለውን ለመመለስ የግድ አንድ ሰው የሚተገብረው ስራ ባለሙያ ያሰኘዋል ወይ የሚለውን ጥያቄ በመጀመሪያ መመልከትን ይጠይቃል:: ለምሳሌ፡- በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትየወንጀል መዝገብ ቁጥር 02-20610[50] በቀረበ አንድ ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ባለሙያ ነው አይደለም በሚል ነጥብ ዙሪያ የሚከተለውን ውሳኔ ተሰጥቷል::

“በዚህ ክስ ዐቃቤ-ሕግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(2) በመጥቀስ ተከሳሽ የሰውን ህይወት ጤንነት የመጠበቅ የሙያ ሃላፊነት እያለበት የያዘውን ቱርክ ሽጉጥ ተጠንቅቆ መያዝ ሲገባው በጥንቃቄ ጉድለት ሽጉጡ ተተኩሶ ሟችን ጡቷ ስር ላይ መትቶ ገድሏታል ሲል ዐቃቤ-ህግ ክስ አቅርቦ ፍርድ ቤቱም የተከሳሽ ድርጊት የሚሸፈነው በየትኛው የህግ ድንጋጌ ነው የሚለውን ጭብጥ ከያዘ በኋላ ዐቃቤ ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 543 (2) በመጥቀስ ክስ ቢያቀርብም መሳሪያ ለመታጠቅ ፍቃድ መኖር ቅድመ ሁኔታ የሆነው ለቁጥጥርና ተያያዝ ለሆኑ ሁኔታዎች አመቺ እንዲሆን እንጂ እራስን ለመከላከል አስፈቅዶ መሳሪያ መታጠቅ የተለየ የሙያ ግዴታ የሚጥል አለመሆኑን ጠቅሶ ድንጋጌውን ቀይሮታል:: የትኞቹ ስራዎች ሙያ ተብለው ይወሰዳሉ የሚሉት እንደ ጉዳዩ አግባብ የሚወሰኑ ሲሆን ከላይ ሙያን እና ስለ

[48]ዝኒ ከማሁ

[49]Larson M. *The rise of professionalism: A sociological analysis,*Berkeley: University of California Press,1977.

[50]በከሳሽ ዐ/ህግ እና በተከሳሽ አቶ እንዳልካቸው ዳምጠው በሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት በቀን 17/5/ 2008 ዓ.ም ውሳኔ ተሰጠ

ሙያ ባህሪያት ያነሳነቸው ሃሳቦች የትኞቹ ስራዎች ሙያ ተደርገው ሊወሰዱ ይገባል የሚለውን ለመረዳት ያግዙናል፡፡

### ሀ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ከ 543(2) የቀጠለ

የዚህ ሃሳብ ደጋፊዎች[51] የወንጀልህግ 543(3) የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ መሰረት ካደረገው የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(2) የቀጠለና የሙያ ሃላፊነት ያለባቸውን ሰዎች የጥንቃቄ መጠን (due care) ከፍ ለማድረግ ታስቦ ተደነገገ የህግ አንቀፅ ነው በማለት ሃሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡ የተሻሻለው የወንጀል ህግ ሃተታ ዘምክንያት 543(3) የተጨመረበትን አላማ ሲያብራራ ድንጋጌው ዝርዝር በማለት የተለያየ ነጥቦችን እንዲይዝ ማስፈለጉን ከግምት እንዳስገባ ያስየናል[52]፡፡ እንዲሁም የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(2) በባለሙያዎች ስለሚፈጸም በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል የሚደነግግ ሲሆን በ1996 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) በመጨመር የተደነገገው ጥፋታቸው ከበድ ያለ ሙያተኞች ላይ ቅጣት ለመጨመር ስለመሆኑ ይህም ሃሳብ አንቀጹ ሲጨመር የተደረገው ውይይትን ይዞ የወጣው የወንጀል ህግ ሃተታ ዘምክንያት ያጠናክራል[53]፡፡

ህግ አውጭው የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(1) ሲያረቅ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች አሽከርካሪዎችን ቅጣቱ ዝቅ ባለ በዚሁ አንቀፅ ይቀጡ እንደነበረና ይህም መሆን ስለሌለበት ሙያን ሳይጨምር ለመጀመሪያ ግዜ አጥፊዎች እንዲውል በማለት ህግ አውጭው የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(1) ተራ ቸልተኝነት በማለት ከንዑስ ቁጥር ሁለት እና ሶስት በተለየ ሁኔታ ያስቀመተው መሆኑን ሃተታ ዘምክንያት ያስረዳል፡፡ በአንቀፁ ንዑስ-ቁጥር አንድ ላይ የተጠቀሱት ጥፋተኞች  በዚያው አንቀጽ ላይ ከተገፈገፍሩት ንዑስ-አንቀጽ ሁለትና ሶስት ዝቅ ያለ የአደገኛነት መጠን ያላቸው ተብለው የሚወሰዱ መሆኑን ሃተታ ዘምክንያት ያስረዳል[54]፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) የተጨመረበት አላማን ሲያስቀምጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ላይ ጉዳት የሚደርስበት ሁኔታ ስላላ በሚል በምሳሌ ሲያሳይ እንደ አሽከርካሪ ያሉ አላግባብ በመጫን ሰውን ጉዳት ላይ በማጋለጥ የዚህን

[51]የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) የሙያ ሃላፊነት ላለባቸው ጥፋተኞች ብቻ የሚያገለግል ነው የሚለውም ሃሳብ የሚያራምዱትንም ሆነ በተቃራኒው የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ላይ የተቀመጡት አማራጮች አንዳቸው ከተሟሉ ባለሙያ መሆን ሳይጠበቅበት በዚህ አንቀፅ ጥፋተኛ ሊባሉ ይችላሉ የሚሉ በሁለት ጎራ የተከፈሉ ሃሳቦችን ዋቢ ተደርገው በዚህ ጽሁፍ ላይ ከተጠቀሱት የውሳኔ መዝገቦች ላይ የተወሰዱ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

[52]ከላይ ከግርጌ ማስታወሻ፣ ገጽ 258

[53]ዝኒ ከማሁ

[54]ዝኒ ከማሁ

ሁኔታ ለመቀነስ ታስቦ መሆኑን ይህ ሰነድ እንደ ማሳያነት ያስቀምጣል[55]። በሌላ በኩል ከዚህ ቀደም በወንጀል ህጉ ያልተቀመጡ ሁኔታዎች አካቶ እንዲያዝ በተለይም ጥፋተኞች የሚያፈሩና የሚያስክሩ ነገሮችን ወስደው የሚደርሱ አደጋዎችን ለመከላከል በማሳብ ወንጀሉን ዘርዘር አድርጎ ማስቀመጡ አስፈላጊ መሆኑን ያሳየናል።[56] ከዚህ የምንገነዘበው የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) የተቀመጠበት አግባብ የጥፋተኛው የጥንቀቃቄ መጠን ከፍተኛ በማድረግ (ደንብ በመጣስ፣ የሚያፈሩና የሚያደነዝዙ ነገሮችን በመውሰድ) በተለያዩ ሰዎች መብት ላይ ጉዳት ሲያደርስ ጠበቅ ያለ የቅጣት ውሳኔ ለማስተላለፍ በማሰብ መሆኑን ነው። የህግ አውጭውም ሃሳብ ሙያ ያለውም ሆነ ሙያ የሌለው ሰው በዚህ አንቀፅ ስር ጥፋተኛ እንዲባል ሳይሆን በማህበረሰቡ ላይ እየደረሰ ያሉ ጉዳቶች እየተበራከቱ በመመጣታቸው የአጥፊውን የጥንቃቄ ደረጃ ከፍ ለማድረግ በማሰብ መሆኑን ከተጠቀሱት ምክንያቶች መረዳት እንችላለን።

በመሆኑን ባለሙያና ሙያ የሌላቸው ሰዎች ሊመዘኑ የሚችሉበት አግባብ በህጉ በተጣለባቸው የጥንቃቄ ደረጃ መለያየት አንጻር በተመሳሳይ የህግ አንቀጽ 543(3) ስር ጥፋተኛ ሊባሉ አይገባም።[57] ምክንያቱም በህጉ ሙያ ላላቸውና ሙያ ለሌላቸው ሰዎች የተቀመጠው የጥንቃቄ ደረጃ ስለሚለያይ ነው። ይህንንም ፊሊፕ ግራቨን በምሳሌ ሲያሳይ አንድ የልብ ቀዶ ጥገና ሃኪም ኦፕሬሽን እያደረገ ታካሚው ቢሞትበት ቸልተኛ ነው ለማለት ይህን ሃኪም በአስተዋይ ሰው መለኪያ የምንለካው አይሆንም ምክንያቱም አስተዋይ ሰው የህክምና እወቀት ያለው ባለመሆኑ ሌላው ተራ የማህበረሰቡ ክፍል ሊመዘንበት በሚችል አግባብ እሱን ልንመዝን አንችልም[58]በማለት ሲያስቀምጥ ከዚሁ ጋር ተያያዝነት ያለውን ሌላ ምሳሌ ሲያስቀምጥ *አንድ ሃኪም ከሃርስ የበለጠ የጥንቃቄ ደረጃ፣ ልምድ ከሌለው ለማጅ አሽከርካሪ ልምድ ያለው አሽከርካሪ የበለጠ የጥንቃቄ ደረጃ እንዲኖር ይጠበቃል በማለት ያብራራል።*[59] ሙያ ያላቸውን እና ሙያ የሌላቸውን ሰዎች እኩል በአንድ አንቀፅ መቅጣታችን ሙያ ባለውና ሙያ በሌለው ሰው መካከል የጥንቃቄ መጠን ልዩነት እንዲኖር መደረጉን በውጤት ደረጃ ባዶ ያደርገዋል። ይህ የህግ ትርጓሜ እና አሰራር ከተጠቀሱት ምክንያቶች አንፃር አግባብነት ያለው በመሆኑ የዚህ ፅሁፍ ፀሃፊ

---

[55]ዝኒ ከማሁ

[56]ዝኒ ከማሁ

[57]የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) የሙያ ግዴታ ላለባቸው ሰዎች ብቻ ያገለግላል የሚለውን የህግ ትርጉም መሰረት የወንጀል ህግ መመሪያ ያጠናው ቡድን የተቀበለው መሆኑን በተሻሻለው የወንጀል ህግ መመሪያ 2/2005 ለዳኞችና ለዐ/ህግ ሀምሌ 2006 ዓ.ም በተዘጋጀ የስልጠና ማንዋል ላይ ተገልፃል።

በግርጌ ማስታወሻ 11፣ ገፅ 161 *"The question is whether a heart surgeon was negligent in the performance of an operation during which the patient died, the surgeon's negligence cannot be determined by reference to the criterion of the reasonable person, for the reasonable person is for all practical purposes a layman in the medical field."*

[59]ዝኒ. *ከማሁ።። a greater amount of care is required of a doctor than of a nurse, of a professional driver than of an ordinary driver, of a master mason than of an apprentice, etc.*

የምትጋራው ሃሳብ ነው። በመሆኑም አንድ መንጃ ፍቃድ የሌለው አሽከርካሪ ከፈጸመው ቸልተኝነት ሰው መግደል በተጨማሪ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክን ለመቆጣጠር የወጣን ደንብ ቁጥር 208/2003 ዓ.ም አንቀፅ 5(6) ቢተላለፍ ጥፋተኛ ማለት ያለብን በ 543(1) ሲሆን የጣሰው ደንብ በወንጀል ህግ ስለተደራራቢ ወንጀሎች በአንቀፅ 60(ሐ) መሰረት በተቀመጠው መልኩ በሁለተኛ ክስነት ደንብ መተላለፉ ሊቀርብ ይገባል ምክንያቱም የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ባለሙያ የምትለው ነጥብ ላይ የተመረኮዘ እና ይህ አንቀፅ የሰውን ህይወት፣ ጤንነትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ ያለባቸው ባለሙያዎች በዚሁ አንቀፅ ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አንዱን ጥሰው ከተገኙ ቅጣታቸው በዚሁ መሰረት ከብዶ እንዲወሰን በመታሰቡ ነው። ይህን ለአብነት ሊያሳዩ የሚችሉ የሚከተሉትን የፍርድ ቤት መዝገቦች እንመልከት።

በምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 20595[60] ተከሳሾች በስር ፍርድ ቤት ዋስትና በመከልከላቸው አንስተው ያቀረቡት አቤቱታ ሲሆን የዞኑ ዐቃቤ-ህግም የመንጃ ፍቃድ ሳይኖረው በማሽከርከር በሁለት ሰዎች ላይ ሞት ያስከተለ በመሆኑ ይህም በወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) የሚወድቅ በመሆኑ ዋስትና እንዲከለከል ሲያሳስብ ፍርድ ቤቱም "በቸልተኝነት ስለሚፈፀም ሰውመግደል የሚያትተው የወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ከንዑስ (1-3) ላሉት ንዑስ-አንቀፆች ስር ሲሆኑን በዚህ ችሎት እምነት አንቀፅ 543(1) የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ሳይኖርበት በቸልተኝነት ሰውን ለገደለ የሚያገለግል ሲሆን አንቀፅ 543(2) ደግሞ የሚሸፍነው ባለሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበትን ሰው ሲሆን በፈጸመው ከባድ ቸልተኝነት ከአንድ በላይ ሰዎችን ለሞት ለለባነት ካበቃ አግባብነት የሚኖረው አንቀፅ 543(3) ይሆናል ይህም ማለት የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) የወንጀል ህግ 543(2) ከባድ ሁኔታ ይሆናል። በመሆኑም አመልካቾች ባለሙያዎች ባለመሆናቸው ድርጊታቸው በአንቀጽ 543(1) ስር የሚወድቅ መሆኑን ጠቅሶ የተነፈጉትን ዋስትና መብት በመፍቀድ ውሳኔ ሰጥቷል። በተመሳሳይ ጉዳይም በባህርዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 04-01208[61] ተከሳሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) እና ደንብ 208/2003 በመተላለፍ መንጃ ፍቃድ ሳይኖረው (unlicinced) ሲያሽከረክር ለእግረኛ ቅድሚያ ባለመስጠቱ ሟችን ገጭቶ የገደለው በመሆኑ በፈፀመው በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ክስ የቀረበበት ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተከሳሹ ጥፋተኛ ሊባልበት የሚገባው ድንጋጌ ይሄ ነወይ የሚል ጭብጥ በመያዝ

[60]በይግባኝ ባዮች እነ ነብዩ ታደሰ እና በመ/ሰጭ ዐ/ህግ በምስራቅ ጎጃም ዞን የወንጀል ችሎት ታህሳስ 21፣2000 ዓ.ም ውሳኔ የተሰጠ

[61]በከሳሽ ዐ/ህግ እና በተከሳሽ አወቀ ካሳ በባህርዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 04-01208 በቀን 05/02/2008ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ።

የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ “የወንጀል ህግ ቁጥር 543(3) መነሻው 543(2) ሆኖ ተፈፃሚነቱ የሌላውን ሰው ህይወት ደህንነት የመጠበቅ የሙያ ሃላፊነት ያለበት ሰው ላይ መሆኑ ከድንጋጌዎቹ የጋራ ንባብ መረዳት ይቻላል” በማለት ተከሳሽ የአሸከርካሪነት ሙያ የሌለው በመሆኑ የተከሰሰበትን የወንጀል ህግ አንቀፅ 543 (3) ስለማያሟላ የተከሰሰበት አንቀፅ ወደ አንቀፅ 543 (1) (ሙያ ሃላፊነት የሌለባቸው) በመለወጥ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሌላ የወንጀል መዝገብ እንዲሁ ባህርዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 01609[62] በተከሻሹ ላይ ክስ የቀረበው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 543 (3) በመተላለፍ እና ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 5(6) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የመንጃ ፍቃድ ሳይኖረው ሲያሽከረክር ከመኪናው ስር ሆኖ መኪናውን ሲያስተካክል የነበረውን ሟች ከስር መኖሩን ሳያረጋግጥ ሞተሩን አስነስቶ በማንቀሳቀሱ በፈጸመው በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ክስ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ተመልክቶ ውሳኔ ሲሰጥ ተከሳሽ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው ሟችን የገደለ በመሆኑ ባለሙያ ስላልሆነ ድርጊቱ የሚሸፈነው በተራ የቸልተኝነት ድርጊት በመሆኑ የተከሰሰበት የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ወደ 543(1) በመለወጥ ጥፋተኛ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በመጨረሻም ህግ አውጭው የወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ን በንዑስ አናቅጽት ከፋፍሎ ሲያስቀምጥ የእያንዳንዱ ንዑስ-አንቀጽ የጥፋተኛውን የወንጀል አፈፃፀም ክብደት ከወንጀለኛው አደገኝነት እና ከደረሰው ጉዳት አንፅር አፅኖት በመስጠት የደነገገ መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት እንረዳለን፡፡ ይህም ህግ አውጭው ቅጣት ሲያስቀምጥ በየደረጃው እንደ ወንጀሉ ክብደት የተቀመጠ ሲሆን ቅጣትም የሚወሰነው በወንጀለኛው የአደገኝነት መጠን እና የአጥፊውን የግል ሁኔታ በማመዛዘን መሆን እንዳለበት አንቀፅ 59(2) የመጨረሻ ፓራግራፍ ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

### ለ. አንቀጽ 543(1) በሚከብድበት ጊዜ

ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ በተቃረነ አንቀጽ 543(3) ሙያ የሌላቸው ሰዎች ጭምር የሚያካትት የህግ አንቀፅ ነው በሚል የሚከራከሩ ሲሆን ለዚህም ምክንያት ብለው ከሚያነሱት ነጥብ አንደኛው ሙያ ያለው ሰው ጊዜና እውቀቱን ሰውቶ በያዘው ሞያዊ ሃላፊነት ተጠያቂነቱን ከተራ ቸልተኝነት እጥፉን ሲከብድበት ሙያ የሌለው ሰው ላጠፋው ተመሳሳይ ጥፋት ግን

[62]በከሳሽ ዐ/ህግ እና በተከሳሽ አምላክ ተስፋዬ የባህርዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ችሎት በቀን 29/02/2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ

ባለሙያ ባለመሆኑ ብቻ ያነሰ ቅጣት ሊወስንበት አይገባም ይህ አተረጓጎም ሰዎች የሕጉን ክፍተት ተጠቅመው በዘፈቀደ እንዲንቀሳቀሱ ይፈቅዳል የሚል ነው።[63] ሌላው የዚህ ሃሳብ መከራከሪያ ዋነኛ ነጥብ በወንጀል ህግ አንቀጽ 543(1) የተጠቀሱት ጥፋተኞች በአንቀፅ 543(3) ላይ ያሉትን አማራጭ ሁኔታዎች አንዱን አሟልተው ሲገኙ በወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) ጥፋተኛ ይባላሉ ምክንያቱም የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) ሙያ የሌላቸውን ሰዎች እንደማያካትት አያመላክትም የሚል ሲሆን ይህ ጥናት በተደረገባቸው ቦታዎች ላይ በስፋት የሚሰራበት የህግ አተረጓጎም ነው። በምሳሌ ለማሳየት

በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 0218217[64] ዐቃቤ ህግ በተከሳሽ

ላይ የኢፌድሪ የወንጀል ህግ 543(3) እና የትራፊክ ደንብ ለመቆጣጠር የወጣውን ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀፅ 5(6) የተመለከተውን በመተላለፍ መንጃ ፍቀድ ሳይኖረውና በመኪና ሰው አሳፍሮ በማሽከርከር ላይ ሳለ መኪናዋ ከድልድይ ጋር አጋጭቶ በቸልተኝነት ሰው የገደለ በመሆኑ ክስ ሲያቀርብ ፍርድ ቤቱም የቀረቡትን ማስረጃዎች ሰምቶ በተከሰሰበት የህግ አንቀፅ ጥፋተኛ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

በሌላ መዝገብ የባህርዳር እና አካባቢዋ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 01761[65] ተከሳሽ የኢፌድሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) በመተላፍ ከፍተኛ ተቀጣጣይነት እና ቃጠሎ ሊያስነሳ የሚችል ባህሪያት ያለውን ቤንዚን ነዳጅ... በሚያፈስ ባለሃያ ሌትር ጀሪካን በመቅዳት ጀሪካኑን ሳይከድን ከሚኖርበት ጠባብ ዶርም ይዞ በመግባቱ እሳት ተነስቶ ሁለት ሰዎች ተቃጥለው እንዲሞቱ ያደረገ በመሆኑ በፈፀመው በቸልተኝነት ሰው መግደል ክስ ቀርቦበት ፍርድ ቤቱም ማንኛውም ግለሰብ ቢሆን ቤንዚን በቀላሉ ሊቀጣጠል የሚችል መሆኑን እያወቀ በጀሪካን ቤንዚን ቢቀዳ እንኩዋን ነፋስ እንዳይወስደው በደንብ መክደንና ጥንቃቄ በተሞላበት እሳት በማይኖርበትአካባቢ መቀመጥ እንዳለበት እያወቀ ተከሳሽ ግን በቀዳዳ ጀሪካን ቤንዚን አስቀድቶ ወደቤት መውሰዱና ወዲያውም እሳት ተነስቶ ሁለት ሰዎች ህይወታቸው ያለፈ በመሆኑ ክስ በቀረበበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) ጥፋተኛ በማለት ወስኗል። በዚህ አሰራር የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) ሙያተኛ የሚለውን መስፈርት መሟላት ሳያስፈልገው ለቅጣት ማክበጃነት

[63]መረጃ ለመመለስ በሄድኩባቸው ዞኖች ካሉ ባለሙያዎች ጋር ባደረኩት የእርስበርስ ውይይት የተገኘ ሃሳብ

[64]በከሳሽ ዐ/ህግ እና ሽኩር ወርቁ ሃሰን እነዲሁም በደ/ወ/ዞ/ከፍ/ፍ/ቤት መ/ቁ/ 7325 በከሳሽ ዐ/ህግ እና በተከሳሽ አስፋው አበራ

[65]በከሳሽ ዐ/ህግ እና በተከሳሽ ታምሩ ውበት የባህርዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ችሎት በቀን 18/05/2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ

አላማ የሚውል ነው፡፡ “ጥፋተኛው” በሚል በዚሁ አንቀጽ የተጠቀሰችው ሃረግ ከአንቀጽ 543(2) የቀጠለ መሆኑን ለማመላከት ሳይሆን ጥፋተኛው የፈፀማቸውን የወንጀል ክብደቶች ለመዘርዘር የህግ አውጭው የተጠቀመበት ቃላት ናት በማለት የዚህ ሃሳብ ደጋፊዎች ክርክራቸውን ያቀርባሉ፡፡

የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(1) ማለት ተራ ቸልተኝነት ሲሆን በዚህ ቸልተኝነት ለምሳሌ አንድ ሰው መሳሪያውን እያጸዳ ባለበት ግዜ ጥይት ባርቆበት ሰው ቢገድል የሚጠየቅበት ድንጋጌ ይህው ሲሆን ነገር ግን ይህ ግለሰብ በድርጊቱ ሞት ያስከተለባቸው ሰዎች ሁለትና ከዚያ በላይ በሚሆኑበት ጊዜ ሊጠየቅ የሚገባው በወንጀል ህግ 543(3) መሰረት ነው የሚል አሰራር ሲሆን በአንቀጽ 543(1) የተጠቀሱ ሁኔታዎች ከብደው በአንቀጽ 543(3) ላይ ከተመለከቱት አማራጮች አንዱን አሟልተው ከተገኙ በአንቀጽ 543(3) መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔ እየተሰጠ ይገኛል፡፡[66]

ለማጠቃለልም ይህን የህግ ትርጉም መሰረት በማድረግ የቀረቡ ክርክሮች ቢኖሩም ልብ ሊባል የሚገባው ዋናው ነጥብ በባለሙያዎች ላይ የወንጀል ሃላፊነታቸው ከብዶ የሚወሰነው ማንኛውም ባለሙያ ሙያውን ሲተገብር ሊወስደው የሚገባውን የጥንቃቄ መጠን ባለሙያ ካልሆኑ ሰዎች በላይ ከፍ ለማደረግ የታሰበ በመሆኑ ነው፡፡ ቸልተኝነትን ስንመዝን በወንጀል ህግ አንቀፅ 59(2) በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት ህጉ ከግምት እንደናስገባ የሚጠይቀን ጥፋተኛው ለድርጊቱ ያለውን የግንዛቤ መጠን በመለካት ሊወስድ የሚገባውን ምክንያታዊ የሆነ የጥንቃቄ መጠን ለማወቅ እንዲያስችለን ነው፡፡

### 2.4 ሌላ ግዴታ (other duty)

ግዴታ ማለት ህጋዊ የሆነ አንዱ ለሌላው ሊተገብረው የሚገባ ግዴታ ወይም በሌላ ሁኔታ መብቱ ላለው ሰው ሊፈጸምለት የሚገባ ግዴታ ነው፡፡[67] በወንጀልህግ አንቀጽ 543(2) ላይ እንደሚያስቀምጠው የሰውን ህይወት፣ ጤንነት እና ደህንነት የመጠበቅ **“ሌላ ግዴታ”**ያለበት በማለት የሚያሰቀምጥ ሲሆን የግዴታውን ምንጭም ሆነ የትኞቹ የግዴታ አይነቶች በዚህ ስር

[66]በሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 13220 በከሳሽ ዐ/ህግ እና በተከሳሽ መቆየት መብራት በቀን 26/11/2005 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ እና በከሳሽ ዐ/ህግ እና በተከሻሽ ሺኩር ወርቁ ሃሰን በወንጀል መዝገብ ቁጥር 02-18217 በቀን 13/4/2007 ዓ.ም በዚሁ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ፣ በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 05417 በከሳሽ ዐ/ህግ እና በተከሳሽ አባ ገ/መድህን ገ/ማሪያም በቀን 5/2/2007 የተሰጠ ውሳኔ ከላይ በተመለከተው መልኩ 543(1) በሚከብድበት ሁኔታ ክስ የቀረበባቸውና በአንቀጽ 543(3) የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠባቸው መዝገቦች ናቸው፡፡

[67]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ፣ ገጽ 543፡፡ *“Duty a legal obligation that is owed or due to another and that needs to be satisfied; an obligation for which some body els have a corresponding rights”*

እንደሚካተቱ ባለማስቀምጡ እንደጉዳዩ አመጣጥ እየታየ የሚወሰን ነው። ነገር ግን የትኖቹ ግዴታ ለሚለው እና ከግዴታዎች ውስጥ በዚህ ዘርፍ እንዴት ሊመደቡ እንደሚችሉ ግልፅ የሆነ ነገር አልተቀመጠም።

ጠቅላላ የህግ ክፍሎችን ስንመለከት ግዴታ ከመብት ወይም ከውል ይመነጫል። በነዚህ የህግ ክፍሎች በአንደኛው የተመሰረቱ ግዴታዎች ካሉ እና እነዚህም ግዴታዎች በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(2) ላይ እንደተጠቀሰው የሰውን ህይወት፣ጤንነት እና ደህንነት የመጠበቅ ሃላፊነት የሚጥሉ ከሆነ እና ይህን ጥፋተኛው ሳይወጣ ቢቀር እና ሞት ቢከሰት በዚህ ንዑስ አንቀፅ ሊጠየቅ እንደሚችል ነው። እዚህ ጋር አፅኖት ሰጥተን ማየት ያለብን በማመሳሰል ወንጀል እየፈጠርን ሳይሆን የህጉን መንፈስ ተከትለን ህግን እየተረጎምን መሆኑን ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው በውል በጉዲፈቻነት ልጅ ሊሳድግ ተስማምቶ ከወሰደ በኋላ ወላጅ ለልጁ በሚገባ ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ማለትም ልጁን ሲታመም ሳያሳክመው እንዲሁም ለእድገቱ እና ለጤናው ተስማሚ የሆነ ምግብ ሳይሰጥ በመቅረቱ በህክምና ቋንቋ (malnourished) ከመሆኑ የተነሳ የልጁ ህይወት ማለፉ በማስረጃ ቢረጋገጥ አሳዳጊው ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት የሰውን ህይወት፣ ጤንነት እና ደህንነት የመጠበቅ ሃላፊነቱን አልተወጣም በማለት ክስ መመስረት እንደምንችል ያሳየናል።

### 2.5 በወንጀል ህግ 543(2) እና 543(3) መካከል ያሉ ዋነኛ የልዩነት ወሰን

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(2) የሰውን ህይወትና ጤንነት የመጠበቅ የሙያ ሃላፊነት ያለባቸው ባለሙያዎች ሲያጠፉ ተጠያቂ የሚሆንበት ንዑስ አንቀፅ ሲሆን በዚህ ንዑስ-አንቀፅ ጥፋተኛው ባለሙያ መሆኑን የሚጠይቅ ሲሆን የፈፀመውም ቸልተኝነት ከአንቀጽ 543(3) አንጻር ከፍተኛ ያልሆነ መደበኛ (ordinary) ሊባል የሚችል ቸልተኝነት መሆኑን ከድንጋጌው መንፈስ እና ከተቀመጠው ቅጣት መረዳት እንችላለን። በአንቀጽ 543(3) ጥፋተኛ ነው ለመባል ደግሞ በአንደኛው አማራጭ ሞት ያስከተለባቸው ሰዎች ቁጥር ብዛት ከሁለትና ከዚያ በላይ መሆኑ ከግምት የሚገባ ሲሆን፣ ተከሳሹ ወንጀሉን የፈጸመው ግልጽ ደንብ ወይም መመሪያን ጥሶ መሆኑ ሌላው መመዘኛ ሲሆን ለምሳሌ አሽከርካሪ እንደሆነ እንደ የፍጥነት ወሰንን መተላለፍ ወ.ዘ.ተ. እንደሆነ በመጨረሻም ጥፋተኛው ጠጥቶ ወይም የሚያደነዝዙ ነገሮች መጠቀሙ የሚደርሰውን ጉዳት በወቅቱ አለማገናዘብመቻሉጥፋተኛውን ከተጠያቂነት እንደማያድነው ድንጋጌው ያስቀምጣል።

አንድ ሰው በወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) ጥፋተኛ ለመባል ከላይ ከተጠቀሱትን አማራጮች ውስጥ ቢያንስ አንዱን ሊያሟላ ይገባዋል፡፡ ዋነኛው የነዚህን አናቅጽት ልዩነት ድንጋጌዎቹን የሚያቀቁሙት የወንጀል ፍሬ ነገሮች መለያየት ሲሆን በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) መሰረት ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈፀመው ግልጽ ደንብ (መመሪያ) ጥሶ ከሆነ፣ ሞት ያስከተለባቸው ሰዎች ቁጥር ሁለትና ከዚያ በላይ ከሆነ፣ወንጀሉን ሲፈጽም የሚያፈዙና የሚያደነገዘዙ ነገሮችን ተጠቅሞ ቢሆን አንኳን በሚል የተደነገገ ሲሆን አንቀፅ 543(2) ግን ጥፋተኛው ተጨማሪ ደንቦችም ይሁን መመሪያዎችን ሳይጥስ፣ የሚያደነገዘዙ ነገሮችን ሳይጠቀም የሞተበት ሰው ቁጥር አንድ ብቻ ሲሆን ጥፋተኛ የሚባልበት የህግ ድንጋጌ ሲሆን በድንጋጌዎቹ መሃከል ያለው ዋነኛው ልዩነት የጥፋተኛው የአደገኝነት መጠን እና የወንጀሉን አፈፃፀም ክብደት መሰረት ነው፡፡ ይህንንም መሰረት አድረጎ አንቀጾቹ ክፍፍል እንደተደረገባቸው ከሚያስከትሉት የቅጣት መጠን መለያየት ጭምር መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 2.6 ግልፅ ደንብ (express regulation)

ደንብ ማለት ስልጣን ባለው አካል አስገዳጅነት ያለው ልንከተላቸው የሚገባቸው መመሪያዎች ሆነው መመሪያውን ያወጣው አካል ለሚቆጣጠራቸው አካላት የተደነገጉ ናቸው[68]፡፡ በመሆኑም ደንብ የሚለውን በዚህ መልኩ ትርጉም ከሰጠነው በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) የተቀመጠው ግልፅ ደንብ ምን ለማለት ነው የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል፡፡ በዚህ ጸሃፊ እምነት ግልፅ ደንብ ስንል (በመመሪያ) ደንብ በግልፅ የተቀመጡ ድንጋጌዎች መጣሱን እና የተጣሰውን ድንጋጌ በመጥቀስ ማሳየት ነው፡፡ በክስ አመሰራረት ጊዜ አልፎ አልፎ የሚስተዋሉት አሰራሮች የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ተጠቅሶ ክስ በሚቀርብበት ጊዜ ተጣሰ የተባለውን ግልፅ ደንብ በክሱ ዝርዝር ውስጥ ገልፆ ብቻ ማለፍ እና የተጣሰው (ደንብ) መመሪያን ድንጋጌ ያለመጥቀስ ይስተዋላሉ፡፡ ለምሳሌ በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 02-05172[69] በተከሳሽ ላይ የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ጠቅሶ ክስ ያቀረበ ሲሆን በክስ ዝርዝሩም ላይ ተከሳሹ የሌላውን ሰው ህይወትና ጤንነት የመጠበቅ ሃላፊነት እያለበት ግልፅ የሆነ ትራፊክ ደንብ በመጣስ በፍጥነት በማሽከርከር... ሚች ቀኝ መስመሩን ይዞ ባጃጅ ሲያሽከረክር ተከሳሽ ወደ ግራመስመር በማለፍ ሚች ሲያሽከረክር የነበረውን ባጃጅ በመግጨት 400 መቶ

[68]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 8 ላይ፡፡ *Regulation is :- A rule of order having the force of law, prescribed by a superior or competent authority, relating to the actions of those under the authority's control*
[69]በከሳሽ ዐቃቤ-ህግ እና በተከሳሽ ሃይሌ ሸዋዬ ግርማይ፣ በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02-05172 በቀን 30/10/2006 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ፡፡

ሜትር ጎትቶ በመውሰድ ሚችን የገደለ መሆኑን ዐቃቤ-ህግ ጠቅሶ ክስ አቅርቧል። እዚህ ጋር ዐቃቤ-ህግ ክስ ሲያቀርብ በፍጥነት ማሽከርከር አንዱ የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ሲሆን ይህን የሚያመለክት የደንብና የደንቡን ደንጋጌ በክሱ ላይ በመጥቀስ ማሳየት አለበት እንጂ በክስ ዝርዝር ውስጥ ተካቶ ብቻ መታለፍ የለነትም። ምክንያቱም በአንቀፅ 543(3) ላይ የተቀመጠው "ግልፅ ደንብ ወይም መመሪያን መተላለፍ" የሚለው ድንጋጌ የትኛውን ደንብ ወይም መመሪያ የሚለውን እንድናሳይ ያመላክተናል። ከዚህ ባሻገር ፍርድ ቤቱም ክሱን ተቀብሎ ሲያስተናግድ ማስረጃ ከመመዘኑ በፊት የወንጀል ህግ አንቀፅ 543 (3) ተላልፏል ለማለት ተጣሰ የተባለው የትኛው (ደንብ) መመሪያ ነው የሚለውን መመርመር አለበት። ሌላው ግልፅ (ደንብ) መመሪያን በተመለከተ የሚነሳው ነጥብ በተለይም አሽከርካሪዎች ቢያንስ አንድ የትራፊክ (ደንብ) መመሪያ ሳይጥሱ ወንጀል ካለመፈፀማቸው ጋር ተያይዞ የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(2) መቼ ነው ተፈጻሚ የሚሆነው የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል። በስራ ላይም አሽከርካሪዎች ክስ የሚቀርባቸው በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ሲሆን በማስረጃ ምዘና ወቅት በተከሰሱበት አንቀፅ መሰረት ባለመመስከሩ ወደ አንቀጽ 543(2) የሚሄድበት አግባብ እንዳለ ከተመለከትኳቸው አንዳንድ መዛግብ መረዳት ችያለሁ። ለምሳሌ በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 02-05172[70] ላይ ተከሳሽ ፍጥነት ነበረው ቢባልም የትራፊክ ደንብ መጣሱ በማስረጃ ባለመረጋገጡ ምክንያት የተከሰሰበትን  የህግ አንቀፅ ተቀይሯል። በመጨረሻም ስለ ግልፅ የሆነ ደንብ መተላለፍ ስናነሳ አጽኖት መሰጠት ያለበት ጉዳይ ተጣሰ የተባለው ግልፅ ደንብ እና ክስ የቀረበበት ጉዳይ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው መሆን አለበት የሚለው ሃሳብ ነው። ይህም ማለት ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈፀመው ግልፅ ደንብን ተላልፎ ከሆነ ይህ የተላለፈው ደንብና የጥፋተኛው ድርጊት ቁርኝት እንዳላቸው ያሳየናል። ደንቦች በባህሪያቸው አንድን ጉዳይ ለመሸፈን የሚወጡ ሲሆን የሚቆጣጠሩትም አካል በዚህ ደንቦች ስር የሚተዳደሩ ናቸው። ለምሳሌ የትራፊክ ህግ... ለአሽከርካሪዎች የጤና ስነ-ምግባር... ለጤና ባለሙያዎች ወዘተ. ለማስተዳደር የሚወጡ ህጎች ናቸው። ለምሳሌ አንድ ሰው በክሊኒኩ ህክምና ሲሰጥ በቸልተኝነት ሰው ቢገድልና በተጨማሪም ክሊኒኩ ንግድ ፍቃድ የሌለው ቢሆን ንግድ ፍቃድ ሳያወጡ መስራት አንድ ደንብ መተላለፍ ቢሆንም ከደረሰው ጉዳት ጋራ ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት የለውም ምክንያቱም ንግድ ፍቃድ ያለማውጣቱ ከገቢን አሳወቆ ግብር ከመክፈል ጋር የተገናኘ እንጂ ተከሳሹ ሚች ላይ ካደረሰው ጉዳት ጋር አይገናኝም። ነገር ግን ጥፋተኛው

[70]በከሳሽ ዐ/ህግ እና ሃይሌ ሸዋዬ ግርማይ በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 0205172 በቀን 30/10/2006 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ።

የሙያ ፍቃድ ሳይኖረው ቢሆን ኖሮ ግን አንድ ሃኪም እውቀትና እና ችሎታ ያለው ስለመሆኑ ብቃቱ ሳይረጋገጥ ህክምና እንዲሰጥ የምግብና መድሃኒትና የጤና አስተዳደር ቁጥጥር አዋጅ ስለማይፈቅድ ይህንኑ ደንብ ተላልፎ ሞት ማስከተሉ ህግ አውጭው ባለሙያዎች የሚወስዱትን የጥንቃቄ መጠን ከሚሰሩት የስራ ሃላፊነት ጋር ያሉትን ደንቦችና መመሪያዎች በሚገባ በመከተል ከፍ ያለ ጥንቃቄን እንዲያደርጉ ሃላፊነት የጣለ መሆኑን ያሳየናል፡፡ ስለዚህም ክስ በሚቀርብበት ወቅት ድርጊቱ የወንጀል ተጠያቂነትን ስለሚያስከትል በተከሳሽ ላይ በተደራቢ ክስነት ሊቀርብ ቢችልም የ543(3) አንዱ አማራጭ ወንጀሉን የፈፀመው "ግልፅ የሆነ ደንብ ወይም መመሪያን ተላልፎ እንደሆነ" በሚል ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ግልፅ ደንብ ተላለፏል ለማለት የተጣሰው ደንብ ከደረሰው ጉዳት ጋር ምክንያታዊ የሆነ ተያያዝነት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

## 3. ማጠቃለያ

ቸልተኝነት በሃገራችን የወንጀል ሃላፊነትን የሚያስከትል ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ጥፋተኞች ድርጊታቸው ጉዳት እንደሚያደርስ ባለማገናዘብ ወይም ድርጊቱ በወንጀል እንደሚያስቀጣ ማወቅ ሲገባቸው ይህን ባለማወቅ በሚያደርጉት ድርጊት የሰው ህይወት አልፎ ከሆነ በቸልተኝነት ሰው መግደል እንደሚቀጡ የተሻሻለው ወንጀል ህግ ይደነግጋል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(1-3) ባሉት ንዑስ አንቀፆች በቸልተኝነት ሰው መግደል የአጥፊዎችን የቸልተኝነት ደረጃዎችን ለይቶ በመዘርዘር በየትኛው የሕግ አግባብ ጥፋተኞች እንደሚቀጡ ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም በወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ስር ከተጠቀሱት ንኡስ ድንጋጌዎች ውስጥ በንዑስ ቁጥር ሶስት ስር የተቀመጠው ንዑስ አንቀፅ ለተለያዩ ትርጉም የተጋለጠ ነው፡፡

ቸልተንነት ከሚመዘንባቸው መለኪያዎች አንፅር ሰዎች ጥፋትን ሲፈፅሙ ለነገሮች ያላቸው ግንዛቤ መሰረት በማድረግ ከመሆኑ አንፃር ባለሙያና ሙያ የሌላቸው ሰዎች ሊመዘኑ የሚችሉበት አግባብ እንዲሁ በህጉ በተጣለባቸው የጥንቃቄ ደረጃ መለያየት አንጻር በተመሳሳይ የወንጀል ህግ አንቀጽ ስር ማለትም በአንቀፅ 543(3) ጥፋተኛ ሊባሉ አይገባም፡፡ ምክንያቱም በህጉ ሙያ ላላቸውና ሙያ ለሌላቸው ሰዎች የተቀመጠው የጥንቃቄ ደረጃ ስለሚለያይ ነው፡፡ ይህ የአሰራር ልዩነት በጥፋተኞች ላይ  የእስራት እና የገንዘብ ቅጣት ልዩነት የሚፈጥር ሲሆን ይህ ደግሞ የወንጀል ህግ ለተመሳሳይ ጥፋት ተቀራረቢ የሆነ ቅጣት መጣል አለበት የሚለውን መርህ እንዳያሳካ ያደረገዋል፡፡ ስለሆነም ይህን የትርጉም ልዩነት ለማስወገድ የህግ አውጭው ይህን አንቀፅ ማሻሻል አንዱ የመፍትሄ አማራጭ ሲሆን በሌላ በኩል ገዢ የሆነ የህግ ትርጉም

**የመስጠት ስልጣን ያለው የፌደራል ጠቅላይፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ቢሰጥበት ይህንን ልዩነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይፈታዋል።**

# የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ካለመቁረጥ ጋር ተያይዞ ስለሚኖር የወንጀል ተጠያቂነት አድማስ

**ሳባ አበረ***

***አህጽሮተ ይዘት***

*የተጨማሪ እሴት ታክስ መንግስት ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ከሚሰበስባቸው የግብር ኣይነቶች አንዱ ሲሆን በባህሪው ውስብስብ ከመሆኑ የተነሳ በአግባቡ የሚሰበሰብበትን መንገድ ማመቻቸት ብሎም በአሰባሰብ ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በሚፈጥሩ ሰዎች ላይ ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማእቀፍ መፍጠር ግድ ነው። በኢትዮጵያ የተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጅ ቁጥር 285/94 ተደንግጎ በስራ ላይ ከዋለ ከአስርተ ዐመታት በላይ አስቆጥሯል። አዋጁ የተጨማሪ እሴት ታክስ አጣጣልን እና አሰባሰብን በሚመለከት ዝርዝር ድንጋጌዎችን ከመያዙም በላይ አዋጁን ተላልፈው ጥፋት የሚፈጽሙ ሰዎች ስለሚኖርባቸው የወንጀል ተጠያቂነትም አክሎ ይሟል። የተጨማሪ እሴት ታክስ አሰባሰቡን ዘመናዊ እና ግልጽ ለማድረግ ያስችል ዘንድ ግብይቶች በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እንዲከናወኑ አዋጁን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 609/2001 ግዴታ ጥሏል። በመሆኑም ይህንን ግዴታ በመተላለፍ ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ማካሄድ ከ 2-5 አመት በሚደርስ እስራት እንዲሁም ከ 10 ሺ-100 ሺ ብር በሚደርስ መቀጮ የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑ የተደነገገ ነው። የዚህን አዋጅ መደንገግ ተከትሎ በፍርድቤት በሚቀርቡ ክርክሮች ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት መፈጸምን በተመለከተ በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚገባው ማነው የሚለው ከፍተኛ የክርክር ምክንያት ነው። ለክርክር ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችም የህግ ሰውነት የሌላቸው ድርጅቶችን በወንጀል ተጠያቂ ማድረግን የሚመለከት፣ የግል ባለሀብቶችን እንዲሁም ተወካዮቻቸውን እንደ ስራ አስኪያጅ ቆጥሮ ጥፋተኛ ማድረግን በሚመለከት፣ በአባሪነት እንዲሁም ተባባሪነት የሚጠየቁ ሰራተኞችን ለይቶ አለማወቅ መሆናቸውን በዚህ ጽሁፍ የሚብራራ ሲሆን ጽሁፉ አይነተኛ የጥናት ዘዴን በመከተል የተመረጡ መዛግብትን እንዲሁም ተመሳሳይ ጽሁፎችን ለግብአትነት ተጠቅሟል።*

**ቁልፍ ቃላት፡- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ ሰው፣ ድርጅት፣ የግል ባለሃብት፣ ተወካይ፣ ስራ አስኪያጅ**

---

* LLM, LLB በአብክመ የ/ፍ/ባ/ማ/ህ/ም/ኢ/ አሰልጣኝ እና ተመራማሪ፡ ጽሁፉ በሚዘጋጅበት ጊዜ መጻህፍቶችን በማዋስ እና ሀሳቦችን በማካፈል የተባበራችሁኝን በሙሉ እያመሰገንኩ በጽሁፉ ላይ አስተያየት ለመስጠት ለሚፈልግ በ saba.abere@gmail.com መጠቀም ይቻላል።

# 1. ስለ ግብር በጠቅላላው

ከህዝብ የሚሰበሰብ ግብር የመንግስት ዋነኛ የገቢ ምንጭ በመሆኑ የመንግስት ህልውና ከሌሳች ከሚሰበሰበው ክፍያ ላይ የተመሰረተ ነው ቢባል የተጋነነ አይሆንም። ለመንግስት የገቢ ምንጭ ከመሆኑም ባለፈ ግብር በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖረውን የሀብት ክፍፍል ለማመጣጠን የሚረዳ መንገድ እንደሆነ ይታመናል። ይኸውም ከፍተኛ ገቢ ባላቸው የማህበረሰቡ ክፍሎች ላይ ከፍተኛ ግብር በመጣል በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላሉት የማህበረሰቡ ክፍሎች አገልግሎቶችን በማስፋፋት የሀገሪቱን የተረጋጋ ኢኮኖሚ መፍጠር የሚያስችል በመሆኑ ነው።[1] ግብር መሰብሰብ የተጀመረበት ጊዜ በውል ባይታወቅም በጥንታዊት ግብጽ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ3000-2800 ዓ.ዓ. በፈርኦን ሥርወ-መንግስት የተመሰረተ መሆኑን የታሪክ መዛግብቶች ያስረዳሉ።[2]

ግብር /ታክስ/ ቃሉ የተወሰደው ታክሶ ከሚለው የላቲን ቃል ሲሆን ትርጓሜውም መገመት ወይም እገምታለሁ የሚል ሲሆን መንግስት በዜጎቹ ላይ ገምቶ የሚያስቀምጠው አስገዳጅ ክፍያ ነው።[3] እንዲሁም የኦክስፎርድ የሕግ መዝገበ ቃላት ታክስ የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ሲተረጉም ታክስ ማለት ለመንግስት ካገዛና አስገዳጅ መዋጮ ሲሆን የመክፈል ግዴታው የሚጣለው በቀጥታ በግብር ከፋዩ ላይ ሆኖ የሚጣሉት የግብር አይነቶችም የገቢ ግብር፣ የካፒታል ግብር፣ የውርስ ግብር፣ የኮርፖሬት ግብር ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ግብር እና በተለያዩ አገልግሎቶች ላይ የሚጣል ግብር እንደሆነ ይገልጻል።[4]

መንግስት የተለያዩ የግብር አይነቶችን በግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ላይ ይጥላል። ባጠቃላይ የግብር ባህሪይ እና ግብሩ የሚከፈልበትን ምክንያት መሰረት ማድረግ ግብር በሁለት አይነት ይከፈላል። እነዚህም ቀጥተኛ ግብር እና ቀጥተኛ ያልሆነ ግብር በማለት ይታወቃሉ።[5] ቀጥተኛ ግብር የሚጣለው በማህበረሰቡ ገቢ፣ ትርፍ፣ ካፒታል እና ሀብት ላይ ሲሆን የገቢ ግብር ከፍተኛውን መጠን የሚይዝ ነው። በሌላ በኩል ቀጥተኛ ያልሆነ ግብር በአገልግሎቶች እና

[1]Wilson,Prichard, taxation Responsiveness and Accountabiity in Sub Saharan African, the danamics of tax bargaining, University of Toronto, 2015, page 1

[2]ግርማ ግዛው፣ የኢትዮጵያ ግብር ሕግ፣ ደንቦች፣ ባህሪያት፣ መርሆዎችና ሥርዓት ማብራሪያ 2004፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 1

[3] ዘኒ ከማሁ ገጽ 7

[4] ዘኒ ከማሁ

[5] Bizualem Belete, practices and challenges of Value Added Tax implementation in Ethiopia, 2015, Addis Ababa Ethiopia, page 1-2

እቃዎች ላይ በሚኖር ግብይት ላይ የሚጣል ነው።[6] የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀጥተኛ ያልሆነ ግብር ከሚባለው መደብ የሚመደብ ሲሆን ከተጠቃሚው ማህበረሰብ በነጋዴው አማካኝነት የሚሰበሰብ ግብር ነው።

የኢትዮጵያ የግብር ማሻሻያ ፕሮግራም በ1994 ዓ.ም ሲቀረጽ የተጨሪ እሴት ታክስን በማስተዋወቅ ሀገሪቱ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንድታገኝ አድርጓታል። የተጨማሪ እሴት ታክስ በሻጭ እና ገዢ ወይም በአገልግሎት ሰጪ እና ተቀባይ መካከል በሚደረግ ግብይት የግብይቱን 15% ገዢው ወይም ተጠቃሚው የሚከፍል ሲሆን በሻጩ/አገልግሎት ሰጪው/ ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ የሚሆንበት የግብር ስርዐት ነው። የተጨማሪ እሴት ታክስ አጣጣል እና አሰባሰብን በሚመለከት አዋጅ ቁጥር 285/94 ተደንግጎ በትግበራ ላይ ይገኛል። አዋጁ ስለተጨማሪ እሴት ታክስ አጣጣል እና አሰባበሰብ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዟል። ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ ግዴታ የሚጣልባቸው ነጋዴዎች በአመት ከ 500ሺ የኢትጵያ ብር በላይ የሚያንቀሳቅሱት ሲሆኑ ሌሎች ነጋዴዎች 75% የእቃ ማቅረብ እና አገልግሎት የመስጠት ስራ የሚያከናውኑት ለተመዘገቡ ሰዎች የሆነ እንደሆነ በፍላጎት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት መመዝገብ ይችላሉ።[7] የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ተለይተው በአዋጁ የተደነገገ ሲሆን የተጨማሪ እሴት ታክስ የማይከፈልባቸው ግብይቶችም እንዲሁ ተለይተዋል። ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ ሰው ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ታክስ ከፋይ ይሆናል። አሰራሩን ግልጽ እና ዘመናዊ በማድረግ በተጨማሪ እሴት ታክስነት የተሰበሰበን ገንዘብ በትክክል ለማወቅ ይረዳ ዘንድ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ ሰዎች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እንዲጠቀሙ ማድረግ አይነተኛ መሳሪያ መሆኑ ስለታመነበት አዋጁ በአዋጅ ቁጥር 609/2001 ተሻሽሎ ማንኛውም የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነ ሰው በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እንዲያስገባ እና ከዚሁ መሳሪያ በሚወጣ ደረሰኝ ግብይት እንዲያካሂድ ግዴታ ተጥሎበታል። ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ተካሄደ የሚባለው ለግብይቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሲሰጥ በመሆኑ ማንኛውም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበና ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የሚያካሂድ ሰው ደረሰኝ ወዲያውኑ መስጠት አለበት።[8] ይህንን ግዴታ ወደ ጎን

[6] ዘኒ ከማሁ
[7] አዋጅ ቁጥር 285/94፣ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 8ኛ አመት ቁጥር 33፣ ሰኔ 27/1994፣ አንቀጽ 16
[8] አዋጅ ቁጥር 285/94፣ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 8ኛ አመት ቁጥር 33፣ ሰኔ 27/1994፣ አንቀጽ 22 በአዋጅ ቁጥር 609/2001፣ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 15ኛ አመት ቁጥር 6 ታህሳስ 16/2001፣ አንቀጽ 10 እንደተሻሻለው

በመተው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን ሳይጠቀሙ ግብይት መፈጸም ወይም ያለደረሰኝ ግብይት መፈጸም የወንጀል ሀላፊነት እንደሚያስከትል አዋጅ ቁጥር 609/2001 በአንቀጽ 19 ይደነግጋል፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ በአግባቡ ተሰብስቦ ወደ መንግስት እንዲገባ ማድረግ የህጉ ዋና አላማ ሲሆን ይህንን አላማ ለማሳካት ደግሞ የሁሉም የመንግስት አካላት ትብብር የሚያስፈልግ በመሆኑ ህግ አስፈጻሚው እና ህግ ተርጓሚው የአዋጁን አላማ በሚያሳካ መልኩ ተግባራቸውን እየከወኑ መሆኑን ማየት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ይህንን አዋጅ ተላልፈው ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት አከናውነው በሚገኙ ሰዎች ላይ የሚጣለው ቅጣት በምን አግባብ መሆን አለበት የሚለውን ከዚህ በሚቀጥሉት ክፍሎች ይመረመራል፡፡

## 2. ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት በማከናወን ለሚፈጸሙ ወንጀሎች የተጠያቂነት አድማስ

አዋጅ ቁጥር 285/94 በክፍል 12 በታክስ ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች እና ስለሚያስከትሉት ቅጣት ዝርዝር ድንጋጌዎችን ከመያዙም በተጨማሪ የወንጀል ድርጊቶቹ ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ክስ አቀራረቡም ሆነ ውሳኔ አሰጣጡ በወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዐት ህጉ የሚመራ መሆኑን በአንቀጽ 48 ደንግጓል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በርካታ ሲሆኑ በታክስ ከፋዩ እና በባለስልጣኑ ሰራተኞች የሚፈጸሙ ወንጀሎች በሚል በሁለት የተከፈሉ ናቸው፡፡ በታክስ ከፋዩ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ህግን በመጣስ ታክስ አለመክፈል፣ ታክስን በተመለከተ አሳሳች ወይም የሀሰት መረጃ ማቅረብ፣ የታክስ ባለስልጣኑን ስራ ማሰናከል እና ለውጥን አለማስታወቅ፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋይነት አለመመዝገብ፣የተጨማሪ እሴት ታክስ ባልሆነ ደረሰኝ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት መፈጸም፣ ያልተፈቀደ ደረሰኝ መጠቀም ወይም ማተም፣የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት የሚፈጸሙ ጥፋቶች ሲሆኑ[9] የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ የማጠንጠኛ ሀሳብ ያለደረሰኝ ግብይት በሚጸምበት ጊዜ ስለሚኖረው የወንጀል ተጠያቂነት ነው፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 609/2001 በአንቀጽ 19 እንደደነገገው ማንኛውም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ ሰው ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ሲያከናውን ከተገኘ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 10 ሺ

[9] የግርጌ ማስታወሻ ቁ.7 አንቀጽ 49-54

በማያንስ እና ከብር 100 ሺ በማይበልጥ መቀጮ እና ከ ሁለት እስከ አምስት አመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል፡፡ ለመሆኑ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የወንጀል ቅጣት የሚጣልባቸው ሰዎች እነማን ናቸው? የሚለው ለክርክር በር የሚከፍት ብሎም ለተለያዩ ትርጓሜዎች የተጋለጠ መሆኑን በፍርድቤት ከቀረቡ የተለያዩ መዛግብት መረዳት ይቻላል፡፡ እንደሚታወቀው በንግድ እቅስቃሴ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ይሳተፋሉ ለምሳሌ በአንድ የምግብ እና መጠጥ አቅርቦት አገልግሎት በሚሰጥ ሆቴል ውስጥ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ቢፈጸም በወንጀል ድርጊቱ ተጠያቂ የሚሆነው አስተናጋጁ፣ ድርጅቱ፣ ገንዘብ ያዡ፣ ስራ አስኪያጁ ወይስ የድርጅቱ ባለቤት? ተጠያቂ የሚሆኑትስ በምን አግባብ ነው? የሚለው ግርታን የሚፈጥር ነው፡፡ በመሆኑም የድርጅቶችን፣ የግል ባለሀብቶቸን፣ የስራ አስኪያጆችን፣ የወኪሎችን፣ የተቀጣሪ ሰራተኞችን የወንጀል ሀላፊነት ምን እደሚመስል መመርመር ያስፈልጋል፡፡

## 2.1. የድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነት

ድርጅቶች በህግ ሰውነት የተሰጣቸው ለንግድ ሆነ ለሌላ ህጋዊ አላማ የተቋቋሙ ሲሆን ልክ እንደ ተፈጥሮ ሰው ህጋዊ ድርጊቶችን የመፈጸም መብት አላቸው፡፡ ውል የመዋዋል፣ ንብረት የማፍራት እና ማስተዳደር፣ ግብይት የመፈጸም፣ መክሰስ እና መከሰስ በራሳቸው ስም ከሚያከውኗቸው ህጋዊ ድርጊቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የህግ ሰውነት የተሰጣቸው ድርጅቶች ምንም እንኳ በተፈጥሮ ሰዎች አማካኝነት ስራቸውን የሚያከናውኑ ቢሆንም ካቋቋሟቸው ሰዎች ውጪ በራሳቸው ስም ሊከሱም ሆነ ሊከሰሱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ድርጅቶች እርስ በርሳቸውም ሆነ ከሌሎች ተፈጥሯዊ ሰዎች ጋር በሚኖራቸው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር ለሚያደርሱት ጉዳት ፍትሀብሔራዊ ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ማድረግ ዳግም ተመሳሳይ ጥፋት እንዳይደገም እና ለደረሰውም ጉዳት ካሳ እንዲሰጥ ማድረጉ ተገቢነት ያለው እንደሆነ እሙን ነው፡፡ ሆኖም አካላዊ ህልውና የሌላቸውን ድርጅቶች በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ ከመሰረታዊው የወንጀል ህግ መርህ የሚጣረስ ነው በሚል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እውቅና ተነፍጎት የነበረ ጉዳይ ነበር፡፡ ምክንያቱም የወንጀል ህግ አላማ የአጥፊውን የማጥፋት ሀሳብ በመቅጣት አጥፊውንም ሆነ ሌላውን ማህበረሰብ ከተመሳሳይ ጥፋት ማቀብ በመሆኑ የአጥፊነት ሀሳብ የወንጀል ህግ ከተመሰረተባቸው መሰረታዊ አምዶች አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በአንድ ሰው/አጥፊ/ ላይ በወንጀል ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት ለመጣል በወንጀል ጥፋት ተብሎ የተፈረጀን ድርጊት በሙሉ ሀሳብ እና ፈቃደኝነት መፈጸሙን ማረጋገጥ ይጠይቃል፡፡

ወንጀሉ እንዲፈጸም መፈለግ፣ ወንጀሉ እንዲፈጸም እውቅና መስጠት እና የሚፈጸመው ድርጊት ወንጀል መሆኑን ማወቅ ሲገባ ጥንቃቄ አለማድረግ የወንጀለንነት ሀሳብ እንደሆነ ይታወቃል። ወንጀል እዲፈጸም መፈለግም ሆነ የሚፈጸመው ድርጊት ወንጀል መሆኑን ማወቅ ለተፈጥሮ ሰዎች ብቻ የሚቻል ጉዳይ ሆኖ ሳለ ግዑዛን የሆኑ ድርጅቶችን በወንጀል ጥፋተኛ ማድረጉ ከዚህ መሰረታዊ መርህ ጋር የሚጣረስ ነው በሚል እስካሁን ድረስ ተግባራዊ ያላደረጉ ሀገራት አሉ።[10]

ከዚህ አንጻር ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ በአንጻራዊነት የቅርብ ጊዜ ክስተት እንደሆነ በጸሀፊዎች የተነገረ ነው። ይኸውም እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን ድርጅቶች መሰረታዊውን የወንጀል ፍሬ ጉዳዮች ማሟላት ስለማይችሉ ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም የሚለው አስተሳሰብ ገዝፎ የነበረ በመሆኑ ነው። ሆኖም በ1900ዎቹ መጀመሪያ የኢንዱስትሪውን መስፋፋት ተከትሎ ድርጅቶች የሚፈጽሙት ጉዳት እየጨመረ በመምጣቱ መቆጣጠሪያ እናም ጥፋት አጥፍተው በተገኙ ጊዜ ቅጣት በመጣል አጠቃላይ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ማስተካከል አስፈላጊ በመሆኑ ድርጅቶችን የወንጀል ተጠያቂነት ማስቀመጠ አስፈላጊ ሆኗል።[11]

በመሆኑም ምንም እንኳ ድርጅቶች ድርጊትን የመፈጸም ሆነ ድርጊቶቹ እንዲፈጸሙ ሀሳብ የማመንጨት ችሎታ ባይኖራቸውም ሰራተኞቻቸው በሚሰሩት ህገወጥ ድርጊት፣ ድርጊቱ ለድርጅቱ ጥቅም እስከሆነ ድረስ ድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነት ሊኖራቸው ተገቢ በመሆኑ በተለያዩ ሀገራት ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል[12]

የንግድ ድርጅቶች ሰው ሰራሽ እንደመሆናቸው መጠን በተለይ የማሰብ ችሎታ ለተፈጥሮ ሰዎች ብቻ የተሰጠ በመሆኑ ድርጅቶች የወንጀል ሀሳብ ይኖራቸዋል ብሎ ማሰብ ከባድ ነው። ከዚህ አንጻር መሰረታዊ የሆነውን የሀሳብ ክፍል በተመለከተ ሁለት አይነት አስተምህሮቶች አሉ። የመጀመሪያው ሀሳብ identification model የሚባል ሲሆን በእንግሊዝ እና ካናዳ በስፋት የሚተገበር ሆኖ የሰራተኞቹ ሀሳብ የድርጅቱ ሀሳብ ነው፣ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች

[10] criminal responsibility of legal person in common law legal system, Paper prepared for OECD Anti-Corruption Unit, Working Group on Bribery in International Business transactions
Paris 4th October 2000

[11] Angira Singhvi,Corporate Crime and Sentencing in India: Required Amendments in Law, *International Journal of Criminal Justice Sciences* Vol 1 Issue.2 July 2006, National Law University, Jodhpur, India, page.2

[12] Edward B. Diskant Comparative Corporate Criminal Liability, Exploring the Uniquely American Doctrine Through Comparative Criminal Procedure, *The Yale Law Journal*, 10/14/2008 11:37:14 AM

በመስራትም ሆነ ባለመስራት የሚፈጽሙት የወንጀል ድርጊት የድርጅቱ ድርጊት እና ሀሳብ እነደሆነ ተቆጥሮ ድርጅቱ በቀጥታ የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርበታል።[13] በዚህ ሞዴል መሰረት አንድ ድርጅት ጥፋተኛ የሚባለው ጥፋቱን የፈጸመው ሰው ጥፋቱን የፈጸመው 'ለድርጅቱ ብሎ' ሳይሆን 'ድርጅቱን ሆኖ' እንደሆነ ስለሚገመት ነው። ከዚህ አንጻር የድርጅቱ ሰራተኞች በሁለት የሚከፈሉ ሲሆን የድርጅቱ ጭንቅላት/ራስ/ እና የድርጅቱ እጅ በመባል ይታወቃሉ በመሆኑም የድርጅቱ ጭንቅላት የሆኑ ሰራተኞች ማለትም በከፍተኛ የስራ አመራር ላይ ያሉ ሰዎች የሚፈጽሙት ጥፋት የድርጅቱ ጥፋት ሆኖ በወንጀል ተጠያቂ የሚያደርገው ሲሆን በሌላ በኩል የድርጅቱ የበታች ሰራተኞች ለሚፈጽሙት ጥፋት ግን ድርጅቱ የወንጀል ተጠያቂነት አይኖርበትም ማለት ነው።[14]

በሌላ በኩል vicarious model የሚባለው እና በዩኤስ አሜሪካ በስፋት የሚታወቀው አስተምህሮ ማናቸውም የድርጅቱ ሰራተኞች የፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ለድርጅቱ ጥቅም የተፈጸመ እንደሆነ የድርጅቱ ጥፋት እንደሆነ ተቆጥሮ ድርጅቱ የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርበታል ማለት ነው። የዚህ ሁለተኛው አስተምህሮ ዋና ሀሳብ ድርጅቶች በወንጀል ድርጊቱ የሚጠየቁት ወንጀሉ የተሰራው ለጥቅማቸው ሲባል መሆኑ ሲረጋገጥ እና አጥፊውም በድርጅቱ የተሰጠውን የስራ ድርሻ ሲያከናውን የፈጸመው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። ከዚህ አንጻር ወንጀሉ የተፈጸመው በድርጅቱ ሀሳብ ነው ለማለት ድርጅቱ በአንድ ምክንያታዊ ሰው እይታ ወንጀሉ እንዳይፈጸም ቅድመ መከላለል ሳያደርግ ቀርቶ ወንጀሉ የተፈጸመ እንደሆነ የወንጀል ሀሳብ አለው ተብሎ ይገመታል። በሌላ በኩል ድርጅቱ ተፈጸመ የተባለውን የወንጀል ድርጊት እንዳይፈጸም ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ እንደሆነ ተጠያቂነት አይኖርበትም።[15]

በአገራችን የሕግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ በኢፌድሪ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 34 እውቅና ሰጥቷል። ይህ ድንጋጌ በንኡስ አንቀጽ 1 እንደሚደነግገው የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሕፈግ ላይ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሊቀጣ ይችላል። ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የህግ ሰውነት ያለው ድርጅት በወንጀል ድርጊት የሚቀጣው በግልጽ በህግ ተደንግጎ በተገኘ ጊዜ ብቻ ነው። ይህም ማለት በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ከተዘረዘሩት ወይም

[13] Allens Arthur Robinson, corporate culture as a basis for the criminal liability of corporation, prepared for the United Nations Special Representative of the SecretaryGeneral on Human Rights and Business, February 2008
[14] ዝኒ ከማሁ ገጽ 1
[15] ዝኒ ከማሁ ገጽ 2

በሌሎች ሕጎች ከተቀመጡ ወንጀሎች ውስጥ በግልጽ የሕግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶችም ይቀጣሉ በሚል ካልተቀመጠ በቀር ድርጅቶች በወንጀል የሚጠየቁ አይሆንም።

በሌላ በኩል በአንቀጽ 34/1/ ሁለተኛ ፓራግራፍ እንደተገለጸው አንድ ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው ከሃላፊዎቹ ወይም ከሰራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ስራ ጋር በተያያዘ የድርጅቱን ጥቅም በህገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ፣ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ፣ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ ነው።

የዚህ ድንጋጌ አጻጻፍ ሲታይ ከላይ በሁለት ከተከፈሉ የድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነት አስተምህሮቶች መካከል vicarious model የሚባለውን ይመስላል። በዚህ ሞዴል መሰረት ማንኛውም የድርጅቱ ሀላፊም ሆነ ሠራተኛ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ የወንጀል ድርጊት ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ድርጅቱም ተጠያቂነት ይኖርበታል ማለት ነው። በሌላ በኩል በvicarious model ድርጅቱ የወንጀል ድርጊቱ እንዳይፈጸም ቅድመ ጥንቃቄ አድርጎ እንደሆነ የወንጀል ተጠያቂነት አይኖርበትም አልያም እንደነገሩ ሁኔታ የቅጣት ማቅለያ ተደርጎ ይወሰድለታል።[16] በሀገራችን የሕግ ስርዓት ግን ይህ ሁኔታ የተቀመጠ አይደለም። ማለትም አንቀጽ 34 የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ወንጀል ተጠያቂ የሚሆንበትን መርህ እንጂ ከቅጣት ነጻ የሚሆንበትን ወይም ቅጣት ሊያቀሉ የሚችሉ ሁኔታዎች አልተደነገጉም።

ድርጅት ማለት መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆነ ወይም ህዝባዊ ሆነ ግላዊ መዋቅር ያለው አካል ሲሆን ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለፖለቲካ ለሀይማኖት ወይም ለሌላ ሕጋዊ አላማ የተቋቋመና በመንግስት እውቅና ያገኘን ማንኛውም ማህበር ያጠቃልላል። ሆኖም የመንግስት አስተዳደረ አካላት የወንጀል ተጠያቂነት እንዳይኖርባቸው አንቀጽ 34 እገዳ ጥሏል።

የህግ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት ላይ የሚጣለው ቅጣት የገንዘብ መቀጮ ሲሆን በተጨማሪም ድርጅቱ እንዲታገድ፣ እንዲዘጋ ወይም እንዲፈርስ ተጨማሪ ቅጣት ሊሰጥ ይችላል /አንቀጽ 34/2/። ሆኖም የገንዘብ መቀጮውን መጠን ወደ አንቀጽ 90 ጠቅላላ ድንጋጌ ይወስደዋል። በዚህም መሰረት አንድ የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል ተግባር ውስጥ የተገኘ እንደሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ከ100-500,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ

[16] Matthew Goode, CORPORATE CRIMINAL LIABILITY, The Common Law: Vicarious Liability and the Development of Primary Liability, Australian Institute of Criminology, available at *www.aic.gov.au/media_library/publications/proceedings/.../**goode**.pd retrived on 27/05/2016 9:40 AM*

እንደሚችል አንቀጽ 90/2/ ያስቀምጣል፡፡ ድርጅቱ የፈጸመው ወንጀል በእስራት ብቻ የሚያስቀጣ ከሆነ እስራቱ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ የሚቀጣ ሲሆን ወንጀሉ በገንዘብ መቀጮ ብቻ የሚያስቀጣ ከሆነ ደግሞ በልዩ ክፍሉ የተደነገገው የቅጣት መጠን እስከ 5 እጥፍ ድረስ ሊወሰን እንደሚችል ተደንግጓል፡፡[17]

### 2.1.1. የድርጅቶች ተጠያቂነት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ

ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ማካሄድን በተመለከተ የድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነት የሚመነጨው ከአዋጁ አንቀጽ 50/ለ/1/ እንደተሻሻለው፣ አንቀጽ 2/11/ እና አንቀጽ 2/5/ የጣምራ ንባብ ነው፡፡ አንቀጽ 50/ለ/1/"ማንኛውም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ **ሰው**...ይቀጣል" የሚል ሲሆን አንቀጽ 2/11/ በበኩሉ ሰው የሚለውን ሲተረጉም፡-

*ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው፣ የግል ባለሀብት፣ **ድርጅት**፣ የጋራ ልማት ማህበር ወይም የሰዎች ህብረት ሲሆን ሌላን ሰው በመወከል ተቀማጭነቱን ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የንግድ ስራ የሚያካሂድ የንግድ ወኪልን ይጨምራል በሚል ያስቀምጣል፡፡*

በመሆኑም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን በመተላለፍ ያለደረሰኝ ግብይት በሚፈጽሙ የንግድ ድርጅቶች በአዋጁ አንቀጽ 5/11/ እና አንቀጽ 50/ለ/ እንደተሻሻለው ተጠያቂ እንደሚሆኑ የተደነገገ ሲሆን ለመሆኑ የትኞቹ የንግድ ድርጅቶች ናቸው ተጠያቂ የሚሆኑት የሚለውን ለመለየት አዋጁ ለድርጅት የሰጠውን ትርጉም መመልከት ያሻል፡፡ በዚህ መሰረት ድርጅት ማለት፡-

*የንግድ ስራ የሚያካሂድ ማንኛውም ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማህበር፣ወይም ከኩባንያ ወይም ከተመዘገበ የሽርክና ማህበር ጋር ተመሳሳይ የሆነና በውጭ ሀገር ህግ መሰረት የተቋቋመ ድርጅት ወይም ማናቸውም የመንግስት የልማት ሰራ ድርጅት ወይም የገንዘብ ድርጅት ሲሆን በውጭ ሀገር ያለን አካል በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ስራ የሚያካሂደውን ወኪል እና ጸንቶ በሚሰራበት የኢትዮጵያ ወይም በሌላ አገር ህግ መሰረት*

[17] በአንቀጽ 90/3/ የእስራት ቅጣቱ ወደ ገንዘብ የሚቀየርበትን ስሌት ያስቀመጠ ሲሆን እስከ 5 አመት ቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር 10 ሺ፣ እስከ 5 አመት ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር 20 ሺ፣ እስከ 10 አመት ጽኑ እስራት ለሚስቀጣ ወንጀል እስከ ብር 50ሺ. እንዲሁም ከ10 አመት በላይ ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ከፍተኛ ጣሪያ /500ሺ/ ድረስ ለመቅጣት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ወንጀሉ በገንዘብ መቀጮ ብቻ የሚያስቀጣ ከሆነ መቀጮው በ 5 እጥፍ አድጎ እንደሚወሰን አንቀጽ 90/4/ ያስቀምጣል፡፡

*የተመሰረተ ወይም እውቅና ያገኘ ቢሆንም ባይሆንም እንደ ድርጅት የሚንቀሳቀስን ይጨምራል።* በማለት ያስቀምጣል።

በሌላ በኩል በንግድ ህጉ አንቀጽ 212 ስድስት የንግድ ማህበር አይነቶች እውቅና የተሰጣቸው ሲሆን እነዚህም የተራ ሽርክና ማህበር፣ የእሽሙር ማህበር፣ የህብረት ሽርክና ማህበር፣ ሁለት አይነት ሀላፊነት ያለበት የሽርክና ማህበር፣ የአክስዮን ማህበር እና ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ናቸው። ከነዚህ መዘርዝሮች ውስጥ የህግ ሰውነት እንዲኖረው እና እንዲመዘገብ የማይጠበቀው የእሽሙር ማህበር ሲሆን ሌሎቹ ግን በህግ ሰውነት እንዳላቸው ሆነው ይቆጠራሉ /አንቀጽ 210/2// በመሆኑም የተመዘገበ የሽርክና ማህበር ኩባንያን ጨምሮ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ፈጽመው የተገኙ እንደሆነ የወንጀል ቅጣት ይጣልባቸዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ በሽርክና ማህበርነት ያልተመዘገቡ ነገር ግን በግል ባለሀብትነት የሚተዳደሩ የንግድ ድርጅቶች በብዛት ያሉባት ሀገር እንደመሆኗ መጠን እነዚህ ድርጅቶች /sole propritery/ በዚህ አዋጅ መሰረት የወንጀል ተጠያቂነት ሊኖርባቸው ይገባል ወይ? የሚለውን በሚመለከት ግልጽ መግባባት የተፈጠረ አይመስልም ምክንያቱም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአንድ ውሳኔው ላይ፡-

*ድርጅት የሚለው ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል መሆኑን የተረዳን ቢሆንም በአዋጁ መግቢያ "ትርጓሜ" ለሚለው አንቀጽ 2/5/ እና 2/11/ ጋር አገናዝበን ስንመለከተው ድርጅት ማለት በሽርክና ማህበር፣ በኩባንያ እና በሰዎች ህብረት ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ አይታይም*[18]

የሚል ውሳኔ ሰጥቷል። ሆኖም የወንጀል ህጉን አንቀጽ 34፣ የንግድ ህጉን አንቀጽ210 እና ተከታዮቹ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን የትርጓሜ ድንጋጌዎች አንቀጽ 2/5/ እና 2/11/ በጣምራ ስንመለከት በዚህ አዋጅ መሰረት የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርባቸው የህግ ሰውነት የተሰጣቸው የንግድ ድርጅቶች ማለትም በንግድ ህጉ አንቀጽ 216 ከተጠቀሱት ከእሽሙር ማህበር ውጪ ያሉ የንግድ ማህበራት፣ እንዲሁም በፍትሐብሄር ህጉ አንቀጽ 404 እና ተከታዮቹ መሰረት የሚቋቋሙ ሰዎች ህብረት እንጂ ከእነዚህ ውጪ ያሉ የንግድ ድርጅቶች በተለይም በግል ባለሃብትነት የሚተዳደሩ ድርጅቶች አይደሉም።

[18] የፌድራል ጠቅላይ ፍርድቤት የሰበር ሰሚ ችሎት የመዝገብ ቁጥር 53612፣ ቅጽ 10 በአመልካች እነ አቶ ፍሰሀ ዓባይ ሁለት ሰዎች እና ተጠሪ ዐ/ህግ ገጽ 204

በወንጀል ህጉ አንቀጽ 34 መሰረት ድርጅቶችን በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ ድርጅቶቹ የህግ ሰውነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ የወንጀል ህጉን መርህ በተከተለ መልኩ ድርጅትን ሲተረጉም ከላይ እንደተገለጸው የሽርክና ማህበራትን፣ ኩባንዎችን እንዲሁም የሰዎች ህብረትን ብቻ በመነጠል ድርጅት ሊባሉ እንደሚገባ በግልጽ ደንግጎ እያለ ድርጅት ማለት በነዚህ ብቻ አይወሰንም በሚል በሰበር ችሎቱ የተሰጠው ውሳኔ የወንጀል ህጉን የህጋዊነት መርህ የሚጣረስ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በአንቀጽ 23 መሰረት አንድ ሰው/የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ/ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው የሕግ፣ የሞራል እና የድርጊት ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የሕግ ሰውነት ያልተሰጣቸውን የንግድ ድርጅቶችን በወንጀል ሀላፊ ለማድረግ የህግ ፍሬ ነገሩ ያልተሟላ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም አዋጁ የድርጅት ስራ አስኪያጅን ሲተረጉም ከላይ የተዘረዘሩትን ኩባንያ፣ የሽርክና ማህበር እንዲሁም የሰዎች ህብረትን የሚያስተዳድሩ እና የሚቆጣጠሩ ሰዎችን የሚመለከት መሆኑ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ የድርጅትን ‘ማእረግ’ የሰጣቸው እኒህን ድርጅቶች ብቻ መሆኑን የሚያጠናክር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ የሚገባው ኩባንያዎች፣ የሽርክና ማህበራት እና የሰዎች ህብረት ብቻ ናቸው፡፡

ሌላው ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ከመፈጸም ወንጀል ጋር ተያይዞ ድርጅቶችን በተመለከተ በተግባር እያጋጠመ ያለው ችግር በድርጅቶቹ ላይ የሚጣለው የገንዘብ ቅጣት መጠን ነው፡፡ ይኸውም ድርጅቶች አካላዊ ህልውና የሌላቸው በመሆኑ በወንጀል ድርጊት ተሳትፈው የተገኙ እንደሆነ ተጨማሪ ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በገንዘብ መቀጮ ብቻ እንደሚቀጡ የወንጀል ህጉ በአንቀጽ 90/2/ እና 34/3/ በግልጽ የደነገገው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በአንቀጽ 90/3/ መሰረት በእስራት ብቻ ለሚያስቀጡ ወንጀሎች የህግ ሰውነት የተሰጣቸው ድርጅቶች ተሳትፈው ሲገኙ እስራት ቅጣቱ በገንዘብ ተቀይሮ ሊቀጡ እንደሚችሉ እንዲሁም በመቀጮ ብቻ ለሚያስቀጡ ወንጀሎች ደግሞ ቅጣቱ እስከ 5 እጥፍ ድረስ ቅጣት ሊሰጥ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ሆኖም በእስራት እና መቀጮ በጣምራ ለሚያስቀጡ ወንጀሎች በምን መልኩ ቅጣት እንደሚሰጥ ግልጽ ህግ የለም፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን በመተላለፍ ያለደረሰኝ ግብይት መፈጸም ደግሞ ከ2-5 አመት በሚደርስ እስራት እንዲሁም ከ10-100 ሺ ብር በሚደርስ መቀጮ የሚያስቀጣ ወንጀል ነው በመሆኑም ሁለቱን ቅጣቶች አጣምሮ

በመወሰን ላይ ተግባራዊ ችግር ሲገጥም ይታያል።[19] ለአብነትም በከሳሽ ዐቃቤ-ሕግ እና ተከሳሾች እነ ታረቀኝ ገ/ጊዮርጊስ 4 ሰዎች በካሌብ ጌጣጌጥ መሸጫ ድርጅት ድርጅቱ የአንገት ሀብል ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሽያጭ የፈጸመ በመሆኑ ጥፋተኛ ከተባለ በኋላ የ60 ሺ ብር መቀጮ እንዲከፍል ተወስኖበታል።[20] በተመሳሳይ በአመልካቾች ዘቴዊንስ ባር እና ሬስቶራንት ሀ/የተ/የግ/ማ/ 2 ሰዎች እና በተጠሪ ዐ/ህግ መካከል በነበረው የሰበር ክርክር አመልካቾች በስር ፍርድቤት በነበራቸው ክርክር ያለደረሰኝ ግብይት መፈጸማቸው ተረጋግጦ አንደኛ አመልካች የሆነው ንግድ ድርጅት በ60 ሺ ብር የተቀጣ መሆኑን ከመዝገቡ ለመረዳት ይቻላል።[21] ከነዚህ መዛግብት መረዳት የሚቻለው ምንም እንኳ ተከሳሽ ድርጅቶች የተለያየ የሀብት መጠን እዲሁም የመክፈል አቅም ሊኖራቸው እንደሚችል ቢገመትም ፍርድቤቶቹ ተመሳሳይ የሆነ ቅጣት ሰጥተዋል።

የድርጅቶችን ቅጣት በተመለከተ የእስራት ቅጣት ወደ ገንዘብ እንደሚቀየር ከመደንገግ በቀር ቅጣቱ ሲሰጥ ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገቡ ጉዳዮች በህጉ ካለመመልከታቸውም በላይ በተለይ የእስራት ቅጣቱ ወደ ገንዘብ ሲቀየር መጀመሪያ ቅጣት ተሰጥቶ ወደ ገንዘብ ይቀየር አልያም እንዲሁ በደፈናው የገንዘብ መቀጮው ይጣል ግልጽ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ አንድ ድርጅት ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት አከናውኖ በተገኘ ጊዜ ቅጣቱ በምን አግባብ ሊጣል እንደሚገባ ፍርድቤቶች ውሳኔውን በሚሰጡበት ወቅት አስቸጋሪ ሁኔታ ያጋጥማቸዋል። ይህንን ችግር ለመፍታት የፌዴራሉ ጠውላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በድርጅቱ ላይ የእስራት ቅጣቱ ከተወሰነ በኋላ በአንቀጽ 90/3/ መሰረት ወደ ገንዘብ ሊቀየር እንደሚገባ በውሳኔው አሳይቷል።[22]

በዚህ ረገድ ከቅጣት አላማዎች አንዱ እና ዋነኛው ወንጀሉ በአጥፊውም ሆነ በሌሎች ድጋሚ እንዳይፈጸም መከላከል /deterrence/ በመሆኑ ማንኛውም ቅጣት በድርጅቶች ላይ የሚጣለውም ቢሆን ይህንን አላማ የሚያሳካ መሆን ይኖርበታል። ይህንን አላማ ለማሳካት ደግሞ ቅጣቱ

[19] Dejene Girma Janka, *Notes on the criminal responsibility of Juridical Persons in Ethiopia*, Jimma University Journal of Law, v2,No.1,April 2009,page83

[20] የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር መዝገብ ቁ/ 48850 በአመልካቾች እነ ታረቀኝ ገ/ጊዮርጊስ ሶስት ሰዎች እና መልስ ሰጪ ዐ/ህግ ቅጽ 10 ገጽ 191

[21] የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር መዝገብ ቁ 51090 ቅጽ11 በአመልካቾች ዘቴዊንስ ባር እና ሬስቶራንት ሀ/የተ/የግ/ማ/ 2 ሰዎች እና ተጠሪ ዐ/ህግ ገጽ 334

[22] የፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ችሎት መዝገብ ቁጥር 74237 ቅጽ 14 ገጽ 247 በአመልካች ዐቃቤህግ እና ተጠሪ እብካለ እንዳሻው ጠ/ንግድ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በህዳር 6 2005 የተወሰነ። በዚህ መዝገብ የቅጣት ውሳኔ ሲሰጥ የወንጀሉን አፈጻጸም ዝቅተኛነት በማስገባት 10ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እና 2 አመት እስራት ከወሰነ በኋላ ሁለት አመት እስራቱን በ8 ሺ ብር መቀጮ በመቀየር በድምሩ 18ሺ ብር እዲቀጣ ወስኗል

ከጠፋው ጥፋት ወይም ከደረሰው ጉዳት አንጻር ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ ጠቅላላ ድንጋጌ በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ የተካተተ ቢሆንም የህግ ሰውነት የተሰጣቸውን ድርጅቶች በሚመለከት ግን ቅጣት ሲጣል ምን ምን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ሊገቡ እንደሚገቡ ማለትም የቅጣት ማቅለያ ወይም ማክበጃ የሚሆኑ ምክንያቶች ተለይተው የተቀመጡ አይደሉም፡፡ በዚህ ረገድ የሌሎች አገራትን ተሞክሮ ስንመለከት በአንድ ድርጅት ላይ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ የሚወሰነው የተፈጸመውን ወንጀል አደገኛነት መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የአደገኝነት መጠን የሚለካው ደግሞ በወንጀሉ የተገኘ ጥቅም፣ በወንጀሉ ምክንያት የደረሰ ጉዳት /በተለይም ጉዳቱ ሆን ተብሎ የተፈጸመ እንደሆነ/፣ የድርጅቱ የቀድሞ የአጥፊነት ልማድን መሰረት በማድረግ ነው፡፡[23]

የወንጀል ህጉ አንቀጽ 90/2/ ፍርድቤት የገንዘብ መቀጮን ሲወስን የተቀጪውን የአደገኝነት መጠን፣ የሀብቱን ሁኔታ፣ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነ ስለሚደነግግ ይህንን ድንጋጌ ለድርጅቶችም መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል የእስራት ቅጣቱ እና መቀጮው ተጣምሮ በሚገኝበት ጊዜ ቅጣቱ በምን መልኩ ነው የሚጣለው የሚለውን በሚመለከት እስራቱ ወደ ገንዘብ ከተቀየረ በኋላ ከገንዘብ መቀጮው ጋር ተደምሮ ሊጣል ይገባል፡፡[24] አንድ ወንጀል በእስራት እና መቀጮ በጣምራ እንዲያስቀጣ ተደርጎ ሲቀረጽ የወንጀሉ ከፍ ያለ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ ነው ከዚህ አንጻር በጣምራ የሚያስቀጣን ወንጀል በእስራት ወይም በመቀጮው ብቻ እንዲቀጣ ማድረግ ተገቢ አይሆንም፡፡ በመሆኑም አንድ ድርጅት ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት አከናውኖ የተገኘ እንደሆነ እስከ 20 ሺ ብር የሚደርስ መቀጮን[25] ከ10 ሺ-100 ሺ የሚደርስ መቀጮው ጋር በመደመር ቅጣት ማስቀመጥ ይገባል፡፡ ሆኖም በአንቀጽ 90/2/ የተደነገጉ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

[23] Clifford Chance, Corporate Liability in Europe January 2012 page 9, Ilene H. Nagel Winthrop M. S wenson, The Federal Sentencing Guidelines for Corporations: Their Development, Theor etical Underpinnings, and Some Thoughts About Their Future, Washington University Law Review, V olume 71 Issue 2 Corporate Sentencing, Januar y 1993, page 37

[24] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 21

[25] የወንጀል ህጉ አንቀጽ 90/3/ የእስራት ቅጣት ወደ ገንዘብ የሚቀየርበትን ሁኔታ ሲያስቀምጥ እስከ 5 አመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ቅጣት እስከ 20 ሺ ብር በሚደርስ መቀጮ የሚቀየር ሲሆን ያለየተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት መፈጸም ከ2 አመት እስከ 5 አመት እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ ወደ ገንዘብ ሲቀየር እስከ 20 ሺ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል ማለት ነው፡፡ የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተም በልዩ ህጉ የተቀመጠው መጠን እስከ 5 እጥፍ ሊደርስ የሚችል በመሆኑ እስከ 500ሺ ብር ሊደርስ ይችላል፡፡

## 2.2. የግል ባለሀብት ተጠያቂነት

የግል ባለሀብት ማለት ከሽርክና ማህበራት ወይም ይጎን ከመሰለ አደረጃጀት ካላቸውና የህግ ሰውነት ከተሰጣቸው ድርጅቶች ውጪ በአንድ ግለሰብ ባለቤትነት ተመዝግቦ ያለን የንግድ ድርጅት የሚመለከት ነው።[26] ማንኛውም ***ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ ሰው*** ያለደረሰኝ ግብይት የፈጸመ እንደሆነ ከ2-5 አመት በሚደርስ እስራት እንዲሁም ከ10-100 ሺ ብር በሚደርስ መቀጮ እንደሚቀጣ ይደነግጋል። በሌላ በኩል በአንቀጽ 2/11/ ደግሞ ሰው የሚለው ሲተረጎም የግል ባለሃትን እንደሚጨምር ተገልጿል። በዚህም መሰረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ የግል ባለሃብት በሚያከናውነው የንግድ ስራ ያለደረሰኝ ግብይት የፈጸመ እንደሆነ ከላይ የተጠቀሰው ቅጣት ይጣልበታል ማለት ነው። ሆኖም የግል ባለሀብቱ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጥፋተኛ የሚባለው እራሱ ደረሰኙን ቆርጦ በማይሰጥበት ጊዜ ነው ወይስ ከሰራተኞቹ አንዱ ወይም ብዙዎቹ በሰሩት በዚህ ድርጊት? የሚለው ግልጽ ባለመሆኑ የተነሳ ለክርክር በር የሚከፍት ነው።

አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ይቀጣ ዘንድ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 ላይ የተቀመጡትን መሰረታውያን ፍሬ-ነገሮች መሟላት ይኖርባቸዋል። ይኸውም በህግ ተለይቶ በተፈቀደ ጊዜ የነዚህ ሁኔታዎች መሟላት ሳያስፈልግ ጥፋተኛ ማድረግ የሚቻል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣው ሁሉም የድርጊት፣ የሀሳብ እና የሕግ ክፍሎች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው። የዚህ ድንጋጌ አስፈላጊነት የሚመነጨው የወንጀል ቅጣት የሚሰጠው የጥፋተኝነት ሀሳብን ለመቅጣት በመሆኑ እና የዚህ ጥፋተኝነት ሀሳብ የሚገለጠው ደግሞ አንድን ድርጊት በማድረግ፣ባለማድረግ እንዲሁም በአንድም ሆነ በሌላ ሁኔታ ድርጊቱ እንዲደረግ ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ አስተዋጽኦ በማድረግ ነው። በመሆኑም አንድ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ የግል ባለሀብት የአዋጁ ድንጋጌ በመጣስ በሚያካሂደው የንግድ ስራ ያለደረሰኝ ግብይት የፈጸመ እንደሆነ የተቀመጠው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆንበታል። ሆኖም ቀደም ባለው ክፍል እንደተገለጸው በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች የሚሳተፉ በተለይም በእለት ከእለት ሽያጭ ላይ የግል ባለሀብቱ የማይሳተፍባቸው እንዲያውም ንግዱ በሰራተኞች ብቻ የሚከናወንበት ጊዜ በርካታ

[26] አበበ አስማረ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ከመስጠት ግዴታ ጋር በተያያዘ ስለሚደረጉ የወንጀል ክርክሮች፡ አንዳንድ ምልከታዎች፣ የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት 25ኛ ቮልዩም ቁ.2 መስከረም 2005 ዓ.ም ገጽ 266

ናቸው ታዲያ በዚህ ሁኔታ የሽያጭ ሰራተኞች በሚፈጽሙት ሽያጭ የወንጀል ድርጊት ቢፈጽሙ ባለሀብቱን ተጠያቂ ማድረግ ይቻላል ወይ የሚለው አከራካሪ ጉዳይ ነው።

በሌሎች ሰዎች ጥፋት ምክንያት የሚኖር ተጠያቂነት /vicarious liability/ በፍትሐብሄራዊ ግንኙነት የተፈቀደ እንደሆነ የፍትሐብሄር ህጉ አንቀጽ 2124 እና ተከታዮቹ ይደነግጋሉ። በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ሰው ለሌላው ሰው ስራ ሀላፊ የሚሆነው ይህ የተባለው ሰው በሕግ ወይም በጥፋት ምክንያት ሀላፊነት ሲኖርበት ነው። ይህ አይነት ሀላፊነት በአብዛኛው በአሰሪ እና ሰራተኛ ግንኙነት ውስጥ የሚከሰት ሲሆን ሠራተኛው ለአሠሪው ጥቅም ሲል በሰራው ሥራ አሰሪው ሊጠየቅ ይገባል ይልቁንም በተሰራው ሥራ ከሰራተኛው ይልቅ አሰሪው የሚጠቀም በመሆኑ እና ከሠራተኛው ይልቅ አሠሪው የተሻለ የመክፈል አቅም ስላለው ምንም እንኳ አሰሪው የሰራተኛው ባጠፋው ጥፋት ተሳታፊ ባይሆንም ፍትሐብሄራዊ ተጠያቂነት ሊኖርበት ይገባል ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነው።

በተመሳሳይ በወንጀል ጉዳዮችም ቢሆን በሕግ በግልጽ ተደንግጎ የተገኘ እንደሆነ ሰራተኞች በፈጸሟቸው የወንጀል ድርጊቶች የሠራተኞቹ ተጠያቂነት እንዳለ ሆነ አሰሪዎችም በተወሰነ መልኩ የሚጠየቁበት አግባብ አለ።[27]

በኢፌድሪ የወንጀል ህግ በወንጀል አፈጻጸም ላይ ተካፋይ ስለመሆን ሲደነግግ በዋናነት ሶስት የተሳትፎ አይነቶች እንዳሉ ይገልጻል እነዚህም ዋና ወንጀል አድራጊ /አንቀጽ 32/፣ አነሳሽ /አንቀጽ 36/፣ አባሪ /አንቀጽ 37/ ናቸው። ከነዚህ የተሳትፎ አይነቶች ውጪ ስለሌላ ሰው ጥፋት በወንጀል ተጠያቂ ስለመሆን በወንጀል ህጉ እውቅና የተሰጠው ጉዳይ አይደለም። በሌላ በኩል የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ የስራ አስኪያጅ ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ድርጊቱ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአባሪነት ወይም በአነሳሽነት ተሳትፎ የሚያደርጉ ሰዎች የሚቀጡ መሆኑን በአንቀጽ 55 ከሚገልጽ በቀር አሰሪዎች/የግል ባለሀብቶች/ በሰራተኞቻቸው ጥፋት ምክንያት ስለሚኖርባቸው የወንጀል ተጠያቂነት የሚለው ነገር የለም። በመሆኑም ያለደረሰኝ ግብይት መፈጸም ወንጀል በተደረገ ጊዜ በወንጀሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተሳተፉ ሰዎች ብቻ ሊጠየቁ እንደሚገባ መገንዘብ ይቻላል። በዚህ ረገድ በአንድ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድቤት በቀረበ ጉዳይ የክፍሉ ዐቃቤ ህግ በንግድ ድርጅት ባለቤቱ እና በሽያጭ

[27] Alex Kreit, *vicarious Criminal Liability and the constitutional Dimension of Pinketon*, AMERICAN UNIVERSITY LAW REVIEW [Vol. 57:585 February 2008 page 11

ሰራተኛ ላይ የአዋጁን አንቀጽ 56/1/ እንደተሸሻለው፣ አንቀጽ 22/1/፣ አንቀጽ 50/መ/ለ/1/ በመጥቀስ ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽመዋል የሚል ክስ ያቀረበባቸው በመሆኑ የስር ፍርድቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካደመጠ በኋላ የሽያጭ ሰራተኛዋ ወንጀሉን ስለመፈጸሟ የተነገረባት በመሆኑና የግል ባለሃብቱም ግብይት ያለደረሰኝ እንዳይከናወን አስፈላጊውን ጥንቃቄ ያላደረገ በመሆኑ ሁለቱንም ተከሳሾች ጥፋተኛ በማለት የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል። ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ከፍተኛው ፍርድቤት ደግሞ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ የሽያጭ ሰራተኛው በወንጀሉ ቀጥተኛ ተሳትፎ ስለነበረው ጥፋተኛ መባሉ አግባብነት አለው የግል ባለሀብቱ ግን በተፈፀመው ድርጊት ቀጥተኛ ተሳትፎ የነበረው ስለመሆኑ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ በነፃ ይሰናበታል የሚል ውሳኔ በመስጠቱ በውሳኔው ቅር የተሰኘው ዐቃቤ-ሕግ ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት አቅርቦ የጠቅላይ ፍርድቤቱ ደግሞ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት የሰጠው ውሳኔ ነው ተገቢ በማለት የከፍተኛ ፍርድቤቱን ውሳኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤቱን ውሳኔ አጽንቷል። አሁንም ተከሳሾች ጠቅላይ ፍርድቤቱ በውሳኔው የሕግ ስህተት ፈጽሟል በማለት አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት የሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል። የሰበር ችሎቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የግል ባለሀብቱ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ተፈጽሟል በተባለበት ጊዜ በተፈፀመው አድራጎት ተሳትፎ የነበረው ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዲይ አይደለም። ይልቁንም የጥፋተኝነት መሰረት ሆኖ የተያዘው በአድራጎቱ የተነሣ የፈፀመው ጥፋት ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ እንደተመለከተው ድርጅቱ አዋጁን በመተላለፍ ስለፈፀመው ጥፋት ተተክቶ ተጠያቂ ሊሆን በመቻሉ ነው በዚህ መሰረት ከተጠያቂነት ለመዳን የሚቻለው በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/3/ የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ለማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ብቻ ነው በማለት የግል ባለሃብቱን ተጠያቂነት የሚመነጨው የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ነው ተብሎ ስለሚገመት ነው እንጂ በወንጀሉ ቀጥተኛ ተሳትፎ አለው በሚል አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል።[28]

ይህ ድምዳሜ በመሰረቱ ሕጉ ድርጅት እና ሥራ አስኪያጅ ብሎ ለይቶ ያስቀመጣቸውን ትርጓሜዎች የተከተለ አይደለም። ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደተቻለው በግል ባለሀብትነት የሚተዳደሩ የንግድ መደብሮች 'ድርጅት' የሚለውን መስፈርት የሚያሟሉ ባለመሆናቸው የወንጀል ተጠያቂነት የሌለባቸው ከመሆናቸውም በላይ ባለቤቶቻቸውም ሆነ ተወካዮች እንደ ስራ አስኪያጅ ተቆጥረው ተጠያቂ የሚሆኑበት የህግ መሰረት አይኖርም። በሌላ በኩል ደግሞ

[28] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 18

ተቀጣሪ ሰራተኞችን በወንጀሉ ተጠያቂ እያደረጉ ከወንጀል ድርጊቱ ተጠቃሚ የሚሆነውን የግል ባለሃቱን ነጻ ማድረግ ፍትሀዊነት የጎደለው ከመሆኑም በላይ ህጉ ሊከላለክ የሚፈልገውን ህገ ወጥ ተግባር እንዳይከላከል መሰናክል የሚፈጥር መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የተጨማሪ እሴት ታክሱ የግል ባለሀብቶች በሰራተኞቻቸው ጥፋት የሚጠየቁበትን የሕግ ማእቀፍ አሻሽሎ ማስቀመጥ ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ አሁን ባለው የሕግ ማእቀፍ ግን ባለሀብቶችን እንደ ሥራ አስኪያጅ በመቁጠር ተጠያቂ ማድረግ የወንጀል ሕጉን የሕጋዊነት መርህ የሚጥስ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በሕግ ላይ ከተደነገጉት ወንጀሎች ጋር ጋር ይመሳሰላል በማለት ወንጀልነቱ በግልጽ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት ፍርድቤት እንደወንጀል ሊቆጥረው እንደማይችል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2/3/ ክልከላ የተደረገ በመሆኑ ይህንን ክልከላ በመተላለፍ በአዋጁ ያልተመለከተን ስለሌላ ሰው ጥፋት የወንጀል ተጠያቂነት ባለቤቶች እንደስራ አስኪያጅ ተቆጥረው ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል በሚል የሚሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ሌላው በተግባር የሚስተዋለው ችግር አንድ የንግድ መደብር ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ባለቤቱ ወይም ተወካዩ በተደራራቢ ወንጀሎች ክስ ሲቀርብበት ይታያል፡፡[29] በንግድ መደብሩ ባለቤቶች እና ተወካዮች የሚቀርቡ ተደራራቢ ክሶች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን አንቀጽ 50/ለ/1/ በመተላለፍ ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽሟል የሚል አንድ ክስ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን አንቀጽ 50/መ/2/ በመተላለፍ ያለደረሰኝ ግብይት በመፈጸሙ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን አለመጠቀም ወንጀል ፈጽሟል የሚል ሌላ ተጨማሪ ክስ ይቀርብበታል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ክስ ሊቀርብበት የሚገባው በተደራራቢ ወንጀል ነው ወይ የሚለውን መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60/ለ/ መሰረት አንድ ሰው በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ ተደራራቢ ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ በአንቀጽ 65 እና 187/1/ ቅጣቱ ከብዶ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች

[29] የምዕ/ት/ዞ/ከ/ፍ/ቤ/ፋ/ቁ/ 49998 በከሳሽ ዐ/ሕግ እና ተከሰሾች እነ ያህያ ሀሚድ 4 ሰዎች፣ የምዕ/ት/ዞ/ከ/ፍ/ቤ/ፋ/ቁ 49997 በከሳሽ ዐ/ሕግ እና ተከሰሾች እነ ኢሳ ጋሻው 2 ሰዎች፣ የምዕ/ት/ዞ/ከ/ፍ/ቤ/ፋ/ቁ/ 08335 በከሳሽ ዐ/ሕግ እና ተከሳሽ ኑርሁሴን አደም፡፡ በነዚህ በሶስቱም መዛግብት ፍርድ ቤቱ የተፈጸመው ድርጊት አንድ በመሆኑ ተደራራቢ ክስ ሊቀርብ አይገባም በሚል ተከሰሾች በአንዱ ክስ ብቻ ጥፋተኛ ያሏቸው መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

የተፈጸሙት በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ ወይም ችልተኝነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ ሲሆን አድራጊው ተመሳሳይ ባህሪ ባላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች የማይቀጣ መሆኑን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 61/1/ ለአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ አንድ ቅጣት በሚለው መርህ አስቀምጧል፡፡

በአንቀጽ 60/ለ/ አንደኛ ፓራግራፍ መሰረት በአንድ ድርጊት ከአንድ በላይ ድንጋጌዎችን መጣስ በምን አይነት ሁኔታዎች እንደሚከሰት መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ ጣምራ ወንጀሎች ተፈጽመዋል ለማለት በአንድ ድርጊት የተፈጸሙ ጥፋቶች የተለያየ ይዘት እና ባህሪይ ያላቸው ወንጀሎች በመሆናቸው በተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች የሚሸፈኑ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ግን የተፈጸመው ድርጊት በተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች ስር የተጠቀሰ ቢሆንም እንኳ አንድ ባህሪ እና ይዘት ኖሮት በአንድ የህግ ድንጋጌ ስር የሚሸፈን ከሆነ አጥፊው በተደራራቢ ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ ከአንድ በላይ በሆኑ የህግ ድንጋጌዎች ክስ ሊቀርብበትም ሆነ ቅጣት ሊጣልበት አይችልም፡፡[30]

ከዚህ አንጻር አንድ ነጋዴ ያለደረሰኝ ግብይት በሚያከናውንበት ጊዜ ከአንድ በላይ የህግ ድንጋጌዎችን በመጣስ ጣምራ ወንጀል ፈጽሟል ለማለት የድንጋጌዎቹን ይዘት እና ባህሪይ መመልከት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ አንቀጽ 50/ለ/1/ እንደተሻሻለው ***የተጨማሪ እሴት ታክስ ባልሆነ ደረሰኝ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ማካሄድ*** የሚል ርእስ የተሰጠው ወንጀል ሲሆን ዝርዝሩም ማንኛውም ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ሲያካሂድ ከተገኘ ከ10 ሺ በማያንስ ከ100 ሺ በማይበልጥ መቀጮ እንዲሁም ከ2- 5 አመት በሚደርስ በማይበልጥ እስራት እንደሚቀጣ ያስቀመጠ ሲሆን አንቀጽ 50/መ/2/ ደግሞ ***የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች*** የሚል ርዕስ የተሰጠው ሆኖ ዝርዝሩም ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው መሳሪያው በጥገና ባለበት ጊዜ ካልሆነ በቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ከ1 አመት በማያንስ እና ከ 2 አመት በማይበልጥ እስራት እደሚቀጣ ይደነግጋል፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች አርእስቶቻቸው እና ይዘታቸው የተለያየ ሲሆን ያለደረሰኝ ግብይት መፈጸምን በሚመለከት ግን በጋራ የሚጋሩት ተመሳሳይ ይዘት እና ባህሪይ ያለው ወንጀል

[30] Philippe Graven, An Introduction to Ethiopian Penal Law( Article 1- 81), Faculty of Law, Haile Silase I University, Adiss Ababa, Ethiopia 1965, p.165

ነው። በመሆኑም አንቀጽ61/1/ እንደሚደነግግው ያለደረሰኝ ግብይት ሲፈጸም ምንም እንኳ በሁለቱም ድንጋጌዎች ላይ እንደሚያስቀጣ የተቀመጠ ቢሆንም ድንጋጌዎቹ ተመሳሳይ ይዘት እና ባህሪይ ያላቸው በመሆኑ ተከሳሹ በተደራራቢ ወንጀል የሚጠየቅበት የህግ ምክንያት አይኖርም ማለት ነው። ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ድርጊቶች የተለያየ አላማ ባላቸው ከአንድ በላይ በሆኑ የህግ ድጋጌዎች አካቶ መያዝ በወንጀል ህጉም ሆነ በተለያዩ አዋጆች ላይ የተለመደ ነው ይኸውም ድርጊቶቹ የሚያስቀጡበትን አድማስ ለማስፋት እና በየትኛውም አላማ ቢፈጸሙ የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለመደንገግ እንጂ ተመሳሳይ ይዘት ባላቸው ነገር ግን በተለያየ አላማ ለተቀመጡ ከአንድ በላይ በሆኑ ድንጋጌዎች ጥፋተኛ ለማለት በማሰብ አይደለም። በመሆኑም ነጋዴው ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነው ለምን አላማ ነው የሚለውን በመመዘን ክስ ሊቀርብት የሚገባው እንደጉዳዩ ሁኔታ ከሁለት በአንዱ ድንጋጌ እንጂ በሁለቱም ሊሆን አይገባም።

## 2.3. የስራ አስኪያጅ ተጠያቂነት

ከአስተዳደራዊው ተጠያቂነት በተጨማሪ አንድ ደርጅት የአዋጁን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ ስራ አስኪያጁ በአዋጁ ላይ የተቀመጡ ቅጣቶች እንደሚፈጸሙበት በአንቀጽ 56/1/ ይደነግጋል። በዚህ ረገድ አንድ ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ቢፈጽም በአንቀጽ 50/ለ/ መሰረት ከብር 10ሺ በማያንስ፣ ከብር 100 ሺ በማይበልጥ መቀጮ እንዲሁም ከ2 አመት በማያንስ፣ከ5 አመት በማይበልጥ እስራት ሲቀጣ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅም በአንቀጽ 56/1/ መሰረት ተመሳሳይ ቅጣት ይጣልበታል ማለት ነው። ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የድርጅት ስራ አስኪያጅ በራሱ በወንጀል ድርጊቱ ምንም አይነት ተሳትፎ ባይኖረውም የድርጅቱ ጥፋት የራሱ እንደሆነ ተቆጥሮ ቅጣት ይጣልበታል። ይህ እንግዲህ ከላይ በዝርዝር የተቀመጠውን ስለሌላ ሰው ወንጀል ሀላፊ መሆን ጽንሰ ሀሳብ የተከተለ ነው። ከዚህ አንጻር የስራ አስኪያጁ ሀላፊነት በህግ ግምት የተወሰደበት በመሆኑ የድርጊትም ሆነ የሀሳብ ክፍሉን ማስረዳት ሳያስፈልግ የድርጅቱ ጥፋተኝነት ከተረጋገጠ ስራ አስኪያጁም ይቀጣል። ይህ የህግ ግምት ተከሳሹ የወንጀል ድርጊቱን እንዳልፈጸመ ማስረጃ የሚያቀርብበት በመሆኑ በማስረጃ ህግ ከሚታወቀው 'the one who claim shall prove it' ከሚለው መሰረታዊ መርህ ልዩ ሁኔታ መሆኑን ልብ ይሏል።

### ስራ አስኪያጅ ማነው?

ስራ አስኪያጅ ማለት በጠቅላላው የድርጅቱን እንቅስቃሴ /የሚመራ/ እና የሚቆጣጠር እንደሆነ እሙን ነው። የንግድ ህጉ አንቀጽ 33 ስራ አስኪያጅን ሲተረጉም ስልጣን ያለው ስራ አስኪያጅ

ማለት በነጋዴው ስም ሆኖ በውክልና እንዲፈርም፣ ስራውን እንዲያካሂድ በግልጽ ወይም በዝምታ ስልጣን የተሰጠው ሰው ሲሆን ስራ አስኪያጁ ከነጋዴው ስራ ጋር ነክነት ያላቸውን ማናቸውንም ግዴታዎቸው ለመፈረም እንዲሁም የሚተላለፉ የንግድ ሰነዶችን ለመፈረም ሙሉ ስልጣን እንዳለው ይቆጠራል፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ በአንቀጽ 56/4/ ስራ አስኪያጅ ማለት፡-

ሀ. የሽርክና ማህበርን በሚመለከት የሽርክና ማህበር አባል ወይም የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ወይም ከሁለቱ ሀላፊነቶች በአንዱ እንደሚሰራ ሆኖ የሚታይ

ለ. ኩባንያን በሚመለከት የኩባያን የስራ መሪ፣ስራ አስኪያጅ ወይም ወይም ማናቸውም ሌላ ሹም ወይም ከነዚህ ሀላፊነቶች በአንዱ እንደሚሰራ ሆኖ የሚታይ

ሐ. የሰዎችን ህብረት በሚመለከት የህብረቱ ስራ አስኪያጅ ወይም በዚሁ ሀላፊነት እደሚሰራ ሆኖ የሚታይ ነው፡፡ በዚህ ትርጓሜ መሰረት ስራ አስኪያጅ ተብሎ በህግ መሰረት የተሾመ ሰው ብቻ ሳይሆን ይህንኑ እንደሚሰራ ሆኖ የሚታይ ሰው ጭምር የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርበታል ማለት ሲሆን በስራ አስኪያጅነት አልተቀጠርኩም ወይም አልተሾምኩም የሚል መከራከሪያ ማቅረብ አይቻልም ማለት ነው፡፡

ይህ ትርጉም ለድርጅት ከተሰጠው ትርጓሜ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ ለተጠቀሱት የሽርክና ማህበር፣ ወይም ኩባንያ፣ ወይም የሰዎች ህብረት ስራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ስራውን የሚያከናውንበት የሽርክና ማህበር ወይም ኩባንያ ወይም የሰዎች ህብረት ያለ ደረሰኝ ግብይት አከናውኖ እንደሆነ ስራ አስኪያጁም የወንጀል ሀላፊነት እንደሚኖርበት የተቀመጠ ነው ማለት ነው፡፡

በዚህ ረገድ የሚስተዋለው ተግባራዊ ችግር ከላይ እንደተመለከትነው በግል ባለሀብትነት የሚተዳደሩ የንግድ መደብሮችም 'ድርጅት' የሚለውን ትርጓሜ ያሟላሉ ተበሎ ስለሚታሰብ የመደብሮቹ ባለቤቶች ወይም መደብሩ በስማቸው ያሉ ሰዎች ወይም ወኪሎቻቸው እንደ ስራ አስኪያጅ ተቆጥረው የወንጀል ቅጣት ሲተላለፍባቸው ማየት የተለመደ ጉዳይ ነው፡፡በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎቱ የግል ባለሃብቱ/ድርጅቱ በስሙ የተመዘገበ ሰው/ የጥፋተኝነት የተወሰነበት የወንጀል ድርጊቱ ቀጥተኛ ተሳትፎ ስለነበረው ሳይሆን የድርጅቱ ስራ

አስኪያጅ ሆኖ ስለሚቆጠር ድርጊቱ እንዳይፈጸም ብርቱ ጥንቃቄ ባለማድረጉ ነው የሚል ተደጋጋሚ ውሳኔ ተሰጥቷል።[31]

በመሰረቱ በግል ባለሃብትነት ስለሚተዳደሩ የንግድ ድርጅቶች ጥቅል የሆነ ድንጋጌ ከማስቀመጥ ባለፈ ዝርዝር ሁኔታ በንግድ ህጉ አልተመለከተም። ይህውም የግል ባለሃብት ስራ አስኪጅ ሊቀጥር እንደሚችል በአንቀጽ 33 የተገለጸ ቢሆንም ስራ አስኪያጅ ባይቀጥር እራሱ እንደ ስራ አስኪያጅ እንደሚቆጠር በህግ የተያዘ ግምት የለም። የግድ ስራ አስኪያጅ እንዲኖራቸው ከሚያስፈልጉ የአክስዮን ማህበር እና ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ውጪ ያሉ የሽርክና ማህበራትን በተመለከተ ግን የሽርክና ማህበሩ ስራ አስኪያጅ ያልቀጠረ እንደሆነ አባላቱ እንደ ስራ አስኪያጅ እንደሚቆጠሩ ይደነግጋል።[32] በመሆኑም የሽርክና ማህበር አባላቱ እንደስራ አስኪያጅ ተቆጥረው የንግድ ድርጅቱ ያለደረሰኝ ግብይት የፈጸመ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 56/1/ መሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ ማለት ነው። የግል ባለሃብትን ግን እንደ ስራ አስኪያጅ የሚቆጠርበት የህግ መሰረት የለም። ለዚህም ይመስላል አዋጁ በትርጓሜው ስራ አስኪጅን ከላይ የተጠቀሱትን የሽርክና ማህበራትን የሚያስተዳድሩትን ብቻ እንዲመለከት ተደርጎ የተቀረጸው። ከዚህ አንጻር የግል ባለሀብቶች እንደ ስራ አስኪያጅ ተቆጥረው በአዋጁ አንቀጽ 56/1/ መሰረት የወንጀል ቅጣት እንዲጣልባቸው የህግ መሰረት የሌለ በመሆኑ የግል ባለሃቱን ተጠያቂነት መሰረት ለማስያዝ የህግ ማእቀፉን ማሻሻል የግድ ይላል።

የካምፓኒ ወይም የሽርክና ማህበር ወይም የሰዎች ህብረት ስራ አስኪያጁ ከአስተዳደራዊውም ሆነ ከወንጀሉ ቅጣት ነጻ የሚሆነው በአንቀጽ 56/3/ እንደተነገረው፡-

ሀ. ጥፋቱ የተፈጸመው ግለሰቡ ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ከሆነ፡

ለ. አንድ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈጸም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን ተገቢውን ትጋት እና የአሰራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ግለሰቡ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ ነው።

ከዚህ አንጻር የስራአስኪያጁ ጥፋተኝነት በህግ ግምት የተወሰደበት በመሆኑ ተከሳሹ ከላይ የተቀመጡትን ልዩ ሁኔታዎች መኖራቸውን ማስረዳት ከቻለ ብቻ ነው ከቅጣት ነጻ ሊሆን

[31] የግርጌ ማስታወሻ ቁ.13፣ የፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ/ 86597 ቅጽ 15 በ21/1/2006 ዓ.ም የተወሰነ ገጽ271

[32] ተራ ሽርክናን በተመለከተ አንቀጽ 236፣ የእሽሙር ማህበርን በተመለከተ አንቀጽ275/2/፣ የህብረት ሽርክናን በሚመለከት አንቀጽ 287/2/ ሁለት አይነት ሀላፊነት ያለበት የሽርክና ማህበርን በሚመለከት አንቀጽ 300

የሚችለው፡፡ ሆኖም እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ በህግ የተደነገጉ ካለመሆናቸውም በላይ በአማራጭ የቀረቡ ይሁኑ ወይም በአንድነት ግልጽ አይደለም፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በድንጋጌው ላይ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች በአንድ ላይ ተሟልተው ሲገኙ ነው ወይስ በተናጥል የሚለውን መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ ድርጊቱ የተፈጸመው ግለሰቡ ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ነው ሲል ምን ማለት ነው? በዚህ ረገድ በአንዳንድ ተከሳሾች የሚነሳ መከራከሪያ አለ ይነውም ወንጀሉ በተፈጸመ ጊዜ በወቅቱ አልነበርኩም በመሆኑም ወንጀሉ የተፈጸመው ሳላውቅ እና ሳልስማማበት ስለሆነ ጥፋተኛ ልባል አይገባም የሚል፡፡[33]

ከዚህ አንጻር ወንጀሉ ሲፈጸም በቦታው አለመኖር ብቻ ወንጀሉን አልተስማማበትም ወይም አላወቀም ለማለት የሚቻል መሆን አለመሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በሰራተኞች ጥፋት ድርጅቶች በወንጀል ተጠያቂ የሚደረጉት ሰራተኛው ጥፋቱን የፈጸመው የድርጅቱን ስራ ሲከናውን እና ለድርጅቱ ጥቅም መሆኑ ሲረጋገጥ መሆኑን ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 34/1/ ዝርዝር ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር የስራ አስኪያጁም ተጠያቂነት የሚመነጨው ድርጅቱ በራሱ ህልው ባለመሆኑ ስራዎችን የሚሰራው በተወካዮቹ አማካኝነት ስለሆነ እና ስራ አስኪያጁ የደርጅቱ ‘ጭንቅላት’ በመሆኑ ሰራተኞች የሚሰሩትን ስራ በአግባቡ መቆጣጠር ሲገባው ይህንን ባለማድረጉ የተነሳ ድርጊቱ እንዲፈጸም ፍላጎት እንዳለው የሚቆጠር በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ስራ አስኪያጁ ያለደረሰኝ ግብይት በሚፈጸምበት ወቅት በቦታው ባይኖርም እንኳ ሰራተኞቹ ህገ ወጥ ድርጊቱን ሊፈጽሙ የሚችሉበትን አጋጣሚ አመቻችቶ ሊሆን ስለሚችል በወቅቱ በቦታው አለመኖሩ ብቻ ድርጊቱን ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ሊያስብለው አይችልም፡፡ ሁሌም ቢሆን ስራ አስኪያጁ እራሱ በሽያጩ ተሳታፊ ካልሆነ በቀር ያለደረሰኝ ግብይት የሚፈጸመው በሽያጭ ሰራተኞች እና ገንዘብ ያገሮች በመሆኑ የስራ አስኪያጁ በቦታው መኖር ወይም አለመኖር ወንጀሉን ስለማወቅ አለማወቁ ልዩነት አያመጣም፡፡ ይልቁንም ስራ አስኪያጁ ወንጀሉ እንዳይፈጸም ብርቱ ጥረት ያደረገ እንደሆነ በቦታው ኖረም አልኖረ ወንጀሉ እንዲፈጸም ስምምነት የለውም የሚል ግምት ተወስዶ ከቅጣት ነጻ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ወንጀሉን ሳያውቅ እና ሳይስማማበት እንዲሁም ወንጀሉን ለመከላከል ብርቱ ጥንቃቄ ያደረገ የሚለው አገለላጸ ተመጋጋቢ እና ተደጋጋፊ በመሆኑ በአንድት ተሟልቶ ሲገኝ ነው ከጥፋተኛነት ነጻ ሊባል የሚገባው፡፡

[33] የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 24

ወንጀሉን አለማወቅ ወይም ስምምነት የለውም ለማለት ደግሞ ስራ አስኪያጁ አንድ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈጸም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን ተገቢውን ትጋት እና የአሰራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ ነው።

ለመሆኑ አንድ ስራ አስኪያጅ ከሰራተኞቹ አንዱ ወይም ብዙዎቹ ያለደረሰኝ ግብይት የማካሄድ ድርጊትን እንዳይፈጽሙ ለመከላከል አንድ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው /reasonable person/ የጥፋቱን መፈጸም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ጥንቃቄዎች ምንድናቸው? አንድ ሰው የፈጸመው ድርጊት በአንድ ሌላ ጠንቃቃ ሰው የሚፈጽመው መሆን አለመሆኑ የዚያን ሰው የፍትሀብሔራዊም ሆነ ወንጀል ሀላፊነት የሚወስን ጉዳይ መሆኑን የህግ ሰርዐታችን የደነገገው ጉዳይ ነው። ከዚህ አንጻር reasonable person standard በአብዛኛው የቸልተኝነት መኖር አለመኖር ለማረጋጥ የምንጠቀምበት ዘዴ ሲሆን ፍትሐብሄራዊ ግንኙነትን በተመለከተ አንድ ሰው አንድ እንዳይፈጸም የሚፈለግን ድርጊት ለመከላከል ሊወስድ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች አብዛኛው ሰው ሊወስዳቸው የሚችሉ ጥንቃቄዎች በመሆናቸው የፈጻሚውን ልዩ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ሳይገባ አብዛኛው የማህበረሰቡ ክፍል የሚፈጽማቸው ጥንቃቄዎች ናቸው።[34] በሌላ በኩል በወንጀል ህጉ አንቀጽ 59/2/ የቸልተኝነት መለኪያ የአጥፊውን እድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የአካባቢ ሁኔታ መሰረት ማድረግ እንደሚገባው ይደነግጋል።

ከዚህ አንጻር የአንድ የንግድ ድርጅት ስራ አስኪያጅ ሊያደርገው የሚገባው ብርቱ ጥንቃቄ አንድ በእሱ ሁኔታ ያለ ሌላ ነጋዴ ሊያደርገው የሚገባውን ነው ማለት ነው። በመሰረቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁም ሆነ አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች አንድ ነጋዴ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን በመተላለፍ ጥፋቶች እንዳይፈጸሙ ሊወስዷቸው የሚገቡ ቅድመ ጥንቃቄዎች ምን ምን እንደሆኑ የገለጹት ነገር የለም። ይልቁንም ክርክር በተነሳ ጊዜ ፍርድቤቶች እንደነገሩ ሁኔታ እየመዘኑ ውሳኔ እንዲሰጡ የተተወላቸው ነው። በዚህ ረገድ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው ያለደረሰኝ ግብይት እንዳይፈጸም ለመከላከል ሊወስዳቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎች ሰራተኞቹ ያለደረሰኝ ግብይት እንዳይፈጽሙ

[34] አንድ ሰው መልካም ጠባይን ተቃዋሚ በሆነ አይነት የማይገባውን ስራ ሰርቷል ወይም የሚገባውን ሥራ ሳይሰራ ቀርቷል ለማለት ትክክለኛ አዕምሮ ባለው ሰው አሰራር ሊመዘን እንደሚገባ የጥፋት አድራጊው ግላዊ ሁኔታ፣ እድሜም ሆነ የአዕምሮ ሁኔታ ከግምት ውስጥ የማይገባ መሆኑን የፍትሐብሄር ህጉ በአንቀጽ 2030 ደንግጓል

ማስጠንቀቂያ ከመስጠት ጀምሮ፣ ደረሰኝ ሳይቀበሉ ገንዘብ እንዳይከፍሉ የሚል ማሳሰቢያ ግልጽ በሆነ ቦታ መለጠፍ፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያውን በቀጥታ ከደንበኛው ጋር በማገናኘት ደረሰኙ እንዲቆረጥ ማድረግ፣የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያቤት እውቅና ከሰጣቸው የቅድመ ጥንቀቁ እርምጃዎች የተወሰኑት ናቸው።[35] ሆኖም የጥንቃቁ እርምጃዎቹ በነዚህ ጉዳዮች ላይ ብቻ ተወስነው የሚቀሩ ካመሆናቸውም በላይ የመተግበር ሁኔታቸውም በእያንዳንዱ ነጋዴ የንቃተ ህሊና መጠን እንዲሁም የስራ ልምድ ላይ የተመሰረተ ይሆናል ማት ነው። በመሆኑም ፍርድቤቶች ጉዳዩን ሲመረምሩ እንደ እያንዳንዱ ነጋዴ ግላዊ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ጉዳዩን መመልከት የሚገባ እንደሆነ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 59/2/ ታሳቢ ያደረገ ውሳኔ መስጠት ያስፈልጋል።

## 2.4. የወኪል ተጠያቂነት

ያለደረሰኝ ግብይት መፈጸምን በተመለከተ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ መሻሻሉን ተከትሎ በርከት ያሉ ክሶች በፍርድቤት ሲስተናገዱ ይስተዋላል። ታዲያ ያለደረሰኝ ግብይት ሲከናወን ድርጊቱን ፈጸመው የሽያጭ ሰራተኛ፣ የድርጅቱ ባለቤት፣ ስራአስኪያጅ፣ የባለቤቱ ወኪል፣ እንዲሁም ድርጅቱ በአንድነት የወንጀል ክስ ሲቀርብባቸው ይስተዋላል። የድርጅቱ ባለቤት ወኪል በወንጀል ድርጊቱ ሊጠየቅበት የሚችልበት የህግ አግባብ አለ የሚለው አሁንም ለክርክር በር የሚከፍት ብሎም ወጥ የሆነ ግንዛቤ የሌለ መሆኑ ይታያል። ለምሳሌ እነ ታደለ አለማየሁ አራት ሰዎች በተከሰሱበት የወንጀል መዝገብ በአንደኛ ተከሳሽ ባለሃብትነት ተመዝግቦ የሚገኝ ሆቴል ያለደረሰኝ ሽያጭ በመፈጸሙ ባለቤቱም፣ ተወካዩም አስተናጋጁ እንዲሁም ገንዘብ ተቀባዩ የወንጀል ክስ ቀርቦባቸው ሁሉም ተከሳሾች የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል።[36]

በተመሳሳይ በከሳሽ ዐ/ህግ እና ተከሳሾች እነ ያህያ ሀሚድ አራት ሰዎች አንደኛ ተከሳሽ የሆነው ያህያ ሀሚድ በውክልና በሚያስተዳድረው በግል ባለሀብትነት በተመዘገበ የህንጻ መሳሪያ መሸጫ መደብር ከ2-4 የተጠቀሱ ተከሳሾች ያለደረሰኝ ግብይት በመፈጸማቸው አንደኛ ተከሳሽ ያለበትን የመቆጣጠር እና የመከታተል ሀላፊነት አልተወጣም በሚል በምእ/ት/ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን አንቀጽ 50/ለ/1/ እንደተሻሻለው ተጠቅሶ ክስ የቀረበበት ሲሆን

[35] በገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የወጣው መመሪያ ቁጥር 46/2000 በአንቀጽ 26 የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ የሆነ ሰው መሳሪያው በተተከለበት አካባቢ ደረሰኝ ሳይቀበሉ አይክፈሉ የሚል፣ የድርጅቱን የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር፣ የየመሳሪያ ተጠቃሚውን ስም፣ መሳሪያው ቢበላሽ በእጅ የተዘጋጀ ደረሰኝ የሚያዘጋጅ መሆኑን የሚገልጽ ማሳሰቢያ እንዲለጥፍ የሚገደድ መሆኑን ይደነግጋል። ሆኖም ይህንን ማድረጉ ብቻ ስራ አስኪያጁን ከተጠያቂነት ሊያድነው ይችላል ወይ የሚለው እንደየጉዳዩ የሚወሰን ይሆናል።

[36] የፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ፋ/ቁ120821 በአመልካች ዐ/ሕግ እና ተጠሪዎች እነ ታደለ አለማየሁ ሁለት ሰዎች

ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ወንጀሉ በተፈጸመ ጊዜ በቦታው አልነበረም በሚል በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 149/2/ መሰረት ነጻ ብሎታል።[37] ሆኖም የክፍሉ ዐቃቤ-ሕግ በፍርድቤቱ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘቱ ይግባኙን ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል። የቅሬታ መነሻውም በንግድ ህጉ አንቀጽ 33/1/ የንግድ ወኪል እንደ ስራ አስኪያጅ ስለሚቆጠር እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ ደግሞ ስራ አስኪያጅ ድርጅቱ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ቅጣት የሚጣልበት እንደሆነ የሚደነግግ በመሆኑ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሊባል ይገባል የሚል ነው። ከዚህ ክርክር የምንረዳው የትኛውም የንግድ መደብር ባለቤትም ሆነ ተወካይ እንደ ስራ አስኪያጅ የሚታይ በመሆኑ በአንቀጽ 56 መሰረት ቅጣት ሊጣልበት ይገባል የሚል መደምደሚያ የያዘ ነው። ሆኖም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ድርጅቱም ሆነ ስራ አስኪያጁ ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት ሊጣልባቸው የሚችለው የንግድ መደብሩ 'ድርጅት' የሚለውን ትርጓሜ ሲያሟላ ብቻ ነው።

ለመሆኑ ተወካዩ የንግድ ድርጅቱ/መደብሩ/ ወንጀል ፈጽሞ ቢገኝ የሚጠየቀው በምን ሁኔታ ነው? ወካዩ በቦታው ሆኖ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ወይስ ወካዩ ሳይኖር ተወካዩ በቦታው ተተክቶ በሚሰራበት እንዲሁም ሁለቱም ወካዩም ተወካዩም በአንድ ድርጊት ሊጠየቁ የሚችሉበት የህግ አግባብ ይኖራል?

ውክልና ተወካይ የተባለ አንድ ሰው ወካይ ለተባለው ሰው እንደራሴ ሆኖ አንድ ወይም ብዙ ህጋዊ ስራዎች በወካዩ ስም ለማከናወን ግዴታ የሚገባበት ውል እንደሆነ የፍትሐብሄር ህጉ አንቀጽ 2199 ይነግረናል። እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ በአንቀጽ 2/2/ ወኪል ማለት በሌላ ሰው ስም እና ትእዛዝ የሚሰራ ማናቸውም ሰው በሚል ይተረጉመዋል።

ወኪል እና የንግድ ወኪል የተለያዩ ነገሮች እንደሆኑ ከንግድ ህጉ አቀማመጥ መረዳት ይቻላል። በዚህም መሰረት በአንቀጽ 31 ከነጋዴው ሰራተኞች አንዱ በዝምታ ወይም በግልጽ ሊወከል እንደሚችል ሲያስቀምጥ በሌላ በኩል የንግድ ወኪል ማለት ከነጋዴው ጋር እንዲሰራ በውል የተቀጠረ ሳይሆን ራሱን የቻለ ስራ ሊሰራ በተወሰነ ስፍራ ሆኖ ሁልጊዜ የነጋዴው እንደራሴ ሊሆን በነጋዴው ስምና ምትክ እንዲሰራ ወይም ውል እንዲዋዋል ውክልና የተሰጠው ሰው ወይም ንግድ ማህበር ነው/አንቀጽ 44/። ከዚህ አንጻር በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ በወንጀል ሊጠየቁ የሚችሉ ወኪሎች የትኞቹ ናቸው ሲባል በአንቀጽ 31 ላይ ያሉ ወኪሎችን ሳይሆን በ አንቀጽ 44 ላይ ያሉትን እንደሆነ ለድርጅት እና ሰው ከተሰጠው ትርጓሜ ለመረዳት ይቻላል።

[37] የም/ዕ/ኅ/ዞን ከ/ፍ/ት ፋ/ቁ/ 49998 በከሰሸ ዐ/ሕግ እና ተከሳሾች እነ ያህያ ሀሚድ አራት ሰዎች

ከላይ እንደተቀመጠው ሰው እና ድርጅት ሲተረጎሙ የንግድ ወኪልን እንደሚጨምሩ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 50/ለ/1/ ማንኛውም ሰው ያለደረሰኝ ግብይት የፈጸመ እንደሆነ ቅጣት እንደሚጣልበት የደነገገ በመሆኑ ማንኛውም የንግድ ወኪል ያለደረሰኝ ግብይት የፈጸመ እንደሆነ የንግድ ወኪሉ በወንጀሉ ተጠያቂ ይሆናል ማለት ነው፡፡

በንግድ ህጉ አንቀጽ 31 እንዲሁም በፍትሐብሄር ህጉ አንቀጽ 2199 እና ተከታዮቹ መሰረት ለሚወከሉ ወኪሎችን በተመለከተ ግን የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ ስለተጠያቂነታቸው የሚለው ነገር የለም፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ በአንቀጽ 24 አንድ ወኪል ወካይ በሆነው ሰው ስም እና ትእዛዝ እቃዎች የማቅረብ ወይም አገልግሎት የመስጠት ስራ ያከናወነ እንደሆነ በወካዩ የተከናወነ ስራ እንደሆነ ይቆጠራል በመሆኑም ሊከፈል ለሚገባው ታክስ ወካዩም ሆነ ወኪሉ ሀላፊ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ ከጠቅላላው የውክልና ህግ መርህ የመነጨ ሲሆን ወኪሉ በውክልና ሰ,ስልጣኑ የፈጸማቸው ተግባራ በወካዩ እንደተፈጸሙ የሚቆጠር በመሆኑ በዚህ ረገድ መቃወሚያ ማንሳት እንደማይቻል የሚያስገነዝብ ሲሆን በተጨማሪም ወካዩ እና ተወካዩ በአንድት ሊከፈል ለሚገባው ታክስ ፍትሐብሄራዊ ተጠያቂነት እንደሚኖርባቸው ሀላፊነት የሚጥል እንጂ በወካዩ እና ተወካዩ ላይ ስለሚኖረው የወንጀል ተጠያቂነት የሚደነግግ አይደለም፡፡ የንግድ ህጉ አንቀጽ 33/1/ም ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡ ይኸውም ስራ አስኪያጁ በባለሀብቱ ስም እንዲፈርም የሚወከል በመሆኑ በስራ አስኪያጁ የተሰሩ ስራዎች የባለሀብቱ ስራዎች እንደሆኑ የሚቆጠሩ በመሆናቸው በዚህ ረገድ መቃወሚያ ማቅረብ እንደማይቻል የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ግን የወንጀል ሀላፊነትን የሚያመለክት አይደለም የግል ባለሀብቱም ሆነ ተወካዩ ተጠያቂ ይሆኑ ዘንድ በህግ በግልጽ መደንገግ ይኖርበርበታል፡፡

በኢትዮጵያ በንግድ ስራ የሚተዳደሩ የግል ባለሃብቶች ተግባሮቻቸውን ሌሎች ሰዎች እንዲያከናውኑላቸው ውክልና መስጠት የተለመደ አሰራር ነው፡፡ የውክልና ስልጣኑም ከተራ ጉዳይ ከማስፈጸም አንስቶ የንግድ መደብሮቻቸውን እስከመሸጥ፣ አስይዞ መበደር፣ በማናቸውም ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን እስከማስተለለፍ የሚደርስ ልዩ ውክልና ስልጣን ሊሆን ይችላል፡፡ በተለይም በንግዱ አለም የቆዩ ወላጆች እና ቤተሰቦች እድሜያቸው ሲገፋ እና ስራውን በአግባቡ መምራት ሳይችሉ ለልጆቻቸው አሊያም ዘመዶቻቸው ውክልና ሰጥተው ስራውን ማሰራት የተለመደ ነው፡፡ የውክልናው ይዘት ሲታይ ተመዘጋቢውን የንግድ መደብር ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር የሚል ሊሆን ይችላል ወይም በደፈናው የድርጅቱን ጉዳይ ለማስፈጸም የሚል፡፡

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ ከላይ እንደተገለጸው ድርጅቱን፣ስራ አስኪያጁን እንዲሁም በወንጀሉ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ አነሳሽነት እንዲሁም አባሪነት የሚሳተፉ ሰዎች ስለሚኖርባቸው ተጠያቂነት የሚደነግጉ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የወኪሎችን በተመለከተ ግን የተባለ ነገር የለም። በመሆኑም ልክ እንደግል ባለሀብቱ ተወካዩ በወንጀል ድርጊቱ መሳተፉ ሲረጋጥ ብቻ ነው የወንጀል ተጠያቂነት ሊኖርበት የሚገባው። ከላይ በዝርዝር እደተመለከትነው ስለሌላ ሰው የሚኖር የወንጀል ሀላፊነት በግልጽ በህጉ መደንገግ ይኖርበታል። በተለይም ከላይ በተገለጸው አይነት በተጨባጭ የንግድ ድርጅቱን የሚያስተዳድረው ማንኛው ነው ተወካዩ ወይስ ባለቤቱ የሚለው ሳይመረመር የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠት ተገቢነት የለውም።

በከሳሽ ዐቃቤ ህግ በኩል በአብዛኛው የሚነሳው መከራከሪያ የግል ባለሀብቶችም ሆኑ ተወካዮቻቸው የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ በመሆናቸው በአንቀጽ 56/1/ መሰረት ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል የሚል ነው።[38] ሆኖም ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው በአዋጁ ድርጅት ተብለው የተለዩ የንግድ ተቋማትን ስራ አስኪያጆች[39] ውጪ ያሉትን የሚመለከት ባለመሆኑ የህግ መሰረት የለውም ማለት ነው።

በተለይም በአንድ ድርጊት ባለሀብቱን ተወካዩንም ጥፋተኛ ማድረግ እና ቅጣት መጣል የወንጀል ህጉን መርህ የሚጣረስ ከመሆኑም በላይ በነጋዴው ማህበረሰብ ላይ የሚፈጥረው ኢኮኖሚያዊ ጫና ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም። ምክንያቱም አዋጁን በመተላለፍ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ከእስራት ቅጣት በተጨማሪ ከፍ ያለ የገንዘብ መቀጮም የሚያስከትሉ በመሆናቸው ባለሀብቱንም ተወካዩንም በአንድ ጉዳይ ተጠያቂ ማድረግ የድርጅቱን ገቢ ማራቆት ነው። በመሰረቱ ስለሌላ ሰው የሚኖር በህግ የተፈቀደ ተጠያቂነት ሳይጨምር በአንድ ድርጊት ከአንድ ሰዎች በላይ የሚጠየቁት እያንዳንዳቸው የወንጀል ተሳትፎ ሲኖራቸው ነው። በዚህ ረገድ ቅጣትም የሚሰጠው እንደ አጥፊው የወንጀል ተሳትፎ መጠን በመሆኑ በተደረገው ድርጊት የባለ ሀብቱም ሆነ የወኪሉ የተሳትፎ መጠን ሊረጋገጥ ይገባል።

[38] የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 36

[39] አንቀጽ 56/4/ ስራ አስኪያጅን ትርጉም የሰጠ ሲሆን ትርጉሙም የግል ባለሃብትን እንዲሁም ተወካዩን የማይመለከት መሆኑን ልብ ይሏል።

## 2.5. በአባሪነት ስለሚጠየቁ ሰዎች

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን በመተላለፍ ያለደረሰኝ ግብይት ማከናወንን በተመለከተ ከዋና ወንጀል አድራጊዎቹ በተጨማሪ በአባሪዎች እና አነሳሾች ላይ በዋና ወንጀል አድራጊዎች ልክ ቅጣት የሚጣልባቸው መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 55 ይደነግጋል። ከላይ እንተመለከትነው የወንጀል ተሳትፎ አይነቶች በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ አነሳሽነት እንዲሁም አባሪነት የሚከፈሉ ናቸው።

እነዚህ የተሳትፎ አይነቶች የየራሳቸው መገለጫ ባህሪያት ያሏቸው ሲሆን ዋና ወንጀል አድራጊነት በወንጀሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ያደረገ፣ ወንጀሉ እንዲፈጸም በመላ ሃሳቡ እና ፍላጎት ያለው ነው። አባሪነት በሌላ በኩል ዋና ወንጀል አድራጊው ወንጀል ከማድረጉም በፊትም ሆነ ወንጀል በሚያደርግበት ጊዜ ወራ በማቀበል፣ በመምከር ወንጀል የሚያደርግበትን ዘዴ ወይም መሳሪያ በማቀበል ወይም ግዙፋዊ እርዳታ በመስጠት አስቦ የረዳ ሰው በአባሪነት ይጠየቃል።[40]

በአንድ የንግድ መደብር ያለደረሰኝ ግብይት በሚያከናውንበት ጊዜ በአብዛኛው በግብይቱ የሚሳተፉት የድርጅቱ ሰራተኞች ማለትም የሽያጭ ሰራተኛ፣ ገንዘብ ያዥ እና አስተናጋጅ የመሳሰሉት ሰራተኞች ሲሆኑ ድርጅቱ እንዲሁም የግል ባለሀብቱ በዋና የወንጀል አድራጊነት ሲከሰሱ ሰራተኞች ደግሞ በአንቀጽ 55 መሰረት በአባሪነት ሲከሰሱ ይታያል። ምክንያቱም ሰራተኞች ምንም እንኳ ደረሰኝ መስጠት እየተገባቸው ባለመስጠት በድርጊቱ ቀጥተኛ ተሳትፎ ቢኖራቸውም ድንጋጌው የሚጠይቀውን ***የተመዘገበ ሰው*** መስፈርት የሚያሟሉ ባለመሆናቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም። በመሆኑም በድርጅት ሰራተኝነት የተሰማሩ ሰዎች የንግድ ድርጅቱ ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት አከናውኖ እንደሆነ ሊጠየቁ የሚችሉት በአባሪነት ነው ማለት ነው። ሆኖም ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚስተዋለው ተግባራዊ ችግር የትኞቹ የድርጅቱ ሰራተኞች ናቸው ሊጠየቁ የሚገባው የሚለው ነው። በተለይም የድርጅቱ ሰራተኞች መሆናቸው ያልተረጋገጠ ሰዎች በዚህ ተግባር ተሳትፈው ቢገኙ ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል ወይ የሚለው አከራካሪ እንደሆነ ከመዛግብት መረዳት ይቻላል። ለአብነት ያህል እነ ኢሳ ጋሻው 3 ሰዎች በተከሰሱበት መዝገብ 2ኛ እና 3ኛ ተከሰሾች የድርጅቱ የሽያጭ ሰራተኞች ሲሆኑ ያለደረሰኝ ግብይት ሲፈጸም ደረሰኝ ቆርጠው ባለመስጠታቸው ክስ

[40] አዋጅ ቁጥር 434/1996፣ የኢፌድሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 37

የቀረበባቸው ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ካደመጠ በኋላ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የድርጅቱ ሠራተኞች መሆናቸው አልተረጋገጠም በሚል በነጻ አሰናብቷቸዋል።[41]

በዚህ ረገድ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም ምክንያቱም የአዋጁ አንቀጽ 55 ማናቸውም ሰው የድርጅቱ ሠራተኛ ሆነም አልሆነ በአዋጁ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንዲጣሱ የረዳ፣ ያበረታታ፣ ያነሳሳ፣ ወይም በምስጢር የተባበረ እንደሆነ እንደዋነኛው ጥፋተኛ ተቆጥሮ ቅጣት እንደሚጣልበት የደነገገ በመሆኑ ያለ ደረሰኝ ግብይት እንዲፈጸም የረዳ ማንኛውም ሰው ተጠያቂነት ይኖርበታል ማለት ነው። በመሰረቱ ድርጅቶች ሁሌም የሽያጭ ሠራተኛ ቀጥረው ላያሰሩ ይችላሉ ይልቁንም አብዛኛው ንግድ በቤተሰብ አባላት የሚከናወን በመሆኑ ያለ ደረሰኝ ግብይት ማከናወን ተግባሩም በቤተሰብ አባላት ሊፈጸም ይችላል። በመሆኑም ማንኛውም ሰው ተቀጣሪ ሆነም አልሆነ ወንጀሉ በሚፈጸምበት ጊዜ አስቦ ግዙፋዊ እርዳታ ያደረገ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 37 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ አንቀጽ 55 መሰረት ተጠያቂ ሊሆን ይገባል።

ሌላው በተግባር የሚስተዋለው ችግር በአንድ የንግድ መደብር ውስጥ ግብይት ያለደረሰኝ ሲከናወን ተጠያቂ ሊሆን የሚገባው ሰው የትኛው ነው የሚለው ነው። ይኸውም በአንድ ድርጊት ላይ የሽያጭ ሠራተኛ፣ አስተናጋጅ፣ ገንዘብ ያዥ እቃ አቀባይ እና ማንኛውም በንግድ ድርጅቱ ውስጥ ያለ ሰው በወንጀል መክሰስ የተለመደ ነው። ለምሳሌ እነ ሀሚድ አብዱራህማን ሁለት ሰዎች በተከሰሱበት መዝገብ የምዕ/ጎ/ገቢዎች ዐ/ሕግ ክስ ሲመሰርት 1ኛ ተከሳሽ ግብይቱን ያለደረሰኝ ሲያከናውን ሁለተኛ ተከሳሽ የተሸጠውን እቃ ከመደርደሪያ አንስቶ ለገዢ የሰጠ በመሆኑ አንደኛ ተከሳሽ ያለደረሰኝ ግብይት እንዲያከናውን ተባብሯል በሚል የአዋጁን አንቀጽ 55 እና 50/ለ/1/ እንደተሻሻለው ጠቅሶ ያቀረበ ሲሆን ፍርድቤቱም የዐ/ህግ ማስረጃ ካደመጠ በኋላ የሁለተኛ ተከሳሽ አድራጎት በህግ ክልከላ የተጣለበት ባለመሆኑ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 23/2/ የሕግ፣ የሞራል እንዲሁም የድርጊት ፍሬ-ነገሮች በአንድነት ተሟልተው የሚገኙ ባለመሆናቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 141 መሰረት መከላከል ሳያስፈልገው በነጻ እንዲሰናበት ወስኗል።[42] በተመሳሳይ እነ በዛብህ ስሜነህ 2 ሰዎች በተከሰሱበት መዝገብ አንደኛ ተከሳሽ ያለደረሰኝ ግብይት ሲያከናውን ሁለተኛ ተከሳሽ የተሸጠውን እቃ ከመጋዘን አምጥቶ ለገዢ

[41] የምዕ/ጎ/ዞ/ከ/ፍ/ቤ/የፋ/ቁ/ 49997 በከሳሽ ዐ/ሕግ እና ተከሳሾች እነ ኢሳ ጋሻው 2 ሰዎች በቀን 15/08/05 ዓ.ም የተወሰነ

[42] የምዕ/ጎ/ዞ/ከ/ፍ/ፋ.ይ/ቁ 50000 በከሳሽ ዐ//ሕግ ተከሳሽ እነ በዛብህ ስሜነህ ሁለት ሰዎች በቀን 20/06/2006 ዓ.ም የተወሰነ

የሰጠ በመሆኑ የመርዳት/መተባበር/ ድርጊት ፈጽሟል በሚል ክስ የቀረበበት ቢሆንም ፍርድቤቱ ተከሳሹ የሽያጭ ሰራተኛ ባለመሆኑ የተሸጠውን እቃ አንስቶ መስጠቱ ብቻ ተጠያቂ ሊያደርገው አይገባም የሚል ውሳኔ ሰጥቷል።[43]

አንድ ሰው በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚገባው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 23 መሰረት ሁሉም የህግ፣ የሞራል እና የድርጊት ፍሬነገሮች ተሟልተው ሲገኙ እንደሆነ በተደጋጋሚ የተነሳ ጉዳይ ነው። ከዚህ አንጻር በአንድ የወንጀል ድርጊት ላይ የሰዎችን የተሳትፎ መጠን እዲሁም ያለባቸውን ሀላፊነት ከግምት ውስጥ መግባት የሚገባቸው መሆኑ ግልጽ ነው። በአንድ የንግድ ድርጅት ውስጥ ብዙ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ የታወቀ ሆኖ ሳለ ያለደረሰኝ ግብይት በሚፈጸምበት ጊዜ በቦታው የነበሩ ሰራተኞችን ሁሉ በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ ይህንን መሰረታዊ የወንጀል መርህ መጣረስ ነው። ከላይ በተጠቀሱት ሁለት መዛግብት ሁለተኛ ተከሳሽ ተብለው የተጠቀሱ ሰዎች የፈጸሙት ድርጊት ያለ ደረሰኝ የተሸጠውን እቃ ለገዢዎች ማቀበል ነው። ከዚህ ውጪ እቃው ያለደረሰኝ እንዲሸጥ በቃልም በድርጊትም የፈጸሙት መተባበር እንዳለ ዐቃቤህግ ማስረዳት አልቻለም። እቃውን ያለደረሰኝ መሸጥ አንድ ድርጊት የተሸጠውን እቃ ደግሞ ለገዢ ማስረከብ ሌላ ድርጊት ነው እቃ አቀባዩ ሻጩን በደረሰኝ እንዲሸጥ አለማድረግ የሚችልበት አጋጣሚም አይኖርም እንዲሁም እቃው በደረሰኝ ይሸጥ አይሸጥ የሚያውቅበት መንገድ አይኖርም ይህ ሁኔታ እስካልተረጋገጠ ድረስ። ባጠቃላይ ያለደረሰኝ በሚካሄድ ግብይት ላይ ከድርጅት ስራ አስኪያጅ በስተቀር የሌሎች ሰዎች የወንጀል ተጠያቂነት በተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በልዩ ሁኔታ ግን እንደ ድርጅቱ ትልቅነት እና የስራ ልምድ ንብረት አስረካቢዎች ደረሰኝ መቆረጡን ሳያረጋግጡ ንብረት እዳያስረክቡ በድርጅቱ የውስጥ መመሪያ ግዴታ ተጥሎባቸው እንደሆነ ይህንን ግዴታ ወደ ጎን በመተው ያለ ደረሰኝ ርክክብ የሚፈጽሙ እንደሆነ ተጠያቂ መሆናቸው እንደተጠበቀ ነው።

[43] የምዕ/ን/ዞ/ከፍ/ፍ/ፋይ/ቁ/ 52518 በከሳሽ ዐ/ሕግ እና ተከሳሾች እነ ሀሚድ አብዱራህማን ሁለት ሰዎች

## 3. የማጠቃለያ ሀሳብ

ግብርን በአግባቡ መክፈል የማንኛውም ዜጋ ግዴታ እንደሆነ የታወቀ ቢሆንም ይህ አስተሳሰብ በማህበረሰቡ ሙሉ በሙሉ ያልሰረጸ በመሆኑ በንግዱ ዘርፍ የተሰማሩ ዜጎች የሚጠበቅባቸውን ግብር ላለመክፈል ሲሉ ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ሲያከናውኑ መመልከት የተለመደ ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ ለመቆጣጠር የወጣው የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግ ማሻሻያ ማንኛውም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ ሰው በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት እንዲያከናውን ደረሰኙንም ወዲያውኑ ለተጠቃሚው እንዲሰጥ ግዴታ ይጥላል፡፡ ይህንን ግዴታ በመጣስ ያለደረሰኝ ግብይት የሚያከናውኑ ሰዎችም የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል የወንጀል ተጠያቂነት በወንጀል ሕጉን መሰረታዊ መርሆዎች ሊከተል የሚገባ ሲሆን በተለይም የወንጀል ሕጉን የሕጋዊነት መርህ መሰረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንጻር የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን በመተላለፍ ያለደረሰኝ ግብይት የተፈጸመ እንደሆነ የንግድ ድርጅቱ ሊጠየቅ የሚችለው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34 እና በአዋጁ አንቀጽ 2/5/ ድርጅት የሚለውን መስፈርት ሲያሟላ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም በግል ባለሀብትነት የሚተዳደሩ የንግድ ተቋማት የወንጀል ተጠያቂነት አይኖርባቸውም፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በአዋጁ መሰረት የግል ባለሀብቶች እንዲሁም ወኪሎቻቸውን በሠራተኞች ጥፋት ምክንያት ተጠያቂ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ የተቀረጸ ባለመሆኑ አፋጣኝ ማሻሻያ ሊደረግበት የሚገባ ሲሆን አሁን ባለው የሕግ ማእቀፍ መሰረት የግል ባለሀብቶችና ወኪሎቻቸውን ጥፋተኛ ማድረግ የወንጀል ሕጉን የሕጋዊነት መርህ የሚጣረስ በመሆኑ ሊታሰብበት ይገባል፡፡ በተጨማሪም የንግድ ተቋሙ ሠራተኞችን በተመለከተም በወንጀሉ ቀጥተኛ ወይም ተዘዋዋሪ ተሳትፎ ያላቸው ብቻ ናቸው ተጠያቂ ሊሆኑ የሚገባው፡፡ በአጠቃላይ የተጨማሪ እሴት ታክስን በአግባቡ እንዲሰበሰብ ጥረት ማድረጉ ተገቢነት ያለው ጉዳይ ቢሆንም የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ ግን የወንጀል ሕጉን መርሆዎች ከግንዛቤ ማስገባት አስፈላጊነቱ አሌ የማይባል በመሆኑ ዐቃብያነ-ሕግ እንዲሁም ዳኞች ጉዳዮችን በሚመረምሩበት ጊዜ እነዚህን መርሆዎች መሰረት አድርገው መሆን አለበት፡፡

# በመንግሥት የግንባታ ውል አፈፃፀምና አተረጓጎም ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ያላቸው ሚና እና ተፈፃሚነት በአማራ ክልል

*በላይነህ አድማሱ*[1]

**አጽሮተ ይዘት**

*በኢትዮጵያ መንግስት የግንባታ ውል ከአስተዳደር ውሎች መካከል አንዱ ሲሆን በአመሰራረት፣ በአፈፃፀም እና በድህረ-አፈፃፀም ወቅት የህግ ክፍተት እና የተግባር ላይ ችግሮች ይስተዋሉበታል። የህግ ክፍተቶችን እና የአፈፃፀም ችግሮችን መነሻ በማድረግ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያገለግሉ ዘዴዎች በሀገራችን የህግ ማዕቀፍ ውስጥ ተደንግገው እናገኛለን። እነዚህም መደበኛ ክርክር እና አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶች ናቸው። እነዚህን ዘዴዎች በመጠቀም ችግሮችን ለመፍታት የሚደረገው ልምድ ሲፈተሽ ወደ መደበኛ ክርክር ያመዘነ ቢሆንም አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶችን መገልገሉም አልፎ አልፎ ይስተዋላል። ይሁን እንጅ በግንባታ ውል አስተዳደር የሚከሰቱትን አለመግባባቶች ለመፍታት አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶችን የመገልገሉ ጉዳይ ከህግ እና ከአፈፃፀም ችግር የፀዳ አይደለም። በመሆኑም በዚህ ፅሁፍ በግንባታ ውል ህግ ማዕቀፍ የሚስተዋሉትን የህግ እና የአፈፃፀም ችግሮች ለመፍታት አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ያላቸውን ጠቀሜታ ለማሳየት ተሞክሯል።*

## 1. *መግቢያ*

**በሀገራችን የህግ ማዕቀፍ ውስጥ ተካተው ከሚገኙ አያሌ የውል አይነቶች መካከል የግንባታ ውል አንዱ ነው። የግንባታ ውል አሰሪ እየተባለ የሚጠራ አንድ ተዋዋይ ወገን ለተለያየ አገልግሎት ሊውል የሚችል ግንባታን ለማሰራት እና በምትኩ ስራው የሚጠይቀውን ክፍያ ለመፈፀም እና ተቋራጭ እየተባለ የሚጠራ ሌላ ወገን የግንባታ ስራውን በማከናወን የተስማሙበትን ዋጋ ለመቀበል በመስማማት ተነፃፃሪ ግዴታን ለማቋቋም እና ግዴታቸውን ለመፈፀም ለመገደድ የሚፈራረሙት ውል ነው። በዚህ ስምምነት መሰረት ተቋራጭ በውሉ የተመለከተውን የግንባታ ስራ ለማከናወን አሰሪው ደግሞ ለተፈፀመው ስራ ክፍያ ለመፈፀም ይዋዋላሉ ማለት ነው።**

[1]LLB, LLM በክልል ዐቃቢያነ-ሕግ ለ5 ዓመት፣ የሕግ ጥናትና ምርምር አስተባባሪ በመሆን ለ2 ዓመት አገልግለዋል። አሁን በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በረዳት ፕሮፌሰርነት እያገለገሉ ይገኛሉ። E-mail badmaasu7@gmail.com ማግኘት ይቻላል።

ከፍ ብሎ በተሰጠው ትርጉም መሰረት የውሉ ተዋዋይ ወገኖች (አሰሪ እና ተቋራጭ) የግዴታቸው አይነት ክፍያ መፈፀም እና የግንባታ ስራውን ማከናወን ይሁን እንጅ የግንባታ ውል ጠቅላላ ፅንሰ-ሀሳብ ሲመረመር ሌሎች ተዋዋይ ወገኖች እና ግዴታዎቻቸውንም ይጨምራል፡፡ በግንባታ ውል አሰሪ እየተባለ የሚጠራው ተዋዋይ ወገን የሚፈልገውን የግንባታ አይነት በሚፈልገው ጥራት እና ደረጃ ተገንብቶ ለመረከብ የበርካታ ባለሙያዎች እገዛ እንደሚያስፈልገው ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ የሚፈልገውን የግንባታ አይነት ንድፍ /design/ ለማሰራት የአርክቴክት /designer/ በንድፉ እና በፕላኑ መሰረት ግንባታውን ለማከናወን የሚያስፈልገውን ቁሳቁስ እና የገንዘብ መጠን ለማወቅ የቀያሽ /quantity surveyor/ እና ንድፉን እና የተገመተውን የገንዘብ መጠን በአግባቡ ስራ ላይ በማዋል ግንባታው በትክክል እየተከናወነ መሆኑን በግንባታ ቦታው በመገኘት በተቋራጩ ላይ አስፈላጊውን ክትትል ለማድረግ የሲቪል መሀንዲስ ድጋፍ ያሻዋል፡፡ ተቋራጩም እንደዚሁ የተለያዩ ቴክኒካዊ ድጋፎችን የሚያደርጉለት አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ እርሱን ተክቶ የተወሰነውን የስራ ክፍል በውሉ መሰረት የሚያከናውንለት ንዑስ ተቋራጭ ሊያሰኘው ይችላል፡፡ አሰሪ እና ተቋራጭ የተባሉ ዋናዎቹ ተዋዋይ ወገኖች ከላይ የተመለከቱትን ልዩ ልዩ ድጋፎች ለማግኘት በርካታ ውሎችን ከእነዚህ ባለሙያዎች ጋር ሊዋዋሉ ይችላሉ፡፡ የግንባታ ውሉን አላማ ከግቡ ለማድረስ በአሰሪው እና በተቋራጩ በኩል የሚደረጉ ውሎች በሙሉ በግንባታ ውል ትርጓሜ ውስጥ እንደሚካተቱ በተለያዩ ምሁራን የተሰነዘሩ ፅንሰ-ሀሳቦች በዚህ ፅሁፍ ተዳሰዋል፡፡

የግንባታ ውል ትርጓሜ እና ፅንሰ-ሀሳብ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል በሚከተሉት ሦስት ዋና ክፍሎች ተመድቦ ሊተነተን ይችላል፡፡ እነዚህም የቁርጥ ክፍያ ውል /lump sum contract/፣ በስራው ልኬት መሰረት የሚከፈል ውል /measurement contract/፣ ስራው ከተጠናቀቀ በኃላ ወጪው የሚወራረድበት ውል /cost re-imbursement contract/ ናቸው፡፡ ከሶስቱ የውል አይነቶች አንዱን መርጦ መዋዋል እና ግንባታውን ማሰራት የአሰሪው እና የተቋራጩ ሀላፊነት ነው፡፡ የሚስማማቸውን የውል አይነት ለመምረጥ ውሎቹ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ሀላፊነት፣ የሚያስወጡትን ወጪ እና የሚያስገኙትንም ትርፍ መመርመር ይኖርባቸዋል፡፡

እነዚህን ነጥቦች በአግባቡ በማጤን ውሳኔ ላይ የደረሰ አሰሪ ተቋራጩን በተለያየ ዘዴ ሊመርጥ ይችላል፡፡ በኢትዮጵያ የመንግስት የግንባታ ውል የአስተዳደር ውል በመሆኑ ተቋራጮች የሚመረጡበት መንገድ ጨረታ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፍ ውስጥ የተለያዩ የጨረታ ዘዴዎች የተካተቱ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ በግንባታ ውል በብዛት ተፈፃሚ የሚሆነው ግልፅ

ጨረታ ነው። ግልፅ ጨረታ በሀገሪቱ ውስጥ በግንባታ ዘርፍ የተሰማሩ ተቋራጮች እኩል መረጃው ደርሷቸው የጨረታ ሰነዱን በመግዛት የሚያዋጣቸውን ዋጋ ሞልተው የሚወዳደሩበት እና አሸናፊው የሚለይበት ስርዓት ነው። በዚህ ውድድር አሸናፊ የሆነው ተቋራጭ በህግ የሚጠበቅበትን ዋስትና በማስያዝ ውሉን ተፈራርሞ የግንባታ ስራውን ማከናወን ይጀምራል።

በዚህ መንገድ ውል የገባው ተቋራጭ በውሉ ውስጥ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ስራውን በጥራት ሰርቶ የማስረከብ ግዴታ እንዳለበት ግልፅ ነው። ሆኖም በውል አፈፃፀም ውስጥ ከግንባታ ጊዜ እና ጥራት ጋር በተያያዘ በርካታ አለመግባባቶች እና ውጣ ውረዶች ይስተዋላሉ። እነዚህን አለመግባባቶች ለመፍታት የፍ/ቤት ክርክርን መጠቀም ይዘወተራል። ይሁን እንጅ ጉዳያቸውን በመደበኛ ክርክር ለመቋጨት የሞከሩ አሰሪዎች እና ተቋራጮች በክርክር ሂደቱ መንዛዛት እና በፍርዱ መዘግየት ሲማረሩ ይሰማል። ይህም የሚሆነው በሀገራችን ብሎም በክልላችን ያሉ ፍ/ቤቶች ባለባቸው የጉዳይ ብዛት እና የስራ ጫና ምክንያት እንደሆነ ይታመናል። በመሆኑም ከግንባታ ውል ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ወይም ችግሮችን ከመደበኛ ክርክር ባሻገር ባሉ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች ለመቋጨት መሞከሩ አይነተኛ መፍትሄ ነው። ይህንንም በአማራ ክልል የሚገኙ አንዳንድ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በአብክመ ፍትህ ቢሮ አማካሪነት ተግባራዊ እያደረጉት እና ለችግሮቻቸው መፍትሄ ወይም እልባት እያስገኘላቸው እንደሆነ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የተተነተኑ ውሎች እና ውሳኔዎች ማሳያዎች ናቸው። የዚህ ፅሁፍ አላማም በግንባታ ውል አስተዳደር ውስጥ የሚያጋጥሙ ዋና ዋና የህግ እና የአፈፃፀም ችግሮችን በጥናት መለየት እና አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶችን ተግባራዊ በማድረግ አለመግባባቶችን ለመፍታት አግባብነት ያላቸውን ህጎች በመፈተሽ በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት የመፍትሄውን አዋጭነት ማሳየት ብሎም ተግባራዊ የሚሆኑበትን መንገድ መጠቆም ነው።

ይህንን አላማ ለማሳካት ፅሁፉ በሰባት ዋና ዋና ክፍሎች ተደራጅቷል። በዚህም መሰረት ክፍል አንድ ስለ ግንባታ ውል በጠቅላላው የሚያወሱ መሰረተ ሀሳቦችን ማለትም ስለ ግንባታ ውል ምንነት፣ አይነቶች እና ተዋዋይ ወገኖች ማንነት ይዳስሳል። በክፍል ሁለት እና ሶስት የግንባታ ውል አመሰራረት እና አፈፃፀም የተብራሩ ሲሆን ጨረታ እና ዋስትና እንዲሁም በውል አፈፃፀም ግዴታ የሚያጋጥሙ ችግሮች በዋናነት ተዳሰውበታል። በክፍል አራት ደግሞ በግንባታ ውል አስተዳደር ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ሊፈፀሙ የሚገባቸው አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች የትኞቹ እንደሆኑ እና በኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፍ ውስጥ

ያላቸው ቦታ ምን እንደሚመስል ለማየት ተሞክሯል። የዕሁፉ ክፍል አምስት፣ ስድስት እና ሰባት በግልግል ዳኝነት የሚታዩ እና የማይታዩ ጉዳዮች በጠቅላላው በተለይም የአስተዳደር እና የግንባታ ውሎችን በግልግል ዳኝነት ለማየት ያሉ ችግሮች እና ምቹ ሁኔታዎች እንዲሁም በአማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት የተሰጡ ውሳኔዎች አፈፃፀም ተብራርተዋል።

በመጨረሻም የጽሁፉ ማጠቃለያ እና በጥናቱ የተለዩ ችግሮች እንዲሁም መፍትሄዎቻቸው ተመልክተዋል።

በጠቅላላው ይህ ዕሁፍ በግንባታ ውል አስተዳደር ውስጥ የሚያጋጥሙ የህግ እና የአፈፃፀም ችግሮችን በመለየት አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች የሚታዩትን ችግሮች በማቅለል ረገድ ያላቸውን ሚና በአጭሩ ያስዳስሳል።

## 1.1 .የግንባታ ውል ትርጓሜ

የግንባታ ውል ምን ማለት እንደሆነ መረዳት ወደ ፊት ለምናደርጋቸው ዝርዝር ውይይቶች የላቀ አስተዋፅኦ ስለሚኖረው በቅድሚያ ትርጉሙን መመልከቱ አስፈላጊ ነው። የግንባታ ውል ሁለት መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳቦችን የያዘ መሆኑን ከቃሉ መረዳት እንችላለን። እነዚህም ግንባታ እና ውል ናቸው። ቃሎቹ በየራሳቸው ጥልቅ የሆነ ሀሳብን እንደያዙ መገንዘቡ ተገቢ ሆኖ ለዚህ ጽሁፍ አላማ ግን ሁለቱን ቃሎች ያገናኘውን ሀይለ ቃል መሰረት አድርጎ ትርጉም መስጠት በቂ ነው። በመሆኑም የግንባታ ውል ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የተለያዩ ባለሙያዎች የሰነዘሩትን ሀሳብ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ጆን አድሪያንስ የተባለ አንድ ምሁር ጥያቄውን ለመመለስ በዋቢነት የተጠቀመው የእንግሊዝ መንግስት እ.ኤ.አ በ1996 ያወጣውን ህግ ነው። ምሁሩ እንደገለፀው ይህ ህግ የግንባታ ልዩ ልዩ የህንፃ እና የሲቪል ምህንድስና ስራዎችን ማለትም የግንባታ ቦታን ማዘጋጀትን፤ ግንባታ መገንባትን፤ ቀለም መቀባትና ማስዋብን እንዲሁም ሌሎች መሰል ስራዎችን ለማከናወን በአሰሪውና በተቋራጩ መካከል በጽሁፍ የሚደረግ ስምምነት ነው ይልና በአማካሪ መሀንዲሱና በአሰሪው መካከል የግንባታ ስራውን ለማስተዳደር ወይም

ለግንባታው አስፈላጊ የሆነውን የሰው ሀይልና የግንባታ እቃ ለማቅረብ የሚደረግ ስምምነትን ሊያካትት ይችላል በማለት ይተረጉመዋል[2]፡፡

ይህንን ትርጉም ስንመለከተው እጅግ በጣም ሰፊና ብዙ ነገሮችን ያካተተ ነው፡፡ ትርጓሜው በአሰሪውና በተቋራጩ መካከል ሊደረግ የሚችለውን የግንባታ ስራ ስምምነት ብቻ ሳይሆን ከአማካሪና ከእቃ አቅራቢዎች ጋር ሊደረጉ የሚችሉትን ውሎች ሁሉ ያካተተ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የውል ጉዳዮች፤ የውል ግዴታዎች እና ተዋዋይ ወገኖች በግንባታ ውል ቁጥራቸው ብዙ እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

የግንባታ ውል ትርጓሜን በተመለከተ ሀድሰን እና ኪቲንግ የተባሉ ምሁራንም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ጽንሰ-ሃሳብን ያስነብቡናል፡፡ ሀድሰን የግንባታ ውልን "አሰሪና ተቋራጭ በሚባሉ ሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚደረግ ስምምነት ሲሆን ተቋራጭ የግንባታ/የሲቭል ምህንድስና/ ስራዎችን ለመስራት አሰሪው ደግሞ ለተሰራው ስራ ክፍያ ለመፈጸም ግዴታ የሚገቡበት የስምምነት አይነት ነው" በማለት ተርጉሞታል[3]፡፡ ኪቲንግም እንዲሁ "ተቋራጭ እየተባለ የሚጠራ አንድ ሰው አሰሪ ለሚባል ሌላ ሰው የግንባታ ስራ ለመስራት እና ለሰራው ስራ ዋጋ ለመቀበል የሚስማማበት ውል ነው" ሲል ገልጾታል፡፡[4]

ከላይ የተመለከትናቸው የግንባታ ስራ ውል ትርጓሜዎች መጀመሪያ ላይ ከተመለከትነው በአንፃሩ ጠበብ ያለ ይዘት ያላቸው ይመስላሉ፡፡ ሁለቱ ምሁራን ለግንባታ ስራ ውል የሰጡት ትርጉም በአሰሪና በተቋራጭ መካከል ያለውን ስምምነት ብቻ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች የሚስማሙበት የውል ጉዳይ የግንባታ ስራ መስራት እና ለተሰራውም ስራ ክፍያ መፈጸም ላይ የሚያጠነጥን ነው፡፡ በውላቸው ውስጥ ተቋራጭ ተብሎ የሚጠራው ተዋዋይ ወገን አሰሪ ተብሎ ለሚጠራው ሌላኛው ወገን ግንባታ እና ከግንባታ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ስራዎች ሰርቶ ለማስረከብ ግዴታ ሲገባ አሰሪ ተብሎ የሚጠራው ሌላኛው ወገን በአንጻሩ ለተሰራለት ስራ የተስማማበትን ክፍያ የመፈጸም ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በትርጓሜዎቹ ውስጥ የምናገኘው ሀይለ ቃልም ይኸው ነው፡፡ ጆን አድሪያንስ ለግንባታ ስራ ውል የሰጠው ትርጓሜ ግን አማካሪዎች /የእቃ

[2] John Adriaanse, Construction Contract,2nd ed, (London south bank university, 2007)
[3] I.N Duncan Wallace, Hudson's Building and Engineering Contracts, 10th ed, /Sweet and Maxwell:London,1970/
[4] ዝኒከማሁ

አቅራቢዎች/ ከአሰሪው /ከተቋራጩ/ ጋር የሚደርጉትን ስምምነት ሁሉ ያካተተ በመሆኑ በይዘቱ ሰፋ ያለ ነው፡፡

ከላይ የተመለከትናቸውን በምሁራን የተሰጡ የግንባታ ስራ ውል ትርጓሜዎችን ይዘን በሀገራችን የህግ ማዕቀፍ ውስጥ ለቃሉ የተሰጠውን ትርጉም ማፈላለግና መመርመሩ በህጎቻችን ውስጥ ያለውን ክፍተት ለመፈተሽ እና በዚህ ረገድ በተግባር ለሚያጋጥሙን ለሚችሉት ችግሮች መፍትሄ ለመሻት ፋይዳው የላቀ ነው፡፡ የግንባታ ውል በሀገራችን በብዛት ከሚሰነዱ የውል አይነቶች መካካል ይገኛል፡፡ በተለይ አሁን አሁን ከግንባታ ስራው መስፋፋት ጋር ተያይዞ የዚህ አይነቱ ውል እጅግ በጣም የሚዘወተር ሆኗል፡፡ በመሆኑም የግንባታ የስራ ውል በሀገራችን ህጎች እንዴት ይገለፃል የሚለው መታየት አለበት፡፡ የግንባታን ውል ምንነት ለመረዳት በቅድሚያ መፈተሽ ያለበት የሀገራችን የፍትሐ ብሔር ህግ ሲሆን የዚሁ ህግ አንቀጽ 2610፤ 2876 እና 3244 አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ አንቀጽ 2610 የስራ ውልን እንደሚከተለው ይተረጉመዋል “የስራ ማከናወኛ ውል ማለት አሰሪው በገባው ውለታ ለአንደኛው ወገን የስራውን ዋጋ ሊከፍለው ስራ ተቋራጩም በሀላፊነት የተሰጠውን አንድ ስራ በገባበት ውለታ ሊፈጽም በሁለቱ ወገኖች መካከል የተደረገ ውል ነው”[5] ይለዋል፡፡

ከዚህ ትርጓሜ ጋር አግባብነት ያለው ሌላው የፍትሐ ብሔር ህግ ድንጋጌ አንቀጽ 3244 (1) ሲሆን የስራ ውልን “የመንግስት ስራዎች ውል የሚባለው አንድ ተቋራጭ የሆነ ሰው ከአንድ የአስተዳደር መስሪያ ቤት ባለስልጣን ጋር በዋጋ ተስማምቶ አንድ የመንግስት የሆነ ህንፃ ስራን ለመስራት፣ ለመጠበቅ ወይም ለማደስ የሚያደርገው ውል ነው” ሲል ይተረጉመዋል፡፡ ሁለቱም ድንጋጌዎች በአሰሪውና በተቋራጩ መካከል ያለን የስራ ውል ለመግለጽ የተደነገጉ በመሆናቸው ለውሉ የሰጡት ትርጓሜ ተቀራራቢ ነው፡፡ በሁለቱም ትርጓሜዎች ለተቋራጭ የተሰጠው ግዴታ የግንባታ ስራን ማከናወን ነው፡፡ ቢሆንም በአንቀጽ 2610 የስራውን አይነት ለመግለጽ የተሞከረበት አግባብ ግልፅ አይደለም፡፡ “...የተሰጠውን አንድ ስራ...” የሚለው ሀረግ አሰሪ እና ተቋራጭ ከሚሉት ተዋዋይ ወገኖች ግዴታ ጋር አጣምረን ትርጉም ካልሰጠነው በቀር የግንባታ ስራ ይሁን ወይስ ሌላ በራሱ የሚገልጸው ነገር የለም፡፡ በ3244 (1) ስር የስራው አይነት ምን እንደሆነ ተገልፆ

[5] የኢትዮጵያ ንጉሰ-ነገስት መንግስት የፍታብሔር ሕግ፣ ቁጥር 2፣ አዲስ አበባ፣ 1952

እናገኘዋለን፡፡ “....የተሰጠውን የህንፃ ስራን ለመስራት፣ ለመጠበቅ ወይም ለማደስ....” የሚለው ሀረግ ለተቋራጩ የተሰጠው ስራ የግንባታ ስራ መሆኑን በግልጽ ያመለክታል፡፡

አንቀፅ 2876’ም የስራውን አይነት ለመረዳት የሚበጅ ድንጋጌን ይዞ እናገኘዋለን፡፡ ድንጋጌውም “አንዱ ወገን ተዋዋይ ለሌላው ወገን ተዋዋይ አንድ ቤት፣ አንድ የቤት ክፍል ወይም ገና የሌለ አንድ የሚሰራ ህንፃ ለመስጠት ግዴታ የሚገባበት ውል የአንድ ህንፃ ስራ ውል ይባላል እንጅ የሽያጭ ውል ሊባል አይችልም” የሚል ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ መሰረታዊ ሀሳቡ ከማይንቀሳቀስ ንብረት የሽያጭ ውል ጋር የተያያዘ ይሁን እንጅ የግንባታ ስራን እንደ አንቀፅ 3244 ሁሉ ህንፃ የሚለውን ቃል አንድ ቤት፣ አንድ የቤት ክፍል ወይም ገና የሌለ አንድ የሚሰራ ህንፃ በሚል ስለሚያብራራው በአንቀፅ 2610 ስር አንድ ስራ ተብሎ የተቀመጠውን ጥቅል ሀሳብ ግልፅ ለማድረግ ጠቀሜታ አለው፡፡

ሌላው በአንቀጸ 2610 እና 3244 መካከል ያለው ልዩነት የመጀመሪያው ድንጋጌ ስለ ስራ ውል በጠቅላላው የሚናገር ሲሆን የኋለኛው ግን ከአስተዳደር አካላት ጋር ስለሚደረግ የመንግስት ግንባታ ስራ ውልን የሚመለከት ነው፡፡ ሁለቱ ድንጋጌዎች ከላይ የተመለከትናቸው ልዩነቶች ይኑራቸው እንጅ የግንባታ ስራ ውልን ለመግለጽ ተገቢነት አላቸው፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት የግንባታ ስራ ውል ተቋራጭ ተብሎ የሚጠራ አንድ ሰው ለስራው ዋጋ ተብሎ አሰሪ ተብሎ ለሚጠራ ሌላ ሰው የግንባታ ስራን ለማከናወን የሚያደርገው ስምምነት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በእንዲህ አይነት ውል ተቋራጭ የግንባታ ስራን ወይም ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ስራዎችን አሰሪ እየተባለ ለሚጠራ ሌላ ተዋዋይ ወገን ሰርቶ ለማስረከብ ሀላፊነት ይኖርበታል:: አሰሪ ደግሞ እንዲሰራለት ያዘዘው የግንባታ ስራ ሲጠናቀቅ ለተቋራጩ በስምምነቱ ላይ የተመለከተውን ክፍያ የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

ይህ የግንባታ ስራ ውል ትርጉም በሌሎች ህጎችና መመሪያዎች ላይም ተመልክቶ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ ረገድ ተጠቃሽ የሆነው መመሪያ የሲቪል ግንባታ ስራዎች ቋሚ የውል መተዳደሪያ ደንብ/ ጠቅላላ የውል ሁኔታዎች/ ነው፡፡ ይህ መመሪያ የግንባታ ስራዎችን አስመልክቶ የሚፈረም ውልን በቀጥታ ባይተረጉመውም እንኳ በውስጡ ምን ምን ማካተት እንዳለበት በማሳየት የውልን ይዘት ለማብራራት ሞክሯል፡፡ በዚህ መሰረት የግንባታ ውል የሚባለው የውል መሠረቶች ፣ የሥራ አሠራር ሁኔታ ዝርዝር የመለኪያ ዘዴዎች ፣ንድፎች ፣ ዋጋ ያላቸው መክፈያ ደረሰኞች፣ የደረጃና ተመን ዝርዝሮች፣ የስምምነት ደብዳቤ ፣ የውል

ስምምነት እንዲሁም በተጨማሪ የሚወጡ ሌሎች ሰነዶችን ያካተተ ነው ። ስለሆነም በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉትን የግንባታ ውል የሚይዛቸውን ሰነዶች ከፍ ብሎ በፍታብሄር ህግ እና በሌሎች የግንባታ ውል ምሁራን የተሰጡትን ትርጓሜዎች ባገናዘበ መልኩ የግንባታ ውልን ትርጉም መረዳት እና መተንተን የዘርፉ ሊቃውንት የሙያ ግዴታ መሆን አለበት፡፡

## 1.2 የግንባታው ውል አይነቶች

ቀደም ሲል የግንባታ ውል መሠረታዊ ባህሪያትን ተመልክተናል፡፡ ባህሪዎቹ እንደተጠበቁ ሆነው የግንባታ ውልን በክፍያው አፈፃፀም ላይ ተመስርተን ልንከፋፍላቸው እንችላለን፡፡ የክፍያ አፈፃፀሙን መሠረት በማድረግ ምሁራን የግንባታ ውሎች በሶስት ዋናዋና ክፍሎች ፈርጀው ይመለከቷቸዋል፡፡ የግንባታው አይነቶችም የቁርጥ ክፍያ፣ በስራው ልኬታ መሠረት የሚከፈል ውል እና ስራው ከተጠናቀቀ በኃላ ወጭ የሚወራረድበት የውል ዓይነቶች ናቸው ። እነዚህ የውል አይነቶች የየራሳቸው የአከፋፈል ሥርዓት አላቸው፡፡ የአከፋፈል ስርዓቱን መሰረት በማድረግ የውል አይነቶች ሲገመገሙ የየራሳቸው ጥቅም እና ጉዳት ይኖራቸዋል፡፡ ተቋራጮችና አሰሪዎች ጥቅምና ጉዳታቸውን መሠረት በማድረግ የሚስማማቸውን የውል አይነት ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡ ሥለሆነም እያንዳንዱን የውል አይነት ከእነ ጥቅምና ጉዳቱ በዝርዝር መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

### 1.2.1. የቁርጥ ክፍያ /Lump-sum contract/

ይህ የውል አይነት አሰሪው የሚያስፈልገውን የግንባታ ሥራ በዝርዝር በባለሙያ በማስጠናት የሚፈጀውን የቁሳቁስ እና የወጭ መጠን ተገንዝቦ ለተቋራጮችም ይህንን የሚያሳይ ሰነድ /bill of quantity/ ሲያቀርብ በተቋራጭም ለግንባታ አስተዳደር ስራው የሚያስፈልገውን ወጭ ሊያስገኛቸው ከሚችለው ትርፍ ጋር በማስላት ገምተዉ ስሌቱን ለአሠሪው በማቅረብ ጠቅላላ ዋጋ ላይ እና በአከፋፈል ስርአቱ ላይ ተስማምተው የሚፈራረሙት ወይም የሚገቡበት የውል አይነት ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ውሉ የቁርጥ ክፍያ ወይም አስቀድሞ የተወሠነ ክፍያ /stipulated cost/ በመባል ይታወቃል፡፡ በዚህ የውል አይነት የተሰማሙ ተቋራጭና አሠሪዎች የሚሰራውን ሥራ በዝርዝር እንደሚያውቁ ይገመታል፡፡

አሠሪው ሊሠራ ያሠበውን ህንፃ፣ መንገድ ወይም ሌላ የግንባታ ስራ ፍላጐቱን መሠረት በማድረግ አማካሪ መሀንዲሱ የህንፃ የመንገድ ወይም ሌላ የግንባታ ስራ አይነት ንድፍ እንደያዘጋጅለት ይስማማል፡፡ አማካሪ መሀንዲሱ የደንበኛውን ወይም የአሠሪውን ፍላጐት

/አላማ/ በመገንዘብ ወደፊት የሚሠራውን ግንባታ ምስል /design/ በስዕል፣ በቻርት ወይም በሌላ ተስማሚ በሆነ መንገድ ያዘጋጅለታል፡፡

ይህንን ስራ ለመስራት የሚያስፈልገው ቁሳቁስ እና ወጭ እንዲሁም አሠሪው በባለሙያው የወቅቱን ገበያ መሠረት በማድረግ ያሠራል፡፡ ሁለቱ ባለሙያዎች ባቀረቡት የግንባታው ዲዛይን እና ወጭ ዝርዝር መሠረት አሠሪውና ተቋራጩ የግንባታ ሥራውን ዝርዝርና የሚያስፈልገውን ወጭ አስቀድመው የማወቅ እድል ይኖራቸዋል፡፡ በስራው ዝርዝር መሠረት የሚያስፈልገው አጠቃላይ ወጪ ከታወቀ ሁለቱም ወገኖች ይህንን አጠቃላይ ወጪ /stipulated cost/ በውላቸው ውስጥ በማስፈር እና የክፍያው አፈፃፀም ሥርዓት ምን እንደሆነ በመስማማት ውል ይፈራረማሉ፡፡ ሥለሆነም ተቋራጩ ለስራው የሚያስፈልገውን ቁሳቁስ እና የሰው ሀይል እንዲሁም የስራ ማስኬጃውን ወጪ አስቀድሞ በመገመት አዋጪ በሆነ መንገድ ለማከናወን ይጥራል፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ ተቋራጩ ስራውን ለመስራት ያወጣው ወጪ አስቀድሞ በግምት በውል ላይ ካሰፈረው ጠቅላላ ዋጋ ያነሰ እንደሆነ ስራው ትርፋማ ይሆናል ፡፡ በእርግጥ የወጣው ወጪ ውል ላይ ከተቀመው ጠቅላላ ዋጋ በጣም ከፍ /ዝቅ/ ማለቱ የትርፉን መጠን ከፍ ዝቅ ማለት ይወስነዋል፡፡ ለምሳሌ /"Z"/ የተሰኘ ተቋራጭ /"E"/ ከተባለ አሠሪ ጋር በባህር ዳር ከተማ ለቢሮ አገልግሎት የሚውል ባለ ሰባት ፎቅ ህንፃ በ20 ሚሊዬን ብር ሊሰራለት ተስማማ እንበል፤ ተቋራጩ ህንፃውን ሰርቶ ሲያጠናቅቅ ያወጣው ወጭ 18 ወይም 17 አልያም 15 ሚሊዬን ብር ቢሆን ያገኘው የትርፍ መጠን ከፍና ዝቅ ማለቱን ያሳየናል፡፡ ነገር ግን ተቋራጩ ህንፃውን ገንብቶ ሲጨርስ በውሉ ላይ ከተቀመጠው ጠቅላላ ዋጋ 20 ሚሊዬን ብር በላይ ቢያወጣ የተለየ ስምምነት ከሌለ በቀር በውሉ ላይ ከተመለከተው ገንዘብ መጠን በላይ እንዲከፈለው አሰሪውን መጠየቅ አይችልም፡፡ ያወጣው ወጪ የራሱ ኪሳራ ሆና ሀላፊነቱን ይሸከማል ፡፡ ይህ የወጣው ወጪ በውሉ ላይዋጋ በላይ መሆኑ ተቋራጩን ለኪሳራ ይዳርገዋል፡፡

### 1.2.2. በስራው ልኬት መሠረት የሚከፈል ውል /measurement contract/

በስራው ልኬት መሠረት የሚከፈል ክፍያ አድጐ የሚፈረም ውል ተቋራጭ የተወሰነውን የስራ ክፍያ ከስራ በኋላ የተሰራው ስራ በዝርዝር ተለክቶ ለስራው የወጣው ወጪ በወቅቱ ባለው የገበያ ዋጋ ተሰልቶ የስራው ዋጋ ለተቋራጭ በአሠሪው እንዲከፈል የሚፈፀም ስምምነት ነው፡፡ ኪቲንግ የተባለው የግንባታ ውል ህግ ምሁር ይህንን የውል አይነት ከላይ በተገለፀበት አግባብ

ሲተነትን የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ አስገብቷል። የመጀመርያውና ዋናው ስራው የሚፈጀው ወጭ በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች አስቀድሞ አለመታወቁ ነው። ተቋራጩም ይህን አሠሪው ወገን የስራውን ዝርዝር ከመነሻው እስከ መድረሻው እንዲሁም ጠቅላላ ወጪውን የማያውቁት ስራው በቁጥቁጥ ስለሚሠራና ዋጋም እሚወጣው ለተሠራው ስራ ብቻ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ጠቅላላ ስራውና የስራው ዋጋ በውሉ ላይ አይመለከትም። የስራው ዋጋ ስራው ተለክቶ የፈጀው የግንባታ እቃና ጉልበት በወቅቱ ምክንያታዊ የገበያ ዋጋ ተሠልቶ ለተቋራጭ የሚከፈል ይሆናል[6]። እዚህ ላይ ልኬታ /measurement/ የስራ ዋጋ /evaluation/ እና የገበያዋጋ /sale of market price/ የሚሉት ወጭውን ለማስላት ወሳኝ መለኪያዎች እንደሆኑ ልብ ማለት ያሻል።

ሌላው ነጥብ የትርፍ ስሌት ጉዳይ ነው። ተቋራጩ ስራውን የሚሰራው ለትርፍ በመሆኑ የውሉ አይነት በመለየቱ የትርፍ ጉዳይ ቸል ሊባል አይገባውም። በመሆኑም በዚህ የውል አይነት ትርፍ በሁለት መንገድ ሊሰላ ይችላል። አንደኛው የትርፍ ስሌት በተቋራጩ እና በአሰሪው ስምምነት የወጪው የተወሰነ መቶኛ ስሌት /ፐርሰንቴጅ/ በትርፍነት ሊከፈለው እንደሚችል በውላቸው ሊያሰፍሩ ይችላሉ። ይህ ማለት የተወሰነውን የስራ ክፍል ለመስራት ተቋራጩ ያወጣውን ወጪ አንድ በመቶ፤ ሁለት በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ተሰልቶ ለተቋራጩ ትርፍ ሊከፈለው ይችላል። ሁለተኛው የስሌት አይነት የእያንዳንዱ እቃ ወይም ስራ ዋጋ በተስማሙበት የገበያ ዋጋ ዝርዝር ውስጥ ተካቶ እንዲታሰብ ሊስማሙ ይችላሉ። በዚህ ስሌት ተዋዋይ ወገኖች ከተስማሙ በእያንዳንዱ እቃ /ስራ/ ዋጋ ውስጥ ተቋራጩ ሊያገኘው የሚገባውን ትርፍ በገንዘብ ገምቶ ከወጪ ስሌት ውስጥ አካቶ ሊያቀርብ ግድ ይላል።

በተሰራው ስራ ልኬታ መሰረት ክፍያ እንዲፈጸም የሚደረግ ውል ከቁርጥ ክፍያ ውል የሚለየው ስራው፤ ወጪው እና የስራው ዋጋ የሚገመትበት የገበያ ዋጋ አለመታወቁ ብቻ ሳይሆን ትርፉን አስቀድሞ በማወቅ የውሉ አካል እንዲሆን ማድረጉ ነው።

### 1.2.3. ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ ወጪው የሚወራረድበት ውል /cost re-imbursement contract/

ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ ወጪው የሚወራረድበት የውል አይነት ተቋራጩ ስራውን ሙሉ በሙሉ በራሱ ወጪ ሰርቶ የስራውን ጠቅላላ ወጪ ከነትርፉ በአሰሪው እንዲመለስለት

[6] በግርጌ ማታወሻ ቁጥር 2 እንደተገለጸው

የሚያስገድድ የውል አይነት ነው። በዚህ ውል ስምምነት መሰረት ተቋራጩ በአሰሪው በሚሰጠው የስራ ትዕዛዝ እና ሌሎች ሰነዶች መሰረት የግንባታውን ስራ በራሱ ወጪ ይሰራል። ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ሲያወጣ ለወጪዎቹ ደረሰኝ ይቀበላል። የግንባታ ስራው ተጠናቆ እርክክቡ በሚፈጸምበት ጊዜ ለስራው የወጣውን ወጪ ዝርዝር የሚያሳይ ደረሰኝ በማቅረብ ያወጣውን ወጪ አሰሪው እንዲተካለት ያደርጋል። የሚተካው ወጪ የግንባታ ቁሳቁስ ዋጋ፣ የሰው ሀይል ክፍያ እና የስራ ማስኬጃ የሚያካትት በመሆኑ ደረሰኙም እነዚህን ክፍያዎች በግልጽ የሚያሳይ እና ህጋዊ መሆን ይኖርበታል። ሌላው በዚህ የውል አይነት ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የትርፉ ጉዳይ ነው። እንዲህ አይነት ውል የሚፈርም ተቋራጭ ሊያገኘው ስለሚችለው ትርፍ ስጋት አይገባውም። ምክንያቱም የትርፉ መጠን በመቶኛ ሊታሰብ እንደሚገባው አስቀድሞ በውሉ ስለሚመለከት ነው። የትርፉ መጠን አስቀድሞ መወሰን ለአሰሪውም የሚያስገኘው ፋይዳ አለ። ይኸውም ተቋራጩ ለግንባታው እቃ፣ ለሰው ሀይል እና ለስራ ማስኬጃ የሚያወጣው ወጪ ከሚያገኘው ትርፍ ጋር ግንኙነት የሌለው በመሆኑ በሚጠቀምባቸው የግንባታ እቃዎች ጥራት ላይም ይሁን በሚቀጥረው የሰው ሀይል አቅም ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ አይኖርም። በሌላ አነጋገር ተቋራጩ የተሻለ ትርፍ ለማግኘት ሲል ጥራቱ የቀነሰ የግንባታ እቃ እና ሙያዊ ብቃት የሌለው የሰው ሀይል ለመጠቀም አይሞክርም። በጠቅላላው ከላይ የተመለከትናቸው ሶስት የግንባታ አይነቶች ስጋትን ከመቀነስ አንጻር የየራሳቸው ጠንካራ እና ደካማ ጎን ስላላቸው ተቋራጮች እና አሰሪዎች ጥቅምና ጉዳታቸውን በመመዘን የተሻለውን የውል አይነት መፈረም ይኖርባቸዋል።

### 1.3 የግንባታ ውል ተዋዋይ ወገኖች እና ሀላፊነታቸው /ግዴታቸው/

በግንባታ ውል ተዋዋይ የሚሆኑ ወገኖች ብዙ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ ተቋራጭ እና አሰሪ ናቸው። በተቋራጭ እና በአሰሪ መካካል በተደረገው ውል ውስጥ የሚገለጸው ግዴታ ግን በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ብቻ ሊፈጸም የሚችል ባለመሆኑ እነዚህ ተዋዋይ ወገኖች ከሌሎች ወገኖች ጋር ተጨማሪ ስምምነት መፈጸም ግድ ይሆንባቸዋል። በተለይ አሰሪው ግንባታን አስመልክቶ የሚኖረው እውቀት ውስን ስለሆነ እሱን ሆነው የግንባታ ስራውን ንድፍ /design/ የሚሰራለት፣ በንድፉ መሰረት የግንባታ ስራው ደረጃውን ጠብቆ እየተሰራ መሆኑን የሚከታተልለት እና ክፍያ የሚያዝለት እንዲሁም ወደ ግንባታ ከመገባቱ በፊት የግንባታ ስራውን እና ወጪውን የሚገምትለት ባለሙያ ማግኘት የግድ ስለሚለው ከአማካሪ መሀንዲስ እና ከቀያሽ /servior/ ጋር ተጨማሪ ውሎችን መዋዋል ይጠይቀዋል።

ተቋራጩም ቢሆን በሁሉም የስራ አይነቶች ላይ የሚያገለግለው እውቀት እና ብቃት ላይኖረው ስለሚችል፤ ቢኖረውም እንኳ ስራውን ለማፋጠን የተለያዩ ንዑስ ስራዎችን ለሌላ ተቋራጭ በስምምነት ሊሰጥ ስለሚችል ተጨማሪ ውል ከሌሎች ንዑስ ተቋራጮች ጋር ሊዋዋል ይችላል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የግንባታ ውል በተቋራጭ እና በአሰሪው መካካል ያለውን ዋና ውል ብቻ ሳይሆን አሰሪው ከአማካሪው መሀንዲስ እና ከቀያሽ ጋር እንዲሁም ተቋራጩ ከንዑስ ተቋራጮች ጋር የሚያደርጓቸውን ውሎች ሁሉ የሚያካትት ነው፡፡ ውሎቹ ብዙ በመሆናቸው ተዋዋይ ወገኖችም እንዲሁ ብዙ ናቸው፡፡ ተዋዋይ ወገኖች እና ውሉ ብዙ መሆናቸውን ተከትሎ ከውሉ የሚመነጩት ግዴታዎችም እንዲሁ ብዙዎች ናቸው፡፡ ተዋዋይ ወገኖች ተቋራጭ፤ አሰሪ፤ አማካሪ መሀንዲስ፤ ቀያሽ እና ንዑስ ተቋራጭ ሲሆኑ የእነዚህ ተዋዋይ ወገኖች ግዴታ ምን እንደሚመስል ቀጥሎ እንመለከታለን፡

### 1.3.1. የተቋራጭ ግዴታ፡-

የግንባታ ውል ትርጉም በተመለከተበት የዚህ ጽሁፍ ክፍል ውስጥ ተቋራጭ ከአሰሪው ጋር በሚገባው ውል ግዴታው ምን እንደሆነ በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ተቋራጭ ከአሰሪው ክፍያ ተቀብሎ ለአሰሪው አንድ የግንባታ ስራን ሰርቶ ለማስረከብ የሚያደርገው ስምምነት የግንባታ ውል የሚባል ሲሆን ከውሉ ጋር ተያያዥነት ያላቸው በርካታ ግዴታዎች ይመነጫሉ፡፡ ከእነዚህ ግዴታዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ዋናው እና የሁሉም ግዴታዎች መነሻ ሆኖ የሚያገለግለው አሰሪው ለተለያየ አገልግሎት የሚፈለገውን አንድ ግንባታ በውሉ እና በተሰጠው ንድፍ ወይም ዲዛይን መሰረት መገንባት ነው፡፡[7] ይህ የግንባታ ስራ በሚከናወንበት ጊዜ ተቋራጩ በውሉ የተመለከቱትን ስምምነቶች እና በሌሎች ተያያዥ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱትን ፍሬ ነገሮች በአግባቡ ማጥናትና ተግባር ላይ ማዋል አለበት፡፡ በተለይ የሚገነባውን ስራ በዝርዝር ለመግለፅ የውሉ አካል ሆነው የሚቀርቡ ሰነዶች ለምሳሌ ንድፍና እቅድ /design & plan/ የግንባታ እቃ እና የዋጋ ዝርዝር /bill of quantity/ እና ሌሎችም ሰነዶች በጥንቃቄ መታየት ይኖርባቸዋል፡፡ ተቋራጩ እነዚህን እና መሰል ሰነዶችን አይቶ ስራውን መገንዘብ እና በጥንቃቄ ስራ ላይ ማዋል ከውሉ ብቻ ሳይሆን ከሙያ ስነ ምግባሩም የሚመነጭ ግዴታ ነው፡፡ በተጨማሪም ከላይ በተመለከቱት ሰነዶች ውስጥ ግንባታውን አስመልክቶ የተሳተ

[7] ቢጫው መፅሀፍ ቁጥር 4(1), ገፅ 11

ስራ ወይም ሌላ ጉድለት/ህፀፅ/ ካለ የዚሁ ማረሚያ ትዕዛዝ በመሀንዲሱ እንደ አስፈላጊነቱ በጽሁፍ ሲሰጥ ተቀብሎ መፈጸም የተቋራጩ ግዴታ ነው፡፡ [8]

- የተቋራጩ ሌላው ግዴታ የተሰራውን ግንባታ (ህንፃ፣ መንገድ፣ ግድብ፣ ድልድይ ሌላም ሊሆን ይችላል) እና ስለ ግንባታ ስራው አስፈላጊውን መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሰነዶችን እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን አብሮ ለአሰሪው ማስረከብ ነው፡፡[9]
- የግንባታው እርክክብ ከተፈፀመ በኋላ በስራው ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን ወይም ብልሽቶችን ተከታትሎ ወይም በአሰሪው የተሰጡ አስተያየቶችን መሰረት በማድረግ አስፈላጊውን ጥገና በጊዜው ማድረግ የተቋራጩ ግዴታ ነው፡፡[10]
- አሰሪው የመጨረሻውን ስራ ከተረከበበት ጊዜ አንስቶ ባሉት 10 አመታት ውስጥ ለሚከሰቱ ጉድለቶች/እንከኖች/ ተቋራጩ ዋቢ መሆኑ በግንባታ ውል ውስጥ ሌላው መሰረታዊ ግዴታ ነው፡፡ [11]እነዚህ ዋና ዋና የተቋራጭ ግዴታዎች ሲሆኑ ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች በርካታ ዝርዝር ግዴታዎችን በውስጣቸው ታቅፈው ይገኛሉ፡፡

### 1.3.2.የአሠሪ ግዴታ፡-

አሰሪ የግንባታ ውልን ከተቋራጭ ጋር በመዋዋል ላሰበው አላማ የሚያውለውን ግንባታ ለማሰራት እቅድ ያለው ለዚህም እውን መሆን ገንዘብ እና የግንባታ ቦታ ከሌሎች አስፈላጊ ነገሮች ጋር አሟልቶ የሚንቀሳቀስ ሰው ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከተቋራጩ ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሰረት የግንባታ ስራው የጥራት ደረጃውን ጠብቆ እንዲሰራለት እና ለሚፈልገው አላማ ያውለው ዘንድ በእርሱ በኩል መሟላት ያለባቸው በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህን በማሟላት ረገድ አሰሪው በውል እና በህግ የሚጣሉበት ግዴታዎች እንዳሉ ግልፅ ነው፡፡ በዚህ ተዋዋይ ወገን ላይ የሚጣሉበት ዋና ዋና ግዴታዎች እንደሚከተለው ተመልክተዋል፡፡

-የአሰሪው የመጀመሪያ ግዴታ በውሉ የተመለከተው ግንባታ የሚያርፍበትን ቦታ መርጦ እና አመቻችቶ ከሚመለከተው ክፍል የወጣ ህጋዊ የግንባታ ፍቃድ አዘጋጅቶ ስራው መጀመር ካለበት ጊዜ አስቀድሞ ለተቋራጩ ማስረከብ ነው፡፡[12] ይህን ቦታ የተረከበ ተቋራጭ በቦታው ላይ

---

[8] ቀዩ መፅሀፍ ቁጥር 4,ገፅ 12
[9] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 4 ንዑስ ቁጥር 2
[10] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 4 ንዑስ ቁጥር 3
[11] ከፍ ብሎ በተራ ቁጥር 4 በተገለፀው አንቀፅ 3282(1) እና የሲቪል ግንባታ ስራዎች ቋሚ የውል መተዳደሪያ ደንቦች (ጠቅላላ የውል ሁኔታዎች) አንቀፅ 71(1)
[12] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 2, ገፅ 8

ስራውን ሰርቶ እስኪጨርስ ድረስ የይዞታ መብት ይኖረዋል። ይህም የግንባታ ቦታውን ከማፅዳት እና ዋናውን ግንባታ ፊዕሞ ለፕሮጀክቱ ባለቤት /ለአሰሪው/ እስኪያስረክብ ድረስ እንዲወጣ እና እንዲገባ ወይም ሌሎች ህጋዊ ስራዎችን እንዲያከናውን ያስችለዋል።

-የግንባታ ቦታው እርክክብ ከተከናወነ በኃላ ተቋራጩ ቦታውን ለማፅዳት እና ግንባታውን ለማከናወን የሚያጋጥሙትን ችግሮች በመቅረፍ እረገድ የአሰሪው ድጋፍ እና ተባባሪነት ያስፈልጋል። በመሆኑም ለስራው መጠናቀቅ አሰሪው እና እርሱን ወክለው ስራውን የሚያስተዳድሩ እና የሚቆጣጠሩ ሰዎች ተቋራጩን በፍፁም ቅንነት መደገፍ እና መተባበር አለባቸው።[13]

-ለስራው በውሉ የተመለከተውን ክፍያ በአማካሪ መሀንዲሱ የፀደቀው የክፍያ የምስክር ወረቀት ከመጠየቂያ ፎርሙ ጋር ተያይዞ በተቋራጩ ከቀረበበት ቀን አንስቶ ባሉት 28 ቀናት ውስጥ ከውሉ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ላይ በተመለከተው የአከፋፈል ስርዓት መሠረት የመክፈል ግዴታ አለበት።[14]ክፍያ ብዙ አይነት ሲሆን ከላይ በተመለከተው ግዴታ ውስጥ የሚካተቱት የትኞቹ ክፍያዎች ናቸው የሚለውን በተመለከተ ፈዲክ ባዘጋጀው የቢጫ መፅሐፍ ቁጥር 14 ስር ያሉትን የክፍያ አይነቶች መመልከት ተገቢ ነው።

-ሌላው የአሰሪ ግዴታ በተቋራጩ የተጠናቀቁ ስራዎችን ከሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች ጋር በውሉ በተመለከተው ጊዜ መረከብ እና አገልግሎት ላይ በማዋል በግንባታው ስራ ላይ የሚታዩትን ጉድለቶች በጊዜው ሪፖርት በማድረግ በተቋራጩ እንዲጠገኑ ማድረግ ነው።

### 1.3.3. የመሀንዲስ ግዴታ፡-

መሀንዲስ የሚባለው ስራውን ከዲዛይን ጀምሮ እስከ ግንባታው ፍፃሜ ድረስ በመከታተል ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን እና በጊዜው ተጠናቆ ለአሰሪው አገልግሎት እንዲውል ሙያዊ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት ነው። የመሀንዲሱ ዋና ኃላፊነት ለደንበኛው /ለአሰሪው/ የምህንድስና ሙያ አገልግሎት መስጠት በመሆኑ ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸው በርካታ ኃላፊነቶችን ይኖሩበታል። ዋና ዋናዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

የመሀንሲዱ የመጀመሪያና ዋና ኃላፊነት የአሰሪውን ፍላጎት በጥልቀት በመረዳት አሰሪው ለሚፈልገው አገልግሎት የሚውል የግንባታ፣ ንድፍ እና እቅድ /design and plan/ ማዘጋጀት ነው።መሀንዲሱ በአብዛኛው አርክቴክት ሲሆን ያለውን ጥበብ እና እውቀት ያለምንም መሰሰት

[13] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 2

[14] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 2(4) እና ቢጫው መፅሀፍ፣ ቁጥር 14

አውጥቶ በመጠቀም ወደ ፊት የሚገነባውን ህንፃ፣ መንገድ፣ ድልድይ፣ ወይም ሌላ መሠረተ ልማት ምስል ከነአገልግሎቱ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ንድፍ እና እቅድ ማዘጋጀት በተቋራጩ ለሚከናወነው ግንባታ መሠረት እና መሪ ነው፡፡ በመሆኑም ወደ ፊት በአካል ቆሞ የምናየው ህንፃ፣ ግድብ፣ መንገድ፣ ድልድይ እና ሌላ መሠረተ ልማት ከአሰሪው ወይም ከመሀንዲሱ አንዳንድ ጊዜም ከተቋራጩ አዕምሮ ፈልቆ በወረቀት ላይ የሚታየው በዚህ ባለሙያ አማካኝነት በመሆኑ ኃላፊነቱ ከባድ ነው፡፡

ሌላው ኃላፊነት በወረቀቱ ላይ የሰፈረው የግንባታ ስራ ሲሰራ የጥራት ደረጃውን ጠብቆ እንዲሰራ ቁጥጥር ማድረግ ነው፡፡ ይህ ስራ ጥራቱ የሚጠበቀው ስራ ላይ የሚውሉት ቁሳቁሶች ጥራት እና የባለሞያዎቹ ብቃት እና ችሎታ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ነገር ግን ቦታውን ለመስራት ጥቅም ላይ የሚውሉት የግንባታ እቃዎች ለምሳሌ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ድንጋይ፣ ሲሚንቶ፣ ብረታ ብረት እና ሌሎችም ጥራት ያላቸው ካልሆኑ በግንባታው ላይ ጉድለት መኖሩ አይቀሬ ነው፡፡ በመሆኑም መሀንዲሱ የእነዚህን የግንባታ እቃዎች የጥራት ደረጃ መፈተሽ እና ማረጋገጥ አለበት፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሊታይ የሚገባው የግንባታ ስራውን የሚያከናውነው ባለሞያ ብቃት እና ችሎታ ነው፡፡ ተቋራጩ የሚያሰማራቸው ሰራተኞች ብቃት እና ችሎታ ከሌላቸው ስራው በጥራት ሊሰራ ስለማይችል መሀንዲሱ የሰራተኞችን ስራ አይቶ ብቃት እና ችሎታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

መሀንዲሱ የስራውን ጥራት አይቶ ካረጋገጠ በኃላ በተቋራጩ የሚቀርብለትን የክፍያ ማመልከቻ ተመልክቶ የክፍያ የምስክር ወረቀት /Payment Certificate/ የማዘዝ ኃላፊነት አለበት፡፡ አሰሪው ክፍያ የሚፈፅመው እርሱን ተክቶ የግንባታ ስራውን የሚቆጣጠረውና የሚያስተዳድረው መሀንዲስ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በመሆኑ መሀንዲሱ በስራው ጥራት ሲተማመን በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ክፍያው እንዲፈፀም የቀረበለትን የክፍያ ማመልከቻ ማፅደቅ አለበት፡፡

በዚህ መልኩ ስራው በሚሰራበት ጊዜ በስራው ላይ ብልሽት /ጉድለት/ ካስተዋለ ስራው እንደገና እንዲሰራ ወይም የተሳተ ስራ ካለ ተጨማሪ ስራ እንዲሰራ መመሪያ /Variation Instruction/ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ ስራው ሲጠናቀቅ ለርክክብ ብቁ መሆኑን ማረጋገጥ እና ማረካከብም የመሀንዲሱ ኃላፊነት ነው፡፡

# 2. ከግንባታ ውል አመሰራረትና አፈፃፀም ጋር ተያይዞ አለመግባባት የሚፈጠሩባቸው አበይት ሁኔታዎች

## 2.1. ጨረታ

ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሕግ ሆኖ እንዲያገለግል በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ህግ አንቀፅ 1731 በግልፅ መደንገጉን ተከትሎ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነታቸው ይኸው ውጤት ያለው መሆኑን በውላቸው በግልጽ ያመለክታሉ፡፡ ውል እንዲህ አይነት ውጤት ይኖረው ዘንድ ሦስት መሠረታዊ ሁኔታዎችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡[15] መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ ሁኔታዎችም የተዋዋይ ወገኖች ችሎታ፣ ከስህተት፣ ከተንኮል እና ከማጭበርበር ነፃ የሆነ ፈቃድ፣ የውሉ ግዴታ ህጋዊነትና ተፈጻሚ መሆን እንዲሁም በህግ የተደነገገ የአፃፃፍ ስርዓት ካለ ይህንን ማሟላት ናቸው፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ሁኔታዎች ከተሟሉ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የውል ግዴታን ለማቋቋም የሚችል ስምምነት ይኖራል፡፡

ከላይ ከተገለፁት መሰረታዊ የውል መስፈርቶች መካከል አንዱ የሆነው ፈቃድ እንዴት ይገለፃል የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ነው፡፡ በግለሰቦች መካከል በሚደረግ ማንኛውም ውል የተለየ ህግ ከሌለ በቀር በማንኛውም መንገድ ሊገለፅ እና በተዋዋይ ወገኖች መካከል መግባባትን ሊፈጥር ይችላል፡፡ ቃል፣ ምልክት፣ ፅሑፍ ወይም ሌላ መንገድ የአንድን ተዋዋይ ወገን ፈቃድ ሊገልፁ የሚችሉ መንገዶች እንደሆኑ የበርካታ ምሁራን ፅሁፎች አስረጅዎች ናቸው፡፡[16]

የዚህ ፅሑፍ መነሻ ነጥብ የሆነው የግንባታ ውል በግለሰቦች፣ በሀገር ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም በመንግስታት ሊመሰረት ይችላል፡፡ በግለሰቦች መካከል የሚደረገው የግንባታ ውል እንደማንኛውም ውል ሁሉ ከላይ  በተጠቀሱት በአንዱ መንገድ ፈቃድ ሊገኝ ይችላል፡፡ ተዋዋይ ወገኖች በምልክት፣ በቃል፣ በፅሑፍ ወይም እነርሱ በመረጡት አመቺ መንገድ ፈቃዳቸውን ገልፀው ሀሳብ ለሀሳብ መግባባት ከቻሉ በመካከላቸው የውል ህግን ማቋቋም ይችላሉ፡፡ ድርጅቶችም እንደዚሁ በመመስረቻ ፅሑፋቸው፣ በመተዳደሪያ ደንባቸው ወይም በሌላ ልማዳዊ አሰራር ፈቃድ የሚገለፅበት መንገድ በግልፅ ካልተቀመጠ በቀር ከግለሰቦች ጋር ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጓቸውን ውሎች በተመለከተ ፈቃዳቸውን በሚያመቻቸው መንገድ ገልፀው ወደ ውል ግዴታ ሊገቡ ይችላሉ፡፡

[15] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4 እንደተገለጸው አንቀፅ 1678
[16] ጥላሁን ተሾመ የኢትዮጵያ የውል ሕግ መሠረት ሀሳቦች 2012፣ አዲስ አበባ፣ ገፅ 28-32

ሆኖም ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የአስተዳደር አካል ተዋዋይ ወገን የሆነበት የግንባታ ውል የሚገቡ በሆነ ጊዜ ሁለቱም ወገኖች ፈቃዳቸውን በፅሁፍ መግለፅ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም የአስተዳደር አካላት ተዋዋይ የሆኑባቸው ውሎች የአስተዳደር ውል በመባል የሚታወቁ ሲሆን በህግ የተገለፀ የውል የአፃፃፍ ስርዓት ስላላቸው ነው።[17] ግንባታ መንግስት መሠረተ ልማቶችን ለማሟላት ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣት በስፋት የሚያከናውነው ተግባር ሲሆን ይህ የግንባታ ዘርፍ በህግ እና በውል የሚመራ ነው። የግንባታ ስራዎችን የሚመለከቱ በርካታ ህጎች፣ ውሎች እና ሌሎች ቋሚ ደንቦች ወጥተው በመስኩ የላቀ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

የግንባታ ህጎች እና ውሎች የሚገዟቸው ውል ተኮር ተግባራት የውል አመሰራረት፣ አፈፃፀም እና ውል የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች ናቸው። ከግንባታ ውል አመሰራረት ጋር በተያያዘ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው የተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ መግለጫ አንዱ መንገድ ነው። የግንባታ ውል ከአስተዳደር ውሎች አንዱ በመሆኑ መንግስት መሰል ውሎችን ለመፈፀም የአገልግሎት ግዥ መፈፀም ይኖርበታል። መንግስት የአገልግሎት ግዥ የሚፈጽምባቸው መንገዶች ብዙ ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ግልፅ ጨረታ፣ ውሱን ጨረታ፣ በመወዳደሪያ ሃሳብ የሚፈፀም ግዥ፣ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ እና ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ የሚፈፀም ግዥ ናቸው። ከእነዚህ የግዥ ዘዴዎች ውስጥ በግንባታ ስራ ዘርፍ የሚያስፈልገውን አገልግሎት ለመግዛት በብዛት ስራ ላይ የሚውለው ግልፅ ጨረታ (Open biding or tenduring) ነው። በመንግሥት የግንባታ ውል አመሠራረት ሂደት ውስጥ አሠሪው መስሪያ ቤት ተቋራጮችን በግልፅ ጨረታ መጥራት ይኖርበታል። የኢፌድሪ የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649 አንቀፅ 35 (1) በግልፅ እንደሚያመለክተው የግልፅ ጨረታ አፈፃፀም በሀገሪቱ ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ የጫረታ ጥሪ መደረግ አለበት። እንደ አስፈላጊነቱም በብሄራዊ ሬድዬና ቴሌቭዥን ጣቢያዎች ሊነገር እንደሚችል የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (2) በግልፅ ይደነግጋል። ይህ የሚሆንበት ምክንያትም የተሻለ አቅም ያላቸውን አገልግሎት ሰጪዎች (እቃ አቅራቢዎች) ለማግኘት፣ እኩል የመረጃ ሥርጭትን ወይም ተደራሽነትን በመፍጠር ፍትሃዊነትን (fairness) ለማረጋገጥና ግልፅ የሆነ አሰራርን ለመዘርጋት ነው። በዚህ ጥሪ መሠረት የሚጫረቱ ተቋራጮች ያቀረቡትን የዋጋ ዝርዝር መሰረት በማድረግ አወዳዳሮ አሸናፊውን መለየት ጨረታ ያወጣው የመንግስት መስሪያ ቤት ኃላፊነት ነው። አሸናፊነቱ በደብዳቤ የተገለፀለት ተቋራጭም ውሉን ለመፈረም አስፈላጊ መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል። ይህ ሂደት ተቋራጮች እና

[17] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4 እንደተገለፀው አንቀፅ 1724፣ 3131

አሰሪዎች ለውል የሚያበቃቸውን ፈቃድ የሚሰጡበት ህጋዊ መንገድ ነው። ይህን መንገድ አልፎ የተመሠረተ የግንባታ ውል በህግ ፊት ያለው ተቀባይነት የሚያነጋግር አይሆንም። ሆኖም ለአፈፃፀሙ ዕርግጠኝነት ውሉ በዚህ መንገድ መፈረሙ ብቻውን ዋስትና ሊሆን አይችልም። ስለሆነም አሸናፊነቱ የተገለጸለት እና የውል ግዴታውን ለመግባት የተስማማው ወገን ለግዴታው አፈፃፀም ዋስትና ማቅረብ ግድ ይለዋል።

## 2.2. ዋስትና (Security)

በግንባታ ውል አፈፃፀም ሂደት ዋስትና ትልቅ ቦታ አለው። ውሉን የሚፈርሙ ተቋራጮች የግዴታቸውን አፈፃፀም ለማረጋገጥ ለአሰሪው ዋስትናን ይሰጣሉ። ዋስትና በውሉ ውስጥ ውል ተቀባይ ተብሎ የተሰየመ አንዱ ወገን የገባውን የውል ግዴታ ውል ሰጭ ተብሎ ለሚጠራው ሌላ ወገን በውሉ መሰረት እንደሚፈፀምለት ለማረጋገጥ የሚሰጠው ማረጋገጫ ወይም መድህን ነው። ለዚህ ግዴታ ማረጋገጫ የሚሆኑ በርካታ የዋስትና ዓይነቶች ሲኖሩ በመንግሥት ግንባታ ውል አስተዳደር ውስጥ የሚዘወተሩት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (bid bond)፣ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (performance bond)፣ የቅድሚያ ክፍያ ማረጋገጫ ዋስትና፣ በየደረጃው ከሚፈጸሙ ክፍያዎች ተቀናሽ እየተደረገ የሚያዝ ዋስትና (retention bond)፣ በስራው ላይ ለሚታዩ ጉድለቶች ዋቢ የሚሆን ዋስትና (maintainance or defects liability bond) ናቸው።

### 2.2.1. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (bidding bond)

ከዚህ በፊት ባለው ርዕስ ለመግለፅ እንደተሞከረው የግንባታ ስራን ማሰራት ያቀደ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቋራጮችን በጨረታ አወዳድሮ አሸናፊውን ከለየ በኃላ ወደ ውል እንዲገባ ጥሪ ያደርግለታል። የኢፌድሪ ሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 17/1997 አንቀፅ 212 የጨረታ ማስከበሪያ ማለት "አንድ የመንግስት መስሪያ ቤት በሚወጣ ጨረታ ሲሳተፍ ሀሳቡን ከገለፀ ወይም አሸናፊነቱ ከተገለፀለት በኃላ ጨረታውን ላለመተው የሚያስይዘው የገንዘብ ዋስትና ነው" ይላል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ጨረታ በአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት እቃ ወይም አገልግሎት ለመግዛት ለአቅራቢዎች የሚያደርገው ህዝባዊ ጥሪ ሲሆን ጥሪውን ተከትሎ በጨረታ የሚወዳደረው ሰው ብዙ ሊሆን ቢችልም አሸናፊው ግን አንድ ነው። በውድድሩ ለመሳተፍ ፈቃዳቸውን የሰጡ ተጫራቾች ከማሸነፋቸው በፊት ወይም ካሸነፉ በኋላ ራሳቸውን ቢያገሉ በአጫራቹ መስሪያ ቤት ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል። ስለዚህ አጫራቹን መስሪያ ቤት

ከዚህ ጉዳት ለመታደግ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተጫራቾቹ እንዲያስይዙ ህጉ ይህንን አሰራር መዘርጋቱ ፍቱን መድሃኒት ነው፡፡

በኢፌዲሪ የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ ተጫራቾች ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር የጨረታ ማስከበሪያ የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው መግለፅ አለባቸው ይላል፡፡[18] ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ጨረታን የሚያወጡ መስሪያ ቤቶች የጨረታ ሰነዱን በሚሸጡበት /ለተጫራቾች/ በሚሰጡበት ጊዜ በጨረታው መሳተፍ /መወዳደር/ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን የተወሰነ የገንዘብ መጠን አስቀድሞ ማስያዝ ያለበት መሆኑን መግለፅ ይኖርበታል፡፡ ይህ ግዴታ እንዳለበት የተገለፀለት ተጫራችም የጨረታ ሰነዱን ሲያስገባ የጨረታ ማስከበሪያውን አብሮ ማስገባት አለበት፡፡

ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ የጨረታ ተወዳዳሪ ወይም አሸናፊነቱ የተገለፀለት ተጫራች ሃሳቡን መቀየር ይችላል ወይስ አይችልም? ሃሳቡን ቀይሮ ከውድድሩ እራሱን ቢያገል ወይም አሸናፊነቱ ከተገለፀለት በኋላ ወደ ውል መግባቱን ቢተው ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለው ነው፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ከፍ ብሎ የተመለከተውን ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ 3 በጥሞና ማንበቡ ተገቢ ይሆናል፡፡ የጨረታ ማስከበሪያው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከውድድሩ ካገለለ ወይም አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት አሸናፊነቱ ከተገለፀለት በኋላ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ ወይም እንዲያቀርብ የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ ካላቀረበ የጨረታ ማስከበሪያው ውርስ ይደረጋል፡፡[19] በዚህ ድንጋጌ ጨረታ ተወዳዳሪው ወይም አሸናፊው እራሳቸውን ከውድድር ማግለል ወይም ያሸነፉበትን ውል አለመፈረም እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡ ከውድድሩ ራስን ማግለል ወይም ያሸነፉበትን ውል መተው የሚያስከትለውን ውጤት በተመለከተም ይኸው ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ይኸውም የጨረታ ተወዳዳሪው ወይም አሸናፊ የሆነ ሰው ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ እንዲመለስለት መጠየቅ አይችልም፡፡ የጨረታው ማስከበሪያ ገንዘብ በጨረታው (በውሉ) መቅረት ምክንያት በመንግስት መስሪያ ቤት ላይ ለደረሰው ጉዳት ማካካሻ ይሆናል፡፡ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ ሆኖ የውል ማስከበሪያ ያላቀረበ ተጫራችም እንደዚሁ የጨረታ ማስከበሪያ መጠየቂያውን ሊመለስ አይችልም፡፡ ከላይ በተመለከትናቸው

[18] የኢፌዲሪ የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2009፣ አንቀፅ 40/1/
[19] ዝኒ ከማሁ፣ ንዑስ-ቁጥር 3

ሶስቱ ምክንያቶች የሚከተለው ውጤት በጨረታ ማስከበሪያ ዋቢነት የተያዘው ገንዘብ በመንግስት መወረስ ነው።

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በኢትዮጵያ የፍትሕብሔር ህግ በአንቀፅ 3156 ላይ የተደነገገው የተለየ ዕንድምታን ይሰጠናል። ይኸውም ጨረታ ተወዳዳሪው የጨረታው ውጤት ከመገለጹ በፊት እራሱን ማግለል አይችልም፤ ይልቁንም የሚገደድበትን ጊዜ፣ ገደብ በጨረታ ሰነዱ ላይ ሊገልፅ ይችላል የሚል ነው። ይህ ድንጋጌ ከፍ ብሎ ከተመለከትነው ከአዋጁ መንፈስ ጋር የሚጣረስ ነው። ሆኖም አዋጁ የቅርብ ጊዜ ከመሆኑም በላይ ግዥን በተመለከተ ልዩ ህግ በመሆኑ ከፍትሕብሔር ህጉ ይልቅ ተፈፃሚነት ይኸው ህግ ነው።

በአጠቃላይ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ከግንባታ ውል ጋር መቆራኘት ካለባቸው ዋስትናዎች መካከል አንዱና ዋነኛው በመሆኑ አሰሪ መስሪያ ቤቶች ለውሉ መፈፀም የሚኖረውን ፋይዳ በማጤን ልዩ ትኩረት ሊያደርጉበት የሚገባው ነጥብ ነው።

### 2.2.2. የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና (performance bond)

የጨረታ አሸናፊ እንደሆነ የተገለፀለት ተቋራጭ ውል ሲፈርም ግዴታውን ተቀብሎ በውሉ መሠረት ለመፈፀም ከውል ሰጪው (ከአሰሪው) ጋር ስምምነት እያደረገ እንደሆነ ይታወቃል። ተቋራጭ ውሉን ከፈረመ በኃላ ውል ተቀባይ እየተባለ የሚጠራ ሲሆን ለገባው የውል ግዴታ አፈፃፀም ዋስትና ማስያዝ ግዴታው ነው። የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና (contract security or performance bond) የሚባለው ውል ተቀባይ በውሉ መሰረት ግዴታውን ለመፈፀም የገባውን ቃል ሳይፈፅም ቢቀር ውል ሰጪ በሆነው አሰሪ የመንግስት መስሪያ ቤት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመካስ የሚያስይዘው የዋስትና አይነት ነው።[20] ይህ ዋስትና ሁለት መሰረታዊ አላማዎች እንዳሉት ከትርጓሜው መገንዘብ ይቻላል። አንዱ እና ዋናው ጨረታውን አሸንፎ ከመንግስት መስሪያ ቤት ጋር ውል የገባው ተቋራጭ በውሉ እና በሌሎች ተያያዥ ሰነዶች ላይ የተመለከተውን ግዴታ በአግባቡ እንዲፈፀም ማስገደድ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ይህንን ግዴታ በተለያዩ ምክንያቶች ውል ተቀባይ ሳይፈፅም የቀረ እንደሆነ ስራው ባለመሰራቱ በውል ሰጪ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ውል ተቀባይ እንዲክስ ማድረግ ነው። የኢፌድሪ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅም "የውል ማስከበሪያ" በሚል ርዕሥ ይህን ጽንሳሳብ አካቷል። አዋጁ "... አቅራቢው በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ በመንግስት መስሪያ ቤቱ ላይ ለሚደርሰው

[20] የኢፌዲሪ ምኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 17/1997፣ አንቀፅ 2

ጉዳት ማካካሻ የሚውል የውል ማስከበሪያ ለባለበጀት መስሪያ ቤቱ መስጠት አለበት…" ይላል። ይህ ድንጋጌ ከፍ ብሎ ከተመለከትነው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ኃላፊነትን በውል ሰጪ (ተቋራጩ) ላይ ይጥላል። ተቋራጩ ውሉን ከፈረመ ግዴታውን በውሉ መሰረት መፈፀም አለያም ባለመፈፀሙ ምክንያት በውል ሰጪ ላይ የደረሰ ጉዳት ካለ መካስ ግዴታው ነው። ይህንን ይበልጥ ተፈፃሚ ለማድረግ ውል ሰጪ በቅድሚያ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ማስያዝ ይኖርበታል። ይህም አሰሪውን ሰዶ ከማሳደድ ያድነዋል።

የጨረታ አሸናፊው ጨረታ እንዳሸነፈ እና ውሉ የሚፈረምበት ቀን ከተገለጸለት ጊዜ አንስቶ ባሉበት 15 ቀናት ከጠቅላላ ዋጋው 10% ማስያዝ ይጠበቅበታል። ዋስትናው የሚያዘው በገንዘብ ወይም የግዥ ማስፈፀሚያ መመሪያው በገለፃቸው ሌሎች መንገዶች ሊሆን ይችላል። ውል ተቀባዩ በውሉ መሠረት ግዴታውን ካልፈፀመ ውሉን ካቋረጠበት ጊዜ አንስቶ በየቀኑ የሚታሰብ 0.01% ከተያዘው ገንዘብ ላይ ተቀናሽ እየሆነ ለውል ሰጭ ገቢ ይሆናል። ይህ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ እስኪያልቅ ድረስ ውል ተቀባይ ግዴታውን ካልፈፀመ በስተቀር ይቀጥላል። በዚህ መልኩ ቀጥሎ ውል ሰጭ መስሪያ ቤት ውል ተቀባይ በዋስትና ካስያዘው ገንዘብ መጠን በላይ ኪሳራ አድርሶበት ከሆነ መጠየቅ ይችላል። ሆኖም የተያዘው ገንዘብ ምንም ሳይነካ ወይም በከፊል እንደተቀነሰ ውል ተቀባይ ግዴታውን ከፈፀመ ውሉ ሲጠናቀቅ ቀሪው ገንዘብ ተመላሽ ይደረጋል። ግዴታውን ካልፈፀመ ግን ሌሎች ህጋዊ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለመልካም ስራ አፈፃፀም የተያዘውን የዋስትና ገንዘብ የተለየ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሌለ በቀር ውል ሰጪው እንደያዘ ያስቀረዋል።[21] በአስረጅነትም የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባ/ቱ/ና ፓርኮች ልማት ቢሮ እና በአምሳሉ ባዜ አለሙ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ መካከል በፋይል ቁጥር 109534 ተከፍቶ በነበረው ፋይል ላይ የሰጠውን ውሳኔ መመልከት ይቻላል። በአጠቃላይ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ውል ተቀባይ የገባውን ግዴታ በውሉ መሠረት እንዲፈፅም የሚያስገድድ እና ይህ ካልሆነ ደግሞ በውል ሰጪው ላይ የሚደርስበትን ጉዳት ለመካስ የሚቀርብ ዋስትና ነው። ይህ አይነቱ ዋስትና በግንባታ ውል አዘውትሮ የሚፈፀም በተቋራጭ እና በአሰሪው ዘንድ የሚታወቅ የዋስትና ዓይነት ነው።

[21] ይህ የሚሆነው ዋስትናው በገንዘብ በገንዘብ ለአሠሪው መስሪ ቤት ገቢ የሆነ እንደሆነ ነው። ከዚህ ውጪ ዋስትናው ሰነድ ወይም የንብረት እንደሆነ ግን መያዣ የሆነ ከሆነ ግን ጉዳዩን ለፍርድ ቤት በማቅረብ ማስወሰን ይጠይቃል።

### 2.2.3. የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና (advanced payement bond)

የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና በግንባታ ስራ ውስጥ ላልተሰራ ስራ ለሚፈፀም ክፍያ ዋስትና ሆኖ የሚያገለግል ነው። በአስተዳደር ውል ህግ ውስጥ ተቋራጩ ላልተሰራ ስራ ክፍያ መጠየቅ አይችልም፤ አሰሪውም ላልተሰራ ስራ ገንዘብ እንዲከፍል አይገደድም (the doctrine of exceptio non adimpleti contractus) የሚል መርህ በኢትዮጵያ የፍታብሔር ህግ ውስጥ ተካቷል።[22]

ሆኖም የኢፌዴሪ የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ከዚህ ጋር በሚቃረን መልኩ ጨረታውን አሸንፎ እና የውል ማስከበሪያ አስይዞ ውሉን በመፈረም ግዴታውን ለመፈፀም ዝግጁ ለሆነ አቅራቢ ወይም ተቋራጭ ቅድሚያ ክፍያ ሊሰጠው እንደሚገባ ይደነግጋል።[23] ይህም ተቋራጩ ወይም አቅራቢው የውል ግዴታውን ለመፈፀም የገንዘብ እጥረት ካለበት ስራውን ለመጀመር ስለሚቸገር ገዢው ወይም አሰሪው አስቀድሞ ከያዘው የአገልግሎት ወይም የስራ ግንባታ ዋጋ የተወሰነውን በመስጠት ስራው እንዲሳለጥ እገዛ የሚያደርግበት መንገድ ነው። ይህን ገንዘብ በቅድሚያ የሚወስደው አቅራቢ (ተቋራጭ) በሚወስደው ገንዘብ ልክ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንዲያስይዝ አሰሪው መጠየቅ አለበት።[24] ይህ ዋስትና ካልቀረበ አሰሪው ቅድሚያ ክፍያውን እንዲከፍል አይገደድም። በጠቅላላው የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና በቅድሚያ በአሰሪው የሚፈፀመውን ክፍያ በመውሰድ አቅራቢው (ተቋራጩ) የውል ግዴታውን መፈፀም እንደሚጀምር ለማረጋገጥ የሚያዝ ዋስትና ነው።

## 3. የመንግሥት ግንባታ ውል አፈፃፀም

### 3.1. የውል አፈፃፀም በጠቅላላው

ውል ከላይ በተመለከተው አኳኋን ከተመሰረተ በተዋዋይ ወገኖች ላይ የሚያስከትለው ውጤት እንዳለ እሙን ነው። ውጤቱም በውሉ አማካኝነት የተቋቋመውን (የተፈጠረውን) ግዴታ እንደ ውሉ መፈፀም ነው። ውል ህጋዊ ውጤት ያለው ተግባር እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዱ ተዋዋይ በውሉ የተጣለበትን ግዴታ መፈፀም ይገባዋል፤ ከውሉ የሚያገኘውንም ጥቅም መጠየቅ ይችላል። በውል የሚመሠረቱ ግዴታዎች አንድን ነገር ከማድረግ፣ ካለማድረግ ወይም ከማስረከብ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ውል መፈፀም ማለት በውሉ መሠረት ማድረግ ወይም ከማድረግ መቆጠብ ወይም በውሉ ላይ የተመለከተውን ዕቃ ማስረከብና ግዴታ የገባበትን

[22] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 3177
[23] አዋጅ ቁጥር 649/2009 አንቀፅ 48(1)
[24] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 48(2)

ንብረት ለሌላው ተዋዋይ በአካል ማስረከብና እንደነገሩ ሁኔታም የባለቤትነት ወይም የይዞታ መብቱን አብሮ ማስተላለፍ ወይም አገልግሎት መስጠት ነው።[25] በግንባታም ውልም ከላይ ከተዘረዘሩ ግዴታዎች መካከል አድርግ የተባሉትን ማድረግ አታድርግ የተባሉትን አለማድረግ እና ማስረከብ (Obligation to deliver) በዋናነት የሚፈፀሙ የውል ግዴታዎች ናቸው። በግንባታ ውል ተቋራጩ ሊያከናውን ውል የገባውን የግንባታ ስራ በውል በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ሰርቶ ማስረከብ ወይም ለግንባታ የሚያስፈልገውን እቃ ሊያስረክብ ውል ገብቶ ከሆነ በዚሁ መሠረት እቃውን በውሉ ላይ በተመለከተው ጊዜ እና ጥራት የማስረከብ ግዴታ ይኖርበታል። የግንባታ ውል ግዴታ አፈፃፀም ከላይ በተመለከቱት መሰረታዊ የውል መርሆዎች የሚገዛ ሲሆን በአፈፃፀም ወቅት የሚፈጠሩ ህፀፆች በውሉ እና በህግ አግባብ የሚፈቱ ናቸው።

በግንባታ ውል ግዴታ አፈፃፀም ወቅት አዘውትረው የሚፈጠሩ ህፀፆች (ጉድለቶች) ከስራ መዘግየትና መራዘም፣ በስራው (በዋጋ) ላይ በሚደረጉ ለውጦች፣ በስራው ላይ ከሚታዩ ጉድለቶች እና ከሚያስፈልጉ ጥገናዎች፣ ከስራ ርክክብ እና መድን እንዲሁም ከጉዳት ካሳና መቀጮ ጋር የተያያዙ ናቸው። እነዚህ ህፀፆች በግንባታ ውል ግዴታ አፈፃፀም ወቅት በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል ለሚፈጠረው ከፍተኛ አለመግባባት በመንስኤነት አዘውትረው ይጠቀሳሉ። ለስራው ጥራት መጓደል ምክንያት በመሆናቸው በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች መካከል ለሚፈጠረው ከፍተኛ አለመግባባት በመንስኤነት አዘውትረው ይጠቀሳሉ። ለስራው ጥራት መጓደል ምክንያት በመሆናቸው ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች በጉዳዮቹ ላይ የየራሳቸው ግዴታ እና ተጠያቂነት አለባቸው። በመሆኑም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የሀገራችን የውል ህጎች ምን እንደሚሉ እና በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚመሰረተው ውል በምን አግባብ ሊያስተናግዳቸው እንደሚገባ ወደፊት ባሉት ክፍሎች በአጭር በአጭሩ እንመለከታለን።

### 3.2. የግንባታ ስራው መዘግየት እና የጊዜ መራዘም (Delay and Extension of time)

በግንባታ ውል አሰሪ ከተቋራጭ ጋር በመስማማት በግልፅ ከሚያመለክታቸው ስምምነቶች መካከል አንዱ እና ዋናው ስራው የሚጠናቀቅበት ጊዜ ነው። አሰሪ የሚያሰራው ነገር ማለትም ት/ቤት፣ ሆስፒታል፣ ለቢሮ እና ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ህንፃዎች፣ መንገዶች፣ ድልድዮች፣ ግድቦችና ሌሎችም የግንባታ ስራዎች በተቻለ ፍጥነት አልቀው ለተፈለገው አገልግሎት ማዋል የአሰሪው (የውል ሰጪው) ዋና ፍላጎት እንደሆነ ይታወቃል። በመሆኑም አሰሪው በአማካሪ መሀንዲሱ አማካኝነት በንድፍ የተቀየሰው የግንባታ ስራ ሊጠናቀቅ

[25] ጥላሁን ተሾመ

የሚችልበትን ምክንያታዊ ጊዜ በውሉ ላይ ያስቀምጣል። ውል ተቀባይም ይህንኑ ጊዜ በመመልከት ተስማምቶ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ነፃ ፈቃድ ተቀባይነት ሲያገኝ የግዴታው ክፍል አካል ሆኖ እንደሚሰፍር ይታወቃል።

ይህ የውል ግዴታ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ተቀባይነት አግኝቶ የውሉ አካል ከሆነበት ጊዜ አንስቶ በመካከላቸው ህግ ሆኖ ያገለግላል። ጊዜን የተመለከተው ስምምነት መከበር ወይም ያለመከበር ጉዳይ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል ያለውን ግንኙነት ያለሰልሳል ወይም ያሻክራል። አሰሪው የሰጠው ስራ በውሉ ላይ በተመለከተው ጊዜ ተጠናቆ የሚረከብ ከሆነ የውሉ አላማ ያለምንም ውጣ ውረድ ተሳካ ማለት ነው።

በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል ያለውን ግንኙነት አስቸጋሪ የሚያደርገው የግንባታ ስራው አፈፃፀም በውሉ ላይ በተመለከተው ጊዜ ሊጠናቀቅ ያልቻለ እንደሆነ ነው። ይህንን ተከትሎ የግንባታ ስራው አፈፃፀም የተጓተተበት (የዘገየበት) ምክንያት፣ መዘግየቱ ሊያስከትለው የሚችለው አንድምታ (ውጤት)፣ ቀሪው ስራ ሊጠናቀቅ የሚችልበት ተጨማሪ ጊዜ አስጣጥ እና ሌሎችም ሁኔታዎች ህጋዊ መፍትሄን የሚሹ ናቸው።

በሀገራችን ብሎም በክልላችን ስራ ላይ ያለው የግንባታ ውል ህጎች የግንባታ ስራ የሚጀመርበት ጊዜ በተመለከተ በግልፅ ያስቀመጡት ጊዜ የለም። የውል ተዋዋይ ወገኖችን በውል ግዴታዎች ዝርዝር ላይ ያላቸውን የመወሰን ነፃነት ታሳቢ በማድረግ ውል ከተፈረመ በኋላ የግንባታ ስራው መጀመር ያለበትን ጊዜ በውላቸው እንዲወሰኑ በዝምታ ታልፏል ማለት ይቻላል። አለም አቀፍ የግንባታ ውሎች መሠረታዊ ሁኔታዎችን የያዘው መፅሀፍ በተ.ቁ. 8.1 ላይ የግንባታ ስራ ውሉ በተዋዋይ ወገኖች ከተፈረመበት ጊዜ አንስቶ (የአሸናፊነት ደብዳቤውን ከተቀበለበት ጊዜ አንስቶ) ባሉት 42 ቀናት መጀመር እንዳለበት እና ይህ ባይሆን አማካሪ መሀንዲሱ የ7 ቀን ማስጠንቀቂያ መስጠት እንዳለበት ያስገነዝባል። ከስራ መጀመሪያው ጊዜ አንስቶ ስራውን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ሳይዘገይ በተቻለ ፍጥነት ማከናወን እንዳለበት በዚሁ ቁጥር ስር ሰፍሮ ይነበባል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ስራው የሚጀመርበት ቀን አስቀድሞ መወሰኑ ተቋራጩ ስራውን ለመጀመር የሚያተጋው መሆኑን ነው። የስራው መጀመሪያ ጊዜ በውል አስቀድሞ ካልተወሰነ ወይም አማካሪ መሀንዲሱ ስራው መጀመር ያለበት ስለመሆኑ ከ7 ቀን ያላነሰ ማሳሰቢያ ካልሰጠ በተቋራጩ በኩል መዘናጋት ሊፈጠር እና በውሉ ላይ የተመለከተውን የስራ ማጠናቀቂያ ጊዜ ሊጋፋው ይችላል። ከዚሁ ድንጋጌ ልንገነዘብ የሚገባው ሌላው አብይ ጉዳይ ስራውን መጀመሩ ብቻውን በቂ አለመሆኑን ነው። ስራው ከተጀመረ በኃላ ሳይዘገይ

በተቻለ ፍጥነት ሊከናወን ይገባል። ከላይ የተመለከቱት ሁለት ተግባራት ማለትም የስራው መጀመር እና በጊዜው መከናወን ከውል አፈፃፀም መዘግየት (መጓተት) ጋር የተያያዙት ችግሮች እንዳይከሰቱ ያደርጋል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ አሰሪው የሚፈልገውን የግንባታ አይነት በጊዜው መረከብ ያልቻለ እንደሆነ ከዚህ በታች የተመለከቱት ውጤቶች ይከተላሉ።

የግንባታ መዘግየት በአሰሪው እና በተቋራጩ መካከል የነበረውን የውል ግንኙነት ሊለውጥ ይችላል። ግንባታው በጊዜው ካላለቀ ተቋራጭ የጊዜ ይራዘምልኝ ጥያቄ የማቅረቡ ጉዳይ የተለመደ ነው። በቀይም[26] ይሁን በቢጫ[27] አለምአቀፍ የግንባታ ስራ ስምምነቶች ላይ የስራው መዘግየት የውል ግዴታ መፈፀሚያ ጊዜ ይራዘምልኝ ጥያቄ ሊነሳ እንደሚችል እና አሰሪው በተስማማ ጊዜ ይኸው ከነውጤቱ ሊከሰት እንደሚችል ያመለክታሉ።[28] ይህ በማይፈፀምበት ጊዜ የግንባታ ውሉ በመሀንዲሱ ሊታገድ (Suspension) ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ስራው ለጊዜው ታግዶ የሚቆይ ሲሆን ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በሁኔታው ላይ መስማማት ከቻሉ በእነዚሁ ሰነዶች አንቀፅ 8 ንዑስ ቁጥር 12 መሠረት ስራው እንደገና ይጀመራል። ሥራው እንደገና ሲጀመርም ሆነ ሲቋረጥ የሚፈጠረው የሥራ መዘግየት ወይም መጓተት በአሠሪው ላይ የሚያደርሰው ጉዳት እንዳለ ግልጽ ነው። በመሆኑም መዘግየት ሊያስከትል የሚችለው ውጤት ቀጥሎ እንመለከታለን።

### 3.3. የመዘግየት ካሳ (Liquidated damage)

ከላይ እንደተመለከትነው የግንባታ ስራው መዘግየት የውል ግዴታው በጊዜው እንዳይፈፀም ሊያደርግ ስለሚችል ተቋራጩን እንደውሉ እንዳልፈፀመ ሊያስቆጥረው ይችላል። ይህንን ተከትሎ የውል ይራዘምልኝ ጥያቄ ለአሰሪው እንዲያቀርብ ይገደዳል። የመራዘሙ ጥያቄ በአሰሪው ተቀባይነትን ካገኘ በመጀመሪያው ውል ላይ የመሻሻል ውጤትን ስለሚያስከትል ሌሎች ተያያዥ ውጤቶች ላይከተሉ ይችላሉ። ይህ ካልሆነ ግን መዘግየትን ተከትሎ ከሚመጡ ነገሮች መካከል አንዱ የካሳ ጥያቄ ይሆናል። የሥራው መዘግየት አሰሪው የሚፈልገውን

[26] ቀዩ መፅሀፍ የሚባለው በአለም አቀፍ የግንባታ ውሎች አመሰራረት፣ አፈፃፀም እና ግጭት አፈታትን አስመልክቶ ተፈፃሚነት የሚኖራቸውን መሰረታዊ የውል መርሆዎች እንዲይዝ ተደርጎ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1999 በአሰሪዎች ተዘጋጅቶ FIDIC በተባለ አለም አቀፍ ማህበር ታትሞ በስራ ላይ የዋለ መፅሀፍ ነው።

[27] ቢጫው መፅሀፍ በመባል የሚታወቀው የልዩ ልዩ ግንባታ ዲዛይኖችን ማለትም የህንፃ፣ የመካኒካል እና የኤሌክትሪካል ዝርጋታን እንዲሁም ሌሎች የሲቪል ምህንድስና ስራዎችን የሚመለከቱ መሰረታዊ የውል መርሆዎችን አካቶ እንዲይዝ ተደርጎ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1999 በተቋራጮች ተነድፎ FIDIC እየተባለ በሚጠራ አለም አቀፍ ማህበር በአለም አቀፍ ግንባታ ውሎች በስፋት እየተተገበረ ያለ መፅሀፍ ነው።

[28] ቀዩ እና ቢጫ መፅሀፍ ቁጥር 8

ውጤት በውሉ ላይ በተመለከተው ጊዜ ባለመረከቡ የሚደርስበት ጉዳት መኖሩን ግምት ውስጥ በማስገባት አሰሪው እና ተቋራጩ በሚፈራረሟቸው ውሎች ውስጥ እልባት ከሚሰጧቸው ችግሮች መካከል በመዘግየት የሚከተለው ጉዳት ነው፡፡ ብዙዎቹ የሀገራችን ውሎች ተቋራጭ የግንባታ ስራውን በጊዜው ባለማጠናቀቁ ሊደርስ የሚችል ጉዳት ካለ በውሉ ላይ የተመለከተው ጠቅላላ ዋጋ 0.001% በየቀኑ ታስቦ በካሳነት ለአሰሪው እንደሚከፈለው ይደነግጋሉ፡፡ ይህም በብዙ ግንባታን የሚመለከቱ ፅሁፎች የመዘግየት ካሳ (Liquidated damage) ተብሎ ይታወቃል፡፡ ይህ አይነት ካሳ በኮመንሎው የህግ ስርዓት ተከታይ ሀገሮች አዘውትሮ ስራ ላይ የሚውል ቢሆንም አሁን አሁን እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የሲቪል ሎው ተከታይ ሀገሮች አገልግሎት ላይም እየዋለ ነው፡፡ በእርግጥ ይህንን የህግ ፅንሰ-ሀሳብ በስራ ላይ ለማዋል ኢትዮጵያ ያላት የህግ መሠረት ምንድን ነው ሲባል ምላሽ የማግኘቱ ጉዳይ ብዙ እርቀትን ይወስዳል፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ የግንባታ ውል የሚገዛባቸው የፍታብሔር ህግ እና ሌሎች አዋጆች ስለመዘግየት ካሳ (liquidated damage) በግልፅ የሚያሰፍሩት ድንጋጌ ስለሌለ ነው፡፡ የአስተዳደር የውል ህግ፣ የህንፃ ግንባታ አዋጅ እና ሌሎችም መሰል ህጎች አንዱ ተቋራጭ በውል የወሰደውን የግንባታ ስራ በሰዓቱ ባያጠናቅቅ እና ባያስረክብ አሰሪው ስራው በመዘግየቱ ሊደርስ የሚችልበትን ጉዳት ለማካካስ የሚወስደው እርምጃ የመዘግየት ካሳ ሊሆን እንደሚችል በግልፅ አልተመለከተም፡፡ ይህንን እንደመፍትሄ ለመውሰድ የህግ መሠረት ሆኖ የሚያገለግለው የሲቪል ግንባታ ስራዎች ቋሚ የውል መተዳደሪያ ደንቦች (ጠቅላላ የውል ሁኔታዎች) ሰነድ ነው፡፡ ሰነዱ አንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1994 “The Redbook” በሚል ርዕስ በFidic ተዘጋጅቶ በአለማቀፍ የግንባታ ስራ ውል ላይ በስፋት ሲተገበር የቆየ እና በኢትዮጵያም እንዳለ ተወስዶ የግንባታ የውል ህግ ሆኖ በስፋት በጥቅም ላይ የዋለ ነው፡፡ የዚህ ሰነድ አንቀፅ 47 የመዘግየት ካሳን አስቀምጧል፡፡ አንቀፁ የግንባታ ሥራ በውሉ በተመለከተው የማጠናቀቂያ ጊዜ ካልተፈፀመ በዘገየበት ቀን ቁጥር ከውሉ አጠቃላይ ዋጋ 1/1000ኛ ወይም 10% እየተቀነሰ ለአሰሪው መስሪያ ቤት በካሳ መልክ እንደሚከፈል እና ይህም በቀረው ሥራ ልክ መሠላት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በአተገባበር ወቅት ከዚህ ጋር በተያያዘ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሻክሩ እና ለክርክር መነሻ የሚሆኑ በርካታ ጥያቄዎች ይከሰታሉ፡፡ ለአብነትም ያህልም የመዘግየት ካሳ ክፍያ በተቋረጡ ውሎች ላይ ሊቀርብ ይችላልን? የመዘግየት ካሳ መጠን ስሌቱስ እንዴት ይሰራል? በምን ጉዳዮች ላይስ ጥያቄው ይቀርባል? የሚሉት ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ እና መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ ልዩ ልዩ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን እና አሰራሮችን በመርመር መወያየት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም በፌደራል

ጠ/ፍ/ቤት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ እና አለማየሁ ሰለሞን ህንፃ ስራ ተቋራጭ በፋይል ቁጥር 95407 ተከፍቶ በቆየው መዝገብ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መመልከት ይቻላል፡፡

### 3.4. የስራ ርክክብ እና መድን

የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ ተቋራጩ ለአሰሪው ማስረከብ ያለበት መሆኑ እውን ነው፡፡ የርክክቡ ሁኔታ እንዴት መሆን አለበት የሚለው ግን አነጋጋሪ በመሆኑ ከውል አልፎ በልዩ ልዩ ህጎች የራሱ የሆነ ቦታ ተሰጥቶት እናገኛለን፡፡ በኢትዮጵያ የፍታብሔር ህግ ከአንቀፅ 3274-3280 ያሉ ድንጋጌዎች የግንባታ ስራ እርክክብ አይነቶች እና ውጤታቸውን አስመልክቶ ዘርዘር ያለ ድንጋጌን ይዞ እናገኛለን፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ርክክብ በሁለት አይነት መንገድ ሊከናወን ይችላል፡፡ የመጀመሪያው ስራው ተሰርቶ እንዳለቀ አሰሪው የስራውን ጥራት ለመመርመር እና ለማረጋገጥ ይችል ዘንድ ለጊዜው ግንባታውን የሚረከብበት መንገድ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የፍታብሔር ህግ አንቀፅ 3274(1)" ለጊዜው የሆነ ርክክብ ማለት ስራዎቹ ተሰርተው ካበቁ በኋላ ወዲያውን ሁለቱ ወገኖች ባሉበት በስራው ላይ የሚደረግ የምርመራ ማረጋገጫ ነው በማለት ለጊዜው የሚደረግ ርክክብን ይደነግጋል፡፡ ይህ የርክክብ አይነት ግንባታውን ከተቋራጭ ይዞታ ወደ አሰሪው እጅ የሚዘዋወርበት እና የስራው ትክክለኛነት የሚረጋገጥበት ነው፡፡[29] ይህ ሁኔታ ተቋራጩን ለስራው ብልሽት ተጠያቂ ከመሆን አያድነውም፡፡ በስራው ጥራት ሁኔታ ላይ ጉድለት የተስተዋለ እንደሆነ ተቋራጩ ለዚህ ጉድለት ርክክቡን መድን አድርጎ ሊያነሳ ወይም ሊከራከር አይችልም፡፡ ነገር ግን ጊዜያዊ ርክክቡ በሚደረግበት ጊዜ የሥራ ዐቅድ ተለውጦ የተከናወኑ ስራዎችን አሰሪው በዝምታ ያለፋቸው እንደሆነ እንደተቀበላቸው ተቆጥሮ ተቋራጩ እንደ መከራከሪያ ሊያነሳው ይችላል፡፡ በጥቅሉ ጊዜያዊ ርክክብ ተቋራጩ የስራውን ጥራት ለማረጋገጥ የሚሰጠው ጊዜ በመሆኑ በዚህ ወቅት የተስተዋሉ የጥራት ጉድለቶችን (የሥራ ብልሽቶችን) በመፈተሽ በተቋራጩ በኩል ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የማዘዝ ስልጣን አሰሪው ይኖረዋል፡፡ ለዚህም ተቋራጩ ዋቢ ነው፡፡[30] ይህ የጊዜያዊ ርክክብ ጊዜው እንደተጠናቀቀ ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች በተገኙበት የመጨረሻው ርክክብ ይደረጋል፡፡[31] አሁንም ልብ ሊባል የሚገባው ነገር የመጨረሻ ርክክብ መደረጉ በግንባታ ስራው ላይ ለሚታዩ ጉድለቶች የተቋራጩ ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ቀሪ አለመሆኑን ነው፡፡

[29] የፍታብሔር ህግ አንቀፅ 3274/2/
[30] ዝኪስማሁ አንቀፅ 3277
[31] ዝኪስማሁ አንቀፅ 3279

የመልካም ስራ አያያዝ ግዴታው ቀሪ ሆኖ የቀረው ክፍያ እንደሚፈፀምለት በፍታብሄር ህግ አንቀፅ 3281 ላይ ቢደነገግም ግንባታው ለተፈለገው አገልግሎት (አላማ) እንዲውል የሚያደርጉ የአሰራር ጉድለቶች ካሉ የመጨረሻው ርክክብ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ለ10 አመት ተቋራጩ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ይህ ኃላፊነት በመጨረሻው ርክክብ ጊዜ የሚስተዋሉ የስራ ጉድለቶችን አይጨምርም፡፡ በአጠቃላይ ግንባታው ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር ከጥራት ጉድለት የፀዳ እና ለተፈለገው አላማ መዋል የሚችል ይሆን ዘንድ ተቋራጩ ሙሉ ኃላፊነት ስላለበት ለጉድለቶቹ ኃላፊ ወይም ተጠያቂ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚነሳው ጥያቄ የኃላፊነት መጠኑ ምን ያህል ነው የሚል ነው፡፡ አንዳንድ ምሁራን የተቋራጩ ስህተት መሠረታዊ ሆኖ የግንባታው ጥራት ለታለመለት አገልግሎት ከማዋል የሚከለክል ከሆነ ስራው ሙሉ በሙሉ ውድቅ ሆኖ ተቋራጩ መሰናበት አለበት ይላሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የስህተቱ ክብደት እና የደረሰው ጉዳት ግምት ውስጥ ሳይገባ ተቋራጩ በግንባታ ስራው ላይ ያሳየው ጉድለት ካለ ስራው ተቋርጦ ውሉ መፍረስ አለበት ይላሉ፡፡ የሆነ ሆኖ ከሁለቱ የህግ ፍልስፍና (አስተሳሰብ) መስመሮች ውስጥ በግንባታ ስራ የውል ህጎች ላይ ተካቶ በስፋት እየተተገበረ ያለው የመጀመሪያው እንደሆነ ልብ ማለት ያሻል፡፡

### 3.5. የለውጥ ሥራ (Variation)

በግንባታ ሥራ ውል አስተዳደር ውስጥ ላለመግባባት እና ለስራ መጓተት መንስኤ ከሚሆኑት ውስጥ አንዱና ዋናው የለውጥ ስራ (Variation) ነው፡፡ የለውጥ ስራ የሚባለው በውሉ በተገለፀው የግንባታ ሥራ ብዛት፣ ጥራት ወይም አይነት ወይም ተጨማሪ ሥራ በመስራት ግንባታው የሚከናወንበትን አላማ ይበልጥ ለማሳካት አስፈላጊ እንደሆነ በመሀንዲሱ (በአማካሪው) ሲታመንበት የሚታዘዝ የማሻሻያ (ተጨማሪ) ሥራ ነው፡፡ ለዚህ ምክንያት የሚሆኑ የሥራ አይነቶች በግንባታ ሥራ ቋሚ ደንቦች (Standard Condition for contract of civil works) በሚለው ሰነድ በአንቀፅ 51 ሥር የተዘረዘሩ ሲሆኑ እነዚህም፡-

- በግንባታ ሥራው መጠን ላይ የሚጨመር (የሚቀነስ) ሥራ
- አላስፈላጊ ሥራዎችን የማስወጣት (የማስወገድ) ሥራ
- የግንባታ ሥራውን ባህሪ (አይነት) ጥራት ለመለወጥ የሚጠይቅ ሥራ
- የግንባታ ሥራውን ከፍታ ወይም መስመር ወይም አቅጣጫ ለመለወጥ የሚጠይቅ ሥራ
- ሥራውን ለማጠናቀቅ እና ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልግ ተጨማሪ ሥራ እና

- **ተጨማሪ ሥራ መስራት አስፈላጊ ሆኖ ይህ** ተጨማሪ ሥራው ካልተሰራ ግንባታውን ዋጋ የሚያሳጣ ሁኔታ መኖር ነው፡፡

እነዚህ ሁኔታዎች በመሀንዲሱ ከታመነባቸው እንደ አዲስ ስራ ተቆጥረው በመሀንዲሱ ትዕዛዝ ለውጥ ሊደረግ ይችላል፡፡ የኢትዮጵያ የፍታብሄር ህግ አንቀፅ 3284-3286 በግንባታ ሥራ ውስጥ አዲስ ስራ ከተከሰተ ለውጥ ሊታዘዝ እንደሚችል በመርህ ደረጃ ከግንባታ ሥራ ቋሚ ደንቦች ጋር የሚመሳሰል ድንጋጌን አስፍሯል፡፡ አንቀፅ 3284 (1) "የአስተዳደር መሥሪያ ቤት በውሉ ውስጥ ያልተመለከቱትን ስራዎች በአንዱ አዲስ በሆነ ዋጋ እንዲሰራው ስራ ተቋራጩን ለማዘዝ ይችላል" በዚህ ድንጋጌ በውሉ ያልተካተተ የሚለው ሀረግ ስራው አዲስ መሆኑን ወይም ተዋዋይ ወገኖች ውሉን በሚፈራረሙበት ጊዜ ያላሰቡት እና በውሉ ያላካተቱት መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡ በተለይ በድንጋጌው ርዕስ ሆኖ ከተቀመጠው "ስለ አዳዲስ ስራዎች" ከሚለው ሀረግ ጋር ሲገናዘብ ይህንን ሀሳብ ይበልጥ ያጠናክራል፡፡ ስለሆነም አዳዲስ ስራዎች (በውሉ ያልተካተቱት ስራዎች) በሚያጋጥሙ ጊዜ አስተዳደር መሥሪያ ቤቱ ተቋራጩን ተጨማሪ ስራ፣ ማሻሻያ ወይም የለውጥ ስራ እንዲሰራ ሊያዘው እንደሚችል ህጉ የፈቀደ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁን እንጅ በውሉ ያልተካተቱ (አዳዲስ ስራዎች) የሚለው ሀረግ በጥንቃቄ መተርጎም ይኖርበታል፡፡ "አዳዲስ ስራዎች" የሚለው ሀረግ ጠበብ ባለመንገድ ካልተተረጎመ በቀር ከውሉ አላማ ውጭ ያሉትን ተጨማሪ (አዳዲስ ሥራዎች) ሁሉ ሊያካትት ይችላል፡፡ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ወይም መሀንዲሱ አዳዲስ ስራዎች የሚለውን ሀረግ ከውሉ አላማ አንፃር ካልተረዱት አዳዲስ ተጨማሪ ሥራዎችን በትዕዛዝ ሊያሰሩ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ የውሉን መንፈስ ባለመረዳት የውል ግዴታውን በተቋራጩ ላይ ሊያከብዱበት ይችላሉ፡፡ ተቋራጩም ከእንዲህ አይነቱ የከበደ ግዴታ ወይም በውል ከተመለከተው ግዴታ ውጭ እንዲሰራ እንዳይገደድ የዚሁ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 2 እና 3 በግልፅ ክልከላን ያስቀምጣሉ፡፡ ይህ "ቢሆንም መሥሪያ ቤቱ በውሉ ከተመለከተው ስራ ፍፁም ልዩ የሆነና ወይም ከዚሁ ሥራ ጋር ግንኙነት የሌለውን ሥራ እንዲሰራ ሥራ ተቋራጩን ሊያዘው አይችልም" በሚል መልኩ ተቀምጧል፡፡ ስለዚህ በውሉ ላይ ከተመለከተው ስራ ፍፁም የተለየ ወይም ግንኙነት የሌለውን ሥራ በለውጥ ስራ ስም ማሰራት ህጉ አይፈቅድም፡፡

ሌላው ከስራ ለውጥ ጋር በተያያዘ የሚነሳው አብይ ነጥብ የለውጥ ስራው መጠን ነው፡፡ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ (አሰሪው) በስራው ላይ የሚያደርገው ለውጥ ካልተወሰነ በቀር አሰሪው

ከልክ ያለፈ የስራ ለውጥን እያደረገ በተቋራጩ መብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖን ሊያሳድር ይችላል። ይህንን ታሳቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ፍታብሔር ህግ የለውጥ መጠኑን የሚወሰን ድንጋጌ አስፍሯል። አንቀፅ 3285(1) "ከአስተዳደር መ/ቤቱ የታዘዙት የስራዎች መጨመር ወይም መጉደል በውሉ ከታሰበው ስራ ከስድስቱ እጅ በላይ የሆነ ልዩነት ያስከተለ እንደሆነ ተቃራኒ የሆነ የውል ቃል ካልኖረ በቀር ስራ ተቋራጩ ውሉን ለማፍረስ መብት አለው" ይላል ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው የተለየ የውል ስምምነት ከሌለ በቀር ከጠቅላላ ስራው ስድስት እጅ ድረስ የስራ ለውጥ ትዕዛዝ ሊሰጥበት እንደሚችል ነው። የተለየ ስምምነት ካለ ግን ከስድስት እጅ በላይ የለውጥ ስራ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል። እዚህ ላይ አነጋጋሪ የሚሆነው (ስድስት እጅ) የሚለው ሀረግ መነሻ የሚያደርገው የትኛውን ቁጥር ነው የሚለው ነው። ከዚህ በመነሳት ከስምንቱ ስድስቱ እጅ ነው ወይስ ከአስሩ እጅ አሊያስ ሌላ የሚለው ጥያቄ በህጉ መልስ ያልተሰጠው በመሆኑ አሻሚነቱ አያከራክርም።

ነገር ግን ከላይ ከሰጠናቸው መነሻ ቁጥሮች አንፃር ማለትም ከስምንቱ ስድስቱ እጅ ከአስሩ ስድስቱ እጅ የለውጥ ስራ ሊሆን እንደሚችል ብናስብና ከመቶ ብናሰላው ሰማንያ እና ስልሳ ፐርሰንት እንደቅደም ተከተላቸው በለውጥ ስራ ሊሸፈን ይችላል። ይህም ከጠቅላላ ስራው አብዛኛው በለውጥ ስራ መሸፈኑን ያሳያል። ይህ ደግሞ ለተቋራጩ ውሉን ለማፍረስ እንደምክንያት ሊወሰድ ይችላል። ስለዚህ ስድስቱ የሚለው ሀረግ በእርግጥ ትክክለኛ ነውን? ከሆነስ ከስንት ይሰላል የሚሉት ጥያቄዎች በህጉ ውስጥ አነጋጋሪ እና በተግባር መልስ ለማግኘት የሚያስቸግሩ ናቸው። ስነሆነም ከለውጥ ስራ መጠን ጋር በተያያዘ ለተነሱ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ለማግኘት የዚህን ድንጋጌ የእንግሊዝኛ ቅጅ እና ሌሎች ህጎችንም መመልከቱ ተገቢ ይሆናል። የድንጋጌው የእንግሊዝኛ ቅጅ "unless otherwise provided in the contract, the contractor may cancel the contract where the increase or reduction of the works as a whole required by the administrative authorities involves a variation of more than one-sixth of the cost mentioned in the contract" ይላል። ይህ ድንጋጌ ከጠቅላላ ስራው ዋጋ ከአንድ ስድስተኛ በላይ የለውጥ ትዕዛዝ መጠኑ ካልበለጠ በቀር ትዕዛዙ ህጋዊ እንደሆነ እና ተቀባይነት እንዳለው ያስገነዝባል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 16.6 በመቶ ድረስ የስራ ለውጥ ማድረግ የተፈቀደ እንደሆነ ከቅጅው መገንዘብ ይቻላል። ሆኖም በእንግሊዝኛው እና በአማርኛው ቅጅ መካከል መጣረስ ወይም ልዩነት ከተፈጠረ የአማርኛው ቅጅ ተፈፃሚ እንዲሆን የሚደነግገው ህግ ይህን እንዳለ ተግባራዊ እንዳይሆን ስለሚከለክል የዚህን ትክክለኛ አተረጓጎም ለማግኘት ሌሎች ህጎችንም መፈተሽ ተገቢ ይሆናል። ለጥያቄዎቹ ትክክለኛ መልስ ለማግኘት ተገቢነት ያላቸው ህጎች

የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2009 እና ይህንኑ ለማስፈፀም የወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያ ናቸው። በተለይ የግዥ መመሪያው በለውጥ ስራ ሊሸፈን የሚችለውን መጠን በግልፅ ያመለከተ እና በተግባርም እየተፈፀመ በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው። የመመሪያው አንቀፅ 25 ንዑስ ቁጥር 3 የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2009 አንቀፅ 25 ንዑስ አንቀፅ 1(ሐ)ን መነሻ በማድረግ ተጨማሪ የግንባታ ሥራ ሊታዘዝ የሚችለው የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው የተገኙ እንደሆነ ነው።

የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ ከስራው ጋር የተገናኘ ሲሆን ይኸውም "የመንግስት መስሪያ ቤቱ በተጨማሪነት እንዲሰሩ የታሰቡት ስራዎች በመጀመሪያው ውል ውስጥ መካተት ይገባቸው የነበሩ እና ስራዎቹን ነጣጥሎ ማሰራት ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ወይም የመስሪያ ቤቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።" ስራው በውሉ ውስጥ መገለፅ ሲገባው የተዘለለ ወይም የታለፈ እንደሆነ ውሉን በማሻሻል ተጨማሪ የግንባታ ስራ ማዘዝ ቀላል እና የተለመደ ቢሆንም ይህ ከመፈፀሙ በፊት ስራው ተነጥሎ (ለብቻው) ሊሰራ የማይችል መሆኑን የሚቻል ቢሆን እንኳ በአሰሪው ላይ መሠረታዊ የሆነ የኢኮኖሚ የጥቅም ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህ ሁኔታ የሚረጋገጠው በመሀንዲስ ሲሆን ሁኔታው እንደተረጋገጠ ተጨማሪ የግንባታ ስራ ትዕዛዝ በማሰራት የተጓለውን ማሟላት ይቻላል። ሆኖም የተጨማሪ ስራ ዋጋው በመጀመሪያ ውሉ ላይ ከተመለከተው የግንባታ ዋጋ ከ30% በላይ መብለጥ የለበትም።[32] ይህ ከፍ ብሎ ላነሳናቸው ከተጨማሪ የግንባታ ስራ መጠን ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች መልስ ሊሰጥ የሚችል ነው።

በአጠቃላይ የለውጥ ስራ ትዕዛዝ ያነሰን ለመጨመር፣ የበዛን ለመቀነስ፣ የጎደለን ለማሟላት የሚያግዝ ወሳኝ የግንባታ ስራ ውል ማሻሻያ መንገድ ቢሆንም የጠቀሜታውን ያህል ጉዳትም ስለሚያስከትል የግንባታ የውል ህግ እና ሌሎች ጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጥንቃቄ ማስተዳደሩ ተገቢ ነው።

## 4. በግንባታ የውል አስተዳደር ሂደት የሚያጋጥሙ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያገለግሉ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች በኢትዮጵያ የሕግ ማዕቀፍ

### 4.1. ስለአማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች ጠቅላላ ሁኔታ

[32] መመሪያ ቁጥር 649/2009 አንቀፅ 25/3/ለ

ቀደም ሲል በተመለከትናቸው የፅሁፉ ክፍሎች የግንባታ ውልን ምንነት እና አጠቃላይ ገፅታ እንዲሁም ለክርክር መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ችግሮች ምን እንደሆኑ ለይተን አግባብነት ካላቸው ህጎች አንፃር ተመልክተናል፡፡ በዚህ አግባብ በሀገራችን በተለይም በአማራ ክልል በግንባታ ሥራ ውስጥ ለክርክር መንስኤ የሚሆኑ ዋና ዋና ጉዳዮች የስራው መዘግየት እና የጊዜ መራዘም፣ የለውጥ ሥራ፣ በስራው ላይ የሚታዩ ጉድለቶችና የሚያስፈልጉ ጥገናዎች፣ የስራ ርክክብና መድን እና የጉዳት ካሳ ናቸው፡፡

እነዚህ ችግሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ባለጉዳዮች ችግሮቹን ለመፍታት አዘውትረው የሚጠቀሙት በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚካሄድ ክርክርን (Litigation) ነው፡፡ ይህ አይነቱ ምርጫ ጊዜና ጉልበትን የሚፈጅ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ እና ብዙ ውጣ-ውረዶች ያሉበት በመሆኑ ባለጉዳዮቹ ለችግራቸው እልባት ለማግኘት የሚያልፉበት ሥነ-ሥርዓት “ከወረቱ ስንቁ ልቆ” እንደሚባለው ይሆናል፡፡ በሌላ አነጋገር ችግሮቹን ለመፍታት የመደበኛ ክርክርን መምረጥ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፡፡

አሁን አሁን ብዙ ምሁራን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ክርክር ባሻገር አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶችን መጠቀሙ የተፋጠነ ፍትህ ለማግኘት ቀላል እና ወጪ ቆጣቢ እንደሆነ ያስምሩበታል፡፡ አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት ከመደበኛ ክርክር ውጭ ያጋጠማቸውን ችግሮች ለመፍታት ባለጉዳዮች የሚገለገሉባቸው ስልቶች ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹም ድርድር (Negotiation)፣ ማግባባት (Mediation)፣ እርቅ (Concilation) እና የግልግል ዳኝነት (Arbitration) ናቸው፡፡ እነዚህ አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶች በልዩ ልዩ መስኮች ተግባራዊ እንደሚሆኑ እውቅና በመስጠት ልዩ ልዩ ህግጋት የመደበኛ ክርክር አማራጭ ሆነው እንደሚያገለግሉ በመደንገግ ባለጉዳዮች ያጋጠማቸውን አለመግባባት ለመፍታት እንደ አማራጭ ዘዴ አድርገው ይጠቀሙባቸው ዘንድ ህግ ዋስትና ሰጥቶ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ፡- በሀገራችን የአሰሪና ሰራተኛ ህግ፣[33] የቤተሰብ ህግ፣[34] የግንባታ ውል ቋሚ ደንቦች፣[35] የፍታብሔር[36] እና የፍትሃ-ብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ[37] እንዲሁም ሌሎች ልዩ ልዩ አዋጆች አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶችን በተመለከተ በርካታ ድንጋጌዎችን አካተዋል፡፡ ሥለሆነም በሚቀጥሉት የዚህ

[33] የአ.ሠ.ህ.አ.ቁ 377/96 አንጽ 141-143
[34] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 6ኛ ዓመት ልዩ ፅትም አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀፅ 118-123
[35] ከፍ ሲል በቁጥር 7 ሥር በተገለጸው መመሪያ አንቀፅ 67
[36] ከፍ ሲል በተራ ቁጥር 4 ስር በተገለፀው አንቀፅ 3307-3345
[37] የኢትዮጵያ ፍትሃብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ 274-277 እና 315- 320 እና 352-357

ዕሁፍ ክፍሎች የእያንዳንዱን የአማራጭ ሙግት መፍቻ ሥርዓት ዕንሰ-ሀሳብ እና አተገባበር አግባብነት ባላቸው ልዩ ልዩ ህጎች አንፃር በአጭር በአጭሩ እንመለከታለን፡፡

## 4.2 ድርድር

ድርድር አለመግባባትን ለመፍታት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በስፋት አገልግሎት ላይ የሚውል ታዋቂ ስልት ቢሆንም በዕንሰ-ሃሳቡ ላይ የተለያዩ ነገር ግን ተቀራራቢነት ያላቸው ሀሳቦች ይንፀባረቃሉ፡፡ የተለያዩ ምሁራን ድርድርን ለማብራራት የተለያየ ሃሳብ ቢሰጡም በመሰረተ ሃሳቡ ላይ ተመሳሳይነት ይስተዋላል፡፡ በመሆኑም ለዚህ ዕሁፍ አላማ የሚከተለውን የድርድር ትርጉም መውሰዱ የተሻለ እንደሆነ የዕሁፉ አብራሪ ያምናል፡፡

ድርድር ማለት አለመግባባትን ለመፍታት ባለጉዳዮች ገፅ ለገፅ ተገናኝተው ያለ ሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ስለችግራቸው የሚነጋገሩበት፣ የሚወያዩበት ወይም ቃል የሚገቡበት ሂደት ነው፡፡[38] በዚህ ትርጉም መሠረት ድርድር በባለጉዳዮች መካከል መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ሊካሄድ ይችላል፡፡ ድርድሩ አላማ የሚያደርገው ግን የተፈጠረን አለመግባባት ያለምንም ውጣውረድ በአጭር ጊዜ እና ወጪን ሳይጠይቅ መፍታትን ነው፡፡ ባለጉዳዮቹ ያለማንም ጣልቃ ገብነት እርስ በርሳቸው በመነጋገር ለችግራቸው መፍትሄ የሚሹበት ሂደት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር ድርድር በባህሪው አሸማጋይ ወይም አስታራቂ አይፈልግም፡፡ በመሆኑም ድርድር በሚከናወንበት ጊዜ አንደኛውን ወገን ወግኖ የሚሞግት ወይም ገለልተኛ ሆኖ ዳኝነት የሚሰጥ ሰው አይኖርም፡፡ ተደራዳሪ ወገኖች ሙያዊ እገዛ የሚያሻቸው በሆነ ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ ከተገቢው ባለሙያ እገዛ መጠየቅ አይከለከሉም፡፡ ለምሳሌ፡- በግንባታ ውል አፈፃፀም ወቅት የተፈጠረ አለመግባባትን ለመፍታት የግንባታ ዘርፍ ውስብስብ እንደመሆኑ መጠን ልዩ ልዩ የሙያ ድጋፍ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ያላቸውን እውቀት እና ክህሎት መለገስ ለችግሩ መቃለል አይነተኛ ሚና ስለሚኖረው በቀጥታ በድርድሩ ባይሳተፉም ከጀርባ በመሆን ለችግሩ መፈታት አስፈላጊውን ድጋፍ ለተደራዳሪዎች ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ይህ ማለት ግን እነዚህ ባለሙያዎች የተደራዳሪነት ሚና ተሰጧቸዋል ማለት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

ተደራዳሪዎች በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ፊት ለፊት በመገናኘት መደበኛ በሆነ መንገድ ወይም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሲወያዩ እራሳቸው በቀጥታ የሚያውቁትን እና ከባለሙያ ያገኙትን

[38] Goldberg, Stephen etal,"Dispute Resolution, Negotiation, Mediation and other processes, 1992

መረጃ ሲለዋወጡ መሠረታዊ የሆኑ የድርድር ስልቶችን መጠቀሙ ለድርድሩ ስኬታማነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ውጤታማ ድርድር በማድረግ ተደማጭነት እና ተቀባይነት ለማግኘት የሚያቅድ ተደራዳሪ የድርድር ሀሳቡ በመርህ ላይ የተመሰረተ፣ አቋሙን በግልፅ የሚያሳይ እና ገቢራዊ (ተፈፃሚ) ሊሆን የሚችል መሆን አለበት። እነዚህን ባህሪያት የተላበሰ የድርድር ሀሳብ የሚያራምድ ተደራዳሪ ሌላኛውን ወገን የማሳመን አቅም እና ችሎታ ስለሚኖረው ድርድሩ ወይም ውይይቱ ፍሬያማ የመሆን እድሉ ከፍ ያለ ነው። በዚህ መልክ የተከናወነ ድርድር የሚያስገኘው ውጤት ምን ሊሆን ይችላል የሚለው ጥያቄ በመጨረሻ መነሳት ያለበት ሀሳብ ነው። ተደራዳሪ ወገኖች ወደውና ፈቅደው ይህንን አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት መርጠው እንደስልት ሲጠቀሙ ያለማንም ጣልቃ ገብነት በራሳችን አለመግባባቱን እንፈታለን በሚል እሳቤ እምነት እንደሆነ ግልፅ ነው። ከዚህ በመነሳት የተደራዳሪዎች ስምምነት የችግሩ መፍቻ ቁልፍ ሆኖ በውጤትነት ሊመዘገብ ይችላል። ይህ ስምምነት ከተገኘ እና አለመግባባቱ በተደራዳሪዎች ከተፈታ ጠቀሜታው የላቀ እንደሆነ ከፍ ብሎ ተመልክተናል። ሌላው የድርድር ውጤት ሊሆን የሚችለው ተደራዳሪዎች ለመስማማት አስበው ቢደራደሩም አለመግባባቱን ለመፍታት ሳይችሉ መቅረታቸው ነው። በሌላ አነጋገር ድርድሩ በስምምነት ቢጀመርም ባለመስማማት ሊቋጭ ይችላል። ተደራዳሪዎች መደማመጥ፣ መቻቻል፣ መሳሳብ እና ሰጥቶ መቀበልን የማይችሉ ከሆነ ድርድሩ ያለስምምነት የመቋጨት እድሉ ሰፊ ነው። በተለይ ተደራዳሪዎች የጋራ መግባባት (Muitual Understanding) እና እኩል የሆነ የተግባቦት ክህሎት እና ችሎታ ከሌላቸው ድርድሩ የእምቧይ ካብ ይሆናል።

ከላይ የተገለፁትን ችግሮች በመቋቋም የግንባታ ውሎችን በተመለከተ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በድርድር የመፍታቱ ጉዳይ በአማራ ብሄራዊ ክልል ፍትህ ቢሮ የፍታብሄር ጉዳዮች የስራ ሂደት በስፋት እየተሰራበት ነው[39]። ለአብነትም በአብክመ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን እና በኤን.ኬ.ኤች ኮንስትራክሽን መካከል ያለው የባህር ዳር እና የደብረ ብርሃን ማረሚያ ቤቶች ግንባታ ውል እንዲሁም በደብረ ማርቆስ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና አስቴር መንግስቱ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭና ውሃ ስራዎች ድርጅት የተደረጉት የድርድር ስምምነቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ[40]።

[39] ተመስገን መላክ፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ የፍታብሄር ጉዳዮች የስራ ሂደት ባለቤት
[40] ገዙ ከማሁ

ድርድር በተደራዳሪዎች መካከል የሚካሄድ ውይይት በመሆኑ ተደራዳሪዎቹ ድርድሩን ለማካሄድ እና የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት ያለማንም ጣልቃ ገብነት እና ተፅእኖ የሚስማሙበት ሂደት እንደሆነ ከፍ ብሎ መገለፁ ይታወሳል። ከዚህ ትርጓሜ በመነሳት አንዳንድ ምሁራን ድርድር በአስተዳደር ውል የሚከሰትን አለመግባባት ለመፍታት ምቹ እና ተመራጭ መንገድ አይደለም ይላሉ[41]። ለዚህም እንደምክንያት የመንግስት መ/ቤትን በመወከል የሚቆሙ ተደራዳሪዎችን ተቀርቋሪነት እና የባለቤትነትን ስሜት፣ ብቃትና ችሎታ፣ ስነ-ምግባር እና በአስተዳደር ውል ውስጥ ሊረጋገጥ የሚገባውን የህዝብ አገልግሎት (ጥቅም) ያነሳሉ። ተደራዳሪዎች ከላይ የተመለከቱትን ባህርያት ካልተላበሱ የህዝብ ጥቅም መደራደሪያ ይሆንና የአስተዳደር ውል በአግባቡ ሳይፈፀም ተለባብሶ ሊቀር ይችላል። በመሆኑም ድርድር በአስተዳደር ውል (የግንባታ ውልን ጨምሮ) ሊፈጠር የሚችለውን አለመግባባት ለመፍታት ተመራጭ አይደለም ይላሉ። ከዚህ አንፃር በአብክመ ማረሚያ ቤቶች እና በኤን.ኬ.ኤች. ኮንስትራክሽን በቀን 20/07/2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ሽኝነት በተላከው ውል አንቀፅ 3/1-3/ የሰፈሩት ስምምነቶች በማሳያነት ከውሉ በቀጥታ ተወስደው ከዚህ በታች የተመለከቱ ስለሆነ መልከቱ ጠቃሚ ነው።

- "የድርድር ውል ሰጪ ውሉ በመቋረጡ ምክንያት ለቀሪ ስራ የሚወጣው ተጨማሪ ወጭን በሚመለከት ከድርድር ውል ተቀባይ መጠየቅ ሊተው ተስማምቷል።"
- "የድርድር ውል ተቀባይ በግንባታው ውል መሠረት የወሰደውን ቅድሚያ ክፍያ በተከታታይ ክፍያዎች የተመለሰው ታስቦ ቀሪውን ብር 2,572,122.68 /ሁለት ሚሊዬን አምስት መቶ ሰባ ሁለት ሺ አንድ መቶ ሃያ ሁለት ብር ከ68 ሣንቲም/ ሊመልስ ተስማምቷል።"
- "የማዘግየት ጉዳት /Liquidated damage/ በሲቪል ግንባታዎች ቋሚ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የውሉ 10% የሚከፈል ቢሆንም ሁለቱ ተዋዋዮች በተስማሙበት መሠረት ውል ተቀባይ የውሉን 5% ብር 1,477,548.73 /አንድ ሚሊዬን አራት መቶ ሰባ ሰባት ሺ አምስት መቶ አርባ ስምንት ብር ከሰባ ሦስት ሳንቲም/ የድርድር ውል ተቀባይ ለድርድር ውል ሰጭ ሊከፍል ተስማምቷል።"

[41] ሐይለማርያም ዮሐንስ፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህግ ት/ቤት የአማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት ከፍተኛ መምህር

በአጠቃላይ ድርድር ያለምንም ውጣውረድ በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ ጉዳዮችን ለመቋጨት የሚጠቅም አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት ቢሆንም የራሱ ደካማ ጎኖች ወይም ውስንነቶች ስላሉበት እንደነገሩ ሁኔታ እየመዘኑ ለሚበጅ ለሚበጀው መገልገሉ ሙያዊ እውቀትን እና ብልህነትን የሚጠይቅ ነው።

### 4.3እርቅ (Concilation)

ይህ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት እንደ ድርድር ሁሉ የራሱ የሆነ ገፅታ እና ጠቀሜታ ያለው ነው። አለመግባባቶችን ለመፍታት ከመደበኛ ፍ/ቤቶች ውጭ አዘውትሮ ይከናወናል። እርቅ በታራቂዎች ወይም በባለጉዳዮች በራሳቸው ስምምነት ወይም በፍርድ ቤት አሳሳቢነት ክስ ከተጀመረ በኋላ ወይም ከመጀመሩ በፊት ሊካሄድ ይችላል።[42] ታዲያ እርቅ ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን ጥያቄ መመለሱ ገፅታውን ይበልጥ ለማሳየት አጋዥ በመሆኑ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

እርቅ እንደአንድ አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት ተወስዶ በኢትዮጵያ የፍታብሄር ህግ ሰፍሯል። ከአንቀፅ 3318-24 ድረስ ያሉ ድንጋጌዎች እርቅን በተመለከተ ገዥ ሃሳቦችን ያስቀመጡ ቢሆንም ግልፅ የሆነ ትርጉምን ለቃሉ አልሰጡም። ድንጋጌዎችን በአግባቡ መመርመር ግን ለቃሉ ትርጉም አጋዥ የሆነ ፍንጭን ሳያጭር አልፏል ማለት አያስደፍርም። የህጉ አንቀፅ 3318 እና 3321 በጣምራ ሲነበቡ የእርቅን ፅንሰ-ሃሳብ ለመገንዘብ የሚያስችል ቁምነገርን ማግኘት ይቻላል። በዚህም መሠረት እርቅ ባለጉዳዮች ያጋጠማቸውን አለመግባባት በሦስተኛ ወገን የነቃ ተሳትፎ ለመፍታት የሚገለገሉበት ሂደት ነው። ከትርጉሙ መረዳት የሚቻለው እርቅ ሦስት ወሳኝ ሁኔታዎችን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ነው። እነዚህም ሁለት እና ከዚያ በላይ ባለጉዳዮች በመካከላቸው ያገናኛቸው ጉዳይ እና አለመግባባት እንዲሁም አለመግባባቱን ለመፍታት ጉዳዩ የማይመለከታቸው ተጋባዥ ሰዎች (ሸማግሌዎች) ናቸው። ባለጉዳዮች በመካከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባት እርስ በርሳቸው ተነጋግረው በድርድር መፍታት ሲያቅታቸው የሚያስታርቃቸው (የሚያሸማግላቸው) ሦስተኛ ወገን እንዲገባ ሊስማሙ ይችላሉ። በስምምነቱ መሰረትም አስታራቂዎች ጉዳዩን በባለቤትነት ይዘው ሁለቱን ወገኖች (ባለጉዳዮች) ሊያስታርቁ ወይም ሊያቀራርቡ ጥረት የማድረግ ግዴታ ይኖርባቸዋል። በፍታብሔር ህግ አንቀፅ 3320 መሰረት አስታራቂዎች ባለጉዳዮችን በሚያስታርቁበት ጊዜ

[42] ከፍ ብሎ በተራ ቁጥር 37 በተገለፀው

የሚኖርባቸውን ግዴታ ያሰፍራል። አንዱ እና ዋናው ግዴታም ባለጉዳዬች ሃሳባቸውን በሙሉ እና በነፃነት ገልፀው የሚነጋገሩበት ሁኔታ ወይም እድል ማመቻቸት ነው። አስታራቂው የወሳኝነት ሚና ባይኖረውም አስታራቂ ሃሳብን ሊያቀርብ ይችላል። በቀረበው አስታራቂ ሃሳብ ወይም አስቀድመው ስምምነት በደረሱበት ጉዳይ ላይ የዕርቅ ስምምነት (settlement agreement) ይቀርባል። እንደዚህ አይነቱን ስምምነት በአስታራቂዎች በፅሑፍ ተዘጋጅቶ በባለጉዳዮች የሚፈረም ሲሆን ይህ ፅሑፍ የእርቅ ስምምነት ሆኖ ከመፅደቁ በፊት ባለጉዳዮች እንዲያነቡት እና አስተያየት እንዲሰጡበት መደረግ አለበት።[43] ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው በባለጉዳዮች መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ጉዳያቸውን በእርቅ መጨረስ እንዳለባቸው የሚያስገድድ የቀደመ ውል ካለ የአስታራቂዎች ግዴታ የጀመሩት እርቅ ውጤት ባያስገኝ አለመስማማቱን (Memorandum of Non-concilation) ማዘጋጀት ያለባቸው መሆኑን ነው።[44] እርቅ የባለጉዳዬች መስማማት ብቻ ሳይሆን ላለመስማማት መስማማታቸውን የሚያካትት በመሆኑ አስታራቂዎች የግልግል ስምምነት ላይ መድረስ በማይቻልበት ጊዜ እርቁን እንደ ውጤት አልባ ከንቱ ልፋት መቁጠር የለባቸውም። ምክንያቱም እርቁን ለማከናወን የወጣ ወጪ፣ የባከነ ጊዜ እና ጉልበት ቢኖርም አለመግባባቱን በስምምነት መቋጨት አለመቻላቸው ቀደም ሲል የተዋዋሉት ውል ክስን እንዳይመሰርቱ ከመሠረቱም ለክሱ መቃወሚያ ሆኖ እንዳይቀርብ የማገልገል ውጤት[45] ስለሚኖረው ነው።

ይህ ማለት ግን የባለጉዳዮች አለመስማማት እንደመልካም ውጤት መወሰድ አለበት ማለት አይደለም። ይልቁንም አስታራቂዎች ባለጉዳዬች እንዲስማሙ የስምምነት ሀሳቡን ከማቅረብ ጀምሮ ሌሎች የማሳመኛ ዘዴዎችን በመጠቀም እርቁን ፍሬያማ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ለውጤቱ ፍሬያማነት አስታራቂዎች ብቻ ሳይሆኑ ባለጉዳዮቹም የበኩላቸውን ድርሻ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል። በተለይም ባለጉዳዬች አለመግባባታቸውን በእርቅ ለመፍታት ከተስማሙበት ጊዜ አንስቶ ስለጉዳያቸው አስፈላጊውን መረጃ ሁሉ በመስጠት እና የእርቁን ሂደት አስቸጋሪ እና የማይቻል ከሚያደጉ ተግባራት በመቆጠብ እርቁ በውጤት እንዲቋጭ ትልቅ አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

እርቅ ከኢትዮጵያ የፍታብሔር ህግ በተጨማሪ በኢፌድሪ የቤተሰብ ህግ ከአንቀፅ 119-122 በኢፌድሪ አሰሪና ሰራተኛ ህግ አንቀፅ 141-143 እንዲሁም በኢትዮጵያ የፍታብሔር ሥነ-

[43] ከፍ ብሎ በተራ ቁጥር 4 በተገለፀው አንቀፅ 3320/1/
[44] ዝኒ ከማሁ፣ 3320/2/
[45] ዝኒ ከማሁ፣ 3312 እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ አንቀጽ 244(1)(ረ)

ሥርዓት ህግ አንቀፅ 275-277 እና በሌሎችም ህጎች ስር ሰፍሮ በየዘርፉ የሚፈጠሩትን አለመግባባቶች ለመፍታት የማይናቅ ሚና እየተጫወተ እንደሆነ በተግባር ማየት ይቻላል። የኢትዮጵያን የግንባታ ውል ህግ ማዕቀፍ ስንፈትሽ በአብዛኛው "አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶችን" (Dispute Settlement mechanisms) ጥቂቶቹ ደግሞ "የግልግል ዳኝነት" (Aribitration)'ን አለመግባባቶችን ለመፍታት መጠቀም እንደሚቻል በተድበሰበሰ መልክ ከመግለፅ በቀር "እርቅን" እንደአማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት የሚደነግግ ውል /ህግ መመሪያን ጨምሮ/ የፅሑፉ አቅራቢ አላገኘም። ሥለሆነም የግልግል ዳኝነት በግንባታ ስራ አስተዳደር ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት ያለውን ወሳኝ ሚና በሚቀጥሉት የፅሁፉ ክፍሎች እንመለከታለን።

## 4.4የግልግል ዳኝነት (Aribitration)

የግልግል ዳኝነት በግንባታ የአስተዳደር ውል ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ አለመግባባቶችን ለመፍታት አገልግሎት ላይ ከሚውሉ ዘዴዎች መካከል አንዱ እና አይነተኛው ነው። አለመግባባቶችን ለመፍታት የግልግል ዳኝነት ስራ ላይ ሲውል ገላጋዮችም ይሁን ተገላጋዮች እንዲሁም ሌሎች ወገኖች ፅንሰ-ሀሳቡን መገንዘብ እና ጥቅም እና ጉዳቱን በመመዘን ሊመርጡት ይገባል። በመሆኑም በዚህ አጭር ፅሁፍ ውስጥ የግልግል ዳኝነት ምን ማለት ነው? ገላጋዮች እንዴት እና በማን ይመረጣሉ? የተገላጋዮችን ጉዳይ እንዴት ይወስናሉ? የሚሉት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ቀለል ባለ መንገድ እንመለከታለን።

### 4.4.1 የግልግል ዳኝነት ትርጉም እና ይዘት

የግልግል ዳኝነትን ምንነት ለመረዳት የኢትዮጵያን የፍታብሄር ህግ እና ሌሎች ፀሐፍት የፃፉትን መጣጥፍ በአግባቡ መፈተሽ የላቀ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ የፍታብሔር ህግ አንቀፅ 3325 (1) የሚከተለውን ትርጓሜ ሰጥቶ እናገኘዋለን። "የግልግል ስምምነት ማለት ተዋዋይ ወገኖች የአንዱ ክርክርን ውሳኔ ለአንዱ የዘመድ ዳኛ ለሆነው ለአንድ ሦስተኛ ሰው አቅርበው የዘመድ ዳኛው ውል በህግ አግባብ መሠረት ይህንኑ ክርክር ለመቁረጥ የሚያደርገው ውል ነው" ይላል። ከዚህ ትርጉም መረዳት የሚቻለው የግልግል ስምምነት አለመግባባቶችን በዘመድ ዳኛ መፍታት ወይም መቋጨት እንደሆነ ነው። የግልግል ሰምምነት አንዳንዴ የግልግል ዳኝነት ወይም ክርክሮችን በዘመድ ዳኛ መቋጨት በሚል አነጋገር ተገልፆ በተለያዩ የህግ ክፍሎቻችን እንመለከታለን። የግልግል ስምምነትም ይባል ዳኝነት የሚይዘው

ሀይለ-ቃል ሁለት ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባት በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት በሚሾም ዳኛ አማካኝነት ተከራክረው በህግ አግባብ አለመግባባቱን የሚፈቱበት ወይም ክርክሩን የሚቋጨበት አግባብ ነው።[46] የኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት እና የማስማማት ማዕከል ደንብ የግልግል ዳኝነትን እና ስምምነትን የተለያየ ነገር ግን ተቀራራቢ የሆነ ትርጓሜ ሰጥቶታል። በዚህ ሰነድ መሰረት የግልግል ዳኝነት ማለት "አለመግባባትን ለመፍታት የሚካሄድ ግል-ነክ ባህሪይ ያለው ሂደት ነው። ይህ ትርጓሜ ከኢትዮጵያ የፍታብሄር ህግ አንቀፅ 3325 (1) ከወሰድነው ፍች ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሲሆን አሁን ለያዝነው ጉዳይም ይበልጥ ተስማሚ ነው። የግልግል ስምምነት ግን ከግልግል ዳኝነት ጋር ቢቀራረብም የይዘት ልዩነት እንዳለው ከሰነዱ መገንዘብ ይቻላል። ደንቡ "የግልግል ስምምነት ማለት ተከራካሪ ወገኖች አንድ አለመግባባት ከመከሰቱ በፊትም ሆነ ከተከሰተ በኃላ አለመግባባቱን በግልግል ዳኝነት ለመፍታት በፅሁፍ የሚያደርጉት ስምምነት ነው። ይህም ስምምነት በግልግል አንቀፅ መልክ ዋናውን ግንኙነት ከሚመሰርተው ግዴታ ጋር ወይም ራሱን በቻለ ሰነድ ሊመለከት ይችላል። ከዚህ ፍች አነጋገር የግልግል ሰምምነት ከግልግል ዳኝነት የሚለይ መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል። ይኸውም የግልግል ዳኝነት በግልግል ስምምነቱ መሠረት የተመረጡት የዘመድ ዳኞች ከባለጉዳዮቹ በተሰጣቸው ሥልጣን ተጠቅመው አለመግባባቱን የሚዳኙበት ሂደት ነው። ከፍ ብሎ ለግልግል ስምምነቱ የተሰጠውን ትርጓሜ በአግባቡ ላጤነው ከግልግል ዳኝነት ይልቅ የግልግል ስምምነት በኢትዮጵያ የፍታብሄር ህግ አንቀፅ 3307 ስር ከሰፈረው Compromise ከሚለው ቃል ጋር አንድነት እንዳለው መረዳት የሚቻል ቢሆንም የግልግል ስምምነት ለተመረጡት ዳኞች ውሳኔ የመስጠት ሥልጣንን የሚያጎናጽፍ በመሆኑ በዚህ ረገድ ልዩነት ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በጥቅሉ በአቶ በዛወርቅ ሽመልስ በቀረበው ፅሁፍ የግልግል ስምምነት ከግልግል ዳኝነት ወይም ክርክርን በዘመድ ዳኛ መቋጨት ከሚለው የህግ መንፈስ ጋር በአንድ ላይ የሚገኙ ሁለት የስምምነት አይነቶች እንደሆኑ እንደተገለፀው ሁሉ በዚህ ፅሁፍ አቅራቢም ሁለቱ ፅንሰ-ሀሳቦች የተደጋገፈ እንጅ የተዋሐደ መንፈስ እንደሌላቸው ይታመናል። የሆነው ሆኖ ለዚህ ፅሁፍ አላማ የሚወሰደው የግልግል ዳኝነት (Arbitration) የሚለው ሲሆን ይህ የክርክር መቋጫ አማራጭ ዘዴ ያሉትን ልዩ ባህሪያት መመልከቱ ተገቢ ይሆናል።

[46] በዛወርቅ ሽመልስ፣ የኢትዮጵያ የሕግ መፅሄት፣ ቅፅ 17

### 4.4.2 የግልግል ዳኝነት መሠረታዊ ባህሪያት

የግልግል ስምምነት ውል ቢመስልም ከሌሎች የውል አይነቶች የሚለይባቸው የራሱ የሆኑ ባህሪያት አሉት፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ የስምምነቱ አላማ እንደሌሎቹ ውሎች መብት እና ግዴታን ከማቋቋም ይልቅ የውል ግዴታን በመፈፀም ረገድ የሚፈጠርን አለመግባባት ተዋዋይ ወገኖች እራሳቸው በመረጡት ገላጋይ አማካኝነት የሚቋጨበትን የክርክር መስመር የሚዘረጋ ነው፡፡ የግልግል ስምምነት (arbitral submission) በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚፈጠር ስምምነት መሆኑ ውል ቢያሰኘውም በተዋዋይ ወገኖች መሰረታዊ የሆነ ግዴታን (substantive right) አያቋቁመም፡፡ ስምምነቱ አለመግባባቱ የሚፈታበት ወይም የሚቋጭበትን መንገድ የሚያሳይ ጽሁፍ ነው፡፡ በስምምነቱ ውስጥ ባለጉዳዮቹ አለመግባባቱ እነማን እንደሚዳኙላቸው፤ ቁጥራቸው ምን ያህል መሆን ሊሆን እንደሚገባው፣ እንዴት እንደሚሾሙ እና እንደሚሻሩ ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም የግልግል ስምምነት (ዳኝነት) ክርክር የሚቋጭበትን መንገድ የሚያሳይ በመሆኑ ከሌሎች የፍሬ ነገር መብትን ከሚያቋቁሙ ውሎች (ስምምነቶች) የተለየ ነው፡፡[47]

ሌላው ባህሪ ደግሞ “….. ተዋዋዮቹ ጉዳያቸውን ለገላጋዩ ለማቅረብ የፈቀዱበት አንድ ስምምነት እና በሌላ በኩል በተዋዋዮቹና በገላጋዩ መሀከል ለመሸምገል የተደረገ ሌላ ስምምነት በአንድ ጉዳይ ላይ ተዋህዶ መገኘቱ ነው፡፡”[48] በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለት ፈርጅ ወይም ገጽታ ያለው ስምምነት ነው ማለት ይቻላል፡፡ አንደኛው ፈርጅ ባለጉዳዮች በመካከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባት ለገላጋይ (ለዘመድ ዳኛ) ለማቅረብ የሚስማሙበት ውል ነው፡፡ ሌላው በገላጋይነት ለመሰየም ፈቃደኛ የሆኑ የዘመድ ዳኞች ሹመቱን ተቀብለው በገላጋይነት ለመሰየም ፈቃደኛ ሆነው በተገኙ ጊዜ የግልግል ዳኝነቱን አስመልክቶ በገላጋዮች እና በባለጉዳዮች መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት መልክ ለማስያዝ የሚመሰረት ውል ነው፡፡ እነዚህ ስምምነቶች የተቀራረበ ነገር ግን የተለያየ አላማ አላቸው፡፡ ሁለቱም ስምምነቶች ለግልግል ዳኝነቱ ስኬት ወሳኝ ሚና ያላቸው በመሆኑ እንደመሰረታዊ የግልግል ዳኝነት ባህሪ ይወሰዳሉ፡፡

ሦስተኛው ልዩ ባህሪ “ተከራካሪ ወገኖች በመሀከላቸው የሚፈጠረውን አለመግባባት ተቀብሎ ለማየት የሚችል የራሳቸው የሆነ የዳኝነት አሰራር ለመፍጠር የመቻላቸው ሁኔታ ነው፡፡” በዚህ አነጋገር ባለጉዳዮች ጉዳያቸውን የሚዳኝላቸው ዳኛ በስምምነት የመሾም ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡

[47] ዝኒ ከማሁ ገፅ 41
[48] ዝኒ ከማሁ

ተሿሚው ዳኛም ባለጉዳዮቹ የሰጡትን ስልጣን በመጠቀም አግባብነት ያለው ህግ ተከትሎ በባለጉዳዮች መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ለመቋጨት የሚያስችል ህጋዊ እልባት ወይም ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ይህም ክርክሩ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት መሄድ ሳያስፈልገው ጉዳዩ ውሳኔ ያገኛል ማለት ነው፡፡ ህግ በሚጠይቀው ሥርዓት ተከትሎ ይግባኝ ካልተባለበት በቀር በግልግል ዩሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ፍርድ ሆኖ ይፈጸማል፡፡[49]

በአጠቃላይ የዕርቅ ስምምነት (compromise)፣ የግልግል ስምምነት (arbitral submission) እና ጉዳይን በዘመድ ዳኛ መቋጨት የሚሉት አነጋገሮች የተቀራረቡ እና አንዳንዱም አንዱ ሌላውን የተካ በሚመስል መልኩ ስራ ላይ (ጥቅም ላይ) እየዋሉ በፅንሰ-ሀሳቡ ላይ ብዥታን ቢፈጥሩም ለዚህ ፅሁፍ አላማ ከላይ በአጭሩ የተብራሩትን ባህሪያት የተላበሰው የግልግል ዳኝነት (Arbitration) ከግንባታ ውል አንፃር መመልከት በመሆኑ ከዚህ የበለጠ ጥልቀት እንደማያስፈልገው ጸሃፊው ያምናል፡፡

### 4.4.3 የግልግል ዳኝነት ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች

የግልግል ዳኝነት እንደሌሎች አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶች ሁሉ የራሱ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ እነዚህ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ከመደበኛው የክርክር ሥርዓት ጋር ሲነፃፀሩ ይበልጥ ደምቀው ይታያሉ፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች ያለውን የፅሁፍ ክፍል የግልግል ዳኝነትን ጠንካራ እና ደካማ ጎን የምንፈትሸበት ይሆናል፡፡

የግልግል ዳኝነት ጥንካሬ ከመደበኛው የክርክር ስርዓት አንፃር ሲታይ በርካታ ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል አንዱ ወጪ ቆጣቢነቱ ነው፡፡ የግልግል ዳኝነት ተገላጋዮች ጉዳያቸውን እራሳቸው በመረጡት ዳኛ ስለሚታይ በዝቅተኛ ወጪና በአጭር ጊዜ የመቋጨት እድል አለው፡፡ ሌላው ጥንካሬ ምስጢራዊነት እና በባለጉዳዮች ህሊና ውስጥ ቂምን ወይም ጠባሳን ጥሎ አለማለፉ ነው፡፡ ተገላጋዮች ወደዚህ የሙግት ሥርዓት የሚገቡት በነፃ ፈቃዳቸው ከመሆኑም በላይ ዳኞቹን የመሾም እና የመሻር እንዲሁም በሚሰጡት ውሳኔ የመገዛት እውነታ የሚመነጨው ከራሳቸው በመሆኑ የአሸናፊነት እና የተሸናፊነት ስሜት ወይም እልህ አለያም ቂም አይኖርም፡፡ ይልቁንም የክርክሩን ሂደት ተቀብለው ሀሳባቸውን በነፃ ገልፀው ውጤቱን ወይም ውሳኔውን በፀጋ ተቀብለው ይፈፅማሉ፡፡

[49] ዝኒ ከማሁ ገፅ 42

የግልግል ዳኝነት በጉዳዩ ላይ ልዩ ዕውቀት ያለው ዳኛ ወይም ገላጋይ ለማግኘት እድል ይፈጥራል። ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው ተገላጋዮች ገላጋይ የሚመርጡት እራሳቸው ናቸው። ይህንን እድል በመጠቀም የተሻለ እውቀት እና ክህሎት ያለውን ገላጋይ የመምረጥ እና የመዳኘት መብት ይኖራቸዋል። በመደበኛ ክርክር ሥርዓት ግን ጉዳዩን የሚያየው በመንግስት የተሾመ ዳኛ በመሆኑ በህጉ አተረጓጎም ላይ የላቀ ዕውቀት ቢኖረውም በጉዳዩ ፍሬ ነገር ላይ ግን ክህሎት የሌለው እና የዘርፉ ስራ የሚጠይቀውን እውነት እና ውስብስብነት ባለመረዳት ፍትሐዊ ላልሆነ ውሳኔ ሊያጋልጥ ይችላል። በመሆኑም የግልግል ዳኝነት እንዲህ አይነቱን ችግር ለመቅረፍ ባለጉዳዮች ጉዳያቸውን በዘርፉ ልዩ እውቀት እና ክህሎት ባለው ባለሙያ እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል።

የግልግል ዳኝነት ከመደበኛው የክርክር ሥርዓት ይልቅ ፈጣን አገልግሎትን እንደሚሰጥ ይታመናል። ምክንያቱም ጉዳዩን ለመወሰን ገላጋዮች የሚከተሉት ሥነ-ሥርዓት ቀለል ያለ እና ቀልጣፋ በመሆኑ[50] ነው። ጉዳዩን ለመወሰን እንደመደበኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ቀጠሮ አያበዙም። ጉዳዩ የሚሰማበት ጊዜ፣ ቦታ እና ሥነ-ሥርዓት እንዲሁም ቋንቋ በተገላጋዮች ስምምነት የሚወሰን ከመሆኑ በተጨማሪ ገላጋዮች የተገላጋዮችን ፈቃድ ግምት ውስጥ የሚያስገቡ በመሆናቸው ክርክሩ ቀላል ያለ እና ቀልጣፋ ያደርገዋል።

የግልግል ዳኝነት ከላይ የተመለከትናቸው ጥንካሬዎች እንዳሉት ሁሉ የሚከተሉት ውስንነቶችም ይስተዋሉበታል። የግልግል ዳኝነት በህግ የተደነገጉትን ሥነ-ሥርዓቶች ብቻ ሳይሆን መርህ እና ርትዕን ታሳቢ ያደረገ ልል ሥነ-ሥርዓትን ስለሚከተል የተገላጋዮች ሥነ-ሥርዓታዊ መብቶች ሊጣሱ ይችላሉ። ይህ የመብት ጥሰት በተገላጋዮች ላይ ጉዳት ያስከትላል። በተለይ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ በኢትዮጵያ የፍትሃ-ብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ አንቀጽ 351 ሥር ከተመለከቱት የሥነ-ሥርዓት እና ማስረጃ ነክ ጉዳዮች በቀር ይግባኝ የማይባልበት እንደመሆኑ መጠን የመብት ጥሰቱ የመታረም እድል አይኖረውም። ይህም በግልግል ዳኝነት ውሳኔ ተጎጅ በሆነው የፍርድ ባለዕዳ ላይ ሊቀለበስ የማይችል ጉዳት ያስከትላል።

[50] ግልግል የፍትሃብሄር ሥነ-ሥርዓት ህጉን መከተል ያለበት ስለሞኑ በፍትሃ ብሄር ህጉ በአንቀጽ 3345 ላይ የተመለከተ ቢሆንም ሁሉንም ሥርዓት ጥብቅ በሆነ መንገድ መከተል ግድ አይደለም። ምክንያቱን የግልግል ዳኝነት መደበኛ የሆነ የክርክር መቋጫ መንገድ ሳይሆን ከመደበኛ የክርክር ሥርዓት መፍቻ ውጪ ክርክር የሚደረግበት መድረክ (tribunal) በመሆኑ ነው። tribunal በባህሪያቸው ጥብቅ ሆነ ሥነሥርዓት መከተል አይጠበቅባቸውም።

ሌላው የግልግል ዳኝነት ውስንነት ክርክሩን ለመቋጨት በተገላጋዮች የሚመረጠው የዘመድ ዳኛ ሙያዊ እውቀት ላይኖረው የሚችል መሆኑ ነው። ተገላጋዮች አለመግባባቱን በሰላማዊ መንገድ በዘመድ ዳኛ ለመቋጨት ሲሉ የፍሬ ነገር እና የሥነ-ሥርዓት እውቀት ያለው ባለሙያን ከመምረጥ ይልቅ ሁለቱን ሊያግባባ የሚችል የዘመድ ሽማግሌ ሊመርጡ ይችላሉ። ተመራጮቹ በእውቀት ጉድለት እና በብቃት ማነስ ጉዳዩን አግባብነት ካለው ህግ አንፃር መርምረው ፍትሀዊ፣ ሚዛናዊ እና ምክንያታዊ ውሳኔን ለመስጠት ይቸገራሉ። ይህም በተገላጋዮች ላይ ከፍ ያለ ጉዳትን ሊያደርስ ይችላል። የግልግል ዳኝነት ሁሉንም ጉዳዮች ማስተናገድ አለመቻሉ በውስንነት ይወሰዳል። በግልግል ዳኝነት የፍታብሔር ጉዳዮች ካልሆኑ በቀር ወንጀል ነክ ጉዳዮች ሊታዩ እና ሊቋጩ አይችሉም። የፍታብሄር ጉዳዮችም ቢሆን ተገላጋዮች ካልፈቀዱ ወይም በውል ካልተስማሙ በቀር በግልግል ዳኝነት ሊቋጩ አይችሉም።

በጠቅላላው የግልግል ዳኝነት ከፍ ብሎ የተመለከቱት ውስንነቶች ቢኖሩበትም አለመግባባቶችን በአጭር ጊዜ፣ ወጪ ቆጣቢ እና ውጣ ውረድ በሌለበት መንገድ ለመቋጨት የላቀ ድርሻ እንዳለው ይታመንበታል።

## 5. በግልግል ዳኝነት የሚታዩና የማይታዩ ጉዳዮች

### 5.1 ጠቅላላ ሁኔታ

በግልግል የሚታዩና የማይታዩ ጉዳዮችን በተመለከተ በዘርፉ ጠበብቶች መካከል በርካታ የሀሳብ ልውውጦች ይደረጋል። በግልግል ዳኝነት የሚታዩና የማይታዩ ጉዳዮችን የምሁራንን ሀሳብ መሰረት በማድረግ የብዙ ሀገር መንግስታት በህግ ይወስናሉ። የጉዳዮችን በግልግል የመታየት ሁኔታ (Arbitablity) የሚወስኑ ህጐች ወጥተው ስራ ላይ ይውላሉ። እነዚህ ህጐች በየዘርፉ ያሉትን ፖሊሲዎች በአግባቡ በመመርመር የጉዳዩ በግልግል ዳኝነት መታየት ያለውን ጠቀሜታ በመመዘን ፈቃጅ ህግጋትን ሲደነግጉ የሚያስከትለውን ጉዳት በማጤን ደግሞ እንደነገሩ ሁኔታ ጉዳዩ በግልግል እንዳይታይ የሚከለክል ህግን አውጥተው ሥራ ላይ ያውላሉ። በሌላ አነጋገር ህግ በግልግል የሚታዩ እና የማይታዩ ጉዳዮችን ለመወሰን ግልግሉ የሚደረግበትን ዘርፍ በአግባቡ መርምሮ ጉዳትና ጥቅሙን መመዘን ያስፈልጋል። ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት ቢታይ ከሚያስከትለው ጉዳት ይልቅ ጠቀሜታው ከላቀ በግልግል ታይቶ እልባት እንዲያገኝ ሲፈቅድ እውነታው ከዚህ በተቃራኒ ከሆነ ግን ክልከላን ያስቀምጣል። ሶስተኛው የህግ አማራጭ ደግሞ አለመግባባቱ በምን መንገድ ሊዳኝ እንደሚችል ሳይገልፀ በዝምታ ማለፍ ነው። በዘርፉ ያለው ህግ ጉዳዩ በግልግል ይታያል ወይም አይታይም ከማለት ይልቅ በዝምታ ያለፈው እንደሆነ

ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት የመቋጨቱ ነገር በባለጉዳዮች ስምምነት ይወሰናል። ባለጉዳዮች አለመግባባታቸውን በግልግል ዳኝነት ለመቋጨት በመካከላቸው ያለውን መብት እና ግዴታ በአቋቋሙበት ውል ውስጥ በሰፈረ ድንጋጌ ወይም በተለየ የውል ስምምነት ሊወስኑ ይችላሉ። ከላይ በተገለፀው አግባብ በአንዱ ስምምነት ላይ የደረሱ እንደሆነ ተቃራኒ ህግ ከሌለ በቀር ይኸው ተፈፃሚ ይሆናል።

በባለጉዳዮች ስምምነት የሚወሰነው በግልግል የሚታይ እና የማይታይ ጉዳይ በተመለከተ በኢትዮጵያ የፍታብሔር ህግ ከአንቀፅ 3325-3345 ባሉት ድንጋጌዎች የሚመራ ሲሆን በሌሎች ህጎች የተቀመጡትን ፈቃጅ እና ከልካይ ድንጋጌዎች በተለይም ከአስተዳደር ውል አንፃር ቀጥሎ እንመለከታለን።

የኢትዮጵያ የህግ ማእቀፍ እንደሌሎቹ ሀገሮች ሁሉ በግልግል የሚታዩ እና የማይታዩ ጉዳዮችን በተመለከተ ፈቃጅ እና ከልካይ ድንጋጌዎችን የያዙ ህግጋትን በማውጣት ስራ ላይ ያውላል። እነዚህ ህግጋት የፖሊሲ መርሆችን ለማስፈፀም ብቁ ሳይሆኑ ሲቀሩ ያሻሽላል። በሌላ አነጋገር በአንድ ወቅት በግልግል ዳኝነት እንዲታይ የተፈቀደ ጉዳይ በሌላ ጊዜ ሊከለከል ይችላል። ለዚህ ጥሩ አብነት የሚሆነው የቤተሰብ ጉዳይ ነው። በ1952 ዓ.ም ወጥቶ ስራ ላይ በነበረው የፍታብሄር  ህግ ውስጥ አንድ አካል ሆኖ ሲሰራበት በነበረው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 722-730 ያሉት ድንጋጌዎች በአግባቡ ሲፈተሹ በግልግል ዳኝነት የሚታዩ እና የማይታዩ  የቤተሰብ ጉዳዮችን ይዘው እናገኛለን። በድንጋጌዎቹ መሰረት መተጫጨትን (አንቀፅ 722)፣ ህጋዊ ጋብቻ መኖር አለመኖርን (አንቀፅ 724) እና ከጋብቻ ውጭ ስላለ የግብረ ስጋ ግንኙነትን (አንቀፅ 730) በተመለከቱ ሁኔታዎች አለመግባባቶች ሲከሰቱ ጉዳዮቹ በግልግል ዳኝነት ወይም በቤተ-ዘመድ ሽማግሌ ዳኝነት መታየት አይችሉም። እነዚህን ጉዳዮች አከራክሮ ውሳኔ መስጠት ለመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ስልጣን ነው። በሌላ በኩል ከአንቀፅ 725-729 ያሉት ድንጋጌዎች በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እና ፍችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን ለቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ተሰጥቷል። በአንቀፅ 729 መሰረት በቤተ ዘመድ የተፈፀመ ፍች በመደበኛ ፍርድ ቤት ታይቶ ይፀድቃል። ከዚህ አነጋገር መረዳት የሚቻለው በቀድሞው የቤተሰብ ህግ ፍችን የሚመለከቱ ጉዳዮች በቤተ ዘመድ ሽምግልና ወይም በግልግል ዳኝነት እየታዩ ሲቋጩ መቆየታቸውን ነው። ሆኖም የቤተ ዘመድ ሽማግሌ ሆነው የሚመረጡ ዳኞች በአድሎ፣ በጉቦ እና በሌሎቹም ኋላቀር አሰራሮች በሴቶች ላይ በደል የሚያደርሱ ኢ-ፍትሀዊ ውሳኔዎችን እያሳረፉ እንደሆነ በልዩ ልዩ ጥናቶች በመረጋገጡና በፖሊሲው

ለታለመው ግብ ስኬት ያላቸው አስተዋፅኦ አሉታዊ በመሆኑ ተሻሽሎ በወጣው የቤተሰብ ህግ የግልግል ዳኝነት በቤተሰብ ጉዳዮች ምንም አይነት ስልጣን እንዳይኖረው ክልከላን ጥሏል። ስለሆነም የግልግል ዳኝነት ስራ ላይ ባለው የኢፌድሪ የቤተሰብ ህግ መሰረት የቤተሰብ ጉዳዮችን ተመልክቶ ዳኝነት አይሰጥም። በሌላ አነጋገር የቤተሰብ ጉዳይ በግልግል ከማይታዩ ጉዳዮች ተፈርጇል ማለት ነው።

## 5.2 የአስተዳደር ውል

እንደቤተሰብ ህግ ሁሉ ሌሎች የኢትዮጵያ ህጐችም በግልግል ዳኝነት ሊታዩ አይገባቸውም የሚሉትን ጉዳዮች ክልከላ ጥለውባቸው እናገኛለን። በዚህ ረገድ ተጠቃሹ የኢትዮጵያ የፍትሃብሄር ስነ-ስርአት ህግ ነው። የዚሁ ህግ አንቀፅ 315(2) " በግልግል እንዳይወሰን በህግ የተከለከለ ጉዳይ ወይም በፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 3131 እንደተነገረው ያለ ጉዳይ ሲሆን ለግልግል ዳኝነት አይቀርብም "በዚህ ድንጋጌ መሰረት በፍታብሄር ህግ አንቀፅ 3131 እና ተከታዮች መሰረት የተቋቋመ የውል ግዴት አስተዳደራዊ ባህሪ ያለው በመሆኑ በግልግል ዳኝነት ሊታይ እንደማይገባው ያስገነዝባል። የአስተዳደር የውል ግዴታዎች የመንግስት እና የህዝብ ጥቅምን ለማስከበር በመንግስት በጀት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ወይም የሚከናወኑ ስራዎችን ለማስፈፀም የሚቋቋሙ በመሆናቸው በገላጋይ እንዲታዩ የመንግስት ፖሊሲ አያበረታታም። ከመንግስት የገንዘብ ቋት ወጭ ሆነው በሚመደቡ በጀቶች የሚሰሩ ልዩ ልዩ ተግባራት የህዝብ ጥቅምን ኢላማ ያደረጉ በመሆናቸው በዚህ ረገድ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች የህዝብ እና የመንግስትን ጣልቃ ገብነት የሚጠይቁ ስለሆኑ በዘመድ ዳኛ ወይም የግልግል ዳኝነት መቋጨታቸው ኢ-መደበኛ ስለሆኑ የህዝብን ጥቅም በአግባቡ አያስከብሩም ተብሎ ይገመታል። በመሆኑም እንዲህ አይነት ጉዳዮች ከአማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት ይልቅ በመደበኛው የክርክር ስርዓት ቢቋጭ የተሻለ እንደሚሆን ይታመናል።

በቅርቡ የወጣው የግዥ እና የመንግስት ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2009 በአንቀፅ 6 (1) ስር በብድር በተገኘ ገንዘብ የሚከናወኑ የመንግስት ፕሮጀክቶችን በተመለከተ አለመግባባት ሲፈጠር በአማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት ወይም በገላጋይ እንደሚፈቱ ስምምነት ካለ በዚሁ መንገድ አለመግባባቱ ሊቋጭ እንደሚችል ያመለክታል። በዚህ ድንጋጌ አነጋገር ከውጭ መንግስታት ወይም ከአለም አቀፍ አበዳሪ ድርጅቶች ጋር የተደረጉ የብድር ስምምነቶች አለመግባባቱ በገላጋይ አማካኝነት መፍትሄ እንደሚያገኝ የተስማሙ ከሆነ ስምምነቱ ከፍ ብሎ

ከተገለፀው ህግ ጋር የሚቃረን ቢሆንም ተፈፃሚ ይሆናል። በሌላ አነጋገር የአስተዳደር ውሎችን በተመለከተ የተፈጠረ አለመግባባት በመርህ ደረጃ በገላጋይ ዳኝነት የሚታይ ባይሆንም በልዩ ሁኔታ በህግ ሲደነገግ በግልግል ሊታይ ይችላል። በዚህ መሰረት ልዩ ልዩ አዋጆች ለተለያዩ የመንግስት ድርጅቶች አለመግባባታቸውን በግልግል እንዲፈቱ ይፈቅዳሉ። ለምሳሌ፡- ለኢትዮጵያ አውራ ጐዳና የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 247/2011 አንቀፅ 10(2)(H) ፣የኢትዮጲያ ፕራይቬታይዜሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 146/1998 አንቀፅ 15(1) ተጠቃሽ ናቸው። በእነዚህ ህግጋት መሰረት ከፍ ብለው የተመለከቱት የልማት ድርጅቶች በሚያስተዳድሯቸው የውል ግዴታ አፈፃፀሞች ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ቢኖሩም በግልግል ለመፍታት የሚያስችላቸው ልዩ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል ማለት ይቻላል።

የአስተዳደር ውሎች በግልግል ዳኝነት እንዳይታዩ በኢትዮጵያ የፍታብሔር ስነ-ስርዓት ህግ አንቀፅ 315(2) ስር የተደነገገው ክልከላ እና በሌሎች ከፍ ብሎ በተመለከትናቸው ህግጋት የተመለከተው ፍቁድነት በጠቅላላ እና በልዩ ሁኔታ የህግ አተረጓጐም አግባብ የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ ይመልከክተው እንጂ በዘርፉ ያሉ ምሁራን (accadamicians) እና የህግ ባለሞያዎች (legal practioners) በጉዳዩ ላይ የየራሳቸውን የሰላ ትችት ይሰነዝራሉ። በአንድ በኩል በኢትዮጵያ የፍታብሔር ስነ-ስርአት ህግ አንቀፅ 315 (2) ስር የተመለከተው ክልከላ የአስተዳደር ውሎች በግልግል እንዳይታዩ የሚከለክል አይደለም ይላሉ። በዛወርቅ አስመላሽ እና ፕሮፌሰር ዘካርያስ ቀንዓን በኢትዮጲያ የህጐች መፅሔት volume 17 ላይ ባሳተሟቸው ፅሁፎች ድንጋጌው የአስተዳደር ውሎች በግልግል ዳኝነት እንዳይታዩ አይከለክልም ይላሉ። ተክሌ ሀጎስ የተባለ ሌላ የህግ ምሁር እንዲሁ በሚዛን ሎው ሪቪው volume 3 ቁጥር 1 በ2009 ባሳተመው ፅሁፍ ይህንኑ የሀሳብ መስመር ያጠናክራል። የኢፌድሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በዘምዘም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና በኢሊባቡር ዞን ትምህርት መምሪያ መካከል በፋይል ቁጥር 16896 ተከፍቶ በነበረው መዝገብ ላይ ይህንኑ አተረጓጐም የሚያጠናክር ሀሳብ ሰጥቷል። ከፍ ብሎ የተገለፁት የምሁራኑ መጣጥፍ እና የፍርድ ቤት ውሳኔዎች የኢትዮጵያ የፍታብሔር ስነ-ስርአት ህግ አንቀፅ 315(2) የያዘውን ድንጋጌ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ የተከተለውን አተረጓጐም የተከተሉ ናቸው። በመሆኑም የአስተዳደር ውሎችን በግልግል ዳኝነት ማየት በኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፍ ሙሉ በሙሉ የተከለከለ ነው ማለት አይቻልም። ይህንን ይበልጥ ለማጠናከር ከአስተዳደር ውሎች አንዱ የሆነውን የግንባታ ውል በተመለከተ የሚነሱትን አለመግባባቶች ለመፍታት አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች

ያላቸውን ሚና ለመገንዘብ በዚህ ዘርፍ ያሉትን ውሎች፣ ህጐች እና የፍርድ ቤት ውሳኔዎች መመልከቱ ተገቢ ነው።

## 6. በግንባታ ውል አስተዳደር ውስጥ የሚከሰቱትን አለመግባባቶች ለመፍታት አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች ያላቸው ተፈፃሚነት

የግንባታ ውል የመንግስት አካላት ከሚዋዋሏቸው እና ከሚያስተዳድሯቸው የውል አይነቶች መካከል አንዱ ነው። ግንባታ ከሚለው ቃል መገንዘብ እንደሚቻለው የዚህ ዘርፍ ውል የሚመሰረተው የግንባታ ስራዎችን ለመስራት ወይም ለማሰራት አላማ ነው። የመንግስት አስተዳደር አካላት ለተለያዩ ተግባራት የሚውሉ ህንፃዎችን (ት/ቤት፣ ሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ) እንዲሁም ሌሎች የልማት አውታሮችን (መንገድ፣ ድልድይ፣ ግድብ) እና ሌሎችን ለመስራት ሙያው ካላቸው እና በዘርፉ ከተሰማሩ ተቋራጮችና መሀንዲሶች ጋር በመዋዋል ከፍተኛ ገንዘብ እና ሀብትን በማፍሰስ የውል ግዴታዎችን ይመሠርታሉ። ዘርፉ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ እና የሰለጠነ የሰው ሃይል የሚንቀሳቀስበት በመሆኑ ግንኙነቱ ውስብስብና አስተዳደሩ ከባድ ነው። ይህንን ውስብስብ ግንኙነት በአግባቡ ለማስተዳደር በመንግስት አስተዳደር አካል እና በተቋራጩ ወይም መሀንዲሱ መካከል ያለውን ግንኙነት በህግ እና በውል መምራት ግድ ይላል። በመሆኑም የግንባታ ስራን የሚመለከቱ በርካታ ህጐች እና ውሎች በብዛት ይስተዋላሉ።

ህጎች እና ውሎች በርካታ ግዴታዎችን በግንባታ ውል ተዋዋዮች መካከል ያቋቁማሉ። ከሚቋቋሙ ግዴታዎች መካከልም በግንባታ ውል አስተዳደር ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶች የሚፈቱበትን መንገድ በማፈላለግ እና በመጠቀም ረገድ ተዋዋዮች የሚኖርባቸው ኃላፊነት ነው። በብዙዎቹ የግንባታ ውሎች መመሪያዎች ሰፍሮ የምናገኘው አለመግባባቶች የሚፈቱበት መንገድ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርአት ነው። ብዙዎቹ ተዋዋዮች የተፈራረሚቸው የግንባታ ውሎች በውል ግዴታ አፈፃፀም ወቅት የሚፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት በውላቸው ውስጥ ያሰፈሩት አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት ድርድር፣ እርቅ፣ የግልግል ዳኝነት ወይንም ሌላ እንደሆነ በግልፅ ባይታወቅም አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት (dispute resolution mechanisms) በሚል ተቀምጦ ይታያል። ለምሳሌም የአብክመ ጤና ቢሮ ከአለማየሁ ሰለሞን እና አበበ ታረቀ ከሚባሉ ጠቅላላ ተቋራጮች ጋር ጤና ጣቢያዎችን ለማሰራት በተፈራረሚቸው የግንባታ ውሎች አንቀፅ 7 (1) ስር የሚከተለው ስምምነት ሰፍሯል። "ከዚህ ውል ጋር በተያያዘ የሚነሳ ማንኛውም አለመግባባት በቅድሚያ በተዋዋዮች

ቀጥተኛ ውይይት በስምምነት ይፈታል። ውይይቱ 3ኛ ወገን ባለበት ሊደረግ ይችላል።" ከዚህ ስምምነት መገንዘብ የሚቻለው ከግንባታ ውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚፈጠር አለመግባባት ካለ በሁለት መንገዶች ሊፈታ እንደሚችል ነው። የመጀመሪያው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሁለት ተዋዋይ ወገኖች በመነጋገር በውይይት አለመግባባታቸውን የሚቋጨበት መንገድ ነው። ይህ አይነት ውል የአለመግባባትን የመቋጫ ዘዴ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው ድርድር (Negotiation) የሚባለው ነው። ይህንን ዘዴ በመጠቀም መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ውይይቶችን በማድረግ አለመግባባቱን ለመፍታት የሶስተኛ ወገኖችን እገዛ አያሻም። ተዋዋይ ወገኖች እራሳቸው ችግሩን በመለየት እና መፍትሄ በማስቀመጥ ለተግባራዊነቱ እራሳቸውን በውል ወይም በስምምነት የሚያስገድዱበት መንገድ ነው።

ሁለተኛው በውሎቹ የተቀመጠው ያለመግባባትን መፍቻ ዘዴ የሶስተኛ ወገኖችን ተሳትፎ ያመላክት እንጅ የየትኛው አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት እንደሆነ ለማሳየት ያስችግራል። በቀደመው የፅሁፋችን ክፍል በሶስተኛ ወገኖች በመታገዝ አለመግባባት የሚቋጨባቸው የተለያዩ መንገዶች እንዳሉ ተመልክቷል። እነዚህም ማስታረቅ (conciliation)፣ ማግባባት (Mediation)፣ እና ግልግል (Arbitration) ናቸው። ሶስቱ በሶስተኛ ወገኖች አስታራቂ፣ አግባቢ እና አሸማጋይ ወይም ገላጋይነት ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባት የሚቋጨባቸው ናቸው። ታዲያ ከፍብሎ በተጠቀሱት የግንባታ ውሎች ቁጥር 7 (1) ስር "ውይይቱ 3ኛ ወገን ባለበት ሊደረግ ይችላል" የሚለው ሁለተኛ አረፍተ ነገር ከሶስቱ የትኛውን አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት ያመለክታል? ወይስ በድርድር ወቅት ለተዋዋይ ወገኖች (ለተዳዳሪዎች) በጀርባ በመሆን ሞያዊ ድጋፍ የሚሰጡትን ልዩ አዋቂዎች (Experts) ለማመልከት የተቀመጠ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ያጭራል። በውሎቹ ቁጥር 7(1) ስር የተቀመጠው ስምምነት በተዋዋያይ ወገኖች መካከል አለመግባባት ከተፈጠረ ከፍርድ ቤት ውጭ ባለ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት ስምምነት ሊፈታ እንደሚችል በደምሳሳው ከማመልከት በቀር የትኛውን አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት ስራ ላይ ሊውል እንደሚችል ስለማያመለክት ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ነው። በአፈጻጸም ወቅት ያለውን አስቸጋሪነት ለማስረዳት የአብክመ ውኃ ኃብት ልማት ቢሮ እና በታሪኩ ገብረየስ ጠቅላላ ውኃ ስራዎች ተቋራጭ መካከል ባለው ክርክር የአብክመ ጠቅላላ ፍርድ ቤት በፋይል ቁጥር 36167 በቀን 28/02/2007 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ መሰረት ተዋዋይ

ወገኖች በስምምነታቸው መሰረት ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት መቋጨት ስለነበረባቸው በፍትህ ቢሮ አማካኝነት የተፈፀመውን የውል ስምምነት መመልከት ይቻላል፡፡

የስምምነቱ መግቢያ የሚከተለውን አስፍሯል "-----ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት ከመታየቱ በፊት ፍርድ ቤቱ የማከራከር ስልጣን የለውም በማለት በሰጠው ብይን መሰረት ጉዳዩን ከገላጋይ ዳኝነት ይልቅ በግልግል መጨረሱ ጊዜንና ወጭን የሚቆጥብ መሆኑን ሁላችንም ወገኖች በማመን በአብክመ ፍትህ ቢሮ አገላጋይነት (አደራዳሪነት) በፍታብሄር ህግ ቁጥር 3307 እና ተከታዮቹ መሰረት የሚከተለውን የግልግል ስምምነት እናደርጋለን፡፡ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ግልግል፣ የግልግል ዳኝነት እና አደራዳሪ የሚሉት ቃላት አጠቃቀም የተነሳ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች በመካከላቸው ያለውን ክርክር ለመቋጨት የትኛውን አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት እንደተጠቀሙ ለመረዳት ብዥታ እንደነበር ግልፅ ነው፡፡ "በፍትህ ቢሮ አደራዳሪነት" የሚለውን ሀረግ ስንመለከት ክርክሩ የተቋጨው በድርድር ነው ወደሚለው መደምደሚያ ያመራናል፡፡ የውሉን ተራ ቁጥር 3 አረፍተ ነገር አያይዘን ስናነበው ጉዳዩ የተቋጨው በድርድር እንደሆነ ይበልጥ ያሳምነናል፡፡ በሌላ በኩል በጥቅሱ ውስጥ "ጉዳዩ ከገላጋይ ዳኝነት ይልቅ በግልግል መጨረሱ ጊዜንና ወጭን የሚቆጥብ" የሚለው ሀረግ ሲታይ የግልግል ዳኝነት እና ግልግል የተለያዩ ሁለት አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች ያሉ ይመስላል፡፡ በጥቅሉ የውሉ ሰነድ አጠቃላይ ይዘት ሲመረመር በአማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች ላይ ግልፅ የሆነ ግንዛቤ ተይዞ እንዳልተዘጋጀ መረዳት ይቻላል፡፡

ይህ አይነቱ የግንዛቤ ችግር በውሎች ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ የተለያዩ ህግጋትን በያዙት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አለመግባባት ከተፈጠረ ተስማሚ በሆነ የሙግት መፍቻ ስርዓት (Amicable dispute settlement mechanisms) እንደሚፈታ ይደነግጋሉ፡፡ ለምሳሌ የመንግስት ድርጅቶችን ወደግል ይዞታነት ለማዞር የወጣው አዋጅ ቁጥር 146/1998፣ የፔትሮልየም አዋጅ ቁጥር 295/1996፣ የማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1993 እና ሌሎችም ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በህግጋቱ ውስጥ የተቀመጡ ድንጋጌዎች በጠቅላላ አነጋገር የተገለፀ በመሆናቸው የትኛውን አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት እንደገለፀ ለመገንዘብ ያስቸግራል፡፡ በተለይም ከአስተዳደር ውሎች ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት የግልግል ዳኝነት ከከለከለው የኢትዮጵያ የፍታብሔር ህግ አንቀፅ 315(2) አንጻር ሲታይ ድንጋጌዎች በጥንቃቄ ተመርምረው መተርጎም አለባቸው፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 80/97 አንቀፅ 10(3) ስር "የባለስልጣኑ ዋና የስራ አስኪያጅ በቦርዱ ሲፈቀድለት አለመግባባቶችን

ከፍርድ ቤት ውጭ በስምምነት ሊፈታ ይችላል" እነዚህ አለመግባባቶች በስምምነት የሚፈቱት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ነው "ይላል" [ትርጉም የፀሀፊው] ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው አለመግባባቶችን ከፍርድ ቤት ውጭ በሚደረግ ስምምነት መቋጨት እንደሚቻል፤ ስራ እስኪያጁ ይህንን ማድረግ የሚችለውም በቦርዱ ፈቃድ እና መመሪያ እንደሆነ ነው። ሆኖም አለመግባባቶችን ከፍርድ ቤት ውጭ በስምምነት ለመቋጨት የትኛውን አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት መጠቀም እንዳለበት በግልፅ አያመለክትም። ተመሳሳይ ድንጋጌን የያዙ በርካታ አዋጆች በኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ ሲሆን እነዚህን አዋጆች በአግባቡ ፈትሾ ህግ አውጭው የትኛውን የሙግት መፍቻ ሥርዓት በህጎቹ ውስጥ ማካተት እና መገልገል እንደፈለገ በጥንቃቄ በመለየት ስራ ላይ ማዋል በየዘርፉ የሚገኙ የህግ ባለሙያዎች ሀላፊነት እና የሙያ ብቃትን ይጠይቃል።

በግንባታ ውል አስተዳደር ውስጥ የብዙዎቹ ግንባታ ውሎች አካል ሆኖ የሚያገለግለው የሲቪል ግንባታ ስራዎች ቋሚ የውል መተዳደሪያ ደንቦች መመሪያ አንዱ ነው። ይህ መመሪያ ከፍ ብሎ ከተመለከትናቸው ህጎች ለየት ባለ ሁኔታ ከግንባታ ውል ጋር በተያያዘ ጉዳዩን አስመልክቶ የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበት አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት ግልግል እንደሆነ በአንቀፅ 67 ላይ ተመልክቷል። በ1999 ዓ.ም የወጡት ቀይ እና ቢጫ መፅሀፍ ተብለው የሚጠሩት የአለምአቀፍ የግንባታ ውል ሰነዶችም እንዲሁ በአንቀፅ 20(6) ስር ይህንኑ የሙግት መፍቻ ስርዓት እንደ አይነተኛ የክርክር መቋጫ ዘዴ አድርገው አስፍረውት ይነበባል። ከዚህ በላይ በተመለከትናቸው ሰነዶች መሰረት ከግንባታ ውል “በተቋራጩና በአሰሪው መካከል ከውል በቀጥታ የመነጨ ወይም ከውል ጋር በተያያዘ በስራው አፈፃፀም ሂደት ላይም ሆነ ስራው ከተፈፀመ በኋላ ወይም ውሉ ከመቋረጡ በፊትና በኋላ ወይም የውል ግዴታን ባለመወጣት የመነጨ ክርክር.....” በግልግል ይቋጫል ይላል። ይህ አነጋገር የግንባታ ውሎችን አፈፃፀም በተመለከተ የሚነሱ አለመግባባቶች በግልግል ሊፈቱ እንደሚችሉ በግልፅ ያመላክታል። ከፍ ብሎ እንደተመለከትናቸው ህጎች በየትኛው አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት መፈታት እንዳለበት መመሪያው ሳይገልፅ አላለፈም። በመሆኑም በዚህ መመሪያ መሰረት ከግንባታ ውል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚመነጩ አለመግባባቶች በየትኛውም ደረጃ ማለትም በውል አመሰራረት፣ አፈፃፀምም ይሁን ከግዴታ አፈፃፀም ወቅትም ይሁን በኋላ ከተከሰቱ በግልግል ሊቋጭ እንደሚችል ያመለክታል።

ድንጋጌው ክርክሩ ወይም አለመግባባቱ መቼ እና በማን ሊቋጭ እንደሚገባው ጭምር ያስረዳል፡፡ እንደ ድንጋጌው ከግንባታ ውል ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች ከዘጠና ቀን በማይበልጥ ጊዜ በመሀንዲሱ ገላጋይነት እልባት ሊያገኙ ይገባል፡፡ በክርክሩ ወቅት አለመግባባቱን ምክንያት በማድረግ የመንግስት የግንባታ ስራ ሊቋረጥ አይገባም፡፡ ይልቁንም በመሀንዲሱ በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ በዚህ አካል ወይም በወኪሉ አማካኝነት የተሰጠው ውሳኔ በተከራካሪ ወገኖች ላይ አስገዳጅ ውጤት ይኖረዋል፡፡

ከላይ በተመለከትናቸው ጉዳዮች ላይ በህግ ባለሙያዎችም ሆነ በዘርፉ በተሰማሩ ሌሎች ባለሙያዎች አዕምሮ ውስጥ የሚመላለሱ እና እስካሁንም ድረስ እልባት ያላገኙ ጥያቄዎች አሉ፡፡ እነዚህም መሀንዲሱ ገላጋይ ሆኖ ሲሰራ ገለልተኛ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል ወይ? መሀንዲሱ ዳኝነት ለመስጠት የሚያስችል በቂ የህግ እውቀት ይኖረዋልን? በዚህ ገላጋይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የሚጠየቅ ይግባኝን የማየት ስልጣን የመንግስት አስፈፃሚ አካል ለሆነ መስሪያ ቤት ማለትም ለስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር እንዴት ይሰጣል? የዳኝነት ስልጣን እና የህግ እውቀት በሌለው መ/ቤት እና ባለሙያ እንደ ቅደምተከተሉ የተሰጠው የይግባኝ ውሳኔ የመጨረሻ እና አስገዳጅ መሆኑ ፍትሀዊ ይሆናልን? የሚሉትን ጥያቄዎች ያስነሳል፡፡

## 7. የእርቅ ስምምነት እና የግልግል ዳኝነት ውሳኔ አፈፃፀም

በቀደሙት የዕሁፋችን ክፍሎች አለመግባባቶች ሊፈቱ የሚችሉበትን ልዩ ልዩ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች ተመልክተናል፡፡ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶችን በመጠቀም ባለጉዳዮች ስምምነት ላይ ይደርሳሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ጉዳዩ በግልግል ቢታይም ገላጋዩ ወይም የቤተዘመድ ሽማግሌው በውሉ መሰረት ውሳኔ እንደሚሰጥ ይጠበቃል፡፡ በባለጉዳዮች የተደረሰበት ስምምነት ወይም በባለጉዳዮች የተሰጠ ውሳኔ ሲፈፀም ወይም ስራ ላይ ሲውል የተፈጠረው አለመግባባት ይከስማል፡፡ በባለጉዳዮች መካከል ያለው አለመግባባት እልባት አግኝቶ ባለጉዳዮቹ ቀደም ሲል ወደ ነበራቸው መልካም ግንኙነት እስካልተመለሱ ድረስ ክርክሩ ቢቋጭም አለመግባባቱ ጠፋ ወይም ቀረ ለማለት ያስቸግራል፡፡ አለመግባባቱን ለማክሰም የስምምነቱ ወይም የውሳኔው መፈፀም ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ የዕሁፍ ክፍል የስምምነት ወይም የገላጋዮች ውሳኔ አፈጻጸም ከኢትዮጵያ ህግ አንጻር ምን እንደሚመስል በመዳሰስ

ከግንባታ ውል ጋር የተያያዙ አለመግባባቶችን በተመለከቱ የሚደረስባቸው ስምምነቶች (ውሳኔዎችን) እንዴት ተፈጻሚ እንደሚሆኑ በአጭሩ ለመመልከት እንሞክራለን፡፡

### 7.1. በስምምነት የተደሰረሰባቸው ውሳኔዎች አፈጻጸም ውጤት

ባለጉዳዮች በመካከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባት በድርድር፣ በእርቅ ወይም በመግባባት ሲቋጩ የሚደርሱበትን ስምምነት በፅሁፍ ያሰፍራሉ፡፡ ይህም ስምምነት በሁለቱ ወገኖች መካካል እንደውል ይቆጠራል፡፡ ውሉም በተዋዋዮች ላይ በኢትዮጵያ የፍታብሔር ህግ አንቀፅ 1679 እና 1731 መሰረት ህግ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዚህም መሰረት ተዋዋዮች የደረሱበትን ስምምነት ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንን መርህ ታሳቢ በማድረግ ብዙ ተዋዋይ ወገኖች የውል ግዴታ በስምምነት ውላቸው ውስጥ ያስቀምጣሉ፡፡ ለምሳሌ በደ/ማርቆስ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና በአስቱር መንግስቱ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭና ውሀ ስራዎች ድርጅት መካከል በተደረገ የስምምነት ውል (settlement agreement) ገጽ 5 ላይ የስምምነት ገደብ በሚል ርዕስ ውሉ በተዋዋዮች መካከል አስገዳጅ እንደሆነ የሚገልፅ አረፍተ ነገር ሰፍሯል፡፡ ይህም የስምምነት ውል (settlement agreement) በተዋዋዮች መካከል የመፈፀም ግዴታን እንደሚያቋቁም ያስገነዝባል፡፡ ምንም እንኳ የስምምነት ውሉ በተዋዋዮች መካከል በተደረገ ድርድር ወይም እርቅ የተደረሰበትን ተፈፃሚነት ያለው ስምምነት ያዘለ ቢሆን እንደውል ከመቆጠር አልፎ እንደመጨረሻ ፍርድ በቀጥታ ተፈፃሚ ላይሆን ይችላል፡፡ አንደኛው ወገን ግዴታውን እንደውሉ ባይፈፅም የሌላኛው ወገን እጣ የሚሆነው እንደውሉ ይፈፀምልኝ የሚል ክስ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ነው፡፡

ይህ አይነቱ ውል የቀረበለት ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ሊሰጠው የሚችለው ውሳኔ ምን ሊሆን ይችላል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የኢትዮጵያ የፍታብሔር ህግ አንቀፅ 3312 እና የኢትዮጵያ የፍታብሔር ስነ-ስርዓት ህግን ከአንቀፅ 284-292 ያሉትን ድንጋጌዎች አጣምሮ በማንበብ መረዳት የዳኞች ሙያዊ ሀላፊነት ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ የፍታብሔር ህግ አንቀፅ 3312(1) ግልግል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ይግባኝ ሳይኖረው መጨረሻ ሆኖ እንደተፈረደ ፍርድ ስልጣን አለው የሚል ድንጋጌ ተቀምጧል፡፡ ይህም በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተደረገ የስምምነት ውል ወይም ድርድር እንደመጨረሻ ፍርድ ሆኖ እንደሚወሰድ እና ድጋሜ በፍርድ ቤት ክርክር እንደማይደረግበት ያስገነዝባል፡፡ ድንጋጌውን መሰረት በማድረግም በስምምነት በተቋጨ ጉዳይ ላይ ክስ ሲመሰረት ተከሳሹ በድጋሜ ልከሰስ አይገባም (resjudicata) ክርክር በመቃወሚያነት ሊያነሳ እንደሚችል ከዚሁ ህግ መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንደነዚህ አይነቶች ጉዳዮች በሚያጋጥሙ ጊዜ ግዴታው እንደውሉ ያልተፈፀመለት ወገን ግልግሉ (settlement agreement) እንዲፈፀምለት በኢትዮጵያ የፍታብሔር ስነ-ስርዓት ህግ አንቀፅ 284 መሰረት ጉዳዩ በተፋጠነ ስነ-ስርዓት እንዲፈፀምለት "summary execution" ሊጠይቅ ይችላል። ፍርድ ቤቱም ጥያቄውን ተቀብሎ ተጠሪ ፈፅሞ እንዲቀርብ ወይም የማይፈፅምበት ምክንያት ካለ ይህንኑ የሚገልፅ መልስ በፅሁፍ እንዲያቀርብ ያዘዋል። በዚህ መንገድ ተፈፃሚ የሚሆነው ስምምነት በፍርድ ቤት ክርክር ባልተጀመረባቸው ጉዳዮች ላይ በባለጉዳዮች መካከል ስምምነት ላይ የተደረሰ እንደሆነ ነው። ባለጉዳዮቹ በፍርድ ቤት በክርክር ሂደት ላይ ባለ ጉዳይ ላይ እርቅ ወይም ስምምነት ካደረጉ አፈፃፀሙ ሌላ ገፅታን ይላበሳል። ይኸውም ስምምነቱ በፍርድ ቤት ለህግ እና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑ ተረጋግጦ ተመዝግቦ እና ፀድቆ የፍርድ መዝገቡ አካል ሆኖ ይያያዛል። በእንዲህ አይነቱ ስምምነት ላይ የአፈፃፀም ክርክር የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በቀጥታ ትዕዛዝ በመስጠት ስምምነቱ እንዲፈፀም ያደርጋል።[51] በአጭሩ ጉዳያቸውን በስምምነት ማለትም በድርድር ወይም በእርቅ የሚቋጩ ባለጉዳዮች የደረሱበትን ስምምነት (settlement agreement) እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቁጠር የመፈፀም ግዴታ እንዳለባቸው ከፍ ብሎ ከተመለከትናቸው ውሎች እና ህግጋት መገንዘብ ይቻላል።

### 7.2 የግልግል ዳኝነት ውሳኔ አፈፃፀም /Enforcement of Arbitration Award/

የግልግል ዳኝነት ክርክር ሂደት ከአማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች ይልቅ ወደ መደበኛው የክርክር ስርዓት እንደሚቀርብ እና በዚህ የክርክር ሂደት አልፎ የተሰጠው ውሳኔ እንደፍርድ እንደሚቆጠር ከፍ ብሎ ተመልክተናል። ውሳኔው እንደፍርድ ተቆጥሮ እንደሚፈፀምም የኢትዮጵያ የፍታብሔር ስነ-ስርዓት ህግ ከአንቀፅ 352 ጀምሮ ያሉ ድንጋጌዎች ያመላክታሉ። በተለይም አንቀፅ 352 እና 355 በግልግል ዳኝነት የተሰጠው ውሳኔ እንደመጀመሪያ ፍርድ ተቆጥሮ ጉዳዩን በይግባኝ ለመመልከት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ እንደሚቀርብበት በግልፅ ይደነግጋሉ። ከዚህም የገላጋይ ዳኝነት ውሳኔ ፍርድ ሆኖ እንደሚፈፀም እና ጉዳዩን በይግባኝ የማየት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ብቻ ሊያሻሽለው ወይ ሊሽረው እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። የግልግል ዳኝነቱን ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ የማየት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ካላገደው፣ ካላሻሻለው ወይም ካልሻረው በቀር ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የማየት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ውሳኔ ተደርጎ ይፈፀማል።

[51] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 277 ንዑስ ቁጥር ፩ እና 2

# 8 መደምደሚያ

የመንግስት የግንባታ ውል መንግስት ህዝባዊ አገልግሎቶቹን ለመስጠት የሚያስችሉትን የግንባታ አይነቶች ለማስገንባት የሚፈፅመው የውል አይነት ነው። መንግስት በርካታ የውል አይነቶችን የሚገባ ሲሆን የግንባታ ውል በአይነቱ ልዩ ነው። ምክንያቱም የግንባታ ውል በመንግስት መ/ቤቶች ግዴታ ሰጭነት /አሰሪነት/ ከተቋራጭ ጋር በሚፈጠር ስምምነት የሚቋቋም ይሁን እንጅ በርካታ ተዋዋይ ወገኖች በስሩ ስላሉት ነው። እነዚህም መሀንዲስ /አማካሪ/፣ ቀያሽ (servior) አርክቴክት እና ሌሎችም ናቸው። ግዴታ ተቀባይ /ተቋራጭ/ እየተባለ በሚጠራው ወገንም በኩል እንዲሁ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ተዋዋይ ወገኖች ይገኛሉ። እነዚህም በንዑስ ተቋራጭነት በየስራ ዘርፉ ግዴታ የሚገቡና የአሰሪውን የግንባታ ስራ በተሟላ መልኩ ሰርቶ ለማስረከብ ከተቋራጩ ጋር ስምምነት የሚያደርጉ ናቸው።

እነዚህ ተዋዋይ ወገኖች በቁጥር ብዙ ይሁኑ እንጂ በውሉ የሚያቋቋመው ግዴታ የአሰሪውን የግንባታ ስራ በወቅቱ አጠናቆ ማስረከብና ከአሰሪው የስራውን ዋጋ መቀበል ነው። ይህንን ዋና ግዴታ በመፈፀም የውሉን አላማ ለማሳካት አሰሪና ተቋራጭ እየተባሉ የሚጠሩ ዋና ዋና ተዋዋይ ወገኖች በውሉ የሚጣልባቸው መሠረታዊ ግዴታዎች ያሉ ሲሆን እነዚህም በፅሁፉ ተብራርተዋል።

ግዴታዎቹን በውሉ መሠረት ለመፈፀም ተዋዋይ ወገኖች ዋስትና በማቅረብ ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። በተለይም ተቋራጩ የሚገባውን ግዴታ በውሉ መሠረት እንደሚፈፅም ለማረጋገጥ ከጨረታ ማስከበሪያ ጀምሮ ልዩ ልዩ ዋስትናዎችን እንዲያስይዝ ህጉ ስርዓት ዘርግቷል። በዚህ መሠረት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና፣ የመልካም ስራ አፈፃፀም ማረጋገጫ ዋስትና፣ የቅድሚያ ክፍያና ሌሎችንም የዋስትና አይነቶች ማቅረብ በመንግስት ግንባታ ውል አስተዳደር ውስጥ የተለመደ ነው።

እነዚህን ዋስትናዎች በአግባቡ አሟልቶ የፈረመ ተቋራጭ የግንባታውን ውል በመፈረም ስራውን ማከናወን እንደሚጀምር ይጠበቃል። የግንባታ ስራ የበርካታ ባለሙያዎችን ክህሎትና ችሎታ ይጠይቃል። በመሆኑም አፈፃፀሙ ውጣ ውረድ የተሞላበትና በርካታ ችግሮች ያሉበት ነው። ከነዚህም መካከል አዘውትረው የሚከሰቱትና በተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባት የሚፈጥሩት የስራ መዘግየትና የጊዜ ይራዘምልኝ ጥያቄ፣ የመዘግየት ካሳ፣ ስሌትና አከፋፈሉ የለውጥ ስራ ጥያቄና ተቀባይነት፣ የስራው ጥራት መጓደልና ጥገና፣ የስራ ርክርብና ሌሎችም

ናቸው። እነዚህን ችግሮች ለመፍታትና በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሊፈጠር የሚችለውን አለመግባባት ለመዳኘት የሚያግዙ በርካታ ህጎችና መመሪያዎች ያሉ ቢሆንም ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ ችግሮቹ በተዋዋዬቹ ሲፈቱ አይስተዋሉም። ይልቁንም ጉዳዬቹን በመደበኛ ክርክር እንዲቋጩ የማድረግ ዝንባሌ ከፍ ያለ ነው። ይሁን እንጂ ይህን አይነቱ ጉዳይን የመቋጨት ዘዴ አዋጭ እዳልሆነ በብዙ ምሁራን ይነገራል። በመሆኑም አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች ግምት ዉስጥ መግባት ይኖርባቸዋል።

አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች በዚህ ረገድ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት ላቅ ያለ ሚና እንዳላቸዉ ታምኖ አልፎ አልፎ በዘርፉ በስራ ላይ እየዋሉ ናቸዉ ። በስራ ላይ እየዋሉ ያሉ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶቹም ድርድር፣ ማግባባት፣ እርቅ እና የግልግል ዳኝነት ሲሆኑ በሀገራችን በተለይም በአማራ ክልል በመንግስት የግንባታ ውል አስተዳደር ውስጥ በስፋት በስራ ላይ እየዋለ ያለው ድርድር ነው። ማግባባት፣ ዕርቅና የግልግል ዳኝነት የሀገራችን የፍታብሄር ህግ ፣የፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህግና ሌሎችም ላይ ተደንግገው ቢገኝም በስራ ላይ እየዋሉ አይደለም። ይልቁንም በጥናቱም በናሙናነት በተወሰዱ የውል ስምምነቶች ውስጥ በሀሳብ ተደባልቀውና ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ሆነው ሰፍረው ተስተውለዋል። በተለያየ ጊዜ በሚወጡ ልዩ ልዩ አዋጆች ውስጥ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች አለመግባባቶችን ለመፍታት በባለጉዳዬች አገልግሎት ላይ ሊውሉ እንደሚችሉ ቢገለፅም አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ተለይቶ ባለመመልከታቸው አፈፃፀሙን ይበልጥ አስቸጋሪ አድርጎታል። በመሆኑም በአማራ ክልል የመንግስት ግንባታ ውል አስተዳደር ውስጥ ከድርድር በቀር ሌሎች አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች በስራ ላይ እየዋሉ አይደለም። በተለይም በስራ ላይ ቢውል በርካታ ፋይዳዎችን ሊያስገኝ የሚችለው እና በሀገራችን የህግ ማዕቀፍ ከድርድር ይልቅ የተሻለ የህግ መሠረት ያለው የግልግል ዳኝነት በስራ ላይ እየዋለ አይደለም። ከድርድር የዘለሉ ጉዳዬችን በቀጥታ ወደ መደበኛ ክርክር ከመውሰድ ይልቅ በግልግል ዳኝነት ማየቱ ጊዜን፣ጉልበትንና ወጭን ከመቆጠብ አንፃር የራሱ አስተዋዕኦ ስላለው በሀገሪቱ ብሎም በክልሉ ያሉትን የግልግል ማዕከሎች በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴነት መጠቀሙ ተገቢ እንደሆነ የፅሁፉ አቅራቢ ያምናል።

# መልካም አስተዳደርን በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ በማስፈን ረገድ የጠበቆች ሚና

**ወርቁ ያዜ ወዳጅ***

## መግቢያ

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን በአጠቃላይ እና በየክልል መንግሥታት በስፋት የመንግሥትንና አጠቃላይ የህብረተሰቡን ትኩረት ከሳቡትና መነጋገሪያ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል በዋነኛነት በመንግሥት ተቋማት ውስጥ የመልካም አስተዳደር እጦት መስፈንና የሙስና እና ብልሹ አሰራር መስፋፋት ይገኙበታል። እነዚህ ችግሮች ከሚታዩባቸው የመንግሥት ተቋማትና የሥራ ዘርፎች መካከልም የፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ አንዱ እንደሆነ በተደጋጋሚ እየተወሳ ያለ ጉዳይ ነው። በፍትሕ አስተዳደር ዘርፍ ውስጥ የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲሰፍን፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራር እንዲስፋፋ የበኩላቸውን አሉታዊ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው በሚል በህብረተሰቡም ሆነ በመንግሥት አካላት ዘንድ በይፋ ከሚወቀሱትና በግልጽ ከሚኮነኑት ወገኖች መካከልም ጠበቆች ይገኙበታል።

የዚህ ጽሁፍ ዓብይ ዓላማም መልካም አስተዳደርን በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ በማስፈን ረገድ የጠበቆች ሚና ምን እንደሆነ ለማሳዬት፣ በዚህ ዘርፍ ውስጥ ስለሚስነዘሩ ክሶችና ስለሚቀርቡ የህዝብ እሮሮዎች ተገቢና በቂ ግንዛቤ ለማስያዝና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በመዋጋትና በመቅረፍ ረገድ ጠበቆች የድርሻቸውን እንዲወጡ ለማነሳሳት ነው።

በዚህም መሠረት ጽሁፉ በቅድሚያ መልካም አስተዳደር ከሚገለጽባቸው አንኳር ጉዳዮች አንጻር የፍትሕ አስተዳደሩን ቦታና በዚህ ረገድ ጠበቆች ያላቸውን ሚና በአጭሩ ይዳስሳል። በመቀጠልም ለመልካም አስተዳደርና ፍትሕዊ አሰራር ተቃራኒ ናቸው በሚል መደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ አቀራረብና አጋጣሚዎች በየቦታው የሚነሱትን አንዳንድ የጠበቃ ተግባራትንና የሥነ-ምግባር ጉድለቶችን በመዘርዘር ስለችግሮቹ የበለጠ ግንዛቤ እንዲያዝ ለማድረግ

---

*ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም፣ ረዳት ፕሮፌሰር፤ ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፣ ሕግ ትምህርት ቤት። የዚህ ጽሁፍ የመጀመሪያ ረቂቅ ከዚህ በፊት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ የሚገኘው የጠበቆች ማህበር መጋቢት 17 ቀን 2008 ዓ/ም በክልሉ ለሚገኙ ጠበቆችና ሌሎች የፍትህ አካላት ባለሙያዎች አዘጋጅቶት በነበረው የአንድ ቀን የውይይት መድረክ ላይ ቀርቦ የነበረ ሲሆን ይዘቱ በወቅቱ ከተሳታፊዎች ሲሰነዘሩ በነበሩ ሀሳቦች የበለጠ የዳበረ ነው። ለዚህም ጸሐፊው የክልሉን የጠበቆች ማህበርና በውይይቱ ላይ ተሳታፊ የነበሩትን ሁሉ ለአደረጉት አስተዋፅኦ ለማመስገን ይወዳል።

ይሞክራል። በመጨረሻም መልካም አስተዳደር በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ እንዲሰፍንና ይኸው ዘርፍ ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዳ እንዲሆን በሌሎች አካላት መደረግ ያለበት እንደተጠበቀ ሆኖ ከጠበቆች ምን እንደሚጠበቅ አንዳንድ አንኳር ነጥቦችን በማንሳት የሚመለከታቸውን ሁሉ ለበለጠ ውይይትና መፍትሄ ፍለጋ ለማነሳሳት ይሻል።

1. **መልካም አስተዳደር ከሚገለጽባቸው አንኳር ጉዳዮች አንጻር የፍትሕ አስተዳደሩ ቦታና በዚህ ረገድ ጠበቆች ያላቸው ሚና**

መልካም አስተዳደር በርካታ አላባዎች (components) እና መገለጫዎች ያሉት በአጠቃላይ የህዝብ አስተዳደር ጉዳይንና የመንግሥት አካላትን አሰራር፤ አገልግሎት አሰጣጥና በሂደቶቹ ግለሰቦችንና ህብረተሰቡን ተሳታፊ በማድረግ አጥጋቢ ውጤትንና አዎንታዊ ግብረ-መልስ ማግኘትን የሚመለከት ሰፊ፣ የጠለቀና ፈርጀ-ብዙ ገጽታ ያለው ጽንሰ-ሀሳብ ነው። አስተዳደራዊ እና የዳኝነት ጉዳዮችን ጨምሮ የአንድ ሀገር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች እንዴት እንደሚዋቀሩና እንደሚመሩ፣ የመንግሥት ስልጣን እንዴት በተግባር እንደሚገለጽ፣ የመንግሥት ተቋማት ለዜጎችና በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዴት እንደሚሰጡ፣ ዜጎችና የተለያዩ የህብረተሰብ ቡድኖችም ጥቅማቸውንና መብታቸውን እንዴት እንደሚያስከብሩና በሂደቶቹም እንዴት ተሳታፊ መሆን እንደሚገባቸው ወይም እንደሚችሉ የሚገልጽ ሰፊ ጽንሰ-ሀሳብ ነው። በአንድ የተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሀ-ግብር ሰነድ ላይ የተገለጸውም ይህን የሚያመላክት ነው። ይኸውም መልካም አስተዳደር ሲባል፦

> [It describes] the totality of the exercise of authority in the management of a country's affairs, comprising the complex mechanisms, processes and institutions through which citizens and groups articulate their interests, exercise their legal rights and mediate their differences. It encompasses the political, economic, legal, judicial, social and administrative authority and therefore includes; government, the private sector and the civil society.[1]

ነው በሚል ተገልጸአል።

[1] United Nations Development Programme (1997): Governance for Sustainable Human Development, as cited by Okibe Daniel Onyekachi, 'Good Governance a Catalyst to Sustainable Development', *(4) (4.3) Afro Asian Journal of Social Sciences (2013),* P. 3.

ከተጠቀሰው ምንጭ ላይ መረዳት እንደሚቻለው የመልካም አስተዳደር ጽንሰ-ሀሳበ ሰፊና በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖርን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የህግ፣ የዳኝነት፣ የማህበራዊ እና የአስተዳደራዊ ጉዳይን ሁሉ አጠቃልሎ የሚይዝ ወይም የሚመለከት፣ ከመንግሥት አልፎም የግል ሴክተሩንና የሲቭል ማህበረሰቡን ግንኙነት ሁሉ የሚመለከት ሰፊ ጽንሰ-ሀሳብ ነው። ይኸውም በአንድ በኩል የመንግሥት ሥልጣንን በያዙ አካላት እና በሌላ በኩል ደግሞ ዜጎች እንዲሁም ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ቡድኖች የሚኖራቸውን ጤናማና የሰመረ መስተጋብር የሚመለከት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ዜጎችና የህብረተሰቡ ልዩ ልዩ ቡድኖች መብታቸውንና ጥቅማቸውን በተመለከተ መናገርና ማስከበር ስለሚችሉበት ሁኔታና በመንግሥትና በግል ሴክተሩ አሰራር ወይም አገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሁም ባለቤት የሚሆኑበትን ጥልቅና ፈርጀ-ብዙ ገጽታ ያለውን ግንኙነት የሚገልጽ ጽንሰ-ሀሳብ ነው።

ይህ የመልካም አስተዳደር ጽንሰ-ሀሳብ በተለይ በሕግ አወጣጥ፣ አፈጻጸምና ትግበራ እንዲሁም መሻሻል ወይም የመሻር ሂደቶች ላይ ሊኖር የሚገባውን የህብረተሰብ ተሳትፎ ጨምሮ የእነዚህን ተግባራት ጥራት፣ ውጤታማነትና ለህዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ መከናወን፣ እንዲሁም እነዚህን ተግባራት በተፈላጊው የውጤታማነት ደረጃ ለማከናወን የሚያስችል ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ብቃት ያለው፣ ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ፣ ከአድሎአዊነት፣ ከዘፈቀዳዊና የሙስና አሠራር የራቀ፣ በህግ የሚመራ በሰለጠነ የሰው ኃይል የተገነባ የህዝብ አስተዳደር መኖርን ሁሉ ታሳቢ የሚያደርግ ነው።[2] አንድ ፍሎሬንቲኖ ፒ ፌሊሲያኖ የተባሉ የህግ ባለሙያና የቀድሞ የፊሊፒንስ ዳኛ ይህን አስመልክቶ ሲጽፉ፡-

> Good governance relates to the participatory nature, the quality and efficiency and transparency of these processes of law prescribing, law-applying and law-enforcing, and law-revision or law-repeal. Indispensable for the efficacy of these inter-related processes is the existence of 'well-functioning public institutions' staffed by trained individuals who are accountable to the general community and who are bound by and do

[2] ሻሌንድራ ዲ ሻርማ የመልካም አስተዳደር ባህሪያትን (Characteristics of good governance) ሲዘረዝሩ፡-

- participatory, consensus oriented, accountable, transparent, responsive, effective, efficient, equitable, and inclusive and rule of law ናቸው ይላሉ። (Shalendra D. Sharma, Democracy, 'Good Governance, and Economic Development', *Taiwan Journal of Democracy, Volume 3, No.1*, (2007), P.31).

comply with laws and regulations and apply them in an efficient and transparent manner, without arbitrariness or corruption.[3]

ብለዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊም መልካም አስተዳደር በብቃት የሚሰሩና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ፣ ዜጎች ዕውቅናና ድጋፍ ሰጥተው በባለቤትነት የሚሳተፉባቸው፣ ሰብአዊ መብቶች የሚከበሩባቸውና የህግ የበላይነት ዕውን የሚሆንባቸው የፖለቲካ፣ የህግ እና የአስተዳደር ተቋማት መኖርን ወይም መገንባትን የግድ የሚል መሆኑን በማለት ፡-

….creating well-functioning and accountable institutions - political, juridical and administrative - that citizens regard as legitimate, through which they participate in decisions that affect their lives, and by which they are empowered. Good governance also entails a respect for human rights and the rule of law generally.[4] በማለት ገልጸውታል።

የቀድሞው የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ኮፊ አናን በተጨማሪ እንደአስገነዘቡት መልካም አስተዳደር ሲባል ድህነትን ለማጥፋት እና ልማትን ለማስፈን በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስና ዋነኛ ቁልፍ የሆነ ነገር ነው። ዋና ጸሐፊው 'good governance is perhaps the single most important factor in eradicating poverty and promoting development[5] በማለት ነው መልካም አስተዳደር ድህነትን በመዋጋትና ልማትን በማስፈን ረገድ ያለውን ቁልፍ ቦታ በአጽንኦት የገለጹት። ይህ ጽሁፍ ይዞት ከተነሳው ውስን ጭብጥ እና ዓላማ አንጻር በዚህ ንዑስ ርዕስ በአጭሩ ለመዳሰስ የምንሞክረውም በዚህ ሰፊና ፈርጀ-ብዙ ገጽታ ባለው ጽንሰ-ሀሳብ ውስጥ የፍትሕ አስተዳደሩ ያለውን ቦታ እና በዚህ ላይ ጠበቆች ያላቸውን ሚና ይሆናል።

### 1.1. መልካም አስተዳደር ከሚገለጽባቸው አንኳር ጉዳዮች አንጻር የፍትሕ አስተዳደሩ ቦታ

የመልካም አስተዳደር አላባዎች ከሆኑትና በአንድ ሀገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ህይወትና የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ የላቀ ቦታ ካላቸው ጉዳዮች መካከል በመንግሥት

[3] Florentino P. Feliciano, 'Reflections on Good Governance, Development and Judicial Reform: Some Perspectives on the Problem of Judicial Corruption', *7 Asian Y.B. Int'l L. (1997)*, P. 8.
[4] As quoted by S de la Harpe, C Rijken and R Roos, 'Good Governance', *11 Potchefstroom Elec. L.J. (2008)*, PP. 6-7.
[5] Kofi Annan, *Partnerships for Global Community: Annual Report on the Work of the Organisation* (UN, 1998), as quoted in Julius Court, Goran Hyden and Ken Mease, THE JUDICIARY AND GOVERNANCE IN 16 DEVELOPING COUNTRIES, *United Nations University, World Governance Survey Discussion Paper 9 May 2003*, P. 2.

ተቋማትና የአሰራር ሂደቶች ውስጥ የሕግ ልዕልና (የበላይነት) መረጋገጥ (rule of law)፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሰራር መኖር (transparency and accountability)፣ የሰዎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነጻነቶች መከበር (Protection of fundamental human and democratic rights)፣የዳኝነት ነፃነት መረጋገጥ (guarantee of judicial independence) እና ትክክለኛ የሆነ የፍትሕ አስተዳደር (realization of accurate and proper administration of justice) መስፈን ይገኙበታል፡፡ እነዚህ የመልካም አስተዳደር ዋነኛ መቋቋሚያዎች፣ ምሰሶዎችና መገለጫዎች (constitutive elements, pillars and manifestations of good governance) ሲሆኑ ሁሉም ለአንድ ሀገር ልማት፣ ሠላምና ደህንነት መረጋገጥ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከፍ ያለ ነው፡፡ ዲሞክራሲያዊ አሰራር ባልሰፈነበት፣ የህግ የበላይነትና ተጠያቂነት ባልተረጋገጠበት፣ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነጻነቶች ባልተከበሩበት፣ ትክክለኛና ፍትሐዊ የሆነ ፍርድና ውሳኔ የሚሰጥ የፍትሕ አስተዳደር ባልተዘረጋበት በአጠቃላይም ማህበራዊ ፍትሕና እኩልነት ባልሰፈነበት ሀገርና ህብረተሰብ ውስጥ መሠረተ-ጽኑና ዘላቂ የሆነ ልማት፣ ሠላምና ደህንነት ማረጋገጥ የማይቻል መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ የህግ የበላይነትና ተጠያቂነት ባልተረጋገጠበት እንዲሁም ፍትሕ በሌለበት ሀገርና መንግሥት ውስጥ መልካም አስተዳደር ሊሰፍን/ሊኖር፣ የሰዎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነጻነቶች ትርጉም ባለው ሁኔታ ከለላና ጥበቃ ሊያገኙ አይችሉም፡፡

በመሆኑም ሀገራችን ኢትዮጵያን ጨምሮ አብዛኛዎቹ የዓለም ሀገራት በአንድ ሀገር ውስጥ የህግ የበላይነት መስፈን፣ ግልጽነት፣ አሳታፊነትና ተጠያቂነት የተዘረጋበት የመንግሥት አሰራር መኖር፣ እኩልነትና የፍትሕ ተደራሽነት የተረጋገጠበት ምቹ ሁኔታ መኖር የመልካም አስተዳደርን ለማምጣትና ዕውን ለማድረግ በጣም አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታዎችና የመልካም አስተዳደር መቋቋሚያ ፍሬ ነገሮችና እንደገናም መልካም አስተዳደር በተግባር የሚገለጽባቸው አንኳር ጉዳዮች እንደሆኑ ያሰምሩበታል፡፡[6] በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍና በአህጉር አቀፍ ደረጃ ይህ የመልካም አስተዳደር ጥያቄና መልካም አስተዳደር የሚገለጽባቸው እንደ የህግ የበላይነት፣ አሳታፊነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሠራር መስፈን፣ የሰአብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መጠበቅና መረጋገጥ፣ ከሙስና እና ብልሹ አሰራር ነጻ የሆነ አሠራር በመንግሥት

[6] T Von Danwitz, 'Good Governance in the Hands of the Judiciary: Lessons from the European Example', *13 Potchefstroom Elec. L.J. (2010),* PP. 2-16. እውነተኛ የፍትሕ አስተዳደር የመልካም አስተዳደር ምሰሶ ስለመሆኑ "The true administration of justice is the firmest pillar of good government." በዚህ ላይ ተመልክቷል፡፡

ተቋማትና በግል ዘርፉ መዘርጋት፣ የዳኝነት ነጻነት መረጋገጥ እና ተደራሽነቱ፣ ተገማችነቱ፣ ወጭ ቆጣቢነቱና ውጤታማነቱ በህብረተሰቡ ዘንድ አመኔታን ያገኘ ትክክለኛ የፍትሕ አስተዳደር የመፍጠር/የመኖር ጉዳይ....ወዘተ ቅድሚያ ትኩረትን ካገኙ ጉዳዮች መካከል የሚመደቡ ናቸው። ይህን ተግባራዊ ለማድረግም ኢትዮጵያን ጨምሮ አብዛኛዎቹ የዓለም ሀገራት በዓለም አቀፍና በክፍለ-አህጉር ደረጃ የወጡ መግለጫዎችን፣ ውሳኔዎችንና ተፈጻሚነት ያላቸው የህግ ማዕቀፎችን ተቀብለው ፈርመዋል።[7] ለምሳሌ በአውሮፓ የሊዝቦን ስምምነትን (Treaty of Lisbon 2007)[8] እና በአፍሪካ ደግሞ የአፍሪካ ህብረት መመስረቻ ህግን (the Constitutive Act of the African Union 2000)[9] እንዲሁም አዲሱ የአፍሪካ ልማት አጋርነትን (ኔፓድ) (New Partnership for African Development 2001) መጥቀስ ይቻላል።

### 1.2. በፍትሕ አስተዳደር ውስጥ ጠበቆች ያላቸው ቦታና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ የሚጫወቱት ሚና

ጠበቆች በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ ያላቸውን ቦታና በዘርፉ ውስጥ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን የሚጫወቱትን ሚና ለመነጋገር በቅድሚያ ስለጥብቅና ሙያ፣ ስለሙያው አስተዋጽኦና የመጨረሻ ግብ እንዲሁም ሙያው ስለሚጠይቀው ኃላፊነትና ሥነ-ምግባር ግልጽ መሆን ያስፈልጋል።

ለመሆኑ "የጥብቅና ሙያ" እና "ጠበቃ" የሚሉት ቃላት ምንን የሚገልጹ ናቸው? የጥብቅና ሙያ ከንግድ ሥራ በምን ይለያል? ጠበቆች ከህግ አውጭዎች፣ ከዳኞች፣ ከዓቃቢያነ ህግ፣ ከፖሊሶች እና ሌሎች አስፈጻሚዎች እንዲሁም ከተራ ተከራካሪ ወገኖች በምን ይለያሉ? የዳኝነት ሥራን ጨምሮ በአጠቃላይ በፍትሕ ሥራ አካሄድ ላይ ከጠበቆች የሚጠበቀውስ ምንድን ነው? በእውነት ፍለጋ (search of truth) ሂደት ላይ የጠበቆች ተሳትፎና ሚናስ ምንድን ነው? ወይም ምን መሆን ይገባዋል? ለእነዚህና የመሳሰሉ ተያያዥ ጥያቄዎች የምንሰጣቸው መልሶች በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ጠበቆች በፍትሕ አስተዳደሩ ውስጥ

---

[7] በዓለም አቀፍ ደረጃ ለምሳሌ United Nations, Commission on Human Rights "The role of good governance in the promotion of Human Right" Resolution 2000/24 እንዲሁም Office of the High Commissioner for Human Rights "Good governance practices for the protection of Human Rights" (2007). ለበለጠ ግንዛቤም Melvin L M Mbao & G. G Komboni 'Promotion of good governance and combating corruption and maladministration: The case of Botswana'ን ይመልከቱ።

[8] ዳንዊኸር፣ ከላይ በግርጌ ማስተዋሻ ቁጥር 6፣ ከገጽ 3-8 ይመልከቱ።

[9] በአንቀጽ 3 እና 4 ስር የተደነገገውን ይመለከታል። በተጨማሪም Sevidzem Stephen Kingah, 'The African Union's Capacity in Promoting Good Governance', *3 Int'l Org. L. Rev. (2006)* PP. 317ff. ይመልከቱ።

ያላቸውን ቦታና ሚና እንዲሁም በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን በማድረግ ረገድ ጠበቆች ያላቸውን አስተዋጽዖ የሚያመላክቱ ናቸው።

የጥብቅና ሙያ (Lawyering or counseling and advocacy service) በህግ ሙያ ውስጥ ከሚገኙት የሥራ/የአገልግሎት ዘርፎች መካከል አንዱ ሲሆን አገልግሎቱ ብዙ ዓይነት ነው። በበርካታ የግል፣ የቡድን፣ የህዝብ እና የመንግሥት ጉዳዮች ላይ የህግ ምክር አገልግሎት መስጠትን፣ የህግ ይዘት ያላቸው እንደ ውል፣ ኑዛዜ፣ የንብረት አስተዳደር፣ የጋብቻ ውል፣ የሥራ ግንኙነት ውል፣ የህንጻ ግንባታ ውል፣ የንግድ ማህበር መመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ የመሳሰሉ ሰነዶችን በህግ አግባብ ማዘጋጀትን፣ በፍርድ ሰጭ እና ሌሎች የፍትሕ እና የአስተዳደር አካላት ፊት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በህግ መሠረት ማዘጋጀትን፣ በፍርድ ሰጭ አካላት ፊት ሌሎችን ወክሎ የወካይን ትክክለኛ እና እውነተኛ መብትና ጥቅም ለማስከበር፣ የወካይን ወይም የተቃራኒ ወገንን፣ ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ሌላ ሰው ትክክለኛ መብት ወይም ግዴታ፣ ስልጣን ወይም ኃላፊነት፣ የመብት/የጥቅም፣ የግዴታ፣ የሥልጣን፣ የኃላፊነት መጠን...ወዘተ ለፍርድ ሰጭ አካላት በትክክል ለማሳዬት በህግ መሠረት መከራከርን፣ በክርክር ላይ ስለሚገኙ አከራካሪ የፍሬ ነገር ሆነ ተያያዥ የማስረጃ ጉዳዮች ዳኞች እውነታው ላይ እንዲደርሱ ህግ በሚፈቅደው አግባብ መሰረት እውነታው ገሀድ እንዲወጣ መስራትን፣ በሂደቱ ተሳታፊ የሆነ ወገን ከህግና ሥርዓት ውጭ በደል እንዳይደርስበት መከላከልን፣ መሰረታዊ እሴቶችንና የህግ መርሆዎችን በሚቃረን መንገድ የሚወጡ፣ የዜጎችን መብትና ጥቅም የሚጻረሩ የበታች ህጎች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈጻሚነት እንዳይኖራቸውና ይልቁንም በአግባቡ እንዲተረጎሙና በተግባር እንዲውሉ በክርክር ሂደቶች ተቃርኖዎችን ማሳዬትን፣ ዘፈቀዳዊ የመንግሥት ባለስልጣናት ውሳኔዎችና አሰራሮች በግለሰቦችና በቡድኖች ላይ ተገቢነት የሌለው ጫናና ጉዳት እንዳያደርሱ መታገልን እንዲሁም እውነትን፣ ሀቀኛነትንና ህግን ተከትሎ ከፍርድ ቤት ውጭ በሌሎች የክርክር መፍቻ መንገዶች የተከራካሪ ወገኖችን ክርክር/ጭቅጭቅ መፍታትን ወይም መቋጨትን ሁሉ የሚመለከት ሰፊ የሙያ ሥራ (Professional service) ነው። በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ምዝገባና የጠበቆች ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 75/1994 አንቀጽ 2 (2) ስር የተመለከተው ሀሳብም በመጠኑም ቢሆን ይህን ቁም ነገር የሚያስገነዝብ ነው። ይኸውም የጥብቅና አገልግሎት ሲባል፡-

የገንዘብ ክፍያ በመቀበል ወይም ወደፊት የሚገኝ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ወይም ያለክፍያ ፍ/ቤት ፊት ሊቀርብ የሚችል ማንኛውንም ዓይነት የውል ስምምነት፣ የድርጅት ማቋቋሚያ፣ ማሻሻያ ወይም ማፍረሻ ሰነድ ወይም ለፍ/ቤት የሚቀርብ

ሰነድ ማዘጋጀትን፣ ሶስተኛ ወገኖችን በመወከል በፍ/ቤት ፊት ቀርቦ መከራከርን እና ማናቸውንም ዓይነት የህግ ምክር አገልግሎት መስጠትን ያጠቃልላል ሲል ይደነግጋል።

የጥብቅና ሥራ/አገልግሎት የሙያ አገልግሎት (professional service) በመሆኑ ከንግድ ሥራ እና ከሌሎች የሰዎች የዕለት ከዕለት ተግባራትና የመንግሥትና የህዝብ ሥራዎች በጣም ይለያል። የጥብቅና አገልግሎት ትርፍን ዋነኛ ዓላማውና ግቡ አድርጎ ከሚከናወን የንግድ ሥራ በእጅጉ ይለያል። እግረ-መንገዱን የጥቅም ማግኛ (means of income generation) መሆኑ ግልጽ ቢሆንም የጥብቅና አገልግሎት ዋና መነሻ መሰረቱ፣ ዓላማው እና የመጨረሻ ግቡ ፍትሕ እንዲሰፍን ማገዝ፤ የግለሰቦችና የቡድኖች ብሎም የህብረተሰቡ መብቶችና ጥቅሞች እንዲከበሩና እንዲረጋገጡ፣ በአጠቃላይም የህግ የበላይነትና ሥርዓት የሰፈነበት፣ ሠላሙና ደህንነቱ የተረጋገጠ ቤተሰብ፣ ህብረተሰብና ሀገር እንዲኖር ማድረግ ነው። የጥብቅና አገልግሎት በህግ ሙያ የሰለጠኑና ሙያውን ያዳበሩ የህግ ባለሙያዎች ህግን መሰረት አድርገው ለግለሰቦች፣ ለቡድኖች በአጠቃላይም ለህብረተሰቡና ለመንግሥት ህግንና ፍትሕን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡበት ወይም የሚያበረክቱበት የህዝብ አገልግሎት (public service) ዓይነት ነው።

በትክክለኛ የህግ አነጋገር <u>"ጠበቃ"</u> የሚባለውም ከላይ የተመለከቱና ተያያዥ የሙያ አገልግሎቶችን ለግለሰቦች፣ ለቡድኖች፣ ለመንግሥትና ለህብረተሰቡ ለመስጠት የሚችል በህግ ሙያ የሰለጠነ እና በሙያው ሰፊ ልምድ ያለው፣ የፍርድ ቤት አሰራርን የሚያውቅና በዚህ የህግ ሙያ ለመስራት ከመንግሥት የሙያ ፈቃድን ያገኘ የህግ ባለሙያ ነው። አከራካሪነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ምድቡም በአብዛኛው ወደፍርድ ሰጭው አካል የሚጠጋ ነው። በርካታ የህግ ሊቃውንትም "ጠበቃ" የተለዩ ዓይነት የፍርድ ቤት ባለሥልጣን/ባለሙያ (a special kind of court or judicial officer) ነው ሲሉ ይገልጹታል።[10] ለምሳሌ ያህል ዲቦራህ የተባሉ የህግ ባለሙያ፡-

> The lawyer is a special kind officer, functioning not within the legislative or executive realms but the judicial, and then not as a judge or administrator, but in a unique sense. Accordingly, when the court distinguishes a lawyer from a political officer or from an administrative or

[10] Deborah M. Hussey Freeland, 'What is a Lawyer? A Reconstruction of the Lawyer as an Officer of the Court', *31 Saint Louis University School of Law (2012)* PP.425-495. Jeffrey P. Maks, 'Client Perjury: The Constitutional Dilemma presents itself -What is the Standard of Appropriate Conduct for the Criminal Defense Attorney?', *31 S.D. L. Rev. (1985-1986),* P. 651.

ministerial officer of the court, the Court does not divest the lawyer of her office, but simply indicates what kind of officer she is.[11] በማለት ጽፈዋል።

ጥብቅና የሙያ አገልግሎት በመሆኑ ባለሙያው (ጠበቃው) የሚመራው እና የሚሰራው የህግ ሙያ በሚያዘውና የጥብቅና ሥነ-ምግባር በሚፈቅደው መሰረት የጠበቃ ነጻነቱን (professional independence of the lawyer) ጠብቆ ነው። በመሆኑም ጠበቃ ማለት እንዲሁ ደንበኛው ያለውን ወይም ደንበኛው የሚፈልገውን ነገር ይዞ የሚሮጥ ወይም እንዲሁ የደንበኛውን ፍላጎት በማንኛውም መንገድና ዘዴ ለማስከበር ወይም ዕውን ለማስደረግ የሚጥር የደንበኛ መሳሪያ ወይም ጉዳይ ፈጻሚ የሆነ ሰው እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል። በህክምና ሙያ አንድ ታካሚ ከሐኪም ዘንድ ቀርቦ ስለገጠመው የጤና እክል ወይም ጤናን በተመለከተ ወደፊት ሊያደርገው ስለሚገባ ነገር መፍትሔውን ከሐኪሙ እንደሚጠብቅ፣ ምክር እንደሚቀበል ወይም የሚታዘዝለትን መድሃኒት እንደሚወስድ ሁሉ በህግ ሙያም ደንበኞች የራሳቸው የግል ውሳኔና ነጻነት (personal autonomy of client) እንደተጠበቀ ሆኖ ወደፊት ስለሚኖራቸው ጉዳይ ወይም አሁን ስለገጠማቸው የህግ ጉዳይ ከጠበቃቸው የህግ ምክር፣ አቅጣጫ ወይም መፍትሔን የሚያገኙ እንጅ ለጠበቃ ገንዘብ ስለከፈሉ ብቻ እነርሱ እንደፈለጉ የሚያዝዙት ወይም እነርሱ መፍትሔ ነው ብለው የሚሰነዝሩትን ሀሳብ እንዲቀበልና ተፈጻሚ እንዲሆን የሚያደርጉበት የሥራ ወይም የአገልግሎት ዓይነት አይደለም።

የጥብቅና አገልግሎት ለግብይት እንደቀረበ ሸቀጥ ወይም ሌላ ዕቃ እንዲሁ በገንዘብ ሆነ በሌላ ነገር የሚገዛ፣ የሚለወጥ፣ የሚሰጥ፣ የሚገኝ... ወዘተ ነገር አይደለም። የአገልግሎት አቅርቦቱ እንደበሽተኛ እና የህክምና ባለሙያ አገልግሎቱን በሚፈልገው ደንበኛ እና አገልግሎቱን በሚሰጥ ጠበቃ መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚጀመርና የሚመሰረት ቢሆንም ጠበቃው የሚሰጠው አገልግሎት የሚመራው በገበያ ደንብ (በመደራደር አቅም) ሳይሆን የህግ ሙያ በሚያዝዘው ወይም በሚፈቅደው እና የጥብቅና ሥነ-ምግባር በሚፈቅደው መሰረት ብቻ የሚመራ ነው። ደንበኛ ከጠበቃ ለሚያገኘው የህግ ምክርና ሌሎች የህግ አገልግሎቶች የሚከፍለውም በገበያ ድርድር በሚወሰን ዋጋ (market value) ሳይሆን በሙያ ክፍያ (professional fee) የተገደበ ነው።

የጥብቅና ሙያ የራሱ የሆነ ጥብቅ የሙያ እና የሥነ-ምግባር ደንብ/መመሪያ ያለው ነው። ጠበቃ የሆነ ሰው ምን ዓይነት ሙያዊ ብቃትና ዝግጅት እንዲሁም ምን ዓይነት ባህሪና ሥነ-

[11] ዲቦራህ፣ ከላይ ግርጌ ማስተዋሻ ቁጥር 10፣ ገጽ 429.

ምግባር ሊኖረው እንደሚገባ በሙያ እና ሥነ-ምግባር ደንብ (Professional and Ethical Code of Conduct) ውስጥ ከሞላ ጎደል ተዘርዝሮ የሚገኝ ሲሆን የጥብቅና ሙያን መርጦ በዚህ አገልግሎት የሚሰማራ ጠበቃ ሁሉ በቅድሚያ ሊያውቀውና ሊተገብረው የሚገባ ነው። ለምሳሌ በሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በፌደራል መንግሥት ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ አውጥተው ለሚሰሩ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 57/1992 ተፈጻሚነት አለው።[12] በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ ለሚሰሩ ደግሞ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ምዝገባና የጠበቆች ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 75/1994 ተፈጻሚነት አለው።

በጥብቅና ሥነ-ምግባር ደንብ ከሚደነገጉ ጉዳዮች መካከልም የጥብቅና አገልግሎት የሚመራባቸውና ማንኛውም ጠበቃ ሊያከብራቸውና ሊተገብራቸው የሚገቡ መርሆዎች (ለምሣሌም ህግን ስለማክበርና ማስከበር፣የፍትሕ አስተዳደርን ስለማገዝ፣ ደንበኛን ጨምሮ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖችንና ጠበቆችን እንዲሁም ዳኞችንና ፍ/ቤትን ስለማክበር፣ ጥብቅናን ጨምሮ የህግ ሙያን ስለማክበር፣ ስለቅንነት፣ ታማኝነት፣ እውነተኛነት)፣ጠበቃ ደንበኛን እንዴት እንደሚቀበልና ከደንበኛ የቀረበለትን ጉዳይ እንዴት እንደሚመረምር፣ ለደንበኛ አስፈላጊ መረጃን ስለመስጠት፣ የደንበኛን ምስጢር ስለመጠበቅ፣ በደንበኛና በጠበቃ መካከል ስለሚኖር የጥቅም ግጭትና ስለተከለከሉ ግንኙነቶች፣ የጥብቅና አገልግሎትን ስለማቋረጥና ስለሚቋረጥባቸው ምክንያቶች... ወዘተ ይገኙበታል። በዚህም መሰረት ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛ የመጣለትን ጉዳይ ተቀብሎ የጉዳዩን ፍሬ ነገርና በማስረጃነት የቀረቡለትን ነገሮች በጥሞናና በማስተዋል በብቃት ከመረመረ በኋላ ጉዳዩ ክስ ለማቅረብ የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ ካገኘው ጉዳዩን መያዝ እንደሌለበት በሙያና ሥነ-ምግባር ደንብ ተደንግጎ ይገኛል። እንዲሁም ማንኛውም ጠበቃ ሌላኛውን ተከራካሪ ወገን ለማጉላላት በማሰብ ክስ ማቅረብ ወይም አከራካሪ የሆነ ጭብጥ በሌለበት ወይም በክርክር ላይ ለውጥ በማያመጣና ግልጽ በሆነ ነገር ላይ ክርክር ማቅረብ እንደሌለበት ተደንግጎ ይገኛል። ሌሎች ዝርዝር የሙያና የሥነ-ምግባር ደንቦችም ይካተታሉ። ጠበቃ የሆነ ማንኛውም ሰው እነዚህንና የመሳሰሉ የሙያና የሥነ-ምግባር ደንቦችን አክብሮና ተከትሎ በመሥራት በህግ ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም በልምድ ያገኘውን ዕውቀትና ክህሎት የፍትህ አስተዳደሩን፣ ደንበኛውንና ህብረተሰቡን በሚጠቅም መንገድ በተግባር ሊያውለው/ሊተረጉመው ይገባል።

[12] ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 6ኛ ዓመት፣ቁጥር 1።

ከላይ እንደተጠቀመውም የጥብቅና ሙያ መነሻ መሰረቶችና መዳረሻ ግቦች የህግ ልዕልና፣ የፍትህ ተደራሽነት፣ በህግ ፊት እኩል መሆንና በህግ መዳኘት/መገዛት እንዲሁም ፍትሐዊነትና የሰዎች በህግ የታወቁ ወይም በህግ መታወቅ ያለባቸው መብቶችና ጥቅሞች መከበር፣ የህግ ከለላና ጥበቃ ማግኘት ናቸው። ጥብቅና የህግ ሙያ ዘርፍ አንዱ አካል በመሆኑም ጠበቆች የሚሰጡት የሙያ አገልግሎት ዕሳቤው በግለሰቦች፣ በቡድኖች፣ በህብረተሰቡና በመንግሥት አካላት መካከል የሚኖሩ መስተጋብሮች ሁሉ ሠላም የሰፈነባቸው፣ ህግና ሥርዓት የነገሰባቸው እንዲሆኑ ማድረግ ነው። በተጨማሪም በቤተሰብ፣ በግለሰቦችና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ አለመግባባቶች በህግ አግባብና በሰለጠነ መንገድ በሥርዓት እንዲፈቱና መልክ እንዲይዙ፣ መብታቸው የተጣሰባቸው ወይም ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች በህግ በተመለከተው አግባብ ከለላ ወይም ካሣ እንዲያገኙ፣ ጥፋት ያደረሱ ሰዎች ደግሞ በህግ ተጠያቂ ወይም ኃላፊ እንዲሆኑ የሚደረግበት ነው። በአጠቃላይ አገልግሎቱ ህግ እንዲከበር፣ የህግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ ሁሉም ሰው በህግ ፊት እኩል እንዲሆንና እኩል እንዲዳኝ፣ የሰመረ ግለሰባዊ፣ ቤተሰባዊ እና ማህበረሰባዊ ግንኙነት እንዲኖር፣ ፍትህ እንዲሰፍን የሚሰጥ አገልግሎት ነው። በመሆኑም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ምዝገባና የጠበቆች ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 75/1994 አንቀጽ 25 ስር “ማንኛውም ጠበቃ ህግን ለማስከበርና ፍትህን ለማስገኘት የፍትሕ አስተዳደሩን የማገዝ ኃላፊነት አለበት” የሚል አጠቃላይ መርህ ተደንግጎ እናገኛለን። የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 3ም በተመሳሳይ ይደነግጋል። አልፎ አልፎ አንዳንድ ሰዎች ሲናገሩ እንደሚሰሙትና እንደሚመስላቸው ሳይሆን የጥብቅና ሙያ ለህግ መከበርና ፍትሐዊነት መረጋገጥ፣ ለመብቶች ከለላና ጥበቃ ማግኘት እንዲሁም ለአጥፊዎች በህግ ፊት መጠዬቅ ዋነኛ አጋዥ መሳሪያ ነው። ጠበቃን እንዲሁ የህግ ዕውቀቱን ተጠቅሞ በሰዎች መካከል ጥል የሚፈጥር፣ በሰዎች የሰመረ ግንኙነት ወይም ትንሽ የሻከረ ግንኙነት ውስጥ በመግባት የሚያከራክርና የሚያጨቃጭቅ ሰበብ የሚፈልግ ነገረኛ ሰው፣ በመዋሸት ወይም ህግን አጣምሞ ወይም አዛብቶ ወይም ማስረጃን ሰውሮ ወይም ሀሰተኛ ማስረጃን አቅርቦ ጥፋት የሰራን ሰው ከተጠያቂነት ነጻ የሚያወጣ ወይም ንጹህ የሆነ ሰውን እንዲጠዬቅ የሚያደርግ፣ ፍርድ ቤትንና ሌሎች የፍትህ አካላትን በሆነ ነገር የሚሸውድ አድርጎ የማዬቱ አዝማሚያ የተሳሳተና ሊታረም የሚገባው አስተሳሰብ ነው።

በትክክል ከተተገበረ የጥብቅና ሙያ እና እውነተኛነት፣ ሀቀኛነት፣ ተአማኒነትና ህግ አክባሪነት አብረው የሚሄዱ እንጅ የሚቃረኑ አይደሉም። በህግ ትምህርት ቤቶችና ማሰልጠኛ ተቋማት

የሚሰጡ ትምህርቶችና ስልጠናዎች አጠቃላይና ዝርዝር ይዘትም ስለእውነተኛነት፣ ስለሀቀኛነት፣ ስለቅን ልቦና፣ ስለተአማኒነትና ህግ አክባሪነት... ወዘተ መልካምነትና ተገቢነት እንዲሁም ስለህጋዊያን ተግባራትና ግንኙነቶች፣ ስለህግ የበላይነትና ፍትሐዊነት፣ የራስንና የሌላውን ትክክለኛ መብትና ጥቅም ስለማክበርና ማስከበር፣ ስለሰላማዊና የሰመረ የሰዎች ግንኙነት... ወዘተ የሚያስገነዝቡና ዕውቀትን የሚያስጨብጡ፣ አዎንታዊ የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ የሚያልሙ እንጅ ስለአፍራሽና ጎጅ ነገሮች የሚያስተምሩ አይደሉም፡፡ ሥራዬ ተብሎ ስለአፍራሽነት፣ ስለተንኮለኛነት፣ ስለሸፍጠኛነትና ነገረኛነት፣ እውነትን ስለመደበቅና በሀሰት ሌላውን ስለማጥፋት፣ ህግን ስለመጣስና ከህግ ተጠያቂነት ስለማምለጥ ትምህርት ወይም ስልጠና እንደማይሰጥ ሁሉም በቀላሉ የሚገነዘበው ነው፡፡ ህግ የሰላም፣ የደህንነት፣ የሥርዓትና የሰመረ መስተጋብር (social harmony) ማስፈኛ መሳሪያ እንደመሆኑ የጥብቅና ሙያም እነዚህን መልካም የህብረተሰብ እሴቶች ማስተግበሪያ መሳሪያ እንደሆነ በሚገባ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ምዝገባና የጠበቆች ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 75/1994 አንቀጽ 25፣26 እና 38 ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 3፣4 እና 26 የሚደነግጉትም ይህን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ማንኛውም ጠበቃ የህግ አገልግሎት ለማግኘት የመጣ ደንበኛን ጉዳይ ተቀብሎ የጉዳዩን ፍሬ ነገርና ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ክርክሩ ህጋዊ መሰረት የሌለው ከሆነ ጉዳዩን መያዝ እንደሌለበት በግልጽ ከመደንገጉም በላይ ለክርክር የሚያበቃ ህጋዊ ምክንያት በተገኘ ጊዜ እንኳ ጠበቃው የደንበኛው ጉዳይ በፍርድ ቤት ቀርቦ ከሚወሰን ይልቅ በእርቅ ቢያልቅ ተገቢውን ውጤት እንደሚያስገኝ ከአሰበ ይኸው ጉዳይ በእርቅ እንዲያልቅ ጥረት እንዲያደርግ ነው የሚጠበቀው፡፡ በተጨማሪም ከላይ እንደተገለጸው ማንኛውም ጠበቃ ህግን ለማስከበርና ፍትህን ለማስገኘት የፍትሕ አስተዳደሩን ከማገዝ በተጨማሪ ደንበኛውን፣ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖችን፣ ሌሎች የህግ ባለሙያዎችንና ፍርድ ቤትን ማክበር ይጠበቅበታል፡፡ ማንኛውም ጠበቃ ሙያውንና በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ የሙያ ኃላፊነቱን በቅንነት፣ በታማኝነት እና በእውነተኛነት መወጣት እንዳለበትም በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በዝርዝር ወደጠበቃ ሚና እና ተሳትፎ ሲገባ እንደየህግ ሥርዓቱና የሀገራት የህግ አቋም የተወሰኑ ልዩነቶች ቢኖሩም በአጠቃላይ አነጋገር ግን ጠበቆች በፍትሕ አስተዳደሩ ውስጥ የማይተካና ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ በተለይም እንደኢትዮጵያ ባሉ በአመዛኙ የፍልሚያ የሙግት

ሥርዓትን (Adversarial/Accusatorial system) በሚከተሉ ሀገሮች ጠበቆች የጎላ ተሳትፎና የማይተካ ሚና አላቸው። በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ሆነ በአጠቃላይ በመንግሥትና በግል ሴክተሩ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን የሚጫወቱት ሚና ከፍ ያለ ነው። የህግ የበላይነትን እና ሰብአዊ መብቶችንና ነጻነቶችን በማስጠበቅና በማስከበር ረገድ ጉልህ ሚና አላቸው። የዳኝነት አካሉ የራሱን ነጻነት በማስጠበቅ ሁሉንም ወገን በህግ ፊት በእኩልነት እንዲያስተናግድና የህግ የበላይነትን እንዲያረጋግጥ፣ ህግ አውጭው አካል ያስቀመጠውን የክርክር ሂደትና የማስረጃ አቀባበል ተከትሎ ትክክለኛና ፍትሐዊ ፍርድና ውሳኔ በተገቢው አጭር ጊዜ እንዲሰጥ በማድረግ ረገድ ጠበቆች የሚጫወቱት ሚና የላቀ ነው። ፊሊፕ ቦይላት የተባሉ ሰው በዚህ ላይ ሲጽፉ፡-

> Lawyers play a fundamental role in upholding the rule of law and human rights. [….] Lawyers lead cases from initial complaints to enforced judgment. The quality and efficiency of judicial proceedings and the success of conflict resolution depend to a large extent on the qualification and professional conscience of the lawyer. The rule of law cannot exist without an independent and professional judiciary, and the latter cannot function properly without a well-organized profession of lawyers, characterized by integrity and professionalism.[13] ብለዋል።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ፊት ተቀባይነትን አግኝቶ የጸደቀው International Principles on the Independence and Accountability of Judges, Lawyers and Prosecutors በሚል የሚታወቀው ሰነድ ላይ፡-

> Lawyers are, with judges and prosecutors, one of the pillars upon which human rights and the rule of law rest. Lawyers play an essential role in protecting human rights and in guaranteeing that the right to a fair trial is respected by providing accused persons with a proper defence in court.

በሚል የተደነገገውም በዓለም አቀፍ ደረጃ የጥብቅና ሙያና ጠበቆች ሊያበረክቱ የሚችሉትን በጎ አስተዋጽዖ በግልጽ የሚያሳይ ነው።

[13] Philippe Boillat, Enhancing Judicial Reform in the Eastern Partnership Countries, May 2012 P. 7 (Foreword).

በተጨማሪም ኦከቹክው ኦኮ የተባሉ የህግ ምሁር ጠበቆች በአንድ ሀገር ውስጥ የዲሞክራሲ እሴቶች እንዲገነቡና ዲሞክራሲያዊ አሰራር እንዲሰፍን ከሚያደርጉት አስተዋጽዖ በተጨማሪ ዘፈቀዳዊ የሆነ የመንግሥት ባለስልጣናት አሰራርን በመቆጣጠር፣ የሰዎችን መብቶች በማስከበርና በማስፋፋት፣ የህግ ተቋማትን በማሻሻል፣ የሲቭል ማህበራትን በማነቃቃትና በአጠቃላይም የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽዖ እንዳላቸው እንዲህ በማለት ይገልጹታል፡-

> Lawyers, more than any other group in society, have the capacity to check the arbitrary powers of government expand and protect citizens' rights, reform legal institutions, rejuvenate the civil society, and induce attitudinal changes necessary to sustain democracy.[14]

ከላይ የተጠቀሰው International Principles on the Independence and Accountability of Judges, Lawyers and Prosecutors የተሰኘው ሰነድ እንደዚሁ፡-

> In protecting human rights, lawyers play a crucial role in protecting the right against arbitrary detentions by challenging arrests, for example through presenting *habeas corpus*. Lawyers also advise and represent victims of human rights violations and their relatives in criminal proceedings against alleged perpetrators of such violations and in proceedings aimed at obtaining reparation. Furthermore, lawyers are in the best position to challenge before courts national legislation that undermines basic principles of human rights and the rule of law. በማለት የጠበቆችን ቦታና የላቀ ሚና ያስቀምጣል፡፡

የፍትሕ ሥርዓቱ የታለመለትን ዓላማና ግብ ያሳካ ዘንድ በተለይም በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ ሂደቱም ሆነ የመጨረሻ ውጤቱ የተዛባ ወይም የተሳሳተ እንዳይሆን የጠበቆች መኖርና በሂደቱ ውስጥ በብቃትና በነጻነት መሳተፍ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ እውነትን ለማግኘት (ከእውነታው ለመድረስ) ብቻ ሳይሆን የእውነት ፍለጋው ሂደትና ግብዓት ህግ አውጭው ባስቀመጠው መንገድና በህግ በተፈቀደው የማስረጃና ሌሎች የማረጋገጫ ዓይነቶች (evidence and other probative materials such as plea of guilty, judicial notice and

[14] Okechukwu Oko, 'Consolidating Democracy on a Troubled Continent: A Challenge for Lawyers in Africa', *33 Vand. J. Transnat'l L. (2000*), PP. 583-584.

presumptions) መሆኑን በአግባቡ ለመምራትና ለማረጋገጥ፣ ንጹኃን ላይ የተሳሳተ ፍርድና ውሳኔ እንዳያርፍ፤ወንጀል ወይም ሌላ ጥፋት በፈጸሙት ላይም በሀሰተኛ ማስረጃና አግባብነት በሌለው ነገር እንዲሁም በህግ ከተፈቀደው ሥርዓት ውጭ በሆነ አሰራር ፍርድ እንዳይሰጥና ፍትሕ እንዳይዛነፍ፣ የዳኝነት አካሉ የተዛባ ወይም የተሳሳተ ትዕዛዝ፣ ብይን፣ ፍርድና ውሳኔ እንዳይሰጥ በማገዝ በአጠቃላይ ትክክለኛ ፍትሕ እንዲሰጥ ለማድረግ የጠበቆች መኖርና በብቃትና በነፃነት መሳተፍ አስፈላጊነቱ የታመነ ነው፡፡ ፊዮና ሊቨሪክ የተባሉ የህግ ባለሙያ በተለይ በወንጀል ክስ ጉዳይ በጠበቃ መረዳት አስፈላጊነት ላይ ሲጽፉ እንደገለጹት የጠበቃን ድጋፍ ማግኘት የስነ-ልቦና ድጋፍን ለማግኘት (provision of emotional support)፣ተገቢነት ከሌለው አያያዝ ለመጠበቅ (protection from ill-treatment)፣ ያለመናገር መብት ምንነትን ተረድቶ ተፈጻሚ ለማድረግ (assistance in understanding or enforcing the right to silence) እና በስህተት ወንጀለኛ ተብሎ የፍርድ ተጎጅ መሆንን አስቀድሞ ለመከላከል (preventing wrongful conviction) በእጅጉ ያግዛል፡፡[15]

ከማስረጃ መምረጥ፣ አሰባሰብና አደረጃጀት እንዲሁም ተገቢነት ያለው አቤቱታ ከማቅረብ ጀምሮ ህግንና ሙያው የሚጠይቀውን ከፍ ያለ ሥነ-ምግባር ጠብቆ ትክክለኛ እና ፍትሐዊ ፍርድ እንዲሰጥ በማድረግ ረገድ ጠበቆች ያላቸው ሚናም የላቀ ነው፡፡ በፍርድ ሰጭ አካላት ፊት ከሚደረግ ክርክር ውጭም ጠበቆች ከላይ እንደተጠቀመው ለአገልግሎት ፈላጊዎች ከህግ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በማሳወቅ፣ ትክክለኛ እና እውነተኛ ምክር በመለገስና ህጋዊ ሰነዶችን በማዘጋጀት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ህብረተሰቡንና የፍትሕ አስተዳደሩን በእጅጉ የሚያግዝ፣ መልካም አስተዳደርን የሚያረጋግጥ፣ መልካም ዕሴቶችን የሚያጎለብት ጠቀሜታው የጎላ ህዝባዊ አገልግሎት (public service) ነው፡፡

በሀገራችንም ከህገ-መንግሥቱ ጀምሮ ከላይ ለማሳዬት እንደተሞከረው ልዩ ልዩ ህጎች ስለጥብቅና ሙያና ስለጠበቆች ዕውቅና ከመስጠት አልፎ ስለሚናቸው በግልጽ ይደነግጋሉ፡፡ ስለሙያውና አገልግሎት አሰጣጡ እንዲሁም በሙያው የተሰማሩ ሰዎች ሊከተሉት ስለሚገባ ሥነ-ምግባርና ስለተጣሉባቸው ኃላፊነቶች በዝርዝር የሚናገሩ ደንቦች በርካታ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የኢፌዴሪ ህገ-መንግሥት በአንቀጽ 20(5) ላይ በወንጀል ስለተከሰሱ ሰዎች መብት ሲደነግግ “በመረጡት የህግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትሕ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው” ማለቱ

[15] Fiona Leverick, ‘The Right to Legal Assistance during Detention’, *15 Edinburgh L. Rev. (2011)*, P. 354.

እንዲሁም በአንቀጽ 21(2) ላይ በጥበቃ ስር ስለአሉና በፍርድ ስለታሰሩ ሰዎች መብት ሲደነግግ "ከህግ አማካሪዎቻቸው ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኟቸውም ዕድል የማግኘት መብት አላቸው" ማለቱ የጥብቅና ሙያና ባለሙያዎቹ የሰብአዊ መብት እንዳይጣስና ፍትሕ እንዳይጓደል በማድረግ ረገድ ያላቸውን የላቀ ቦታና ሚና በግልጽ ያሳያል። ሀገራችን ተቀብላ በአጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሁሉአቀፍ መግለጫ[16]፣ዓለም አቀፍ የሲቭልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት[17] እንዲሁም የአፍሪካ የግለሰቦችና ህዝቦች ቻርተር[18] ተመሳሳይ አቋም እናገኛለን። እነዚህ ዓለምአቀፋዊ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ሰነዶች በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 9(4) መሠረት የኢትዮጵያ ህግ አካል ተደርገው የሚውሰዱና ተፈጻሚነት ያላቸው ናቸው። ከዚህ ሌላም የኢትዮጵያ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ (ለምሣሌ አንቀጽ 61)፣የፍትሐ ብሔር ህግ እንዲሁም የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ሁሉ ስለጥብቅና ሙያና ስለጠበቆች ግልጽ ድንጋጌዎችን ይዘዋል።

ከእነዚህና ከመሳሰሉት አጠቃላይ የህግና የጥብቅና ሙያ መርሆዎች፣ የህግ ማዕቀፎችና የሥነ-ምግባር ደንቦች ተነስተን በሀገራችን በተጨባጭ በተግባር ያለውን ስንቃኝ ግን ብዙ ግራ የሚያጋቡ እና አንዳንድ ጊዜም የህግ ሙያን በግልጽ የሚቃረኑ ክስተቶች እናገኛለን። ይህ ደግሞ ምክንያቱ ብዙና የተለያዬ ነው። ለመሆኑ ራሳቸው ጠበቆች ስለጥብቅና ሙያና ስለተሸከሙት ኃላፊነትና ሚና ምን ያህል የተሟላ ግንዛቤ አላቸው? ስለጥብቅና ሙያና ስለጠበቆች ሚና በፍትህ አካላትና ሌሎች የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ያሉ ዳኞች፣ ዓቃቢያነ ህግ፣ ፖሊሶችና ሌሎች ባለስልጣናትና ሠራተኞች እንዲሁም አጠቃላይ ህብረተሰቡ ያለው ምስልና ግንዛቤስ ምን ያህል ከላይ ከገለጽነውና ከህጉ ጋር የተገናዘበ ነው? ጠበቆች እንደህክምና ባለሙያዎች ወይም በሌላ የሙያ ሥራ ላይ እንደተሰማሩ ሰዎች ህግን አክብረውና ተከትለው፣ ሥርዓትን ጠብቀው፣ ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ-ምግባር ተላብሰው፣ በነጻነትና በአመኑበት ብቻ ለመስራትስ ምን ያህል ከግለሰቦች፣ ከቤተሰብ፣ በአጠቃላይም ከህብረተሰቡና ከመንግሥት አካላት ያልተገባ ጫናና ግፊት ነጻ ናቸው? የሚሉት ጥያቄዎች በተጨባጭ ከሚታዬውና

[16] ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሁሉአቀፍ መግለጫ (እ.ኤ.አ. 1948 )፣ አንቀጽ 10ን መንፈስ ይመለከታል። ይህ ሰነድ ያካተታቸውን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ኢትዮጵያ ሀገራችን በ1983 ዓ/ም በጸደቀው የሽግግር ወቅት ቻርተር ተቀብላ ያጸደቀቻቸው እንደነበር የሚታወስ ነው።

[17] ዓለም አቀፍ የሲቭልና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት (እ.ኤ.አ በ1966 የወጣና ከ1976 ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለ)፣ አንቀጽ 14(3)(ለ) እና (መ) በግልጽ የሚደነግገውን ይመለከታል። ይህን ስምምነት ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. ሰኔ 11 ቀን 1993 ተቀብላ ማጽደቋ ይታወቃል።

[18] የአፍሪካ የግለሰቦችና ህዝቦች ቻርተር (እ.ኤ.አ በ1981 የወጣና ከ1986 ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ)፣ አንቀጽ 7 (1) (ሐ) የሚደነግገውን ይመለከታል።ይህን ቻርተር ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. ሰኔ 15 ቀን 1998 ተቀብላ ማጽደቋ ይታወቃል።

በየጊዜው ከሚነገሩት አንዳንድ ነገሮች አንጻር የሚያጠያይቅ ይመስላል። ልዩ ልዩ የዲሞክራሲ ዕሴቶች፣ መቻቻልና የሌላውን መብትና ጥቅም ማክበርና ማስከበር፣ የህግ የበላይነትና ተጠያቂነት ገና በሚገባ ባልዳበሩበት ማህበረሰብ ውስጥ እንዲሁም በአድሎአዊነት፣በሙስና፣ በዘመድ አዝማድና በሌላ ግንኙነት መስራት ... ወዘተ በሚገባ በማህበረሰቡ ባልተወገዘበት አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ፣ የዳኝነት ተቋሙ ሆነ ሌሎች የፍትሕ አካላት እንዲሁም ሌሎች የመንግሥትና የግል ዘርፎች፣ የሐይማኖት ተቋማትና የሲቭል ማህበራት በየዘርፋቸው መልካም የህብረተሰብ እሴቶችንና ህጋዊ አሰራሮችን ዕውን ለማድረግ በሚያስችል የተሟላ ቁመና ላይ ገና ባልደረሱበት ሁኔታ የጥብቅና ሙያና በሙያው ውስጥ የተሰማሩት ጠበቆች ብቻቸውን እንደደሴት ነጥረው ይወጣሉ ብሎ ማሰብም የዋህነት ነው።

ለተዛባ አመለካከትና ተግባር ምክንያት የሚሆኑ ከሙያውና ሙያው ከሚጠይቀው ሥነ-ምግባር ውጭ የሆኑ በርካታ የጠበቃ እንከኖች በሀገራችን እንዳሉ ባያከራክርም የተዛባው አመለካከትና ተግባር ግን ከጠበቃው አልፎ ሙያውን፣ ሙያው ሊያበረክት የሚችለውን፣ በሙያው ተገልጋይ የሆነውንና ከእያንዳንዱ ጠበቃ ጀርባ ያለውን ግለሰብ እና በአጠቃላይም የህብረተሰብ መብትና ጥቅም እንዳያስረሳ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። ሙያውን በአሉታዊ ጎኑ ጎልቶ እንዲታይና ጠበቃ ማለት የእውነት ፍለጋን የሚያደናቅፍ የህግ ባለሙያ ነው (lawyers as obstacles to the discovery of the truth) ብሎ ለመፈረጅ ሰበብ የሚሆኑ ጉልህና ጥቃቅን እንከኖች ከዚህም ከዚያም ቢኖሩም ችግሮቹን መዋጋትና መቅረፍ ሲገባ ያልተገባ ጽንፍ መያዝና ሙያው እንዲቀጭጭ ማድረግ የባሰ ጥፋት ነው የሚያስከትለው።

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የጥብቅና ሙያና ጠበቆች የሚሰጡት አገልግሎት የግለሰብ መብቶችንና ጥቅሞችን ከማስከበር በላይ በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን፣ የህግ የበላይነትና ተጠያቂነት እንዲረጋጥ፣ የሰዎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነጻነቶች እንዲከበሩና እንዲረጋገጡ፣ ትክክለኛ ፍትሕ እንዲሰጥ ለማድረግና ህብረተሰቡ በህግና በፍትሕ ተቋማት ብሎም በአጠቃላይ በመንግሥት ላይ አመኔታ እንዲኖረው... ወዘተ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወቱ መቸውኑም ቢሆን መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው።

በእርግጥ እነዚህንና የመሳሰሉ ግላዊና ህዝባዊ የሙያ አገልግሎቶችን ለማበርከት በቅድሚያ ራሳቸው ጠበቆች የህግ ሙያ የሚጠይቀውን ዕውቀት፣ ክህሎት፣ ልምድና ሥነ ምግባር የተላበሱ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ከላይ የጠቀስነው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ምዝገባና የጠበቆች ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 75/1994

መግቢያው ይህን በተመለከተ በግልጽ ይናገራል። ይኸውም "የጥብቅና አገልግሎት በህግ ሙያ የሰለጠነ እና በሙያው ሰፊ ልምድ ያለው፣ የፍርድ ቤት አሰራርን ጠንቅቆ የሚያውቅ" ሰው የሚሰማራበት የህግ ሙያ መሆኑን ከመግለጽ በአሻገር ይህ የህግ ባለሙያ "የታማኝነት፣ የቅንነትና የእውነተኝነት መንፈስን የተላበሰ ሰው" መሆን እንደአለበት በግልጽ ተመልክቷል። በተጨማሪም የጥብቅና አገልግሎት ሙያ ለጠበቃው "ለህግ የበላይነትና ለፍትሕ መስፈን ከፍተህ አካላት ጎን በአጋዥነት የሚሰለፍበት ሙያ" እንደሆነ በማሻማ መልኩ ተገልጾ እናገኘዋለን።

የህግ ሙያ በአጠቃላይና የጥብቅና ሙያ በተለይ የሚጠብቀውና የሚያዝዘው ከላይ የተመለከቱና የመሳሰሉ መልካም ዕሴቶችን በተግባር ላይ ማዋል ነው። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በጥብቅና አገልግሎት ዘርፉ ውስጥ በርካታ እጥረቶችና ጉድለቶች (በሌሎች የፍትህ አካላትና ባለሙያዎች ያሉት እጥረቶችና ጉድለቶች እንደተጠበቁ ሆኖ) ይስተዋላሉ። ከዚህ በመቀጠል የምንመለከተውም በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ መልካም አስተዳደር እንዳይሰፍን ይልቁንም አድሎአዊነትና ኢ-ፍትሐዊነት እንዲነግስ የበኩላቸውን አሉታዊ አስተዋጽዖ እያደረጉ ናቸው በሚል በመንግሥትና በህብረተሰቡ ዘንድ በግልጽ ስለሚነገሩና በተጨባጭም ስለሚታዩ አንዳንድ የጠበቃ ተግባራትና የሥነ-ምግባር ጉድለቶች ይሆናል።

2. **ለመልካም አስተዳደርና ፍትሕዊ አሰራር ተቃራኒ የሆኑ አንዳንድ የጠበቃ ተግባራትና የሥነ-ምግባር ጉድለቶች**

በመግቢያችን ላይ እንደተጠቀመው በሀገራችን በአጠቃላይና በየክልሎች የመልካም አስተዳደር እጦት፣ሙስና እና ብልሹ አሰራር ሰፍኖባቸዋል በሚል በመንግሥትና በህብረተሰቡ ዘንድ ከሚነሱት ዘርፎች መካከል አንዱ የፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ነው። የፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ስንልም በዋነኛነት የፖሊስና ዓቃቢያነ ህግ ተቋማትን፣ ፍርድ ቤቶችንና ማረሚያ ቤቶችን የሚመለከት ነው። በተለይም ስለሙስና ሲነሳ የእነዚህ ተቋማት ስም ብዙውን ጊዜ አብሮ መነሳቱ የተለመደ ነው። በእርግጥ እ.ኤ.አ በ2010 በውጭ ሀገር ባለሙያዎች የተደረገው Diagnosing Corruption in Ethiopia: Perceptions, Realities, and the Way Forward for Key Sectors የተሰኘ ጥናት እንደሚያመለክተው የፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ከሌሎች ሴክተሮች ጋር ሲነጻጸር የሚታይበት የሙስና ችግር በአንጻራዊነት ሲታይ ዝቅተኛ ነው። ግዘፈቱና ጥልቀቱ በህብረተሰቡ ዘንድ ካለው ግንዛቤ ያነሰም ቢሆንም ችግሩ እንዳለ ግን የሚያከራክር አይደለም። በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ የመልካም አስተዳደር እጦት አለ፤ሙስና እና ብልሹ አሰራርም አለ። የተወሰኑ ፖሊሶች፣ ዓቃቢያነ ህግ፣ ዳኞችና የማረሚያ

ቤት ኃላፊዎችና ሠራተኞች በሙስና እንደሚሰሩ በገሀድ እየተነገረ ነው፤ በአንዳንዶች ላይም ርምጃ እንደተወሰደባቸው የሚያሳዩ ማረጋገጫዎች አሉ።

ከሌሎች የመንግሥት ተቋማት አንጻር በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ የሚታየው ችግርና የችግሩ ግዘፈት በንጽጽር ሲታይ ዝቅተኛ ቢሆንም አንድምታው ግን በሌሎች ዘርፎች ከሚታየው በላይ እንደሆነ ግልጽ ነው። የህግ የበላይነትንና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ፣ ያጠፋን ለመቅጣት፣ የተበደለን ለማስካስ፣ የሰዎችን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነጻነቶች እንዲከበሩና እንዲረጋገጡ ለማድረግ፣ ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት፣ ህብረተሰቡ በህግና በፍትሕ ተቋማት ብሎም በአጠቃላይ በመንግሥትና በአሰራሩ ላይ አመኔታ እንዲኖረው ለማድረግ የተቋቋሙት አካላት ራሳቸው በመልካም አስተዳደር ችግር፣ በሙስና እና ብልሹ አሰራር ከተዘፈቁ የሚፈጠረው አሉታዊ ውጤት ግልጽ ነው። እነዚህ ችግሮች መኖራቸው ህብረተሰቡ በፍትሕ አስተዳደር ተቋማትና በአጠቃላይም በህግና በመንግሥት ላይ ያለውን አመኔታ የሚሸረሽር ነው። ሰዎች በህግ ፊት እኩል የማይታዩበት፣ የተበደለ ሰው ትክክለኛ ፍትሕ የማያገኝበት፣ ያጠፋም የማይጠየቅበት ሁኔታ እየሰፋ ከሄደ፣ በአጠቃላይም የፍትሕ አካላቱ አሰራር ግልጽነት ከጎደለው፣ ተደራሽነቱና ተገማችነቱ ጥያቄ ውስጥ ከገባ፣ ውጣ ውረዱና እንግልቱ እንዲሁም የሚያስከትለው ወጭ እየናረ ከሄደ ህብረተሰቡ በህግ የበላይነትና የመንግሥት አሰራር ላይ ተስፋው እንዲሟጠጥ በማድረግ ወደ ሥርዓት-አልበኝነትና ህጉን ወደእጅ የማስገባት አዝማሚያ ሊወስደው ይችላል።

በመሆኑም ምንም ያህል ዝቅተኛ ቢሆን እንኳ በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ የሚታይ የመልካም አስተዳደር ችግር፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራር በቀላሉ ሊታይ አይገባውም። በእርግጥ እነዚህ ችግሮች እንዲኖሩ የሚያደርጉ በርካታ ምክንያቶችና ሰበቦች እንዳሉ ግልጽ ነው። ችግሮቹ እንዲሁ በባዶ በአየር ላይ የሚወለዱ አይደሉምና። ለምሳሌ አንዳንድ ፖሊሶች ወይም ዳኞች ጉቦ በመቀበል እንደሚሰሩ በስፋት የሚነገረውን ለብቻ ወስደን ብንመለከት ይህ ድርጊት ያለጉቦ ሰጭዎችና ጉቦ አቀባባዮች ሊፈጸም እንደማይችል ግልጽ ነው። ህብረተሰቡ እንዲህ ዓይነት ፍላጎት እና ተግባር ያላቸውን ሰዎች (ጠበቃዎችን ጨምሮ) በውስጡ ያለ ውግዘትና ነቀፌታ ታቅፎ መገኘቱ በራሱ ትልቅ  ችግር ነው። ከዳኞች በሙስና መዘፈቅ ጋር በተያያዘ ፌሊሲያኖ ሲጽፉ፡-

> ….corrupt judges do not exist in a vacuum. There are corrupt judges because, *inter alia,* there are corrupt lawyers and litigants willing to offer a

bribe or who, for diverse reasons, are unwilling to resist a demand for a bribe from an aggressively corrupt judge and who refuse to go to the appropriate judicial authority which can discipline and remove such judges.[19] ብለዋል።

ከድሮ ጀምሮ በህብረተሰቡ ዘንድ የላቀ ክበሬታንና አድናቆትን ካገኙት እንደ ህክምና ያሉ የሙያ መስኮች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚመደበው የህግ ሙያና የጥብቅና አገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያዩ ምክንያት ክብሩ እየወረደ በአሁኑ ወቅት በተለይ ጠበቃ ሲባል የማይታመን ወይም በጥርጣሬ የሚታይ ለህግ ሙያ መከበር፤ ለእውነትና አጠቃለይ ትክክለኛ ፍትሕ መስፈን በእውነት የሚወጣና የሚወርድ ሳይሆን ለገንዘብ ሲል የማይገቡ ተግባራትን ሁሉ እስከማድረግ ድረስ የሚንቀሳቀስ ዓይነት ሰው እንደሆነ በህብረተሰቡ ዘንድ የተዛባ ምስል እየተያዘ የመጣበት ዘመን ላይ ደርሰናል። በተጨባጭ በየሀገራቱ ያለው ነባራዊ ሁኔታና ደረጃው ቢለያይም በሀገራችን ብቻ ሣይሆን በሌላው ዓለምም ከጊዜ ወደ ጊዜ ህብረተሰቡ ስለጠበቆች ያለው አመለካከት አሉታዊ ገጽታን እየተላበሰ የመጣ ይመስላል። አንድ በጥብቅና ሙያ በአሜሪካን ሀገር ለበርካታ አመታት ያገለገሉና ስመ-ጥር የሆኑ ሰው ሲናገሩ፡-

[…] Lawyers today are viewed with distrust, dislike, and suspicion by too many people in too many places. The public has a widespread impression that the practice of law has become primarily a money-grabbing, profit maximizing, hustling business, rather than a profession to be admired.[20] ያሉት ከፍ ሲል ስለህግ ሙያና ስለጠበቆች የተጠቀሰውን የህብረተሰብ አመለካከት ለውጥ የሚጠቁም ነው።

ከመልካም አስተዳደር ችግር፣ ከሙስና እና ብልሹ አሰራር ጋር በተያያዘ የሀገራችን ጠበቆች በተለይ የሚከሰሱባቸውና የሚኮነኑባቸው ለመልካም አስተዳደር እንቅፋት የሆኑ፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን የሚያስፋፉ ተግባራትና የሥነ-ምግባር ጉድለቶች እንዳሉ በመንግሥት ባለሥልጣናት፣ በህብረተሰቡና በልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በስፋት በአደባባይ እየተነገረ ነው። ይህን ሀሳብ የሚጋሩ ፖሊሶችን፣ ዓቃቢያነ ህግን፣ ዳኞችንና ሌሎች የህግ ባለሙያዎችን ጨምሮ ጠበቆች በመንግሥት አካላትና በአጠቃላይ በህብረተሰቡ ዘንድ መደበኛ እና መደበኛ

[19] ፌሊሲያኖ፣ ክላይ ግርጌ ማስዋሻ ቁጥር 3፣ ገጽ 15።
[20] Joseph D. Jamail, 'Advocacy and Lawyers and Their Role', *47 Baylor L. Rev. (1995),* P.1162.

ባልሆኑ አጋጣሚዎችና መድረኮች ከሚከሰሱባቸውና ከሚኮነኑባቸው ጉዳዮች/ተግባራት መካከል፡-

- ደንበኞችን ስለጉዳያቸው በሚገባና በጥልቀት ያለመመርመርና ስለሚይዙት/ስለያዙት ጉዳይ አጠቃላይና ዝርዝር የህግና የፍሬ ነገር መሠረት እንዲሁም የማስረጃ ሁኔታ በቂ ግንዛቤ ያለመያዝ፤
- የህግ ወይም የማስረጃ ድጋፍ የሌላቸውን የማያዋጡ ጉዳዮች ገቢ ለማግኘት ሲሉ እንዲሁ መያዝ፤
- አገልግሎት ፈላጊዎች ጉዳያቸውን ከፍርድ ቤት ውጭ በሠላምና በመግባባት እንዲጨርሱ ያለማበረታታት፤
- ጉዳዮችን ከሚያስገኙት የገንዘብ ጥቅም አንጻር እየመረጡ መያዝ፤
- ፖሊስና ዓቃቢያነ ህግ በዳኞች ዘንድ የበለጠ ተሰሚነት አላቸው በሚል የወንጀል ጉዳዮችን በብዛት ያለመያዝ፤
- ከአገልግሎት ፈላጊዎች የሚያገኙትን የገንዘብ ጥቅም በማሰብ ልዩ ስልጠና ወይም የዳበረ ልምድ ባካበቱባቸው የተወሰኑ የህግ ዘርፎች ሳይወሰኑ እንዲሁ ሁሉንም ዓይነት ጉዳይ (irrespective of specialization or relevant sound experience) በድፍረት መያዝ፤
- አቤቱታዎችንና ማስረጃዎችን በበቂ ሁኔታና በህግ አግባብ አደራጅቶ ያለማቅረብ፤
- ከደንበኞች ፍላጎት ውጭ ወይም ደንበኞችን በመገፋፋት ነገሮችን አጋንኖና አወሳስቦ አቤቱታዎችን ማቅረብ፤
- በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ተገቢነቱ አጠያያቂ የሆነ ወይም የተጋነነ የጠበቃ አበል ከደንበኞች መጠየቅ፤
- አገልግሎት ፈላጊዎች ጉዳያቸውን ለመረጡት ለሌላ ጠበቃ እንዳይሰጡ ወይም "ገበያ እንዳያመልጥ" በሚል ስሌት በአገናኝ ደላሎች በመጠቀም፣ ዳኛውን አውቀዋለሁ ወይም ከዳኛው ጋር እንቀራረባለን በሚል እንዲሁም ከጉዳዩና ከክርክር አድማሱ ጋር ያልገናዘበ እጅግ አነስተኛ የሆነ የሙያ ክፍያ ሰብሮ በመንገር ጉዳዮችን መያዝ፤
- የደንበኞችን ምስጢር በተሟላ ሁኔታ አለመጠበቅ፤
- ከተቃራኒ ተከራካሪ ወገን ወይም ጠበቃ ጋር ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት በመፍጠር የደንበኛን ጥቅም/መብት በሚጎዳ ሁኔታ መስራት፤
- ለተያዘ ወይም ለሚያዝ ጭብጥ ደጋፊ ወይም ማስተባበያ የሚሆን ህገ-ወጥ/ሀሰተኛ ማስረጃ እንዲዘጋጅ ደንበኞችን ማገዝ ወይም ለደንበኞች ምክር መለገስ፤
- የተቃራኒ ተከራካሪ ወገን ማስረጃ እንዲጠፋ ደንበኞችን ማገዝ፤
- የደንበኞች ወይም የተቃራኒ ተከራካሪ ወገን ምስክሮች በሀሰት አጥንተው እንዲመሰክሩ ማገዝ፤
- ደንበኞች በህግ የሚጠበቅባቸውን የዳኝነት ክፍያ ላለመፈጸም የሚያደርጉትን ተገቢ ያልሆነ ሽሽት ማገዝ፤

- ለተቃራኒ ተከራካሪ ወገን መጥሪያ በአግባቡ እንዳይደርሰው ወይም ዘግይቶ እንዲደርሰው ደንበኞችን ማገዝ፤
- በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ዳኞች ተገቢ ያልሆነና የሥነ-ሥርዓት ህጉን ያላገናዘበ የመጥሪያ ትዕዛዝ እንዲሰጡ ማሳሰብ/መጠዬቅ፤
- ከመዝገብ ቤትና ሌሎች ድጋፍ ሠጭ የአስተዳደር ሠራተኞች ጋር ተገቢ/ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት በመፍጠር አገልግሎት ማግኘት፣ሰነዶችን ወይም ፋይሎችን ማስደበቅ/ማስጠፋት፤
- የደንበኛን ጉዳይ በአግባቡና በተሟላ ሁኔታ አለመከታተልና ጉዳዩ ያለበትን ሁኔታ/ደረጃ ለደንበኛ ያለማሳወቅ፤
- ከፖሊስና ሌሎች የአስተዳደር አካላት ጋር ተገቢ/ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት በመፍጠር የጉዳዮችን ትክክለኛ አካሔድ ማዛባት፤
- ከዳኛ ጋር ተገቢ/ጤናማ ያልሆኑ ግንኙነቶች በመፍጠር (ለምሳሌ ጉቦ በመስጠት፣ ጓደኝነት በመፍጠር) በጉዳዮች አካሄድ ወይም የመጨረሻ ውጤት ላይ ተጽዕኖ ማሳደር፤የተዛባ ፍርድ ማሰጠት፣
- ክርክሮች በተገቢው አጭር ጊዜ እልባት እንዳያገኙ የህግ ክፍተቶችን አላግባብ በመጠቀም ወይም ሰበብ በመፈለግ በእንጭጭጫፊ ወይም ለተያዘው/ለሚያዘው ጭብጥ አስተዋፅኦ የማያደርጉ መቃወሚያዎችንና ክርክሮችን ማቅረብ፤
- ለተቃራኒ ተከራካሪ ወገን/ጠበቃ፣ ለምስክሮች፣ ለተበዳዮችና ለዳኞች ተገቢውን አክብሮት ያለመስጠት፤
- ለአስፈጻሚ አካላት ባለስልጣኖች፣ ለፍርድ ቤት ኃላፊዎች፣ ለሚዲያ ሰዎች፣ ለፖለቲካ ድርጅቶች ... ወዘተ ተገቢነት በሌለው አካሄድ በመቅረብና በመንገር በሂደት ላይ ባሉ ጉዳዮች ላይ ጉዳዩን የያዙ ባለሙያዎች ጣልቃ እንዲገባባቸውና በተጽዕኖ እንዲሰሩ ማድረግ፣
- ተቃራኒ ተከራካሪ ወገን/ጠበቃ፣ ምስክሮች፣ ግል-ተበዳዮች እንዲሁም ዳኞች በተለያዬ መንገድ/ሁኔታ ተገቢ ያልሆነ የስነ-ልቦና ጫና እንዲደርስባቸው ማድረግ፤
- በፍርድ ተረች ሲሆኑ በዳኛ ሥነ-ምግባር ወይም ችሎታ ላይ ያነጣጠሩ (ያልተረጋገጡ) ግምቶችን ወይም ሀሜታዎችን ለደንበኞችና ሌሎች ሰዎች መንገር ወይም መጋራት፤...ወዘተ የሚሉት ይገኙበታል።

እነዚህና የመሳሰሉት ጉድለቶች፣ ህገ-ወጥና ከሥነ-ምግባር የወጡ ተግባራት ሁሉንም ጠበቃ የማይመለከቱ ሲሆን እያንዳንዱን ነጥብ እየመዘዙ ትክክለኛ ክስ፣ትችት ወይም ኩነኔ ስለመሆን አለመሆኑ ከዚህ ላይ ከመነጋገር ወይም ከመጠራጠር ይልቅ በልበ-ሰፊነትና በቅንነት ነጥቦችን ወደራስ ወስዶ በመመርመር ሙያውን፣ የራስ መተዳደሪያ የሆነውንና ለህብረተሰቡ የፍትሕ አገልግሎት የላቀ ድርሻ ያለውን ቁልፍ የህግ ሙያ እንዲሁም የጥብቅና አገልግሎት በአዎንታዊ

ጎኑ በህብረተሰቡ ውስጥ ለማስረጽና ለማስከበር መጣሩ የተሻለ ይሆናል።[21] ከእነዚህና ሌሎች ያልተጠቀሱ ተግባራትና የሥነ-ምግባር ችግሮች በመራቅ ሙያው በሚጠብቀው ትክክለኛና ህጋዊ መንገድ በመንቀሳቀስ እንዲሁም ሙያው የሚጠይቀውን ችሎታ፣ ዝግጁነት፣ ንጹህነት፣ ሀቀኛነት፣ እውነተኛነት፣ ተአማኒነት፣ ወኔ እና ሌሎች የሥነ-ምግባር እሴቶች በመላበስ በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ መልካም አስተዳደርና ትክክለኛ ፍትሐዊ አሰራር እንዲሰፍን የበኩልን አስተዋፅኦ በማድረግ ከሚቀርቡ ክሶችና አሉታዊ ትችቶች መላቀቅ አስፈላጊነቱ የሚያከራክር አይደለም።

ከዚህ በመቀጠልም በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን፣ ዘርፉ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ግልጽ፣ ተደራሽ፣ ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዳ፣ ተጠየቂነትና የህግ ልዕልና የሰፈነበት እንዲሆን፣ በአሁኑ ወቅት በመንግሥትና በህብረተሰቡ እየተነሳ ያለውን ችግርም ለመቅረፍ ከእያንዳንዱ ጠበቃ ምን እንደሚጠበቅ አንዳንድ ነጥቦችን በአጭሩ እንዳስሳለን።

### 3. መልካም አስተዳደር በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ እንዲሰፍን ከጠበቃ የሚጠበቅ ሙያዊ ተሳትፎና አስተዋፅኦ

በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ከሁሉ በፊት ዘርፉ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ግልጽ እና በቀላሉ ተደራሽ፣ ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዳ፣ ተጠየቂነትና የህግ ልዕልና የሰፈነበት መሆን ይኖርበታል። ማንኛውም ሰው በፖለቲካ አመለካከት፣ በሐይማኖት፣ በፆታ፣ በሀብት ደረጃ... ወዘተ ልዩነት ሳይደረግበት በህግ ፊት እኩል የሚታይበትና የሚስተናገድበት መሆን ይገባዋል። ያለብዙ ውጣ ውረድና ተገቢነት የሌለው እንግልት እንዲሁም ወጭ በተገቢው ጊዜ ትክክለኛና ጥራት ያለው ፍትሕ የሚሰጥበት ዘርፍ መሆን ይገባዋል። የአሰራር ሂደቱ ሁሉ በህጋዊ መንገድ የሚመራ፣ ግልጽና ተገማች እንዲሁም የህብረተሰቡን አመኔታ ያገኘ መሆን ይገባዋል።

ይህ እውን እንዲሆን በሁሉም የመንግሥት አካላትና የግሉ ሴክተር በተለይ ደግሞ በፖሊስና በዓቃቢያነ ህግ ተቋማት፣ በፍርድ ቤቶች እና በማረሚያ ቤቶች እንደገና መፈተሽ ያለባቸው በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ ሆኖ የመንግሥት አካል ባልሆነው የጠበቆች ማህበርና በእያንዳንዱ ጠበቃ በኩልም በርካታ መፈተሽ ያለባቸው ሙያዊ ጉዳዮች፣ አሰራሮችና የሥነ-ምግባር

[21] ከላይ የተዘረዘሩ የጠበቃ ጉድለቶች፣ ጥፋቶችና እንከኖች በትክክል በተጨባጭ የሚታዩና በየጉዳዮች የሚንጸባረቁ መሆናቸውን በውይይት መድረኩ ላይ የተሳተፉት ጠበቆችና ሌሎች የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች የተስማሙበት ሲሆን አንዳንዶች እንዲያውም ችግሩ ከዚህ የከፋና የሰፋ እንደሆነም በምሬትና በሀዘኔታ ገልጸዋል።

ሁኔታዎች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ከዚህ በታች ዋና ዋናዎቹን ለበለጠ ግንዛቤና ለተግባራዊ ለውጥ እናቀርባለን፡፡ እነዚህም:-

- ጠበቆች ራሳቸው ስለጥብቅና ሙያ ትክክለኛ ዕሳቤ (Essence) እና ስለጥብቅና ሙያ መሰረቱ፣ ዓላማና ስለመጨረሻ ግቡ (mission and functions)፣ በዚህ ውስጥ እያንዳንዳቸው ስለአላቸው ሚና እና ስለተሸከሙት የህብረተሰብ ኃላፊነት (role and social responsibility) በሚገባ ግልጽ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ሙያው የሌሎችን ምስጢር የመስማትና የመያዝ፣ የሌሎችን ችግርና ስቀይ የማዬትና የመሸከም፣ የተቸገረን የመርዳት፣ ህግን በመጣስ በሌሎች ላይ ጉዳትን ያደረሱትን በፍትሕ አደባባይ የመፋለም፣ በአጠቃላይም ስለሌሎች መብቶችና ጥቅሞች መከበር ከለላ ሆኖ መቆምን የሚጠይቅ እንደሆነ ምንጊዜም ማስታወስና በተግባር ማዋል ይገባል፡፡ ጀምስ ዲ ጎርዶን በዚህ ረገድ ሲናገሩ፡-

  Good lawyers must have the skills required for professional competence. But this is not enough.They must know how to carry the burdens of other people on their shoulders. They must know of pain, and how to help heal it. Lawyers can be healers. Like physicians, ministers, and other healers, lawyers are persons to whom people open up their innermost secrets when they have suffered or are threatened with serious injury. People go to them to be healed, to be made whole, and to regain control over their lives. These are large and important tasks, and they require all that we have to offer. They require both good minds and good hearts - not only mental acuity and professional skill, but also compassion, righteousness, mercy, and strength to suffer and carry pain. That is what it takes to be a truly good lawyer. And the world desperately needs truly good lawyers.[22]

ያሉት ለእኛም የሚሰራ ነውና ጠበቃ የሆነ ሁሉ ይህን በተግባር ሊተረጉም ይገባል፡፡ ለህግ፣ ለፍትሕ ሥርዓቱ፣ ለህብረተሰቡና ለእያንዳንዱ ተገልጋይ የሚሰጥን ሙያዊ

[22] James D. Gordon as quoted by Therese Maynard, 'Teaching Professionalism: The Lawyer as a Professional' *34 Ga. L. Rev. (1999-2000*), P. 928.

አበርክቶት (contributions) በየጊዜው በመገምገም ማሻሻልም ይገባል። ጥብቅና የህዝብ አገልግሎት የሚሰጥበት ሙያ ከመሆኑ የመነጨ ማህበራዊ ኃላፊነትን የያዘ እንደሆነ መቸም ቢሆን መዘንጋት አይገባም። በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ መልካም አስተዳደር፣ ትክክለኛና ፍትሐዊ አሰራር እንዲሰፍን ምንጊዜም ህጋዊና ሙያዊ ኃላፊነትን መወጣት ያስፈልጋል።

- ጠበቆች የሰለጠኑበት የህግ ሙያ እንዲሁም የሚመሩበት ህግ እና የሥነ-ምግባር ደንብ እንደሚጠይቀውና እንደሚደነግገው የራስን ብቃት (competence) በማሳደግና የራስን ነጻነት (independence) በማስከበር ሥራዬ ብለው በቁም ነገር ተሰልፈው ለደንበኞች የተሟላና ብቃት ያለው ትክክለኛ፣ እውነተኛና በህግ የተደገፈ ምክርና ድጋፍ በተገቢው ጊዜ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ለደንበኞች በቂ ጊዜና ትኩረት ሰጥተው በአግባቡና በጥልቀት ስለጉዳያቸው የመጠይቅና የመመርመር ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይገባል። ከዚህ ላይ ጆሴፍ ዲ ጃሚል የተባሉ የህግ ባለሙያ ያሉትን ማስታወስ ያስፈልጋል፡-

  A lawyer sits in the lofty position of making decisions over people's lives. If he begins to do it without real thought or does it routinely, callously, and without regard to the consequences of his actions, then he is unworthy of the trust placed in him and is no lawyer-indeed, he is no advocate and should think about another line of endeavor….[23]

- ጠበቆች በህግና በህጋዊ አግባብ ብቻ በመስራትና በመንቀሳቀስ፣ በንጹህነትና በሐቀኛነት (honesty and integrity) እንዲሁም በተአማኒነት (loyalty) መስራት ይኖርባቸዋል። ጠበቆች ደንበኞች የነገሯቸውንና ያዘዟቸውን ብቻ ይዘው የሚሮጡ፣ በሀሰትና በማጭበርበር ድርጊት ሳይቀር የደንበኞችን ጥቅምና ፍላጎት የሚያስጠብቁ እንዳልሆኑ በሚገባ ሊታወቅ ይገባል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ከፍ ሲል ከተጠቀሱትና ለመልካም አስተዳደርና ፍትሐዊ አሰራር ተጻራሪ ከሆኑ ጉድለቶች፣ህገ-ወጥና ከሥነ-ምግባር የወጡ ተግባራት መራቅ የግድ ይላቸዋል።

[23] Joseph D. Jamail, 'Advocacy and Lawyers and Their Role', *47 Baylor L. Rev. (1995)*, P. 1160.

- ጠበቆች ለዕለታዊ የገንዘብ ጥቅምና ሌሎች ውስጣዊና ውጫዊ ተጽዕኖዎች ሳይንበረከኩ በወኔና በሙያዊ ፍቅር ለሙያው መርሆዎችና ለህብረተሰቡ ትክክለኛና ጠቃሚ እሴቶች መከበር በጽናት በመቆም (courage & commitment) የድርሻቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ጠበቆች ለአገልግሎት ፈላጊዎችና ደንበኞች ህግን የተከተለ የማማከር፣ህጋዊ ሰነዶች የማዘጋጀት፣አገልግሎት ፈላጊዎችና ደንበኞች አለመግባባታቸውን ከፍርድ ቤት ውጭ በሰላም እንዲፈቱ የማበረታታትና የማገዝ ኃላፊነት እንደአለባቸው ማስታወስና ይህን ኃላፊነት መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡
- ጠበቆች ለህግ፣ ለደንበኞች፣ ለፍርድ ቤት፣ ለተቃራኒ ወገን ተከራካሪ፣ ለምስክሮችና ተበዳዮች እንዲሁም ለሌሎች ጠበቆች ግዴታዎች እንዳሉባቸው ማስታወስና በየዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያቸው መተግበር ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም አንዳንድ ጊዜ የሚያወዛግቡና ግልጽ ያልሆኑ የጠበቃ ሚና፣ ተግባራት እና ኃላፊነቶች እንዲሁም የሥነ-ምግባር ጉዳዮች እንደሚገጥሙ ማውሳት ተገቢ ነው፡፡ ለምሳሌ የደንበኞችን ምስጢር አሳልፎ ላለመስጠት በሂደት የሚታወቁ የደንበኞችን የሀሰት ማስረጃዎች በተመለከተ ምን ማድረግ ወይም በምን ሁኔታ ማለፍ እንደሚገባ፣ በምስጢር የተነገረን የደንበኛን ጥፋት ደንበኛውን በማይጎዳና በማያጋልጥ አኳኋን በመያዝ እንዴት ብሎ ተገቢውን የጥብቅና አገልግሎት መስጠት እንደሚቻልና ጠበቃ ለሙያው፣ ለፍርድ ቤትና ለትክክለኛ ፍትሕ መስፈን ያለበት ሙያዊ ግዴታ ሲጣረስ የትኛውን አካሄድ መምረጥ እንደሚገባ በሌሎች ሀገሮችም የሚያወዛግቡ ነገሮች አሉ፡፡ በእነዚህና የመሳሰሉ የሚያወዛግቡና ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮች ላይ የጠለቀ ግንዛቤና እይታን በመፍጠር በየጊዜውም አቅምን በማጎልበት ተገቢውን መፈጸም ያስፈልጋል፡፡ በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን፣ሙስና እና ብልሹ አሰራር እንዲጠፋ የበኩልን ማበርከት እንዲቻል በሙያው ዙሪያ ያሉ ብኽርታዎችንና ተቃርኖዎችን የበለጠ በማንበብና ከሌላው ዓለም የዳበረ አሰራር በመማር ትክክለኛ ግንዛቤ በመጨበጥ በአግባቡ መንቀሳቀስና በአርአያነት መስራት ያስፈልጋል፡፡

**ማጠቃለያ**

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን በአጠቃላይ እና በየክልሎች የመልካም አስተዳደር እጦት መስፈንና የሙስና እና ብልሹ አሰራር እየተስፋፋ መምጣት አሳሳቢነቱ እየተገለጸ ነው፡፡ የእንዲህ ዓይነት ችግሮች መኖርና እየተስፋፋ መምጣት በርካታ የህብረተሰብ ጠቃሚ እሴቶችን የሚጻረርና የሚሸረሽር ነው፡፡ ሰላምና ደህንነትን የሚያውክ፣ ጤነኛና የተረጋጋ ማህበራዊ መስተጋብርን

የሚያደፈርስ ነው። በመንግሥት ተቋማትና አሰራር ውስጥ የሕግ የበላይነትና ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሰራር እንዳይሰፍን የሚያደርግ ነው።

የመልካም አስተዳደር እጦት ካለ፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራር ከሰፈነ የሰዎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነጻነቶች በተጨባጭ ሊከበሩና ዋስትና ሊያገኙ አይችሉም፤ መሠረተ-ጽኑና ዘላቂ የሆነ ልማት ማምጣትም ሆነ ሠላምና ደህንነቱ የተረጋገጠ ህብረተሰብ መገንባት አይቻልም። እነዚህ ችግሮች ባሉበት ሁኔታ የዳኝነት ነፃነት ሊረጋገጥ እና ትክክለኛ የሆነ የፍትሕ አስተዳደርም ሊሰፍን አይችልም። በተለይም እነዚህ የመልካም አስተዳደር እጦትና የሙስና እና ብልሹ አሰራር ችግሮች በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥ ስር መስደድ ከጀመሩ አንድምታቸውና አሉታዊ ውጤታቸው እጅግ ከባድ መሆኑ ለማንኛውም ሰው ግልጽ ነው። ሕግ የጣሰ፣ ወንጀል የፈጸመ፣ በማንኛውም ሁኔታ በግለሰቦችና በህብረተሰብ ክፍሎች ላይ በደል ያደረሰ ሰው በኃላፊነት የማይጠይቅበትና የማይቀጣበት ሁኔታ ከተፈጠረ፣ በአንጻሩ በደል የደረሰባቸው ሰዎችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በፍትሕ አካላት ዘንድ በእኩልነት የማይስተናገዱበትና የማይደመጡበት፣ ለደረሰባቸው በደልም በተገቢው አጭር ጊዜ በህግ መሰረት ካሳ የማያገኙበት ሁኔታ ከተፈጠረ በሂደት ሰዎች በመንግሥትና በተቋማቱ አሰራር ብሎም በህግ ላይ አመኔታ እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ነው። እንዲህ ዓይነቱ የተስፋ መቁረጥ ዝንባሌ ደግሞ ወደ ሥርዓት-አልበኝነትና ማንኛውንም አቋራጭ ግላዊ መፍትሔ ለመሻትና ለመመውሰድ የሚገፋፋ በመሆኑ ችግሩ በሁሉም ዘንድ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው።

በመሆኑም ከሌሎች ዘርፎች ባልተናነሰ ሁኔታ በፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ ውስጥም የመልካም አስተዳደር እንዲሰፍን፣ሙስና እና ብልሹ አሰራር እንዲጠፋ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ በሌሎች የፍትሕ አካላት ሆነ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ያለው ሚናና ድርሻ እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ሙያና በሙያው ውስጥ የተሰለፉ ጠበቆችም በዚህ ጽሑፍ ለማመላከት እንደተሞከረውም ጉልህ ቦታና ድርሻ አላቸው።

ጠበቆች የዲሞክራሲ ዕሴቶች እንዲያድጉ፣የሁሉም ወገን መብትና ጥቅም እንዲከበርና እንዲረጋገጥ፣በአድሎ፣በሙስና፣ በዘመድ አዝማድና በሌላ ያልተገባ ግንኙነት መሠረት መስራት እንዲቆምና የህግ የበላይነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን በማድረግ ረገድና ትክክለኛና ፍትሐዊ አሰራር እንዲኖር አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር ረገድ ከፍ ያለ ሙያዊ የህብረተሰብ ኃላፊነት አለባቸው። ዘርፉ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ግልጽና በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ ሙያዊና ህጋዊ ግዴታም አለባቸው። በመሆኑም ማንኛውም ጠበቃ በህግና በህጋዊ አግባብ ብቻ

በመስራትና ሙያው የሚጠይቀውን ከፍ ያለ ሥነ-ምግባር ጠብቆ በመንቀሳቀስ፣ በብቃት፣ በታታሪነት፣ በተቆርቋሪነት፣ በንጹህነትና በሐቀኛነት እንዲሁም በተአማኒነት በመስራት የፍትሕ አስተዳደር ዘርፉ እየቀረበበት ካለው ጉድፍና እንከን የጸዳ እንዲሆን የበኩሉን ሚና ሊጫወት ይገባል፡፡ የጥብቅና ሙያ ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ተብሎ የሚሰጥ አገልግሎት ሳይሆን የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ፣ የሰዎችና የቡድኖች መብቶችና ጥቅሞች እንዲከበሩ፣ እውነተኛነትና ሐቀኛነት እንዲሰፍን፣ በግለሰቦች፣ በቤተሰብና በህብረተሰብ ደረጃ ሁሉ የሰመረና ጤናማ ግንኙነት እንዲኖር የሚጣርበት ትክክለኛ የህግ ሙያ ዘርፍ እንደሆነ እያንዳንዱ ጠበቃ በተግባር ሊያሳይና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በአንዳንድ ሰዎች እንደሚነገረው ጠበቃ ማለት ነገር የሚያነፈንፍ፣ በትንሽ በትልቁ ጉዳይ ጣልቃ እየገባ ቁርሾን የሚያባብስ፣ የእውነት ፍለጋንና ትክክለኛ አሠራርን በሆነ ባልሆነው መንገድ የሚያደናቅፍ ሳይሆን ምንጊዜም በዬትኛውም ደረጃና ቦታ ሠላምንና የሰመረ ግንኙነትን (peace and harmony) ለማረጋገጥ/ለማስፈን የበኩሉን ጥረት የሚያደርግ፣ በሕግ መሠረት ብቻ የሚሠራ፣ ሕግንና የጥብቅና ሙያ ሥነ-ምግባርን ጠብቆ የሚንቀሳቀስ ትክክለኛ የፍትሕ አጋዥ ባለሙያ መሆኑንም በተግባሩ ማሳዬትና ማረጋገጥ ይገባል፡፡

# አንድ የክስ ምክንያትን ያለመነጣጠል ጽንሰ ሐሳብ እና አተገባበሩ፡ በአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት

**አጽህሮተ–ይዘት** **ሳባ ደመቀ**[1]

*በፍትሐ ብሔር ጉዳይ አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የሚከለክለው መርህ በአብዛኛው በአለማችን ባሉ የሕግ ሥርዓቶች ውስጥ ተቀባይነት ያለው መርሕ ነዉ። ጽንሰ ሀሳቡም ከሳሽ ከአንድ የክስ ምክንያት የመነጨ የዳኝነት ጥያቄዎቹን ሁሉ በአንድ አቤቱታ ውስጥ አጠቃልሎ ማቅረብ እንዳለበት እና ቀንሶ ባስቀረው ክስ ወይም ሀብት ላይ በድጋሚ አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚከለከልበት ሥነ ሥርዓት ላይ ትኩረት ያደርጋል። መርሁ በዋናነት ተከሳሽን በተደጋጋሚ ክርክር ምክንያት ከሚደርስበት እንግልት የመጠበቅ፣የፍርድ ቤቶችን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም እንዲሁም ከሳሽን የማንቃት እና የማስጠንቀቅ አበይት አላማዎችን አካቷል።የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግም እነዚህን ቁልፍ አላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን አስቀምጧል።ይሁን እንጂ መርሁን በማንሳት መቃወም ያለበት ማነው? ተቃውሞው መቼ ይነሳል? የማይንቀሳቀስ ንብረት ከማስመለስ ክስ ጋር ተያይዘዉ ሊነሱ የሚችሉ እንደ አላባና ኪራይ የመሳሰሉትን ሌሎች ክሶችን አጣምሮ በማቅረብ ረገድ ሀጉ ፈቃጂ ነዉ ወይስ አስገዳጂ? በሚሉት ጉዳዮች ላይ በባለሙያዎች ዘንድ የተለያዩ አቋሞች ይንጸባረቃሉ። በመሆኑም ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በኢትዮጵያ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ አንድ የክስ ምክንያት ያለመነጣጠል ጽንሰ ሀሳብን በመተንተን የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች አግባብነት ይዳስሳል።የጥናቱ ዘዴ አይነታዊ (Qualitative) ሲሆን በጥናቱም በአ/ብ/ክ/መ/ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚችሎት የተሰጡ ውሳኔዎች ሆነ ተብለው (purposely) ተለይተው ከጽንሰ ሀሳቡ ጋር ተፈትሸዋል። ቃለ-መጠይቅና የትኩረት ቡድን ውይይትን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል። ይህንንም መሰረት በማድረግ ፅሁፉ ፅንሰ ሃሳቡን በመረዳት በኩል በባለሙያዎች መካከል ሰፊ የአስተሳሰብ ልዩነቶች እንዳሉ እንዲሁም አንድ የክስ ምክንያት ያለመነጣጠል መርህን በመወሰን ረገድ መብት የሚያቋቁሙ መሰረታዊ ሕጎችን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕጉ ጋር አጣምሮ ያለመመርመር ክፍተቶችን ያሳያል።*

**ቁልፍ ቃላት፦ የክስ ምክንያት፣ አንድ የክስ ምክንያት፣ አንድ የክስ ምክንያትን ያለመነጣጠል መርህ፣ የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች መርህ** (Res Judicata)

---

[1]LLM, LLB በአብክመ የፍ//ባ/ማ/ሕ/ም/ኢ/ አሰልጣኝ እና ተመራማሪ። ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ ሳዘጋጅ ጊዜያቸውን ሰውተው መረጃ በመስጠት እና ጠቃሚ ሀሳቦችን በማቀበል የተባበሩኝን ግለሰቦች እና ተቋማት ሁሉ በእጂጉ እያመሰገንኩ አስተያየታችሁን በ ኢ-ሜ-ል አድራሻ sabityemama@yahoo.com ልታደርሱኝ ትችላላችሁ።

## 1. አንድ የክስ ምክንያትን መነጣጠል የመከልከል ጽንሰ ሐሳብ

### 1.1 "የክስ ምክንያት" ትርጉም

በመሰረቱ የክስ ምክንያት የሚለው ሐረግ በራሱ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ ግልጽ ትርጉም መስጠት ለበርካታ ምሁራን እጂግ አስቸጋሪ መሆኑ በስፋት ይገለጻል። በዚህ ረገድ የተለያየ ውጤት ያላቸው በርካታ ሙከራዎች የተከናወኑ ቢሆንም ትርጉም ከመስጠት ይልቅ ጽንሰ ሐሳቡን መግለጽ የተሻለ ይሆናል ።[2]ይህ ሐረግ እጂግ አወዛጋቢ እና አከራካሪ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይም በሕግ ዘርፍ ውስጥ ባሉ ጉዳዮች ተጠቃሽ የሆነው ብላክስ ሎው መዝገበ ቃላት በሚከተለው መልኩ ይገልጸዋል።

> *"A group of operative facts giving rise to one or more basis for suing: a factual situation that entitles one person to obtain a remedy in court from another person."* [3]

ይህንንም በግርድፉ ወደ አማርኛው ቅጂ ስንመልሰው የክስ ምክንያት ማለት ለአንድ እና ከዛ በላይ ለሆኑ ክሶች መነሻ ሆኖ አንድ ሰው በሌላኛው ሰው ላይ በፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ መብቱን የሚያስከብርበትን ሁኔታ የሚፈጥር ነው ። ሐረጉ በዝርዝር እና መሰረታዊ ሕግጋት እውቅናና ጥበቃ የተሰጠው መብት መጣስን ተከትሎ ፍርድ ሠጭ በሆነ አካል ካሳ ወይም ዳኝነት ሊጠየቅበት የሚችል ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚነሳ ጽንስ ሐሳብ እንደሆነም መመልከት ይቻላል።[4] ወደ ኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ስንመለስ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ለክስ ምክንያት ትርጉም የሰጠ ባይሆንም በርካታው የሕጉ ክፍል የተቀረጸበት የህንዱ የሥነ ሥርዓት ሕግ ከፍ ሲል በተመለከተው አይነት ያስቀመጠ ሲሆን አገላለፁም በፍርድ ቤቶች የዳበረ ውስን እና ሠፊ ትርጉም የተሰጠው መሆኑንም ማየት ይቻላል።

> "In *the restricted sense the term cause of action means the circumstance forming the fraction of the right or the immediate occasion for the action .In the wider sense it means necessary conditions for the maintenance of suit, including not only the infracytion right, but the infraction coupled with the right itself.Compendiously the*

---

[2] Silas A.Harris, what is a cause of action, 16 Cal.L.Rev.459 (1928) Available at: http://scholarship.law.berkeley.edu/californialawreview/vol16/iss6/1 የተገኘው በ2/6/2008 ዓ.ም

[3] Blacks's Law Dictionary, 7th ed. westgroup–ST. Poul. MiNN.,1999 p.214

[4] የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሰረታዊ ችግሮች ማሻሻያ ላይ ያተኮረ ኮንፈረንስ አበበ ሙላቱ (16-17) ሕዳር 1998 አዲስ አበባ፤ በኮንፈረንሱ የቀረቡ የምርምር ጽሑፎች እና አስተያየቶች፤ ሀምሌ 1998 ገጽ 37

*expression means every face which it could be necessary for the plaintiff to prove ,if traversed ,inorder to support his right to the judgement of the court…".*[5]

ከእነዚህ አገላለጾች የምንረዳው በርግጥም የክስ ምክንያት ስንል በፍርድ አንድ ሰው ሊያስከብረው የሚችለው መብት ወይም ጥቅም ጋር የተያያዘ እና በከሳሽ በኩል ወደፊት በማስረጃ መረጋገጥ ያለበት ጽንስ ሐሳብ መሆኑን ነው።

### 1.2 አንድ የክስ ምክንያትን ያለመነጣጠል መርህ መሰረታዊ አላማ

አንድ የክስ ምክንያት ያለመነጣጠል መርህ በአብዛኛው ለዳኝነት ሂደቶች ብቃት እንዲሁም አጠቃላይ ውጤታማነት መሰረታዊ የሚባል አስተዋጽኦ እንዳለው በእጁጉ ይታመናል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ግንባር ቀደም ከሚባሉ እና በተለይም ድጋሚ ያለመከሰስ መርህ ላይ ከሰሩ ብዙ ምሁራን መካከል (Robert C. casad) የተባሉት

> *"Modern procedure seeks to maximize the efficiency of judicial proceedings by encouraging the presentation of all claims that can conveniently be tried together in the framework of a single lawsuit."* [6] *በማለት ያሰቀምጣሉ ።*

ይኸውም ዘመናዊው ሥነ ሥርዓት በዋናነት ሁሉም ዳኝነት የሚጠየቅባቸውና ያለምንም ችግር መቅረብ የሚችሉ ጥያቄዎች ሁሉ በአንድ ክስ ውስጥ በአንድ ጊዜ የሚቀርቡበትን ሁኔታ ይበልጥ በማበረታታት የፍርድ ሂደት ብቃትና ውጤታማነት ማሳደግን በእጁጉ የሚሻ ነው በሚል ይገልጻል። በዚህም አግባብ ሁሉም የሥነ ሥርዓት ሕግጋት በተቻለ መጠን ክርክርን የሚያጓትቱ የሙግት አመራሮችን ለማስቀረት የሚያስችሉና ይህንን መሰረት ያደረጉ ዝርዝር ደንጋጌዎች ይኖሯቸዋል። ከነዚህ መካከል የክስ ምክንያት ያለመነጣጠል መርህ ጥቅል በሆነ አገላለጽ አንድ ምክንያት በተለያዩ ክሶች እየተከፋፈለ ሊቀርብ እንደማይችል ክልከላ የሚያስቀምጥ ሲሆን በጠቅላላው ከተመሳሳይ ሁኔታ የሚመነጩ ጥያቄዎች ሁሉ በተለያየ መልክ የሚቀርቡበትን የሙግት ሂደት ለመከላከል ታስቦ የተነደፈ ነው። በዚህም መሰረት ከሳሽ ወደፊት አንድ የክስ ምክንያትን የሚጋሩ ክሶችን ነጣጥሎ የማቅረብ እድሉን በማሳጣት ሁሉንም ጉዳዩች በነጠላ ክስ ውስጥ አጠቃልሎ እንዲያቀርብ ያስገድዳል። [7]

---

[5] M.p.Jain's The Code of Civil Procedure, ed. 2004, wadhwa &Company Nagpur. New delhi.India p.111

[6] Yuval Sinai ,The Downside of Preclusion: some Behavioural and Economic Effects of Cause of Action Estoppel in Civil actions, McGill Law Journal vol. 56, n° 3, 2011, 673-716. p. 676 ትርጉም የጸሀፊው ነው www.lawjournal.**mcgill**.ca/userfiles/other/6060424-**Sinai**.pdf *የተገኘው በ 2/6/2008 ዓ.ም*

[7] Charles E. Clark Joinder and Splitting of Causes of Action, 25 Michigan Law Review 393 (1927) "a single cause shall not be split or divided among several suits; it is generally designed to prevent litigation of the same question in different suits. Therefore it compels a certain extension of the issues in a single suit on pain of forfeiting opportunity to litigate them elsewere.

ቀደም ሲል የነበረው እና አንዳንድ ሥርዓቶች ያስቀጠሉት ግንዛቤ አቤቱታ የሚለውን ቃል ከአንድ ነጠላ የሕግ ጽንሰ ሀሳብ (single legal theory) ወይም ከአሳሹ ነጠላ መብት (single right) ጋር ባጠነጠነ ጠባብ ትርጉም ላይ ብቻ የተወሰነ ነበር።[8]

ይሁን እንጂ ዘመናዊው እይታ ደግሞ አሳሽ በአንድ ማመልከቻ ውስጥ ከአንድ ነጠላ ግንኙነት የመነጨ ማናቸውንም ክሶችን በተሟላ መልኩ አጠቃልሎ በማቅረብ መከራከር አለበት የሚል ጠንከር ያለ ሀሳብን የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን። ስለሆነም ፍርድ ሰጭ የሆነው አካል የቀረበውን ጥያቄ አስመልክቶ በወሰነው ጉዳይ ላይ ድጋሚ የማከራከር ብቻ ሳይሆን ተቀንሶ የቀረውንም የዳኝነት ጥያቄም ጭምር ሊቀርብ የሚችልበትን ማናቸውም አካሄድ ፈጽሞ የሚከለክል በመሆኑ የክስ ባለቤት የሆነው አሳሽ ቀድሞውኑ ከአንድ የክስ ምክንያት የሚነሱ የዳኝነት ጥያቄዎችን በጥንቃቄ ዘርዝሮ ማቅረብ ይጠበቅበታል። ይህም ሥርዓት ፍትሐዊነት ያዘለ የፍርድ ውጤታማነትን ያሳድጋል ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነው።[9]

በመሰረቱ የፍትሐ ብሔር ሙግት አብይ አላማ በአንድ አድራጎት ጉዳት የደረሰበት አካል ለዚሁ ጉዳት ማካካሻ የሚሆን ካሳ እንዲያገኝ ማስቻልን ማዕከል ያደረገ በመሆኑ አሳሽ ከጉዳቱ የመነጨ እና ይገባኛል የሚላቸውን ጥያቄዎች በሙሉ በአንድ ክስ ውስጥ አጠቃሎ ማቅረብ እንዳለበት በትእዛዝ መልክ መደንገጉ አግባብነት አለው።[10] ይኸውም በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በግልጽ ማንኛውም ለፍርድ ቤት የሚቀርብ አቤቱታ ሁሉ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ትክክለኛውን ፍርድ ለመስጠት በሚያስችለው፣ በዚያው ነገር ሌላ አከራካሪ ጉዳይ በማያስከትል ሁኔታና ግልጽ በሆነ አጻጻፍ መቅረብ አለበት በሚል ተመልክቷል ።[11] በዚህ ረገድ የህንድ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግም ይህንን ደንብ በትእዛዝ II መርህ (1) ሥር "*every suit shall as far as practicable, be framed so* as to afford grounds for final decision upon the subject in dispute and to prevent further litigation concerning it." በማለት ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ደንግጎ እናገኛለን። ከዚሁ ጋር ተይይዞ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለበት ነጥብ ከሳሽ የክሱ ባለቤት ወይም በላቲን (dominus litis) በመሆኑ ጉዳዩን ባሻው መልኩ

---

www.http://digitalcommons, Law.Yale.edu/fss_papers የተገኘው በ6/7/2008 ዓ.ም

[8] Kevin M.Clermont, civil procedure, Civil Procedure, second Edition, West Publishing. Co. (1988) ገጽ 264

[9] ዝኒ ከማሁ

[10] አለን ሴድለር (ሳሙኤል ጣሰው እንደተረጎመው) የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ማብራሪያ፣ አዲስ አበባ፣ 1999 ዓ.ም፣ ከገጽ 531-533

[11] አንቀጽ 216(1) የኢትዮጵያ ንጉሰ-ነገስት መንግስት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 3/1958 (ከዚህ በኋላ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ወይም የፍ/ሥ/ሥ/ሕ እተባለ የሚጠራው)

አዘጋጅቶ ለማቅረብ የሚችል ቢሆንም ይህንን ሲያደርግ በርግጥም በአግባቡ ተዘጋጅተው ያልቀረቡ ክሶችን ተከትሎ የሚመጣውን ውጤትም ጭምር ሁሌም ማሰብ ይጠበቅበታል፡፡ [12]

በሌላ አገላለጽ ከሳሽ ይህንን ደንብ ተጠቅሞ በአንድ የክስ ምክንያት ላይ ያለውን አቤቱታ ሊያቀርብበት የሚችል መብትን ማካተት እየተገባው ይህንን ተፈጻሚ ሣያደርግ በቀረ ጊዜ ድጋሚ ያንኑ የክስ ምክንያት የተመለከቱ ማናቸውም ጥያቄዎች ማንሳት የማይችልበትን አንድ የክስ ምክንያት መከፍፈልን የሚከለክል መርህ እንዳለ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡[13] የዚህ መርህ ጠቅላላ አላማ በላቲን ቋንቋ (interest repulicae ut sit finis litium) ወይም የሙግት መቋጫ ሊኖረው ይገባል) የሚል የጠቅላላውን ህዝብ ፍላጎት የያዘው አባባል እንደሆነ ይገለጻል፡፡ [14] በአጠቃላይ አንድ የክስ ምክንያትን ያለመነጣጠል መርህ አላማ ሙግትን በሆነ ቦታ እና ጊዜ መቋጨትን መሰረት ካደረገው የሥነ ሥርዓት ሕጉ አላማ ውስጥ የሚካተት ሆኖ ዝርዝር አላማዎቹንም እንደሚከተለው ለይቶ መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

### 1.2.1 ግለሰብን ከእንግልት መጠበቅ

በመሰረቱ ተከሳሽ ሳይፈልግ ወደ ሙግት ተጠርቶ የሚገባ በመሆኑ ለአላስፈላጊ እንግልት እንዳይዳረግ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል፡፡ በመሆኑም አንድ የክስ ምክንያትን መነጣጠል የሚከለክለው መርህ ሲቀረጽ ከሌሎች ተጨማሪ አላማዎች በላቀ ሁኔታ ተከሳሽን በየጊዜው ሊቀርብ ከሚችል ተደጋጋሚ ክስ መጠበቅን ማእከል አድርጎ ነው፡፡[15]

በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ እስካልተረጋገጠ ድረስ ንጹህ ሆኖ የመገመት (presumption of innocence) ህገ መንግስታዊ መብት እንዳለው ሁሉ በፍትሐ ብሔር ጉዳይም ለቀረበበት ክስ ሀላፊ እንዳልሆነ የመገት (presumption of non liability) የሚባል ተቀባይነት ያለው መርህ እንዳለ ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡[16] ይህንንም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዝርዝር ድንጋጌዎች በሥነ ሥርዓቱ ውስጥ ተደንግገው የሚገኙ ሲሆን ለአብነትም

---

[12] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ገጽ 439

[13] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 216(2)

[14] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ከገጽ 439-440

[15] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 7 በመሰረቱ የግለሰቦች ለተደጋጋሚ ሙግት ከመዳረግ የመጠበቅ መብት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዩችን አስመልክቶ የተቀመጠው ሰፊ መርህ (Res judicata) ውስጥ የተካተተው ከአራተኛው ምዕተ አመት በፊት Lord Coke የተባሉ ዳኛ Ferrer case በተባለ ጉዳይ ላይ በሰጡት ውሳኔ መነሻነት ሲሆን: "Otherwise great oppression might be done under colour and pretence of law; for if there should not be an end to suits, then a rich and malicious man would infinitely vex him who hath right by suits and actions; and in the end (because he cannot come to any end) compel him (to redeem to his charge and vexation) to leave and relinquish his right . . ."Yuval Sinai,Reconsidering Res Judicata: A Comparative Perspective, Duke Journal of Comparative & International Law Vol 21:353(2011)

[16] አለ. መሀመድ አለ፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኛ ጋር መጋቢት 2 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ምን ይዞ እንደሚመጣ የማይታወቅ ቢሆንም ቢያንስ ተከሳሽ በሚኖርበት አካባቢ በሚገኝ የግዛት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት መሆን ያለበት መሆኑን በመመልከት ሕጉ ለተከሳሽ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ከእንግልት ነጻ የሚሆንበትን መድረክ ያመቻቸ መሆኑን ለመገንዘብ ያስችላል።[17] በተመሳሳይ አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የሚቃወመው መርህ መሰረት ያደረው የፍትሐዊነት መገለጫ ተደርጎ የሚወሰደው ግለሰቦችን ከተደጋጋሚ የሙግት እንግልት መታደግ ሲሆን ይኸውም በአብዛኛው የአለማችን የሕግ ሥርዓቶች ውስጥ ተካትቶ ይገኛል። ይህ አላማ የተወሰደውም *"Nemo devet bis vexari pro una et eadem causa'' 'no person should be vexed twice over the same cause"* ከሚል የላቲን አባባል (maxim) ሲሆን ወደ አማርኛ ሲመለስ ማንኛውም ሰው ከአንድ አይነት የክስ ምክንያት በመነጨ ጉዳይ ሁለት ጊዜ ክስ ሊቀርብበት አይገባም የሚል መርህን መሰረት ያደረገ ነው።[18] ይህም በርግጥም አንዳንድ ቂመኛ ከሳሾች ነጠላ ጥፍት ባደረሰባቸው ተከሳሽ ላይ በርከት ያሉ ክሶችን በማቅረብ ተከሳሾችን የሚረብሹበት ሁኔታ እንዳለ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን መገንዘብ ያስችላል።[19] በመሰረቱ በዚህ መልኩ ተከሳሾችን ከተደጋጋሚ እንግልት መጠበቅ ካልተቻለ ምርታማነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚሳድር ከመሆኑም ባለፈ በሀገር ምጣኔ ሀብት ላይ ጉዳትን ያስከትላል።[20]ይኸውም ተከሳሽ ከአንድ አድራጎቱ በመነጨ ሁኔታ በተለያየ ጊዜ ለሙግት የሚጠራበትን መንገድ መዘጋት የሚያስችል ሥርዓት ከሌለ ተከሳሽ በከሳሽ ፍላጎት ለሚቀርብበት ሙግት ሰፊ ጊዜውን ለምርታማነት ሳይሆን ረዥም ጊዜን ለሚወስደው የፍርድ ቤት ውሎ የሚያውል በመሆኑ በግለሰቡ ምርታማነት እንዲሁም በሂደት የሀገር እድገትን ከማረጋገጥ አኳያ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀርም።[21]

[17] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 19ን ይመልከቱ።

[18] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ገጽ 441 እና የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 216

[19] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ገጽ 531

[20]ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኞች አቶ አሊ መሀመድ አሊ፣ አቶ ተፈሪ ገብሩ ጋር መጋቢት 2 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ ከአቶ አስቻለው አሻግሬ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ቤት መምህር፣ የሕግ አማካሪ ና ጠበቃ እንዲሁም ጸሀፊ ጋር የካቲት 29 ቀን 2007 ዓ.ም የተደረገ ቃለ መጠይ

[21] ዝኒ ከማሁ

### 1.2.2 የፍርድ ቤቶችን ውጤታማነት ማሳደግ

በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ በአነስተኛ ገንዘብ እና ጉልበት የፍትሕ ሥርዓቱን ውጤታማነት ማረጋገጥ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አይነተኛ ባህርይ ሲሆን ምጣኔ ሀብታዊ እሳቤውም ከህብረተሰቡ እንዲሁም ከግለሰብ ፍላጎት አንጻር የሚታይ ነው።[22]

በዚህ ረገድ ፍርድ ቤቶች ከህዝብ በሚመነጭ በጀት የሚንቀሳቀሱ ተቋማት እንደመሆናቸው መጠን ሁሉም ክርክሮች ሲካሄዱ የተቋሙን ምጣኔ ሀብት (Judicial Economy) ማለትም ጊዜ፣ጉልበት እና ገንዘብን ከመቆጠብ አንጻር መቃኘት ይኖርባቸዋል። ይህን ማድረግ ከተቻለ ባለው የሰው ሀይል ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚቀርቡ ጉዳዩችን በአግባቡ በመወሰን የመዛግበት ክምችትን (Case backlog) መቀነስም ያስችላል።[23] ስለሆነም ይህ መርህ በተደጋጋሚ ለሚቀረቡ ክርክሮች የሚወጣን አጠቃላይ ጊዜ፣ወጭ እና ጉልበትን ለመቆጠብ የሚያስችል በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሁለንተናዊ ውጤታማነትን ለማምጣት ያስችላቸዋል። ከዚህም የተነሳ አንድ የክስ ምክንያትን መነጣጠል የሚከለክለው መርህ መሰግትን የመቋጨት ፍላጎትን ማንጸባረቅ ብቻም ሳይሆን የፍርድ ቤቶችን ሀብት በአግባቡ ለጥቅም ማዋል ላይ ትኩረት ያደረገ ቁልፍ ሚና ይጫወታል በሚል የሚገለጸው።[24]

ከዚህ በተጨማሪ አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የሚከለክለው መርህ መኖሩ በራሱ ዳኞች በአንድ ጊዜ ማስረጃዎችን ሰምተው ለመወሰን ሰፊ እድል የሚፈጥርላቸው ሲሆን ከአንድ ጉዳይ የመነጩ ክሶች በተለያዩ ጊዜያት እየቀረቡ የተለያዩ ወሳኔዎች ሊሰጡ የሚችሉበትን አጋጣሚ በእጅጉ ይቀንሳል። ይህም ሁኔታ የውሳኔዎችን ተገማችነት በመጨመር የዳኝነት አካሉ በህብረተሰቡ ዘንድ አመኔታን እንዲያገኝ ያግዘዋል።[25]

---

[22] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 ገጽ 258

[23] ዝኒ ከማሁ

[24] Rechard et al., Civil procedure: A Modern Approach, Fourth Edition, West Publishing Co. 2008 ገጽ 111

[25]ከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኞች አቶ አለ መሀመድ አለ ፣እና ተፈሪ ገብሩ ጋር መጋቢት 2 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ ከ አቶ አስቻለው አሻግሬ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት መምህር፣ የህግ አማካሪ ና ጠበቃ እንዲሁም ጸሀፊ ጋር ተካቲት 29 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተጨማሪም ከአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኞች አቶ ጸጋዬ ወርቃየሁ፣በሪሁን አዱኛ ምህረቴ፣ በሪሁን አዱኛ ታምራት፣ አብዬ ካሳሁን፣ምትኩ ወንዴ፣ ሀብታሙ እርቅይሁን፣ዬሀንስ ቢሻው፣ ጌታዬ እንዳለው፣ ሀይሌ አስናቀ ጋር በቀን ሚያዚያ 9ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገ የትኩረት ቡድን ውይይት

ይሕውም ሀሳብ በስፋት …Most of the arguments are expressions of public policy is promotion of economical litigation; the need to ration judicial and other court time and resources; avoidance of inconsistent decisions; prevention of additional delay in the disposal of litigation; preserving the authority of courts to reach decisions which will be presumptively binding. . . These considerations of public policy and private justice apply most clearly to the general rule set out of same cause of action. **በሚል ይገለጻል** Yuval Sinai, Reconsiderning ResJudicata: A Comparative Perspective, Duke Journal of Comparative & International Law [Vol 21:35 (2011) p. 262-263

### 1.2.3 ክሳሽን ማንቃት እና ማስጠንቀቅ

ክፍ ሲል እንደተመለከተው ይህ መርህ በዋናነት ከአንድ ድርጊት በመነጨ ጥፋት ተከሳሽ ላይ ተደጋጋሚ ክሶች በየጊዜው እየቀረቡ እንዳይንገላታ መጠበቅ ሲሆን በተጨማሪ በፍርድ ቤቶች ላይ የስራ ጫናን እንዳይፈጥሩ መከላከል መሆኑ ይታወቃል።[26] ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ መርሁን መከተል በከሳሽም ላይ ራሱን የቻለ የማንቃት ብሎም የማስጠንቀቅ አላማም እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል። በርግጥ ከሳሽ በመጀመርያው ክስ ወስጥ በተነሳው አንድ ምክንያት መጠቃለል ያለባቸውን ሁሉንም ጥቄዎች ማካተት አለመቻሉ አዲሱን ክስ አልተሟላም በሚል የማስቆም ወይም ውድቅ የማስደረግ ውጤትን አያስከትልም። ይልቁንም በዚህ ሁኔታ ከሳሽ የተወሰነውን ክፍል ሳያካትት መቅረቱ ወደፊት በቀረው መብት ላይ አዲስ ክስ እና ዳኝነት ለማንሳት የሚችልበትን እድል ዝግ በማድረግ መርሁ ቅጣት ያስቀምጣል።[27] በመሆኑም ከሳሽ ቀድሞውኑም በመጀመሪያው ክስ ጊዜ በከፊል ላላካተተው መብት ድጋሚ ፍርድ ቤት ቀርቦ ተከሳሽን ሊሞግት እንደማይችል ቅድመ እውቅና የሚሰጠው በመሆኑ ክሱንና የሚጠይቀውን ዳኝነት እንዲሁም ማስረጃዎቹን ሁሉ አጠቃልሎ በማቅረብ ረገድ ጥንቁቅ እንዲሆን ያደርጋል።[28]

## 1.3 አንድ የክስ ምክንያትን ያለመነጣጠል ጽንሰ ሐሳብ እና አንዳንድ መሰረታዊ ነጥቦች

በመሰረታዊነት በከሳሽ በኩል የሚኖረው አቤቱታ የተከራካሪዎችን ማንነት እና ክሱ የሚቀርብበትን ፍርድ ቤት ስም ከያዘ ርዕስ በተጨማሪ አጭር እና ግልጽ በሆነ መልኩ የተዘጋጀ የክስ ምክንያት ዝርዝር እንዲሁም የዳኝነት ጥያቄ ሁሉ ማካተት ይኖርበታል።[29] በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግም ለፍርድ ቤት የሚቀርብ አቤቱታ ከሳሽ የሚጠይቀውን ሁሉ ዘርዝሮ የሚገልጽ ጽሁፍ ፤የተከሳሽ ከሳሽ የሚያቀርበው የክስ ጽሁፍ ማመልከቻን ሁሉ እንደሚይዝ ተመልክቷል።[30] በመሆኑም የከሳሽ ማመልከቻ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች እንዲሁም የተፈጠሩበት ጊዜ እና ቦታ ከማካተት በተጨማሪ ይነሳኛል

---

[26] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10 ገጽ 531

[27] Fleming James et al., Civil procedure, little Fourth Edition, Brown &company. United states of America,1992 ገጽ ከ589-90

[28] Yuval Sinai, Reconsiderning Res Judicata : A Comparative Perspective , Duke Journal of Comparative & International Law [Vol 21:35 (2011) p. 262-263 www.http/*scholarship.law.duke.edu/cgi/viewcontent.cgi?article=1025&context=djci ዮተገኘው በ1/6/2008ዓ. ም* እንዲሁም__የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ216 (3) እና (4) ሥር የተደነገገውን ይመልከቱ።

[29] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 80(1)

[30]Melton D.Green, Basic Civil Procedure, edition second,(1979) Mineola, New York,The foundation Press. p.113

የሚላቸውን የዳኝነት ጥያቄዎች ሁሉ በማቅረብ የሚጠይቀውን ዳኝነት በግልጽ ዘርዝሮ ማስቀመጥ እንደሚጠበቅበት የሥነ ሥርአት ሕጉ ይደነግጋል፡፡ [31]

በተመሳሳይ የአሜሪካ የፌደራል ሥነ ሥርዓትን ስንመለከት በተለይም ስለ ጠቅላላው የአቤቱታ አቀራረብ መርሆዎችን ያስቀመጠው መርህ 8 ለፍርድ ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የሚፈለገውን የዳኝነት ጥያቄ መያዝ ብቻ ሳይሆን በዳኝነት ጥያቄው ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸውን ጉዳዮች ሁሉ በአስገዳጁ ሁኔታ በዝርዝር አመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው መሆኑን በግልጽ ከማስቀመጥ፣ አቤቱታ አቅራቢው ዳኝነት ሊጠይቅ የሚችልበት መብት እንዳለው የሚያሳይ አጭር እና ግልጽ የክስ ማመልከቻ ማዘጋጀት ያለበት ሲሆን የሚጠየቀው ዳኝነት በአማራጭ የሚቀርብ ወይም የተለያየ አይነት ዳኝነት ከሆነ ይኸውም በግልጽ መቅረብ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡[32] በዚህ ረገድ የፍትሐ ብሔር ሕጉ የክስ ምክንያትም ሆነ የዳኝነት ጥያቄዎች በክስ አቤቱታው ውስጥ በግልጽ ተዘርዝረው እንዲቀርቡ ያስቀመጣቸው ድንጋጌዎች በርግጥም ከዚህ በታች በስፋት ለሚነሳው አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን በግልጽ ለሚከለክለው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ አንቀጽ 216 መሰረት ይጥላሉ ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ሌላው በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ውስጥ አንድ የክስ ምክንያት ያለመነጣጠል ጽንሰ ሀሳብ ሲነሳ በተወሰነ ደረጃ የመጨረሻ ፍርድ ስላገኙ ጉዳዮች (Res Judicata) የተመለከተው መርህ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማየት አስፈላጊ ነው ብሎ ጸሀፊው ያምናል፡፡

### 1.3.1 አንድ የክስ ምክንያትን ያለመነጣጠል ጽንሰ ሀሳብ የመጨረሻ ፍርድ ካገኙ ጉዳዮች (Res Judicata) መርህ ጋር ያለው ግንኙነት

አንድ ጉዳይ በተደጋጋሚ የሚቀርብበት ሥርዓት ላይ የሚደረግ ክልከላን የሚደግፉ ተቀባይነት ያላቸው አብዛኛዎቹ ፓሊሲዎች በተደጋጋሚ የሚካሔድ ሙግት የፍርድ ቤቶችን ፣ የተከራካሪዎችን እንዲሁም የጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም ላይ ጫና ይጨምራል ከሚል እውነታ ይመነጫሉ፡፡[33] በመሰረቱ በተለይም በኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው

---

[31] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 222(1) ረ እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ አንቀጽ 224(1) ይመልከቱ፡፡

[32]Federal rules of civil procedure, Cornell University law school, Legal Information Institute 2015 Edition, P 81 **Rule 8. General Rules of Pleading**

(a) Claim for Relief. A pleading that states a claim for relief must contain:

(1) a short and plain statement of the grounds for the court's jurisdiction, unless the court already has jurisdiction and the claim needs no new jurisdictional support;

(2) a short and plain statement of the claim showing that the pleader is entitled to relief; and

(3) a demand for the relief sought, which may include relief in the alternative or different types of relief.

[33] Gene R.shreve and Peter Raven-Hansen Understanding civil procedure, Matthew Bender &co.United states of America, New York (1989) ከገጽ 117-18. በጥቅሉ የመርሁ መነደፍን አላማ በዚህ መልኩ

ጉዳዩችን አስመልክቶ የተቀመጠው ሕግ (Res Judicata) አንድም የቀደመ ውሳኔ አንድን የፍሬ ነገር ወይም የህግ ጭብጥ እንዴት ለተደጋጋሚ ክርክር መሰረት ከመሆን ይከለክላል? በሚለው ጥያቄ ላይ ከሚያጠነጥነው (Issue preclusion) እንዲሁም የቀደመ ውሳኔ በዛው ጉዳይ ላይ ዳኝነት ወይም የክስ ምክንያትን ድጋሜ የማንሳት ዕድልን ቀሪ እንደሚያደርግ የሚያሳየው (Claim preclusion) ንዑስ መርሆዎችን ለረዥም ጊዜያት አካትቶ ቆይቷል።[34] ከዚህም የተነሣ አንድ የክስ ምክንያትን ያለመነጣጠል መርህ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠባቸው ጉዳዮችን የሚመለከተው (Res Judicata) ንድፈ ሐሳብ አካል ተደርጎ ይወሰዳል።[35] በኢትዮጵያ የሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን እና አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የተመለከቱት መርሆዎች ተለያይተው የተደነገጉበት ሁኔታ ቢኖርም ሁለቱም ለአንድ ክርክር መቋጫ ማበጀትን መሰረት ካደረገ የጋራ አላማ የመነጩ መሆናቸው ግንኙነታቸውን ጥብቅ ያደርገዋል።[36] ከሳሽ ከአንድ ምክንያት የመነጨ የተወሰነውን የክሱን ክፍል አንድ ጊዜ ቀሪውን ደግሞ ሌላ ጊዜ ለማቅረብ በማሰብ ክሱን መከፋፈል የማይችል በመሆኑ አሉኝ የሚላቸውን ክሶች እና የዳኝነት ጥያቄዎች በሙሉ አጠቃልሎ ማቅረብ ያለበት መሆኑ በአንቀጽ 216 (1)(2) ተመልክቷል። በተመሳሳይ መልኩ ለሥነ ሥርዓቱ ጠቅላላ አላማ ሲባልም የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች መርህም የክስ ባለቤቱ ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ አቤቱታውን ለመደገፍ የሚያስችሉ መሰረቶችን እንዲሁም ተከሳሽም በበኩሉ የመከራከሪያ መሰረቶቹን ገልጾ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል። በመሆኑም ተከራካሪዎች ይህንን ያደርጋሉ ብሎ የሚያስብ ስለሆነም የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች መርህ በተከራራሪዎች በግልጽ ቀርበው ውሳኔ ባረፈባቸው ጭብጦች ብቻ ሳይሆን ቢያነሳቸው ኖሮ ሊወሰኑ የሚችሉ ጭብጦችንም ጭምር የሚያካትት ወሰን ኖሮት እናገኛለን። ከእነዚህ በተጨማሪም በቀድሞው ክርክር ውስጥ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆባቸው ተቀባይነት ሳያገኙ የታለፉትም ቢሆን ዳኝነት እንደተነፈጉ ይቆጠራል።[37] በዚህ በኩል የህንዱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ የሁለቱን መርሆዎች ግንኙነት ሲያስቀምጥ ሕጉ አቤቱታውን በጉዳዮ ላይ ተጨማሪ ክርክር በማያስነሳ አኳኃን አጠቃልሎ

---

ያስቀምጠዋል። "Commonly accepted policies supporting preclusion are derived from the fact that repetitive litigation takes the toll (duty) of the court, litigants and the public. In this regard the objectives of res judicata are to save judicial energy, to prevent harassment of the defendant, to further socital interest in the orderly and expeditious resolution of controversies, and to provide response."

[34] ዝኒ ከማሁ

[35] ዝኒ ከማሁ

[36] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10 ገጽ 319

[37] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 5 እና 216 እና የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10 ገጽ 520

ማቅረብ እንዳለበት የተቀመጠውን ደንብ ያልተከተለ ካሳሽ በሁለቱም መርሆዎች ቅጣት እንደሚያገኘው ያስቀምጣል፡፡ [38]ይኸውም ፦

የመጀመሪያው የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዩችን (Res Judicata) መርህ ውስጥ እንደተመለከተው በቀድሞ ክርክር ውስጥ የማስረጃ ወይም የመከላከያ ወይም የመቃወሚያ መሰረት መሆን ይገባቸው ነበር ወይም ለመሆን ይችሉ ነበር የሚባሉት ነገሮችና ምክንያቶች ሁሉ ለሥረ ነገሩ መሰረት በመሆን ከቀድሞው ውሳኔ ጋር ተቀላቅለው እንዳለቁ የሚቆጠሩ በመሆናቸው በእነኝህ ጉዳዮች ላይ ወደፊት ክስ የሚያቀርብበትን መንገድ እስከ ወዲያኛው መከልከል ነው፡፡

ሁለተኛው ቅጣት ደግሞ አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የሚከለክለው መርህ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ሲሆን ከሳሽ ከአንድ የክስ ምክንያት የመነጨ ክስና የዳኝነት ጥያቄዎቹን ሊከስ ሲችል ሆነ ብሎ ባስቀረው ሀብት ላይ ድጋሚ ክስ ለማቅረብ እንደማይችል የተቀመጠው ገደብ ይፈጸምበታል፡፡

ነገር ግን ሁለቱም መርሆዎች ክርክርን መቋጨት መሰረት ያደረገ የጋራ አላማ ይኑራቸው እንጂ አንድ አይነት ይዘት እና ገጽታ እንደሌላቸው ሊሰመርበት ይገባል፡፡[39] በመሰረቱ የመጨረሻ ፍርድ ስላገኙ ጉዳዮች (Res Judicata) የተመለከተው መርህ ትኩረቱ አንድም ውሳኔ ባረፈበት የቀደመ ክርክር ወቅት የፍርድ ቤቱን በር የረገጡ ወይም ተነስቶ የነበረ ስረ ነገር እና ጭብጥ ጋር አንድ አይነት በሆነ ጊዜ በዚያው ነገር ላይ ድጋሚ ክስም ሆነ ማናቸውንም ዓይነት ክርክር ለማቅረብ መከልከል ላይ ነው፡፡ [40] በሌላ በኩል ደግሞ የሁለተኛው ክስ መታገድ በቀድሞ ክርክር ወቅት በቀረቡት ነጥቦች ላይ ብቻ ሳይገደብ ለቀድሞው ክርክር የማስረጃ ወይም የመከላከያ ወይም የመቃወሚያ መሰረት መሆን ይገባቸው የነበሩ ነገሮችን እና ምክንያቶችን ሁሉ ይጨምራል፡፡[41] ይኸውም ለዚህ መርህ ሲባል በቀድሞው ክርክር ወቅት ለፍርድ ቤቱ የቀረቡትም ሆኑ ያልቀረቡት ነጥቦች ሁሉ የሚመዘኑት ውሳኔ ላገኘው ክስ ካላቸው ቅርበት እንጂ ራሱን ችሎ ስለሚቀርብ ክስ ወይም የዳኝነት ጥያቄ የሚመለከቱ አለመሆናቸውን ከድንጋጌው መረዳት ይቻላል፡፡[42] በሌላ በኩል አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የሚከለክለው

---

[38] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ገጽ 439 እና የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 5 እና 216

[39] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ገጽ 485

[40] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ገጽ 485 እና የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ 5

[41] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 5(1) እና (2)

[42] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 5 እንዲሁም የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 ገጽ 485 ገጽ 485 እንዲሁም ከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኛ አቶ ተፈሪ ገብሩ ጋር

ደንብ የሚመለከተው በቀድሞው ውሳኔ ውስጥ የፍርድ ቤቱን በር ያልረገጡ ክሶች እና የዳኝነት ጥያቄዎችን ሲሆን የመጀመሪያው ክስ የመነጨበትን ምክንያት የሚጋሩ ቢሆኑም እንኳን በከሳሽ ተቀንሰው የቀሩ ጉዳዩች አመራርን ነው።[43] ግንኙነታቸውን ከመቃኘት አንጻር ከእነዚህ ሁለት መርሆዎች ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ በአንቀጽ 216(2) እና 5(3) መካከል አንዳች ግንኙነት አለ? ከሚለው ጥያቄ የሚመነጭ ሲሆን በተለይም በዳኞች ዘንድ ሁለት አይነት ሀሳቦች ይሰነዘሩባቸዋል ። ቀዳሚውን አረዳድ ስንመለከት በአንቀጽ 216(4) ላይ እንደተደነገገው ከሳሽ ከፊሉን ዳኝነት ሌላ ጊዜ ለማንሳት እንዲፈቀድለት ፍርድ ቤቱን ዕድል እንዲሰጠው ሊጠይቅ የሚችልበት ሥርዓት እንዳለ ተመልክቷል። በአንጻሩ ግን ፈቃድ ተጠይቆ ምላሽ ባልተሰጠበት መብት ውጤትን በተመለከተ ሁለት አይነት ሀሳቦች ይራመዳሉ ። የመጀሪያው ፍርድ ቤቱ በጥያቄው ላይ ምንም ምላሽ ሳይሰጥ ካለፈው ወደፊት ከሳሽ ይኸንን ክፍል አንስቶ አዲስ ክስ ለማንሳት ቢፈልግ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት በዝምታ ያለፈው የዳኝነት ጥያቄ እንደተከለከለ ስለሚቆጠር ከሳሽ በድጋሚ ሊያነሳው የማይችል መሆኑን የሚያስቀምጠው መርህ አንቀጽ 5 (3) ተፈጻሚ መሆን ይገባዋል የሚል ነው። ይኸውም ሁኔታ ይልቁንም አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የሚከለክለው እና የመጨረሻ ውሳኔ ስላገኙ ጉዳዮች አስመልክቶ የተደነገገው መርህን አይነተኛ ግንኙነት የሚታይበት ሁኔታ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል በሚል ይገለጻል።[44] በሌላ በኩል ደግሞ በአንቀጽ 216 (4) ሥር እንደተመለከተው ከሳሽ የተወሰነውን የዳኝነት ክፍል ቀንሶ ለማስቀረት የሚጠይቀው ፈቃድ **መሰረታዊ** የሆነውን ዳኝነት ሳይሆን **ሥነ ሥርዓታዊ የክስ** አቀራረብ ሂደትን የሚመለከት ሲሆን በአንቀጽ 5(3) ስር የተመለከተው ዳኝነት ግን መሰረታዊ የሆነውን የዳኝነት ጥያቄ የሚገዛ መርህ በመሆኑ ሁለቱ መርሆዎች በዚህ ረገድ ምንም ሊያገናኛቸው የሚችል ነገር የለም። በመሆኑም በአንቀጽ 216(4) መሰረት ወደፊት ከፊሉን የዳኝነት ክፍል ለማቅረብ ፈቃድ ጠይቆ ምንም ምላሽ ሳይሰጠው የታለፈ ከሳሽ ፍርድ ቤቱ ፈቃዱን ቢሰጠው ወደፊት ሊያቀርብ የሚችለውን መብት እና ዳኝነት የሚመለከት አይሆንም። ከዚህም በተጨማሪ ዳኞች ሁልጊዜ ህግን ሲተረጉሙ መብትን በሚያሰፋ እንጂ በሚያጣብብ መልኩ ሊሆን አይገባም የሚል ክርክር

---

መጋቢት 2 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገ ቃለ-መጠይቅ፣ ከአቶ አስቻለው አሻግሬ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት መምህር ፣ የህግ አማካሪ ና ጠበቃ እንዲሁም ጸሀፊ ጋር ተካቲት 29 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገ ቃለ መጠይቅ

[43] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 216

[44] ከፊደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኛ አቶ አሊ መሀመድ አሊ ጋር መጋቢት 2 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ እና የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኞች ፡አቶ ምትኩ ወንደ ፣አቶ ዬሀንስ ቢሻው ጋር ሚያዚያ 9 ቀን 2008 ዓ.ም በተደረገ የትኩረት ቡድን ውይይት።

ይቀርባል።[45] ይሁን እንጂ በጸሀፊውም እምነት በተለይም ከሳሽ የመጀመሪያውን ክስ ሲያቀርብና በክርክሩ ውስጥም ወደፊት በተወሰነው የዳኝነት ክፍል ላይ ክስ ላቅርብ የሚለውን የሂደት ጥያቄ ሲያነሳ ሊቀንስ የፈለገውንም ዳኝነት ጭምር እያሳወቀ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ያለውን ነገር ሁሉ ለፍርድ ቤቱ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ እንደሰጠ መወሰድ አለበት። በመሆኑም ፈቃዱን ፍርድ ቤቱ ሰምቶ ምላሽ ሳይሰጥ ካለፈው በአንቀጽ 5 (3)የመጨረሻ ውሳኔ ስላገኙ ጉዳዩችን የተመለከተው መርህ ጋር ተጣምሮ ታይቶ ውጤቱም ዳኝነት እንደተነፈገ ሊቆጠር እና ድጋሚ በዛ ጉዳይ ክስ ለማቅረብ ክልከላ ሊደረግበት ይገባል ።

### 1.3.2 አንድ የክስ ምክንያትን መነጣጠል የሚከለክለው ጠቅላላ መርሕ

አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የሚከለክለው መርህ በተለይም ክፍ ብሎ የተመለከቱትን አላማዎች በአግባቡ ለማሳከት ያስችለው ዘንድ ከሳሽ በማንኛውም ፍርድ ቤት የሚያቀርበውን አቤቱታ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት በሚያስችል እና ለተደጋጋሚ ክርክር በር በማይከፍት መልኩ ግልጽ አድርጎ አጠቃልሎ ማቅረብ ያለበት መሆኑ ቀድሞውኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216 ስር ተገንግንል። ይህም ባልተፈጸመ ጊዜ አንድ የክስ መነጣጠልን የሚከለክለው መርህ ጉዳይ እንደሚነሳ ይታወቃል።[46] በመሰረቱ ይህ አይነት ሥርዓት በተለያዩ ሀገራት የሕግ ማዕቀፎች ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ለአብነትም የኪዩቢክ የፍትሐ ብሔር ሕግ፣ የሉዚያና የፍትሐ ብሔር ሕግ እንዲሁም የፈረንሳይ የፍትሐ ብሔር ሕግ እና ደንብን መውሰድ ይቻላል።[47] ስለሆነም ይህንን ደንብ ተላለፎ ከአንድ የክስ ምክንያት የመነጨ ሁሉንም ክስና ዳኝነት አሟጦ ማቅረብ እየተገባው **ሆነ ብሎ** ቀንሶ ባስቀረው ሀብት ላይ ድጋሚ ሊከስ እንደማይችል በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ተደንግጎ እናገኛለን።[48]

በርግጥ የዚህን አንቀጽ አቀማመጥ በእንግሊዝኛው ትርጉም ውስጥ አማርኛው ውስጥ ሆነ ብሎ በመቀነስ (intentionally relinquishes) ከሚለው በተጨማሪ ከተወ (omits) የሚል ቃል

[45] የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኛ አቶ በሪሁን አዱኛ ታምራት ጋር ሚያዚያ 9 ቀን 2008 ዓ.ም በተደረገ የትኩረት ቡድን ውይይት።

[46] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 216(1)

[47] Charles W.Darnall Jr., Louisiana Practice -splitting CausesofAction,14La.L.Rev.(1954) Availableat:http://digitalcommons.law.lsu.edu/laIrev/vol14/iss4/15p.907-8. የተገኘው በ2/5/2008 ዓ.ም

[48] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 216 (3)

ተመልክቶ እናገኛለን፡፡[49] በዚህ ረገድ የህንዱን የሥነ ሥርዓት ሕግ ስንመለከትም ከእንግሊዝኛው ንባብ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የተቀመጠ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡[50] ይህንንም ለማስፈጸም በተለይም ከሳሽ ሳይከስ ያለፈው፣ የተወውን ወይም የረሳውን …*omits to sue…* እና ሆነ ብሎ ቀንሶ ያስቀረውን… *intentionally relinquishes…* በሚል የተቀመጡትን ሁኔታዎች አስመልክቶ የህንዱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ለእነዚህ ንዑስ አንቀጾች ያስቀመጠውን ማብራሪያ ጋር መመልከት ያስፈልጋል፡፡

በመርህ ደረጃ ከሳሽ የሚጠይቀውን ዳኝነት በሙሉ አጠቃልሎ ማቅረብ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሳሽ ክሱን በአንድ በተለየ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር ለማቅረብ እንዲያመቸው አስቦ በክሱ ከሚጠይቀው ሀብት ውስጥ ቀንሶ ለመክሰስ ይችላል፡፡ ነገር ግን ስልታዊ በሆነ በዚህ መንገድ አስቦ የቀነሰውን ሀብት በተመለከተ ወደፊት አዲስ የክስ ፍይል ለማስከፈት የማይችል መሆኑን መርሁ እንደሚያስረዳ ያስቀመጠ ሲሆን ይኸውም ተዋረድ በእንግሊዝኛው ብቻ ሳይሆን በአማርኛውም ቅጅ ጭምር በተመሳሳይ ሁኔታ ተቀርጻል፡፡[51]

ሌላው ነጥብ የህንዱ ማብራሪያ እንደሚያመለክተው ይህ ክልከላ በዚህ ሁኔታ ብቻ ሳይወሰን በማናቸውም ምክንያት ከሳሽ ሳይከስ ያለፈውን (…if the plaintiff for any reason, omits to sue…) የተወሰነ የክስ ክፍልም ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ሲሆን ይህውም በእንግሊዝኛው ቅጂ ብቻ ላይ በአንቀጽ 216(3) ስር ተመልክቶ ይገኛል፡፡[52] በመሰረቱ ከሳሽ ከአንድ አይነት የክስ ምክንያት የመነጨ ከአንድ በላይ የዳኝነት ጥያቄዎች ሲኖሩትም ለሁሉም ወይም ከሁሉም መካከል የፈለገውን መርጦ ሊከስ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሳይከስ የተወው የዳኝነት ክፍል ያለ ፍርድ ቤቱ ፈቃድ ከሆነ እንደገና በቀሪው ዳኝነት ላይ ወደፊት ሊከስ እንደማይችል በተመሳሳይ ሁኔታ ማብራሪያው ያስገነዝባል፡፡[53]

---

[49] **ART. 216(3)** Civil procedure code of the Empire of Ethiopia, Decree no.52 of 1965.
A plaintiff who omits to sue in respect of, or intentionally relinquishes, any portion of his claim shall not afterwards sue with respect to the portion so omitted or relinquished.

[50] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ገጽ 439
Order II Rule 2. (2)Were a plaintiff omits to sue in respect of, or intentionally relinquishes any portion of hisclaim, shall not afterwards sue with respect to the portion so omitted or relinquished.

[51] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 216 (2) እና (3) እና የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ከገጽ 440- 443 እና በተመሳሳይም የሱዚያና code of practice1825 አንቀጽ 92(2) "… But if one,inorder to give jurisdiction to a judge, demand a sum below that which is really due him, he shall be presuemed to have remitted the over plus ,and after having obtained for the sum he has claimed ,he shall lose all right of action for the overplus." በሚል አስቀምጦታል፡፡ እና የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 44

[52] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ገጽ 440

[53] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 216(3) እና የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ገጽ 440ን ይመልከቱ፡፡

ከዚህ መርህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ሌላኛው ጉዳይ በተለይም የሀሳብ ክፍልን የሚመለከተው **ሆነ ብሎ** የሚለውን ሐረግ አቀማመጥና አተረጓጎም ይሆናል፡፡ የክስ ባለቤት ሁልጊዜ የሚያቀርበውን ክስ እና የሚጠይቀውን ዳኝነት በአግባቡ የሚያውቅ ለመብቱ ቀናኢ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚህ አንጻር ከመነሻው ሊከስ ሲችል ቀንሶ ካስቀረ የሕጉ ግምት ሆነ ብሎ እንደተወው የሚያስቆጥር በመሆኑ ይህንን የሕግ ግምት የማስተባበል ሸክም በራሱ ላይ እንደሚያርፍ ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ እና በዚሁ አግባብ ሊተረጎም ይገባል፡፡[54] በመሰረቱ መብቱ ከአንድ የክስ ምክንያት የመነጨም ቢሆን የመጀመሪያው ክስ በቀረበ ጊዜ ሊጠየቅ የሚችል የተከሳሽ ግዴታ ወይም የከሳሽ የበሰለ መብት መሆን ይኖርበታል፡፡[55] ከዚሁ ጎን ለጎን ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ትክክለኛ ፍትህን የመስጠት ሀላፊነትም ያለበት በመሆኑ ከሳሽ ሆነ ብሎ መርሁን በመጣስ አንድን የክስ ምክንያት እየነጣጠለ ነው ወይም አይደለም የሚለውን ብይን ከመስጠቱ በፊት በዋናነት የክርክሩን አመጣጥ እና ባህሪ በማጤን አግባብነት ካላቸው ማስረጃዎች እና ህግጋት ጋር አጣምሮ መመርመር እንደ አስፈላጊነቱ የምክንያታዊ ሰው መለኪያን (Resonable man standard) ሁሉ መጠቀም ይጠበቅበታል፡፡[56]

በዚህ ረገድ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጂ የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሳኔዎች ይህ አይነት አካሄድ የተንጸባረቀባቸው ሲሆን ለአብነትም በፌ/ሰ/መ/ቁ 36776 በአመልካች መብራቱ ፣ተ/ማርያም ፣ገ/ማርያም የሽርክና ማህበር እና በተጠሪ አቶ መብራቱ አንዳይ መካከል የነበረውን ክርክር መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ክርክር በሰበር እንዲቀርብ መነሻ የሆነው አመልካች ተጠሪ የማህበሩ ሊቀ መንበር ሆነው ሲሰሩ በእጃቸው የገባውን የማህበሩን 100.000 ( አንድ መቶ ሽህ ብር) ለግል መኪናቸው መግዣ ያዋሉ በመሆኑ ገንዘቡ ከባንክ ወጭ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ በሚል ክስ አቅርቧል፡፡ተጠሪው በበኩሉ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ አስመልክቶ ቀደም ሲል አመልካች አቅርቦ በነበረው ክስ ውስጥ አጠቃልሎ ማቅረብ እየተገባው ሌላ ክስ ማቅረቡ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216 አንጻር ተገቢነት የለውም የሚል መቃወምያን ያነሳል፡፡ ክርክሩም በቅድሚያ ከመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንስቶ የተለያየ ውሳኔ እየተሰጠበት ከቆየ በኋላ በመጨረሻም ለፌደራል ሰበር ስሚ ችሎቱ ቀርቧል፡፡ ችሎቱም አመልካች በአቤቱታቸው ላይ ተጠሪ የተጠቀሰውን 100, 000(አንድ መቶ ሽህ ብር) ለግል መኪና መግዣ ያዋሉት መሆኑ የተረጋገጠው የመጀመሪያው

[54] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 20
[55] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10 ገጽ 541
[56] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 20

ክስ ከቀረበ በኋላ በመሆኑ አመልካች ሆነ ብሎ ቀንሶ ያስቀረው ነው በሚል በፍ/ሥ/ሥሕ/ቁ 216(3) መሰረት ክሱ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት መርምሯል።

ችሎቱም በተጠሪ ላይ የቀረበው የ100,000 ብር ክስ እንዳለ ሆኖ በሌላ በኩል ሚያዚያ 24 ቀን 1997 ዓ.ም በዚሁ ማህበር ውስጥ በነበራቸው ሀላፊነት በእጃቸው ከገባው ገንዘብ ውስጥ 689,306,49(ስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሽህ ሦስት መቶ ስድስት ብር ከ አርባ ዘጠኝ ሳንቲም አጉድለዋል የሚል ክስ ተመስርቶባቸው የነበረ መሆኑን በክርክሩ ሂደት አጥርቷል። ከዚህም በመነሳት በርግጥም በሁለቱም ክሶች የቀረበው ጥያቄ ተጠሪ የማህበሩ ሊቀ መንበር ሆነው ሲሰሩ ያጎደሉትን ገንዘብ እንዲከፍሉ በመሆኑ አመልካች በሁለተኛው ክስ ያቀረበው ጥያቄ በመጀመርያው ክስ ተጠቃልሎ መቅረብ የነበረበት መሆኑን ያተተ ሲሆን ይኸውም ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216(1) ከተቀመጠው መርህ አንጻር የተመዘነ መሆኑን ያስገነዝባል ። ቀጥሎም ተጠሪ 100, 000 ብር ያጎደሉ መሆናቸው የተረጋገጠው የኦዲት ሪፖርት ከተሰራና የመጀመሪያው ክስ 689, 306, 49( ስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሽህ ሦስት መቶ ስድስት ብር ከ አርባ ዘጠኝ ሳንቲም) አጉድለዋል የሚል ክስ ከቀረበ በኋላ በመሆኑ ሆነ ብሎ ገንዘቡን ቀንሶ ክስ መስርቷል ሊባል አይችልም የሚል መከራከሪያ ጎልቶ የወጣ ስለነበር ችሎቱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እና በተለይም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216(3) በተመለከተው ሁኔታ አመልካች ቀደም ብሎ ባቀረበው ክስ ሊከስ እየቻለ ሆነ ብሎ ቀንሶ ያስቀረውን ክስ ነው በድጋሚ ያቀረበው የሚለውን ለመመርመር አመልካች ቀደም ሲል በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስከፈቱትን የመዝገብ ቁጥር 33585ን አስቀርቦ መርምሯል። በዚህም ምርመራ አመልካች በተጠሪ ላይ የመጀመሪያውን ክስ ያቀረበው ሚያዚያ 24 ቀን 1997 ዓ.ም ሲሆን 100,000 ብር ደግሞ አጉድሏል በሚል ሁለተኛው ክስ የቀረበው ግንቦት 3 ቀን 1997 ዓ.ም ይህውም የመጀመሪያው ክስ ከቀረበ በ10 ቀን እንኳን ሳያሞላው ማለት ነው። በተጨማሪም ችሎቱ ተጠሪ 100,000 ማጉደሉ በኦዲት መረጋገጡን ያወቀው የመጀመሪያው ክስ እንደቀረበ እና ተጠሪ ለመጀመሪያው ክስ እንኳን መልስ ሣይሰጥ በፊት እንደሆነም ጭምር በማረጋገጡ አመልካች ክሱን በማሻሻል በዚህ መዝገብ ክስ የቀረበበትን ጉዳይም አጠቃልሎ ለማቅረብ እየቻለ ሁለተኛ ክስ ማቅረቡ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216(3) አንጸር የተከለከለ መሆኑን በማተት አመልካችን አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል ።[57]

[57] የፌ/ሰ/መ/ቁ/ 36776 በአመልካች መብራቱ፣ ተ/ማርያም፣ ገ/ማርያም የሽርክና ማህበር እና በተጠሪ አቶ መብራቱ አንዳይ መካከል በነበረው ክርክር መጋቢት 2 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ይመልከቱ።

በዚህ ውሳኔ ውስጥ ችሎቱ ይህን ያህል የክርክሩን ሂደት ከቀረቡት ማስረጃዎች እና አግባብነት ካላቸው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216 ንኡስ ቁጥር 1 እና 3 ጋር አጣምሮ መመርመሩ በዋናነት አመልካች በሁለተኛው ክስ ያቀረበው ጉዳይ የመጀመርያውን ክስ በማሻሻል መጨመር የሚችል መሆኑን ፣ይህንንም ለማድረግ ሰፊ ሥነ ሥርዓታዊ ጊዜ እና እድል እንደነበረው እና በመጨረሻም ይህን ሳያደርግ መቅረቱ በአንድ ምክንያታዊ ሰው መለኪያ (Resonable man standard) ሲለካ ሆነ ብሎ ከፍሎ ያስቀረው ነው ወደሚል ፍንትው ያለ የሀሳብ ክፍል ማረጋገጫ ላይ ያደረሰው መሆኑን ነው።[58] በዚህ ገረድ ለምሳሌነት የሉዚያናን ሕግ ስንመለከት በርግጥም ከሳሽ በመጀመሪያው ክሱ ውስጥ ጨምሮ መጠየቅ ሲችል ያሰቀረውን ጥያቄ ክሱን በማሻሻል ሳይጨምር ከቀረ ወደፊት ለቀረው አዲስ ክስ ማቅረብ የሚችልበትን እድል እንደሚያጣ የደነገገ ሲሆን ተመሳሳይ ክልከላ በፈረንሳይ የፍትሐ ብሔር ደንብ አንቀጽ 6 እና የፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 1346 ሥር ተመልክቶ ይገኛል ።[59]

ይሁን እንጂ ይህንን የሕጉን ግምት የማስተባበል ሀላፊነት የከሳሽ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዳኞችም ፍትሐዊ ፍርድ የመስጠት ሀላፊነት ያለባቸው በመሆኑ እንደ ነገሩ ሁኔታ ክርክሩ የበቀለበትን መሰረታዊ ሕግ ፣የክርክሩን ባህሪ እና አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች (ለምሳሌ፡ የቀደመ ውሳኔ ተሰጥቶበታል የተባለው መዝገብ) ከሥነ ሥርዓት ሕጉ ጋር አጣምረው በመመርመር ፍትሐዊ ውሳኔ መስጠት እንደሚገባቸው ያስገነዝባል።

### 1. 3. 3 አንድ የክስ ምክንያት ያለመነጣጠልን መርሕ አስመልክቶ የሚነሳ ተቃውሞ በማን እና መቼ ይነሳል?

በመሰረቱ አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የተመለከተው ጽንሰ ሐሳብ ሲነሳ በተለይም ሊጠብቅ ካሰበው ፍላጎት አንጻር ተያይዞ የሚነሳው ሌላኛው ነጥብ ደግሞ ይህ **ተቃውሞ በማን እና መቼ** ይነሳል? የሚለው ሲሆን ይህንን ማየት በተለይም መርሁን በማስፈጸም በኩል ተከራካሪ ወገኖችም ሆኑ ዳኞች በጉዳዩ ላይ የሚኖራቸውን ሚና በውል ለመረዳት ያስችላል። ይሁን እንጂ የሥነ ሥርአት ሕጉ አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን አስመልክቶ የሚቀርብ መቃወሚያ በማን እና መቼ መነሳት እንዳለበት ግልጽ የሆኑ ድንጋጌዎችን አስቀምጦ አናገኘውም። ከዚህም የተነሳ በጉዳዩ ላይ በዋናነት ሁለት አይነት ሀሳቦች በዳኞች መካከል እንደሚንጸባረቁ ማየት ይቻላል።

---

[58] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 91 ተከራካሪዎች ክሳቸውን ለማሻሻል ከፈለጉ ጥያቄ ለፍርድ ቤቱ ጥያቄ ማቅረብ ስለሚችሉበት እና ክስ መሻሻል ስለሚቻልበት ስርአት ያስረዳል።

[59] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 44

ቀዳሚው አቋም ተከሳሽ መርሁን አንስቶ መቃወም ያለበት ቢሆንም ይህንን ባላደረገ ጊዜ ዳኞች ባወቁበት ሁኔታ ሁሉ ማንሳት መቻል አለባቸው የሚል ነው።[60] ለዚህም መደምደሚያ የሚቀርቡትን ሀሳቦችን ስንመለከት አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የሚከለክለው መርህን ጨምሮ የያዘው ጠቅላላው የሥነ ሥርዓቱ አላማ ሁሉም ክርክሮች የፍርድ ቤቶችንም ሆነ የተከራካሪ ወገኖችን ወጭ፣ጊዜ፣እና ሀይል ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲቋጩ ማድረግ ነው ። ይህንን ሁለንተናዊ የሆነ የፍርድ ቤቶችን ውጤታማነትን (Judicial Efficiency) ለማረጋገጥ ዳኞች አጠቃላይ ክርክሮችን በበላይነት የመምራት እና የመቆጣጠር ሰፊ ሚና ሊኖራቸው ይገባል። ስለሆነም ተከሳሽ ባይቃወምም እንኳን ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት በርግጥም ከሳሽ ከአንድ አድራጎት በመነጨ ምክንያት በድጋሚ ክስ እያቀረበ መሆኑን በማንኛውም የክርክር ደረጃ ላይ በተረዳ ጊዜ ማንሳት እና አስፈላጊውን ማጣራት ሁሉ አድርጎ መወሰን ይጠበቅበታል የሚል ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ለቀረበው አቋም ማጠናከሪያ ነው በሚል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዘገብ ቁጥር 17361 የሰጠውን ውሳኔ መሰረት ያደርጋል።[61] ይህም በተለይም ዳኞች የሥነ ሥርዓት ሕጉን አላማ ለማሳካት ሲባል በተከራካሪዎች ተቃውሞ ባይቀርብበትም እንኳን ሥነ ሥርዓታዊ ይርጋን ራሳቸው አንስተው መወሰን እንዳለባቸው አስገዳጂ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል። ስለሆነም አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የሚከለክለው መርህም ቢሆን የፍርድ ቤቶችን ውጤታማነት ጠብቆ የሚሄድ በመሆኑ ዳኞች በተመሳሳይ ሁኔታ በንቃት ሊመረምሩት የሚገባ እንጂ በብቸኝነት ለተከሳሽ የተተወ ተግባር ተደርጎ የሚወሰድ ከሆነ የሥነ ሥርዓቱን ምሰሶ የሚንድ በመሆኑ አግባብነት አይኖረውም በማለት ያስቀምጣሉ።[62]

ሁለተኛው ሀሳብ ደግሞ ከዚህ በተለየ ሁኔታ በተለይም የፍርድ ቤቶችን ሚና በተወሰነ መልኩ የሚገድብ ሆኖ የሚቀርብ ነው። ክፍ ሲል ለማብራራት እንደተሞከረው አንድ የክስ ምክንያትን መነጣጠል የሚከለክለው መርህ ከፍርድ ቤቶች ውጤታማነት እና ከክስ አቅራቢው ጋር የተያያዘ አላማ ያለው ቢሆንም በዋናነት የተነደፈው ሳይፈልጉ ወደ ለክርክር የሚጠሩ ተከሳሾች በአንድ ጥፋት በየጊዜው ክስ እየቀረበባቸው ለከፍተኛ እንግልት እንዳይጋለጡ መጠበቅን መሰረት ያደረገ የፍትሐዊነት ትኩረቱ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ መርሁን አንስቶ መቃወም

[60] የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኞች አቶ ጸጋዬ ወርቃየሁ፣ በሪሁን አዱኛ ምህረቱ፣ ሀብታሙ እርቅይሁን በቀን ሚያዚያ 9ቀን 2008 ዓ.ም በተደረገ የትኩረት ቡድን ውይይት።

[61] የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰ/ሰችሎት በመዝገብ ቁጥር 17361 ሀምሌ 25 ቀን 1997 በአመልካች ወ/ሮ ጋዲሴ አርጌ እና በተጠሪ ወርቅ አንጥፉ በቀለ መካከል በነበረው ክርክር የሰጠው ውሳኔ ቅጽ 1 እና ይሕው ውሳኔ በመዘገብ ቁጥር 76601 ላይ አስገዳጅነቱ ተረጋግጦ ተጠቅሷል ቅጽ 13

[62] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 55

የሚጠቅመው ተከሳሽ በርግጥም በአዲስ መልክ በከሳሽ በኩል እየቀረበ ያለው ክስ እና የዳኝነት ጥያቄ ቀደም ሲል ከቀረበ አንድ ምክንያት የመነጨ አንደሆነ በፍሬ ነገር ደረጃ በማሳየት መቃወም ይጠበቅበታል እንጂ ፍርድ ቤቶች በራሳቸው የሚያነሱት ሊሆን አይገባም፡፡ ይህንን ማንሳት ካልቻለ ግን መቃወም እንዳልፈለገ ተቆጥሮ ክርክሩ ሊቀጥል የሚገባ በመሆኑ ይህንን መርህ አስመልክቶ የሚነሳው ተቃውሞ በተከሳሽ ሊተው የሚችል (waviable objection) ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል በሚል ያስቀምጣሉ ፡፡ [63]

በዚህ መልኩ ለተመሳሳይ አብይ አላማ የተቀመጠው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን (Res Judicata)ንም ስንመለከት በተከራካሪዎች በመቃወሚያነት ካልተነሳ ሆነ ብሎ እንደተተወ የሚወሰድ መሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244 ድንጋጌ መንፈስ እንረዳለን፡፡ በዚህ ረገድ መርሁ የፍርድ ቤቶችን አጠቃላይ ወጭ የመቆጠብ አላማ ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ በተደጋጋሚ መቅረቡ በባህሪው የዳኝነት ስልጣን ጉዳይ ባለመሆኑ እንደ ሥረ ነገር ስልጣን አለመኖር ያን ያህል ፍርድ ቤቱን ዋጋ ያለው ውሳኔ (valid judgement) ከመስጠት የሚከለክለው ባለመሆኑ በተከሳሽ በኩል ግልጽ ተቃውሞ ባልተነሳበት ወይም በተተወበት ሁኔታ ሁሉ ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት አንስቶ ውድቅ ሊያደርግ የሚችልበት ሥርዓት የለም፡፡ ለዚህም ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት በራሱ መርምሮ የክስ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ብሎ ሊወስን ከሚችልባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ህግ አውጭው አካቶት አለመግኘቱ በራሱ ጥሩ ማሳያ ሆኖ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ከዚህም በዘለለ በዚህ ረገድ ለተከራካሪዎች የተተው ተቃውሞዎችን ዳኞች እያነሡ ሰፊ ክርክር እንዲያካዱ ማድረግ በርግጥም የገለልተኛነት ጥያቄ ሁሉ እንደሚያስነሳ መታወቅ አለበት በማለት ይከራከራሉ፡፡[64] በርግጥ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎቱ በተለይም የሥነ ሥርዓት ይርጋን በተመለከተ በተከሳሽ ቢታለፉም እንኳ ፍርድ ቤቱ በራሱ ማንሳት ያለበት መሆኑን ውሳኔ ያሳረፈ መሆኑን በቀደመው አቋም ላይ የተመለከተ ቢሆንም ውሳኔውም ሆነ ለውሳኔው መዳረሻ የሆኑት ምክንያቶች በግልጽ ይርጋን የተመለከቱ በመሆናቸው የክስ ምክንያት መነጣጠልን በተመለከተው መርህ ላይ አስገዳጅ ተፈጻሚነት ስለማይኖረው በተመሳሳይ በዳኞች ሊነሳ ይገባል የሚል መከራከሪያ ሊቀርብ አይችልም፡፡[65]

---

[63] ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኞች አቶ አሊ መሀመድ አሊ ፣ አቶ ተፈሪ ገብሩ ጋር መጋቢት 2 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ ከአቶ አስቻለው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት መምህር፣ የሕግ አማካሪ ና ጠበቃ እንዲሁም ጸሀፊ ጋር ተካቲት 29 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገ ቃለ-መጠይቅ እንዲሁም የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኞች አቶ በሪሁን አዱኛ ታምራት፣ ምትኩ ወንደ በቀን ሚያዚያ 9 ቀን 2008 ዓ.ም በተደረገ የትኩረት ቡድን ውይይት፡፡

[64]ዝኒ ከማሁ እንዲሁም የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 231

[65]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 58

ጸሀፊውም እንደሚጋራው በርግጥም ዳኞች የፍርድ ቤቶችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ሥነ ሥርዓቱን የመቆጣጠር ሀላፊነት ያለባቸው ቢሆንም ዝርዝር ሚናቸውን በተመለከተ መርሁ ከተከራካሪዎች ፍላጎት ጋር ካለው ቅርበትም ጭምር አብሮ ሊመዘን እና ሊታይ ይገባል። ከዚህ አንጻር ክፍ ሲል የመርሁ አላማ ላይ በስፋት ለማየት እንደተሞከረው አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የሚከለክለው መርህ የፍርድ ቤቶችን ብቃት ከማሳደግ የበለጠ ተከሳሽን ካልተገባ እንግልት ለመከላከል ታስቦ የተነደፈ የፍትሐዊነት መገለጫ በመሆኑ ተከሳሽ ተቃውሞውን ለማንሳትም ሆነ ለመተው የሚችል እንደሆነ በዚህ ርእስ ዙሪያ የተጻፉ ጽሁፎች ያሳያሉ።[66] ከዚህም የተነሳ እንዲያውም በአብዛኛው የኮመን ሎው የህግ ሥርአት ውስጥ ያሉ የፍትሐ ብሔር የሕግ ማዕቀፎች ውስጥ የተከሳሹ ሳይቃወም መቅረት ስምምነቱን እንደሚያሳይ ተቆጥሮ ክርክሩ እንደሚቀጥል እና ይልቁንም ይህ አጋጣሚ አንዱ የጠቅላላ መርሁ ልዩ ሁኔታ ተደርጎ እንደሚወሰድ ማየት ይቻላል።[67]

ሌላው አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን አስመልክቶ የሚቀርበው ተቃውሞ በማን መነሳት አለበት  የሚለው ነጥብ ላይ እንደታየው ሁሉ ተቃውሞው ሊቀርብ ስለሚገባበት ጊዜ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ግልጽ ምላሽ አይሰጥም። በሌላ በኩል ይህንን መርህ በአላማ የሚጋራው የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ደንብ (Res Judicata) ግን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሊነሱ ከሚገባቸው ሁኔታዎች ዝርዝር መካካል ሕግ አውጭው አስቀምጦታል። ይሁን እንጂ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244 በራሱ ሁሉንም ሁኔታዎች ዘርዝሮ የጨረሰ (exhaustive) ባለመሆኑ አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን አስመልክቶ የሚቀርብን መቃወሚያ የሚካተት እና በዚሁ ሥርዓት መሰረት ቀርቦ እንዲመራ አድርጎ መተርጎም ተገቢነት እንዳለው ይገለጻል።[68]

### 1. 3. 3 አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠል የሚፈቀድበት ልዩ ሁኔታ

ከፍ ሲል እንደተገለጸው የክስ ባለቤት የሆነው ከሳሽ በርግጥም ከአንድ የተከሳሽ አድራጎት የመነጨ ማናቸውም ክሶች እና የዳኝነት ጥያቄዎች በሙሉ አጠቃልሎ ማቅረብ ያለበት መሆኑ እና ይህንን ሳያደርግ በቀረ ጊዜ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የሚከለክለው መርህን መቃወም ሆኖ ውጤቱም ድጋሚ በጉዳዩ ላይ ምንም አይነት ጥያቄ የማንሳት እድልን ዝግ እንደሚያደርግ ተመልክተናል። በአንጻሩ ይህ አጠቃላይ መርህ ልክ እንደ አብዛኞቹ መርሆዎች

[66] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 7
[67] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 ከገጽ 265- 267
[68] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ  244 ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10 ገጽ 487 እንዲሁም የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 58 ስር የተመለከቱት ዳኞች እና ሌሎች የሕግ ባለሙያዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ እና የትኩረት ቡድን ውይይት ላይ ሀሳቡ በስፋት ተነስቷል።

ሊፈጸም የማይችልበት ልዩ ሁኔታ (Exception) እንዳለው ደግሞ ማየት አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ ረገድ በኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት ከአንድ ምክንያት በመነጨ ክስ መሰረት ፍርድ ያገኘ ሰው ሌላ ጊዜ በዚያው የክስ ምክንያት ጥያቄ ሊያነሳ እንደማይችል የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ ይህ አጠቃላይ መርህ በጥቂት የሥርዓቱ ተከታይ ሀገራት ሥነ ሥርዓት ውስጥ በአንዳንድ ሁኔታዎች ገቢራዊ የማይሆንበት የተለየ ሁኔታም ጭምር እንዳለ ማየት ይቻላል። [69] ለአብነትም በአሜሪካ የፌደራል የፍትሐ ብሔር መርሆዎችም በተመረጡ አንዳንድ ጉዳዮችና ሁኔታዎች የአሜሪካ ፌደራል ፍርድ ቤት ጉዳዮችን ለማስተካከል ሲል በተመሳሳይ የክስ ምክንያት መሰረት ውሳኔ የተሰጠባቸውን ጉዳዮችን መልሶ የሚያይበት ሥርዓት እንዳለ ተመልክቷል።[70]

ሌላው ከሳሽ ያቀረበው ክስ ቀደም ሲል በቀረበና ውሳኔ ካረፈበት አንድ የክስ ምክንያት የመነጨ መሆኑን ተረድቶ በድጋሚ የቀረበበትን ክስ መቃወም ያለበት ሲሆን ተካሳሽ ይህንን ሳያደርግ መቅረቱ ወይም መተው በክሱ መቀጠልን የሚያስከትል ብሎም መስማማትን የሚያመለክት ስለሚሆን የመርሁን ተፈጻሚነት ቀሪ የሚያደርግ ልዩ ሁኔታ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በተመሳሳይ ይህ ሁኔታ እንደ አሜሪካ ባሉ የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓትን የሚከተሉ ሀገራት የፍትሐ ብሔር ሕግጋት ውስጥ የተከሳሹ ዝም ማለት ደንቡ ተፈጻሚ እንዳይሆን የሚያደርግ የጠቅላላ መርሁ ልዩ ሁኔታ ( Exeption to the rule aginest splitting a single cause of action) ተደርጎ እንደሚወሰድ ያስቀምጣሉ።[71]

ሌላው በዚህ መርህ ረገድ እምብዛም ጥብቅ ያልሆነ ሥርዓት ባላቸው ሀገራት የሕግ ማዕቀፎች የክስ ምክንያት መነጣጠልን በተለይም ተቀባይነት ያለውን የከሳሽን ስልታዊ እሳቤን (legitimate strategic considerations) መሰረት ባደረጉ አጋጣሚዎች ሁሉ የሚፈቀድበትን ሁኔታ ያስቀምጣሉ። ይህም ሲባል ከሳሽ በተለይም በአንድ ሙግት ውስጥ ባለ የክርክር ደረጃ ላይ ሁሉንም ክስና የዳኝነት ጥያቄዎቹን አጠቃልሎ የግድ ማቅረብ ሳይጠበቅበት በአንድ የክስ ወይም የዳኝነት ጥያቄ ላይ ባለው ፍላጎት ላይ ብቻ ትኩረት ሰጥቶ ማስወሰን የሚችልበት ሁኔታም አለ። [72] ይህ ልዩ ሁኔታ በተለይም የረዥም ጊዜ የጠነከረ የንግድ ግንኙነት ያላቸው ተካራካሪዎች ባሉበት ሙግት ተቀባይነት እንዳለውም ይገለጻል። ስለሆነም በእነዚህ አይነት

[69] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 28 ገጽ 372
[70] Federal rules of civil procedure, Cornell University Law school Legal Information Institute (LII), 2015 edition, 2014. P.
[71] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 ገጽ 265
[72] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6 ገጽ 689

ጉዳዮች ውስጥ የክስ ምክንያት ያለመነጣጠል መርህን ተፈጻሚ ማድረግ ወደፊት ተከራካሪዎች ሊኖራቸው የሚችላቸውን ግንኙነቶች የሚጎዳ ብሎም ከፍ ወደአለ የሕግ ሙግት (Legal battle field) የሚመራ ይሆናል የሚል ምክንያትም የእስራኤል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ *Stefania Hotel Ltd v. Miller Estate* ጉዳይ ላይ በሰጠው የውሰኔ ትንታኔ ውስጥ ተቀምጧል።[73]

በዚህ ረገድ በህንድ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ደግሞ የፍርድ ቤት ፈቃድ (Judicial permission) አንድ የክስ ምክንያትን መነጣጠልን ለሚከለክልው ጠቅላላ መርህ ልዩ ሁኔታ ተደርጎ በትእዛዝ II መርህ 3 ስር ተመልክቷል።[74] በተለይም ሕጉ ...if he omits, except with the leave of the court, to sue for all such reliefs… የሚለው አገላለጽ በልዩ ሁኔታ በፍርድ ቤት ፈቃድ ከሳሽ ክሱን ወይም የዳኝነት ጥያቄውን በሙሉ ወይም በከፊል አቆይቶ ሌላ ጊዜ ሊያነሳ እንደሚችል የሚያሳይ ሲሆን እንዲህም ባለ ጊዜ ጠቅላላው የክልከላ ደንብ እንደማይፈጸም ያሳያል።[75] ወደ ኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ስንመለስ በአንቀጽ 216(4) ከሳሽ ያቀረበው ክስ በአንድ ጉዳይ ላይ የተመሰረተ ሆኖ የሚጠይቀው ዳኝነት ግን ከአንድ በላይ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ሳይፈቅድለት ሊጠይቅ ይገባው ከነበረው ዳኝነት ውስጥ በከፊል ራሱ ቀንሶ ያስቀረውን መብት እንደገና ሊከስበት አይችልም በማለት ከህንዱ መርህ በተመሳሳይ ሲያስቀምጥ በርግጥም በፍርድ ቤቱ እውቅናና እና ፈቃድ በከፊል ቀንሶ ባስቀረው የዳኝነት ጥያቄ (መብት) ላይ ድጋሚ ክስ ለማቅረብ እንደማይከለከል ነው።[76]

ይኸውም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት በሚሰጣቸው አስገዳጂነት ያላቸው ውሳኔዎች ላይ የተመለከተ ሲሆን ለአብነትም በአመልካች እነ ይልማ አንበሴ እና ተጠሪዎች እነ እመቤት መንገሻ መካካል የነበረን ከሆቴል ክራይ ጋር ተያያዘ ክርክር ማየት ይቻላል። በዚህም ሰፊ ክርክር ከቀረቡት ቅሬታች መካከል በአንደኛው አመልካች ያቀረበው ተጠሪዎች ቀደም ሲል ባቀረቡት የሆቴል ይለቀቅልን ክስ ላይ ሆቴሉ እስኪለቀቅላቸው ድረስ ክራይ መጠየቅ ሲችሉ ነጥለው ባቀረቡት ክስ ላይ ድጋሚ ክስ ለማቅረብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.216 ይከለክላቸዋል የሚል ሲሆን ችሎቱም ምላሽ ሊሰጥባቸው ይገባል በሚል በጭብጥነት ከያዛቸው 6 ነጥቦች መካከል በቁ.2 ስር የተመለከተውና በርግጥም ክሱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.216/4/መሰረት

---

[73] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 28 ገጽ 374 እና የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6 ገጽ 690-91

[74] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ገጽ 440 ይኸውም A person entitled to more than one relief in respect of the same cause of action may sue for all or any of such reliefs; If he omits, except with the leave of the court, to sue for all such reliefs, he shall not after wards sue for all such reliefs, he shall not afterwards sue for any relief so omitted. በሚል ያሰቀምጠዋል።

[75] ዝኒ ከማሁ

[76] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 216(4)

በድጋሚ ሊቀርብ ይችላል ወይስ አይችልም?የሚለው ይገኝበታል። በዚህም ውሳኔ ውስጥ ፍርድ ቤቱም ያለአግባብ የሆቴል ድርጂቱን ስለያዙ ክሱ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ ያለውን ኪሳራ ሊወስን ከክሱ በኋላ ላለው ጊዜ በሕጉ መሰረት ወደፊት ክስ የማቅረብ መብታቸውን ጠብቆላቸዋል። ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.216(3) መሰረት ከሳሽ ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ አጠቃልሎ ማቅረብ እንዳለበት እና ክስ ለማቅረብ ሲችል ሆነ ብሎ ቀንሶ ባስቀረው ንብረት ድጋሚ ክስ ለማቅረብ የማይችል መሆኑን አጠቃላይ መርህ ደንግጓል። ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱን በማስፈቀድ ሊጠይቅ ይገባው ከነበረው ውስጥ ማስቀረት እንደሚችል እና በከፊል በቀረው በዚሁ መብት ላይም ድጋሚ ክስ ማቅረብ እንደማይከለክል ደግሞ ንዑስ አንቀጽ (4) ልዩ ሁኔታን አስቀምጧል። በተያዘውም ጉዳይ ተጠሪዎች ከክሱ በኋላ ላለው ጊዜ የመክሰስ መብታቸውን የጠበቀላቸው በመሆኑ ቀደም ሲል ሊከሱ ሲገባ ቀንሰው ስላስቀሩ በድጋሚ ሊከሱ አይገባም የሚለው የአንደኛው አመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም " ሲል የፍርድ ቤት ፈቃድ የክስ ምክንያት መከፍፈል የሚከለክለው መርህ ልዩ ሁኔታ ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑን አረጋግጧል። [77]

ሌላው ከዚህ መርህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው መሰረታዊ ነጥብ ደግሞ በተለይም የማይንቀሳቀስ ንብረትን ከማስመለስ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ክሶች የሚመሩበትን ሥርዓት የሚደነግገው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 218 ጋር ይያያዛል። በመሰረቱ ከአንድ የክስ ምክንያት የመነጩ ክሶች እና የዳኝነት ጥያቄዎች በአንድ ላይ ተጠቃለው መቅረብ እንዳለባቸው **በአስገዳጂ ሁኔታ** መርህ አድርጎ በአንቀጽ 216 ያስቀመጠ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር ተያይዞ ወደ ተመለከተው ስንመጣ ራሱን የቻለ አመራር ተመልክቶ እናገኛለን። የፍ/ሥ/ሥ/ሕ /ቁ 218 የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ማስመለስን አስመልክቶ የሚቀርብ ክስ የሚመራበት ሥርዓትን የያዘ ሲሆን በተለይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ማስመለስን አስመልክቶ የሚቀርብ ክስ ብቻውን ተነጥሎ ሊቀርብ እንደሚገባ ሕግ አውጭው አስቀምጧል። በአንቀጽ 218 የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ ተጣምረው ስለሚቀርቡ ክሶች በሚል ባስቀመጠው ርእስ ከስር በ ሀ፣ ለ እና ሐ በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር የማንቀሳቀስ ንብረትን የማስመለስ ጉዳይ የሚመለከት ክስን ከሌሎች ጋር አጣምሮ (Joinder) ለማቅረብ አይቻልም በሚል ያስቀመጠ

[77] የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 43992 በአመልካቾች እነ ይልማ አንበሴ እና በተጠሪ እነ እመቤት መንገሻ መካከል በነበረው ክርክር መጋቢት 6 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ ይመልከቱ።

ሲሆን በርግጥም በዚህ ረገድ ጠቅላላ መርሁ መጣመርን በአስገዳጂነት የሚከለክል መሆኑን ያሳያል።[78]

ይሁን እንጂ በድንጋጌው ቅርጽ ውስጥ (...ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ማለትም (ሀ፣ለ እና ሐ ካልሆነ በቀር...) ይልና... (... አጣምሮ ማቅረብ አይችልም።) የሚለውን አገላለጽ በተመለከተ የተለያዩ አረዳዶች ያሉ ሲሆን በተለይም እነዚህ ሁኔታዎችን በተመለከተ ከሳሽን አጣምሮ እንዲያቀርብ **የሚያስገድድ** ነው? አጣምሮ ካላቀረበ አንድ የክስ ምክንያትን ነጣጥሏል የሚያሰኝ ሊሆን ይችላል? የሚለው ነጥብ ላይ ሁለት አቋሞች ለማየት ይቻላል።

ቀዳሚው አቋም ማንኛውም የክስ አቤቱታ (ለሚንቀሳቀስም ሆነ ለማይንቀሳቀስ ንብረት ጉዳይ) አቀራረብ ምን መምሰል እንዳለበት የሚያመለክተው ጠቅላላው መርህ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 216 ተደንግጓል በሚል ይነሳል።[79] በዚህም ሥርዓት ውስጥ ከሳሽ ከአንድ የክስ ምክንያት የመነጨ ማናቸውንም ክስ እና የዳኝነት ጥያቄዎችን ሁሉ ሳይነጣጥል በጥንቃቄ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ይህንንም ባላደረገ ጊዜ ሳያካትት በቀረው ላይ ድጋሚ ምንም አይነት ጥያቄ ማቅረብ ይከለከላል። ይሕንን መሰረት በማድረግ ወደ ክስ አቀራረብ ሲመጣ ከመነሻው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 218 የሚናገረው ክሶችን ስለማጣመር ሆኖ የማይንቀሳቀስ ንብረት የማስመለስ ክስን ከሌሎች ክሶች ጋር አንድ ላይ አጣምሮ ማቅረብ የተከለከለ መሆኑን ነው። በስሩ በ ሀ፣ለ እና ሐ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከማይንቀሳቀስ ንብረት ማስመለስ ጋር በተጨማሪነት በሚመጡበት ጊዜ ደግሞ አንቀጽ 218 በአንቀጽ 216 ስር ከተደነገገው ጠቅላላ መርህ አንጻር መታየት እና መመዘን ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ከሳሽ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ከማስመለስ ክሱ በተጨማሪ ከዛው ጋር ተያያዥ የሆኑ ክሶች ካሉት አጣምሮ እንዲያቀርብ መገደድ ያለበት ሲሆን ነጣጥሎ ካቀረበ ግን አንድ የክስ ምክንያትን መነጣጠል ሆኖ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል እንጂ ለከሳሽ ምርጫ የሚሰጥ አይደለም ።[80] ይህንኑም ለማጠናከር ሌላው የሚነሳው ነጥብ ደግሞ የህግ አውጭውን ፍላጎት መዕከል ያደረገ ሆኖ በርግጥም የሥነ ሥርዓቱ በ ሀ ፣

---

[78] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 218 ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ካልሆነ በቀር የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን የማስመለስ ጉዳይ የሚመለከቱ ክሶችን አጣምሮ ማቅረብ አይቻልም።

(ሀ) የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚገኘውን ጥቅም ወይም ከዚሁ ላይ የሚሰበሰበውን ውዝፍ ኪራይ ወይም ከንብረቱ ላይ የሚገኘውን ገቢ በከፊል ለመጠየቅ ሲሆን

(ለ) የማይንቀሳቀሰውን ንብረት በሚመለከት በማናቸውም ምክንያት የተደረገውን ውል በመተላላፍ የሚደርሰውን የጉዳት ካሳ ወይም ማናቸውንም ኪሳራ ለመጠየቅ ሲሆን ወይም ውሉ ይህንኑ ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል የሚመለከት ሲሆን

(ሐ) የተጠየቀው ዳኝነት የተመለከተው ባንድ አይነት ምክንያት ላይ ሲሆን።

[79] የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኞች አቶ ጸጋዬ ወርቃየሁ፣በሪሁን አዱኛ ምህረቴ፣ሀብታሙ እርቅይሁን ፣ አብዬ ካሳሁን በቀን 9/08/2008 ዓ.ም በተደረገ የትእረት ቡድን ውይይት።

[80] ዝኒ ከማሁ

ለ እና ሐ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ክስ አቀራረብን ሲያስቀምጥ ከሳሹ ከፈለገ አጣምሮ ካልሆነ ደግሞ ነጣጥሎ እንዲያቀርብ ቢፈልግ ኖሮ አንቀጽ 218 (ሀ ፣ለ እና ሐ) የአንቀጽ 216 ልዩ ሁኔታ ይሆኑ ስለነበር በግልጽ ፈቃጂ መሆኑን ያመለክት ነበር በማለት ያክላሉ፡፡ ይኸውም አተረጓጎም የበለጠ ለክርክሮች መቋጫ ለማበጀት እና የፍርድ ቤቶችን ውጤታማነት በተሻለ ደረጃ ለማረጋገጥ ያስችላል በሚል ነው፡፡ [81]

ሁለተኛው አረዳድ ደግሞ ከዚህ ሀሳብ የተለየ እይታ ያለው ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህንን አቋም የሚያንጸባርቁ ባለሙያዎች የሚያነሱት የመጀመሪያው ነጥብ የማይንቀሳቀስ ንብረት መብት ግዙፍ ከመሆኑ ጋር ተያዘዞ ከሣው የሚነሡ ክርክሮች በአብዛኛው በተግባርም ቀላል ባህሪ አይኖራቸውም የሚል ነው፡፡[82] ስለሆነም ከዚህ ልዩ ባህሪ የተነሳ በተለይም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን የማስመለስ ጉዳይን የተመለከቱ ክሶች አቀራረብን በተመለከተ ከሌሎች ክሶች ጋር አጣምሮ ማቅረብ እንደማይቻል በአንቀጽ 218 ተመልክቷል፡፡ ይኸውም የአቀራረብ ሥርዓት በአንቀጽ 216 የተቀመጠው ጠቅላላ መርህ ልዩ ሁኔታ ተደርጎ መያዝ አለበት፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አንቀጽ 218 (በ ሀ፣ ለ እና ሐ በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር…) (… አጣምሮ ማቅረብ አይችልም፡፡) በሚል የተጠቀመበትም አግባብ መታየት ያለበት ከአንቀጽ 216 ጋር ሳይሆን ከራሱ ከአንቀጽ 218 የክልከላ መርህ አንጻር ሊሆን ይገባል፡፡ በ ሀ፣ለ እና ሐ ሁኔታዎችም ሲታዩ በባህርያቸው ንብረት ከማስመለሱ ጉዳይ ጋር ካላቸው ቅርበት አንጻር ቢጣመሩ በክርክሩ ላይ አስቸጋሪ ሁኔታን የመፍጠር እድላቸው አናሳ በመሆኑ የክስ ባለቤቱ አጣምሮ ለማቅረብ ወይም ለመነጣጠል ይችላል የሚል ምርጫ የሚሰጥ (permissive) ተደርገው ሊወሰዱ ይገባል፡፡ በሌላ አገላለጽ የአንቀጽ 216 ጠቅላላ መርህ ሲሆን የማይንቀሳቀስ ንብረትን ማስመለስን ስለተመለከተ ክስ አቀራረብ የሚደነግገው አንቀጽ 218 ልዩ ሁኔታ ሆኖ በስሩ የተመለከቱት ሁኔታዎች ደግሞ የዚሁ ሌላ ልዩ ሁኔታዎች (Exception to the Exception) ሆነው መተርጎም እና በዚህ አግባብ የክስ ባለቤቱ ንብረቱን ከማስመለስ ክሱ ጋር የሚኖረውን ተጨማሪ ክስ ነጥሎ በማቅረቡ አንድ የክስ ምክንያትን ነጣጥሏል ሊያሰኝ የሚችል ተደርጎ መተርጎም የለበትም የሚል ነው፡፡[83]

---

[81] ዝኒ ከማሁ

[82] ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኞች አቶ አሊ መሀመድ አሊ ፣ተፈሪ ገብሩ ጋር መጋቢት 2 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገ ቃለ-መጠይቅ፣ ከአቶ አስቻለው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት መምህር፣ የሕግ አማካሪ ና ጠበቃ እንዲሁም ጸሀፊ ጋር ተካቲት 29 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገ ቃለ-መጠይቅ፣ በተጨማሪም የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኛ አቶ በሪሁን አዱኛ ታምራት ጋር ሚያዚያ ቀን 2008 ዓ.ም በተደረገ የትኩረት በድን ውይይት፡፡

[83] ዝኒ ከማሁ

## 2. አንድ የክስ ምክንያትን መነጣጠል የሚከለክለው ጽንሰ ሐሳብ አተገባበር

በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት የፍርድ ሰጭ አካላትን ዳኝነት የሚሻው የክስ ምክንያት ቀድሞውኑም በሕግ ጥበቃ የተደረገለት መሆን የሚገባው ሲሆን ይኸውም ጥቅም ወይም መብት ከሕግ ወይም ከውል ይመነጫል።[84] ከዚሁ ጋር ተያይዞ የፍትሐ ብሔር ሕግን መሰረት አድርገው ውሳኔ በሚሰጡ ፍርድ ቤቶች የክስ ምክንያት አለመኖር አንደ አንድ የክስ ማመልከቻ ውድቅ ማድረጊያ መሰረት እንደሆነ በሥነ ሥርዓት ሕጉ ላይ ተመልክቷል።[85] ይኸም ማለት የፍርድ ቤቱ ሪጂስትራር አንድ አቤቱታ ሲቀርብለት የአቤቱታውን ቴክኒካል ብቃት ከመፈተሽ በዘለለ የክስ ምክንያት መኖርን የሚያረጋግጥ ባለመሆኑ አቤቱታው ፋይል ተከፍቶለት የሚቀርብላቸው ዳኞች ተቀዳሚ ተግባር የሚሆነው የቀረበው ጉዳይ የክስ ምክንያት አለው ወይስ የለውም የሚለውን (legal sufficiency) መመርምር ሆኖ ከሌለው ወድያውኑ ክሱን ውድቅ ያደርጉታል። [86] ይኸውም የክስ ምክንያትን መወሰን በራሱ የዳኞች የትኩረት መነሻ ቁልፍ ሀላፊነትም መሆኑን ያስገነዝባል። በእርግጥ ፍርድን ከመስጠት ጋር ተያይዞ ዳኝነት ለማግኘት የሚቻለው የግድ ከመደበኛው ፍርድ ቤት ብቻ ሳይሆን መብቱን ለማስተካከል በሕግ ስልጣን የተሰጣቸው አካላትንም (other forums) የሚመለከት በመሆኑ የሀይማኖት ፍርድ ቤቶች፣ የሽምግልና መደረኮች፣ የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች የመሳሰሉትን ሁሉ እንደሚጨምር ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል።[87]

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ጥናት የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አንድ የክስ ምክንያት ያለመነጣጠል ጽንሰ ሐሳብን በተለይም የማይንቀሳቀስ ንብረት የማስመለስ ክስ አቀራረብ ከሚመራበት ሥርዓት ጋር አያይዞ የሰጣቸውን አንዳንድ ውሳኔዎች ይዘት እንመለከታለን። ክፍ ብሎ በተመለከተው ክፍል በተለይም ከማይንቀሳቀስ ንብረት ማስመለስ ጋር ተያይዘው ስለሚነሱ ሌሎች ጥቂዎች ክስ አቀራረብን በተመለከተ የተለያዩ አቋምች እንዳሉ ለመብራራት ተሞክሯል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ

[84]አንቀጽ 1731 የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የፍትሐብሔር ሕግ፣ አዋጂ ቁጥር--1960 (ከዚህ በኋላ የፍትሐብሔር ሕግ ተብሎ የሚጠራው)

[85] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ *230 እና 231*

[86] ዝኒ ከማሁ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ህግ አንቀጽ 229፣ 230 እና 231 ይህውም የክስ ምክንያት በርግጥም ወደፊት የፍትሐ ብሔር ክርክር መኖር አለመኖርን በመወሰን ረገድ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ያሳያል።

[87] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት ፣1987፣የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጂ ቁጥር 1/1987፣ 1ኛ አመት ቁጥር 1፣ አዲስ አበባ፣ አንቀጽ 37(1) ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው። በማለት ደንግጓል።

ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በርካታ ውሳኔዎች የሚሰጡ ሲሆን ከነኝህም መካከል በተለይም ያለአግባብ የተያዘ የይዞታ መሬት ይመለስልኝ እና የአላባ ጥቅም ጥያቄ እንዲሁም ጋብቻ በፍች ከፈረሰ በኋላ ስለሚቀርብ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ (በተለይም የጋራ የይዞታ መሬት ክፍፍል) የሚመለከቱ ክርክሮች ላይ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ አንቀጽ 216 እና 218(ሀ)ን በማጣመር የተሰጡ ውሳኔዎችን እንመለከታለን፡፡

ለአብነት የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሠ/መ/ቁ 11019 በአመልካች ህጻን ምንአልኩት ሞላ (ሞግዚት ተጓድ ዋጋው) እና በተጠሪ እነ ስለሽ ውበቱ መካከል በነበረው ክርክር የሰጠውን ውሳኔ ስንመለከት ለክርክሩ መነሻ ሆነው የአሁን አመልካች (የስር ከሳሽ) ያለአግባብ የተያዘብኝ የይዞታ መሬት እንዲመለስልኝ የሚል ክስ በአንደኛ ተጠሪ ላይ በወረዳ ፍርድ ቤት ክስ መስርቶ ህዳር 16 ቀን 2000 ዓ.ም ተጠሪ መሬቱን እንዲያስረክብ ተወስኗል፡፡ በዚህም ውሳኔ መሰረት አመልካች መሬቱን ከተረከበ በኋላ ከአመልካች ጋር በክርክር በነበሩበት ጊዜ 1999 እና 2000 ዓ.ም በመሬቱ ላይ ያገኘውን አላባ ይክፈለኝ የሚል ክስ በድጋሚ አቀረበ፡፡ ክርክሩም በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች በተለያየ ሁኔታ ተጠሪዎች የአላባ ግምት እንዲከፍሉ ይወሰናል ፡፡ ተጠሪዎችም በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብለው እንዲያውም አመልካች ባልታወቀ ሀብት ላይ ክስ የመሰረተ በመሆኑ የአላባ ጥያቄን የማቅረብ መብት የለውም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻሩ ምክንያት አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠውን ውሳኔ ስንመለከት የክርክር ሂደትን ውጤታማነት እና ስልጠት እንዲኖረው ለመድረግ እንዲቻል ተከራካሪዎች ክሳቸው ነገሩ ወይም ከነገሩ ጋር በተያያዘ ሌላ አከራካሪ ሁኔታ በማይፈጥር መልኩ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ከመሬት ባለይዞታነት ጋር የተያየዘ የአላባ ጥያቄ ካለ የይዞታው ማስመለስ ክስ በቀረበ ጊዜ ካልቀረበ ሆነ ተብሎ ተቀንሶ እንደቀረ የሚታሰብ በመሆኑ ድጋሚ ክስ ሊቀርብበት አይችልም፡፡ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(1) (3) (4) እና 218 (ሀ) መሰረት ባለጉዳዩች በአንድ ጊዜ ተጠቃለው መቅረብ ያለባቸውን ጥያቄዎች በተለያዩ ጊዜያት እንደፈለጉ በማቅረብ የሥነ ሥርዓቱን ምሰሶ ለማፍረስ አይችሉም በማለት አትቷል፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካች ከ 1ኛ ተጠሪ ጋር በነበረው የይዞታ ይገባኛል ክርክር ጊዜ የአላባ ጥያቄውን አብራ

ዳኝነት ልትጠይቅ የምትችልበት እድል አልፋ ቀንሳ ካስቀረች በኋላ ድጋሚ ያነሳቸው የአላባ ጥያቄ ሥነ ሥርዓታዊ ተቀባይነት የለውም በሚል ውድቅ አድርጎታል።[88]

በውሳኔ ውሰጥ እንደተመለከተው ከሳሽ በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበው ክስ ያለአግባብ የተወሰደውን ይዞታ ማስመለስን በመሆኑ መሬቱ በተከሳሽ ይዞታ ስር በቆየበት ጊዜ የነበረ የአላባ ጥቅምን አስመልክቶ የሚቀርብ ክስ ከዚያው የይዞታ የክስ ምክንያት የሚመነጭ በመሆኑ ከሳሽ የይዞታ ማስመለስ እና የአላባ ገቢ ጥያቄዎቹን በአንድ ክስ ውስጥ አጠቃልሎ እንዲያቀርብ መገደድ አለበት የሚል አቋም ይዘት ያለው ሲሆን ሴድለርም ሀሳቡ አከራካሪ እንደሆነ በማመልከት ይህ ሀሳን የተሻለ እንደሆነ ያስቀምጣሉ ። [89] ከሳሽ ነጣጥሎ እንዲያቀርብ መፍቀድ ፍርድ ቤቱንም ሆነ ተከራካሪዎችን ለከፍተኛ ወጭ እና ጊዜ መባከን የሚዳርጉ ብሎም ለክርክሮች መቋጫ ማበጀትን አላማ ያደረገውን የሥነ ሥርዓት ሕጉ መሰረት መጣስን ያስከትላል ከሚል እይታ ይመነጫል።

ይሁን እንጂ ከፍ ሲል በክፍል አንድ ላይ ለማብራራት እንደተሞከረው በመጀመሪያ ደረጃ ከመነሻውም የማይንቀሳቀስ ንብረትን ማስመለስ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ በባህሪው ውስብስብ በመሆኑ በመርህ ደረጃ ተነጥሎ እንዲቀርብ በአንቀጽ 218 በአስገዳጂ መርህነት የመደንገጉ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል። ከዚህ አንጻር በ ሀ ፣ለ እና ሐ ስር የተመለከቱትና የመርሁ ልዩ ሁኔታዎች ሲታዩ ከሳሽ የይዞታ ማስመለስ እና የአላባ ክሶቹን የግድ አጣምሮ እንዲያቀርብ የሚያስገድድ ሳይሆን ይህንን ለመወሰን ለክሱ ባለቤት ምርጫ የሚሰጥ ፈቃጅ ሆኖ መወሰድ አለበት የሚለውን አስተያየት ጸሐፊውም ይጋራል።

ከዚህም በተጨማሪ የሥነ ሥርዓት ሕግ በርግጥም ፍትሐ ብሔራዊ ሙግቶችን ለመምራት እጅግ ወሳኝ ቢሆንም ይህ ሕግ ምንጊዜም ቢሆን በመሰረታዊ የሕግ ማዕቀፎች እውቅናና ጥበቃ የተሰጣቸው መብቶችን ለማስፈጸም የወጣ በመሆኑ ከመሰረታዊ ሕገጋት የላቀ ዋጋ ሊሰጠው አይገባም። በመሆኑም የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን የተመለከቱ ጥያቄዎች ሲነሱ በተለይም ክርክሩ የመነጨበትን መብት፣ መብቱን ያቋቋመውን ሕግ መንፈስ አላማ እና ግብ ከክርክሩን ባህሪ ጋር በማጣመር መመርምርም ብቻ ሳይሆን ለሚጠየቁት ዳኝነቶች ውሳኔ የሚሰጡ አካላትን ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ለዚህም ነው የሥነ ሥርዓት

[88] የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 11019 በአመልካች ህጻን ምን አልኩት ሞላ እና በተጠሪ ስለሽ ውበቱ መካካል በነበረ ክርክር ህዳር 11 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ በመ/ቁ/ 26941፣ 16810፣ 23693፣ 29811 በተመሳሳይ ምክንያቶች የተሰጡ ውሳኔዎች መሆናቸውን መመልከት ይቻላል።

[89] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10 ገጽ 544

ሕጉ ወጭ ቆጣቢ እና  ቀልጣፍ ብቻ ሳይሆን ፍትሐዊነትን የማረጋገጥ ቀልፍ አላማ እንዳለው በስፋት የሚገጸው፡፡

በዚህ ረገድ በመሬት ይዞታ ማስመለስ እና የአላባ ጥቅም ክሶች አቀራረብን በተመለከተ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚሁ ክልል በተነሳና በመ/ቁ 106932 በአመልካች 1ኛ አቶ አብጤ ወርቁ 2ኛ አቶ ሞላ ወርቁ እና በተጠሪ ወ/ሮ አንጓች ወርቁ መካከል በነበረው ክርክር የሰጠውን የህግ ትርጉም መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ክርክሩ የተነሳው ያላግባብ የተያዘ ነው ከተባለ የእርሻ መሬት የተገኘ የአላባ ጥቅምን ለማስከፈል በተጠሪ ከሳሽነት በአዊ ብሔረሰብ ዞን በዳንግላ ወረዳ ፍ/ቤት የቀረበ የክስ ምክንያት ነው፡፡ በክሱም ውስጥ የአሁን አመልካቾች ለተጠሪ ይገባ የነበረውን የእርሻ ጥማድ መሬት በዕጃቸው ይዘው አንለቅም በማለታቸው ተጠሪ ክስ መስርተው በማስፈረድ ይዞታውን መረከባቸው ተመልክቷል፡፡ይህንንም መሰረት በማድረግ ተጠሪ መሬቱ በአመልካቾች እጂ በነበረበት ከ2003 እስከ 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ እያረሱ ያገኙትን የአላባ ጥቅም ግምት የእንዳንዳቸውን  የግዴታ መጠን ለያይተው እንዲከፍሏቸው ዳኝነት ይጠይቃሉ፡፡ አመልካቾችም በሰጡት መልስ ተጠሪ የመሬት ይዞታውን አቅርበውት በነበረው ክስ ውስጥ ይህንን የአላባ ጥያቄ አጠቃለው ማቅረብ እየተገባቸው ይዞታውን አስወስነው ከተረከቡ በኋላ ያቀረቡት የአላባ ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 36(4) ፣216(3) እና (4) እንዲሁም 218(ሀ) ድንጋጌዎች ካስቀመጡት የክስ አቀራረብ ሥርዓት ውጭ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስተው ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ይጠይቃሉ፡፡ በዚህ ክርክር ውስጥ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ድረስ አመልካቾች በተለያየ መጠን የአላባ ግምቱን እንዲከፍሉ ይወሰንባቸዋል፡፡ ታዲያ በዚህ ክርክር የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካቾች ባቀረቡትን ቅሬታ መሰረት በርግጥም በዋናነት ተጠሪ ከአንድ የክስ ምክንያት የመነጨ ዳኝነት ነጣጥለዋል የሚለውን ጭብጥ ሲመረምር ሥነ ሥርዓቱን ብቻ ሳይሆን ክርክር የተደረገበትን መብት ያቋቋመው መሰረታዊ ሕግ፣ የመብቱን ልዩ ባህሪ፣ የተጠየቀውን ዳኝነት ለመወሰን የሚችለው የዳኝነት አካል (Forum) ጋር በአግባቡ መርምሯል፡፡ በዚህም አግባብ የሰጠውን ውሳኔ የበለጠ ለመረዳት እንዳለ ማስቀመጡ የተሻለ ይሆናል፡፡

ተጠሪዋ በመጀመሪያ ያቀረቡት ክስ አመልካቾች በጥማድ ይዘው ከቆዩ በኋላ አንለቅም ብለዋል የተባለውን የእርሻ ይዞታ መሬት ለማስመለስ ነው፡፡ በገጠር የእርሻ ይዞታ መሬት መብት ውስጥ ላይ የሚነሳው ክርክር ጉዳይ በሚመለከታቸው ተከራካሪዎች በውይይት እና በስምምነት እንዲፈታ ጥረት የሚደረግ ስለመሆኑ እና በስምምነት ሊፈታ ካልቻለ በተከራካሪ ወገኖች በተመረጠ የሽምግልና ወይንም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጂ ቁጥር

456/1997 አንቀጽ 12 ስር ተደንግጎ ይገኛል። በተለይም ከእርሻ መሬት ይዞታ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች በወረዳ ፍርድ ቤት ቀርበው ከመታየታቸው በፊት በስምምነት እና ቀጥሎም በሽምግልና መታየት የሚገባቸው ስለመሆኑ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባወጣው የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጁ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 29 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 35 ተመልክቷል።ከላይ በተጠቀሱት አዋጁ እና ደምብ ድንጋጌዎች መሰረት ለፍርድ ቤቱ ከመቅረቡ በፊት በስምምነት እና በሽምግልና እንዲታይ የሚደረገው ጉዳይ የእርሻ ይዞታ ክርክር እንጂ ከእርሻው የሚገኘውን ጥቅም ወይም አላባ ጭምር አይደለም። ከሳሽ ወገን ለስምምነት እና ቀጥሎም ለሽምግልና የሚያቀርበው ጉዳይ ከእርሻ ይዞታው የሚገኘውን ጥቅም የሚያካትት ካልሆነ ደግሞ ከእርሻው መሬቱ የሚገኘውን ጥቅም አስመልክቶ የሚያቀርበውን ክስ የእርሻ ይዞታውን ለማስለቀቅ ከሚያቀርበው ክስ ጋር አጣምሮ ሊያቀርብ የሚችልበት አግባብ አይኖርም። ከእርሻ መሬት የሚገኘውን ጥቅም አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ጉዳይ አመልካቾቹ ጠቅሰው የሚከራከሩባቸው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 218 (ሀ) እና 216(3) ድንጋጌዎች መተርጎም የሚገባቸው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን አስመልክቶ ከወጡ ሕግጋት ጋር ተገናዝበው ነው። [90] በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል።

በመሆኑም ከፍ ሲል ከቀረቡት ነጥቦች አንጻር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ መልኩ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በርግጥም ቀልጣፍና ወጭ ቆጣቢ የሆነ ሥርዓትን ማዳበር ላይ ያተኮረ መሆኑ አንደኛው የሥነ ሥርዓቱ አላማ በመሆኑ መልካም እንደሆነ መውሰድ ይቻላል። ይሁን እንጂ ሥነ ሥርዓቱም ቢሆን በመሰረታዊ ሕግጋት ጥበቃ የተደረገላቸውን መብቶች በአግባቡ እንዲተገበሩ የተቀረጸ በመሆኑ በተለይም ሥነ ሥርዓታዊ ክርክሮች በሚነሱነት ጊዜ የክርክሩ መነሻ የሆነውን መብት ያቋቋመውን መሰረታዊ ሕግም ብቻ ሳይሆን ሊያሳከው ከፈለገው አላማ እና ዳኝነት ከሚጠየቅበት ፍርድ ሰጭ አካላት ማንነት አንጻር ተጣምሮ በጥልቀት መመርመር ሲኖርበት ይህ መታለፉ የሥነ ሥርአት ሕጉ ቀልጣፍና ወጭ ቀጣቢ እንዲሆን ካለው አላማ ያለፈውን የፍትሐዊነት አስፈላጊነት መልሶ ጥያቄ ያስገባዋል።

በሌላ በኩል በርግጥም በተለይም ከመሬት ይዞታ ማስመለስ እና የአላባ ጥቅም ጥያቄ ክስ የሚቀርብበትም አግባብ ብቻውን ይታይ ቢባል እንኳን የሥነ ሥርዓት ሕግ 218 የማይንቀሳቀስ

[90] የፌ/ስ/ስ/ችሎት በመ/ቁ106932 ጥር 3 ቀን 2008 ዓ.ም በአመልካች 1ኛ.አቶ አብጤ ወርቁ 2ኛ አቶ ሞላ ወርቁ እና በተጠሪ ወ/ሮ አንጓች ወርቁ መካከል በነበረው ክርክር የሰጠው ውሳኔ እና በመዝገብ ቁጥር 108060 በ18/07/2007 ዓ.ም የሰጠው አስገዳጁ የህግ ትርጉም ይመልከቱ።

ንብረት የማስመለስ ክርክር ካለው ውስብስብነት አኳያ ከሌሎች ክሶች ጋር ተጣምሮ እንዲቀርብ ፍላጎቱ ከልካይ መሆኑን ካስቀመጠ በኋላ የተቀመጡት ሁኔታዎች ቢቻል ተለያይተው ካልሆነ ደግሞ ካላቸው ቅርበት አንጻር ከሳሽ ከፈለገ ተጣምሮ እንዲያቀርብ ልዩ ፈቃድ እንደተሰጠው መወሰድ ያለበት ነው። ሆኖም በዚህ ረገድ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የይዞታ መሬት ማስመለስ እና የአላባ ጥያቄ ክሶች የግድ ተጣምረው መቅረብ ያለባቸው ናቸው ካልሆነ ግን የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቀጥር 216 የተመለከተው የክስ ምክንያት መነጣጠል ክልከላን ይተላለፋል በሚል ያቀረበው እይታ ሕጉ ከፈለገው ልዩ አቀራረብ አንጻር የታየ አይመስልም።

ሌላው ከዚህ ጽንሰ ሐሳብ ጋር በተያያዘ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 216 እና 218 ከፍች እና የፍች ውጤት ከሆነው ከጋራ ንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ ያላቸውን አፈጻጸም ማየት አስፈላጊ በመሆኑ በአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዘገብ ቁጥር 24728 በሰኔ 03/ 2005 ዓ. ም በአመልካች አቶ ታዴ ዘሪሁን እና ተጠሪ ወ/ሮ ሽጉልትሽ መልካሙ መካካል በነበረው ክርክር ላይ የሰጠውን ውሳኔ ለአብነት እንመለከታለን ።

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ተጠሪ (የስር ከሳሽ) በ19/06/2004 ዓ.ም በተጻፈ የክስ ማመልከቻ አመልካች (የስር ተከሳሽ) ላይ የመሰረቱት ክስ ሲሆን ይዘቱም በሁለቱ መካካል ቀደም ሲል ተፈጽሞ የነበረው ጋብቻ ፈርሶ የንብረት ክፍፍል ማድረጋቸውን በማረጋገጥ ይህ ክፍፍል ሲደረግ ያልጠየቀችውን 4 ጥማድ የጋራ የገጠር ይዞታ መሬት አመልካች ሊያካልፍለኝ ይገባል በሚል ለማቻከል ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረበችው ክስ መነሻነት ነው። አመልካች በበኩሉ ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ተጠሪ ፍች በተፈጸመ ጊዜ የንብረት ዝርዝር አቅርባ ውድቅ የተደረገባት በመሆኑ አዲስ ክስ ልታቀርብ አትችልም በተጨማሪም መሬቱን በ1989 ዓ.ም በግሌ የተመዘገብኩበት በመሆኑ ላካፍል አይገባም በማለት ተከራክሯል። ፍርድ ቤቱም ጉዳዮን ከመረመረ በኋላ መሬቱ በግራ ቀኙ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የወሰነ ሲሆን የአመልካችን ይግባኝ የመረመረውም የምስራቅ ጎጃም ዞን ክፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳውን ውሳኔ አጽንቶታል። በመቀጠልም አመልካች እነኝህን ውሳኔዎች በመቃወም እና በስር ፍርድ ቤቶች ያነሳቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በማንሳት የሰበር አቤቱታውን ለአማራ ክልል ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል። ተጠሪም በበኩሏ የስር ፍርድ ቤቶች በየደረጃው የሰጡትን ውሳኔ እንዲጸና ተከራክራለች።

እነዚህን ፍሬ ነገሮች መሰረት በማድረግ የሰበር ችሎቱ ቀደም ሲል በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ ፈርሶ የንብረት ክርክር ሲደረግ ዳኝነት ሳይጠየቅበት ተነጥሎ የቀረውን የገጠር ይዞታ መሬት አስመልክቶ ተጠሪ አዲስ ክስ የማቅረብ መብት አላት ወይስ የላትም? የሚለውን ጭብጥ መርምሯል። ችሎቱ በምርመራው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራት ጋብቻ እንዲፈርስ እና የጋራ ንብረት እንዲያካፍላት ክስ መስርታ ፍርድ ቤቱም ጋብቻውን አፍርሶ የጋራ ንብረታቸውን እንዲካፈሉ ውሳኔ መስጠቱን ከስር ፍርድ ቤቱ የመዝገብ ግልባጭ የተገነዘበ መሆኑን አስቀምጧል። ከዚህም በመነሳት ችሎቱ ለያዘው ጭብጥ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ አንቀጽ 216 (2) እና (3) ን መሰረት በማድረግ ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ሁሉ አጠቃሎ ማቅረብ እንዳለበት እና ጠቅልሎ ሊከስ ሲችል ሆነ ብሎ ቀንሶ ባስቀረው ሀብት ላይ ድጋሜ ሌላ ክስ ማቅረብ እንደማይችል ያስረዳል። ከዚህ በመነሳት ችሎቱ ተጠሪ ቀደም ሲል የጋራ ንብረት ያካፍልኝ የሚል ክስ በአመልካች ላይ መስርታ የተወሰነላት መሆኑ ተረጋግጧል። በመሆኑም አሁን ክስ የቀረበበት መሬት የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው ከተባለ የፍች ጉዳይ ሲቀርብ ከሌላው ንብረት ጋር ዳኝነት ልትጠይቅ ይገባ የነበረ ቢሆንም አሁን ክስ የቀረበበትን መሬት በተመለከተ ዳኝነት አለመጠየቋ ሲታይ ተጠሪ ሆነ ብላ ነጥላ ያስቀረችው መሆኑን ያመለክታል። ስለሆነም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/አንቀጽ 216 (3) መሰረት ከሳሽ ሆነ ብሎ ባስቀረው ሀብት ላይ ድጋሚ ክስ ሊመሰርት እንደማይችል በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪ አመልካች መሬት እንዲያካፍላት ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት ክሱን ከመጀመሪያው በዚህ አግባብ ውድቅ ማድረግ ሲገባው ወደ ፍሬ ነገር ገብቶ ውሳኔ መስጠቱ እንዲሁም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ወስኗል። [91]

ከፍ ብሎ የገጠር ይዞታ መሬት እና የአላባ ጥያቄ ክስ ላይ እንደተመለከተው ሁሉ ሰበር ችሎቱ ሲወስን የሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 216 የተመለከተው ጠቅላላ መርህ በ አንቀጽ 218 ሀ፣ለ እና ሐ ለተመለከቱት ሁኔታዎችም አስገዳጂ ተፈጻሚነት እንዳለው በመውሰድ ነው። ከዚህም በመነሳት ተጠሪ የጋራ የይዞታ መሬት ለመካፈል ያቀረበችው ክስ ቀድሞውኑ ልክ እንደሌሎች

[91] የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዘገብ ቁጥር 24728 በሰኔ 03 ቀን 2005 ዓ.ም በአመልካች አቶ ታዴ ዘሪሁን እና ተጠሪ ወ/ሮ ሽጉልትሽ መልካሙ መካከል በነበረው ክርክር ላይ የሰጠውን ውሳኔ። ይዘቱ በተወሰነ መልኩ የተለየ ቢሆንም ተመሳሳይ አቋም የተንጸባረቀበት ችሎቱ በሰ/አቤ/መ/ ቁጥር 03-3794 ሚያዚያ 16 ቀን 2007 ዓ.ም በአመልካች ሽፈራው በላይ እና በተጠሪ ፋሲካ አበጋዝ መካከል በነበረው ክርክር የተሰጠውን ውሳኔ መመልከት ይቻላል።

የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ሁሉ በቀድሞው ክስ ውስጥ የግድ ማካተት የነበረበት እና ሊነጣጠል እንደማይችል ይተነትናል።

ይሁን እንጂ ከፍ ሲል ለማብራራት እንደተሞከረው የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 218 በተለይም የማይንቀሳቀስ ንብረት የማስመለስ ክስን በተመለከት ብቻውን እንዲቀርብ የሚፈልግ መሆኑን ለሕጉ ቅርበት ካለው የሕንዱ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ አንጻር መፈተሽ ይቻላል። በዚህ አግባብ የሕንዱን ሕግ ስንመለከት የማይንቀሳቀስ ንብረት ማስመለስን አስመልክቶ የሚቀርብ ክስ ከሌሎች ክሶች ጋር ተጣምሮ ሊቀርብ የሚችልበትን ልዩ ሁኔታ ሲደነግግ በኢትዮጵያ የሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 218 ሀ፣ለ እና ሐ ስር የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች አመልክቶ ከእነዚህ ወጭ ባሉ ሁኔታዎች ደግሞ **ፍርድ ቤቱን በማሰፈቀድ** የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ የሚቀርብን ክስ ከሌሎች ክሶች ጋር አጣምሮ ለማቅረብ የሚቻልበትን ሥርዓትን ጨምሯል።[92] በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 218 ልክ እንደ ሕንዱ ሕግ ሁሉ በሌሎች ሁኔታዎች ፍርድ ቤቶች የነገሮችን ሁኔታ እየመዘኑ **መጣመርህን የሚፈቅዱበት እና የሚከለክሉበትን ስልጣን የሚሰጥ ሥርዓትን** አለማስቀመጡ ሲታይ ከመነሻውም ሕጉ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልቶ ጥብቅ የሆነ መጣመርን የመከልከል ፍላጎት እንዳለው ያሳያል። ከዚህም አንጻር ሲታይ በድንጋጌው ስር የተቀመጡት ሀ፣ለ እና ሐ ከሳሽ ከማይንቀሳቀስ ንብረት የማስመለስ ክስ ጋር አብረው ከመጡ ከሳሽ ከፈለገ አጣምሮ ሊያቀርብ የሚችልባቸው ሁኔታዎች እንጂ የሚገደድባቸው ናቸው የሚለው የሰበር ችሎቱ ውሳኔ ከመርሁ ጥብቅነት ጋር የሚጋጪ ነው ለማለት ያስችላል። ከዚህም በተጨማሪ ሥነ ሥርዓቱ የመሰረታዊ ሕጎች መስፈጸሚያ ከመሆኑም ባለፈ ፍትሐዊነትን የማረጋገጥ ቁልፍ አላማን የያዘ በመሆኑ ሥነ ሥርዓታዊ ክርክሮች ሲነሱ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሰረታዊ ሕጉ ጋር አጣምሮ መመርመር ይገባል። በዚህ አግባብ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራት ጋብቻ ሲፈርስ የሚከተለው የጋራ ንብረትን የመክፈል ሥርዓት መሆኑ ይታወቃል። ይሕ ሲባል ግን ሁሉም ንብረቶች ወዲያውኑ የግድ የሚከፈሉ ናቸው

[92] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 ገጽ 445 እና 446 **Rule 4.** Only certain claims to be joined for the Recovery of Immovable property
No cause of action shall, **unless with the leave of the court**, be joined with the suit for the recovery of immovable property, except —
(a) Claims for mesne profits or arrears of rent in respect to the property claimed or any part thereof ;
(b) Claims for damages for breach of any contract under which the property or any part thereof is held; and
(c) Claims in which the relief sought is based on the same cause of action

መደሚል መደምደሚያ የሚያመጣ ባለመሆኑ የሚከፈሉት የጋራ ንብረቶቹ ላይ መብት ያቋቋሙ እና ልዩ ጥበቃ ለማድረግ ታስበው የወጡ መሰረታዊ ሕግጋት አብሮ የመመርመር ልምድ ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ በተነሳው ጉዳይ የተሰጠው ፍርድ የሥነ ሥርዓት ህጉ ጠቅላላ ክልከላ የሆነውን አንድ የክስ ምክንያት የመነጣጠል መርሕን የፍርድ ሂደትን ከማፋጠን እና ወጭን ከመቀነስ አንጻር ብቻ መወሰኑ በዚህ አግባብ ተጠሪ ትልቅ ሕገ መንግስታዊ ዋስትና የተሰጠው ከይዞታ ያለመፈናቀል መብት እና በልዩ ሕግ ጥበቃ የሚደረግለትን የገጠር ይዞታ መሬት ድርሻዋን እንድታጣ ያደረገ በመሆኑ ፍትሐዊነት ተጓድሎበታል ለማለት ያስደፍራል።

- **ማጠቃለያ እና አስተያየት**

በመሰረታዊ ሕግጋት ጥበቃ የተደረገለት መብት መጣስን ተከትሎ ለሚቀርብ ክስና የዳኝነት ጥያቄ ላይ ውሳኔ የሚሰጡ አካላት በሥነ ሥርዓት ሕጉ በመመራት ፈጣን፤ ወጭ ቆጣቢ እንዲሁም ፍትሐዊ ውሳኔ እንዲሰጡ ይጠበቃል። በዚህ አግባብ ከተነደፉ ሥርዓቶች ውስጥ አንድ የክስ ምክንያትን ያለመነጣጠል ጽንሰ ሐሳብ አንዱ ሲሆን ከአንድ አድራጎት የሚመነጩ ማናቸውም ክስና የዳኝነት ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ ተጠቃልለው የሚቀርቡበትን ሥርዓት ያስቀምጣል።

ጽንሰ ሀሳቡ ተከሳሽን በየጊዜው ከሚቀርብበት ክስ እና እንግልት የመታደግ ፣ለክርክሮች መቋጫ በማበጀት የፍርድ ቤቶችን ሁለንተናዊ ውጤታማነት ማሳደግ እና ለመብቱ ቀናኢ የሆነ ከሳሽ መፍጠርን ማዕከል ባደረጉ አበይት አላማዎች የተመሰረተ ነው። ይህንንም መሰረት በማድረግ የመርሁን ጠቅላላ ይዘት ስንመለከት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 ስር የተመለከተ ሆኖ በፍርድ ሰጭ አካል የሚቀርብ አቤቱታ ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት በሚያመች መልኩ ተጠቃልሎ መቅረብ ያለበት መሆኑን ያስቀምጣል። በመሆኑም ከሳሽ ክሱን በሚያቀርብበት ጊዜ ሊጠየቁ የሚችሉ የበሰሉ ግዴታዎችን ሁሉ ዘርዝሮ ማቅረብ እየተገባው ሆነ ብሎ ቀንሶ ባስቀረው ወይም ፍርድ ቤቱን ሳያስፈቅድ በተወው ሀብት ላይ ድጋሚ ክስ ለማቅረብ ይከለከላል። በመሰረቱ ህጉ ከመነሻውም የጉዳዮችን ተጠቃልሎ መቅረብ የሚፈልግ በመሆኑ ከሳሽ ሊከስ ሲችል ቀንሶ ማስቀረቱ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠ ፍርድ ቤቱ ሆነ ብሎ እንደቀነሰው ግምቱን መውሰድ ይኖርበታል ። ይሁን እንጂ ይህንን በመወሰን ረገድ ዳኞች ትክክለኛ ፍትሕ የመስጠት ሀላፊነት ያለባቸው በመሆኑ አግባብነት ካላቸው የሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች በተጨማሪ ክርክር የሚደረግበትን መብትን ያቋቋመው ሕግ አላማ ፣ የክርክሩን ባህሪ እና ድጋሚ የቀረበው ክስ ወይም ዳኝነት የቀድሞው ክስ ቀርቦ በነበረበት ጊዜ የበሰለ መሆን አለመሆኑን ሁሉ አጣምረው መመርመር ይጠበቅባቸዋል ።

ከዚሁ ጽንሰ ሐሳብ ጋር ተያይዞ የሥነ ሥርዓት ሕጉ አንድ የክስ ምክንያት መነጣጠልን የሚከለክለውን መርህ አንስቶ መቃወም ያለበት ማነው እና መቼስ መነሳት አለበት የሚሉት ነጥቦች ላይ ግልጽ ምላሽ የሚሰጥ ባለመሆኑ በህግ ባለሙያዎች በተለይም በዳኞች ዘንድ የተለያዩ አቋሞች ይስተዋላሉ፡፡

በእርግጥ መርሁ አንድም የፍርድ ቤቶችን ሀብት (Judicial Economy) በአግባቡ ለመጠቀም ታስቦ የተቀመጠ ቢሆንም በዋናነት መጠበቅ የሚፈልገው በአንድ ጥፋት ምክንያት በአንዳንድ ቂመኛ ከሳሾች ለከፍተኛ እንግልት የሚዳረገውን ተከሳሽ በመሆኑ ከፍርድ ቤቱ የበለጠ ተከሳሽ በዚህ ጉዳይ ላይ ንቁ ሆኖ መቃወም ይጠበቅበታል፡፡ ለተመሳሳይ አላማ የተቀመጠውም የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን የተመለከተው መርህ (Res Judicata) በአንቀጽ 5 እና 244 በግልጽ እንደተመለከተው ይህንን መርህ አንስቶ መቃወም ያለበት ወገን መርሁን ማንሳት የሚጠቅመው ተከሳሽ እንጂ ፍርድ ቤቱ ባለመሆኑ ይህ አይነት አረዳድ አንድ የክስ ምክንያት ያለመነጣጠል መርህ ጋርም ሊወሰድ ይገባል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ ይህንን መርህ በማንሳት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በሚቀርብበት ጊዜ አንስቶ ካልተቃወመ እንደተወው ተቆጥሮ ክርክሩን የማስቀጠል ውጤት ያለው (Waiveable objection) ለታለፍ የሚችል ተቃውሞ መሆን የሚኖርበት ሲሆን የሌሎችን ሀገራት የሕግ ማእቀፎችም ይህንን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ሌላው አንድ የክስ ምክንያት ያለመነጣጠል ጽንሰ ሀሳብ ጋር በተያያዘ የሚነሳው አከራካሪ ጉዳይ በተለይም የማይንቀሳቀስ ንብረትን የማስመለስ ክስ አቀራረብን የሚመለከተው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 218 ነው፡፡ በመሰረቱ ሕጉ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የማስመለስ ክስ ከሌሎች ክሶች ጋር ተጣምሮ ሊቀርብ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አይነት ክስ በስሩ ሀ፣ለ እና ሐ የተመለከቱት ሁኔታዎች ጋር አብሮ በሚመጣበት ጊዜ የግድ ክሱ መጣመር ያለበት በመሆኑ ይኸንን ያልፈጸመ ከሳሽ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/አንቀጽ 216 እና 218 መሰረት አንድ የክስ ምክንያት ነጣጥሏል በሚል ድጋሚ ነጥሎ ያቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል አቋም በአንዳንድ የሕግ ባለሙያዎች ዘንድ ይቀርባል፡፡ ይህ አቋም የሚንጸባረቅባቸው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎችን ( ያለአግባብ የተወሰደ ገጠር ይዞታ መሬት የማስመለስ እና የአላባ ጥያቄ፤ ከፍች በኋላ የሚቀርብ የጋራ ይዞታ መሬት ክፍፍል ክሶች) ለመዳሰስ እንደተሞከረው የክስ ምክንያት ያለመነጣጠል መርህን በመወሰን ረገድ መሰረታዊ የሆኑ ሕጎችን አጣምሮ የመመርመር ሁኔታ ባለመኖሩ እነዚህ ውሳኔዎች ላይ ፍትሐዊነትን የማረጋገጥ ጉዳይ ጥያቄ ወስጥ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ የሥነ ሥርዓት ሕጉ በአንቀጽ 216 ጠቅላላ የክስ አቀራረብ ሥርዓትን ሲያስቀምጥ ከአንድ የክስ ምክንያት የመነጨ

ጥያቄዎች ሁሉ ተጠቃለው መቅረብ እንዳለባቸው ከደነገገ በኋላ ዝቅ ብሎ በአንቀጽ 218 ስር የማይንቀሳቀስ ንብረት የማስመለስ ክስ ግን ከሌሎች ክሶች ጋር ተጣምሮ ሊቀርብ እንደማይችል ማመልከቱ ሕግ አውጭው የማይንቀሳቀስ ንብረት ማስመለስን አስመልክቶ የተለየ ጥንቃቄ ያስቀመጠ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ በስር ሀ፣ለ እና ሐ የተመለከቱት ሁኔታዎችም ቢሆኑ ባህሪያቸው ከማይንቀሳቀስ ንብረቱ ጋር ካላቸው ቅርበት አንጻር አብረው ቢቀርቡም የክርክሩን ጠቅላላ ሂደት ውስብስብ አያደርገውም በሚል ለከሳሽ ፈቃድ የሰጠ ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል። ከዚህ ባለፈ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የማስመለስ ክስ በተፈጥሮው ካለው ውስብስብ ባህርይ አኳያ ብቻውን እንዲቀርብ ሕጉ ለብቻው መቀመጡ ማሳያ ሲሆን መርሁ መጣመርን የሚከለክል ከሆነ ደግሞ ልዩ ሁኔታው በተቃራኒ ተጣምሮ መቅረብን የሚያስገድድ ነው በሚል የሚቀርበው ክርክር ምክንያታዊ አይሆንም። በአቀራረጽ ረገድ ለሕጉ ቅርበት ያለው የሕንዱ ሕግ በ ሀ፣ ለ እና ሐ ከተመለከቱት ሁኔታዎች በተጨማሪ በፍርድ ቤት ፈቃድ ሌሎች ክሶችም የማይንቀሳቀስ ንብረትን ከማስመለስ ክስ ጋር አብረው ሊቀርቡ የሚችሉበትን ደምብ ሲያስቀምጥ የኢትዮጵያ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/አንቀጽ 218 ግን በግልጽ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ ለፍርድ ቤት ይሕን ስልጣን አለመስጠቱ ሲታይ ጥብቅ የሆነ ሥርዓትን ያስቀመጠ መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ ሊገባል ይገባል። በሌላ በኩል የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ወጭ ቆጣቢ እና ፈጣን በሆነ መልኩ ሙግቶች እንዲቋጩ የሚፈልግ ከመሆኑ እኩል ፍትሐዊነትን የማረጋገጥ አላማን ያካተተ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

በመሆኑም የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓቱን አላማ በተማላ መልኩ ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ አንድ የክስ ምክንያት ባለመነጣጠል ሥርዓት ዙሪያ የሚነሱ ክርክሮችን በመወሰን ረገድ አግባብነት ያላቸው የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን ከክርክሩ ባሕሪ፣ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መብት ካቋቋመው መሰረታዊ ሕግ እና መንፈስ ብሎም ለቀረቡ ጉዳዩች ዳኝነት የሚሰጡ አካላትን በመለየት (forums) የመመርምር የዳኝነት ጥበብ (Judicial wisdom) ሊዳብር ይገባል።

# የመዳረግ መብት በኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ሕግ አጭር ዳሰሳ

***በላይ ወርቁ አለም****

***አህጽሮተ-ጹሑፍ***

*መዳረግ በኢንሹራንስ ህግ እንደ አንድ መርህ የሚወሰድ ጽንሰ-ሃሰብ ነው። መዳረግ የኢንሹራንስ ሰጪው ኩባንያ በኢንሹራንስ ፖሊሲው ሽፋን ኖሮት ለደረሰው ጉዳት ካሳ ከከፈለ በኋላ በኢንሹራንስ ገቢው ተተክቶ ኢንሹራንስ ገቢው በጉዳት አድራሹ ሶስተኛ ወገን ሊኖረው የሚችለውን መብት በኢንሹራንስ ገቢው ስም መጠየቅ የሚችልበት ስርዓት ነው።ይህ ጹህፍ የመዳረግ መርህ በኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ህግ ስለተካተተበት አግባብና በተግባር የሚከሰቱ ችግሮችን ዳስሷል። ለዚህ አላማ ጸሃፊው የኢትጵያን የኢንሹራንስ ህግችና ውስን የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን መርምሯል። በተደረገው የህግና የተግባር ዳሰሳ የሃላፊነት ኢንሹራንስ ጋር ተያይዞ ለሚነሳው የመዳረግ መብት ጉዳይ የኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ህግ ግልጽነት የሚጎድለው ስለመሆኑ ከዚህም የተነሳ ፍርድ ቤቶች ሃላፊነት ኢንሹራንስ ላይ ኢንሹራንስ ሰጪው የመዳረግ መብት አለው የለውም በሚለው ላይ ወጥ የሆነ ግንዛቤ እንደሌላቸው ታይቷል። ከዚህም በተጨማሪ ፍርድ ቤቶች በሃላፊነትና በሰዎች ኢንሹራንስ መካከል በቀላሉ ልዩነት ለመፍጠር እንደሚቸገሩና ይህ በበኩሉ በመዳረግ መብት አፈጻጸም ላይ ስለሚያመጣው ችግር ተዳስሷል። ስለዚህም ጹህፉ የንግድ ህጉና የተሸከርካሪ የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ ህግ አደጋ በደረሰ ጊዜ በሃላፊነት ኢንሹራንስ ፖሊሲው መሰረት ካሳ የከፈለ የኢንሹራንስ ኩባንያ በኢንሹራንስ ገቢው ቦታ ተተክቶ የጉዳት አድራሽ ከሆነው ሶስተኛ ወገን መብት መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ በግልጽ ማሳየት በሚችል መልኩ መሻሻል እንዳለባቸው ይጠቁማል።*

## 1. የመዳረግ መብት ምንነት

መዳረግ በቀላል አገላለጽ መተካካት ማለት ነው።[1] መዳረግ በኢንሹራንስ ውሉ መሰረት ሽፋን ያገኘው አደጋ በደረሰ ጊዜ ለኢንሹራንስ ገቢው ካሳ የከፈለ የኢንሹራንስ ሰጪ በኢንሹራንስ ገቢ እግር በመተካት አደጋ ካደረሰው ሶስተኛ ወገን መብት የሚጠይቅበት አግባብ ነው።[2]ይህም ኢንሹራንስ ሰጪው የኢንሹራንስ ገቢውን ጉዳት ከካሰ በኋላ የኢንሹራንስ ገቢው መብት የሆነውን ከጉዳት አድራሹ ካሳ የመቀበል መብት ይወርሳል ማለት ነው።[3] የኢንሹራንስ ሰጪው የመዳረግ መብት ተጠቃሚ ለመሆን ኢንሹራንስ ገቢው ሙሉ በሙሉ የተካሰ መሆን አለበት።[4] ከዚህ መረዳት የሚቻለው ምንም እንኳ የኢንሹራንስ ሰጪው የኢንሹራንስ ገቢው አረቦን እየከፈለ የኢንሹራንስ ሽፋን ባገኘበት ልክ የኢንሹራንስ ሃላፊነቱን ቢወጣም የደረሰው ጉዳት ግን ከኢንሹራንስ ሽፋን በላይ ከሆነ የጉዳት ካሳ ከሶስተኛ ወገን የመጠየቅ መብት የኢንሹራንስ ገቢው ይሆናል ማለት ነው። እንደዚህ አይነቱ አረዳድ የኮመን ሎ የህግ ስርዓት መነሻ እንዳለው ይነገራል። የሲቪል ሎ የህግ ስርዓትን የተመለከትን እንደሆነ ግን መዳረግን በተመለከተ በህግ ወይም በኢንሹራንስ ፖሊሲ ላይ እልባት መስጠት የተለመደ ነው።

የመዳረግ መብት ሊነሳ የሚችልባቸው ሶስት ዋና ዋና ሁኔታዎች አሉ።[5] የመጀመሪያው የመዳረግ መብት የሚነሳው የኢንሹራንስ ሰጪው በኢንሹራንስ ውል ላይ በተቀመጠው መሰረት በኢንሹራንስ ገቢው ላይ የደረሰውን ውድመት የመካስ ሃላፊነት የተወጣ እንደሆነ ነው። በዚህ አግባብ የመዳረግ መብት ለማንሳት ጉዳቱ ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያገኘ መሆን አለበት። ይህ በሆነ ጊዜ ማንኛውም ከሶስተኛ ወገን የሚገኝ መብት ቅድሚያ የኢንሹራንስ ሰጪው ለኢንሹራንስ ገቢው ያወጣውን ካሳ እንዲሸፍን የመጠየቅ መብቱ የኢንሹራንስ ሰጪው እንዲሆን ይደረጋል። ምናልባትም የኢንሹራንስ ሰጪው ከከፈለው ካሳ በላይ ከሶስተኛ ወገን ያገኘ እንደሆነ ነው ለኢንሹራንስ ገቢው እንዲመልስ የሚጠየቀው።

ሁለተኛው የኢንሹራንስ ሰጪው የመዳረግ መብት ሊያነሳ የሚችልበት ሁኔታ የሚከሰተው የኢንሹራንስ ገቢው ቀድሞ ከሶስተኛ ወገን ካሳ ከተቀበለና ከኢንሹራንስ ሰጪውም እንዲሁ

---

*(LL.B, B.A, LL.M), በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህግ ት/ቤት የህግ መምህር። ጸሃፊውን በአሚል አደራሻው belayworku24@gmail.com ማግኘት ይችላሉ። የአብክመ የፍ/ባ/ስ/ም/ተ የምርምር የስራ ሂደት ባለቤት የሆኑትን አቶ ጋሻየ ቢያድጌ ይህንን ጹህፍ እንድጽፍ ስለጋበዙኝና ስላበረታቱኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

[1] Leigh-Jones et al, "MacGillivray on Insurance Law", 10th Ed (2003) at ገጽ 568

[2] ዝኒ ከማሁ

[3] C. Brown and J. Menezes, Insurance Law in Canada, Vol. 1, Looseleaf(Toronto:Carswell,1999, ገጽ 5

[4] ዝኒ ከማሁ

[5] C. Brown and J. Menezes, Insurance Law in Canada, Vol. 1, Looseleaf(Toronto:Carswell,1999, ገጽ 6

በፖሊሲው መሰረት ካሳ ያገኘ እንደሆነ ነው። እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ከተፈጠረ የኢንሹራንስ ሰጪው ከደረሰው ጉዳት በላይ የኢንሹራንስ ገቢው የወሰደውን ገንዘብ እንዲመልስ የመጠየቅ መብት ይኖረዋል።

ሶስተኛው የመዳረግ ሁኔታ የሚከሰተው የኢንሹራንስ ሽፋን ያገኘው አደጋ ተከስቶ የኢንሹራንስ ገቢው የጉዳት አድራሽ በሆነው ሶስተኛ ወገን የተካሰ እንደሆነ ነው። ኢንሹራንስ ተቀባዩ በዚህ አግባብ መካሱን ከተረዳ የኢንሹራንስ ሰጪው በኢንሹራንስ ፖሊሲው ላይ የተመለከተውን ካሳ ባለመክፈል የመዳረግ መብት ተጠቃሚ ይሆናል።

በጥቅሉ መዳረግ በኢንሹራንስ ገቢው ላይ የደረሰውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ የካሰ የኢንሹራንስ ሰጪ ከሶስተኛ ወገን ጋር የሚኖረውን ማንኛውንም ሃደት በኢንሹራንስ ገቢው ስም የሚቆጣጠርበት ስርዓት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።[6] ከሶስተኛ ወገን ጋር ስለሚኖረው ክርክር በተመለከተም በዋናነት በኢንሹራንስ ሰጪው ይወሰናል። የኢንሹራንስ ገቢው ክርክሩን ወይም ድርድሩን ሊመራ የሚችል ቢሆንም ይህን በሚያደርግበት ጊዜ በፍጹም ቅን ልቦና ላይ መመስረት ይጠበቅበታል።[7]

### 2. የመዳረግ መብት አስፈላጊነት

የመዳረግ መብትን አስፈላጊነት ስናነሳ መነሻው በዋናነት ከተመጣጣኝ ካሳ መርህ ጋር የሚያያዝ ነው። የተመጣጣኝ ካሳ መርህ የኢንሹራንስ ገቢዎች በደረሰው ጉዳት ልክ መካስ የሚገባቸው ስለመሆኑ ያመለክታል። የመርሁ መነሻ ኢንሹራንስ ገቢዎች ከደረሰባቸው ጉዳት በላይ የሚካሱ ከሆነ አደጋውን እንደ ጉዳት ሳይሆን እንደ አትራፊ ድርጊት ሊወስዱት ይችላሉ የሚል ስጋት ነው። ይህ ስጋት በመሰረቱ ተገቢነት አለው። ምክንያቱም የኢንሹራንስ ገቢዎቹ ከደረሰው ጉዳት በላይ የሚካሱ ከሆነ አደጋ ሲደርስ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ስለሚገምቱ ኢንሹራንስ የተገባለትን ንብረት ሃላፊነት በጎደለው መልኩ ይጠቀማሉ። ኃላፊነት በጎደለው መንገድ በሚጠቀሙበት ጊዜ ደግሞ በሰው ህይወት፣ አካል፣ ንብረት ወዘተ ውድመት በማደረስ በህዝብ ጥቅም ላይ አደጋ ይቃጣሉ።[8]

---

[6] R. Deman, Current Problems in Subrogation, 1994, ገጽ 22

[7] ቅን ልቦና ሊኖረው ይገባል ሲባል ኢንሹራንስ ተቀባዩ ከሶስተኛ ወገን ጋር ሲደራደር ወይም ሲከራከር የኢንሹራንስ ሰጪውን መብት በሚጎዳ አካሄድ መሆን የለበትም። ቀሪውን በተመለከተ የኢንሹራንስ ሰጪው እንደሚሸፍነው ታሳቢ በማድረግ kሶስተኛ ወገን ምክንያታዊነት በጎደለው መልኩ ትንሽ የጉዳት ካሳ መጠየቅ የቅን ልቦና መጓደል ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል።

[8] እስካድማስ ፀሐዩ፣ የኢንሹራንስ ኩባንያ ህግና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች፣ነጭ ሣር ማተሚያ ድርጅት፣ ገጽ 23

ኢንሹራንስ ከዚህ በተጻራሪ መንገድ አደጋ የመቀነስ ውጤት እንዲኖረው ይፈለጋል። ይህ የሚሆነው የኢንሹራንስ ውል ገቢውና የኢንሹራንስ ኩባንያው በፖሊሲ ላይ እንደመብትና ግዴታ ከሚያስቀምጧቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ካሳ ሊከፈል ይቻል ዘንድ የኢንሹራንስ ገቢው አደጋ እንደይከሰት ወይም ለመቀነስ መስራት ያለበት መሆኑ ነው። ሆን ብሎ ወይም በቸልተኛነት የኢንሹራንስ ገቢው ያመጣው አደጋ ካለ የኢንሹራንስ ሰጪው የመክፈል ግዴታ የለበትም። ስለዚህም ኢንሹራንስ ገቢው ምንም እንኳ እቃው ወይም ሃላፊነቱ የኢንሹራንስ ሽፋን ቢኖረውም ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል።[9]

የኢንሹራንስ ኩባንያው ግን ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት በመሆኑ እንዲያተርፍ ይፈለጋል። ምክንያቱም ማትረፍ ካልቻለ አስተዳደራዊና አስተዳዳራዊ ያልሆኑ ወጪዎችን መሸፈን ስለማይችል እንደ ኩባንያ ሊቀጥል አይችልም። የኢንሹራንስ ኩባንያው ሊኖር አልቻለም ማለት እንግዲህ  የኢንሹራንስ ሽፋን ማግኘት ያለመቻልን የሚያስከትል በመሆኑ ውጤቱ ከባድ ነው።

የመዳረግ መብት አስፈላጊ የሚሆነው እንግዲህ ከላይ የተነሱ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ነው። የኢንሹራንስ ገቢው በበቂ ሁኔታ ከተካሰ ከሶስተኛ ወገን ከጉዳቱ በላይ የተቀበለው ካሳ ካለ ለኢንሹራንስ ሰጪው መመለስ አለበት። ይህ የሚሆነው የኢንሹራንስ ገቢው ከጉዳት አድራሹ ካሳ በጠየቀ ጊዜ የኢንሹራንስ ሽፋን ስላለህ ከኢንሹራንስ ሰጪው ጠይቅ ተብሎ መከላከያ የማይነሳበት በመሆኑ በቀላሉ ጉዳቱን ማስረዳት እስከቻለ ድረስ የኢንሹራንስ ድርጅቱን ከመጠየቁ በፊት ቀጥታ ከጉዳት አድራሹ ካሳ ማግኘት እንደሚችል ስለሚታሰብ ነው።

በአጠቃላይ ግን የመዳረግ መርህ በኢንሹራንስ ኩባንያዎችና ኢንሹራንስ ገቢዎች መካካል የጥቅም ሚዛን ከሚያስተካክሉ መርሆች ውስጥ አንዱ ነው። የኢንሹራንስ ገቢዎች በደረሰው ጉዳት ልክ እንዲካሱ እንጂ ኢንሹራንሱን ላይ ቁማር እንዲጫወቱ አይፈለግም። ስለዚህም የኢንሹራንስ ሽፋን ባገኘው የአደጋ መንስኤ ጉዳት ከደረሰ መካስ የሚችሉት ወይ በኢንሹራንስ ሰጪው አሊያ ደግሞ በጉዳት አድራሽ በሆነው ሶስተኛ ወገን ያውም እስከ ጉዳቱ ብቻ ነው። በቀሪው መብት ላይ ኢንሹራንስ ሰጪው መተካት አለበት።

[9]ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኛነቱ አደጋ እንዲከሰት ያደረገ እንደሆነ የሚያጣው ሁለት ነገር ነው። አንደኛው ንብረቱን ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በአረቦን መልኩ ለኩባንያው ሲከፍለው የነበረውን ገንዘብ ነው።

### 3. የመዳረግ መብት፡- የኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ህግና ተግባር ዳሰሳ

በዚህ ክፍል የመዳረግ መብትን የሚመለከቱ የኢንሹራንስ ድንጋጌዎችንና የሚነሱ የተግባር ችግሮችን ለመዳሰስ ተሞክሯል። የኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ህግ ድንጋጌዎችን የተመለከትን እንደሆነ መዳረግ ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎች አሉት።[10] የንግድ ህጉ ድንጋጌዎችን ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው የመጀመሪያው ጉዳይ ኢንሹራንስ ሰጪው ኩባንያ የመዳረግ መብት ሊኖረው የሚችለው በየትኞቹ የኢንሹራንስ አይነቶች ነው የሚለው ነው።

የኢንሹራንስ አይነቶችን የንግድ ህጉ በሶስት ግዙፍ ክፍሎች ከፋፍሎ አስቀምጧል። እነሱም፡- የእቃዎች ኢንሹራንስ (Insurance ofobjects)[11] የሃላፊነት ኢንሹራንስ (Liability Insurance)[12]ና የሰዎች ኢንሹራንስ (Insurance of persons)[13] ናቸው። የእቃዎች ኢንሹራንስ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ በእቃው ላይ ጥቅም ያለው[14] ግለሰብ እቃው ቢወድም የሚደርሰውን ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ለመቋቋም ሲል የሚገባው የኢንሹራንስ አይነት ነው። የጥፋት ሃላፊነት ኢንሹራንስ ደግሞ በአንድ ግለሰብ እጅ ያለ ነገር ወይም ራሱ ግለሰቡ በሌላ ሶስተኛ ወገን ንብረት፣ አካል፣ ወዘተ አደጋ ያደረሰ እንደሆነ ለዚሁ ሃላፊነት ሽፋን ለማግኘት የሚገባ ኢንሹራንስ ነው። የሰዎች ኢንሹራንስ በአንጻሩ ደግሞ ሰው የሞተ እንደሆነ ለሌሎች ጥገኞቹ ጥቅም ሲል፣ የታመመ እንደሆነ የህክምና ወጭ እንዲሸፈንለት፣ አደጋ የደረሰ እንደሆነ መካስ እንዲችል ወዘተ የሚገባ ኢንሹራንስ ነው።

እንግዲህ የኢንሹራንስ ህጋችን ውስጥ የመዳረግ መብትን ከእነዚህ የኢንሹራንስ አይነቶች አንጻር ከተመለከትነው ግልጽነት ይጎደለዋል። በመጀመሪያ ደረጃ የእቃዎች ኢንሹራንስ (Insurance of objects) ያየን እንደሆነ እንዲህ አይነቱን ኢንሹራንስ የሚገዛው ክፍል ላይ የኢንሹራንስ ሰጪው የመዳረግ መብት የሚኖረው ስለመሆኑ በግልጽ ያስቀምጣል።[15]

የንግድ ህጉ በፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን መጠን የከፈለ የኢንሹራንስ ሰጭ ሶስተኛ ወገን ላይ የሚኖረውን መብት ለመጠቀም አላማ በኢንሹራንስ ገቢው ቦታ እንደሚተካ ያሳያል። የኢንሹራንስ ገቢው በመተካት/መዳረግ ሂደት ላይ መተባበር ያለበት ስለመሆኑም ከንግድ ህጉ

[10] የንግድ ህጉን አንቀጽ 683 እና 690 ይመልከቱ
[11] የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አንቀጽ 675-684
[12] የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አንቀጽ 685-688
[13] የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አንቀጽ 689-712
[14] በእቃው ላይ ጥቅም አለ ስለሚባልበት አግባብ በቀጥታም ባይሆን ለየት ባለ አገላለጽ አንቀጽ 675 ላይ ተደንግጎ እናገኛዋለን።
[15] የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አንቀጽ 683/1/

አንቀጽ 683/2/ እንረዳለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኢንሹራንስ ሸጪው የኢንሹራንስ ገቢው የመዳረግ መብቱን እንዳይጠቀም ያደረገ እንደሆነ የኢንሹራንስ ሰጪው በፖሊሲው ላይ ከተቀመጠውን ሃላፊነት በሙሉም ሆነ በከፊል ነፃ ይሆናል ሲል ይደነግጋል፡፡[16] የሰዎች ኢንሹራንስ (Insurance of persons) ያየን እንደሆነ ደግሞ ኢንሹራንስ ሰጪው የመዳረግ መብት ሊጠቀምበት እንደማይችል ያሳያል፡፡[17] ይህ እንግዲህ ከላይ ከተነሳው የተመጣጣኝ ካሳ መርህ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

በንብረት ኢንሹራንስ የተመጣጣኝ ካሳ መርህ የሚሰራ ሲሆን በሰዎች ኢንሹራንስ ግን የደረሰውን ጉዳት በገንዘብ ማስላት ከባድ በመሆኑ በኢንሹራንስ ፖሊሲው ላይ እንደፈለጉ ከፍና ዝቅ አድርጎ መስማማት የሚቻል ስለሆነ የደረሰው ካሳና ጉዳት በተመጣጣኝ ካሳ መርህ ላይ ሊመሰረት አይችልም፡፡ ስለዚህም ነው የመዳረግ/የመተካት መብት እንዲኖረው ማድረግ ከባድ የሚሆነው፡፡ ህጉ ይህን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ የመዳረግ መብት የለም ማለት የኢንሹራንስ ገቢው ከኢንሹራንስ ሰጪው የኢንሹራንስ ካሳ ቢያገኝም ጉዳት አድራሹ ላይ የሚኖረውን መብት መጠቀም ይችላል ማለት ነው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ሊነሳ የሚችለው በጥፋት ሃላፊነት ኢንሹራንስ (Liability Insurance)[18]ጋር የተያያዘ የመተካት/የመዳረግ ጉዳይ ነው፡፡ ይህንኑ ጉዳይ ያነሳነው እንደሆነ ከህጉ አወቃቀር ጀምሮ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የሃላፊነት ኢንሹራንስ ተደንግጎ የምናገኘው የጉዳት ኪሳራ ኢንሹራንስ በሚገዛው የድንጋጌ ክፍል ነው፡፡[19] በዚህ ምዕራፍ ስር የእቃ ኢንሹራንስና የሃላፊነት ኢንሹራንስ በማለት የጉዳት ኪሳራ ኢንሹራንስን በሁለት ከፍሎታል፡፡ የመጀመሪያውን ክፍል በሚገዛው ድንጋጌ ስር ስለመዳረግ ከላይ ማብራራት በተቻለው አግባብ ማካተት የቻለ ሲሆን በሁለተኛው ክፍል ግን እንዲሁ በዝምታ አልፎታል፡፡[20] ይህ አይነቱ የህግ አወቃቀር በጥፋት ሃላፊነት ኢንሹራንስ የኢንሹራንስ ሰጪው የመዳረግ መብት አለው የለውም የሚል ክርክር እንዲነሳ በር ከፈቷል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በብዛት ክርክር የሚነሳባቸው የሃላፊነት ኢንሹራንሶች የሶስኛ ወገን አስገዳጅ የተሸከርካሪ ኢንሹራንስና ቀጣሪ የሰራተኞችን መብት ለማስጠበቅ ሲል የሚገባው ኢንሹራንስ

[16] የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አንቀጽ 683/2/
[17] የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አንቀጽ 690
[18] የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አንቀጽ 685-688
[19] በንግድ ህግ የኢንሹራንስ ህጉን ምዕራፍ 3 ይመልከቱ
[20] መዳረግ እንደሚቻል አልጠቆመም ወይም በሰዎች ኢንሹራንስ ላይ ባስቀመጠው አግባብ በግልጽ አልከለከለም

ነው። አዋጁ ማንኛውም ተሸከርካሪ ሶስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው አደጋ ከኢንሹራንስ/መድን ኩባንያ[21] ሽፋን ማግኘት እንዳለበት ያስቀምጣል።

የሶስተኛ ወገን የተሸከርካሪ ኢንሹራንስ እንግዲህ ተሸከርካሪ አደጋ ባደረሰ ጊዜ የሶስተኛ ወገን ጥቅም በቀላሉ ማስጠበቅ ይቻል ዘንድ ተፈልጎ በመንግስት በኩል እንደ ግዴታ እንዲወሰድ አቋም የተያዘበት የኢንሹራንስ ዓይነት ነው።[22]

የተሸከርካሪ አደጋ በደረሰ ጊዜ ሶስተኛ ወገን ተጎጂዎቹ በሁለት መንገድ የሚካሱ ይሆናል። ተሸከርካሪው የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ ያለው ከሆነ ሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ በተገባበት ኩባንያ ይካሳሉ። የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ የሌለውና የማይታወቅ ከሆነ በኢንሹራንስ ፈንድ ኤጀንሲ ይካሳሉ።[23]

አሁን ጥያቄ የሚሆነው ታዲያ ኩባንያውና  ኢንሹራንስ ፈንድ ኤጀንሲው ለሶስተኛ ወገን ካሳ ከከፈሉ በኋላ የመዳረግ መብት አላቸው ወይ የሚለው ነው። የተሸከርካሪ አደጋ ሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ አዋጅ የኩባንያውን የመዳረግ መብት በተመለከተ እንደ ንግድ ህጉ በዝምታ አለፎታል። ይሁን እንጂ ለኢንሹራንስ ፈንድ ኤጀንሲው ግን የመዳረግ መብት የሰጠ ይመስላል። የአወጁን አንቀጽ 20/3/ ስንመለከት የመድን አስተዳደር አጀንሲው ጉዳት ለደረሰበት ሶስተኛ ወገን ያወጠውን ወጭ ለጉዳት በሃላፊነት ተጠያቂ ከሆነው ሰው የማስመለስ መብት እንዳለው ይጠቁማል። የሃላፊነት ኢንሹራንስ የመዳረግ መብት የማይከለከልበት መሆኑን የምንረዳበት አንደኛው ነጥብ ይህ ነው።እንግዲህ እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጉዳይ ለኢንሹራንስ ፈንድ አስተዳደር የተሰጠው የመዳረግ መብት ለምን ለኢንሹራንስ ኩባንያዎችስ አልተሰጠም የሚል ነው። ይህ ምክንያት የጎደለው ይመስላል። ለምሳሌ፡- አንድ ኢንሹራንስ ያለው መኪና ከባህርዳር አዲስ አበባ በመጓዝ ላይ እያለ መኪናው አንድ እግረኛ ላይ አደጋ ቢያደርስ የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው መኪና ከሆነ የኢንሹራንስ ኩባንያው ለእግረኛው ካሳ ይከፍላል[24]፤ የኢንሹራንስ ሽፋን ከሌለው ግን ካሳው የሚከፈለው በኢንሹራንስ ፈንድ ኤጀንሲው ነው። ለዚህ አላማ  ያወጣው ወጭ ኤጀንሲው ተከታትሎ ማስመለስ ይችላል።

ከላይ የተነሳው ሌላው የሃላፊነት ኢንሹራንስ ቀጣሪ ለሰራተኞቹ የሚገባው ኢንሹራንስ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ምክንያት በፍላጎቱ ወይም በህግ የተቀመጠውን የሰራተኞች መብት

[21] የመድን ኩባንያ ማለት በዚህ ህግ መሰረት ጠቅላላ የኢንሹራንስ ስራ እንዲሰራ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ነው።
[22] የተሸከርካሪ አደጋ ሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ አዋጅ 799/2005 መግቢያውን ይመልከቱ።
[23] ህጉ ግልጽ ባይሆንም ከተሸከርካሪ አደጋ ሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ አዋጅ 799/2005 አንቀጽ 20/3/ መረዳት ይቻላ።
[24] በከፈለው ልክ ከጉዳት አድራሹ ማስመለስ መቻል ስላለመቻሉ ግን ያለው ነገር የለም።

ለማስጠበቅ ቀጣሪ ኢንሹራንስ ሊገባ ይችላል። ለምሳሌ ያህል የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ምንም ጥፋት ባይኖርም ሰራተኛው በስራ ላይ በሚደርስበት ጉዳት ሃላፊነት እንዳለበት ይደነግጋል።[25]

ይህንኑ ግዴታ ለመወጣት አሰሪው ለሰራተኞች ኢንሹራንስ ይገባል። በፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን ግዴታ በተገቢው መንገድ የተወጣ የኢንሹራንስ ኩባንያ ቀጣሪው ጥቅም ላይ ተተክቶ መብት መጠየቅ ይችላል አይችልም ብለን ስንጠይቅ ግልጽ የሆነ መልስ ላናገኝ እንችላለን። ይሁን እንጂ በምክንያት ላይ ስንመሰረት አዎንታዊ መልስ ይኖረዋል። ይህም የሚሆነው ከትክክለኛ እሳቤዎች መነሳት ስንችል ነው። በመጀመሪያ ደረጃ የዚህ ኢንሹራንስ እሳቤ የሚፈራው አደጋ ቢደርስ ቀጣሪው ካሳ ለመክፈል ይቸገራል ነው። ስለዚህ ቀጣሪው የሚፈልገው ሰራተኞቹ የስራ ላይ አደጋ በደረሰ ጊዜ እንዲካሱለት ነው። ስለዚህ ከሶስተኛ ወገን መጠየቅ አይችልም።በሁለተኛ ደረጃ ሰራተኞቹም ካሳ እንዲያገኙ እንጂ ትርፍ እንዲያግበሰብሱ አይፈለግም። ስለዚህ በተገቢው መንገድ በኢንሹራንስ ፖሊሲ ላይ የተቀመጠውን ግዴታ የተወጣ ኩባንያ በሶስተኛ ወገን ላይ በሚኖረው የቀጣሪ/ ኢንሹራንስ ገቢ ጥቅም ላይ እንዳይተካ የሚከለከልበት አመክንዮ ያለ አይመስለኝም።

በተግባርም ሲታይ ችግሮች እንዳሉ እንገነዘባለን።የችግሩ ምንጮች አንደኛው ከላይ እንደተነሳው ራሱ የህጉ የአወቃቀር ችግር ሲሆን ሁለተኛው ፍርድ ቤቶች በሃላፊነት ኢንሹራንስና በሰዎች ኢንሹራንስ መካከል ያለውን ልዩነት በተገቢው መንገድ መረዳት አለመቻላቸው ነው።

ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለውን አንድ ውሳኔ እናንሳ።[26] ጉዳዩ የተነሳው ከሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የውሳኔው ይዘት እንደሚከተለው ነው። የደቡብ ውሃ ስራዎች ድርጅት ለሰራተኞቹ የስራ ላይ አደጋና ህመም ኢንሹራንስ ሽፋን ፖሊሲ ከአትዮጵያ መድን ድርጅት(አመልካች) አግኝቷል። ሽፋኑንን ካገኘ በኋላ ንብረትነቱ የአፍሪካ ቤዛ ኮሌጅ(ተጠሪ) የሆነው መኪና አቶ ሙላት ሃዋዝ በተባለ  የደቡብ ውሃ ስራዎች ድርጅት ሰራተኛ ላይ የሞት አደጋ አድርሶ የኢትዮጵያ የመድን ድርጅቱ ካሳ ከፍሏል። ክርክሩ የተነሳው የመድን ድርጅቱ ከጉዳት አድራሹ/አፍሪካ ቤዛ ኮሌጅ የደቡብ ውሃ ስራዎች ድርጅትን ተክቶ መብት በጠየቁ ነው። ጉዳዩ የቀረበለት የሃዋሳ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተከፈለው የህይወት ኢንሹራንስ ካሳ ስለሆነ አመልካች የመዳረግ መብት የለውም በማለት የንግድ ህጉን አንቀጽ 690 ጠቅሶ አሰናብቷል። ከዚህ የተነሳ ይግባኝ የቀረበለት የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ይህ የሓላፊነት

[25] የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96/1/

[26] *የኢትዮጵያ መድን ድርጅትና የአፍሪካ ቤዛ ኮሌጅ፣ የሰበር መ/ቁ/ 99179  መስከረም 25፣ 2008 ዓ/ም*

ኢንሹራንስ ስለሆነ አመልካቹ የመዳረግ መብት ስላለው ለተጎጂው የከፈለውን ገንዘብ ተጠሪው ሊመልስ ይገባል ሲል ወስኗል። በዚህ ቅር የተሰኘው ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ሰበር ሰሚው ፍ/ቤት የጠቅላይ ፍ/ቤቱን ውሳኔ ሽሮ የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ ያጸና ሲሆን የመዳረግ መብትን የሚመለከተው የንግድ ህጉ አንቀጽ 683/1/ ተፈጻሚነቱ ለእቃዎች ኢንሹራንስ ብቻ እንጂ ለሃላፊነት ኢንሹራንስ ጭምር አይደለም በማለት ወስኗል። ይህ ጉደይ የቀረበለት የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሌላ ውሳኔ እስኪሻርም ቢሆን ተፈጻሚነት ያለውን አስገደጅ ውሳኔ አስተላልፏል። የውሳኔው ጥቅል ሃሳብ እንደሚያመለክተው በደቡብ ውሃ ስራዎች ድርጅትና በኢትዮጵያ መድን ድርጅት መካከል የሃላፊነት ኢንሹራንስ ፖሊሲ እንጂ የህይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ እንዳለ የሚያመለክት ነገር የለም። የሃላፊነት ኢንሹራንስ ደግሞ በካሳ መርህ የሚመራ በመሆኑ በአንቀጽ 683/1/ መሰረት ተጠሪው የመዳረግ መብት አለው በማለት ውሳኔ አሳርፏል።

### 4. መደምደሚያና የጥቆማ ሃሳብ

የመዳረግ መብት በኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ህግ ግልጽነት በጎደለው መልኩ ሰፍሮ የምናገኘው አንዱ የኢንሹራንስ መርህ ነው። ለግልጽነት ማነስ መነሻ የሆነው አንዱ በንግድ ህጉና በሌሎች ህጎች የተደነገገበት አግባብ ነው። በንግድ ህጉ መዳረግን የተመለከተው ድንጋጌ በኢንሹራንስ አይነቶች መሰረት የተቀመጠ ሲሆን በእቃዎች ኢንሹራንስ የመዳረግ መብትን ለኢንሹራንስ ሰጪው በሚሰጥ አግባብ በሰዎች ኢንሹራንስ ደግሞ የመዳረግ መብትን በሚከለክል አግባብ በግልጽ ደንግጓል። ይሁን እንጂ የሃላፊነት ኢንሹራንስን በተመለከተ በግልጽ አልፈቀደም ወይም አልከለከለም። ይህ ደግሞ በክርክር ወቅት የተለያየ አረዳድ እንዲኖር በር ከፍቷል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ፍ/ቤቶችም ጭምር የተለያየ ውሳኔ ሲያሳልፉ ይታያል።

የሰራተኞችን የስራ ላይ አደጋ የኢንሹራንስ ሽፋን ለማግኘት የሚገባ ኢንሹራንስና የተሸከርካሪ ሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ የሃለፊነት ኢንሹራንስ አይነቶች ናቸው። የመዳረግ መብት በብዛት የሚነሳው ከእነዚህ ጉዳዮች ቢሆንም ከህጉ ግልጽ መልስ አልተገኘም። የተሸከርካሪ ሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ ኣዋጅ የኢንሹራንስ ፈንድ ኤጀንሲ ኢንሹራንስ በሌላቸው ወይም ባልታወቁ ተሸከርካሪዎች ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች የከፈለውን ካሳ ከጉዳት አድራሹ ማስመለስ እንደደሚችል ከደነገገ በኋላ የኢንሹራንስ ድርጅቶችን የመዳረግ መብት በተመለከተ በዝምታ አልፎታል።

ይሁን እንጂ እነዚህ የኢንሹራንስ ዓይነቶች የሃላፊነት ኢንሹራንስ አካል ስለሆኑ የሃላፊነት ኢንሹራንስ በባህሪው ደግሞ በካሳ መርህ ስለሚመራ የመዳረግ/መተካት መብት የሚከለከልበት ምክንያት አይኖርም። ስለዚህም የመፍትሄ ሃሳቦችን እንደሚቀጥለው እጠቁማለሁ፡-

1. የንግድ ህግ አንቀጽ 683 ለእቃዎች ኢንሹራንስና ለሃላፊነት ኢንሹራንስ ሊተገበር በሚችል መንገድ ጠቅላላ የጋራ ድንጋጌ ሆኖ መቀመጥ አለበት፤ አለዚያ የሃላፊነት ኢንሹራንስ በሚገዛው ክፍልም ተደግሞ መካተት ይኖርበታል።
2. የተሸከርካሪ የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ አዋጅ የመዳረግ መብትን በአንቀጽ 20/3/ ለኢንሹራንስ ፈንድ ኤጀንሲ በሰጠበት አግባብ ለኢንሹራንስ ድርጅቶችም መስጠት አለበት።
3. የሃላፊነት ኢንሹራንስና የሰዎች ኢንሹራንስ መካካል ያለውን ልዩነት ዳኞች በቀላሉ ለይተው መዳረግ ጋር ለተያያዙ ክርክሮች እልባት መስጠት ይችሉ ዘንድ ሁለቱንም የኢንሹራንስ ዓይነቶች የሚገዙ ድንጋጌዎች ግልጽ በሆነ መንገድ እንደገና መርቀቅ (re-draft) አለባቸው።